

ስካን በማድረግ ያግኙን
Scan and contact us on

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ቅጽ-26

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች



ለላቀና ተደራሽነት ላለው የዳኝነት አገልግሎት እንተጋለን!
We strive for an efficient and accessible justice service!

## ቅጽ - 26

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ-26


የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የሕግ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት



ሐምሌ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ



ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et<br>
ስልክ፡-+251-11-1-55-34-00/011-1-11-04-32<br>
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33<br>
የመ.ሣ.ቁ. 6166<br>
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992

# ክቡር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት መልዕክት



የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሳኔዎች በተከታታይ በድረ-ገጽ እንዲሁም በሕትመት ተደራሽ ለማድረግ ጥረት ሲደረግ የቆየ ሲሆን በዚሁ አግባብ ቅጽ 26 በሕትመት ተዘጋጅቶ ስናቀርብላችሁ ደስታ ይሰማናል፡፡

ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጡ ውሳኔዎች አስገዳጅ በመሆናቸው በሀገሪቱ የሕግ ስርዓት ውስጥ ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የዳኝነት አካሉ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ወጥ እና ተገማች ለማድረግ ታስቦ የተዘረጋ ሥርዓት እንደመሆኑ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉ ይህን ለማሳካት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህም በሻገር ውሳኔዎቹ ለሕግ አስተምህሮት እና ምርምር ግብዓትና መነሻ በመሆን የህግ እውቀት በተለይም ሀገር በቀል የሕግ ሳይንስ በማዳበር በኩል አስተዋጽኦዎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ለማሳካት አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎችን በመመርመር፣ በመተንተንና በመተቸት ረገድ ጥረትና ተሳትፎ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የፍርዶችን ጥራት ለማሻሻል እንዲሁም ለማረም የተቀመጠውን መንገድ በመጠቀም የተዛነፉ አካሄዶች ካሉ የሚታረምበትን መላ ለመምታት የተለያዩ አተያዮች፣ አረዳዶች እና ግንዛቤዎች በአደባባይ ወጥተው ውይይት የማድረግና የማረም፣ የማዳበር እና የማስረጹን ስራ ማገዝ ላይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ ይህ ቅጽ በሕትመት መልክ እንዲሁም በዲጂታል አማራጭ በፍርድ ቤቱ ዌብሳይት በአግባቡ ተዘጋጅቶ አንባቢ ዘንድ ተደራሽ መደረጉ በቀጣይ የሕግ ሳይንስ እንዲዳብር የሚያስችል በመሆኑ ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

መልካም ንባብ!!

**ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ**

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት**

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕግ ጥናት እና ምርምር ዳይሬክተር መልዕክት

የተከበራችሁ አንባብያን

ሁላችንም እንደምናውቀው የሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ባላነሱ ዳኞች የተሰጡና አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች በተመሳሳይ ጉዳይ ወደፊት ለሚነሱ ክርክሮች እንደገዢ ሕግ የሚወሰዱ እንደመሆናቸው መጠን እነዚህን ውሳኔዎች ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት ከ1997 ዓ.ም አንስቶ ላለፉት 19 ዓመታት ሳይቋረጥ እነዚህን ውሳኔዎች በማሳተም ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በያዝነው ዓመትም ከሕትመት እና ስርጭት ጋር ተያይዞ ያሉትን ችግሮች እና ውጣ ውረዶችን ለማስወገድ ከብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር የሕትመቱን እና የስርጭቱን ስራ በነሱ በኩል እንዲከናወን በማድረግ ህትመቶቹን የበለጠ ለሕብረተሰቡ ለማድረስ እና የሕብረተሰቡ የሕግ ግንዛቤ እንዲዳብር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

አሁንም በዚህ በ26ኛ ቅጽ በተመሳሳይ የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሳኔዎች ስናቀርብ አንባብያን በተለይም ደግሞ የሕጉ ማህበረሰብ ያለው ግንዛቤ እየጨመረ እንደሚመጣ እና ለሃገራችን የፍትህ አስተዳደር መሻሻል የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚነሳሳ ተስፋ በማድረግ ነው፡፡

በስተመጨረሻም በቀጣይ በ27ኛው ቅጽ እስከምንገናኝ ድረስ መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ፡፡

መልካም ንባብ !

**አሮን ደጎል ሃብቱ**

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

**የሕግ ጥናት እና ምርምር ዳይሬክተር**

# የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ /ቅፅ 26/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | **1** |
| 1. | የከሳሽ ክስ በተከሳሽ የተካደ እንደሆነ በቅድሚያ ማስረጃዎችን አቅርቦ የማስረዳቱ ሸክም የሚወድቀዉ በመርህ ደረጃ በከሳሽ ላይ መሆኑ የማስረጃ አቀራረብ እና የማስረዳት ሸክም መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ከከሳሽ ወደ ተከሳሽ ሊዞር የሚችለዉ ተከሳሽ በከሳሽ የተመለከተዉን ፍሬ ነገር አምኖ ኃላፊነት የለብኝም የሚልበትን አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ካቀረበ ወይም ከሳሽ የህግ ወይም የፍሬ ነገር ግምት ተጠቃሚ ከሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 258(1) እና 259(1) | 205626 | ኩማ አስመጪና ላኪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ገበያው ይስማው<br>(23 ሰዎች) | ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም | 2 |
| 2. | ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345 መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ የመቀበልና የመመዘን ሥልጣን ያለው በመሆኑ በዚህ አግባብ ማስረጃ ተቀብሎ በመመዘን የሚሰጠው ውሳኔ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ያልቀረበ ማስረጃና ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም የማይባልና የክርክር አመራር ጉድለት ወይም የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ | 208350 | ኤፍ.ቲ.ሲ.(FTC) ጠቅላላ የግንባታ ሥራዎች ኃ/የተ/የግል ማሕበር<br>እና<br>እነ አቶ ዳንኤል ዘውዴ<br>(4 ሰዎች) | ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም | 7 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3. | ክስ ማሻሻል አስፈላጊ ከሚሆንባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ የሆነው የክሱ ምክንያት ጠቃሚ አካል የሆነ ፍሬ ነገር ሳይጠቀስ የቀረ እንደሆነና ይህንኑ ፍሬ ነገር ማካተት አስፈላጊ ሆኖ ለክሱ መሰረታዊ የሆነዉ ነጥብ ግልጽ ካልሆነ፤ የክስ አቤቱታ እንዲሻሻል በማድረግ ክርክሩ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት በተከተለ መንገድ ሊመራና ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በተከራካሪ ወገኖች ጠያቂነት ወይም በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት ክሱ እንዲሻሻል መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 91/1 | 198035 | ቡለሌ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማኀበር<br>እና<br>የሄጦሳ ወረዳ ገበሬዎች ሕብረት ሥራ ኃላ/የተ/የግ/ማኀበር | ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም | 12 |
| 4. | የቀረበ ክስ በአንድ በኩል የውል አለመፈጸምንም መሠረት ያደረገ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል ውሉ ከሚሸፍነው ጉዳት በላይ ስለደረሰ ጉዳቱን አጠቃሎ የቀረበ ከሆነ ከውል ውጭ ግንኙነትንም መሠረት ያደረገ የክስ አቀራረብ የተከተለና የውል ጉዳት ኪሣራ ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይ እንጂ ግንኙነቱን ከውል ውጭ የሚያደርገውና ክስ አቀራረቡ የክሱን መሠረት ግልጽ ያላደረገ በመሆኑ በክስ አቤቱታው ላይ ትክክለኛ የሆነው የውል ግንኙነት በሚያሳይ መልኩ እንዲሻሽልና ተከሳሽም በተሻሻለው ክስ መሠረት ክርክር እንዲያቀርብ ተደርጎ ክርክሩ የሚመራ ስለመሆኑ<br>የፍብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 91/1/ | 211408 | አቶ አማረ አምባዬ<br>እና<br>ወ/ሮ ነጃት ሰይድ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት | ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም | 20 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 5. | ክስ ለማቅረብ በሕግ ችሎታ የሌለው ሰው በመሆኑ በሞግዚት ወይም በተሾመለት እንደራሴ አማካይነት ክስ ሊቀርብ ሲገባ በዚህ አግባብ ሞግዚትና አሳዳሪ ሆኖ የተሾመ ስለመሆኑ የቀረበ የፍርድ ቤት ውሳኔ በሌለበትና ክስ ለማቅረብ ችሎታ ያለው መሆኑን ሳይረጋገጥ ወደ ክሱ ሥረ-ነገር በመግባት ውሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ<br>የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(1)፣ 34(1) እና የፍ/ሕ/ቁ. 210 | 202734 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሶማሌ ሪጅን<br>እና<br>የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣<br>አቶ ፋራሕ አብዲ | ሚያዚያ 26 ቀን 2014 ዓ/ም | 24 |
| 6. | በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት በተደረገ ክርክር የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የሚነካበት ሦስተኛ ወገን የመቃወም አቤቱታዉን አቅርቦ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን ተከራክሮ መብቱን ማስከበር እንዲችል ታስቦ እንጂ ወኪል ሆኖ ሊከራከር የሚችልበት መብትና ጥቅም ክርክር በማድረግ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን ባለዉ ጉዳዩ በሚመለከተዉ አካል ክርክር ቀርቦበት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ዉሳኔዉን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358 መሠረት መቃወም የሚቻልበት ህጋዊ አግባብ ያለ ስላለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 33(3) እና 92<br>**(የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 37502 መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ተለውጧል፡፡)** | 190307 | የካ ክ/ከተማ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ አቶ አበበ በቀለ<br>(9 ሰዎች) | ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም | 28 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 7. | ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት የማይችልና በተከራካሪ ወገን ያልተነሳን መከራከሪያ ፍርድ ቤት በራሱ አንስቶ ውሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) | 215134 | አቶ አሚን ሙመድ አሊ እና ኢብሳ አህመድ ሙመድ | ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም | 36 |
| 8. | የአክሲዮን ማህበር አባላት የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎች ሳይከፍሉ በመቅረታቸዉ ከማህበር አባልነታቸዉ እንዲወጡ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የወሰነዉ ዉሳኔ እንዲሰረዝላቸዉ ክስ አቅርበዉ ተቀባይነት ያጣ ሆኖ ሳለ፣ በፍ/ቤት ክርክር የማህበሩ አባላት ከአባልነት ይሰረዙ በማለት ማህበሩ የሚያቀርበዉ አቤቱታ ዳግመኛ የቀረበ ጉዳይና የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት ነዉ የሚባል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 (1) | 214136 | እነ አቶ ደለሳ ጅማ (13 ሰዎች) እና ኮልፌ ቀዱስ ራጉኤል አዲስ ህይወት አክሲዮን ማህበር | ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም | 43 |
| 9. | ፍርድ ቤት በክስ አቤቱታ ላይ የተገለፀው ነገር የማያስከስስ ሆኖ ሲያገኘው፤ እንዲሁም በክሱ ላይ የተገለፀው ጉዳይ ከፍርድ ቤቱ ሥልጣን ውጪ ሲሆን የቀረበለትን የክስ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብሎ መወሰኑ ከሳሽ ክሱን አሻሽሎና አስተካክሎ እንዳያቀርብ የማይከለክልና ክሱ ተቀባይነት የለውም መባሉ ወይም መሰረዙ ከሳሽ ክሱን አሻሽሎ እና የጎደለውን አሟልቶ በዚያው ነገር እንደገና ክስ ከማቅረብ የሚያግደው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231(1)፣ 232(2) እና 231 | 208632 | አቶ ፀጋነው መንበሩ እና አራዳ ክ/ከ/አነስተኛ ግብ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት | ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም | 48 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥ እና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሳይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5(1)<br>ኪሳራ ለማስከፈል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ሲሆን መሰል የዳኝነት ጥያቄን ተቀብሎ ዳኝነት ሊሰጥ የሚችል ሌላ የዳኝነት አካል በሌለበትና የፍርድ ቤት ስልጣንም በቀጥታም ይሁን በግልጽ ባልታገደበት ሁኔታ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሚወስን ስላለመሆኑ | | | | |
| 10. | ይግባኝ ባይ ያቀረበዉ የይግባኝ ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.327 (2) መሰረት ከሥር ፍ/ቤቶች የመዛግብት ግልባጭ ጋር ለፍ/ቤት ተያይዞ ባልቀረበለት፣ መዝገቡ ቀጠሮ የተሰጠው መሆኑን በግልጽ ለይግባኝ ባይ መነገሩ ባልተረጋገጠበት ወይም ይግባኝ ባይ ቀጠሮን ባላወቀበት ሁኔታ በቀጠሮ ቀን ባለመቅረቡ ቅሬታዉን መስማት አለመቻሉንና ቅሬታዉን የማሰማት መብትም መታለፉን በመጥቀስ ይግባኙ አያስቀርብም በማለትና በመሰረዝ ፍርድ ቤት የሚያሳልፈዉ ትዕዛዝ የህግ ድጋፍ የሌለዉ ስለመሆኑ | 201886 | አቶ ታዬ ሰይፉ መኩሪያ<br>እና<br>የሚች ወ/ሮ ስርጉት ተፈራ ወራሾች<br>(4 ሰዎች) | ሚያዚያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም | 52 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 11. | የፍትሐ ብሔር ክርክርን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባልጠየቁት ጉዳይ ላይ ዳኝነት የሚሰጥ ስላለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 182(2)<br><br>በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር ላይ ያልተነሳ አዲስ ክርክር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ደረጃ ሊነሳ የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329(1) | 203290 | ወ/ሮ ዘቢደር ከበደ አማረ<br>እና<br>አቶ አወል ሼይቶ | ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም | 58 |
| 12. | በጣልቃ ገብነት ይርጋን በመቃወሚያነት በማንሳት ለሚቀርብ ክርክር የሌላኛው ተከራካሪ ወገን ከሚያቀርበው መከራከሪያ ጋር አከራክሮ ውሳኔ መስጠት ሲገባ ጣልቃ ገብቶ የሚከራከር ወገን ይርጋን እንደመቃወሚያ አንስቶ ሊከራከር አይችልም በሚል የይርጋ መቃወሚያ ክርክር ውድቅ የሚደረግ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358-360 | 196255 | ወ/ሮ ክላሪስ ዴኒስ ቶምሰን<br>እና<br>ወ/ት ቤቴልሄም አስራት | 25/4/2014 ዓ/ም | 63 |
| 13. | ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ በዋናው ፍሬ ጉዳይ ላይ ክርክር ለመስማት ቀጠሮ መለወጡ ብቻ ከስረ-ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችልና በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ወይም እልባት የተሰጠበት ባለመሆኑ በዚህ ሁኔታ ቅሬታ ካለ በስረ-ነገሩ ጉዳይ ላይ | 200117 | እነ ወ/ሮ አታሪ አሳሌ<br>(3 ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሹምቡቤ ሻሬቾ | ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ/ም | 67 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ መቃወሚያው በመታለፉም ያለውን ቅሬታ ጨምሮ በአንድ ላይ በማጠቃለል ይግባኙን/የሰበር አቤቱታው የሚቀርብ እንጂ ክርክሩ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ በመቃወሚያ በተሰጠ ብይን ላይ ይግባኝ የሚቀርብ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(3) | | (7 ሰዎች) | | |
| 14. | በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር የቀረበለት ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች በዝርዝር ባቀረቡት ወይም በግልጽ ባመለከቱት ጉዳይ ላይ ተመስርቶ በህጉ አግባባ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህን ውሳኔ ሲሽርም ሆነ ሲያሻሽል ግን በህግና በማስረጃ የተደገፈ ምክንያት ሊሰጥ፣ ግራ ቀኝ የጠየቁትን የይግባኝ የዳኝነት ጥያቄ፤ ክርክሩ የሚመራበት የሥነ ሥርዓት ህግ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን የዳኝነት ስልጣን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ሊያደረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) እና 348(1) | 213074 | ወ/ሮ ሩቂያ መሀመድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አይሻ በያን<br>(2 ሰዎች) | ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም | 71 |
| 15. | በስር ፍርድ ቤት ለቀረበ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበው ክርክር ከተሰማ በኋላ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የገመተውን ማስረጃ በመመርምር የቀረበው መቃወሚያ በተገቢና በቂ በሆነ ማስረጃ የተደገፈ መሆን አለመሆኑን ፍሬ | 208253 | እነ ወ/ሮ ብርቂ ታደሰ<br>(3 ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ታደሰ | ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም | 77 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ነገርን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሰጠውን ውሳኔ፤ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃውን መዝኖ፣ ከወረዳ ፍርድ ቤት እስከ ክልል ይግባኝ ሰሚ ድረስ ያሉ ችሎቶች አግባብነትና ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ተቀብለው በመመዘን አረጋገጥን ከሚሉት የፍሬ ነገር መደምደሚያ በመውጣት ወሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 245(1) እና (2) | | | | |
| | **ውል** | | | | **81** |
| 16. | በተዋዋይ ወገኖች መካከል በተደረገ ውል የአፓርትመንት ቤቶችን ገንብቶ ለማስረክብ እና ክፍያዎችም መፈጸም የሚገባቸዉ የግንባታ ዉሎች፣ የእነዚህ ዉሎች አካል እንዲሆኑ የተስማሙባቸዉ ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን መሰረት መሆን እንዳለበት በተደረገ ስምምነት ቤቶች ተሰርተው ባለመጠናቀቃቸው ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ እንዲያስረክብ በሚል የሚሰጥ ውሳኔ፤ ተሰርቶ የተጠናቀቁ ወይም ያልተጠናቀቁ ሥራዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ከዉሉ አንጻር የተሰሩ ሥራዎችንና ግንባታዉ የደረሰበት ደረጃ በባለሙያ ሳይጣራ፤ ምን ያህል ክፍያ መከፈል እንዳለበት ተጣርቶ ሳይገመትና ምንም ዓይነት ክርክር ሳይነሳበት፤ በግንባታ ዉል መሰረት ሙሉ ክፍያዎች ሊከፈለኝ ይገባል በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 188102 | መይ ሪል ስቴት ዴቨሎፐመንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ፋሲል ጌታቸዉ (24 ሰዎች) | ጥቅምት 25 ቀን 2014 ዓ.ም | 82 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለዉሎች በጠቅላላዉ የተመለከቱት የፍትሐ ብሔር ሕግ እንዲሁም የሕንጻ ሥራን የሚመለከቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3019-3040 ድንጋጌዎች | | | | |
| 17. | በሽያጭ ውል ሻጭ ለተሸጠዉ ንብረት ዋጋዉን ከገዥ መጠየቅ የሚችለዉ እና ገዥም ንብረቱን የገዛበትን ዋጋ ለሻጭ ለመክፈል የሚገደደዉ ንብረቱን በዉሉ በተመለከተዉ አግባብ ከተረከበ ወይም ያለበቂ ምክንያት ንብረቱን ለመረከብ ፍቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ብቻ መሆኑን፣ ገዥዉ ንብረቱን ተረክቦ ወይም መረከብ ሲገባዉ ያለ በቂ እና ህጋዊ ምክንያት ሳይረከብ ቀርቶ የንብረቱን ዋጋ ለሻጭ ያልከፈለዉ እንደሆነ ሻጭ ገዥዉ ገንዘቡን ተገዶ እንዲከፍል ወይም ዉሉ እንዲሰረዝ ወይም/እና ካሳ እንዲከፈለዉ ዳኝነት መጠየቅ የሚችል መሆኑን እና ሻጭ ይህን ዳኝነት ለመጠየቅ ግን በበኩሉ በዉሉ መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ መሆኑን ወይም ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 2274፣ 2279፣ 2303፣ 2329-2359 እና 2360 | 201665 | ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ<br>እና<br>አቶ ኤፍሬም ደሳለኝ | ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም | 95 |
| 18. | ዉል በፀና አኳኋን ተደርጓል ሊባል በሚችል አኳኋን በተዋዋዮች ፈቃድ እና ችሎታ፣ የዉሉ ጉዳይ የሚቻል፣ ሕጋዊና ሞራላዊ ከመሆን አኳያ እና በሕግ ከተደነገገዉ ፎርም አንጻር ጉድለት ሳይኖርበት ጉድለት አለበት በሚል ክርክር ሳይቀርብበትና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ዉል የሚያስፈርስ ምክንያት በሌለበት፤ የዉል ግዴታ መፈጸሚያ ጊዜ በመዘግየቱ ምክንያት የደረሰ ጉዳት | 203358 | እነ አቶ ደልቦ ደንድሬ (2 ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ደጀኔ ጌታነህ | የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ/ም | 101 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ካለ ተገቢዉን ኪሳራ እንዲጠየቅ ከሚቻል በስተቀር በዉሉ የተመለከተዉን ጊዜ አለማክበር ዐይነተኛ የሆነ የዉል መጣስ ወይም ቁርጠኛ የሆነ የዉል መፈጸሚያ ጊዜ ተጥሷል የማይባልና ዉል የሚያስፈርስና የሚያሰርዝ ምክንያት ባለመሆኑ ውሉ ሊፈጸም የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1711፣1808<br><br>ተዋዋይ ወገኖች የኪሣራ ክፍያ የተዋዋሉት ለውሉ አፈጻጸም መዘግየት ስለመሆኑ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ሊፈጸም የሚችል ውል ላይ ኪሣራ ለመጠየቅ የሚቻል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 1890(2) | | | | |
| 19. | በሽያጭ ውል ገዥዉ እቃዉ እንደዉሉ ትክክል አይደለም ወይም ጉድለት አለበት በማለት እንዲሟላ ወይም ጉድለቱ እንዲስተካከል ለመጠየቅ ያለዉ መብት በጊዜ የተገደበ በመሆኑ የተረከበዉን እቃ ባጭር ጊዜ ዉስጥ መመርመር እና ልዩነት ካለም ባጭር ጊዜ ዉስጥ ማስታወቅ ያለበትና በእቃዉ ላይ ጉድለት መኖር አለመኖሩን ለማስታወቅ የሚቻልበት ጊዜ በስምምነት የተወሰነ ከሆነ ገዥዉ በዉል በተወሰነዉ ጊዜ ዉስጥ የማስታወቅ ግዴታውን ካልተወጣ ይህን የሚያነሳዉን የመብት ጥያቄ ሊያጣ የሚችል ስለመሆኑ<br>በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2291(1) እና 2292፣ 2294፣ 2293 | 207371 | ኤልባን ጌት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ዋቻሞ ዩንቨርሲቲ | ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም | 106 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ በተሟላ ሁኔታ ሳይሰማ እና ሳይጣራ የሚሰጥ ዉሳኔ የክርክር አመራር ጉድለት ብቻ ሳይሆን የተከራካሪ ወገኖችን እኩል የመሰማት መብት እና አንጻራዊ እዉነትን ከማረጋገጥ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ሊታረም የሚገባ ስለመሆኑ | | | | |
| 20. | በቤት ሽያጭ ውል ሻጭ የሆነው አካል ቤቱን ገዝቻለሁ ከማለት ውጪ ለገዥ ለማስተላለፍ በስሙ ያስመዘገበበት ሁኔታ ስለመኖሩ የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ሌላ ህጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ የሚያስረዳ ማስረጃ በሌለበት የቤቱ ስመ ሀብት በገዥ ስም በመመዝገቡ ብቻ ሻጭ ቤቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ ከዉል ወይም ከህግ የመነጨ መብት ያለዉ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ባልተወጣበትና የራስ ባልሆነ ቤት ላይ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808፣1784 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች፣የፍ/ብ/ህ/ቁ 2281 እና 2282፣ እንዲሁም 1195 እና 1196 | 208266 | አቶ ስሜነህ ዘሪሁን<br>እና<br>እነ አቶ ጀማል ሰይድ<br>(3 ሰዎች) | ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓ.ም | 112 |
| 21. | በግራ ቀኙ መካከል የሽያጭ ውል የሌለና ረቂቅ ውል መሆኑና የሚፈጽሙት የቤት ሽያጭ ዉል የለም ከተባለ ግራ ቀኙ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ የሚመለሱና ለቤት ሽያጭ በሚል የተከፈለው ገንዘብ የሽያጭ ዋጋ ከፊል (ቅድሚያ) ክፍያ እንጂ ቀብድ አለመሆኑ ከተረጋገጠ | 211204 | አቶ ጌታሁን ኪዳነማርያም<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አሰለፈች በቀለ<br>(7 ሰዎች) | ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም | 119 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተከፈለ ገንዘብ ያህል መመለስ እንጂ አጠፌታ እንዲከፍል የሚያስገድዱ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1885(2) እና 1815(1) | | | | |
| 22. | ውል ያልፈጸመ ወገን ያልተፈጸመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውል ያልፈጸመው ወገን የደረሰውን የጉዳት ኪሣራ የሚከፈለው ተዋዋዮች በፍ/ሕ/ቁ. 1889 መሠረት አስቀድመው የወሰኑት ከሆነ በውሉ የተመለከተውን መጠን ሲሆን ተዋዋዮች አስቀድመው ኪሣራውን ካልወሰኑ በክርክር ሂደት ፍርድ ቤት ኪሣራውን በማስረጃ አጣርቶ የሚወሰን ሲሆን ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት ያደረገ ከሆነ የሚከፈለው ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ ወይም ተመጣጣኝ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 1790 እና 1791 እንዲሁም 2090(1) | 216155 | አቶ ታደሰ ጉታ<br>እና<br>የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣<br>የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፣<br>የጅግጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት<br>(3 ሰዎች) | ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም | 128 |
| 23. | የቤት ሽያጭ ዉል ስለመደረጉ ክርክር በቀረበበት ሁኔታ ዉሉ በጽሁፍ መደረጉን ብቻ ሳይሆን ስርዓቱን ተከትሎ ዉል ለማዋዋል ስልጣን ባለዉ አካል ፊት የተረጋገጠ የቤት ሽያጭ ዉል ባልቀረበበትና ይህም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሆኖ፣ ረቂቅ ነዉ የተባለ ሰነድ ላይ ያለዉን | 215762 | እነ አቶ ጳውሎስ ኦርጂኖ<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ኤጌዶ | ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም | 133 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፊርማ እና የምስክሮች ቃል መሰረት በማድረግ በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩ ሊረጋገጥ የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1720(1) እና 1723/1/፣ 1678 (ሐ)፣ 1719(2)<br><br>የቤት ሽያጭ ዉል የለም ከተባለ ግራ ቀኙ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ ሲመለሱ ለቤት መግዣ በሚል የተከለፈ ገንዘብ ቀብድ ሳይሆን የሽያጭ ዋጋ ከፊል ክፍያ መሆኑ ከተረጋገጠ የተከፈለው ገንዘብ ያህል የሚመለስ እንጂ አጠፌታ እንዲከፍል በሚል የሚያስገድድ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1885(2) እና 1815(1) | | | | |
| **ንብረት** | | | | | **139** |
| 24. | ንብረት ያረፈበት ቦታ ለልማት ሲፈልግ ወይም በመሬት ላይ የሚገኝ ንብረት የተወሰደበት ሰዉ እንደ አግባብነቱ ምትክ ቦታ እንዲሰጠዉ ወይም ከመሬት ላይ ለተነሳዉ ንብረት የማፈናቀያ ካሳ እንዲከፍለዉ የመጠየቅ መብት ያለዉ ሲሆን መንግስትም ይህን የማድረግ ግዴታና ንብረቱ የተወሰደበት ወይም ከቦታዉ እንዲነሳ የተደረገ ሰዉ የሚያቀርበዉ የካሳ ይገባኛል ጥያቄ ይህን ሁሉ ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ | 184596 | አቶ ጫላ ያኢ ፋሪ<br>እና<br>የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት | ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም | 140 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(8) እና ለህዝብ ጥቅም ሲባል የግል ንብረትን መዉሰድ የሚቻልበትን አግባብ የሚደነግግ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 7 እና 8 | | | | |
| 25. | አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለሀብትነት በማወቅ የመመዝገብ ሥልጣን ያለው አካል ይዞታ በስጦታ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጦ በባህር መዝገብ ተመዝግቦ የዚህ ይዞታና ቤት ባለቤት ስለመሆን በሚመለከተው አካል ፊት የተረጋገጠ እንዲሁም የባለይዞታው ህጋዊ ይዞታ አይደለም የሚል ወገን ቢመጣም መቃወሚያ እንዳይሆን የሚያደርግ ህጋዊ ሂደቱ ተጠብቆ በህግ ጥበቃ እየተደረገለት ያለ መብት በህግ አግባብ ለባለይዞታ የተላለፈ እና ይህንኑ ንብረት ህጋዊ ውክልናን በመያዝ ሲተዳድር የቆየ መሆኑ የሚያሳይ ሆኖ እያለ ይዞታው እንዲለቀቅና በውርስ ህግ አግባብ ሊጠየቅ ይገባል በሚል የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | 201741 | ፅጌ ቀለመወርቅ<br>እና<br>ወ/ሮ አረጋይ ከበደው | ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ.ም | 148 |
| 26. | በመሬት ሽያጭ ግዢ ውል የተገኘ ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ በስም ውጥቶለትና ቤት በመስራት ግብርም እየተገበረበት ያለ ቢሆንም የመሬት ሽያጭ የተከለከለ በመሆኑ ይዞታው የተገኘበት መንገድ ህገወጥ ሊባል ሲገባ የይዞታው መተላለፊያ መንገድ ሳይመረመር እና ህጋዊነቱም ከህገ መንግሥት ስለመሬት ማስተላለፊያ መንገዶች በህጋዊ መንገድ ለመተላለፉ ሳይረጋግጥ ውሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ | 201894 | ቢላድ አህመድ ከሊፋ<br>እና<br>አንበር አህመድ ኡመር | መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም | 155 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (3) | | | | |
| 27. | የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረውና ይህንኑ በሀይል ሲነጠቅ ወይም በይዞታዉ ስር ባለ ንብረት ላይ የመጠቀም መብቱን የሚያዉክ ተግባር ሲፈጸም እንዲሁም ንብረቱ በሕግ አግባብ በይዞታው ሥር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የሀይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጥር ንብረቱን እንደወሰደበት ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1149/1 | 197183 | ደበርማዊ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን<br>እና<br>እነ አለማየሁ ቶሎሳ<br>(2 ሰዎች) | ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም | 160 |
| 28. | ከሁከት ይወገድልኝ ክስ ጋር በተያያዘ የፍርድ ቤት ክርክር የክስ ማቅረቢያ ጊዜ አስመልክቶ ለአስተዳደር አካል የመብት ጥያቄ ማቅረቢያ ጊዜ እና ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረቢያ ጊዜን ለይቶ ማየትና የቀረበ የመብት ጥያቄ በእርግጥም በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ለማጣራት ለመብቱ መጠየቅ መሰረት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበትን እና ለአስተዳደር አካል እና ለፍርድ ቤት የመብት ጥያቄው የቀረበበትን ጊዜ በአግባቡ ማየት የሚገባ ስለመሆኑ<br><br>የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1149(2) እና የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2010 አንቀፅ 56(1(ሀ)) | 202845 | አቶ በላይ ማሞ<br>እና<br>የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን | ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ.ም | 166 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በፍትሐ ብሔር ክርክር ጉዳይ ወደ ክስ ሥረ ነገር ክርክር ሳይገባ ክሱን ያቀረበው አካል ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የለውም በሚል ምክንያት አቤቱታውን ውድቅ ለማድረግ ክስ ያቀረበው አካል በእርግጥም መብት እና ጥቅም የሌለው ለመሆኑ እርግጠኛ መሆንና በዚህ አኳኋን አቋም ለመውሰድ የሚያስችል ግልፅ ማሳያ ከሌለ በቀር ክሱን ያቀረበው አካል የሚኖረው መብት እና ጥቅም በሥረ ነገር ክርክር ወቅት በማስረጃ የሚረጋገጥና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33 መሰረት አቤቱታው ውድቅ የሚደረግ ስላለመሆኑ<br><br>የሁከት ይወገድልኝ ክስ በቀረበበት ወቅት ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በከሳሽ እጅ መኖሩ ካልተካደ ሁኔታው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ በቂ መብት የሚፈጥር በመሆኑ ከሳሽ በመጀመሪያው የክርክር ምዕራፍ ላይ መብት እና ጥቅም የለውም ሊባል የማይችልና የቤቱ አያያዝ ህጋዊነት፣ በህግ ረገድ ስለሚኖረው ውጤት እና ተያያዥ ጉዳዮች በክርክር ሂደት ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት የተሟላ ክርክር እና ማስረጃ ነጥሮ የሚወጣ ጉዳይ እንጂ ክስ ለማቅረብ ከሚኖር መብት እና ጥቅም ጋር የሚያያዝ ስላለመሆኑ | | | | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ንብረቱን በተመለከተ በህግ ከተረጋገጡለት መብቶች ውስጥ አንዱ በሀብቱ ላይ የተፈጠረው ህገ ወጥ ሁከት እንዲወገድለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ሰው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች የሆኑትን ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት መሆኑን ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ/1140፣ 1146 እና 1149 | | | | |
| 29. | ሁከት እንዲወገድ በሚል በቀረበ ክስ ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ቤት ባለቤትነት አከራካሪ፣ ከሳሽም ቤቱ በውርስ የተገኘና ባለቤት እንደሆነ የገለጸ ከሆነ፤ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት ያለውና ቤቱ የከሳሽ የግል ሀብት አለመሆኑ ተጣርቶ የሚሰጥ ውሳኔ ከሳሽ ለጠየቁት ዳኝነት ምላሽ የሰጠ እና በአግባቡ የተሰጠ ፍርድ ነው ከሚባል በቀር፤ፍርድ ቤት ከቀረበለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ጭብጥ ወጥቶ የቤት ባለቤትነት ጉዳይ ላይ ፍርድ ሰጥቷል የሚያስብል ስላለመሆኑ | 203882 | እነ አቶ ብርሃኑ ሻይ<br>(4 ሰዎች)<br>እና<br>የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ<br>የይዞታ አስተዳደር<br>የሽግግር ጊዜ አገልግሎት<br>ፕሮጀክት ጽ/ቤት<br>(2 ሰዎች) | መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም | 172 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 30. | የሁከት ይወገድልኝ የክስ አቤቱታ ቀርቧል ለማለት የሚቻለው ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ንብረት በእጅ አድርጎ የሚገኝ እና ንብረቱ ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጭበረበረና በማናቸውም መንገድ ሕገ ወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተያዘ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ተከሣሽ ድርጊቱን እንዲፈፅም የተፈቀደለት መብት ወይም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በማይታበይ ሁኔታ ማስረዳት የሚጠበቅ ስለመሆኑ<br><br>የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1140ና 1149 | 218309 | ቄስ ቀፀላጊዮርጊስ ደስታ<br>እና<br>እነ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ፅ/ቤት<br>(2 ሰዎች) | ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም | 176 |
| **ውርስ** | | | | | **181** |
| 31. | ቤት የተሰራበት ይዞታ ለባልና ሚስት በጋራ የተመራና ከአንደኛው ተጋቢ በሞት መለየት በኂላ በህይወት ባለው ሌላኛው ተጋቢ የተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ በጋራ የተመሩት ቦታ የከተማ ይዞታ ሆኖ ቦታው የተሰጠው የመኖሪያ ቤት ለመሥራት በመሆኑ ቤቱ የመሬቱ አንድ አቋም ተደርጎ ስለሚቆጠር ቤቱን የሰራው ተጋቢ በቤቱ ላይ ያለው ባለሀብትነት መሬቱንም የሚጨምር ሆኖ እያለ፤ ባልና እና ሚስት አከራካሪው ቤት የተሰራበትን የከተማ ይዞታ አብረው ስለተመሩ ብቻ በአንደኛው ተጋቢ ጥረት የተፈራው ቤትና ሟቹ ያልነበረው መብት በውርስ ሊተላለፍ የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1131፣ 1132 እና 826(2) | 202027 | ወ/ሮ አስማረች ጀምበሬ<br>እና<br>አቶ አፅምሮ አወቀ | ጥር 23 ቀን 2014 ዓ/ም | 182 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 32. | ኑዛዜ በመንፈስ መጫን የተደረገና ከሟች የቀድሞ ጋብቻ የሚወለዱ ልጆችን በዝምታ ከውርስ የመንቀል ውጤት አለው በሚል ኑዛዜ እንዲሰረዝ ለቀረበ አቤቱታ ተናዛዡ የኑዛዜ ተጠቃሚዎች እንዳያበላልጥ በህግ የተቀመጠ ክልከላ ሳይኖር ሟች የሰሩ መብት ለወራሾች መስጠታቸው ኑዛዜው በመንፈስ መጫን የተደረገ፣ የሌሎች ወራሾችን መብት የጎዳና ውርሱ ተጣርቶ የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻው ሳይታወቅ በውጤቱ ወራሾችን ከውርስ የነቀለ በመሆኑ ፈራሽ ነው የሚባል ስላለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 868 | 216298 | እነ ወ/ሮ አስቴር ለማ (3 ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሜሮን ስዩም (2 ሰዎች) | ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ/ም | 187 |
| 33. | የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ በወራሾች መካከል የውርስ ሀብት ክፍፍል ስምምነት ሊፈፀም የሚገባበትን ፎርማሊትን አስመልክቶ ግልጽ የህግ ድንጋጌ ባይኖርም የሚደረገው ስምምነት በተስማሚዎቹ መካከል መብትና ግዴታን የሚፈጥር ውል እንደመሆኑ መጠን የሚደረግ የክፍፍል ወይም የማዛወር ስምምነቶች ሁሉ በጽሑፍ በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ሊደረግና በሚመለከታቸው ወራሾች የተፈረመበት ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1079፡ 1719፣1677 እና የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1723(2) | 199901 | እነ ወ/ሮ ዘውዴ እረዳ (4 ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ የሹምነሽ ስዩም | መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም | 192 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 34. | የወራሽነት ምስክር ወረቀት የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ በፍ/ሕ/ቁ. 997 መሰረት ወራሹ በምስክር ወረቀቱ እንደተገለጸው ወራሽ እንደሆነ ግምት የሚወሰድ ቢሆንም በፍ/ሕ/ቁ. 946 እና ተከታዮቹ መሰረት ወርስ ተጣርቶ የወራሾች ማንነትና የወራሾች የዉርስ ሀብት ድርሻ ተለይቶ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 996 መሰረት ተገልጾ የተሰጠ የወራሽነት ምስክር ወረቀት ባለመሆኑ በህግ የተገኘን መብት ለማረጋገጥ የሚሰጥ እንጂ የወራሽነት ማስረጃዉን በመጥቀስ ክርክር የማይቀርብበትና በእራሱ የተለየ መብት የሚሰጥ ስላለመሆኑ<br><br>አንድ ድርጊት ወይም መብትና ግዴታ በተፈጠረበት ጊዜ የነበረዉ ህግ በሌላ ህግ የተተካ ሆኖ ሲገኝ እና ክርክሩ ለፍርድ ቤት ወይም ለዳኝነት ሰጪ አካል የቀረበዉ አዲሱ ህግ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ሆኖ ከተገኘ ይህ መሠረታዊ ህግ (substantive law) ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ህግ አዉጪዉ እራሱ በልዩ ሁኔታ ካላመላከተ በስተቀር፣ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መምራት እና ዉሳኔ መስጠት ያለበት በተሻረዉ ህግ መሠረት ሲሆን ክርክሩ አዲሱ ህግ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለፍርድ ቤት መቅረቡ ጉዳዩ በአዲሱ ህግ መሠረት እንዲመራ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስላለመሆኑ | 191393 | እነ አቶ ሰይፈ ላቀው<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አሸናፊ ተክሉ | ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ/ም | 198 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 51/1999 እንዲሁም የአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 252/2009<br><br>በፍ/ሕ/ቁ. 826(1) እንደተመለከተው ዉርስ የሚከፈተዉ አዉራሹ በሞተበት ጊዜ እና ቦታ በመሆኑ ለውርስ ክርክር ወራሾቹ ሆነ ቀዳሚ ወራሾች እነማን ናቸው የሚለው ሊወሰን የሚገባው አውራሽ በሞተበት ጊዜ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት እንጂ በክርክሩ ጊዜ አዲስ ሥራ ላይ በዋለው ሕግ መሰረት ስላለመሆኑ<br>**(የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 86089፣ 99587፣ 121822 እና 183645 መዝገቦች ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ተለውጧል።)** | | | | |
| 35. | ምንም እንኳን የፍርድ መቃወሚያ የቀረበው አስቀድሞ የነበረ ክርክር በሚታወቅበት ሁኔታ ቢሆንም የፍርድ መቃወሚያ የቀረበበት ክርክር የውርስ ሀብትን መሰረት ያደረገ ከሆነ የውርስ ሀብቱ ክፍፍል ከተደረገ በኋላም ቢሆን የሚቻል ክርክር በመሆኑ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ | 144359 | እነ አቶ መስፍን እንደሬ (4 ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ብዙነሽ እሸቴ | የካቲት 14 ቀን 2010 ዓ.ም | 208 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አመልካች አስቀድሞ ክርክሩን ያውቅ ነበር በሚል ውድቅ የማይደረግና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ድንጋጌ የውርስ ሀብት ክርክርን በተመለከተ ተፈፃሚነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ<br>የፍትሀ ብሄር ህግ ቁጥር 1080 | | (2 ሰዎች) | | |
| 36. | የሟች ወራሽ ላልሆነ ሰዉ የተሰጠ የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰረዝ መብት ያለዉ ሰዉ ክስ ሲያቀርብ ተከሳሹ የወራሽነት መብት የሌለዉ መሆኑን በክሱ የማሳየት እና ይህንኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 997-999<br>በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1000(1) ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ጊዜ የወራሽነት ማስረጃን ለማሰረዝ ወይም ህጋዊ መብት በሌለዉ ሰዉ የተያዘ የዉርስ ንብረት እንዲለቀቅ የሚቀርብ ክስ የሚቀርብበትን ጊዜ የሚመለከት በመሆኑ ይህም በባህሪዉ ክስ እንዳይቀርብ የሚከለክል (limitation of actions) ስለመሆኑ<br>አንድ ሰዉ የወራሽነት ማስረጃን በተወሰነ ጊዜ ዉስጥ ከፍርድ ቤት ካልወሰደ ወይም ወራሽነቱን ካላሳወጀ የመዉረስ መብት እንደሚያጣ (extinctive prescriptive) በህግ የተመለከተ ድንጋጌ ባለመኖሩ የተሰጠ ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል በሚል የሚቀርብ ዳኝነት ተቀባይነት የሌለዉ ስለመሆኑ | 236246 | ወ/ሮ ገነት ጉልላት<br>እና<br>ወ/ሮ ተቋመወርቅ በለጠ | ሰኔ 26 ቀን 2015 ዓ.ም | 212 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ቤተሰብ** | | | | **216** |
| 37. | በትዳር ጊዜ በርከት ያለ ገንዘብ ወጪ ያደረገ ተጋቢ ይኸው ገንዘብ ለትዳር ጥቅም እንዳልዋለ ክርክር ሲቀርብበት ገንዘቡ በሙሉ ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ማስተባበል የሚጠበቅበት ሲሆን ማስተባበል ካልቻለ የሌላውን ተጋቢ ድርሻ ገንዘብ የሚከፍል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(1) | 215583 | ወ/ሮ ምስራቅ ሞገስ<br>እና<br>አቶ ገብረፃዲቅ አባይ | ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ/ም | 217 |
| 38. | ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ሳይቋረጥ ሌላ ትዳር ከተመሰረተ በኂላ በተፈራ ቤት ላይ የበፊት/የመጀመሪያው ተጋቢ በቤት ማፍራቱ ላይ አስተዋፅኦ የሌለው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ቤቱ በተፈራበት ወቅት የቀደመው ጋብቻ ያልተቋረጠ የነበረ በመሆኑ በቤቱ መፈራአት ላይ አስተዋጽኦ የሌለው ተጋቢ የቤቱ ቀሪ ግማሽ ድርሻ(50%) ከሆነው ከቀድሞ ተጋቢ ድርሻ ውስጥ ግማሹን (25%) ድርሻ የማያሳጣውና የሁለተኛው ጋብቻ ባል/ሚስት ቤቱ የተፈራው በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ወቅት በመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(2) መሰረት የቤቱ ግማሽ (50%) ድርሻ ባለመብት ስለመሆኑ | 196814 | ሃዲያ ያሲን ሸዩቦ<br>እና<br>ሁሴን ሰኒ ኢብራሂም | ጥቅምት 3 2014 ዓ.ም | 222 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 39. | በባል ወይም በሚስት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት በጋብቻ ወቅት በጋራ ጥቅም ላይ የዋለ በመሆኑ የጋራ ነው በሚል የንብረት ክፍፍል ዳኝነት ሲቀርብ የጋራ ንብረት ነው የተባለበት ምክንያት በትዳር ውስጥ ስላፈሩት ነው ወይስ የግል ንብረት የነበረውን በጋብቻቸው ጊዜ የጋራ ያደረጉት የሚለውን በመለየት ውሳኔ የሚሰጥበትና ቤቱ የግሌ ነው በሚል የሚቀርብ ክርክር የግል ስለመሆኑ ማስረዳት የሚጠበቅበትና የግል ንብረት መሆኑን ካሳየ የግል ንብረቱ የጋራ ሆኗል የሚል ተከራካሪም ይህንን ማስረዳት የሚጠበቅበት ስለመሆኑ<br><br>ቤት በባል ወይም በሚስት ስም ተመዝግቦ ያለ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በትዳር ባሉበት ጊዜ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ባልተካደበት የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የተቀመጠውን የህግ ግምት ቤቱ በስሙ የተመዘገበው ተጋቢ የግል ንብረቱ መሆኑን በማስረጃ ማስረዳት እየተገባ የጋራ ንብረት መሆኑን አላስረዳም/አላስረዳችም ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 63(1) | 212845 | ወ/ሮ ገነት ገለቱ<br>እና<br>አቶ ዮሀንስ ዛቲ | 22/09/2014 ዓ/ም | 227 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 40. | ኢትዮጵያዊ የሆነ ዜጋና የውጭ ሀገር ዜጋ ህጋዊ ጋብቻ ፈፅመው በትዳር አብረው መኖር የሚከለክላቸው ህግ እስከሌለ ድረስ ጉዲፈቻ ለውጭ ሀገር ዜጋ ተከልክሏል በሚል ብቻ ከትዳራቸው በፊት የባል ወይም የሚስት ልጅ የሆነውን ሌላኛው ተጋቢ በጉዲፈቻ ለመውሰድ የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲፀድቅላቸው የሚያቀርቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 187 | 215383 | እነ ወ/ሮ አርሴማ ኤልያስ<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>-------- | ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም | 232 |
| 41. | በቤተሰብ ህግ መሰረት ባልና ሚስት ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ በተደገነገበት ሁኔታ በጋብቻ ወቅት ባልና ሚስት በፍ/ቤት ወይም ስልጣን ባለው አካል ባልፀደቀ ውል ከውርስ የሚገኝ ንብረት የጋራ ነው በሚል ቢዋዋሉም ውሉ በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ በቀር ውጤት ስለሌለው በጋብቻ ወቅት በውርስ የተገኘ ንብረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ሆኖ የሚቀጥል ስለመሆኑ<br>የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 73 እና 89 | 198277 | አቶ ተሾመ ቶላ<br>እና<br>ወ/ሮ አሰጉ ፈዬ | ጥቅምት 2 ቀን 2014 ዓ.ም | 237 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 42. | ♣ ከብር 500.00(አምስት መቶ ብር) በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰዉ ዋስ ለመሆን የተጋቢዎቹ ስምምነት የሕግ ግዴታን ባለማክበር አንዱ ተጋቢ የውል ግዴታ ገብቶ ሲገኝ ሌላኛው ተጋቢ ግዴታው እንዲፈርስ ክስ ሲያቀርብ የውል ግዴታ የገባው ተጋቢ ሌላኛው ተጋቢ ግዴታ መገባቱን ያውቃል በሚል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2 ስር የተደነገገዉን የ6 ወር የይርጋ ጊዜ በመቃወሚያ የሚያቀርብ ተከራካሪ (ተጋቢ) ሌላኛዉ ተጋቢ ግዴታዉ መገባቱን እንዴትና መቼ እንዳወቀ ማስረዳት የሚጠበቅበት ስለመሆኑ<br><br>♣ በአንደኛዉ ተጋቢ የዉል ግዴታ ሲገባ በስምምነቱ ተሳታፊ ያልሆነ[ዉ]ችዉ ተጋቢ ዉል ይፍረስልኝ ክስ ለማቅረብ በሚያስችል ልክ ስለዉሉ መኖር የተሟላ እዉቀት ሊኖረዉ(ልኖራት) ስለሚገባ በአንደኛዉ ተጋቢ የተደረገ የገንዘብ ብድር ዉል መኖሩን ሌላዉ/ዋ ተጋቢ አወቀ/አወቀች ሊባል/ልትባል የሚችለዉ/የምትችለዉ ቢያንስ የገንዘብ ብድር ዉሉ ከማን ጋር እንደተደረገ፣ የምን ያህል ገንዘብ ብድር ዉል እንደሆነ፣ መቼ የተደረገ የብድር ዉል እንደሆነ ማወቅ ሲችል/ስትችል ስለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(2 እና 3) ፣ 80(2-4)፣85 እና 222/1፣ 258-260 እንዲሁም የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001/1 | 208197 | ዓለማየሁ አባተ(ዶ/ር)<br>እና<br>ወ/ሮ መፅሄት ዓይነኩሉ | መጋቢት 26 ቀን 2014 ዓ/ም | 241 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ♣ የጋብቻ ፍቺ ተከትሎ በሚደረገዉ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጊዜ ካልሆነ በቀር በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 68/መ እና 69/1 መሰረት የገንዘብ ብድር ዉል ሲደረግ ያልተሳተፈ ተጋቢ የብድር ዉሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ምክንያት ሊያደርግ የሚገባዉና ዉሉ እንዲፈርስ ከመወሰኑ በፊት በፍሬ ነገር ደረጃ ሊረጋገጥ የሚገባዉ በገንዘብ ብድር ዉል ግዴታዉ በተዋዋይነት አለመሳተፉን ብቻ እንጂ ከዚህ ዉጭ ዉል ይፍረስልኝ በሚል ከሚቀርብ ክስ ጋር በተያያዘ በብድር ተገኘ የተባለዉ ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ዉሏል ወይስ አልዋለም በሚለዉ ጭብጥ ላይ በማከራከር ዉሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ | | | | |
| 43. | ጋብቻ የተፈፀመበትን ትክክለኛ ጊዜ በተመለከተ በጋብቻ በምስክር ወረቀት ላይ የተገለፀውና በጋብቻ ክብር መዝገብ ላይ የተመዘገበው የተለያየ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ውሳኔ ስለሚሰጥበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 28፣ 30(ሐ) እና 94 | 198553 | አቶ እሸቴ አድኔ<br>እና<br>ወ/ሮ አስናቀች ለውጤ | ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም | 249 |
| 44. | ስለ ጋብቻ መፍረስ በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ቢሆንም ባልና ሚስት ለረጅም ጊዜ ተለያይተው የራሳቸውን ህይወት በየፊናቸው በመኖራቸው ጋብቻው የተቋረጠ በመሆኑ ተለያይተው ስለኖሩ ብቻ ጋብቻ በሁኔታ የለም በሚል ከፍርድ ቤት ውሳኔ | 205579 | አቶ ፍቃዱ ገብሬ<br>እና<br>ወ/ሮ እመቤት ኃይሉ | 25/4/2014 ዓ/ም | 253 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ውጪ የጋብቻ ፍቺ አለ በሚል የሚሰጥ ውሳኔ ተፈጻሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 75 እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌደሬሽን ም/ቤት በመ/ቁጥር 50/10 መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ/ም 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ አምስተኛ ዓመት፣ አንደኛ መደበኛ ስብሰባ የተሰጠ ውሳኔ | | | | |
| 45. | በባልና ሚስት ንብረት ክርክር የጋራ ንብረት የሆነውን የግል የሚያደርግ፣ የግል የሆነውን ንብረት የጋራ የሚያደርግ የንብረት ክፍፍል ስምምነት ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 97(1) እና አንቀጽ 101 | 205500 | ወ/ሮ አሰለፈች ዘነበ<br>እና<br>አቶ ቀጸላ አበበ | 24/5/2014 ዓ.ም | 256 |
| 46. | የተጋቢዎች ስምምነት ሳይኖር የጋራ ንብረት የሆነ ቤት ላይ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ስልጣን ባለው ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ፅ/ቤት ባልተመዘገበበት ሁኔታ በውሉ ላይ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ የተደረገውን የሽያጭ ውል አውቆ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁጥር 1723 እና 2878 | 190729 | አቶ አያልነህ ገ/ማርያም<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ክብነሽ ጎሹ<br>(2 ሰዎች) | የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ/ም | 260 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 69 መሰረት ከባልና ሚስት ከጋራ ስምምነት ውጪ የተደረገ ውል ስለሚያስከትለው ውጤት በማንኛውም ሁኔታ ውሉ ከተደረገበት ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ የውል ይፍረስልኝ ክስ መቅረብ አለበት የሚለው ደንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ውሉ ቢመዘገብ ወይም ባይመዘገብም እንኳን በሌላ አግባብ ስለውሉ መደረግ በሚያውቅ ተጋቢ ላይ ሲሆን የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው የውሉ መደረግ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ | | | | |
| 47. | የባልና ሚስት የጋራ ሀብት በዓይነት እንዲከፋፈል ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባዉ የክፍፍል ሥርዓት መሆኑን እና በግራ ቀኝ ስምምነት ለአንደኛዉ ተጋቢ ንብረቱ እንዲሰጥ የማይደረግ ከሆነ ንብረቱ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚደረገዉ ንብረቱን በዓይነት ማካፈል እንደማይቻል ሲረጋገጥ እና እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰዉ ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባዉ የክፍፍል ሥርዓት ሲሆን በዚህ መልኩ እኩል ማከፋፈል የማይቻል እንደሆነ ልዩነቱን በገንዘብ እንዲካካስ በማድረግ ክፍፍሉን መፈጸም የሚገባ ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 102 (1 እና 2) | 203209 | አቶ ስንታየሁ አባተ<br>እና<br>ወ/ሮ ታድፋለች ገላዬ | ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም | 266 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ስልጣን** | | | | | **271** |
| 48. | የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን በሆኑ ጉዳዮች ላይ የክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፣ በቅደም ተከተል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን በዉክልና የማየት ስልጣን ያላቸው ሲሆን ሆኖም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትንም ሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል ማደራጀት እንደሚቻል በተደነገገው መሰረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከተደራጀ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉክልና የማየት ስልጣን የሌለዉ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2 እና 4)፣ አንቀጽ 78 (2) እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን በተወሰኑ ክልሎች ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ቁጥር 322/95 አንቀጽ 2<br><br>የፍትሐብሔር ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቅድሚያ እንዲያከናዉን ከሚጠበቁት ተግባራት ዉስጥ አንዱ የቀረበው ክስ ህጋዊ ብቃት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን የማረጋገጥ ተግባር በመሆኑ ይህ ሲረጋገጥ መሰረት የሚደርገዉም በከሳሽ የቀረበዉን ክስ መሠረታዊ ይዘት እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን ማንነት እና አድራሻ መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ የቀረበዉ ክስ | 204107 | ብዙነህ ቢሌ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ<br>እና<br>ሲ.አር.ሲ.ሲ ጋምቤላ አቦቮ ፑኚዶ መንገድ ስራ ፕሮጀክት | ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም | 272 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ህጋዊ ብቃቱን ያሟላ መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ ግምት ዉስጥ መግባት ካለባቸዉ ሁኔታዎች ዉስጥም አንዱ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን ያለመሆኑ ስለሆነ በስልጣን ስር ሊወድቅ የሚችል ካልሆነ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 231 (1/ለ) እና አንቀጽ 9 | | | | |
| 49. | የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጦብኛል፣ በዉል ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ፣ እንዲወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 (1) (ሀ) እና (መ)፣ በድሬደዋ አስተዳደር ቻርተር በአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33 (1) (ሀ) እና (መ) ሥር የሚወድቅ ጉዳይ መሆኑን የሚያመለክት ነገር ስለሌለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ሆነ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ ከሊዝ ዉል አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የሚቀርበዉን ክስ ሰምቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እንጂ የአዲስ አበባም ሆነ የድሬዳዋ ከተማ የአስተዳደር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸው ስላለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 (1)፣ 79 (1) እና | 220566 | ሐጂ መሀመድ እስማኤል<br>እና<br>የድሬዳዋ አስተዳደር ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፣<br>አቶ ጌታቸዉ ረጋሳ ካባ | መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም | 276 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.4<br>**(የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ.54697 መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ተለውጧል።)**<br><br>የሊዝ ውል በሕግ በግልጽ የአስተዳደር ውል ነው ተብሎ ያልተመለከተ እና የከተማ ቦታን በሊዝ ውል በመያዝ የመጠቀም መብት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132 ድንጋጌ አንጻር ሲታይ በዚህ ድንጋጌ ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ባለመሆኑ የአስተዳደር ውሎች ሥር የሚወድቅ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ | | | | |
| **ንግድና ኢንሹራንስ** | | | | | **284** |
| 50. | በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ አብሮ የመስራት ፍላጎት ባልጠፋበት፣ የማህበሩ አባላት ተስማምተው ለመስራት ፍላጎት እያላቸው፣ ማህበር አባላትን ለማሰናበት የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ህግ ካስቀመጣቸው አማራጮች መካከል የመጨረሻ አማራጭ የሆነውንና ለተፈጠረ አነስተኛ ጥፋት፣ የማህበሩን ህልውና ለማስቀጠል እንደማይችል ተደርጎ ከማህበሩ እንዲሰናበቱ መወሰኑ የንግድ ህጉንም ሆነ የማህበሩን ደንብ መሰረት ያላደረገና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 216384 | እነ አቶ ሰለሞን እሸቱ (3 ሰዎች)<br>እና<br>ሰዓዳ ጌቱ እና ጓደኞቻቸው ሻወርና መፀዳጃ ህ/ሽ/ማህበር | ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ/ም | 285 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 51. | የመድን ሽፋን ለተሰጠው ከቀረጥ ነጻ የገባ ተሽከርካሪ ጉዳት ሲደርስበት የመድን ሽፋን ሰጪው ከደንበኛው ጋር በገባው የመድን ውል ላይ ስለቀረጥ እና ታክስ የመድህን ሽፋን ለመስጠቱ በውሉ ላይ ቢገለጽም ባይገለጽም፤ የመድን ሽፋን ሰጪው ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ቀረጥ እና ታክስ ለሚመለከተው ለመንግስት አካል፤ ቀረውን ለደንበኛው መክፈሉ በህግ የተጣለበትን ግዴታ መወጣቱን የሚያሳይ እና ይህ እስከተረጋገጠ ድረስ ለጉዳቱ ሀላፊነት ያለበት ወገን የተከፈለውን ቀረጥ እና ታክስ ለመተካት ከህግ የመነጨ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 129 እና 130/3 እንዲሁም ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎችን የቀረጥ እና ታክስ አከፋፈል ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 52/2003 አንቀጽ 5/1 እና አንቀጽ 14/1<br><br>የአደጋ መነሻ ክፍያን በሚመለከት የአደጋ መነሻ መሰላት ያለበት የመድን ሽፋን ከተሰጠው አጠቃላይ የተሽከርካሪ ዋጋ ላይ ነው ወይስ አደጋው በደረሰ ወቅት ባለው የተሽከርካሪ ዋጋ ላይ ነው በሚል ለሚነሳ ክርክር እልባት ለመስጠት የውሉን ይዘት መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥ ስለመሆኑ | 194796 | ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ ገ/ስላሴ በየነ | ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም | 290 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 52. | ተሽከርካሪ ከሚያደርሰው ግጭት የሚመነጭ ኃላፊነትን መድን ገቢው የመድን ሽፋን እንዲኖረው በማድረግ ኃላፊነት፤ በንብረት ላይ ለሚደርስ ኪሣራ የመድን ሰጭው የኃላፊነት መጠን ጣሪያው 100,000.00 ያልበለጠ እንደሆነ የተመለከተው በዋነኛነት የተጎጂውን ቁጥር ሳይሆን ጣሪያው የተወሰነው አደጋ በደረሠ ጊዜ እና የኃላፊነት ጣሪያው የደረሠን አደጋ የሚከተልና ጉዳት በንብረት ላይ በሚደርስ ጊዜ ጉዳት የደረሠባቸው የባለንብረቶች ቁጥር ግምት ውስጥ ሳይገባ በጠቅላላው አንድ ጊዜ ለተከሠተ አደጋ በንብረት ላይ ለሚደርስ ኪሣራ የተገለጸ ጣሪያ መሆኑና በአንድ ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ በተከሠተ አደጋ በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት፤ አደጋው በብዙ ባለንብረቶች ላይ ወይም በአንድ ሠው ንብረት ላይ ያደረሠው ኪሣራ ከ100ሺ. በላይ ከሆነ መድን ሰጭው የመሽፈን ኃላፊነት ያለበት እስከ ብር 100,000.00 ድረስ ብቻ ስለመሆኑ<br>የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1) (ሐ) | 203888 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና<br>እነ ቃልኪዳን ተስፋዬ<br>(2 ሰዎች) | የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ.ም | 296 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 53. | መድን ሰጪ ለኢንሹራንስ ገቢዉ /ለደንበኛዉ/ በከፈለዉ የገንዘብ መጠን ጉዳት እንዲደርስ ባደረጉት ሶስተኛ ወገኖች በከፈለዉ ገንዝብ መጠን ባሉት መብቶችና ክሶች በደንበኛዉ ምትክ ሆኖ መጠየቅ የሚችል በመሆኑ መድን ሰጪው ለደንበኛው በከፈለዉ የገንዘብ መጠን ባሉት መብቶች በደንበኛው እግር ተተክቶ ወይም በምትክነት ለጉዳቱ መንስኤ ነዉ የተባለዉን ተሽከርካሪ ከሶ ከመጠየቅ የሚያግደዉ ነገር ስለሌለ በደንበኛው ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት መንስኤ ነዉ የተባለዉን ተሽከርካሪ ባለቤት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ካሳ ድርሻዉን መክፈል አለበት በሚል ለሚቀርብ ክርክር ፍ/ቤት ይህን ሶስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባ ከማድረግ የሚከለክል ነገር የሌለ ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ አንቀጽ 683 /1/ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.43 /1/ | 124957 | አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ /አ.ማ/<br>እና<br>እነ አቶ መብራቱ ፈንታሁን<br>(2 ሰዎች) | ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም | 300 |
| **አፈፃፀም** | | | | | **304** |
| 54. | የእርቅ ሥምምነት በፍርድ ቤት ከጸደቀ እንደ ፍርድ ተቆጥሮ የሚፈጸም በመሆኑ በዚህ መሰረት የአፈጻጸም ክስን መሠረት በማድረግ ጉዳዩ በመደበኛ ክስ አግባብ ሳይሆን በአፈጻጸም ክርክር ሥርዓት ሊመራ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277(2) እና የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 | 199094 | አቶ መንግስቱ የሺጥላ<br>እና<br>ቢ.ኤንድ ዋይ ፖልትሪ ፋርም ኃ/የተ/የግል ማሕበር | ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም | 305 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ላቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ባለዕዳ የሆነውን ወገን ፍርድን ፈጽሞ እንዲቀርብ ወይም የማይፈጸምበትን ሕጋዊ ምክንያት በቃል እንዲያስረዳ ማዘዝ ሲገባ እንደ መደበኛ ክስ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጥበት የሚደረግ ስላለመሆኑ<br><br>በፍርድ ቤት የጸደቀ ለአፈጻጸም የቀረበ ዕርቅ እንደ ፍርድ የሚቆጠር እንጂ እንደ ውል ታይቶ በውል ሕግ መሰረት በፍ/ሕ/ቁ. 1678፣ 1731፣ 1757 እና 1771 ድንጋጌዎች መሰረት የሚመራ ስላለመሆኑ<br><br>በፍርድ ቤት በፀደቀ የእርቅ ስምምነት ንብረት ከማዛወር ጋር በተያያዘ ሊከፈል የሚገባ የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ በእርቅ ሥምምነቱ ማን ሊከፍል እንደሚገባ ያልተመለከተ ከሆነ የታክስ ክፍያው በገዢ (በመጨረሻ ተጠቃሚው) ሊከፍል የሚገባ ስለሆነ ሥመ-ሀብቱ ሲዛወር ገዢ ሊከፍል ይገባል በሚል የሚሰጥ ውሳኔ ፍርዱን ለማስፈጸምና ሥመ-ሀብቱን ለማዛወር መታለፍ ያለባቸውን ሂደቶች እልባት የሚሰጥ እንጂ ከፍርዱ/ከዕርቅ ሥምምነቱ ውጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ተደርጎ የማይወሰድና የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያው የሚመለከተው ለየትኛው ንብረት ነው፣ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ሊዛወር የሚችል ንብረት መኖር | | | | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አለመኖሩን በመለየት አፈጻጸሙም የሚቀጥል ስለመሆኑ<br>በተሰጠ ፍርድ ላይ ሥመ-ሀብት ዝውውር የሚደረገው ክፍያው ተጠናቆ ከመከፈል ጋር ያልተያያዘ ሆኖ የፍርድ ባለመብት ያልተፈጸመለት እንዲፈፀም የአፈጻጸም ክስ ባቀረበበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ዳኝነቱን ማስፈጽም ሲገባ አቤቱታ ሲቀርብ የሚታይ ነው በሚል የሚሰጥ ውሳኔ አፈጻጸም ችሎት ያለውን ተግባርና ኃላፊነት ያልተከተለ ስለመሆኑ<br>ግዴታ ለመፈጸም ዋስትና እንዲቀርብ በዕርቅ በሥምምነት ላይ ባልተመለከተበት ሁኔታ በዕርቅ ሥምነት መሠረት ካልተፈጸመ የአፈጻጸም ክስ በማቅረብና ገንዘብ በባለዕዳው ካልተከፈለ ንብረት በማስከበር መብትን ማስፈጸም እንጂ ግዴታን ለመወጣት ቅድሚያ ዋስ እንዲቀርብ መጠየቅ ፍርድንና የሥነ-ሥርዓት ሕግን የተከተለ ስላለመሆኑ | | | | |
| 55. | ፍርድ የተፈረደለት ሰዉ ማመልከቻ በማቅረብ የፍርድ አፈጻጸም ሲጠይቅ ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት እንዲፈጸም የተጠየቀዉን ፍርድ መሰረት በማድረግ ፍርዱን ለማስፈጸም በሚል የሚሰጠዉ ትእዛዝ፣ ፍርዱን ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑንና የተወሰነላቸዉ ሰዎች የተወሰነላቸዉን ነገር እንዲያገኙ ለማድረግ የሚችል ተስማሚ ትእዛዝ መሆኑን መረጋገጥ ያለበትና ራሱን ችሎ ክርክር ባልተደረገበት ጉዳይ ላይ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ስላለመሆኑ | 199836 | አቶ ፀጋዬ አለሙ<br>እና<br>አቶ ያሲን ኑሩ | ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ/ም | 311 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 378 እና 392/1 | | | | |
| 56. | በግራ ቀኝ መካከል ላለ ክርክር አልባት ለመስጠት የእርቅ ስምምነት ተፈጽሞ በፍርድ ቤት በማጽደቅ በተሰጠ ዉሳኔ ሶስተኛ ወገንን በተመለከተ የተደረገ ክርክር ካለመኖሩም በተጨማሪ የተሰጠ ዉሳኔ በሌለበት ፍርድ የመፈጸም ግዴታ የሚኖርበት የፍርድ ባለእዳዉ እንጂ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለዉ ሦስተኛ ወገን ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 378 እና 392/1 | 200228 | ወ/ሮ አገሪቱ አስናቀ<br>እና<br>ሼህ ኡመር መሀመድ | 03/02/2014ዓ.ም | 316 |
| 57. | በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ ፍርድ ቤቶች ሊያስፈጽሙ የሚገባው በተሰጠው ፍርድ መሰረትና በህግ አግባብ ከተዘረጋው ስርአት ውጪ የአፈጻጸም ችሎት የፍርዱን ይዘት በሚቀይር መልኩ ወይም ፍርድ ያልተሰጠበትን ነገር የሚያስፈጸም ስላለመሆኑ<br>የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች | 200919 | አቶ በቀለ ድሪብሳ<br>እና<br>አቶ የምክር በሪሁን | ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም | 321 |
| 58. | የአፈፃፀም ተከሳሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 439 መሰረት በዋናው ፍርድ ላይ እንዲከፍል የተወሰነበትን እዳና ቤቱም በጨረታ ለመሸጥ የወጣውን ወጪ መክፈል እንደሚፈልግና ገንዘቡን እንደሚያሲዝ በመግለፅ የጨረታው ሒደት እንዲቆምለት እና በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 430(1)፣(3) ድንጋጌን መሰረት አድርጎ በቤቱ ሽያጭ ጨረታ ላይ በአፈፃፀም ከሳሾች ተፈፅመዋል የሚላቸውን ቅን ልቦናን መሰረት ያላደረጉ እና ሕገ ወጥ | 206151 | አቶ አቡበከር ዓሊ<br>እና<br>እነ አቶ ተስፋዬ እንድሪስ<br>(2 ሰዎች) | ታህሳስ 25 ቀን 2014 ዓ.ም | 325 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ድርጊቶች በመዘርዘር ጨረታው እንዲሰረዝለት የሚያቀርባቸው አቤቱታዎች የተለያዩ ፍሬ ነገሮችን መሰረት ያደረጉና የሚያስከትሉት ውጤትም ለየቅል በመሆኑ ጉዳዩ በአግባቡ ሣይመርምር አቤቱታው በድጋሚ የቀረበ ነው፤ ጨረታው የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በሚል አቤቱታው ውድቅ የሚደረግ ስላለመሆኑ | | | | |
| 59. | አፈፃፀም ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነውን መሰረታዊ ፍርድ/ውሳኔ የሚከተል በመሆኑ ለአፈፃፀም መነሻ የሆነን ፍርድ በይግባኝ ያላሻረ ወይም እንዲሻሻል ያላደረገ ተከራካሪ ወገን በዋናው ጉዳይ ላይ ሊነሱ የሚገባቸውን የክርክር ነጥቦች በአፈፃፀም በተያዘው መዝገብ ላይ የክርክሩ መሰረት ሊያደርጋቸው የማይችልና የተሰጠው ፍርድ እንዲሻር የተደረገ መሆኑን በመጥቀስ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ከሌለ አፈፃፀሙን የሚመራው ፍርድ ቤት ፍርዱን የሚያስፈፅመው በስነ ስርዐት ህጉ በተዘረጋው ስርዐት መሰረት እንደ ፍርዱ ይዘትና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ በፍርዱ አግባብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.372፣378፣392(1) | 215049 | ወ/ሮ ማርታ ዴሬ<br>እና<br>አቶ ኢያሱ ፀጋዬ | ታህሳስ 25 ቀን 2014 ዓ.ም | 329 |
| 60. | ፍርድ ያረፈበት ንብረት በአፈፃፀም ደረጃ ላይ እያለ የተቃውሞ ማመልከቻ ክርክር በሚቀርብበት ጊዜ ተቃውሞ የቀረበው በሥረ-ነገሩ በተሠጠው ፍርድ ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሠረት ነው ወይሥ ለፍርድ አፈጻጸሙ በተከበረው ንብረት ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ነው የሚለውን | 174573 | እነ ወ/ሮ መዓዛ አባተ<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ጥሩአለም ረታ | ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም | 333 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመለየት ተቃውሞው የቀረበበትን ምክንያት የሚጠይቀውን የክርክር ሂደት መከተል እንጂ የአፈጻጸሙ ክርክር ዋናው ፍርድ በተሠጠበት መዝገብ ላይ የሚመራ ስላለመሆኑ | | (4 ሰዎች) | | |
| **የወንጀል ህግ** | | | | | **337** |
| 61. | ተደራራቢ ወንጀሎች በአጠቃላይ በአንድ ጊዜ (ሀሳባዊ መደራረብ) ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ጊዜያት የተፈፀሙ ድርጊቶችን (ቁሳዊ መደራረብ) የሚመለከቱ ሲሆኑ መደጋገም የቁሳዊ መደራረብ መለያ ባህሪ በመሆኑ ተመሳሳይ ድርጊቶች በተለያዩ ጊዜያት ቢፈፀሙ ወይም የተለያዩ ድርጊቶች በተለያዩ ጊዜ ተፈፅመው ቢገኙ ቁሳዊ መደራረብ አለ ለማለት የሚቻል ሲሆን፣ በአንድ ነጠላ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ወንጀሎች መፈፀማቸው የሀሳባዊ መደራረብ መለያ ባህሪ ስለመሆኑ<br>የወ/ህ/አ.60(ሀ)እና(ለ)<br>በተደራራቢ ክሶች ፍ/ቤት በወ/ሕ/አ/577/3/ ድንጋጌ መሰረት የአምባጓሮ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ያመነ ከሆነ ዐቃቤ ሕግ የወ/ሕ/አ/539/1/ሀ/ ተጠቅሶ በዛው በተፈጠረ አምባጓሮ ድርጊት ምክንያት ሰው የሞተ መሆኑን በመጥቀስ ተከሳሽ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ ድርጊቱ የተደራራቢ ወንጀልን መስፈርት የማያሟላ መሆኑን በመረዳት 2ኛው ክስ በ1ኛው ክስ ውስጥ የሚጠቃለል ነው ብሎ መወሰንና በአንድ | 203746 | ታሪኩ ኬዶ ኬሪ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ | መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም | 338 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወንጀል የመስራት ሃሣብ የተፈፀመን ድርጊት ወንጀል እንደተደራረበ አድርጐ ተከሳሽ በ2ኛው ክስ ጥፋተኛ የሚባል ስላለመሆኑ | | | | |
| 62. | በስራ ሂደት አስተባባሪ የስራ ሀላፊነት በስራ መዘርዝር አግባብ ስራን አለመስራት ምክንያት የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመ በወ/ህ/አ.420(2) መሰረት የስራ ሀላፊነትን ባለመወጣት የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ እንጂ ስራዎችን መከታተልና መቆጣጠር ሲገባ ይህንን ግዴታ ባለመወጣት በስር የማስተባብር የስራ ሀላፊነት በአግባቡ ባለመቆጣጠር የመንግስትን ስራ በማያመች አኳኋን በመመምራትና የደረሰን ጉዳት በመጥቀስ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 13(2) መሰረት በማድረግ ክስ የሚቀርብ ስላለመሆኑ | 211167 | የአ.ብ.ክ.መ. ጠቅላይ ዓ/ህግ<br>እና<br>አቶ አዲስ አለሙ | ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም | 346 |
| 63. | የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ይዘት ድንጋጌዎቹን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ ድርጊቱ የተፈጸመው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ነው የሚለውን የሕጉን መስፈርት ማሟላት በሚያስችል ሁኔታ በተከሳሽ ተፈጽሟል የተባለውን ግዙፋዊ ፍሬ ነገር /material fact/ በአግባቡ መመሥረት እና ማስረዳት በሚያስችል ሁኔታ መመሥረት የሚጠበቅበት ሲሆን ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከል ብይን ሊሰጥ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ | 202508 | አቶ ፈለቀ ታደሰ ዘነበ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ | ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም | 353 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወንጀል ሕግ አንቀጽ 411/1(ሐ) እና (2)፣ እንዲሁም አንቀጽ 407/1 (ሀ) እና (2) | | | | |
| 64. | ተከሳሽ ወንጀል የፈፀመው ከሌሎች ሰዎች ጋር መሆኑ ቢረጋገጥም ግብረ አበሮች የወንበዴ ቡድን አባል ስለመሆናቸው የቀረበ ክርክርና ማስረጃ በሌለበት በስምምነት ከሌሎች ሰዎች ጋር የተፈፀመ ወንጀል ሁሉ ከባድ ውንብድና ወንጀል ማቋቋሚያ የሆነውን መመዘኛ የማያሟላና ተከሳሽ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 670 የተከለከለውን የውንብድና ድርጊት ተላልፎ በፈፀመው የውንብድና ወንጀል እንጂ በከባድ ውንብድና ወንጀል ስላለመሆኑ<br><br>የወንጀል ሕግ አንቀፅ 670 እና 671(1)(ለ)ና (ሐ)<br><br>በተከሳሽና በግብረ አበሮቹ የተፈፀመ የማስፈራራትም ሆነ የሐይል ድርጊት በኑሮ ልማድ እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 671 ማቋቋሚያ መርሆዎች መሰረት ሲመዘን ከፍ ያለ ፍርሀትን ወይም ሞትን በሚያስከትል መሳሪያ ስለመፈፀሙ ካልተረጋገጠ የተፈፀመው የሐይል ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 670 ስር የሚሸፈን ስለመሆኑ | 208890 | ዮናታን ጎንቴ ዋልኮ<br><br>እና<br><br>የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ | ታሕሳስ 26 ቀን 2014 ዓ.ም | 361 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 65. | ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ላይ የሚወሰን ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዊች ውጪ በደፈናው ቅጣቱን መገደብ ጥፋተኛውን ያስተምራል ወይም ሌሎችንም ያስጠነቅቃል ብዬ አላመንኩበትም በሚል ቅጣት እንዳይገደብ ማድረግ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በሕጉ ላይ የተገለፀ ባለመሆኑ የተላለፈ ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች መኖራቸውን በውሳኔው ላይ ሳይገለጽ፣ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የቅጣት ገደብ ጥያቄን ውድቅ ማድረግ አግባብ ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች | 218957 | እነ ዳበረ ሆቴል ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ | መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም | 364 |
| **አሠሪ እና ሰራተኛ** | | | | | **369** |
| 66. | በመርህ ደረጃ ደመወዝ የሚከፈለዉ በስራ ገበታዉ ላይ ተገኝቶ ተገቢዉን አገልግሎት ለሰጠ የመንግስት ሠራተኛ በመሆኑ እና ስራ ሳይሰራ ደመወዝ የሚከፈለዉ በህግ የተመለከተ ድንጋጌ ሲኖር ብቻ እና ይህም ለመርሁ ልዩ ሁኔታ በመሆኑ በጠባቡ መተርጎም የሚገባዉ ሲሆን በወንጀል ተጠርጠሮ ጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ የነበረና በእስር ምክንያት በስራ ገበታዉ ላይ ሳልተገኘ ሠራተኛ መስሪያ ቤቱ ደመወዝ ለመክፈል የሚገደድ ስላለመሆኑ | 201933 | ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ገ/ፃዲቅ | ጥቅምት 04 ቀን 2014 ዓ.ም | 370 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 36 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች | | | | |
| 67. | ከሕግ-ዉጭ የሥራ ዉል ተቋርጦብኛል የሚል ሰራተኛ በአሠሪዉ የሥራ ዉሉ ከሕግ አግባብ ዉጭ በሆነ አኳኋን እንደተቋረጠበት ማስረዳት የሚጠበቅበትና ሰራተኛው የሚሰራውን ስራ አሰሪው መቀበሉን፣ ሥራን መስራት እንዳይቻል ወይም ሥራ መከልከልን በክርክር ማስረዳት አሰሪው ከሕግ አግባብ ዉጭ የሥራ ዉል አቋርጧል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ስላለመሆኑ<br>አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 12(1-3) እና 32 (1/መ እና 2) | 205420 | ጋራንባ ቦትሊንግ ኃላ/የተ/የግል ማኅበር<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ፋሲል | ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ/ም | 375 |
| 68. | ሰራተኛ በህመም ምክንያት ለአሰሪው ማሳወቅ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር አሰሪውን በማሳወቅ እና በመንግስት እውቅና ካለው የህክምና ተቋም የህክምና ፈቃድ በማቅረብ እረፍት የማግኘት መብት ያለው ሲሆን ሰራተኛ ለአሰሪው የሀኪም ፍቃድ ሳያቀርብ በህመም ምክንያት ፍቃድ ሲጠይቅ አሰሪው የስራው ሁኔታ አይፈቅድም በሚል ፍቃደኛ ሳይሆን ከቀረ ሰራተኛው በህግ አግባብ መብቱን ከሚያስከብር በስተቀር አሰሪው ፍቃድ እየከለከለው ሰራተኛው በራሱ ፍቃድ ከስራ የሚቀር ከሆነ ያለበቂ ምክንያት ከስራ እንደመቅረት የሚያስቆጥርና አሰሪው የስራ ውል ለማቋረጥ | 209939 | ኢስት ዌስት ኢትዮ ትራንስፖርት ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ የበጋ እሸት ወልደጻዲቅ | ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም | 379 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚያስችለው ምክንያት/ጥፋት ስለመሆኑ<br>አሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/1/ለ | | | | |
| 69. | አንድ ሰራተኛ በራሱ ጥፋት በድርጅት ንብረት ላይ ከተሰወነ የገንዘብ መጠን በላይ ጉዳት ማድረሱ በዲስፐሊን ኮሚቴ ከተረጋገጠ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከስራ የሚሰናበት ስለመሆኑ በህብረት ስምምነት ላይ ተደንግጎ በዚህ መሰረት ጥፋት የተፈፀመ ቢሆንም ሰራተኛው ከስራ ሳይሰናበት በገንዘብ መቀጮ ከደመወዙ በየወሩ 1/3ኛ እየተቀነሰ እንዲከፍል በሚል የሚሰጥ ውሳኔ ከደመወዝ እየተቀነሰ ሊከፍል የሚገባዉ በህብረት ስምምነቱ ላይ በተገለፀው የገንዘብ መጠን ድረስ ያለዉን ጉዳት እንጂ ከተቀመጠዉ ጣሪያ በላይ ሊሆን የማይገባና ከዚህ በላይ ለሆነዉ ገንዘብ ሊጠየቅ የሚገባዉ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክርና በማስረጃ ተጣርቶ ሲወሰን ብቻ ስለመሆኑ | 206283 | አቶ ጌታቸው ሀይሉ<br>እና<br>የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት | 01/02/2014 ዓ.ም | 383 |
| 70. | በሕብረት ሥምምነት መሰረት የሰራተኛ ተወካይ የሆነ ግለሰብ የማሕበሩ ተወካይ በመሆኑ በዚህ አመራርነት የመገናኛ ብዙኃንን በመቀጠም በማሕበሩ አባላት ላይ ደርሰዋል ያሉትን የመብት ጥሰቶችና ግድፈቶች በመግለጽ ሠራተኛዉ በአጠቃላይ ችግሮች አሉበት የሚል የተደረገ ቃለ-ምልልስ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ስምና ዝና የሚያጎድፍ፣ መልካም ግንኙነት የማያሻክርና ከባድ ጥፋት ተፈጽሟል የማያስብልና የአሠሪና | 212603 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ<br>እና<br>አቶ ተከስተ ካሴ | ሰኔ 02 ቀን 2014 ዓ.ም | 389 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ድንጋጌ ተጥሷል በሚል ለስራ ስንብት ምክንያት ሊሆን የሚችል ስላለመሆኑ | | | | |
| 71. | የሰራተኛ ማህበር አመራር በግሉ ሳይሆን በሠራተኛ ማሕበሩ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት በሚዲያ የሚሰጥ የቃለምልልስ ማብራሪያ በጥቅሉ አሰሪውን የማይወክሉና ምክትል ሊቀመንበርነት በሚመራው ማሕበርና በማሕበሩ አባላት ላይ ደርሰዋል ያሉትን የመብት ጥሰቶችና ግድፈቶች በመግለጻቸው የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ስምና ዝና የሚያጎድፍ፣ መልካም ግንኙነት የሚሻክር ከባድ ጥፋትና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ድንጋጌ መጣሱን የሚያስረዳ ሳይሆን በአሰሪው ዲሲፕሊን ኮሚቴው በሕብረት ሥምምነቱ በተመለከተው አግባብ የሠራተኛ ማሕበር ተወካዮች መሳተፍ ሲገባቸው ባልተገኙበት የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ አስፈላጊ ሂደቶችን ሳይከተል በተሰጠ ውሳኔ የሚደረግ የሥራ ስንብት ሕገ-ወጥ ስለመሆኑ<br>የአሰሪው ስንብት ህገ ወጥ ከሆነ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ በአሠሪው የተቋረጠበት ሠራተኛው ወደሥራ ሊመለስ የማይችለው ከሥራው ጠባይ ግንኙነት የተነሳ ወይም ከክርክር ሂደት ከተወሰደው ግንዛቤ በሥራ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ያስከትላል ተብሎ በፍርድ ቤቱ ሲታመን እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 43(3) ላይ የተደነገገው ከፍተኛ ችግር የሚለው የሕጉ አነጋገር | 213472 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ<br>እና<br>አቶ ማርቆስ የሱወርቅ | ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም | 395 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት ሠራተኛውን ወደሥራው እንዳይመለስ ማድረግ የማይችል እና የሚያስከትለው ጉዳት ጉልህ ሊሆን የሚገባና ሰራተኛው ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር የተያያዘ ጥፋት ካልፈፀመና ወደሥራ ቢመለስ ሥራው ላይ የሚያደርሰዉ ከፍተኛ ጉዳትን አሰሪው ካላሳየ በቀር ሰራተኛው ወደስራው የሚመለስ ስለመሆኑ<br>የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(1)(2) | | | | |
| **ከውል ውጪ ኃላፊነት** | | | | | **403** |
| 72. | ሊከፍል የማይገባዉን ገንዘብ የከፈለ ሰዉ ገንዘቡ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት ያለዉ ቢሆንም፤ ስህተት ሳይኖር፣ የሚያስከፍለዉም የህግ ወይም የዉል ግዴታ ምክንያት ያለመኖሩን እየተረዳዉ የተከፋይ ሰው ስም እና የባንክ ሂሳብ ቁጥር በመፃፍ ገንዘብ ገቢ ያደረገ ሰው፤ በራስ ፍቃድ ታስቦበት እንደተከፈለ ስለሚቆጠር ገንዘቡ እንዲመለስ መጠየቅ የሚቻል ስላለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 2165 | 175660 | ወ/ሮ ድንቃለም ግዛዉ<br>እና<br>ወ/ሮ መሠረት ዘርፉ | ህዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም | 404 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የወንጀል ሥነ ስርዓት ህግ** | | | | **407** |
| 73. | አንድን የቀረበ የወንጀል ክስ ለማረጋገጥ የሚያስችሉትን ማስረጃዎች የመለየት እና የመወሰን ስልጣኑ የዓቃቤ በመሆኑ ክሱን ያረጋግጡልኛል ያላቸውን ማስረጃዎች እስካቀረበ ድረስ የቀረቡት ማስረጃዎች በእርግጥም ክሱን በህግ በተቀመጠው የማስረዳት ደረጃ የሚያረጋግጡ መሆን ያለመሆናቸው ከሚመዘን በቀር አንድን የማስረጃ አይነት ለይቶ "ካላቀረብክ" ተብሎ የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 133፣ 134፣ 141 እና 149(1)<br><br>በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ ደግሞ በማስረጃነት እንዳይቀርብ በህግ በልዩ ሁኔታ ካልተከለከለ በቀር ስለ ድርጊቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊያረጋግጥ የሚችል ማናቸውም ማስረጃ ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 19(5) እና የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 137 | 208644<br>እና<br>208645 | እነ ሽከታ ተፈራ<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ | ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም | 408 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የቀረበን ክስን ለማረጋገጥ ቀርበው ከተሰሙ ምስክሮች ውስጥ የግል ተበዳዮች በማስረጃነት ስለመቆጠራቸው እና ቀርበው ያለመሰማታቸው ሌሎች ማስረጃዎች እንዳይመዘኑ የማያደርግ እና ተከሳሽም ቢሆን የቀረበውን ማስረጃ በተገቢው ስርዓት ከሚጠይቅ በቀር ተበዳዮች በማስረጃነት ያለመቅረባቸው ለተከሳሽ መስቀልኛ ጥያቄን ከመጠየቅ አንፃር የመብት መጣበብ የሚፈጥር ስላለመሆኑ | | | | |
| 74. | ተከሳሽ የዋስትና መብት ተጠብቆለት የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመ ብይን ለመስጠት በተያዘው ቀነ ቀጠሮ አለመቅረቡ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ መርምሮ አስቀድሞ የሰራውን ብይን እንዳያነብ፤አስቀድሞ የተሰራ ብይን ከሌለም በዕለቱ ወይም በቀጣይ ቀጠሮ ብይን እንዳይሰጥ የሚያግድው ስላለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 161 እና ተከታይ ድንጋጌዎች፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20/4 | 211518 | የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>አስቴር አዱሽ ደበሌ | ጥር 30 ቀን 2014 ዓ.ም | 414 |
| 75. | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ተፈጽሟል በሚል የቀረበን ክስ ጨምሮ በተከሳሽ ላይ በቀረበዉ የወንጀል ክስ የተጠቀሰዉ ድንጋጌ የሚያስቀጣዉ መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት ባነሰ ጽኑ እስራት ሆኖ የድንጋጌዉ | 231732 | በፍትሕ ሚኒስቴር የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ<br>እና | ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ/ም | 418 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጣሪያ ደግሞ ከአስራ ሁለት ዓመት በላይ ከሆነና ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ሊቀጣ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ከሆነ ተከሳሹ በሌለበት ክርክር የሚሰማ ስላለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) | | ዘነበች ቸሩ | | |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | **432** |
| 76. | የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ በሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው የክስሳ አቤቱታ ማቅረብ የሚችል ሲሆን ከዚህ በቀር የአስተዳደር ውሳኔው የተሰጠው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከተሰጠ ውሳኔ ጋር በተያያዘ በመሆኑ የክስሳ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም እንዲሁም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስልጣን አይኖረውም የሚባልበት የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለ አስተዳደር ክፍሎች አንቀጽ ሶስት ምዕራፍ አንድ ቁጥር 401(1) እና 402(1) እንዲሁም የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 48(2) እና 49(1) | 217557 | ዳሽን ባንክ አክስዮን ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ፣<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ | ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም | 433 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጁ መሰረት በሚከናወኑ የክለሳ ክርክሮች በአዋጁ የተመለከቱ ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች የሚፈፀሙ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክለሳ ስነ ስርዓት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸው ስለመሆኑ<br>አስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 58 | | | | |
| 77. | የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል አለ ከተባለ በአጓጓዡ እና በእቃ አስጫኙ መካከል ከዚህ ውል ጋር ተያይዞ በመካከላቸው ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች ተፈጻሚነት የሚኖረው ህግ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ እንደሚሆን በአዋጅ ተደንግጎ እያለ ይህን ልዩ ህግ በመተው ጉዳዩ ከውል ውጪ ሃላፊነትን በሚመለከቱ የፍትሀ ብሔር ህግ ድንጋጌዎች ሊታይ የሚችል ስላለመሆኑ<br>የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/99 አንቀጽ 3/1<br>በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መነሻ በአጓጓዡ እና በእቃ አስጫኙ መካከል በተጭበረበረ ሰነድ ወጪ የተደረገን እቃን በሚመለከት ክስ ከቀረበ፤ ክሱ የቀረበው በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መሰረት በመሆኑ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይርጋ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 548/99 አንቀጽ 40(1) እና (2) እንጂ የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 2143/1 ላይ | 204288 | የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ ድርጅት<br>እና<br>ማርቨልደን ካንፓኒ ሊሚትድ | ጥር 24 ቀን 2014 ዓ/ም | 439 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተመለከተው ድንጋጌ ስላለመሆኑ | | | | |
| 78. | ከይዞታ ላይ አላግባብ ተቀንሶ የተሰጠ ካርታ ይምከንልኝ የዳኝነት አቤቱታን ጨምሮ የአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ ከወጣ በኋላ በአስተዳዳር መስሪያ ቤቶች በዕለት ዕለት ስራቸዉ መሰረት የሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው አካል በአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት ያሉትን ሂደቶች ተከትሎ ሳይጨርስ (exhaustion of available remedies) በአስተዳደራዊ ተቋሞቹ የቅሬታ ማስተናገጃ ቅሬታ ሰሚ አካል ጋር ቀርቦ ተቋሙ የመጨረሻ ዉሳኔውን ባልሰጠበት ሂደት ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ለማየት ስልጣን ያላቸው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 9(2)፣ እና የአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ 1183/2013 አንቀጽ 2(3)፣ 43 እና 44 | 220042 | ወ/ሮ ሀና ሰለሞን ዘነበ<br>እና<br>ወ/ሮ አስናቀች ወልዴ ገ/ማሪያም፣<br>የካ/ክ/ከ/መ/ል/ማ/ጽ/ቤት | ህዳር 30 ቀን 2015 | 444 |
| 79. | የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ መሠረት ይህ አዋጅ ወጥቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በፊት በፈቃድም ሆነ ያለፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአዋጁ ለፈቃድ ማውጫ በተቀመጠው አንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ እንዲሁም በተለምዶ የጦር መሳሪያ የሚያዝባቸዉ አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ እና ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የጦር መሣሪያ የያዙ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 8(1) መሰረት እንዲያስመዘግቡ በተፈቀደዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ | 239711<br>እና<br>233141 | የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር<br>እና<br>አቶ ካሳሁን ግዛቸው፣<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር<br>እና | ሐምሌ 28 2015 ዓ.ም | 450 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የአዋጁን አንቀጽ 4፣ 22(2)፤ እንዲሁም 22(3) ድንጋጌዎች በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስላለመሆኑ<br><br>በአፍሪካ ቀንድና በታላላቅ ሀይቆች አካባቢ ሕገ ወጥ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በናይሮቢ ከተማ ሚያዝያ 13 ቀን 1996 የተፈረመውን የናይሮቢ ፕሮቶኮል ለማጽደቅ አዋጅ ቁጥር 429/1997፣የጦር መሣሪያዎችን፤ መለዋወጫዎቻቸውንና አካሎቻቸውን እንዲሁም ፈንጂዎችን በሕገ ወጥ ማምረትንና ማዘዋወርን ለመከካከል የወጣው ፕሮቶኮልም አዋጅ ቁጥር 735/2004፣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4፣ 22(2)፣ 23(2) ንዑስ አንቀጽ 3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2)፤ እንዲሁም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(2)<br><br>**(የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 205727 እና 205827 መዝገቦች ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ተለውጧል፡፡)** | | አቶ ኢሳያስ መኮንን | | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 80. | ከፍርድ ቤት ውጭ በሕግ የዳኝነት ነክ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚሰጡ ዉሳኔዎችንም ሆነ በሕግ በተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሰጧቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በዳኝነታዊ ክለሳ ሂደት በማለፍ በፍርድ ቤት መታየት የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 79(1)፣ 78(4) እና 37፣ እንዲሁም አንቀጽ 13(1)፣ የፍ/ሕ/ቁጥር 401/1 እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 12/2፣ 321 እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 54<br>አንድ አስተዳደራዊ ውሳኔ በሕግ በልዩ ሁኔታ በቀጥታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ እስካልተደነገገ ድረስ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ከሆነ በሰበር ሥርዓት ታይቶ ሊታረም የሚችለው በሰበር ከመታየቱ በፊት እንደ ነገሩ ሁኔታ በይግባኝ ወይም በዳኝነታዊ ክለሳ ሥነ ሥርዓት ከታይ በኋላ ስለመሆኑ<br>የዳኞች አስተዳደር ጉባኤው በሚሰጠው ውሳኔ ላይም ሆነ ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጋር በተያያዘ የሕጋዊነት ቅሬታ ያለው ዳኛ ወይም የጉባኤ ተሿሚ ቅሬታውን በምን አግባብ ለማን ማቅረብ እንዳለበት በፌዴራልም ሆነ በክልል ሕግጋተ መንግስታት በግልጽ የተዘረጋ ሥርዓት ካለመኖሩም በተጨማሪ በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ስለዚህ ጉዳይ በግልጽ | 214219 | የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣<br>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ አበባዉ ታደሰ | መጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ/ም | 462 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተዘረጋ ሥርዓት የሌለና የሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ በጉባኤው ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ከተመላከተ የመጨረሻ ዉሳኔ ነው የሚለው አገላለጽ ይግባኝ ሊባልበት የማይችል ዉሳኔ ነው የሚል ሀሳብ የያዘ ቢሆንም ድንጋጌው ከርዕሱ ጀምሮ ስለይግባኝ አቀራረብ የሚደነግግ አንጂ ዳኝነታዊ ክለሳ (judicial review) የሚመለከት ባለመሆኑ ዳኝነታዊ ክለሳን የሚከለክል ስላለመሆኑ<br>የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 209/2006<br><br>በክልልም ሆነ በፌዴራል ሕግጋተ መንግስታት አንቀጽ 9 ላይ ሕግጋተ መንግስታቱ እንደ ቅደም ተከተላቸው በክልሉና በአገሪቱ የበላይ ሕግጋት በመሆናቸው የጉባኤው ውሳኔ ይህንን መርህ ያከበረ(ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች ያከበረ) መሆን ካለመሆኑ አንጻር፣ የጉባኤው ውሳኔ እና ውሳኔ የተሰጠበት ሂደት በአንቀጽ 12 ስር ስለመንግስት አሠራር ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ከመሆን አለመሆን አኳያ፤ እንዲሁም የጉባኤው ውሳኔ በሕግጋተ መንግስታቱ አንቀጽ 37/1 ላይ የተደነገገውን የተጠሪን ፍትህ የማግኘት መብት ያከበረ ከመሆን አለመሆን ጋር እና በጥቅሉ የሕገ መንግስቱ ዓላማ የሆነውን የሕግ | | | | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የበላይነት የተረጋገጠበት መሆን ካለመሆኑ አንጻር ተገናዝቦ ጉባኤው የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሕጋዊነት በዳኝነታዊ ክለሳ እና በሰበር አቀራረብ ሥርዓት ሊመረመር የሚገባ ስለመሆኑ<br><br>የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አንድ ዳኛ በዲሲፕሊን ምክንያት ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ከሥራ እንዲሰናበት ከሚሰጠው ውሳኔ ወይም በሕመም ምክንያት ዳኛዉ ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አልቻለም ብሎ እንዲሰናበት ውሳኔ እንዲሰጥ ከተሰጠው ዳኝነት-ነክ ሥልጣኑ ዉጭ በሆነ አግባብ ሥልጣንና ተግባሩን መነሻ በማድረግ በሚያስተላልፋቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ ከግምት ሊገቡ የሚገባቸውን ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸውን የመሰማትና ሌሎች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት (due process of law) መሰል መመዘኛዎች ከግምት ሳይገቡ ተወስኖ ከሆነ መብቱ በተነካበት ሰው አቤቱታ መነሻ በዳኝነታዊ ክለሳ ታይቶ ጉድለቱ እንዲታረም ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ<br>በክልል ፍርድ ቤት አዋጅ በተደነገገው መሰረት የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ማየት የሚችለው በአንድ ጉዳይ ላይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር ከሆነ ይህ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን በአንድ | | | | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አስተዳደራዊ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተነሳ የሕጋዊነት ጥያቄ በዳኝነት አይቶ ከመከለስ የተለየ በመሆኑ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ወይም በሌላ አስተዳደራዊ አካል የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ የማየት ሥልጣን እንዳለው በአዋጅ ካልተደነገገ በክልሉ ሰበር ችሎት ከመመርመሩ በፊት በመጀመሪያ በዳኝነታዊ ክለሳ በክልላዊ ጉዳይ ከፍተኛ እና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔው ሊከለስ የሚገባ ስለመሆኑ<br><br>የፌዴራል ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 እና 80/2፣ የተሻሻለው የአማራ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 እና 67(2/ሀ) እንዲሁም የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17/1 | | | | |

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

**የሰ/መ/ቁ.** 205626

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች፡-** ኩማ አስመጪና ላኪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር- ጠበቃ ዶ/ር ነዋይ ዘርጌ - ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-**

1. አቶ ገበያው ይስማው
2. አቶ ደምስ ሁሴን
3. አቶ ዘሪሁን ባየ
4. አቶ ተመስገን አብይ
5. አቶ ይበልጣል ገበየሁ
6. አቶ አበበ ደሳለኝ
7. አቶ ገረመው ደቦጭ
8. አቶ እንዳ ደበበ
9. አቶ ታምራት ጎሹ
10. አቶ እንዳለ ተጎድ
11. አቶ ሀሰን ይማም
12. አቶ ተክለማርያም ግዛው
13. አቶ ሀብቴ ያለው
14. አቶ መዝገቡ ዋለ
15. አቶ ጌጡ አበባው
16. አቶ ደስታ ተመስገን
17. አቶ ክልሴ አለሙ
18. አቶ ምስክር ተክሌ
19. አቶ ሲሳይ አስፋው
20. አቶ እንድሪስ ሰይድ
21. አቶ መሀመድ አስፋው
22. አቶ ጀማል ያሲን
23. አቶ ተሾመ ኢዶላ

ሁሉም ቀርበዋል።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አሰሪና ሰራተኛን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በተለያየ የቅጥር ዘመን በሳምንት በቁርጥ ከፍተኛው ብር 3,500.00፣ መካከለኛው ብር 2,000.00 እና ዝቅተኛዉ 1,500.00 እየተከፈለን ስንሰራ የቆየን ቢሆንም አመልካች የትርፍ ሰዓት ስራ አልሰራችሁም በማለት በህገ-ወጥ መንገድ የስራ ውላችንን ስላቋረጠዉ ከህገ-ወጥ ስንብት ጋር የተያያዙት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ ካሳ፣ ለዘገየ ክፍያ ቅጣት እና የዓመት እረፍት ክፍያ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለን ይወሰንልን በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ።

አመልካች በበኩሉ በቀን 21/02/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሱ ተጠሪዎች የቀን ሰራተኞች ሆነው በሰሩት ልክ ይከፈላቸዋል እንጂ በመካከላችን የስራ ውል ግንኙነት የለም፤ ተጠሪዎች የስራ ግብር እና የጡረታ መዋጮ እንዳይቆረጥባቸው ከአመልካች ጋር የስራ ውል ግንኙነት የለንም ባሉበት ክስ ማቅረባቸው ተገቢ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የስራ ውል ግንኙነት የለኝም ቢልም ይህንን በማስረጃ አስደግፎ አላስረዳም፤ ተጠሪዎች በሰሩት ልክ የሚከፈላቸው መሆኑ ብቻውን የስራ ውል ግንኙነት የለም የሚያስብል ባለመሆኑ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የስራ ውል ግንኙነት አለ ተብሎ የህግ ግምት ተወስዷል፤ አመልካች ተጠሪዎች ወደ ስራ ቦታ እንዳይገቡ በጥበቃ ሰራተኞች አማካኝነት የተከለከሉ በመሆኑ አመልካች የስራ ውሉን በህገ-ወጥ መንገድ ያቋረጠ መሆኑን ያሳያል፤ ደመወዝን በሚመለከት ተጠሪዎች በሰሩት ልክ የሚከፈላቸው እና ወጥነት ያለው ስለመሆኑ ከቀረበው ማስረጃ በመረጋገጡ ለክፍያ ስሌት ዓላማ ብር 1,500.00 በመያዝ በዚሁ መጠን ተሰልቶ ለእያንዳንዳቸው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ ካሳ እና የዓመት እረፍት ክፍያ ይከፈላቸው በማለት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተሠርዟል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 29/07/2013 ዓ.ም በተፃፈ 11 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ ተጠሪዎች የመጫን እና የማውረድ ስራ የሚሰሩ መሆናቸውን አምነው፣ ይህንንም ስራ በተለያዩ ድርጅቶች እየተዘዋወሩ የሚሰሩ እና ቋሚ ደመወዝ የሌላቸው ሆነው እያለ፣ ከአመልካች ጋር ምንም

ዓይነት የስራ ውል ግንኙነት ያላቸው ስለመሆኑም በማስረጃ ሳይረጋገጥ፣ እንዲሁም እንዲቀርብልን የጠየቅነው ማስረጃ ሳይቀርብ እና ምስክር የማሰማት መብታችን ያለአግባብ ታልፎ ህጉን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎምና በመረዳት የስር ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የስራ ውል ግንኙነት እንዳላቸው ግምት ተወስዶ የጠየቁት ክፍያ በሙሉ እንዲከፈላቸው መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዎች ሰራተኞቼ አይደሉም ብሎ በካደበት እና ፍርድ ቤቶች በኮቪድ ምክንያት በከፊል ዝግ በነበሩበት ወቅት ምስክር አላቀረበም በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ማስረጃ ሳይሰማ እና እንዲቀርቡ የተጠየቁ የሰነድና የሰው ማስረጃዎች በማለፍ ተጠሪዎች በህግ ግምት ሰራተኞች ናቸው፣ የስራ ውላቸውም በህገ-ወጥ መንገድ ነው የተቋረጠው በማለት የወሰነበት አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት በቀን 19/09/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከስድስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ አገልግሎት ያለን ሲሆን አመልካችም የስራ ግንኙነት ያለን ስለመሆኑ በግልጽ አልካደም፤ ማስረጃን በሚመለከት አመልካች በተደጋጋሚ ምስክሮቹን አቅርቦ እንዲያሰማ ተለዋጭ ቀጠሮ ቢሰጠውም ባለማቅረቡ ምስክር የማሰማት መብቱ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች ያላግባብ ከስራ ያሰናበታቸዉ መሆኑን የጠቀሱ ቢሆንም አመልካች በሰጠዉ መልስ ተጠሪዎች በቀን ሰራተኝነት በሰሩት ልክ የሚከፈላቸዉ እንጂ በመካላቸዉ የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረበዉ ቅሬታም ተጠሪዎች ስሊጥ ወደ መጋዘን ሲገባ የማራገፍ ስራ የሚሰሩ ሲሆን የሚከፈላቸዉም ባራገፉት የኩንታል ልክ እየታሰበ መሆኑን በመጥቀስ ይከራከራል፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች ክርክር በአሠሪና ሠራተኛ ህጉ የሚሸፈን ዓይነት የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት በመካከላቸዉ የለም የሚል ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪዎችን ያሰናበተዉ በህጋዊ መንገድ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ነጥብ ከመታየቱ በፊት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት በጭብጥነት ተይዞ በግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ ተጣርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ትክክለኛ ጭብጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 4 ላይ በተመለከተዉ አግባብ በግራ ቀኝ መካከል የስራ ቅጥር ዉል አለ ወይስ የለም? የሚል ነዉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት በመካከላቸዉ አለ በሚል ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ ምክንያት ይህን በቅድሚያ የማስረዳት

ሽክሙ የአመልካች መሆኑንና አመልካች ምስክሮችን እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ ታዞ ለማቅረብ አለመቻሉን ነዉ፡፡

በመሠረቱ የከሳሽ ክስ በተከሳሽ የተካደ እንደሆነ በቅድሚያ ማስረጃዎችን አቅርቦ የማስረዳቱ ሸክም የሚወድቀዉ በመርህ ደረጃ በከሳሽ ላይ መሆኑ ከማስረጃ አቀራረብ እና የማስረዳት ሸክም ጋር በተያያዘ ተቀባይነት ካገኙት መርሆዎች ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡ ይህ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ከከሳሽ ወደ ተከሳሽ ሊዞር የሚችለዉ ተከሳሽ በከሳሽ የተመለከተዉን ፍሬ ነገር አምኖ ኃላፊነት የለብኝም የሚልበትን አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ካቀረበ ወይም ከሳሽ የህግ ወይም የፍሬ ነገር ግምት ተጠቃሚ ከሆነ ስለመሆኑም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 258(1) እና 259(1) የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ናቸዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ የሚሸፈን የስራ ቅጥር ዉል ከአመልካች ጋር እንዳላቸዉ የጠቀሱ ቢሆንም አመልካች ይህን ፍሬ ነገር በግልጽ ክዶ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎች ባወረዱት ኩንታል ልክ ታስቦ ገንዘብ የሚከፈላቸዉ ስለመሆኑ ገልፆ መከራከሩ በአሠሪና ሠራተኛ ህጉ የሚሸፈን በመካከላቸዉ የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት መኖሩን ማመኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጠቀሰዉ የአዋጁ አንቀጽ 4 ድንጋጌም የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት የለም የሚል ክርክር ያቀረበ ተከሳሽ ይህን አስቀድሞ የማስረዳት ሸክም እንዳለበት እና የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት እንዳለ ግምት ይወሰዳል የሚል ይዘት የለዉም፡፡ ይልቁንም አመልካች ክሱን በግልጽ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ከአመልካች ጋር በአዋጁ አንቀጽ 4 ላይ በተመለከተዉ አግባብ የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት ያላቸዉ ስለመሆኑ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክሙ የተጠሪዎች እንጂ የአመልካች ሊሆን የሚችልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት በመካከላቸዉ አለመኖሩን አመልካች በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም አለበት በሚል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተቀባይነት ያገኘዉን የማስረጃ አቀራረብ እና የማስረዳት ሸክም መርህን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸዉን ምስክሮች ያልሰማበት ምክንያት አመልካች ምስክሮችን እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ ጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቶት ማቅረብ ያለመቻሉን ሲሆን፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ወቅቱ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ፍርድ ቤቶች በከፊል ዝግ በሆኑበት ሐምሌ ወር 2012 መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት መልስ ምስክሮቹ እንዲያቀርቡ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የተሰጠዉ አመልካች በአቤቱታዉ በጠቀሰዉ ጊዜ ስለመሆኑ ክደዉ አልተከራከሩም፡፡ ሐምሌ ወር 2012 ዓ.ም በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ፍርድ ቤቶች በከፊል ዝግ ሆነዉ የቆዩ ስለመሆኑ ይህ ፍርድ ቤትም ግንዛቤ የሚወስድበት ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ምስክሮቹ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሲሰጥም ሆነ ባለመቅረባቸዉ ምክንያት የሚወስደዉ እርምጃም ይህንኑ እዉነታ ከግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን እንደሚገባ ይታመናል፡፡ ይሁንና ፍርድ ቤቱ ይህን ከግምት ዉስጥ ያላስገባ ከመሆኑም በላይ ምስክሮቹን የማሰማት መብት በትዕዛዝ ከታለፈ በኋላ አመልካች ይህንኑ

እዉነታ በመጥቀስ ምስክሮቹ እንዲሰሙለት ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉንም ከግራ ቀኝ ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በመካከላቸዉ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የሚሸፈን የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት የሌለ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች ግልጽ ክርክር አቅርቦ እያለ እና የስራ ቅጥር ውል በመካከላቸዉ መኖሩን በቅድሚያ የማስረዳት ሸክሙ የተጠሪዎች ሆኖ እያለ፣ ምስክሮች ቀርበዉ እንዲሰሙ ጊዜዉን ያላገናዘበ ትዕዛዝ በመስጠት የአመልካች ምስክሮችን ሳይሰማ በግራ ቀኛቸዉ የስራ ቅጥር ዉል እንዳለ ግምት በመዉሰድ ስንብቱም ህገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 89033 በቀን 05/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 267743 በቀን 20/07/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በግራ ቀኝ መካከል በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 የሚሸፈን የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት መኖር ያለመኖሩን አስመልክቶ በቅድሚያ የተጠሪዎችን ምስክር እና ማስረጃ በመስማት በመቀጠል እንደአግባብነቱ የአመልካችን የሰዉ ምስክር እና ማስረጃ በመስማት እና አስፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ ማስረጃዎችን በማስቀረብ እና በመመርመር አግባብ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

3. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 12/08/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 208350

ቀን፡- ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ኤፍ.ቲ.ሲ.(FTC) ጠቅላላ የግንባታ ሥራዎች ኃ/የተ/የግል ማሕበር

ተጠሪ፡- 1. አቶ ዳንኤል ዘውዴ

2. አቶ ሐቢብ ቃሲም

3. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

4. ኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ(አ/ማ)

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር መዝገቡ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተከሳሾች፤ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-60518 መኪና በሻሸመኔ ከተማ እየተሽከረከረ እያለ የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-34249 ኢት የሆነ ተሽከርካሪ የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ የራሱን የቀኝ አቅጣጫ መንገዱን ሙሉ በሙሉ በመልቀቅ በአመልካች ተሽከርካሪ አቅጣጫ ውስጥ በመግባት ገጭቶ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ ለጥገና፣ ለትራንስፖርት የወጣውን ወጪና የ15 ቀናት ገቢ በመቋረጡ የደረሰውን ጉዳት በድምሩ ብር 549,975.00 የተሽከርካሪው ባለቤት 1ኛ ተጠሪና ሹፌሩ 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሠጡት መልስ ጥፋት የፈጸመው የአመልካች ተሽከርካሪ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊ አይደለሁም በማለት የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተሽከርካሪያቸው በአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት ተገጭቶ ጉዳት የደረሰበት ስለሆነ የጥገና ወጪ ብር 367,070.38 እና 230 ቀናት የተቋረጠ ገቢ በቀን ብር 2,154.00 ሂሳብ ብር 495,461.40 በድምሩ ብር 867,181.78 አመልካች እንዲከፍላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ባቀረበው መልስ ጥፋቱ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ስለሆነ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብኝም፤ በማስረጃነት የቀረበው የፍርድ ውሳኔ በይግባኝ ተሽሯል። 3ኛ እና 4ኛ ጣልቃ ገቦች ኃላፊነቴን እንዲጋሩ በክርክሩ ጣልቃ ገብተው ይከራከሩ በማለት ጠይቋል። በአመልካች ጥያቄ መሠረት 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ የታዘዘ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ያቀረበው መልስ 1ኛ ተጠሪ አስገዳጅ የሆነው 3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ሳይኖረው ነው ያሽከረከረ። በአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት ጉዳት መድረሱ ስላልተረጋገጠ በኃላፊነት አልጠየቀም ያለ ሲሆን 4ኛ ተጠሪ በበኩሉ የኃላፊነት ወሰኑ እስከ ብር 100,000.00 ብቻ ነው መሆኑን በመጥቀስ ተከራክሯል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደቡብ ምድብ ችሎት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት የግጭት አደጋው ፕላን የተነሳው ከአራት ቀናት በኋላ ነው፣ፕላን የሰራው ባለሙያ በወንጀል ክርክሩ ቀርቦ ጥፋተኛው የአመልካች ሾፌር ስለመሆኑ አስረድቷል። የክልል ፖሊስ ኮሚሽን ባለሙያ ፕላኑ ግልጽነት የሌለው፣ ማን ጥፋት እንዳለበት የማያሳይ ስለመሆኑ ቀርቦ ያስረዳ ቢሆንም ፕላን ያነሳው ባለሙያ የሰጠው ምስክርነት፣ ዓይን እማኞች ከሰጡት ቃል ተመዝኖ ሊወሰን የሚገባው ነው። የአመልካች የሰው ምስክሮች የዓይን ምስክር አይደሉም፤ በሌላ በኩል በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች አደጋው ሲከሰት በቦታው የነበሩ ምስክሮች መሆናቸው ሲታይ ለአደጋው ጥፋት ያለበት የአመልካች ተሽከርካሪ ስለመሆኑ የቀረበው ማስረጃ ያስገንዝባል። ስለሆነም ጥፋቱ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ባለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም። 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መሠረት አመልካችና 4ኛ ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው። 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም። የጉዳት መጠኑ በቀረበውና ፍርድ ቤቱ ባጣራው ማስረጃ መሰረት የጥገና ወጪና የተቋረጠ ገቢ ብር 409,180.38 አመልካች ሊከፍል ይገባል። ከዚህ ወስጥ 4ኛ ተጠሪ ብር 100,000.00 ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል። አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራቀኙን አከራክሮ የአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት ስለመሆኑ ተመዝኖ የተወሰነ ነው፤ የአመልካች አንዱ ምስክር ሾፌሩ ሆኖ እያለ የዓይን ምስክር አልቀረበም መባሉ ተገቢ ባይሆንም አጠቃላይ የምዘና ውጤቱን የሚለውጥ አይደለም። የአመልካች ተሽከርካሪ ሾፌር የወንጀል ጥፋተኝነት በይግባኝ ተሽሮ የተመለሰ ቢሆንም የተመለሰለት ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ያለው ስለመሆኑ በተጠሪዎች የቀረበውን ክርክር ላይ አመልካች የማስተባበያ ክርክር አላቀረበም። ስለሆነም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም 3ኛ ተጠሪ እስከ ብር 100,000.00 ድረስ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አምኖ ተከራክሮ እያለ መታለፉ ተገቢ አይደለም። ጥፋቱ የ1ኛ ተጠሪ ነው። የወንጀል ጥፋተኝነት ፍርድ በሥር ሳይቀርብ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ መቀበሉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም። በአዋጅ ቁጥር 799/2005 መሠረት የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን የመድን ሽፋን ሳይኖረው ሲሽከረከር የነበረ በመሆኑና ይሕ ጥሰት በመሆኑ እንዲሁም

ከቀረጥ ነጻ የገባውን ተሽከርካሪ ለሌላ ዓላማ ሲያውል የደረሰ አደጋ ስለሆነ ጥፋቱ በፍ/ሕ/ቁ. 2035 መሠረት የ1ኛ ተጠሪ ነው። የጉዳት መጠን ገማች ፈቃድ የሌለው ሰው ነው። ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይሻርልን የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የ3ኛ ተጠሪ ኃላፊነት መታለፉና በሥር ያልቀረበ ማስረጃ በይግባኝ ቀርቦ መመዘኑ ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሠጡት መልስ የአመልካች ሾፌር በወንጀል ጥፋተኛ ተብሏል፤ በሥር ፍርድ ቤትም የወንጀል ጥፋተኝነት ማስረጃው ቀርቦ ነበር። ጥፋት ያለበት ስለመሆኑ ማስረጃ ቀርቦ ተመዝኖ የተረጋገጠ ነው። 3ኛ ወገን መድን ሽፋን ነበረው፣ በአደጋው ቀን ውሉ ሳይታደስ በመቅረቱ ነው፤ በኋላም ታድሷል። ውሉ ባለመታደሱ ሌላ አካል ከሚጠይቅ በስተቀር 3ኛ ወገን የመድን ሽፋን የሌለው ተሽከርካሪ ንብረት እንዲወድም ወይም እንዲገጭ የሚያደርግ አይደለም። ከኃላፊነትም ነጻ አያደርገውም። ከቀረጥ ነጻ ለገባበት ዓላማ የዋለ ነው። ገማች ባለሙያው ፈቃድ ያለው ሰው ነው። ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብለዋል። 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ጥፋቱ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ነው። የአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት አለ ከተባለ እስከ ብር 100,000.00 ድረስ ነው የኃላፊነት ወሰኔ ሲል ተከራክሯል። 4ኛ ተጠሪ እስከ ኃላፊነት ጣሪያ ድረስ እንድከፍል ተወስኖ ክፍያውን የፈጸምኩ በመሆኑ በዚህ ችሎት ተከራካሪ ልሆን አይገባም ብሏል። አመልካች ለ1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መልስ ላይ የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር፣ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-60518 መኪና በሻሸመኔ ከተማ እየተሽከረከረ እያለ የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-34249 ኢት የሆነ ተሽከርካሪ የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ የራሱን የቀኝ አቅጣጫ መንገዱን ሙሉ በሙሉ በመልቀቅ በአመልካች ተሽከርካሪ አቅጣጫ ውስጥ በመግባት ገጭቶ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ ብር 549,975.00 የተሽከርካሪው ባለቤት 1ኛ ተጠሪና ሾፌሩ 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ጥፋት የፈጸመው የአመልካች ተሽከርካሪ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊ አይደለሁም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተሽከርካሪያቸው በአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት ተገጭቶ ጉዳት የደረሰበት ስለሆነ ብር 867,181.78 አመልካች እንዲከፍላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል። ጉዳዩ ከውል ውጭ ኃላፊነት የጉዳት ካሣ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ሁለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ሲጋጩ አንዱ በአንዱ ላይ አደጋ እንዳደረሰ እንደሚቆጠር በፍ/ሕ/ቁ. 2084(1) ላይ የተመለከተ ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሦስት ላይ ደግሞ አደጋው የደረሰው በአንደኛው አሽከርካሪ ስህተት መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳቱን የመሸፈን ኃላፊነት ጥፋት የፈጸመው ተሽከርካሪ ስለመሆኑ ተመልክቷል።

በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር ነው፡፡ የማስረጃ ተገቢነት የማስረጃውና ተቀባይነትን ደንቦችን በመከተል የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመዘን ለአደጋው ጥፋት ያለበት የአመልካች ተሽከርካሪ ስለመሆኑ የቀረበው አረጋግጠዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች ተሽከርካሪ ሾፌር በወንጀል ጥፋተኛ ስለመባሉ ማስረጃ ተቀብሎ መመዘኑ በሥር ያልቀረበ ማስረጃ ባለመሆኑ ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም በማለት የተከራከረ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ባቀረበው መልስ በማስረጃነት የቀረበው የፍርድ ውሳኔ በይግባኝ ተሽሯል በማለት መግለጹ፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ፐላን የሰራው ባለሙያ በወንጀል ክርክሩ ቀርቦ ጥፋተኛው የአመልካች ሾፌር ስለመሆኑ አስረድቷል በማለት በውሳኔው መግለጹ የወንጀል ጥፋተኝነቱ በሥር ፍርድ ቤት የክርክርና የውሳኔ አካል የነበረ መሆኑን ከማሳየቱም ባለፈ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345 እንደተመለከተው ተጨማሪ ማስረጃ የመቀበልና የመመዘን ሥልጣን ያለው በመሆኑ የአመልካች ተሽከርካሪ ሾፌር ለክሱ ምክንያት በሆነው አደጋ ተከሶ ጥፋተኛ መባሉን በመመዘን የሠጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የክርክር አመራር ጉድለት የለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች የፈጸሙት የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ባቀረበው የሠበር አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 መሠረት የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን የመድን ሽፋን ሳይኖረው ሲሽከረከር የነበረ በመሆኑና ይሕ ጥሰት በመሆኑ እንዲሁም ከቀረጥ ነጻ የገባውን ተሽከርካሪ ለሌላ ዓላማ ሲያዉል የደረሰ አደጋ ስለሆነ ጥፋቱ በፍ/ሕ/ቁ. 2035 መሠረት የ1ኛ ተጠሪ ነው ሊባል ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን የፍ/ሕ/ቁ. 2035 ጥፋት ላይ የተመሰረተ ከውል ውጭ ኃላፊነትን የሚመለከት ድንጋጌ ይዘቱም ጉዳት ያደረሰው ድርጊት የተከሰተው ሕግን በመጣስ ወይም አድራጊው ሕግን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ ጉዳት ካደረሰ ለጉዳቱ ኃላፊ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ለጉዳቱ መንስኤ የሆነው ጥፋት የፈጸመው የአመልካች ተሽከርካሪ ስለመሆኑ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው 1ኛ ተጠሪ ሕግ ተላልፏል በሚል የጠቀሳቸው ድርጊቶች ከደረሰው ግጭት/ጉዳት ጋር ተያያዥነት የሌላቸው በመሆኑ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ነው በሚል የሥር ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ተቀብለነዋል፡፡

የካሣ መጠኑን በተመለከተ ካሣ በፍ/ሕ/ቁ. 2090(1) እንደተመለከተው ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ ወይም ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት መርህ የተቀመጠ ሲሆን የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት በማስረጃ በማረጋገጥ የጥገና ወጪና የተቋረጠ ገቢ ብር 409,180.38 አመልካች ሊከፍል ይገባል፣ ከዚህ ወስጥ 4ኛ ተጠሪ ብር 100,000.00 ሊከፍል ይገባል በማለት መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል 3ኛ ተጠሪ ወደክርክሩ ጣልቃ የገባው የአመልካች ተሽከርካሪ ለሚያደርሰው ጉዳት የ3ኛ ወገን የመድን ኃላፊነት ሽፋን ሰጥቷል በሚል የአመልካችን ኃላፊነት ለመጋራት ሲሆን 3ኛ ተጠሪ የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን ክዶ አይከራከርም፡፡ የ3ኛ ተጠሪ ክርክር የአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት ያልፈጸመ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ነው፡፡ የአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋትና ኃላፊነት ደግሞ በሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ ስለሆነም 3ኛ ተጠሪ በሰጠው የመድን ሽፋን መሠረት ብር 100,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል መወሰን ሲገባው መታለፉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 182518 የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 238330 ሰኔ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ብር 409,180.38 ለ1ኛ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል፣ ከዚህ ወስጥ 4ኛ ተጠሪ ብር 100,000.00 ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. 3ኛ ተጠሪ አመልካች ካለበት ኃላፊነት ውስጥ ብር 100,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- ❖ አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሥ/መ/ቁጥር 198035

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች፡- ቡለሌ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር- ጠበቃ ብሩክ አሰፋ - ቀረቡ**

**ተጠሪዎች፡- የሄጦሳ ወረዳ ገበሬዎች ሕብረት ሥራ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር - ነገረ ፈጅ ደዋኖ ሻሺ - ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከዉል የመነጨ ኪሳራ ነዉ የተባለዉን ለማስከፈል የተጠየቀ ዳኝነት መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ ግራ ቀኙ መካከል በቀን 04/12/2007ዓ/ም በተዋዋልነዉ ዉል አመልካች ከቻይና አገር ባለሙያዎችን፣ ኢንጂነሮችን እና ከዩሻን ግሩፕ ካምፓኒ ኤሌክትሪሻኖችን ወደ አገር ዉስጥ በማስመጣት ለተጠሪ የዱቄት ፋብሪካ ማሽን በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ ለመትከል ግዴታ የገባ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ለማሽን ተከላ 98,746.00 ዶላር፣ የአገልግሎት ክፍያ 400,000.00፣ ፋብሪካዉን ለመትከል ለሚያስፈልግ የሙያ ምክር አገልግሎት 83,892፣ ለነዳጅ 103,500.00 እንዲሁም ለአልጋና ለምግብ ብር 293,000.00 ለመክፈል ግዴታ ገብቷል፡፡ አመልካች በዉሉ መሰረት ባለሙያዎችን አስመጥቶ በቀን 06/12/2007ዓ/ም ሥራ ጀምሯል፡፡ ሆኖም የኤሌክትሪክ ፣የዉሃ፣ የመብራት፣ የብረት፣ የኦክስጂን፣ የኬብል ትሪዮ፣ የስሚንቶ፣ የጠጠርና የመሳሰሉት እጥረት በመኖሩ ተጠሪ ማቅረብ ባለመቻሉ በ3 ወር ዉስጥ ሥራዉን መጨረስ አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ የዱቄት ፋብሪካዉን ወደ ምግብ ማቀነባበሪያ ለማሳደግ በመፈለጉና ይህንንም ለአመልካች በጽሁፍ በማሳወቁ በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ ስራዉን ማጠናቀቅ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ለዱቄት ፋብሪካ የተሰራዉ ግንባታ አመቺ እና አስፈላጊ ስላልሆነ ለሚፈጠረዉ ችግር ተጠሪ ኃላፊነት እንደሚወስድ በጽሁፍ ለአመልካች አሳዉቋል፡፡ ለግንባታ የሚያስፈልገዉ ኢልቬተር ካናስ የሚባለዉ እቃ አገር ዉስጥ ተፈልጎ ባለመገኘቱ የመጡት ባለሙያዎች ተመልሰዉ ሊሄዱ ሲሉ ተጠሪ ባለሙያዎቹ ያለሥራ ለቆዩበት ጊዜ ክፍያ እፈጽማለሁ በማለት ግዴታ በመግባቱ ባለሙያዎቹ ቆይተዉ የግንባታ ሥራዉ ተጠናቆ በቀን 14/03/2010ዓ/ም ተመርቋል፡፡

ሥራዉ የተሰራዉ ከቻይና አገር በመጡ ባለሙያዎችና አስቀድሞ የራያ ዩኒዬን ፋብሪካ ለመትከል ወደ አገር ዉስጥ ገብተዉ የነበሩ ባለሙያዎችን በመጠቀም ሲሆን ከቻይና አገር ላስመጠናቸዉ ባለሙያዎች ደመወዝ፣ ምግብ እና የአልጋ ወጪ ለ323 ቀናት በተጠሪ ችግር ምክንያት አመልካች ተጨማሪ ወጪ

ስላወጣሁ ተጠሪ ሊተካልኝ ይገባል፡፡ በዉላችን መሰረት በዶላር የሚከፈሉ ክፍያዎችን በተመለከተ ለአንድ ቀን 1,097.14 ዶላር ስለሆነ የ323 ቀን ታስቦ 50,257.31 ዶላር ከፍሎ 304,081.11 ዶላር ስለሚቀር በዚያን ጊዜ ምንዛሬ 1 ዶላር ብር 27.63 ስለሆነ ብር 8,401,761.06 እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ፡፡ በዉሉ መሰረት ተጠሪ በብር ለመክፈል የተስማማዉን በተመለከተ የ323 ቀን በቀን በብር 9781 ታስቦ መክፈል ካለበት ከብር 3,159,377.00 ዉስጥ ብር 138,484.00 ብቻ ክፍሎ ቀሪዉን ብር 3,020,893.09 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ፡፡ ተጠሪ ከቻይና ለመጡ ባለሙያዎች ለምግብና ለሆቴል የወጣዉን ወጪ አልከፈለም፡፡ በዚህ ምክንያት አመልካች በቀን 700.00 ብር የሚያከራየዉ መኪና ለ69 ቀናት ተይዞ ስለቆየ ብር 48,300.00 ገቢ አጥቷል፡፡ በተጨማሪም ክፍያ ባለመፈጸሙ ለአየር መንገድ ቲኬት ቅጣት ብር 13,288.00 ወጪ አዉጥቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በአጠቃላይ ብር 11,435,942.06 ከወለድና ክሱ ካስከተለዉ ወጪዎች ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም ለክሱ በሰጠዉ መልስ ለማሽን መትከያ ለመክፈል የተስማማሁበትን 98,746.00 ዶላር በቀን 08/12/2008ዓ/ም በኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ በኩል ብር 2,197,606.49 አመልካች ወስዷል፡፡ የአገልግሎት ክፍያ ብር 400,000.00፣የምክር አገልግሎት ክፍያ 83,892.00፣ የትራንስፖርትና የነዳጅ ክፍያ ብር 103,500.00 በአጠቃላይ 880,392.00 አመልካች ወስዷል፡፡ የማሽን ተከላዉ ቀን ሲራዘም ክፍያ ይከፈላል የሚል ስምምነት የለንም፡፡ ስለሆነም ለ323 ቀናት ለማሽን ተከላ፣የምክርና የትራንስፖርት ክፍያ ተብሎ የተጠየቀዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የ69 ቀናት የመኪና ኪራይ ክፍያ በሚል የጠየቀዉም ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ያቀረበዉ በመሆኑ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ የአዉሮፕላን ቲኬት ቅጣት ብሎ የጠየቀዉም የማስረጃ ድጋፍ ያለዉ አይደለም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡ እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 275545 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 01/04/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ያቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ዉድቅ አድርጓል፡፡ ዋናዉን ክስ በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል የዱቄት ፋብሪካ ግንባታ ዉል በቀን 04/12/2007ዓ/ም መደረጉ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ በቁጥር HFCU/116/68/17/08 በቀን 08/06/2008ዓ/ም በጻፈዉ ደብዳቤ የዱቄት ፋብሪካ ግንባታዉ ወደ ምግብ ማቀነባበሪያ ፍብሪካ መቀየሩ በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡ በዉሉ ላይ ግንባታዉ በ90 ቀናት ዉስጥ እንዲጠናቀቅ ስምምነት ቢደረግም አመልካች ከቻይና አገር ሰራተኞችን አምጥቶ ሥራ ለመጀመር ዝግጁ ሆኖ የነበረ ቢሆንም ተጠሪ ለግንባታዉ የሚያስፈልጉትን ሥራዎች ማቅረብ ባለመቻሉ ምክንያት ሥራዉ በ90 ቀናት ዉስጥ አለመጠናቀቁን ተጠሪ ካለመካዱም በተጨማሪ የአመልካች ምስክሮችም ይህንኑ ስላስረዱ ጊዜዉ በመራዘሙ ምክንያት በአመልካች ላይ የደረሰዉን ኪሳራ ተጠሪ የመተካት ኃላፊነት አለበት፡፡ አመልካች ሥራዉን በቀን 16/09/2008ዓ/ም ጀምሮ እስከ ቀን 16/02/2009ዓ/ም ድረስ ከራያ ዋካና የገበሬዎች ሕብረት ሥራ ማኅበር ዩኒየን በመጡ ባለሙያዎች ለ198 ቀናት እንደሰራ ማስረጃዉ ስለሚያሳይ አመልካች በዉሉ ከተመለከተዉ ጊዜ ዉጭ ለ102 ቀናት እንደሰራ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ባለሙያዎቹ

ለ323 ቀናት መቆየታቸዉን በማስረጃ ስላላስረዳ ሊተካለት የሚገባዉ የ102 ቀናት ወጪ ነዉ፡፡ እንዲሁም አመልካች በእነዚህ ቀናት 8 ባለሙያዎች በተጠሪ ሥራ ላይ እንደነበሩ አላስረዳም፡፡ ይልቁንም ከራያ ዋከና ህብረት ሥራ ማኅበር ዩኒየን የተላከዉ ማስረጃ የሚያሳየዉ ከቻይና ከመጡ ባለሙያዎች ለተጠሪ የተላኩት 3 ሠራተኞች እንደሆኑ ስለተገለጸ ይህንን መነሻ በማድረግ ተጠሪ ለአመልካች የ2 ባለሙያዎች የ102 ቀናት ሊተካለት ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት በዉሉ የተመለከተዉ ለማሽን ተከላ የሚከፈል 98,146 ዶላር፣ የአገልግሎት ብር 400,000.00፣ የሙያ ምክር መክፈያ ብር 83,892.00፣ ለአገልግሎት ክፍያ ብር 293,000.00 ተጠሪ መክፈሉን አመልካች አልካደም፡፡ እነዚህ ክፍያዎች ከጊዜ መራዘም ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ክፍያዎች ስላልሆኑና አስቀድሞ የተከፈሉ ክፍያዎች ስለሆኑ አመልካች እነዚህን ክፍያዎች ወደ ቀናት ቀይሮ እንዲከፈለዉ በድጋሚ መጠየቁ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ እንዲሁም ባለሙያዎቹ ከሥራ ዉጭ ሆነዉ ለቆዩበት ጊዜ የትራንስፖርት በማለት የጠየቀዉንም በዉሉ መሰረት ከመቀበሉም በተጨማሪ ለትራንስፖርት ወጪ ማዉጣቱን በማስረጃ ስላላረጋገጠ ዉድቅ ተደርጓል፡፡ መኪናዬ ስለተያዘብኝ የብር 48,300.00 ገቢ አጥቻለሁ በማለት እንዲተካለት የጠየቀዉም ከክርክሩ ጋር ተያያዥነት ስለሌለዉ አልተቀበልንም፡፡ ከቻይና ለመጡ ባለሙያዎች የተቆረጠዉ ቲኬት ቀን በመቀየሩ ለቅጣት ከፈልኩኝ ያለዉን 13,288.00 በማስረጃ ባለማስረዳቱ አልተቀበልንም፡፡ የባለሙያዎቹ የቀን አበል 200 ዶላር እንደሆነ ከራያ ዋከና ገበሬዎች ሕብረት ሥራ ማኅበር ዩኒየን ከመጣዉ ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት የ2 ባለሙያዎችን በ102 ቀናት በማብዛት የአንድ የአሜሪካን ዶላር በወቅቱ በኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር የነበረዉ በብር 27.63 እንደሆነ በመግለጽ ተጠሪ ለአመልካች ብር 1,127,304.00 እንዲከፍል እንዲሁም ለሰራተኞቹ ለአልጋ ያወጣዉን ወጪ ብር 20,000.00 ተጨምሮ በድምሩ ብር 1,147,704.00 ከቀን 25/10/2010ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በተጨማሪም አመልካች ለጠበቃ አበል ላወጣዉ ወጪ የዚህን ገንዘብ 10% እና የዳኝነት ክፍያ በተወሰነለት ልክ በታሪፉ መሰረት ብር 3571.55 እንዲሁም ለሌሎች ወጪዎች ብር 5000.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ በመ/ቁጥር 190005 ላይ ቢያቀርብም ችሎቱ በቀን 12/12/2012 ዓ/ም በተሰጠ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞበታል፡፡ አመልካች በቀን 24/05/2013 ዓ/ም የተጻፈ የተሻሻለ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

በቀን 04/12/2007ዓ/ም በግራ ቀኙ መካከል በተደረገ ዉል መነሻ አመልካች የማሽን ተከላ የሚያከናዉኑ ባለሙያዎች በቦታዉ እንዲገኙ በማድረግ አመልካች የተከላ ሥራዉን በቀን 06/12/2007 ዓ/ም ስለጀመረ የ3 ወር ጊዜ ተጠናቆ ሥራዉ ሳይጠናቀቅ መዘግየት የጀመረዉ ከቀን 04/03/2008ዓ/ም ጀምሮ ነዉ፡፡ ተጠሪ በእሱ ችግር ሥራ መዘግየቱን አምኖ በቀን 05/03/2008ዓ/ም በቦርዱ ዉሳኔ ባለሙያዎቹ እንዲቆዩ በማስወሰን በቀን 23/05/2008ዓ/ም ለኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ በጻፈዉ እና

በቀን 08/06/2008ዓ/ም ለአመልካች ተወካይ በጻፈዉ ደብዳቤ አሳዉቋል፡፡ በተጠሪ ጥያቄ መሰረት አመልካች ባለሙያዎቹን አገር ዉስጥ እንዲቆዩ አድርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ሠራተኞቹ ለተጨማሪ 323 ቀናት ቆይተዋል፡፡ተጠሪ በቀን 25/11/2009ዓ/ም በቁጥር hfcu/558/17/09 በተጻፈዉ ደብዳቤ ባለሙያዎቹ ከአንድ አመት በላይ እንደቆዩ አምኖ ወደ ሀገራቸዉ እንዳይመለሱ ለአመልካች እስካሳወቀበት ቀን ድረስ ሀገር ዉስጥ ለተጨማሪ ጊዜ እንዲቆዩ መደረጉን በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የ323 ቀናት ክፍያ የመፈጸም ግዴታ አለበት ብሎ አለመወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም በክሱ በተጠየቀዉና በዉሉ ስምምነት በተደረገበት አግባብ ክፍያዎችን በዶላር እና በብር እንዲከፈል አለመወሰኑ ስህተት ስለሆነ የ323 ቀናት በዶላር የሚከፈለዉ ክፍያ 1097.17*323=354,385.91ዶላር ነዉ፤ እንዲሁም በብር የሚከፈለዉ ክፍያ ደግሞ ብር 3,020,983.009 ስለሆነ ተጠሪ የከፈለዉ ብር 1,147,704 ተቀንሶ ብር 10,288,238.00 ለአመልካች ሊከፈል ይገባል ተብሎ የሥር ፍርድ ቤት ከሕግ፣ ከዉልና ከማስረጃ ዉጭ በሆነ አኳኋን የ102 ቀን የ2 ሠራተኞች ወጪ በቀን ዉሎ አበል በ200 ዶላር ሂሳብ አስልቶ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡ እንዲሁም አመልካች በተወሰነለት ገንዘብ ልክ እንኳ በታሪፉ መሰረት የከፈለዉ የዳኝነት ክፍያ ብር 17,000.00 ገደማ ሆኖ እያለ በታሪፉ መሰረት ብር 3571.55 እንዲተካለት ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔም ከዳኝነት ታሪፍ ዉጭ ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች የተጠሪ ፋብሪካ ማሽን ተከላ አከናዉኖ ለመጨረስ በቀን 14/12/2007ዓ/ም ከተደረገዉ ስምምነት ዉጭ ሌላ ተጨማሪ ሥራ እንዲሰራ በቀን 08/06/2008ዓ/ም በተጠሪ ጥያቄ የቀረበ ስለመሆኑና ከተለያዩ የአቅርቦት ችግር የተነሳ ያለሥራ የባከነ ጊዜን ጨምሮ ሥራዉ በቀን 25/11/2009 ዓ/ም እንደተጠናቀቀ ጠቅሶ ከዉጭ ሀገር የመጡ ባለሙያዎች እንዲሰናበቱ የሚል ማስረጃ ቀርቦ ባለበት ባለሙያዎቹ ሥራ ላይ የቆዩት ለ102 ቀናት ነዉ በሚል የወሰነበትን አግባብ ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 30/07/2013ዓ/ም የተጻፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች የተወሰነለትን ገንዘብ አስፈጽሞ ከተቀበለ በኋላ ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የስር ፍርድ ቤት በሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት የፌዴራል ኢሚግሬሽን በላከዉ ምላሽ ስምንት ባለሙያዎች ከ2000ዓ/ም እስከ 2002ዓ/ም ወደ ሀገር ዉስጥ እንደገቡ የገለጸበት ማስረጃ አመልካች ዉል ከፈረመበት ቀን 04/12/2007ዓ/ም ጀምሮ ዉሉ እስከሚያበቃበት ቀን 30/02/2008ዓ/ም ድረስ በተጠሪ ስም ከቻይና አገር ወደ ሀገር ዉስጥ ሠራተኞችን እንዳላስገባ የሚያሳይ ነዉ፡፡ አመልካች ስምንት ባለሙያዎች በተጠሪ ስም ማስገባቱንና የቆዩበትን ጊዜ የማስረዳት ኃላፊነት የአመልካች ቢሆንም አላስረዳም፡፡ አመልካች የተጠሪን ስራ ለመስራት የተጠቀመባቸዉን ሠራተኞች አስቀድሞ ከራያ ዋከና ዩኒየን ጋር በገባዉ ዉል መሰረት የራያ ዋከና ዩኒየንን ሥራ ለመስራት ያስገባቸዉ ሰራተኞች ናቸዉ፡፡ እነዚህን 8

ሰራተኞች ወደ ተጠሪ በማምጣት በዉሉ በተቀመጠዉ ጊዜ ዉስጥ ሥራ ቢገልጽም የተጠሪን ሥራ የጀመረዉ በቀን 16/07/2008ዓ/ም እንደሆነ እና በተጠሪ ፋብሪካ የተሳተፉት 3 ባለሙያዎች እንደሆኑ ከራያ ዋከና ዩኒዬን ለፍርድ ቤቱ የተላከዉ የሰነድ ማስረጃ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ የራያ ዋከና ዩኒየን የላከዉ ማስረጃ እንደሚያሳየዉ ሠራተኞቹ ለ198 ቀናት ሥራ ላይ እንደቆዩና ከዚህ ላይ በዉሉ የተመለከተዉ 90 ቀን ሲቀነስ ለ102 ቀናት ዉሉ ጊዜ እንደተራዘመ ተረጋገጦ፣ ተጨማሪዉ ስራ ራሱን በቻለ ዉል የተፈጸመ መሆኑን፣ ውሉ ላይ አመልካች ስንት ባለሙያዎችን አገር ዉስጥ አስገብቶ ስራዉን እንደሚሰራ በግልጽ ስምምነት ባለመደረጉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1738/1 መሰረት ዉሉ መተርጎም ያለበት በዉሉ ተገዳጅ የሆነዉን ተጠሪን በሚጠቅም መልኩ እንደሆነ የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ሥራዉን 3 ባለሙያዎች እንደሰሩ ቢረጋገጥም ተጠሪ የሁለት ባለሙያዎችን በቀን የዉሎ አበል 200 ዶላር አስልቶ የ102 ቀናት እንዲከፈለዉ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም በቀን 28/08/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ዉሳኔ ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና አተገባበር አንጻር የያዘዉን ጭብጥ በመለወጥ ከክርክር አመራር አንጻር በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ ከተጠሪ ጋር በቀን 04/12/2007ዓ/ም በተዋዋልነዉ ዉል አመልካች ከቻይና አገር ባለሙያዎችን፣ ኢንጂነሮችን እና ከዩሻን ግሩፕ ካምፓኒ ኤሌክትሪሻኖችን ወደ አገር ዉስጥ በማስመጣት የተጠሪ የዱቄት ፋብሪካ ማሽን በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ ለመትከል ግዴታ ገብቷል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ለማሽን ተከላ 98,746.00 ዶላር፣ የአገልግሎት ክፍያ 400,000.00፣ ፋብሪካዉን ለመትከል ለሚያስፈልግ የሙያ ምክር አገልግሎት 83,892፣ ለነዳጅ 103,500.00 እንዲሁም ለአልጋና ለምግብ ብር 293,000.00 ለመክፈል ግዴታ ገብቷል፡፡ ተጠሪ ለማሽን ተከላዉ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማሟላት ባለመቻሉና የዱቄት ፋብሪካዉን ወደ ምግብ ማቀነባበሪያ በመቀየር ለዚህ የሚያስፈልገዉን ምክንያት በዉሉ በተመለከተዉ 3 ወር ጊዜ ዉስጥ የማሽን ተከላዉ ባለማለቁና ለተጨማሪ 323 ቀናት ጊዜዉ በመራዘሙ ምክንያት በዶላር የሚከፈለዉ ክፍያ 1097.17*323=354,385.91ዶላር እና በብር የሚከፈለዉ ክፍያ ደግሞ ብር 3,020,983.009 እንዲሁም የታጣ ገቢ ብር 48,300.00 እና ለአየር መንገድ ቲኬት ቅጣት የተከፈለ ብር 13,288.00 ጨምሮ ተጠሪ በአጠቃላይ ብር 11,435,942.06 እንዲከፍለዉ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ ደግሞ የማሽን ተከላዉ ቀን ሲራዘም ክፍያ ይከፈላል የሚል ስምምነት የለንም፡፡ በዉሉ በዶላርና በብር ለመክፈል ስምምነት የተደረገበትን ክፍያዎች በሙሉ ለአመልካች ተከፍሎታል፡፡ ስለሆነም ለ323 ቀናት ለማሽን ተከላ፣ የምክርና የትራንስፖርት ክፍያ ተብሎ የተጠየቀዉ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክራል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪ ምክንያት በዉሉ የተመለከተዉ ጊዜ ለ102 ቀናት በመራዘሙ የአመልካች 2 ሰራተኞች ለ102 ቀናት ያለሥራ

በመቀመጣቸዉ በአመልካች ላይ ለደረሰዉ ኪሳራ ለአንድ ሠራተኛ በቀን 200 ዶላር አበል ሂሳብ በማስላት ተጠሪ ለአመልካች ብር 1,127,304.00 እንዲከፍል እንዲሁም አመልካች ለሰራተኞቹ ለአል,ጋ ያወጣዉን ወጪ ብር 20,000.00 ተጨምሮ በድምሩ ብር 1,147,704.00 እንዲከፍል መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182/2 ስር እንደተመለከተዉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ ለመስጠት እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ የሚሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ በክሱ ላይ እና በመከላከያ መልስ ላይ ተዘርዝሮ በተገለጸ ፍሬ ነገር እና በተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 91/1 ስር እንደተደነገገዉ በአንድ ለፍርድ ቤት በቀረበ አቤቱታ(ክስ ወይም መከላከያ መልስ) ዉስጥ በተመለከተዉ ስህተት ወይም በግልጽ ካለመቅረብ የተነሳ ተከራካሪ ወገኖች ተገቢዉን ክርክር የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብቶች በጽኑ የሚነኩ መሆናቸዉን የተገነዘበ እንደሆነ የአቤቱታዉ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ ያብራራል ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት ይረዳል የሚያስብል ሁኔታ በገጠመ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች ጠያቂነት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አቤቱታዉ እንዲሻሻል ማድረግ ይችላል፡፡ በዚህ አግባብ ክስ ማሻሻል አስፈላጊ ከሚሆንባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ የክሱ ምክንያት ጠቃሚ አካል የሆኑ ፍሬ ነገር ሳይጠቀስ የቀረ እንደሆነና ይህንኑ ፍሬ ነገር ማካተት አስፈላጊ ሲሆን ነዉ፡፡ ለክሱ መሰረታዊ የሆነዉ ነጥብ ግልጽ ባልሆነበት የክስ አቤቱታ እንዲሻሻል ሳይደረግ ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጠብ ከመሆኑም በተጨማሪ ለክርክሩ ትክክለኛ እልባት ወይም ትክክለኛ ፍትህ እንዳይሰጥ ስለሚያደርግ እንዲሁም ይህ ጉድለት እንዲስተካከል በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች በሚደረግ ምልልስ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ክርክሮች በአነስተኛ ሀብት(የሰዉም ሆነ የገንዘብ) እንዲሁም በምክንያታዊ አጭር ጊዜ ጉዳዮች እልባት እንዲያገኙ ያለመዉ ዓላማ ከግብ ሳይደርስ እንዲቀር ስለሚያደርግ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 91/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በተከራካሪ ወገኖች ጠያቂነት ወይም በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት ክሱ እንዲሻሻል መደረግ ይኖርበታል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ እንደተገለጸዉ በዉሉ ላይ ተጠሪ ለአመልካች በዶላርና በብር ለመክፈል የተስማማቸዉን ክፍያዎች በሙሉ ተጠሪ አስቀድሞ ለአመልካች እንደከፈለ አመልካች ካለመካዱም በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት በማስረጃም ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ እነዚህ ክፍያዎች ለማሽን ተከላ፣ ለአገልግሎት ክፍያ ፣ ፋብሪካዉን ለመትከል ለሚያስፈልግ የሙያ ምክር አገልግሎት ፣ ለነዳጅ ፣ ለአል,ጋና ለምግብ በዶላርና በብር ለመክፈል ሥምምነት የተደረገባቸዉ ክፍያዎች እንደሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ተረድተናል፡፡ በዚህ አግባብ ስምምነት የተደረገዉ የዱቄት ፋብሪካ ተከላዉ በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ እንደሚጠናቀቅ ታሳቢ በማድረግ ጭምር ቢሆንም የክፍያዎቹ አይነት ሲታይ ለነዳጅ፣ ለአል,ጋና ለምግብ ለመክፈል ስምምነት ከተደረገበት ክፍያ ዉጭ ያሉት ክፍያዎች በቀጥታ ከጊዜ መራዘም ጋር ግንኙነት ያላቸዉ እንዳልሆኑ ተገንዝበናል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ

በአመልካች በኩል በተፈጠረ ችግር(ምክንያት) በዉሉ ከተመለከተዉ 3 ወር ዉጭ ለ323 ቀናት ጊዜዉ በመራዘሙ ለተጠሪ ሥራ ከቻይና አገር ያመጠኟቸዉ ባለሙያዎች ያለሥራ በመቀመጣቸዉ ምክንያት ኪሳራ ደረሰብኝ ወይም ለወጪ ተዳረኩኝ በሚል ምክንያት በመሆኑ የክስ አቤቱታዉን በግልጽ አብራርቶ ማቅረብ የሚጠበቅበት በዉሉ በዶላርና በብር ለመክፈል ስምምነት ከተደረገበት ተግባራት እና አገልግሎቶች አንጻር ሳይሆን ለምን ያህል ሠራተኞች፣ ለምን ጉዳይ ምን ያህል ወጪ እንዳወጣ በማሳየት ሊሆን ይገባል፡፡ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት አመልካች በዉሉ በዶላርና በብር ለመክፈል ስምምነት ከተደረገበት ክፍያዎች አንጻር ወደ ቀን ቀይሮ በጠየቀዉ መሰረት ሊከፈለዉ አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍ ባይሆንም ዉሳኔ የሰጠዉ አመልካች በክሱ ላይ ለተጠሪ ሥራ ከቻይና አገር ያስመጣቸዉና ከሌላ ድርጅት ጋር በገባዉ የዉል ስምምነት መነሻ አስቀድሞ ያስገባቸዉ ሠራተኞች እና በዉሉ ከተመለከተዉ የ3 ወር ጊዜ ዉጭ ለሆነዉ ጊዜ ለተጠሪ ሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ምን ያህል እንደሆኑና ለእነዚሁ ሠራተኞች ያወጣዉ ወጪ አይነትና መጠን በግልጽ የሚያሳይ ክስ ባልቀረበበትና ተጠሪም በዚህ አግባብ በግልጽ የተዘጋጀ ክስ ደርሶት የራሱን መከላከያ መልስ አቅርቦ ባልተከራከረበት ከተጠየቀዉ አግባብ ዉጭ በሆነ አኳኋን ዉሳኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ የተራዘመዉ ጊዜ 102 ቀናት ነዉ ወደሚል እና የሠራተኞቹን ቁጥር 2 ናቸዉ የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰበት አግባብም ግልጽ ካለመሆኑም በተጨማሪ በግራ ቀኙ ክርክር ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ በሚረዳ አኳኋን የክስ አቤቱታዉ እንዲሻሻል በማድረግ ክርክሩ መምራት ሲገባዉ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት ባልተከተለ መንገድ እና በክሱ ተዘርዝሮ ከተመለከተዉ ዉጭ በሆነ አኳኋን ክርክሩን በመምራት ዉሳኔ መስጠቱ ስለተረጋገጠ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የክርክር አመራር ጉድለት ተፈጽሟል ብለናል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የይግባኝ ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ የሚታየዉን ስህተት ሳያርም ይግባኙን በትእዛዝ መሰረዙ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 275545 ላይ በቀን 01/04/2012ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 190005 ላይ በቀን 12/12/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ አመልካች የክስ አቤቱታዉን ከላይ በፍርድ ክፍል ላይ በተገለጸዉ መሰረት በዉሉ ከተመለከተዉ 3 ወር ዉጭ በተጠሪ ምክንያት የተራዘመዉን ጊዜ ብዛት፣ ለተጠሪ ሥራ ከቻይና አገር መጥተዉ በተራዘመዉ ጊዜ ሥራ ፈተዉ የተቀመጡ ሠራተኞች(ባለሙያዎች) ብዛት፣ ለሠራተኞቹ ያወጣቸዉን ወጪዎች አይነትና የወጪዉን መጠን በግልጽ ዘርዝሮ የክስ አቤቱታዉን አሻሽሎ እንዲያቀርብና በተሻሻለዉ ክስ ላይ ተጠሪ መከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ አድርጎ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ ክርክሩን በመምራት

ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

**<u>ት እ ዛ ዝ</u>**

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 211408

ቀን፡- ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ አማረ አምባዬ፡- ጠበቃ ትዕግስት ተስፋዬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡-1. ወ/ሮ ነጃት ሰይድ፡- አልቀረቡም

2. በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 438 የሆነ ቤትና ቦታ ያለኝ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ አጎራባች ይዞታ ያላቸው በመሆኑ ተገቢውን ርቀት ጠብቀው ሕንጻቸውን መገንባት ሲገባቸው ከግድግዳዬ ጋር አጣብቀው የሠሩ በመሆኑ ቤቱ በመፍረሱ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል የደረሰውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እተካለሁ በማለት ሥምምነት ያደረጉ ቢሆንም የበለጠ ጉዳት አድርሰው ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት ደርሷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ሰርተው እንዲያስረክቡ ብጠይቃቸውም ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ለደረሰው ጉደት ብር 726,417.91 እና የማከራየው ቤት ገቢ ስለተቋረጠ በየወሩ ብር 1,100.00 ካሣው ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንዲከፍሉ፣ ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ የገነቡትን ግንባታ አፍርሶ በሕግ የተቀመጠውን የቦታ ርቀት ያስጠብቅ ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ጉዳዩ በሥምምነት ያለቀ ነው፤ ከአመልካች ጋር በሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የውል ሥምምነት ደረሰ የተባለው ጉዳት በሽማግሌዎች ተገምቶ ክፍያ እንዲከፈልና ግንባታው እንዲቀጥል ውል አድርገናል፡፡ ክሱ ውደቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የቃል ክርክር ሲደረግም አመልካች ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ውል ዕቃን እንጂ ቤትን የሚመለከት አይደለም፤ ውሉም ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ሌላ ውል ተተክቷል፡፡ በውል ከተስማማነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት አድርሷል ብለዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው ሥምምነት ስለቤቱ ጉዳትም ሥምምነት አድርገዋል፡፡ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በእርቅ ወይም በሥምምነት የጨረሱትን ነገር ላይ ክስ መቅረቡ ተገቢነት የለውም፤ በሥምምነቱ መሠረት ካልተፈጸመ በሥምምነቱ መሠረት እንዲፈጸም ክስ ማቅረብ እንጂ ከዚህ ውጭ አዲስ ክስ መቅረቡ ተገቢነት የለውም በማለት የአመልችን ክስ ውደቅ አድርጓል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ላይ የተጠየቀው ዳኝነት የማየት ሥልጣን ፍርድ ቤቱ የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም እርቁ ወይም ውሉ ተፈጸመ የሚባለው ክፍያ ሲፈጸም ወይም ንብረቱን ሲያድሱ ነው፡፡ ጉዳቱ አሁንም እየቀጠለ ባለበትና ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ውል ዕቃን ብቻ የሚመለከት ሆኖ እያለ ክሱ ውድቅ መደረጉ ተገቢነት የለውም፡፡ ፍርድ ቤቱ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገውን ሥምምነት መሠረት አድርጎ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ተጨማሪ ጉዳት በማድረሳቸውና ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ጉዳት ስለደረሰ አጠቃልዬ ካሳ መጠየቄ ተገቢ ነው፡፡ በሥምምነቱ ባልተሸፈነው ጉዳት ላይ ውሳኔ ሳይሰጥበት ወይም ክስ የማቅረብ መብቴ አለመጠበቁ ስህተት ያለበት ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ሳይሰማ ሥልጣን የለኝም ማለቱ ሕጋዊ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ በግራቀኙ መካከል ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገውን ሥምምነት ውሳኔ ሳይሰጥበት ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ሥምምነት መሠረት በማድረግ ብቻ ክሱን በብይን ውድቅ ያደረግበትን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘትም ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው ውል አልተተካም፡፡ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ ሥምምነት ካለም ሥምምነቱን መሠረት በማድረግ መብታቸውን ይጠይቃሉ እንጂ በራሳቸው በባለሙያ አስገምተው ካሣ መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም፡፡ ስለሆነም የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ 1ኛ ተጠሪ የግንባታ ፈቃድ የወሰዱት ከ2ኛ ተጠሪ ጽ/ቤት ሳይሆን ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የግንባታና ፈቃድ ቁጥጥር ጽ/ቤት በመሆኑና የአጎራባች ሥምምነት የሚፈጸመው በተጠሪ ጽ/ቤቱ በኩል ባለመሆኑ ክሱ አይመለከተኝም ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 438 የሆነ ቤትና ቦታ ያለኝ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ አጎራባች ይዞታ ያላቸው በመሆኑ ተገቢውን ርቅት ጠብቀው ሕንጻቸውን መገንባት ሲገባቸው ከግድግዳዬ ጋር አጣብቀው የሠሩ በመሆኑ

ቤቱ በመፍረሱ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል የደረሰውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እተካለሁ በማለት ሥምምነት ያደረጉ ቢሆንም ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት ስለደረሰ ብር 726,417.91 እና የማከራየው ቤት ገቢ ስለተቋረጠ በየወሩ ብር 1,100.00 ካሣው ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንዲከፍሉ፣ ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ የገነቡትን ግንባታ አፍርሶ በሕግ የተቀመጠውን የቦታ ርቀት ያስጠብቅ ተብሎ ይሰወንልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች ቤት ላይ ጉዳት ሲደርስ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ከውል ውጭ ግንኙነት የነበራቸው ሲሆን ጉዳቱ መድረስ ከጀመረ በኂላ ግንኙነታቸው ውል መሠረት በማድረግ ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው ሥምምነት ስለቤቱ ጉዳት ላይ መዋዋላቸውን የሥር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካችም በክስ ማመልከቻው ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም ሥምምነት መደረጉንና ተጠሪ በውሉ መሠረት ካለመፈጸማቸውም በላይ ተጨማሪ ጉዳት ማድረሳቸውን ገልጸዋል፡፡ ይሕም ለክሱ መሠረት የሆነው አለመግባባት ግራቀኙ ካደረጉት ውልና ካለባቸው ግዴታ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የክሱ መሠረት የውል ግንኙነት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በአመልካች የክስ አቤቱታ ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል የደረሰውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እተካለሁ በማለት 1ኛ ተጠሪ ሥምምነት ያደረጉ ቢሆንም የበለጠ ጉዳት አድርሰው ውሉ ከሚሸፍነው በላይ ተጨማሪ ጉዳት ደርሷል፣ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ሰርተው እንዲያስረክቡ ብጠይቃቸውም ፈቃደኛ አይደሉም በማለት ያካተቱት ፍሬ ነገር ክሱ በአንድ በኩል የውል አለመፈጸምንም መሠረት ያደረገ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል ውሉ ከሚሸፍነው ጉዳት በላይ ስለደረሰ ጉዳቱን አጠቃልዬ ማቅረቤ ተገቢ ነው የሚለው የአመልካች መከራከሪያ ከውል ውጭ ግንኙነትንም መሠረት ያደረገ የክስ አቀራረብ የተከተሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የውል ሥምምነት ካደረጉ በኂላ 1ኛ ተጠሪ የውል ሥምምነቱን በመፈጸም ሂደት ተጨማሪ ጉዳት ካደረሱ የውል ጉዳት ኪሣራ ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይ እንጂ ግንኙነቱን ከውል ውጭ የሚያደርገው አይደለም፡፡ ይሕም ክስ አቀራረቡ የክሱን መሠረት ግልጽ ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በክስ በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሱት ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ ሥምምነት ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ በመከላከያ ክርክራቸው ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ ሥምምነት በመጥቀሳቸው የሥር ፍርድ ቤት በክሱ የተጠቀሰውን የግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም ሥምምነት በዝምታ በማለፍ ውሳኔውን ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው ሥምምነት ላይ መስርቷል፡፡ በክሱ የተጠቀሰውን የውል ሥምምነት መታለፉ የክርክር አመራር ግድፈት ያለበት መሆኑ እንደጠበቀ ሆኖ በሁለቱ የውል ሥምምነቶች መካከል ያለው ተዛምዶ ምን እንደሆነ በክሱ ተብራርቶ አለመቅረቡ የክርክር አመራር ግድፈት ለመፈጸሙ እንደመነሻ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ በፍብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 91/1/

እንደተመለከተው ክርክርን ለመለወጥ፣ አቤቱታውን ለማብራራት ሆነ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ አቤቱታን ማሻሻል ይቻላል፡፡ ክስ የሚሻሻለው የቀረበውን አቤቱታ ለማብራራት ወይም ለፍትሕ መሰናክል የሆነ ነገር ካለ አስተካክሎ በመምራት ውጤት ጋር እንዲደርስ ለማስቻል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚቸገር ከሆነ እንደሁኔታው ክስ ወይም መልስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማድረግ የክርክር ሂደቱንም ሆነ የውጤቱን ፍትሐዊነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም አመልካች በክስ አቤቱታቸው የገለጹትን በማሻሻል ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያላቸውን ትክክለኛ የሆነው የውል ግንኙነት በሚያሳይ መልኩ እንዲያሻሽሉ ተደርጎ 1ኛ ተጠሪም በተሻሻለው ክስ መሠረት ክርክር እንዲያቀርቡ ተደርጎ ክርክሩ መመራት ሲገባው ይህ ሳይፈጸም ክርክሩ በቀረበው የክስ ጭብጥ መሠረት መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከውል አንጻር 1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ሲያቀርቡ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ከዋናው ዳኝነት ጋር የተገናኘ ግን ደግሞ ከውል ውጭ ባለ ኃላፊነት 1ኛ ተጠሪ የገነቡትን ግንባታ አፍርሶ በሕግ የተቀመጠውን የቦታ ርቀት ያስጠብቅ ተብሎ ይወሰንልኝ ሲሉ ክሱን አጣምረው አቅርበዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት በአንድነት ተጣምረው መታየት የሚችሉ ጉዳዮች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ተነጥሎ ከታየ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ሊያሳካው የፈለገውን ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክርን የመምራት ዓላማ እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 17(2) ላይ በአንድ ክስ ውስጥ የተለያዩ ዳኝነቶች ሲቀርቡ ዋናውን ወይም ከፍተኛውን ዳኝነት የሚመለከተው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንዳለው ተመልክቷል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ዋናው የክስ መሠረት ንብረታቸው ላይ ጉዳት መድረስ ጋር ተያያዝ ዳኝነት በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ የተጠየቀው ዳኝነትም ተከታይና ተጨማሪ ዳኝነት በመሆኑ ዋናውን ዳኝነት ለመወሰን ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት አብሮ መወሰን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ዳኝነት ለመመልከት ሥልጣን የለኝም ማለቱ መሠረታዊ የሆነ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

## **<u>ውሳኔ</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 205335 ሰኔ 16 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 236665 መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በፍርድ በተመለከተው አግባብ የክሱን መሠረት ለይተውና አብራርተው ክሱን አሻሽለው እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ የተጠሪዎችን መልስ በመቀበል ግራቀኙን አከራክሮ የመሠለውን እንዲወሰን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 202734

ቀን፡- ሚያዚያ 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሶማሌ ሪጅን

ተጠሪ፡- 1. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

2. አቶ ፋራሕ አብዲ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ እና 2ኛ ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ሟች አብዱልአዚዝ አቦሽ የአመልካች ሠራተኛና የሊፍት መኪና ሾፌር ሲሆን በወር ብር 9,000.00 ደመወዝ ይከፈለው ነበር፡፡ ነሀሴ 28 ቀን 2011 ዓ/ም ሥራ ላይ እያለ አመልካች በቸልተኝነት የኤሌክትሪክ ኃይሉ ጠፍቷል በማለት የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ሟች

በሚነዳው ተሽከርካሪ የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር በሊፍት ለመጫን ሲሞክር በኤሌክትሪክ አደጋ ሕይወቱ አልፏል፡፡ ሟች በሕይወት እያለ አባታቸው የሞተባቸው ስድስት ወንደሞች አሳዳጊ ነበር፤ በአደጋውም መተዳደሪያ ገቢያቸውን አጥተዋል፡፡ ስለሆነም የቀብር ወጪ ብር 25,000.00 እና ካሣ ብር 475,000.00 በድምሩ ብር 500,000.00 ለሟች ወንድሞች እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ አመልካች የሠጠው መልስ 2ኛ ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የተከራከረ ሲሆን ጣልቃ የገባው 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ በደንብ ቁጥር 303/2006 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 382/2008 መሠረት ዓይነቱ 15 ኬቪ የሆነ የኤሌክትሪክ ገመድ የአመልካች ንብረት የሆነና በፍ/ሕ/ቁ. 2069(2) መሠረት ኃላፊ ሊሆን የሚገባው አመልካች እንጂ ጣልቃ ገብ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከደቡብ ጅግጅጋ ወረዳ ፍርድ ቤት ሟች ልጅ ባይኖረውም ወንድሞቹ የሆኑት ወራሾች መሆናቸው የሚያረጋግጥ ውሳኔ ስለቀረበ እና ሟች ታናናሽ ወንድሞች አሳዳጊ የነበረ በመሆኑ የቀረበ ክስ ነው፡፡ አመልካች የቀጠራቸውን ሠራተኞች ከአደጋ የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፤ የኤሌክትሪክ ኃይሉ ሳይጠፋ በቸልተኝነት ጠፍቷል በማለት የደረሰ አደጋ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋራ ብር 500,000.00 ለወራሾች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝ አጣምሮ የተመለከተው የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ 2ኛ ተጠሪ የሟች ወራሾች አሳዳጊ በመሆኑ፣ ሟች በሕይወት እያለ ይሰጣቸው የነበረው የመተዳደሪያ ገቢ ለመጠየቅ ክስ ማቅረቡ በፍ/ሕ/ቁ. 807፣ 808፣ 812፣ 845፣ እና 2216(1) እንዲሁም በክልሉ ባሕላዊ ሕግ መሠረት ተገቢ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሳይከሰስና በራሱ ፈቃድ ጣልቃ ከመግባት በፊት በግድ ጣልቃ እንዲገባ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሟች በአመልካች መስመር ላይ ሲሰራ አደጋ ስለደረሰበት ካሣ ብር 500,000.00 ሊከፍል የሚገባው አመልካች ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡ 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪም ኃላፊነት አለበት ካለ ክስ ከመመስረት እንደማይገደው በውሳኔው ገልጿል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በፍ/ሕ/ቁ. 2095 ካሣ ለመጠየቅ ከሚችሉ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ 2ኛ ተጠሪ የለም፤ የሰ/መ/ቁ. 30442 (በቅጽ 5 የታተመ)፣ በሰመ/ቁ. 134240 (በቅጽ 22 የታተመ) መሠረት ተደርጎ የተወሰነ አይደለም፡፡ ጥገና ስንሰራ ኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ባለቤትና አስተዳዳሪ የሆነው 1ኛ ተጠሪ ኃይል ማቋረጫ ደብዳቤ በማስገባት እንዲቋረጥ የሚደረግበት የውልና የሥራ ግንኙነት አለን፤ ፊደር 2 ባለ 15 ኬቪ የሆነ መስመር ኤሌክትሪክ ኃይል እንዲቋረጥ ጠይቀን መስመሩ የተቋረጠ/የጠፋ መሆኑን በማረጋገጡ የጥገና ሥራው በሆዮ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ማሕበር እያሰራ እያለ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲቋረጥ ከተጠየቀበት ሰዓት በፊት 9:30 አካባቢ ኃይል በመልቀቁ የደረሰ አደጋ በመሆኑ ኃላፊነቱ የ1ኛ ተጠሪ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ንግድ ጣልቃ የገባ ነው በማለት ከክርክሩ ውጭ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሟች ስንት ወራሾች እንዳለው፣ ሟች በሕይወት እያለ በመተዳደሪያ ረገድ ገንዘብ ይሰጣቸው የነበረ ስለመሆን

አለመሆኑ፣ አደጋው እንዴት እንደደረሰ፣ ሟች ለማሽከርከር ፈቃድ ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ማስረጃ ሳይሰማና ሳይመዘን የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ስለሆነ ውሳኔው ይሻርልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ 2ኛ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም በሚል የቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ ከፍ/ሕ/ቁ. 2095 አኳያ ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያቀረበው መልስ ሟች ካሣ ከአሠሪው ዲዜድ ኮንስትራክሽን ነው መጠየቅ ያለበት፤ 2ኛ ተጠሪ የሟች አጎት ነው፣ ሞግዚት ስለመሆኑም ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ካሣ ለመጠየቅ መብት የለውም፡፡ ሟች ወራሾቹን ይረዳ የነበረ ስለመሆኑ በክሱ አልተጠቀሰም፣ ማስረጃም አልቀረበም፤ ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብሏል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንጂ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ አይገባም፡፡ ሟች በሕይወት እያለ ስድስቱን ሕጻናት ወንድሞቹን ሲያስተዳድር ነበር፤ ሞግዚትነቴ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ ነው፡፡ ውሳኔው ማስረጃው ተመዝኖ የተሰጠ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልሰ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙ ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ፤ በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ሟች አብዱልአዚዝ አቦሽ ነሀሴ 28 ቀን 2011 ዓ/ም ሥራ ላይ እያለ አመልካች በቸልተኝነት የኤሌክትሪክ ኃይሉ ጠፍቷል በማለት የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ሟች በሚነዳው ተሽከርካሪ የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር በሊፍት ለመጫን ሲሞክር በኤሌክትሪክ አደጋ ሕይወቱ አልፏል፤ ሟች በሕይወት እያለ አባታቸው የሞተባቸው ስድስት ወንደሞች አሳዳጊ ነበር፤ በአደጋውም መተዳደሪያ ገቢያቸውን አጥተዋል፡፡ ስለሆነም የቀብር ወጪ ብር 25,000.00 እና ካሣ ብር 475,000.00 በድምሩ ብር 500,000.00 ለሟች ወንድሞች እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ለአደጋው ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ በክርክሩ ሂደትም 1ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ ክሱን ያቀረቡት ስለሟች ወንድሞች ስለመሆኑ በክሱ የገለጹ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ የሟች ወንድሞችን ወክለው ክስ ለማቅረብ ችሎታ ያላቸው ስለመሆን አለመሆኑ መርምረናል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(1) መሠረት ክስ ለማቅረብ በሕግ ችሎታ ያለው ሰው መሆን ይገባዋል፡፡ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወይም መብቱ በፍርድ የተከለከለ ሰው በራሱ ክስ ለማቅረብ ችሎታ የለውም፤ ክስ ለማቅረብ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 34(1) እንደተመለከተው በሞግዚት ወይም በተሾመለት እንደራሴ አማካይነት ክስ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ድርጅት፣ ማሕበር ወይም ሌላ አካል ከሆነ ደግሞ ክስ ለማቅረብ በሕግ ሰውነት ያገኘ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት የተገነዘብነው 2ኛ ተጠሪ የሟች አብዱልአዚዝ አቦሽ ሆነ የሟች ወንድሞች አጎት ናቸው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ.

210 መሠረት የሕጻናቱ አባትና እናት በሕይወት ከሌሉ አጎትም የሕጻናቱ ሞግዚት ሆኖ ሊሾም ይችላል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በዚህ አግባብ ሞግዚትና አሳዳሪ ሆነው የተሾሙ ስለመሆኑ የቀረበ የፍርድ ቤት ውሳኔ የለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች 2ኛ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን ሳያረጋግጡ ወደ ክሱ ሥረ-ነገር በመግባት ካሣ መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሳኔ

1. የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 05-1-26/13 ታህሳስ 06 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 052-65/2012 ነሀሴ 18 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. 2ኛ ተጠሪ የሚች አብዱልአዚዝ አቦሽ ወንድሞችን ወክለው ክስ ለማቅረብ ችሎታ የላቸውም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

**የሰ/መ/ቁ.** 190307

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** የካ ክ/ከተማ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት

**ተጠሪዎች-**

1. አቶ አበበ በቀለ
2. ሻለቃ ደሳለኝ ኃይሌ
3. ፶ አለቃ ሻሜ አስቻለዉ
4. ፶ አለቃ ኃ/ስላሴ አደራ
5. አቶ አሰፋ ክፍሌ
6. አቶ መንግስቱ ይታፈሩ
7. አቶ ሁንዴሳ ጎሴ
8. አስር አለቃ አራርሳ ደገፉ
9. አቶ ቡልቶ ስሜ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ የሚስተናገድበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ የጉዳዩም አመጣጥ ሲታይ ተጠሪዎች በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ቤትና ንብረታቸዉን ያላግባብ አፍርሶ በመዉሰድ ጉዳት ያደረሰባቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ ካሳ እንዲከፈላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩን መርምሮ የተለያዩ ንብረቶች ዋጋ ብር 443,215.00 ንብረቱ ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ከሆነ በኂላ ተከሳሽ በነበረዉ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ሊሻር ይገባዋል በማለት አመልካች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ

አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ የሚቀርበዉ ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ ያረፈዉ የክርክሩ ምክንያት በሆነዉ ንብረት ላይ ሆኖ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገንን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን፣ በተያዘዉ ጉዳይ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ክርክሩን ማሰማት ባለመፈለጉ ምክንያት በሌለበት ዉሳኔ በተሰጠበት ሁኔታ አመልካች ተከሳሹ ክርክሩን አላሳወቀንም የሚል ምክንያት በመጥቀስ ዉሳኔዉ ይሻርልን በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 358 ዓላማ ያገናዘበ አይደለም በማለት ዉድቅ አድርጎታል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በትዕዛዝ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች የካቲት 02 ቀን 2012 ዓ.ም አዘጋጅቶ ያቀረበዉ አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአፈፃፀምና ማዘጋጃ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 35/2004፣ አዋጅ ቁጥር 64/2011 ላይ በተመለከተዉ መሠረት አመልካች የከተማ አስተዳደሩ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም ለማስከበር በማናቸዉም ዳኝነት አካል ዘንድ የመቃወሚያ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዉ፤ ተከሳሽ የነበረዉ ተቋም እና አመልካች በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ስር መገኘታቸዉ ብቻ አከራካሪዉን ጉዳይ በተመለከተ ተመሳሳይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸዉ ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37502 ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይህንኑ አረጋግጧል፤ ይህ ሆኖ እያለ አመልካች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም አመልካች የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ የከተማ አስተዳደሩን መብትና ጥቅም ማስከበር እንደሚችል በህግ ስልጣን ተሰጥቶት እያለ አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በሰጡት መልስ አመልካች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረበዉን የመቃወም አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለመኖሩን ጠቅሰዉ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ላቀረበዉ የመቃወም አቤቱታ መሠረት ያደረገዉ ተጠሪዎች በስር ተከሳሽ በነበረዉ የየካ ክ/ከተማ ወረዳ

01 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ያቀረቡትን ክስ መሠረት በማድረግ ብር 443,215.00 ከወለድ ጋር ለተጠሪዎች እንዲከፈል ፍርድ ቤቱ የሰጠዉ ዉሳኔ የአስተዳደሩ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ እና አመልካች በፍርድ ቤት ክርክር አቅርቦ ይህን መብት ለማስከበር በህግ ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በእርግጥ አመልካች በፍርድ ቤት ክርክር አቅርቦ የክፍለ ከተማ አስተዳደሩንና የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም የማስከበር ስልጣን በህግ የተሰጠዉ መሆኑ አላከራከረም፡፡ አከራካሪዉ እና የዚህን ችሎት እልባት የሚያሻዉ ጭብጥ አመልካች በፍርድ ቤት ክርክር በማድረግ የከተማዉ ነዋሪዎችን/የህዝብና የመንግስትን መብትና ጥቅም ለማስከበር ያለዉ መብት/ስልጣን ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር ስልጣንና ኃላፊነት ባለዉ ሌላ የከተማዉ አስተዳደር አካል ክርክር ተደርጎበት ዉሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በድጋሚ እንዲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ ያስችለዋል ወይ? የሚለዉ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸዉን የጽሑፍ ክርክር መርምረዉ፣ በቃል የሚቀርቡ ክርክሮችን አዳምጠዉ፣ ማስረጃዎችን መዝነዉ እና መሠረታዊ ህጎችን ተርጉመዉ ዉጤት ላይ መድረስ ይችሉ ዘንድ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ክርክሮች የሚመሩባቸዉ ሥርዓት እና ደንቦች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ተቀርጸዉ ስራ ላይ እንዲዉሉ የሚደረግበት ምክንያትም ይሄዉ ነዉ፡፡ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የፍትሐ ብሔር ክርክሮችን አስመልክቶ የምንከተለዉ ስርዓት ሲሆን አጠቃላይ ዓላማዉም የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ በመምራት ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲያገኙ ማስቻል ነዉ፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተለያዩ ደንቦች እና መርሆዎችን ይደነግጋል፡፡ ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን ሥርዓት ባለዉ ሁኔታ እንዲመሩ በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን፣ ብሎም ክርክሮች ባነሰ ወጪ እና ጊዜ መቋጫ እንዲያገኙ በማድረግ በፍርድ ቤት እና በተከራካሪ ወገኖች ላይ ያላግባብ የሚደርሰዉን የገንዘብ እና የጊዜ ብክነት በማስቀረት የክርክሩ ሂደትም ሆነ ዉጤቱ ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የሚኖረዉ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በህጉ ላይ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲዉሉ የማድረጉ አስፈላጊነትም የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

በዚህ ረገድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ ደንቦች ዉስጥ አንዱ በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ከተሰየሙት ወገኖች ዉጪ ያሉ ሦስተኛ ወገኖች የክርክር ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚመለከተዉ ደንብ ነዉ፡፡ በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ከተሰየሙት ተከራካሪዎች ዉጭ የሆነ ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ተሳታፊ ካልሆነ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የማይችል ዓይነት (indispensable party) ከሆነ በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት ወይም መብት ባለዉ ሰዉ አቤቱታ አቅራቢነት፣ እንዲሁም ዉጤቱ መብቴን ሊነካ ይችላል በሚል ወገን (interested party) አቤቱታ አቅራቢነት ሦስተኛ ወገን በተጀመረ ክርክር ተሳታፊ የሚሆንበትን ሥርዓት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ይዘረጋል (አንቀጽ 40 እና 41 ይመለከቷል)፡፡ ዓላማዉም የጉዳዩ አመራር ፍትሐዊ

እንዲሆንና በሥርዓት እንዲከናወን ለማስቻል ሲባል ነዉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ከላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ በክርክሩ ተሳታፊ ሆኖ መብቱን ማስከበር ይችል የነበረ ሰዉ ተሳታፊ ባልሆነበት መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ስለሆነም በፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ባለዉ አካል በተሰጠ ዉሳኔ መብቴ ተነክቷል የሚል ሦስተኛ ወገን አቤቱታዉን በማቅረብ ዉሳኔዉን በመቃወም መብቱን ሊያስከብር የሚችልበትን ሥርዓት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ የድንጋጌዉ ሙሉ ይዘትም፡-

> በክርክሩ ዉስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባዉ ወይም በክርክሩ ዉስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠዉ ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸዉም ሰዉ ራሱ ወይም ጠበቃዉ ወይም ነገረ ፈጁ ተካፋይ በልሆነበት ክርክር የተሰጠዉ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያዉን ለማቅረብ ይችላል የሚል ሲሆን የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዝኛዉ ቅጅም Any person who should or could or could have been a party to a suit and whose interests are affected by a judgment in the suit may, if he was not a party to such suit either in person or through a representative, file an opposition to such judgment at any time before such judgment is executed በማለት ይደነግጋል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉም ክርክሩ መጀመሩን ሳይረዳና ሳያዉቅ በከሳሽነትና በተከሳሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል የተደረገዉ ክርክር ተጠናቆ መወሰኑ እንኳ ቢታወቅ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ በዉሳኔዉ መብቴ ተነክቷል የሚለዉ የክርክሩ ተካፋይ ያልነበረዉ ሰዉ ይህንኑ ዉሳኔ መቃወም የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡ በተለይም በድንጋጌዉ ማናቸዉም ሰዉ ራሱ ወይም ጠበቃዉ ወይም ነገረ ፈጁ ተካፋይ ባልሆነበት ወይም በእንግሊዝኛዉ if he was not a party to such suit either in person or through a representative በሚል የተገለጸዉ የሚያሳየዉ ሦስተኛ ወገን የሚያቀርበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረዉ አቤቱታ አቅራቢዉ ለአቤቱታዉ በምክንያትነት የጠቀሰዉ ጉዳይ በቀደመዉ የክርክር ሂደት በመቃወም አመልካቹ በእራሱ ወይም በወኪሉ ወይም ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን ባለዉ ሰዉ ክርክር ያልቀረበበት ሲሆን ነዉ፡፡ በሌላ አገላለጽ የመቃወም አመልካቹ ለአቤቱታዉ መሰረት ያደረገዉ ክርክሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ጉዳዩ የሚያገባዉ ሰዉ የክርክሩ ተሳታፊ በሆነበት ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ከሆነ እና የመቃወም አመልካቹ ዉሳኔዉ '*በግል*' መብቱን የሚነካ መሆኑን በአቤቱታዉ ካላሳየ በስተቀር አቤቱታዉ ተቀባይነት የሚኖረዉ አይደለም፡፡ የመቃወም አመልካች ለመቃወሚያዉ ምክንያት የሆኑትን ዝርዝር ምክንያቶች እና የሚጠይቀዉን ዳኝነት በአቤቱታዉ በዝርዝር መግለጽ እንዲሁም አቤቱታዉ ለሌሎች ተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስ ተደርጎ ክርክሩም የሚሰማዉ የመጀመሪያዉ ክርክር በተሰማበት ሂደት ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 359 እና 360 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም የሚያሳዩት ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ የመቃወም አመልካቹን መብትና ጥቅም በግል የሚነካ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ

የመቃወም አመልካቹ እና በክርክሩ ተሳታፊ የሆኑ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ታይቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም በፍርድ ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠዉ የዳኝነት አካል የተሰጠን ዉሳኔን መቃወም የሚቻልበትን ሥርዓት አስመልክቶ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተዉ ድንጋጌ በዉሳኔዉ መብቱ *'በግል'* የተነካበት ሰዉ መቃወሚያዉን አቅርቦ መብቱን ለማስከበር እንዲችል እንጂ አንድን መብትና ጥቅም ለማስከበር የተለያዩ ሰዎች ተፈራርቀዉ የሚያቀርቡትን አቤቱታ ለማስተናገድ ያለመሆኑን መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ይልቁንም የመቃወም አቤቱታ የሚቀርብበትን ሁኔታ አስመልክቶ በድንጋጌዉ ላይ ከተመለከቱት መስፈርቶች አንፃር ሲታይ የድንጋጌዉ ዓይነተኛ ዓላማ በአንድ በኩል በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በተሰየሙ ወገኖች መካከል በተደረገ ክርክር መነሻነት የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የሚነካበት ሰዉ ዉሳኔዉን በመቃወም ተከራክሮ መብቱን እንዲያስከብር በማድረግ ፍትሕ የማግኘት መብቱን በማረጋገጥ፣ በሌላ በኩል በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል ክርክር ተደርጎበት እልባት ባገኘ ጉዳይ ላይ በድጋሚ ክርክር በማቅረብ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚል በሦስተኛ ወገን የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት እንዳይኖረዉ በማድረግ በአንድ ጉዳይ ላይ ወይም ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር በሚል ክርክሮች በተደጋጋሚ ሊቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታ በማስቀረት ክርክሮች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ መቋጫ እንዲያገኙ ብሎም የፍርድ ሂደቱም ሆነ ዉጤቱ ተገማች እንዲሆን ማድረግ ነዉ፡፡ ስለሆነም በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የቀረበ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚሰጠዉ ትርጉም ይህንኑ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ በተጠሪዎች ከሳሽነት በስር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት የተሰየመዉ የየካ ክ/ከተማ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ሲሆን ለቀረበዉ ክስ ምክንያት የሆነዉም የተጠሪዎችን ቤት አፍርሶ ንብረታቸዉንም ያላግባብ በመዉሰድ ጉዳት ያደረሰባቸዉ መሆኑ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ይህ ድርጊት በስር ተከሳሽ መስሪያ ቤት የተፈጸመ እና ለጉዳቱ ኃላፊነቱን የሚወስደዉም መስሪያ ቤቱ ስለመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 33(3) እና 92 መሠረት አረጋግጠዉ ክስ ያቀረቡ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ በመሆኑም አመልካች በህጉ አንቀጽ 33(3) መሠረት በቀጥታ ተከሳሽ ሆኖ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በተከሳሽነት የተሰየመዉ የወረዳዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ ባለመከራከሩም ዉሳኔ በሌለበት ተሰጥቷል፡፡ አመልካች የህግ ሰዉነት የተሰጠዉ ተቋም በመሆኑ የህግ ሰዉነት የተሰጠዉ የመንግስት ወይም የግል ተቋም እንደሚያደርገዉ ሁሉ በቀጥታ ተቋሙን በሚመለከተዉ ጉዳይ ላይ በከሳሽነት፣ በተከሳሽነት፣ በጣልቃ ገብነት ወይም በመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢነት በፍርድ ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠዉ የዳኝነት አካል ቀርቦ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን እንደ ተቋም ያለዉን መብት የማስከበር መብትም ግዴታም አለዉ፡፡ ይሁንና በተያዘዉ ጉዳይ ላይ አመልካች በተጠሪዎች የቀረበዉ ክስ ይመለከተኛል ወይም በህጉ አንቀጽ 33(3) መሠረት በተከሳሽነት መጠራት የነበረብኝ እኔ ነኝ የሚል ክርክር የለዉም፤ ይልቁንም

በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ያቀረብኩት የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረዉ ይገባል በማለት የሚከራከረዉ በስር ተከሳሽ የነበረዉ የየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር እንዲከፍል የተወሰነበት ገንዘብ የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑን እና የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ መከራከር እንዲችል በህግ ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑን ነዉ፡፡ በእርግጥም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 5 የዐቃቤ ሕግ ቢሮ የከተማዉ አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የአስተዳደሩና የነዋሪዉ መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ እንደሚከራከር የተመለከተ ሲሆን፣ አመልካች የክፍለ ከተማ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት በመሆኑ ስለ ክፍለ ከተማ የሥልጣን አካላት ሥልጣንና ተግባር በሚደነግገዉ ክፍል አንቀጽ 78 መሠረት የክ/ከተማዉንና የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ወኪል ሆኖ ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን በተሰጠዉ አካል ቀርቦ ክርክር የማቅረብ ስልጣን ይኖረዋል፡፡

በዚህም መሠረት በክፍለ ከተማዉ እና በስሩ የተደራጁት መስሪያ ቤቶች ከክፍለ ከተማዉ ነዋሪዎች መብትና ጥቅም ጋር በተያያዘ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ተሳታፊ በሆኑበት ጉዳይ ላይ አመልካች ወኪል ሆኖ መከራከር ይችላል፡፡ እንዲሁም እነዚህ መስሪያ ቤቶች የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ሲገባቸዉ ተሳታፊ ባልሆኑበት የተሰጠ ዉሳኔ ሲኖር እና ዉሳኔዉም የክ/ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የሚጎዳ ከሆነ የሚመለከተዉን የክፍለ ከተማዉን መስሪያ ቤት በመወከል በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ወይም በጣልቃ ገብነት ወይም በመቃወም አመልካችነት የክርክር ተሳታፊ ሲሆን መስሪያ ቤቱ በእራሱ የህግ ባለሙያ ወይም ነገረ ፈጅ ክርክሩን ማቅረብ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ የሚታወቅ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ በፍርድ ቤት ክርክር አድርጎ አንድን መብትና ጥቅም በማስከበር ሂደት አመልካች (ዐቃቤ ህግ) እና ጉዳዩ የሚመለከተዉ መስሪያ ቤት ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበት ዕድል መኖሩን ነዉ፡፡ ይህ ማለት ግን ሁለቱ ተቋማት አንድን መብትና ጥቅም ለማስከበር በጋራ ተከራካሪ በመሆን ይቀርባሉ ወይም ከሁለቱ አንደኛዉ መስሪያ ቤቱን በመወከል ክርክር አድርጎ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ሌላኛዉ ወገን ተመሳሳይ መብትን የማስከበር በህግ ስልጣን/መብት ስላለዉ ብቻ ዉሳኔዉን ለመቃወም አቤቱታ ያቀርባል ማለት እንዳልሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ይልቁንም የከተማዉን/የክፍለከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም ከማስከበር ጋር በተያያዘ ክርክር ሲኖር የሚመለከተዉን መስሪያ ቤት ወክሎ ክርክሩን ማቅረብ የሚችል አካል ከአቃቤ ህግ እና ከመስሪያ ቤቱ የህግ ባለሙያ ማን መሆን እንዳለበት የአቃቤ ህግ መስሪያ ቤት እና መስሪያ ቤቱ ተነጋግረዉ የሚወስኑት ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ተነጋግረዉ ጉዳዩን አቃቤ ህግ እንዲይዝ ከተወሰነ ሌላ የተለየ ዉክልና እንዲያቀርብ ማድረግ ሳያስፈልግ ጉዳዩን የሚመለከተዉ ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ የሚያቀርበዉን ክርክር መቀበል እንዲችል የተመለከተ ድንጋጌ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ ዐቃቤ ህግ ጉዳዩ የከተማዉ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም የሚመለከት በመሆኑ ብቻ የሚመለከተዉ መስሪያ ቤት የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን

በተደረገ ክርክር መሠረት ዉሳኔ ያገኘዉን መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን አለኝ በሚል ብቻ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ማስከበርን መሠረት ያደረገ አቤቱታ በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ አይችልም። ዐቃቤ ህግ ክርክር በማቅረብ የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም ማስከበር እንደሚችል ስልጣን የሚሰጠዉ ከላይ የተመለከተዉ የአዋጁ ድንጋጌ አተገባበርም ይህን እዉነታ ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ክሱ የቀረበበት የየካ ክፍለከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት ለፍርድ ቤት ቀርቦ ባለመከራከሩ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠ ሲሆን፣ ክርክር ሳይደረግ የተሰጠ ዉሳኔ የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የሚጎዳ ነዉ የሚል ከሆነ እና ተከሳሹ መስሪያ ቤት ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ክርክሩን ሊያቀርብ ያልቻለበት በቂ እና አሳማኝ ምክንያት አለዉ የሚል ከሆነ ከተከሳሽ መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር አቤቱታዉ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 78 መሠረት ማቅረብ ይችል ነበር። አመልካች ይህን ሳያደርግ እና በዚህም ምክንያት በተከሳሽነት የተሰየመዉ መስሪያ ቤት በሌለበት ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጎ የተሰጠ ዉሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ ነዉ ተብሎ በሚገመትበት ሁኔታ ዉሳኔዉን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም።

ሲጠቃለል በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት በተደረገ ክርክር የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የሚነካበት ሦስተኛ ወገን የመቃወም አቤቱታዉን አቅርቦ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን ተከራክሮ መብቱን ማስከበር እንዲችል ታስቦ የተዘረጋ ነዉ። በመሆኑም አቃቤ ህግ ወኪል ሆኖ ሊከራከር የሚችልበት መብትና ጥቅም ክርክር በማድረግ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን ባለዉ ጉዳዩ በሚመለከተዉ መስሪያ ቤት ክርክር ቀርቦበት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ አቃቤ ህግ ዉሳኔዉን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ሊቃወም የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም። በዚህ አግባብ ለመወሰን ለክርክሩ ምክንያት ከሆነዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሁለቱም (ዐቃቤ ህግ እና ጉዳዩ የሚመለከተዉ መስሪያ ቤት) የሚያስከብሩት መብትና ጥቅም አንድ እስከሆነ ድረስ የአቃቤ ህግ መስሪያ ቤት እና በክርክሩ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የተሰየመ መስሪያ ቤት የየራሳቸዉ ስልጣንና ኃላፊነት ያላቸዉ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባዉ ጉዳይም አይደለም። ስለሆነም ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ተገቢነት የለዉም። በእርግጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37502 በቅጽ 8 ላይ በታተመዉ ዉሳኔ ሁለት ራሳቸዉን የቻሉና የህግ ሰዉነት ያላቸዉ ተቋሞች በአንድ የመንግስት መዋቅር ሥር የሚገኙ በመሆናቸዉ ብቻ ተመሳሳይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸዉ ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አለመሆኑን በመጥቀስ ከከተማ አስተዳደሩ አንዱ አካል የክርክሩ ተሳታፊ በሆነበት ክርክር ተደርጎ ዉሳኔ መሰጠቱ የአመልካች መስሪያ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ እንዳያቀርብ የሚከለክል አይደለም የሚል ይዘት ያለዉ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። ይሁንና ይህ የህግ ትርጉም በሦስተኛ ወገን አቤቱታ

የሚቀርብበትን ሁኔታ አስመልክቶ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ዓላማ ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊለወጥ የሚገባዉ የህግ ትርጉም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1. የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 210662 ላይ ሐምሌ 02 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 181686 ላይ ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37502 (ቅጽ 8 ላይ እንደታተመዉ) የሰጠዉ የህግ ትርጉም ተለዉጧል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ ዐቃቤ ህግ ቢሮ (በየደረጃዉ ያሉ ዐቃቤ ህግ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል) ወኪል ሆኖ ክርክር በማቅረብ የነዋሪዉን መብትና ጥቅም እንዲያስከብር በአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጁ ስልጣን የተሰጠዉ ቢሆንም፣ ይህ ስልጣኑ ብቻዉን ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር ስልጣን ያለዉ የሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል የክርክሩ ተሳታፊ በሆነበት ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ መሠረት አድርጎ እንደገና ክርክር ለማድረግ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ እንዲያቀርብ ምክንያት አይሆንም፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. የሰበር አጣሪ ችሎት የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

ማ/አ                                        የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 215134

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ አሚን ሙመድ አሊ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ኢብሳ አህመድ ሙመድ - ጠበቃ ዲንቃ ደረጀ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በቀን 10/02/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 376128 በቀን 25/01/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በስር የሀሮማያ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ በቀን 22/04/2013 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በሀሮማያ ወረዳ ኢፋ ኦሮሚያ አሊ ወዳይ ቀበሌ ውስጥ የእርሻ መሬት ይዞታ የሆነ 26 ከተራ ጫት በላዩ ላይ የሚገኝ የጫትና የእህል መሬት የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰ 1 ጥማድ መሬቴን ተከሳሽ ዘመዴ ስለሆነ በቀን 21/10/2009 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት በጫቱ ውስጥ እህል ዘርቶ የጫቴን ስርም ኮትኩቶልኝ ከጫቱ ላይ የሚገኘውን ምርት ለእኔ ገቢ እንዲያደርግልኝና እሱም እህል ዘርቶ ምርቱን እንዲወስድ ተባብለን እንደ አካባቢያችን ባህል በሰው ምስክሮች ዘንድ በቃል ውል ተዋውለን መሬቴን ሰጥቼዋለሁ፡፡ ነገር ግን ከተሰጠው ቀን ጀምሮ እንደ ውላችን በእምነት ከጫቱ የሚገባልኝን እኩል እስከ 2013 ዓ.ም ሊሰጠኝ አልቻለም፤ ለራሱ ጫቱን ሸጦ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ ስለሆነም ድርሻየን በበጠቅላላው 48,000.00 (አርባ ስምንት ሺህ) ብር እንዲከፍለኝና መሬቱን እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር ተከሳሽ በበኩላቸው በቀን 03/05/2013 ዓ.ም በሰጡት መልስ ክሱ የሀሰት ነው፤ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ተከሳሽ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ 15 አመት ሙሉ አርሼ የምጠቀምበት፣ ልጆቼን ምራዝ አውጥቼበት የሚገኝ ስለሆነ ከሳሽ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ መሬቱን አስመልክቶ የእርቅ ሽማግሌዎች ውጤት መልስ ባልሰጠሁበት ከእኔ ኋላ ተጽፎ የተሰጠ ስለሆነ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16(1) መሰረት ተቀባይነት የለውም፤ ስለሆነም የቀረበው

የሀሰት ክስ ውድቅ ሆኖ ወጪና ኪሳራዬ ተከፍሎኝ ልሰናበት በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አማራጭ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የመቃወሚያ ክርክራቸውንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ እንዲሁም ተጨማሪ ማስረጃዎችንም ከሰማ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ በክሱ በጠቀሰው መልኩ በተደረገ ስምምነት መሬቱን ማስተላለፉና ካስተላለፈው 4 ዓመት ብቻ ስለመሆኑ በማስረጃዎቹ ሚዛን በሚደፋ መልኩ አላስረዳም፤ ይልቁንም ተከሳሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ይዞ መጠቀም የጀመረው ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በማስረጃዎቹ እንዲሁም በተጨማሪ በቀረቡ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ ተከሳሽ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ይዞታ ይዞ መጠቀም ከጀመረ 15 አመት በላይ መሆኑን በከሳሽ ምስክሮችና በቀረቡ ተጨማሪ ምስክሮች ተረጋግጦ ስለሚገኝ በደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32 መሰረት ከ12 አመት በኋላ ከሳሽ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ይግባኝ ለሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ክርክር እና ማስረጃውን መርምሮ ተከሳሽ መሬቱን ይዞ ከ15 ዓመት በላይ እየተገለገለበት መሆኑ በማስረጃዎቹ ስለተረጋገጠ የስር ፍርድ ቤት ክሱን በይርጋ ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው በማለት ውሳኔውን አፅንቷል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ይግባኙ የቀረበለት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት ከግራ ቀኙ ምስክሮች በተጨማሪ የመሬቱን ጉዳይ በቅርበት የመሬቱ አዋሳኝ ባለይዞታዎችን በተጨማሪ ማስረጃነት ሰምቶ የሰጠው ውሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

ከሳሽ በመጨረሻ ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ ጉዳዩን መርምሮ መሬቱ ከከሳሽ እጅ ወጥቶ በተከሳሽ እጅ ሊገባ የቻለው ከሳሽ በመቸገሩ ምክንያት ተከሳሽ ገንዘብ ሰጥቶት ነው፤ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 40(3) በይዞታ መሬት ላይ ግዥና ሽያጭ መዋዋል እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው የእርሻ ይዞታ መሬት በህግ መሰረት ያገኘ እንደሆነ እንጂ ከህገ መንግስት ተቃራኒ በሆነ መንገድ ያገኘ እንደሆነ የይርጋ ጊዜ እንደ መጀመሪያ ተቃውሞ ቀርቦ ክሱ ውድቅ መሆን ስለማይችል የስር ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ ይዞታውን በህጋዊ መንገድ እንዳገኘ በመውሰድ ከሳሽ ያቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡ አከራካሪውን መሬት ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲለቅ በማለትም በዚያው ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት ተጠሪ በራሱ ፍላጎት በ1995 ዓ.ም ሰጥቶኝ ያለምንም ተቃውሞ ከ15 አመት በላይ ስጠቀምበት የቆየሁት መሆኑን አረጋግጬ እያለ እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 113973 አንድ ሰው ለ3ኛ ወገን አሳልፎ ይዞታውን ከሰጠ መልሶ ለመቀበል እንደማይችል አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባላነሳው ክርክር ገንዘብ ወስዶ

መሬቱን ወሰደ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ብር የሰጠሁት በወንጀል ስለተከሰሰ ልረዳው እንጂ ከመሬቱ ጋር በተገናኘ አይደለም፤ ይህ ስለመሆኑም ምስክሮች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ተጠሪም ብር ስለሰጠኝ መሬቱን ወሰደብኝ ብሎ አልተከራከረም፣ ክስም አላቀረበም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ ይዞታውን ለእኔ መስጠቱን ራሱ አምኖ ተከራክሯል፡፡ በክሱ ላይ ጫቱን ለራሴ ገቢ እንዲያደርግ ፤ ጫቱ ስር የሚዘራው እህል ደግሞ ለራሱ እንዲጠቀም ተስማምተናል ብሎ ያቀረበውን ክስ በተመለከተ በጫት ስር ምንም አህል እንደማይዘራ የታወቀ ነው፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ያላነሳውን በራሱ ተነሳሽነት ጭብጥ በመያዝ የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርመሮ አከራካሪው መሬት በሽያጭ የተላለፈ ስለመሆኑ በስር ወረዳ ፍ/ቤት ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የተደረገ ክርክር ሳይኖር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሽያጭ ያገኘው መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 25/06/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ በስር ወረዳ ፍ/ቤት የቃል ክርክር ስናደርግ ተከሳሽ እንደሚሉትም ቢሆን ህገ ወጥ ውል በመሆኑ በይርጋ አይታገድም በማለት አንስቼ ስለተከራከርኩ በስር ፍ/ቤቶች ያልተነሳ ክርክር አይደለም፤ ፍ/ቤቶችም ህገ መንግስቱ እንዳይጣስ የማረጋገጥ ሀላፊነት ስላለባቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 69291 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንድ ሰው የተወሰነ ገንዘብ ተቀብሎ የእርሻ መሬቱን ላልተወሰነ ግዜ ወይም በዘለቄታዊነት በውል ለሌላ ሰው ቢያስተላልፍ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 40(3) የሚጥስና ከአዋጅ ቁጥር 456/97 ጋር የሚቃረን በመሆኑ ውሉ ህገ ወጥ ነው በማለት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የገጠር እርሻ መሬት መሸጥ ወይም መለወጥ ህገ ወጥ ድርጊት በመሆኑ በይርጋ ሳይገደብ በማንኛውም ግዜ ሊፈርስና መሬቱ እንዲመለስ መጠየቅ እንደሚቻል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 110549 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ገንዘብ ሰጥቶ መሬቱን መውሰዱ በሌላ ቋንቋ መግዛቱ ስለሆነ ህገ ወጥ በመሆኑ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የለውም ውሳኔው እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ ያያዘውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የመንግስትና የህዝብ ሀብት መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40(3) ስር ተደንግጓል፡፡ መሬት የመንግስትና የህዝብ ሀብት ሆኖ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ አርሶ

አደር የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀም ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40(4) ስር በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የአርሶ አደሮች የመሬት ባለይዞታ የመሆን፤ በመሬት የመጠቀምና ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብት ህጋዊና ተግባራዊ ለማድረግም የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 እና በኦሮሚያ ክልልም አዋጅ ቁጥር 130/99 እና ማስፈፀሚያ ደንቡ ወጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በአንፃሩ ክርክሩ የፍትሐ ብሄር በመሆኑ ሊመራ የሚገባውም በፍትሐብሄር ሥነ ስርዓት ህጉ አግባብ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለውም የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራከራዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት አይችልም፡፡ ስለሆነም በተከራካሪ ወገን ያልተነሳን መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ በራሱ አንስቶ እንዲወስን አይጠበቅም፡፡

በተያዘውን ጉዳይ ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በመቸገሬ ምክንያት አመልካች ገንዘብ ሰጥቶኝ በሽያጭ ውል መሬቱን አስተላልፌያለሁ፤ ስምምነታችን ህገ ወጥ ስለሆነ ቀሪ ተደርጎ መሬቱን ይመልስልኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ በዚህ መልኩ ክርክር በቃልም ቢሆን ስለማቅረባቸው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አያሳይም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ ያቀረቡት ክስና የጠየቁት ግልፅ ዳኝነት በተጠሪና አመልካች መካከል በቀን 21/10/2009 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት አመልካች በጫት ውስጥ እህል ዘርቶ የጫቱን ስር እየኮተኮተ ከጫቱ ላይ የሚገኘውን ምርት ለእኔ ገቢ እንዲያደርግልኝና እሱም የእህል ምርቱን እንዲወስድ ስምምነት አድርገን ነበር እንደ ውላችን ከጫቱ የሚገባኝን እስከ 2013 ዓ.ም ሊሰጠኝ አልቻለም፤ ስለሆነም የድርሻዬን ግምት 48,000.00 (አርባ ስምንት ሺህ) ብር ከፍሎይልቀቅልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች እንደዚህ አይነት ስምምነት አለመኖሩን ክደው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ከፍ ሲል የተገለፀውን ፍሬ ነገር መሰረት አድርገው ክስ ቢመሰርቱም ፍሬ ነገር ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን በህጉ ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በክሱ በጠቀሰው መልኩ ከአመልካች ጋር በተደረገ ስምምነት መሬቱን ስለማስተላለፉቸው በማስረጃ አለማስረዳታቸውን፤ ከዚህ ይልቅ አመልካች ያለተቃውሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ይዘው ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ እየተጠቀሙበት መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡንና በደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32 መሰረት ከ12 አመት በኂላ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ወስኗል፡፡ ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ እና ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ችሎቶችም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በዚህ መልኩ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ክርክሩ የሚመራበት የሥነ ሥርዓት ህግ ለመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት (ለወረዳው ፍርድ ቤት) የሰጠውን የዳኝነት ስልጣን እንዲሁም የክልሉን የገጠር መሬት አዋጅና ደንብ የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ አልነበረም፡፡

ይሁንና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ያልተነሳ ክርክር እና ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ያልተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ መሬቱ ከተጠሪ እጅ ወጥቶ

በአመልካች እጅ ሊገባ የቻለው በሽያጭ ነው፤ ከህገ መንግስት ተቃራኒ በሆነ መንገድ በሽያጭ ከተገኘ የይርጋ ጊዜ እንደ መጀመሪያ ተቃውሞ ሊቀርብ አይችልም የሚሉ ምክንያቶች ሰጥቶ ውሳኔውን መሻሩ የግራ ቀኙን ክርክር እና ጉዳዩ የሚመራበትን የሥነ ሥርዓት ህግ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ከመደረጉ በቀር በፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ አለመሰጠቱ እንኳ እየታወቀ የክልሉ ሰበር ችሎት በራሱ ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ አከራካሪውን መሬት ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲለቅ በማለት መወሰኑም ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ሰበር ችሎት ያሳለፈው ውሳኔ የግራ ቀኙን ክርክር፤ የመሬት አዋጅና ደንቡን እንዲሁም የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን የጠበቀ ባለመሆኑና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 376128 በቀን 25/01/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሀሮማያ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 82622 በቀን 13/07/2013 ዓ.ም፤ የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 89818 በቀን 08/08/2013 ዓ.ም፤ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 371139 በቀን 10/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 25/2014 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

## <u>የልዩነት ሀሳብ</u>

### ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የሚገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለው አስቀምጫለሁ

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ የአሁን አመልካች የመሬት ይዞታዬን ይዞ ስለሚገኝ ይልቀቅልኝ በሚል የጠየቀ ሲሆን የአሁን አመልካችም መሬቱ ለረጅም ጊዜ በእጄ የቆየ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ከሳሽ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄው የንብረት መፋለም ክርክር ሲሆን ይሄውም ተከሳሽ መሬቴን ስለያዘብኝ ይመልስልኝ የሚል ነው፡፡ ከሳሽ የአሁን ተጠሪ የንብረት መፋለም ክርክር ሲያቀርብ ተከሳሽ መሬቴን ስለያዘብኝ ይልቀቅልኝ የሚል ክስ ቢያቀርብ በቂ የሚሆን ሲሆን ይህን የንብረት የመፋለም ክስ ለማቅረብ ምክንያቶች የጠቀሰ ሲሆን ተከሳሽ ንብረቱን እንዴት እንደያዘበት በሀይል፣ በወረራ በስምምነት ወይም በሌላ ምክንያት እንደሆነ ምክንያቱን መጥቀሱ አስፈላጊ የሚሆን አይደለም፡፡ ይሄውም በንብረት መፋለም ክርክር መሬቱ እንዴት እንደተያዘበት ተወሮ ወይም በሀይል ወይም በስምምነት ይሁን አይሁን የተያዘበትን ምክንያት ለመጥቀስ ግዴታ የሌለበትና መሬቱ በተከሳሽ ስለተያዘበት እንዲለቀቅለት መጠየቅ ብቻ በቂ የሚሆን ነው፡፡ ለንብረት መፋለም ክስ እንደ ሁከት ክስ በሀይል፣ በወረራ ወይም የውል ክርክር የውሉን አይነት መጥቀስ አይገደድም፡፡ ፍ/ቤቶችም ጭብጥ ሲይዙ ዋናው የፍሬ ነገር ክርክር የንብረት መፋለም ክስ ከሆነ ንብረቱ የማነው የሚል ጭብጥ አንጂ ምክንያቱ ወረራ ስለመኖር አለመኖሩ ጭብጥ ሊሆን አይገባም፡፡ በክርክር ሂደት ውስጥ ከሳሽ አንድ ፍትህ ለማግኘት የሚጠይቀው ዳኝነት ዋናውን ጉዳይ ዳኝነቱን ለመጠየቅ የሚያነሳቸው ምክንያቶች አሉ፡፡ በክሱ ውስጥ ዋናውን ዳኝነትና ዳኝነቱን ለመጠየቅ የተነሱ ምክንያቶችን መለየት አለብን፡፡ ብዙ ጊዜ ከሳሹ የሚጠይቀውን ዋናውን ዳኝነት ትተን ከክርክራቸው ውጪ በምክንያቱ ላይ ጭብጥ ይዘን ስንወስን ይታያል፡፡ ከሳሽ ላቀረበው የመፋለም ክስ ተከሳሽ መሬቴን ስለያዘብኝ ይልቀቅልኝ ክስ ተከሳሽ የሰጠው መልስ መሬቱ ለረጅም ጊዜ በእጄ የቆየ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ተከሳሽ መሬቱ የከሳሽ መሆኑን ተቀብሎ በይርጋ ቀሪ ይሆናል እያለ በመሆኑ የክርክር ጭብጥ የሚያዘው ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 246 እና 247 ላይ እንደሚደነግገው ከክስና ከቀረበው መልስ ሲሆን፣ ተከሳሽ መሬቱ የከሳሽ መሆኑን ተቀብሎ ይርጋን መከራከሪያ ያነሳ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ስለመሆን አለመሆኑ ለመለየት ተከሳሽ የከሳሽን መሬት የያዘው በህጋዊ መንገድ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መለየት የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ ተከሳሽ ያከራከረውን መሬት እንዴት ያዘው የክርክሩ ጭብጥ የሚሆን ነው፡፡ ከሳሽ በክሱ ለጠየቀው ዳኝነት የገለጸውን ምክንያት አላስረዳምና ክሱ ውድቅ ነው ብለው የሚያስቡ ሰዎች፣ የክርክር ጭብጥ ማለት የተጠየቀው ዳኝነትን ብቻ የክርክር ጭብጥ አድርገው የሚወስዱ ሰዎች ናቸው፡፡ እንዲ ከሆነማ የግራ ቀኙን ክርክር ጭብጥ መያዝ ሳያስፈልግ ክሱን ብቻ እንደጭብጥ ወስዶ ውሳኔ መስጠትን የሚያስከትልና ሥነ ሥረዓታዊም የማይሆን ኢፍትሃዊ ውሳኔ የሚያስከትል ነው፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር ጭብጥ ተይዞ የሚጣራው ከሳሽ የጠየቀው ዳኝነት ብቻ ሳይሆን የቀረበው ክስ የተሰጠው መልስ ከተደረገው የቃል ክርክር መሰረት ተደረጎ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የፌደራል

ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 47252 የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከሳሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤት የቃል ምርመራ ሲያደረግ የሚያገኘውን ፍሬ ነገር ጉዳይ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የውል ጉዳይ ሳይሆን የገጠር የመሬት ይዞታ በመሆኑ እና የገጠር የመሬት ይዞታ ክርክር ደግሞ በየክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት የሚዳኝ መሆኑ የማያከራክርና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ትርጉም ሰጥቶበት የሚገኝ ነው፡፡

በግራ ቀኙ በተደረገው ክርክር የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ክሱ በይርጋ ቀሪ ስለመሆን አለመሆኑ ለማጣራት ተከሳሽ የአሁን አመልካች መሬቱን የያዘው በህጋዊ መንገድ ስለመሆን አለመሆኑ መጣራት ያለበት በመሆኑ በዚሁ መሰረት በተደረገው ማጣራት የተሰሙት የሰው ምስክሮች ተከሳሽ መሬቱን የያዘው ለከሳሽ ለአሁን ተጠሪ ገንዘብ ከፍሎት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 179827 ላይ በሰጠው ውሳኔ በህገ ወጥ መንገድ የተያዙ መሬቶች ማለት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ከሚፈቅደው ህጋዊ መንገድ ውጪ የተያዙ መሬቶች ሁሉ በህገ ወጥ መንገድ የተያዙ ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት የሚገኝና በህገ ወጥ መንገድ የተያዙ መሬቶች ሁሉ ደግሞ በይርጋ እንደማይታገዱ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም መሬትን በሽያጭ፣ ህግ በሚደነግገው ውጪ ማስተላለፍ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(4) የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑንና ፍ/ቤቶች የመሬት ክርክርን በይርጋ ውድቅ በማድረግ የሰጡትን ውሳኔ ህገ መንግስቱን የሚጻረር በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ሲል የወሰነበት ነው፡፡ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 112906 ላይ በሰጠው ውሳኔ መሬት በህገ ወጥ መንገድ ለረዥም ጊዜ በመያዝ የመሬቱ ባለይዞታ እንደማይኮን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጣቸው የህግ ትርጉሞች እስካልተለወጡ ድረስ በማንኛውም ደራጃ ላሉ ፍ/ቤቶች አስገዳጅነት ያለው ትርጉም ስለመሆኑም የፌደራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አሁን ግራ እና ቀኙን ያከራከረው የመሬት ይዞታ በሽያጭም ይሁን በስጦታ በህገ ወጥ መንገድ የአሁን አመልካች እጅ የገባ መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ ተረጋግጦ እያለና የአሁን አመልካች ክስ በይርጋ የማይቋረጥ ሆኖ እያለ እንዲሁም የአሁን አመልካች መሬቱ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ ያልተከራከረና የሚያምን በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ተገንዝቦ የሰጠውን ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በሚል ህጋዊና በቂ ባልሆነ ምክንያት ክሱን ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ብዬ ስለማላምን የተለየ ሀሳቤን አስቀምጫለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.214136

ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡......1. አቶ ደለሳ ጅማ -- ቀረቡ

2. አቶ ጌቱ አበበ ቱጂ -- ቀረቡ

3. አቶ አዳነ ነጊያ ደንቦባ

4. አቶ ጌቱ ይመር ዋኬኔ } አልቀረቡም

5. አቶ ሽምሱ ሲፋ ሁሴን

6. አቶ በድሩ ሃምዛ ቡሽራ -- ቀረቡ

7. አቶ ሃይሉ ቤኛ ጉደታ -- አልቀረቡም

8. አቶ ተሾመ ደምሴ ምህረቱ -- ቀረቡ

9. አቶ ከማል ሽፋ እንቁ

10. አቶ ዘይኑ አሊ አማን } አልቀረቡም

11. አቶ ተሻለ ፍቃዱ ናዶም -- ቀረቡ

12. አቶ ጸጋዬ ጉደታ አለጋ

13. ወ/ሮ ቦጋለች ደሴ አርጌ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡-...ኮልፌ ቅዱስ ራጉኤል አዲስ ሕይወት አክስዮን ማህበር-- ጠበቃ ሲሳይ መኮንን - ቀረቡ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የማህበር አባልነት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት እነ አቶ አምሳሉ ባህሩ የሥር ጣልቃ ገቦች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.269920 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም

የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች የከሳሽ ማህበር አባላት ሁኖ የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎችን ባለመፈጸማቸዉ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ከማህበሩ እንዲሰናበቱ የወሰነ ሲሆን፣ ተከሳሾች ይህን ዉሳኔ ለማሰረዝ ክስ አቅርበዉ ዉድቅ የሆነባቸዉ ሲሆን፣ በዚህ ዉሳኔ መሰረት ለማስፈጸም ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ ክፍያ ያልከፈሉ አባላት ክፍያዉንና ቅጣቱን በሁለት ወራት ዉስጥ እንዲከፍሉ፣ ይህ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ በማስገባት ክፍያዉ ተሳስቦ እንዲከፈላቸዉ የተወሰነ በመሆኑ፣ ተከሳሾች ዉሳኔዉን ለማሰረዝ ክስ አቅርበዉ ዉድቅ የሆነባቸዉ ስለሆነ፣ ተከሳሾች አልከፈሏቸዉም ያለዉን ክፍያዎች በመዘርዘር፣ በጠቅላላ ጉባኤዉ ዉሳኔ መሰረት ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ተከሳሾች ከማህበሩ አባልነት እንዲሰረዙ በማለት የወሰነዉ ሥራ አልዋለም፤ ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም የተወሰነዉ ዉሳኔ የቀደመዉን ዉሳኔ የሚሽር ነዉ፤ ተከሳሽ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ እንጂ በማስታወቂያ ከማህበሩ ሊወጡ እንደማይገባ፤ ከሳሽ የጠቀሳቸዉ ክፍያዎች የተከፈሉትን ክፍያዎችንና የተዋጡ መዋጮዎችን ታሳቢ ያላደረገ ነዉ፤ ከማህበሩ ጋር በነበረዉ ዉይይት የማህበሩ ሂሳብ በባለሙያ ተጣርቶ እዳ ያለባቸዉ እንዲከፍሉ፣ ክፍያዎችን መክፈል ያልቻሉትን ደግሞ ማህበሩ ትብብር አድርጎላቸዉ ከአበዳሪ ተቋማት ብድር ወስደዉ እንዲከፍሉ ስለተባለ በዚህ አግባብ ትብብር እንዲደረግልን፤ ተከሳሾች ከማህበሩ ሊወጡ ይገባል የሚባል ከሆን እንኳን የማህበሩ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ድርሻችን ተከፍሎን ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ የከሳሽ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ አባላት የሆኑት ተከሳሾች የግንባታና የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ በወሰነዉ መሰረት መክፈል ያለመቻላቸዉን ተከሳሾችም ያመኑ ጉዳይ ሲሆን፣ ተከሳሾች በዚህ አግባብ መክፈል ባለመቻላቸዉ ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነ ቢሆንም በዚህ መሰረትም መክፈል ስላልቻሉ፣ ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲከፍሉ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ ገቢ ተደርገዉ ያላቸዉ ሂሳብ ተሰልቶ እንዲከፈላቸዉ የተወሰነ ሲሆን፣ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ መሰረትም ግዴታቸዉን አልተወጡም፡፡ ተከሳሾች እነዚህን የጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔዎችን ለማሻር ክስ አቅርበዉ ዉድቅ የተደረገባቸዉ መሆኑን በግራ ቀኙ የታመነ እና በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፤ ተከሳሾች አሁን የጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ ዉድቅ ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፤ የጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ ለማሻር የሚያስችል የሕግ መሰረት የለም፤ ተከሳሾች የሚጠበቅባቸዉን ግዴታቸዉን

ሙሉ በሙሉ ያልተወጡ በመሆናቸዉ ከማህበሩ ሲወጡ ሊከፈላቸዉ ስለሚገባዉ ክፍያ ማጣራት ስለሚኖር በዚህ አግባብ መብታቸዉ የሚጠበቅ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሂሳብ ማጣራቱ ተገቢ አይደለም፡፡ በዚህ መሰረት ተከሳሾች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔዎች መሰረት ግዴታቸዉን ሊወጡ ባለመቻላቸዉ ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ የተወሰኑ በመሆኑና ዉሳኔዉን የሚያሽር በቂ ምክንያት ባለመገኘቱ በዉሳኔዉ መሰረት ተከሳሾች ከማህበር አባልነታቸዉ እንዲወጡ በማለት ወስኗል፡፡

ተከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በ10/1/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የተጠሪ ማህበር አመልካቾች ክፍያ ስላልከፈሉ ከማህበሩ አባልነታቸዉ እንዲወጡ በማለት ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ባደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ የወሰነ ቢሆንም ይህን ለመወሰን ስልጣን የለዉም፤ ስልጣን አለዉ ቢባል እንኳን አሁን ለፍ/ቤት አመልካቾች ከአባልነት ይሰረዙ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ ዳግመኛ የቀረበ ጉዳይና የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት ነዉ፤ አመልካቾች የተለያዩ ክፍያዎችን ስንከፍል የቆየን ቢሆንም ይህን የተከፈለዉን ክፍያ በሂሳብ ባለሙያ እንዲጣራ ሳያደርግ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 3 (ለ) በመጣስ ከማህበር አባልነት እንድንሰናበት የሰጠዉ ዉሳኔን ፍ/ቤቱም በመቀበል ዳግመኛ ከማህበር አባልነት ተሰናብታችኋል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት የሚያስወጣን ምንም የህግ ምክንያት የለም ተብሎ እንዲወሰንልን፤ አመልካቾች ከማህበሩ ሊወጡ ይገባል የሚባል ከሆነ ለአመልካቾች ሊከፈለን የሚገባዉ የገንዘብ መጠን የማህበሩ ሀብት ተሰልቶ በከፈልነዉ የገንዘብ መጠን ሊከፈለን ይገባል በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፤የአሁን አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ የሥር ፍ/ቤት የወሰነበትን አግባብ ከመተዳደሪያ ደንብና አግባብነት ካላቸዉ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት መጋቢት 7 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎችን ባለመክፈላቸዉ የተጠሪ ማህበር ከአባልነት እንዲሰናበቱ የወሰነዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ ያሳለፉት ዉሳኔ ከሕግ የሚቃረን ስላልሆነ፣ የአመልካቾች ቅሬታ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በ23/7/2014 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካቾች የተጠሪ ማህበር አባላት መሆናቸዉ፣ አመልካቾች የግንባታ እና የተለያዩ ክፍያዎችን መክፈል ባለመቻላቸዉ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከማህበሩ አባልነት እንዲሰናበቱ መወሰኑን፣ ይህን ዉሳኔ ለማስፈጸም ሲባል የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም ባሳለፈዉ ዉሳኔ አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎች በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲከፍሉ፣ ይህ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ ገቢ ተደርጎ ያላቸዉ ሂሳብ ታስቦ እንዲከፈላቸዉ በማለት መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ አመልካቾች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ መሰረት ግዴታቸዉን መወጣት ያለመቻላቸዉን በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ አመልካቾችም ያመኑት ጉዳይ መሆኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች እነዚህ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔዎች ከሕግ ዉጭ የተወሰኑ መሆናቸዉን በመጥቀስ ዉሳኔዎቹ እንዲሰረዙላቸዉ ለፍ/ቤት ክስ አቅርበዉ ክሳቸዉም ዉድቅ የሆነባቸዉ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡በመሆኑም አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ክፍያዎች ሳይከፍሉ መቅረታቸዉን መነሻ በማድረግ ከማህበር አባልነታቸዉ እንዲወጡ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የወሰነዉ ዉሳኔ እንዲሰረዝላቸዉ ክስ አቅርበዉ ተቀባይነት ያጣ ሆኖ ሳለ፣ አሁን ጠቅላላ ጉባኤ ያሳለፈዉ ዉሳኔ ከመተዳደሪያ ደንብና ከሕግ ዉጭ ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 (1) መሰረት ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካቾች ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከማህበር አባልነት እንዲሰናበቱ ያሳለፈዉን ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤቶች በመቀበል አመልካቾች ከማህበር አባልነት እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ የወሰነዉ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካቾች ከማህበር አባልነት እንዲሰናበቱ የተወሰነዉን ዉሳኔ በተመለከተ ያቀረቡት ቅሬታ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ባለመሆኑ ቅሬታቸዉ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ነገር ግን አመልካቾች ከማህበር አባልነት እንዲወጡ እስከተወሰነ ድረስ፣ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የገንዘብ መጠን ምን ያህል ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የተጠሪ ማህበር ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም ባደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ አመልካቾች መክፈል ያለባቸዉን ክፍያዎች በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ ሊከፍሉ እንደሚገባ ይህ ካልሆነ ሱቆቻቸዉ ወደ ማህበሩ ገቢ ተደርገዉ ያላቸዉ ሂሳብ ተሰልቶ ሊመለስላቸዉ እንደሚገባዉ መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለዉ አመልካቾች ከማህበሩ ሲወጡ ያላቸዉ ሂሳብ ተጣርቶ ሊከፈላቸዉ የሚገባቸዉ ገንዘብ መኖሩ ከተረጋገጠ እንደሚመለስላቸዉ ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች

አመልካቾች ከማህበሩ አባልነት እንዲወጡ ወስኖ ሲያበቃ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉን ክፍያ በተመለከተ ከማህበሩ ሲወጡ ሂሳብ ማጣራቱ ስለማይቀር መብታቸዉ በዛ አግባብ የሚጠበቅ ይሆናል በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ ከማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ይህንን ደግሞ የፍትሀብሔር ሥነሥርዓት ሕጉ በዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት አጣርቶ መወሰን ይገባል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ያሳለፈዉ ዉሳኔ የሚሻርበት በቂ ምክንያት የለዉም ያለዉ ተገቢ ቢሆንም፣ ዉሳኔዉን በከፊል በመቀበል ከፊሉን ደግሞ ባለመቀበል ለአመልካቾች የሚከፈለዉ ክፍያ ካለ አሁን ተሰልቶ ሊከፈላቸዉ እንደሚገባ መወሰን ሲገባዉ አጥጋቢ ያልሆነ ምክንያት በመጥቀስ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ ከማህበር አባልነት ሊወጡ ወይም ሊሰረዙ ይገባል በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ ተገቢ ቢሆንም ከማህበሩ አባልነት ሲወጡ ግን የሚከፈላቸዉ ክፍያ ካለ ተጣርቶ መወሰን ሲገባዉ ሳይወሰን መታለፉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.276498 ታህሳስ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ያሳለፈዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.269920 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካቾች ከማህበሩ አባልነታቸዉ እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ የተወሰነዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለአመልካቾች ሊከፈላቸዉ የሚገባቸዉ የገንዘብ መጠን በሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ ግራ ቀኙ ሪፖርቱ ላይ አስተያየታቸዉን እንዲሰጡ በማድረግ፣ እንዲሁም ጉዳዩን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ሁሉ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ከተጠሪ ማህበር አባልነት እንዲወጡ ወይም እንዲሰረዙ በማለት ያሳለፉት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

 አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 208632

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ፀጋነው መንበሩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አራዳ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ሔኖክ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 30/09/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 199733 በቀን 27/05/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 202785 በቀን 09/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ ላይ ተጠሪ የመጀመሪያ መቃወሚያዎችን አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ከሳሽ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ለማየት ፍርድ ቤቱ ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? ከሳሽ ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦችን ይዞ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በሰጠው ውሳኔ በዚህ መዝገብ የተጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ አላግባብ የተወሰነ ግብርን ተንተርሶ የደረሰ ኪሳራ በሚል ኪሳራውን ለማስከፈል የቀረበ ሲሆን ግብሩ አላግባብ ተወስኗል ወይስ አልተወሰነም የሚለውን ለማየት ፍ/ቤቱ ስልጣን የሌለው በመሆኑ ይህን ተከትሎ የደረሰ ኪሳራ ለመወሰን ቀድሞ ጥፋት ባልተረጋገጠበት ሊወሰን ስለማይችል ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፡፡ በሌላም በኩል ከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 165438 ተከሳሽ አላግባብ ግብር የወሰነብኝ በመሆኑ ኪሳራ ይከፈለኝ በሚል ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ብሎ መዝገቡን የዘጋው በመሆኑና ውሳኔውን በይግባኝ ሳያሽሩ የገንዘብ መጠን ከፍ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይዘው መቅረባቸው አግባብ አይደለም፡፡ የተጠየቀው ዳኝነት አንድ አይነት ሲሆን ፍ/ቤቱ ወደ ፍሬ ነገር ገብቶ

ያላከራከረ ቢሆንም በተሰጠው ብይን ይግባኝ ከማለት በቀር የገንዘብ መጠን ጨምሮ ክስ ማቅረብ አግባብ ባለመሆኑ የከሳሽ ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ በሚል ስልጣኑ ለሆነው ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኝነት ጠየቅኩ እንጂ ግብር ይነሳልኝ አላልኩም፤ ተጠሪ ለአመልካች የከለከለኝን የተሻሻለ ውሳኔ ግልባጭ ህግ እንዲሰጥ ስለሚያስገድደው እና በአስተዳደራዊ አሰራር እስከ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አዲስ አበባ ገቢዎች ባለስልጣን ሄጄ መፍትሄ ያልተገኘ ስለሆነ እንዲሁም በአስተዳደራዊ ችግር መፍትሄ የሚያፈላልገው የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ተቋም ሳይቀር ጠይቆ ፈቃደኛ አልሆነም፤ አመልካች **ያቀረብኩት አቤቱታ ጭብጥና ይዘት ሳይመረምር አመልካች የተጠሪዎች ጥፋት የተሻሻለ ውሳኔ መከልከላቸው እና ይህም ወደ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እና ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቅሬታዬን** እንዳላቀርብ ምክንያት በመሆናቸው ለጉዳቱ ሀላፊነት ይወስዳሉ የሚል ሲሆን ፍ/ቤቱ አመልካች የግብር ይነሳልኝ እና የግብር ስሌት ይታይልኝ ዳኝነት የጠየቅኩ በማስመሰል የግብር ጉዳይ የማየት ስልጣን የለኝም ሲል የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ የክስ ጉዳይ በሌላ ፍ/ቤት ታይቷል የሚባለው ፍ/ቤቱ ስልጣኑ ሆኖ ከሳሽ እና ተከሳሽን አከራክሮ ብይን የሰጠበት ጉዳይ ብቻ ሲሆን የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የጉዳዩን ስረ ነገር ሳያይ ስልጣኔ አይደለም ሲል ብይን በመስጠቱ አመልካች ክሴን አሻሽዬ ስልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚያግደኝ ህግ የለም፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የስረ ነገር ጉዳዩን ያለማየቱን እና ስልጣኑ ያለመሆኑን ጠቅሶ መዝገቡን እንደዘጋው ከሰጠው ብይን ማየት እየቻለ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊየን) ኪሳራ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለቱ የሰበር አመልካች ለቀጣይ ፍ/ቤት የጉዳት ኪሳራ ይከፈለኝ ጥያቄ ማቅረባቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 ድንጋጌን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 25/06/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ አመልካች በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በከፍተኛው ፍ/ቤት ያቀረበው ክስና የጠየቀው ዳኝነት በግልጽ እንደተቀመጠው የብር መጠን ከማበላለጥ ውጭ ግብር አላግባብ መወሰኑ ጋር ተያይዞ ለደረሰባቸው ካሳና ኪሳራ ይከፈለኝ የሚል በመሆኑ የሁለቱም ክርክሮች ሥረ ነገርና የተያዘው ጭብጥ ተመሳሳይ በመሆኑ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ነው በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጉ አግባብ ነው፡፡ አመልካች

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ፍ/ቤቱ የቀረበውን የ1,000,000 (አንድ ሚሊየን) ብር ካሳና ኪሳራ ጥያቄ ፍ/ቤቱ ከ500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ብር በላይ የማየት ስልጣን የለኝም ብሎ ብይን የሰጠ አስመስሎ ፍ/ቤቱን ለማሳሳት አቀረቡ እንጂ በዚህ አግባብ ውሳኔ አልተሰጠም፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ያቀረቡት ዳኝነትና ጭብጥ ተጠሪ ግብር አላግባብ በመወሰን የንግድ ስራ እንዳቆም በማድረጉ ይህን ተከትሎ ለደረሰብኝ ኪሳራና ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል ሲሉ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊየን) እና ለከፍተኛ ፍ/ቤት የብር 4,497,685.00 (አራት ሚሊየን አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ አምስት) የካሳ መጠኑን ጨምሮ ተመሳሳይ ዳኝነት በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊነቀፍ አይገባም ተብሎ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን አጠናክረው የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231(1) ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ በክሱ አቤቱታ ላይ የተገለፀው ነገር የማያስከስስ ሆኖ ሲያገኘው፤ እንዲሁም በክሱ ላይ የተገለፀው ጉዳይ ከፍርድ ቤቱ ሥልጣን ውጪ መሆኑን ሲረዳው የቀረበለትን የክስ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብሎ በመወሰን ሊመልስ ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ መወሰኑ ከሳሽ ክሱን አሻሽሎና አስተካክሎ እንዳያቀርብ የሚከለክል አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 232(2) በግልጽ እንደተመለከተው በቁጥር 231 በተመለከተው መሰረት ክሱ ተቀባይነት የለውም መባሉ ወይም መሰረዙ ከሳሽ ክሱን አሻሽሎ እና የጎደለውን አሟልቶ በዚያው ነገር እንደገና ክስ ከማቅረብ የሚያግደው አይሆንም፡፡

በሌላም በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5(1) በግልጽ እንደተመለከተው በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥ እና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሳይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌደራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ከመዝጋቱ በቀር በፍሬ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ውሳኔ አለመኖሩ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠየቀው ዳኝነት አስቀድሞ ከቀረበው ጋር አንድ አይነት ነው፤ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ፍሬ ነገር ገብቶ ያላከራከረና በፍሬ ጉዳዩ ውሳኔ ያልሰጠ ቢሆንም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጉ ከፍ ሲል የተገለፀውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5(1) ትክክለኛ ይዘት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ውሳኔው ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይህን ሳያርም ማለፉ የሚነቀፍ ነው፡፡

በሌላም በኩል የስር ፍርድ ቤት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ አላግባብ የተወሰነ ግብርን ተንተርሶ የደረሰ ኪሳራ ለማስከፈል የቀረበ ቢሆንም ኪሳራውን ለማስከፈል ግብሩ አላግባብ ተወስኗል ወይስ አልተወሰነም የሚለውን ለማየት ፍ/ቤቱ ስልጣን የሌለው በመሆኑ ይህን ተከትሎ የደረሰ ኪሳራ ለመወሰን ቀድሞ ጥፋት ባልተረጋገጠበት ሊወሰን ስለማይችል ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለትም ወስኗል፡፡ ይሁንና ለጉዳቱ ተጠሪ ሀላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጭብጥ የግራቀኙ ዝርዝር ክርክርና ማስረጃ ከቀረበ በኋላ የሚወሰን ከመሆኑም በላይ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ፍርድ ቤቱ የግብር ስሌትን መሰረት አድርጎ እንዲያርም የቀረበ አይደለም፡፡ ኪሳራ ለማስከፈል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ሲሆን መሰል የዳኝነት ጥያቄን ተቀብሎ ዳኝነት ሊሰጥ የሚችል ሌላ የዳኝነት አካል በሌለበትና የፍርድ ቤቱ ስልጣንም በቀጥታም ይሁን በግልጽ ባልታገደበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መወሰኑ የሚነቀፍ ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች ክሱን ውድቅ በማድረግ ያሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 199733 በቀን 27/05/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 202785 በቀን 09/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ቀሪውን ክርክር መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341/1/ መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.201886

ሚያዚያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡-....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡........አቶ ታዬ ሰይፉ መኩሪያ ------ የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡.......1. ሚች ወ/ሮ ስርጉት ተፈራ ወራሾች ከ2ኛ--4ኛ ተጠሪዎች

2. አቶ የሺጥላ ሰይፉ መኩሪያ

3. ወ/ሮ አባይነሽ ሰይፉ መኩሪያ

4. አቶ ዓለማየሁ ሰይፉ መኩሪያ

(ተጠሪዎች 1–4፡ የቀረበ የለም)

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የዉርስ ሀብት ይጣራልኝ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.194893 በ27/2/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ሟች አባቴ አቶ ሰይፉ መኩሪያ በሕይወት እያለ ከሟች አባቱ አቶ መኩሪያ እምሩ በዉርስ የተላለፈለትን በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 ዉስጥ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር 128 ስፋቱ 1300 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈዉን የመኖሪያ ቤት ያለዉ ሲሆን፣ በተከሳሾች መካከል በነበረን ጥብቅ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነት ምክንያት ሳይከፋፈል የቆየዉን 1ኛ እና 4ኛ ተከሳሽ ከሕግ ዉጭ በድብቅ ተከፋፍለዉ ወደ ስማቸዉ በማዞራቸዉ የዉርስ ሀብቱ ተጣርቶ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መቃወሚያ ከሳሽ ያቀረበዉ ክስ በይርጋ የታገደ ስለሆነ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክረዋል፤ በአማራጭ ክርክር አከራካሪዉን ቤት 1ኛ ተከሳሽ የሰሩት፣ ግብር የሚገብሩበትና ካርታ በስማቸዉ ተሰጥቷል፤ ስፋቱ 875 ካ.ሜ ይዞታ ደግሞ በሊዝ ሕግ መሰረት ለኢንቨርስትመንት ለ4ኛ ተከሳሽ ከሚመለከተዉ አካል የተሰጠዉ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች ከሳሽ ያቀረበዉ ክስ በይርጋ ታግዷል በማለት ዉድቅ ያደረገ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.111958 በ29/10/2007 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና በማየት ከሳሽ ያቀረበዉ የዉርስ ይጣራልኝ ክስ በተመለከተ ተከሳሾች ያነሱት የይርጋ መቃወሚያ በግራ ቀኙ መካከል ባለዉ ቤተሰባዊ ግንኙነት በመከባበር ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.1853 (1) መሰረት ተቋርጧል ወይስ አልተቋረጠም? የሚለዉ በማስረጃ ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በመለሰዉ መሰረት የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮች በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በነበራቸዉ ዝምድና እና መከባበር መሰረት ይርጋዉ የተቋረጠ ነዉ በማለት መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ ዉርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዉርስ አጣሪ የሚችን የዉርስ ሀብት በማጣራት ሪፖርት እና ጉዳዩን በማጣራት አከራካሪዉ ቤት እና ይዞታ የሟች አቶ ሰይፉ መኩሪያ እና የወ/ሮ ስርጉት ተፈራ የጋራ ሀብት በመሆኑ፣ ግማሹ የ1ኛ ተከሳሽ (ወ/ሮ ስርጉት ተፈራ) እና ግማሹ ደግሞ ከሳሽን ጨምሮ ከ2ኛ--4ኛ ተከሳሾች 1/4ኛ ድርሻ አላቸዉ በማለት ሪፖርቱን በማጽደቅ ወስኗል፡፡

ተከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከሳሽ ያቀረበዉ ክስ 1ኛ ተከሳሽ በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.1853 (1) መሰረት በይርጋ ቀሪ አልሆነም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነዉ፤ ነገር ግን 2ኛ--4ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.1853 (1) መሰረት ይርጋ የሚያቋርጥ ምክንያት መኖሩን ከሳሽ በማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑ እነርሱን በተመለከተ የከሳሽ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል፤ በከሳሽ እና በ1ኛ ተከሳሽ መካከል ያለዉን ክርክር ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻሻል ለሥር ፍ/ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡

ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ በትዕዛዝ በመሰረዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ጥቅምት 15 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታዬን አቅርቤ የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የሥር ፍ/ቤት መዝገብ እንዲመጣ ትዕዛዝ በመስጠት፣ ቅሬታዬ ለመስማት ለህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም ቀጠሮ የሰጡኝ ሲሆን አመልካች በቀጠሮዉ ሲቀርብ መዝገቡ ለችሎት ሳይቀርብ በመቅረቱ ችሎት ጸሐፊ ሲጠይቅ መዝገቡ በ17/2/2013 ዓ.ም ለችሎት እንደቀረበ እና በእኔ አለመቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ ለ27/2/2013 ዓ.ም ተሰጥቶ አሁንም አመልካች ባለመቅረቡ ይግባኙን የመስማት መብት ታልፎ መዝገቡ ተመርምሮ ይግባኙ አያስቀርብም ተብሎ መዝገቡ እንደተዘጋ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ስህተት የተፈጠረዉ በሬጅስትራር ክፍል የተጨመረዉ ሰዉ ቀጠሮዉን እንዳዛባዉና ስህተቱ

የፍ/ቤቱ መሆኑን መግለጫ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ረገድ በአመልካች ምክንያት የተፈጠረ ስህተት የለም፡፡ አመልካች ይህን በመጥቀስ ለፍ/ቤቱ አቤቱታ ያቀረብኩኝ ቢሆንም መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ በመሆኑ አቤቱታዉ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ጥፋት ባልሆነ ምክንያት ቅሬታዬን የማሰማት መብቴ መታለፉ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የማያስችልና የምስክሮችን ቃል መርምሮ መዝኖ ትክክለኛ ዉሳኔ የማግኘት መብቴን የሚያጣበብ ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከማስረጃ ምዝና አንጻር የምስክሮችን ቃል ዘርዝሬ ባቀረብኩት ቅሬታ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሥር መዝገብ ሳይቀርብና ሳይመረመር በደፈናዉ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች ያቀረብኳቸዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች ከሁሉም ተጠሪዎች ጋር የመከባበርና የመፈቃቀር ግንኙነት እንዳላቸዉ አረጋግጠዉ እያለ የሥር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1853 (1) መሰረት ይርጋ የተቋረጠዉ ከ1ኛ ተጠሪ በተመለከተ እንጂ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር አይቋረጥም በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲሻርልኝ፣ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት ታህሳስ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ አመልካች ባቀረበዉ ቅሬታ ይግባኛቸዉን ሳያሰሙ የታለፉት በቀጠሮ መሳሳት ምክንያት መሆኑን፣ ስህተቱም በሬጅስትራር የተፈጸመ እንጂ በችሎት አለመሆኑን አረጋግጠዉ ያቀረቡ ቢሆንም ሬጅስትራር ጥፋት ፈጽመዉ ከተገኘ በአስተዳደር ከሚያስጠይቅ በቀር እንደ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተቆጥሮ በሰበር የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረቡትን የምስክሮች ቃል በመመርመር በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ይርጋዉን የሚያቋርጥ ምክንያት መኖሩን እንጂ ከ2ኛ--4ኛ ተጠሪዎች በተመለከተ አልተመሰከረም በማለት ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ ጉዳዩ የምስክሮች ቃል የማስረጃ ምዘና ሆኖ ባለበት አቤቱታዉ ያስቀርባል መባል አልነበረበትም፡፡ በመሆኑም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍቤት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አቤቱታዉ ዉድቅ ሆኖ ዉሳኔዉ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ሚያዚያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፤የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ካቀረበዉ የይግባኝ ማመልከቻ ጋር የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ተያይዞ ባልቀረበበት፣ የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የሥር መዝገብ እንዲቀርብ የሰጠዉ ቀጠሮ ሳይደርስ፣ ለአመልካች ቀጠሮዉ ተነግሮት ባላወቀበት በቀጠሮ ባለመቅረቡ የመሰማት መብቱ ታልፏል በማለት የይግባኝ ቅሬታዉን በትዕዛዝ በመሰረዝ ያሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ መሰረት አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.231500 ጥር 22 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ ማመልከቻ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የመ.ቁ.194893 በመክፈት፣ የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር በ26/12/2012 ዓ.ም በተጻፈዉ ደብዳቤ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ.87486 እና የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ.231500 የሆኑት መዛግብት በ7/3/2013 ዓ.ም ከሆነዉ ቀጠሮ በፊት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 3ኛ ፍትሐ ብሔር ችሎት እንዲላክልን፣ በቀጠሮ ላይ ከሆነ የመዝገቡ ግልባጭ እንዲላክልን በማለት መጠየቁን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ተፈላጊዎቹ የሥር ፍ/ቤቶች መዛግብት ወይም የመዛግብቱ ግልባጭ መቅረቡን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡

ከሥር መዝገብ ማየት እንደሚቻለዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በ17/2/2013 ዓ.ም በሰጠዉ ትዕዛዝ መዝገቡን መርምሮ ቅሬታዉን ለመስማት ለ27/2/2013 ዓ.ም ቀጠሮ መስጠቱን ያመለክታል፡፡ በዚህ መሰረት ፍ/ቤቱ በ27/2/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት አመልካች ባለመቅረቡ ቅሬታቸዉን መስማት ባለመቻሉ ቅሬታዉን የማሰማት መብታቸዉ ታልፏል፡፡ በመቀጠል ፍ/ቤቱ የይግባኝ ቅሬታዉን በመመርመር ባሳለፈዉ ትዕዛዝ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በፍሬ ነገርም ሆነ በሕግ ረገድ ጉድለት ያልተገኘበት ስለሆነ ቅሬታዉን ባለመቀበል ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት መዘጋቱን የትዕዛዙ ግልባጭ ያሳያል፡፡

እንደሚታወቀዉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ የሚባልበትን ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ዉሳኔ ወይም ፍርድ ያሳለፈዉ እንደሆነ ይግባኝ ባይ ቅሬታዉን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማቅረብ የሚገባዉ የፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት የይግባኝ ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.327 ሥር የተመለከቱትን ነገሮች አሟልቶ መቅረብ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 327 (2) መሰረት ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የሰጠዉ ፍ/ቤት የመዝገብና የፍርድ ግልባጭ ትክክል ግልባጭ ለመሆኑ ታትሞበትና ተፈርሞበት ከይግባኝ ማመልከቻ ጋር ተያይዞ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንግዲህ በዚህ መልክ የይግባኝ ማመልከቻዉ በሕጉ የተመለከቱትን ነገሮች አሟልቶ የቀረበ እንደሆነ፣ የይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩ ወይም ጠበቃዉ የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያዉ ደረጃ ፍ/ቤት ፍርድ የሰጠበትን የመዝገብ ግልባጭ መርምሮ ፍርዱ ጉድለት የሌለበት መሆኑን ከተረዳዉ መልስ ሰጭዉን ሳይጠራ ይግባኙን ዘግቶ ይግባኝ ባዩን ማሰናበት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት የይግባኝ ማመልከቻዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.327 መሰረት ተሟልቶ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ወይም የመዝገቡ ግልባጭ ጋር ተያይዞ ከቀረበለት በኋላና የይግባኝ ባዩን ቅሬታ በመስማት የይግባኝ ባይ ቅሬታን ከሥር ፍ/ቤት የመዝገብ ግልባጭ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍሬ ነገርም ሆነ በሕግ ረገድ ጉድለት የሌለበት መሆኑን የተገነዘበ እንደሆነ መልስ ሰጪዉን ማስቀረብ ሳያስፈግል የይግባኝ ማመልከቻዉን በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቶ

ይግባኝ ባዩን ማሰናበት እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ወይም የመዝገቡ ግልባጭ ሳይቀርብለትና ለይግባኝ ባይ በግልጽ የተነገረዉን ቀጠሮ እያወቀ ካልቀረበ በስተቀር ይግባኝ ባዩን ስለቅሬታዉ ሳይሰማ ጉዳዩን መርምሮ የይግባኝ ማመልከቻዉን መሰረዝ የህግ ድጋፍ የሌለዉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያሳለፈዉ ፍርድ በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻዉን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የሥር ፍ/ቤቶች መዛግብት ወይም የመዛግብቱ ግልባጭ ከህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም ቀጠሮ በፊት እንዲቀርብ የጠየቀ ሲሆን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እነዚህ ተፈላጊዎቹ የሥር ፍ/ቤቶች መዛግብት ሳይቀርቡ፣ በሬጅስትራር በኩል ለአመልካች የተሰጠዉ ቀጠሮ ህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም ሳይደርስ፣ ችሎቱ በጥቅምት ወር ዉስጥ ቀጠሮ መያዙ ለአመልካች በግልጽ የተነገረ መሆኑን የሚያመለክት ነገር ሳይኖር፣ መዝገቡ ለችሎቱ በጥቅምት 17 እና 27 ቀን 2013 ዓ.ም ቀርቦለት አመልካች ባለመቅረቡ ቅሬታዉን መስማት አለመቻሉን፣ ቅሬታዉን የመሰማት መብቱ በዚህ ምክንያት መታለፉን በመጥቀስ፣ የይግባኝ ማመልከቻዉን አያስቀርብም በማለት በመሰረዝ ትዕዛዝ መስጠቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ከዚህ የሚንገነዘበዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበዉ የይግባኝ ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.327 (2) መሰረት ከሥር ፍ/ቤቶች የመዛግብት ወይም የመዛግብቱ ግልባጭ ጋር ተያይዞ ባልቀረበለት፣ መዝገቡ በጥቅምት ወር 2013 ዓ.ም ዉስጥ የተቀጠረ መሆኑን በግልጽ ለአመልካች መነገሩ ባልተረጋገጠበት፣ አመልካች ለህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም እንዲቀርብ በሬጅስትራር በኩል ቀጠሮ ተሰጥቶት ከሄደ በኋላ ፍ/ቤቱ አመልካቹ ቀጠሮን ባላወቀበት ሁኔታ በቀጠሮ ባለመቅረቡ ቅሬታዉን መስማት አለመቻሉንና ቅሬታዉን የማሰማት መብቱም መታለፉን በመጥቀስ ይግባኙን አያስቀርብም በማለት በመሰረዝ ያሳለፈዉ ትዕዛዝ ከፍ ሲል የተጠቀሱት የህግ ድንጋጌ የሚቃረን ጉዳይ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበዉን የይግባኝ ማመልከቻ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች መዛግብት ተያይዞ ባልቀረቡለት፣ ለአመልካችም የተነገረዉ ቀጠሮ ለህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም ሆኖ ሳለ፣ አመልካች በችሎቱ የተያዘዉ ቀጠሮ በግልጽ ተነግሮት የሚያዉቅ መሆኑን የሚያመለክት ነገር በሌለበት፣ አመልካቹ ወይም ጠበቃዉ ቅሬታዉን ባላሰማበትና የይግባኝ ቅሬታዉን ከሥር ፍ/ቤቶች መዛግብት ጋር ተገናዝቦ ባልተመረመረበት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ጉድለት የለዉም፣ የይግባኝ ማመልከቻዉ አያስቀርብም በማለት በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቶ አመልካችን ማሰናበቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.194893 በ27/2/2013 ዓ.ም ያሳለፈዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ መሰረት የሥር ፍ/ቤቶች መዛግብት ወይም የመዛግብቱ ግልባጭ እንዲቀርብ በማድረግ አመልካች ያቀረበዉን ቅሬታ ለመስማት ለአመልካቹ በግልጽ የተነገረዉን ቀጠሮ በመስጠቱ፣ አመልካቹ ወይም ጠበቃዉ ስለይግባኝ ቅሬታዉ በመስማት፣ የይግባኝ ቅሬታዉን ከሥር ፍ/ቤቶች መዛግብት ጋር በመመርመር፣ የይግባኝ ማመልከቻዉ ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም? በሚለዉ ጉዳይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

አ/መ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 203290

ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም

***ዳኞች***:- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘቢደር ከበደ አማረ - አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ መኩሪያ አለሙ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አወል ሼይቶ - ቀርቧል

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

አመልካች የተጠሪ አባት አከራካሪውን መሬት ለሟች ባለቤት በ1991 ዓ/ም ኪራይ ሰጥቶ ህይወቱ ካለፈ ከ18 ዓመት በኋላ መሬቱን እንድትለቅ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ያቀረበችው መቃወሚያ ያለበቂ ምክንያት ታልፎ ሟቹ የተጠሪ አባት ያልነበረውን የይዞታ መብት ተጠሪ እንዲወርስ መወሰኑ የህግ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑም በላይ አላግባብ መሬቱ የተገኘው በግዥ እና ሽያጭ ነው በማለት አመልካችን ከይዞታዋ ላይ በማፈናቀል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በመባሉ መዝገቡ ለችሎት ቀርቦ ታይቷል።

ጉዳዩ የገጠር መሬት ይዞታ ወራሽነትን የሚመለከት ሆኖ ክሱ በቀረበበት የደሎ መና ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ አመልካች ተከሳሽ ነበሩ። ተጠሪ በደሎ መና ወረዳ ፍርድ ቤት መገኛው እና አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተገለፀው 16 ጥማድ የሆነ የአመልካች ባለቤት ከሟች አባቱ በኮንትራት ወስዶ ሲያርስ የነበረውን መሬት ከሐምሌ ወር 2011 ዓ/ም ከባሏ ሞት በኋላ አመልካች ምንም መብት ሳይኖራት አርሶ እንዳይጠቀም በማድረግ ይዞታዬ ነው በማለት በኃይል የያዘችውን የሟች አባቴን ይዞታ ትልቀቅልኝ በማለት ሐምሌ 20 ቀን 2012 ዓ/ም የተፃፈ ክስ አቅርቧል። አመልካችም ለክሱ በሰጠችው ምላሽ ሟች የአመልካች አባት ለሟች ባለቤቷ ሐምሌ 19 ቀን 1991 ዓ/ም እና ህዳር 7 ቀን 1995 ዓ/ም በተፃፈ ውል አቅሙ ደክሞ ማረስ ስለማይችል ***የድካሙን ሰጥቶት*** መሬቱን እንዲወስድ ባደረጉት ስምምነት ሰጥቶት እንጅ በጉልበት አለመያዟን በመግለፅ ፣ በአጠቃላይ መሬቱ ከ18(አሥራ ስምንት ዓመት) በላይ በእጃቸው የቆየ በመሆኑ የቀረበባት ክስ ውደቅ ሆኖ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቃለች።

ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ መዝገቡን እንደመረመረው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት የተጠሪ አባት መሆኑ እና በአመልካች እጅ መኖሩ በማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ

ሟች የተጠሪ ባል የሟች የተጠሪ አባት የቤተሰብ አባል ባለመሆኑ በሕጉ አግባብ መሬት በስጦታ የሚተላለፍለት ባለመሆኑ፤ የሟች አባቱ የመሬት ይዞታ በውርስ ለተጠሪ የሚተላለፍ በመሆኑ አመልካች ከሕግ ውጭ አላግባብ የያዘችውን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ እንደትለቅለት ወሰኗል። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ባቀረቡት ይግባኝ ጉዳዩን ያየው የባሌ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ሟች አባቱ ለሟች የአመልካች ባል በኮንትራት ሰጥቷል በማለት ያቀረበውን ክርክር በማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑ የክርክሩ ይዞታ አስቀድሞ የሟች የተጠሪ አባት ቢሆንም ለረዥም ጊዜ ከእጁ ወጥቶ በአመልካች እና በባሌበቷ እጅ ገብቶ ሲጠቀሙበት የቆዩ ስለሆነና በአመልካች በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ በአመልካች ባል እና በተጠሪ አባት መካከል የተደረገው ውል የስጦታ ወይንም የግዥ እና ሽያጭ እንደሆነ አያሳይም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ማግኘቱን ገልፆ፤ በኮንትራት ሳይሆን ባልታወቀ መንገድ ከ1990ዎቹ አንስተው አመልካች እና ባለቤቷ ሲጠቀሙበት የነበረውን መሬት ሊለቅ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያው ታልፎ አከራካሪውን የመሬት ይዞታ እንድትለቅ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል። አከራካሪውን መሬት ሟች የመልስ ሰጭ ባለቤት የያዘው በግዥ እና ሽያጭ ውል መሆኑ ታውቆ እያለ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉን በመቃወሜ ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ ጉዳዩን ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ቋሚ ችሎት፤ ክርክር የተነሳበት መሬት የገጠር መሬት ይዞታ መሰረቱ የሟች የተጠሪ አባት ሆኖ ሟች የተጠሪ አባት በ1995 ዓ/ም በ750.00(ሰባት መቶ ሃምሳ) ብር ተቀብሎ ለሟች የአመልካች ባለቤት ያስተላለፈ መሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ ማስተዋሉን ገልፆ፤ የገጠር መሬት ግዥ እና ሽያጭ ውል በሕገ መንግስቱም ሆነ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጁ ሕገ ወጥ ድርጊት በመሆኑ በዚህ አግባብ የተያዘ መሬትን ለማስለቀቅ የሚቀርበው ክስ በይርጋ የማይታገድ ሆኖ እያለ፤ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ማለቱ ስህተት ነው በማለት የደሎ መና ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል።

አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ በመሰረዙ ያቀረበችውን በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ ፤ የተጠሪ አባት መጠቀም ያቆመውን አከራካሪውን መሬት አመልካች ለረዥም ዓመት ሲጠቀሙበት እንደነበረ በሥር ፍርድ ቤት በተረጋገጠበት ሁኔታ የሽያጭ ውል ባልቀረበበት አከራካሪው መሬት በ750.00(ሰባት መቶ ሃምሳ) ብር ተሸጧል ተብሎ ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም የመባሉ አግባብነት መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በመልሱ፡- አመልካች አከራካሪው መሬት የሟቹ የተጠሪ አባት መሆኑን አምና ሟቹ ለቆልናል በማለት ያቀረበችው ውል ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ እና አመልካች ያቀረበችው የሽያጭ ውል ሟች የተጠሪ አባት ያልፈረሙት የሀሰት በመሆኑ ፤ እንዲሁም ያቀረበችው ክርክር ተአማኒነት ባለው ማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ በይዞታው ላይ የባለቤትነት መብት የሌላት የእኩል አራሽ ሆና ከ2010 ዓ/ም ጀምሮ አላግባብ የያዘችውን ይዞታ እንድትለቅ የቀረበው ክስ በይርጋ

ቀሪ ነው በማለት ያቀረበችው ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቶ ወጪ እና ኪሳራ እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡ አመልካችም አከራካሪውን መሬት በግዥ እና ሽያጭ አግቻለሁ የሚል መከራከሪያ ባላነሳችበት እና በጭብጥነት ባልተያዘ ጉዳይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሬት ሽያጭ ውል ተፈፅሟል ማለቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚመራው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌ ተከትሎ ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር ክርክርን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባልጠየቁት ጉዳይ ላይ ዳኝነት መስጠት የማይችል መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 182(2) ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበው ክስ አስቀድሞ በኮንትራት የአመልካች ባለቤት ይዞት የነበረው እና ከባለቤቷ ሞት በኋላ በጉልበት የያዘችውን የሟች አባቱ የሆነ በውርስ ለእሱ ሊተላለፍ የሚገባውን የገጠር መሬት ይዞታ እንድትለቅለት ላቀረበው ክስ፤ አመልካች ሟች የአመልካች አባት ለሟች ባለቤቷ ሐምሌ 19 ቀን 1991 ዓ/ም እና ህዳር 7 ቀን 1995 ዓ/ም በተፃፈ ውል መሬቱን ለማረስ አቅመ ደካማ በመሆኑ ***የድካሙን ሰጥቶት*** መሬቱን እንዲወስድ ባደረጉት ስምምነት የሰጠው እንጅ በጉልበት አለመያዟን እና መሬቱም ከ18(አሥራ ስምንት ዓመት) በላይ በእጃቸው የቆየ በመሆኑ የቀረበባት ክስ ውደቅ ሊሆን ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርባለች፡፡ ከቀረበው ክስም ሆነ ተጠሪ ከሰጠው መልስ መረዳት የሚቻለው ግራ ቀኙ በግልጽ ሕገ ወጥ የገጠር መሬት ግብይትን አስመልክቶ የጠየቁት ዳኝነት የሌለ ሲሆን ፤በአመልካች በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ በአመልካች ባለቤት እና በተጠሪ አባት መካከል የተደረገው ውል የስጦታ ወይንም የግዥ እና ሽያጭ መሆኑን እንደማያሳይ የደሎ መና ወረዳ ፍርድ ቤት የደረሰበት የፍሬ ነገር መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡ የገጠር መሬት ይዞታ ግዥ እና ሽያጭን አስመልክቶ ግልጽ ዳኝነት ተጠይቆ ፣ ክርክር ተደርጎ ፣ አከራካሪው ጭብጥ ተለይቶ በማስረጃ ተጣርቶ ተገቢ መደምደሚያ ላይ መደረስ ሲገባ፤ የዶሎ መና ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪው መሬት አመልካች እጅ የገባው በኮንትራት ውል ነው ወይስ በስጦታ? በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ እና ግብር በማን ስም እንደሚከፈል የያዘውን ጭብጥ ለማጣራት ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ የአመልካች 1ኛ ምስክር አከራካሪውን መሬት ሟች የአመልካች ባለቤት 750.00(ሰባት መቶ ሃምሳ) ብር ሰጥቶ ከሟች የተጠሪ አባት በስጦታ ማግኘቱን የመሰከረ ሲሆን ፤ የወረዳ ፍርድ ቤቱ ግልጽ ዳኝነት ያልተጠየቀበትንና አከራካሪ ጭብጥ ያልሆነውን የመሬት ሽያጭ እና ግዥ ጥያቄ ወደጎን በመተው ሟች የአመልካች ባለቤት የሟች የተጠሪ አባት የቤተሰብ አባል ባለመሆኑ በስጦታ የገጠር መሬት ማግኘት አይችልም በማለት ወስኗል፡፡ አከራካሪው መሬት የሟች የተጠሪ አባት የነበረ መሆኑ በአመልካችም ያልተካደ ሲሆን በማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ያቀረበችው ይርጋ መቃወሚያ መታለፉን በመቃወም ባቀረበችው ይግባኝ የባሌ

ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች እና ባለቤቷ ባልታወቀ መንገድ ከ1990ዎቹ አንስቶ አከራካሪውን መሬት ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ አመልካች አከራካሪውን መሬት እንድትለቅ መወሰኑ አግባብነት የለውም ማለቱ ከተጠየቀው ዳኝነት አንፃር ተገቢ ሆኖ እያለ ፤ አከራካሪውን መሬት ሟች የአመልካች ባለቤት የያዘው በግዥ እና ሽያጭ ውል መሆኑ ታውቆ እያለ በይርጋ ይታገዳል መባሉን በመቃወም ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ጉዳዩን ያየው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ምድብ ቋሚ ችሎት ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ባየው የደሎ መና ወረዳ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በይግባኝ ደረጃ መነሳቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329(1) ድንጋጌን የሚፃረር ሆኖ እያለ ፤ተጠሪ የገጠር መሬት ይዞታ ግዥ እና ሽያጭን የሚመለከት ክርክር እና ማስረጃ ባላቀረበበት አንድ የአመልካች ምስክር የአመልካች ባለቤት 750.00(ሰባት መቶ ሃምሳ) ሰጥቶ ከሟች የተጠሪ አባት በስጦታ አከራካሪውን መሬት አግኝቷል የሚል ምስክርነት ሰጥቷል በማለት መወሰኑ እንዲሁም የሰበር አጣሪ ችሎቱም ስህተቱን ማረም ሲገባው በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ወድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 335556 የካቲት 16 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ምድብ ቋሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 325933 ጥር 27 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት **ተሽሯል፡፡**
2. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31529 ህዳር 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት **ፀንቷል፡፡**
3. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ውጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

**ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ**

በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ የአሁን አመልካች የአባቴ የመሬት ይዞታ የሆነውን በኮንትራት ወስደው አልመልስ ስላሉኝ ይመልሱልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን አመልካችም ክስ የቀረበበት የመሬት ይዞታ አባቴ የሚገባኝን ሰጥታችሁኝ ውሰዱ ብሎ ለባለቤቴ የሰጠው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ነው ስትል ተከራክራለች፡፡ የስር ፍ/ቤቶች አከራክረው ያከራከረው የመሬት ይዞታ የአሁን ተጠሪ

አባት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ያከራከረው መሬት በአሁን አመልካች እጅ የገባው በሽያጭና ገኘ ውል መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ የአሁን አመልካች ምስክሮች ጭምር ያከራከረውን መሬት በግዥ የያዘችው መሆኑን መስክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች ሟች ተገቢውን ሰጥታችሁኝ ውሰዱ የሚል መልስ ጭምር ሽያጭ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤቶች በሽያጭ የመሬት ይዞታ ማስተላለፍ ህገ መንግስቱንና የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የሚቃረን በመሆኑ የአሁን አመልካች እንድትለቅ ሲሉ ወስነዋል፡፡ የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርባለች፡፡

የከተማም ይሁን የገጠር የእርሻ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑን የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) ደንግጎ ይገኛል፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 (4) መሰረት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከመሬታቸዉ ያለመነቀል መብታቸዉ የተከበረ መሆኑንም ይደነግጋል፡፡ የክልሉ ህገ መንግስት እና የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ መሰረት መሬት የማይሸጥ መሆኑ የተደነገገና ይህም ድንጋጌ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ከወጣ ጊዜ ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ ከዚያን ጊዜ በፊትም በደረግ መንግስትም ቢሆን መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ የገጠር መሬት ክርክርም ሊዳኝ የሚገባው በመሬት አዋጅ መሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ ይህ ሆኖ አንድ ሰው መሬት እንደማይሸጥ እያወቀ ከህጉ ድንጋጌ ውጪ ህገ መንግስቱን በመጻረር መሬት የገዛ ከሆነ ህገ ወጥ ድርጊት ወይም ውል እየፈጸመ መሆኑን ያውቃል፡፡ የመሬት ሽያጭ ውሉ ህገ ወጥ ውል በመሆኑ መሬቱም ለባለመሬቱ (ለባለይዞታው) እንደሚመለስም ያውቃል፡፡ የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም መሬትን በሽያጭ፣ ህግ በሚደነግገው ውጪ ማስተላለፍ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(4) የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን ውሳኔ ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ ይህ የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ም/ቤት ውሳኔ ፍ/ቤቶች የመሬት ክርክርን በይርጋ ውድቅ በማድረግ የሰጡትን ውሳኔ ህገ መንግስቱን የሚጻረር በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ሲል የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79394 ላይ በሰጠው ውሳኔ በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻውም ውጤት የሌለውና ፈራሽ መሆኑን፣ የውሉ መሰረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ በመሆኑ በዚሁ መሰረት የአሁን አመልካች መሬቱን እንድትለቅ መወሰኑ ተገቢ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሊጸና ይገባል እላለሁ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር 196255

ቀን 25/4/2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- ወ/ሮ ክላሪስ ዴኒስ ቶምሰን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ት ቤቴልሄም አስራት - ጠበቃ መላኩ አድነው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መስከረም 21 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 176059 ሰኔ 26 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የይርጋ መቃወምያዬን ውድቅ ያደረገው ይርጋ የሚያነሳው የመቃወሚያ ተጠሪ እንጂ የመቃወሚያ አመልካች አይደለችም በሚል አረዳድ ሲሆን የመቃወሚያ አመልካች በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ጣልቃ ገብታ ስትከራከር የመቃወሚያ ተጠሪን አቤቱታ በመቃወም በመሆኑ አመልካች እንደሚቀርብባት አቤቱታ መወሰድ ነበረበት፡፡ የመቃወሚያ ተጠሪ ማስረጃውን የወሰደችው ከ3 ዓመት በኋላ በመሆኑ ማስረጃዋ በይርጋ ሊሰረዝ ሲገባ መታለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የመቃወሚያ አመልካች (የአሁን አመልካች) ባቀረበችው አቤቱታ የመቃወሚያ ተጠሪ (የአሁን ተጠሪ) በመ/ቁጥር 0100297 ላይ የተሰጣት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝልኝ፡፡ ይሄውም የመቃወሚያ ተጠሪ ማስረጃውን ለማግኘት አቤቱታ ያቀረበችው አቶ አስራት ግዛው ከሞቱ ከ4 ዓመት በኋላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የመቃወሚያ ተጠሪ የሟች አቶ አስራት ግዛው ልጅ አይደለችም፡፡ ልጅነቷንም አልተቀበለም ማስረጃዋ ውድቅ ይሁንልኝ ስትል ጠይቃለች፡፡ የመቃወሚያ ተጠሪም ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታዋን በቀጥታ ተቀብሎ ማስተናገድ አይችልም፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ማየት እንጂ ጉዳዩን በቀጥታ ማየት የማይችልና ጉዳዩን ማየት የሚችለው ማስረጃውን የሰጠው ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች አቤቱታዋን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላትም፡፡ ጉዳዩ በሌላ ፍ/ቤት እየታየ በመሆኑ አቤቱታዋ ውድቅ ይሁንልኝ፡፡ የወራሽነት ማስረጃ

የተሰጠኝ ልጅነቴን አረጋግጬ ነው፡፡ በውርስ በሚደርሰኝ ንብረቶችም እየተጠቀምኩበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡ የመቃወሚያ አመልካች የሟች አቶ አስራት ልጅ አይደለችም፡፡ ከሟች እህቶቼና ወንድሞቹ ጋር ተከራክራ የሀሰት ልጅነት ማስረጃ ወስዳለች፡፡ የወሰደችው የልጅነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ በሚል መልስ ሰጥታለች፡፡ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 0123495 ሰኔ 28 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የመቃወሚያ አመልካች ያቀረበችውን የመቃወሚያ ተጠሪ የሟች አቶ አስራት ግዛው ልጅ አይደለችም፣ የወራሽነት ማስረጃዋ ይሰረዝልኝ አቤቱታ በማስረጃ ያላስረዳች በመሆኑ የመቃወሚያ አቤቱታዋ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የመቃወሚያ አመልካች ለአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ አከራክሮ በመ/ቁጥር 01-19572 የካቲት 26 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ሟች አቶ አስራት ግዛው የሞተው በ15/4/2003 ዓ/ም ሲሆን የመቃወሚያ ተጠሪ የወራሽት ማስረጃ ይሰጠኝ አቤቱታ ለወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበችው በ7/8/2007 ዓ/ም ነው፡፡ ማስረጃው የተሰጣት በ9/8/2007 ዓ/ም ነው፡፡ የመቃወሚያ ተጠሪ ጥያቄውን ያቀረበችው ከ3 ዓመት ከ4 ወር በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1000(1) መሰረት ማስረጃ የወሰደችው ከ3 ዓመት በኋላ በመሆኑ አቤቱታዋ በይርጋ ውድቅ የሚሆን ነው፡፡ የወሰደችው የወራሽነት ማስረጃዋ ተሰርዟል ሲል የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ወስኗል፡፡ የመቃወሚያ ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ አከራክሮ በመ/ቁጥር 176059 ሰኔ 26 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የመቃወሚያ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ አቤቱታ ያቀረበችው የመቃወሚያ አመልካች አንጂ የመቃወሚያ ተጠሪ አይደለችም፡፡ የይርጋ መቃወሚያ የሚታየው ከእውነተኛ የወራሽነት ጥያቄ አንጻር አንጂ የመቃወሚያ ተጠሪ አስቀድማ ከወሰደችው የወራሽነት ማስረጃ ላይ ባለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ/ተጠሪን አቤቱታ በይርጋ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም ሲል የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ሲል መልሶለታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርባለች፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በፍርድ ቤት አስቀድሞ በተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ ላይ ተቃውሞ በሚያቀርብ አመልካች በኩል ይርጋ ሊነሳ አይገባም ተብሎ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 1000 እና 999 አንጻር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ስትል ተከራክራለች፡፡ አመልካችም መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አሁን ለዚህ

ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ምክንያት የሆነው የይርጋ ክርክር በተመለከተ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ባቀረበችው አቤቱታ ተጠሪ የሚች አቶ አስራት የወራሽነት ማስረጃ የወሰደችው ከ3 ዓመት በኋላ በመሆኑ አቤቱታዋ በይርጋ ውድቅ መሆን ሲገባ ወራሽ ነች ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ ማስረጃዋ ይሰረዝልኝ ስትል የጠየቀች ሲሆን ተጠሪም የአሁን አመልካች ላቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ በውርስ በሚደርሰኝ ንብረቶች እየተጠቀምኩበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ስትል መልስ ሰጥታለች፡፡ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ያቀረበችውን የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተ የሰጠው ብይን ስለመኖሩ ውሳኔው አያመለክትም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5(3) በቀድሞው ክርክርና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ የታለፈ እንደሆነ በዚህ ቁጥር አግባብ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ እንደሚቆጠር ደንግጎ ይገኛል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 24574 ላይ በሰጠው ውሳኔም ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የአሁን አመልካች ይርጋን በመቃወሚያነት ያቀረበችውን ክርክር የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ምንም ሳይል በማለፉ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባበት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ያቀረበችውን ይርጋ መቃወሚያ አከራክሮ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባበት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራክሮ የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሆና ካልቀረበች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ባቀረበችው አቤቱታ ይርጋን እንደመቃወሚያ ልታነሳ አትችልም በሚል ትርጉም የአሁን አመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 በክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ራሱ ወይም ጠበቃው ወይም ነገረ ፈጁ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ላማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 360(2) የመቃወሚያው ክርክር የሚሰማው የመጀመሪያው ክርክር በተሰማበት ሥነ ሥረዓት መሰረት ሆኖ ፍርድ ቤቱ ነገሩን ካጣራ በኋላ መቃወሚያ የቀረበበትን ፍርድ ለማጽደቅ ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ወይም ለመሰረዝ እንደሚችል ደንግጎ ይገኛል፡፡ ፍ/ቤቶች ክርክሩን በመደበኛው ሥነ ሥረዓት ግራ ቀኙን ሲያከራክሩ በተሰጠው ውሳኔ መብቴ ተነክቶብኛል ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ጣልቃ ገብቶ የሚከራከር ወገን መብቱ የሚነካበትን ምክንያት እና ውሳኔውን ለማስለወጥ ቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ ክርክር ውስጥ ተካፋይ ቢሆን ኖሮ ሊያነሳቸው የሚገባቸውን ክርክሮች ሁሉ አንስቶ መከራከር ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ጣልቃ ገብታ የምትከራከረው የአሁን ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተጠሪ የሚች ወራሽ ነች ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መብቷን የሚነካበትን ሁኔታ ቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ ተከራካሪ ብትሆን ኖሮ ሊታነሳ የምትችለውን መከራከሪያዎች፣ የተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝላት የሚገባበትን ምክንያቶች ሁሉ አንስታ መከራከር የሚገባትና የአሁን ተጠሪ የወራሽነት

ማስረጃ የወሰደችው አቤቱታዋን ማቅረብ በሚገባት ጊዜ ውስጥ አይደለም አቤቱታዋ በይርጋ ቀሪ መሆን ነበረበት የሚል መቃወሚያንም ጨምሮ አንስታ መከራከር የምትችል፣ ፍ/ቤቶችም አከራክረው ውሳኔ መስጠት የሚገባቸው ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ይርጋን በመቃወሚያነት ያቀረበችውን ክርክር የአሁን ተጠሪም በውርስ ንብረቱ እየተጠቀምኩበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ስትል ካቀረበችው መከራከሪያ ጋር አከራክሮ መወሰን ሲገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ጣልቃ ገብቶ የሚከራከር ወገን ይርጋን እንደመቃወሚያ አንስቶ ሊከራከር አይችልም ሲል የአሁን አመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ክርክር ውድቅ ማድረጉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358-360 ድንጋጌዎች ውጪ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 176059 ሰኔ 26 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ይርጋን በመቃወሚያነት ያቀረበችውን ክርክር እና የአሁን ተጠሪም በውርስ ንብረቱ እየተጠቀምኩበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ስትል ካቀረበችው መከራከሪያ ጋር አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መልሰንለታል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. ከስር ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት ሁኔታ ይመለስ ብለናል፡፡

5. በሰበር ሰሚ ችሎት ጥር 20 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመ/ቁጥር 19572 ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡

6. የአሁን ተጠሪ ያቀረበችው የመስቀለኛ አቤቱታ በዚህ ውሳኔ እልባት ያገኘ በመሆኑ ታልፏል፡፡

7. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

8. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ 200117

ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- 1ኛ. ወ/ሮ አታሬ አሳሌ

2ኛ. አቶ አይዲቆ ዋና

3ኛ. አቶ መንግስቱ ዋና

2ኛ አመልካች በራሳቸውና ስለሌሎችም ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሹምቡቤ ሻሬቾ

2ኛ. አቶ ዋድሎ ዋና

3ኛ. አቶ ቹቹ ዋና

4ኛ. ወ/ሮ አንድነት ዋና

5ኛ. ወ/ሮ አስቴር ዋና

6ኛ. አቶ ደሳለኝ ዋና

7ኛ. ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዋና

አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 19/04/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10475 በቀን 18/05/2012 ዓ.ም፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 47822 በቀን 12/06/12 ዓ.ም፣ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33354 በቀን 02/07/2012 ዓ.ም፤ እንዲሁም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 33561 በቀን 28/03/2011 ዓ.ም የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ጉዳዩ የውርስና የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን መሰረት ያደረገ ሲሆን የቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበለትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

መርምሮ ብይን ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ብይን ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉት ተጠሪዎች የሟች ዋና ሆንችሎ ልጆች በመሆናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው፤ በመሆኑም የውርሱ ሀብት ከዘር የወረደ እርስት በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) ድንጋጌ መሰረት አቤቱታቸው ይርጋ አያግደውም፤ የሟች አባታቸው የውርስ ሀብት ላይ መብት ያላቸው በመሆኑ እና የውርስ ተጠቃሚ በመሆናቸውም በዚህ ረገድ የቀረበው መቃወሚያም ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡ የ1ኛ ተጠሪን በተመለከተም የሟች ሚስት በመሆነቸውና ሟች ስንት ሚስቶች እንደነበሩት፣ የትና እንዴት ባለ ሁኔታ እንዳኖራቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በማስረጃ የሚጣራ መሆኑን ጠቅሶ የአሁን አመልካቾች ያቀረቧቸውን መቃወሚያዎች ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህን ተከትሎም በዋናው ፍሬ ጉዳይ ላይ ለማከራከር ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲሁም ይግባኝና የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ብይን ጉድለት የለውም ተብሎ ቅሬታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካቾች በቀን 19/04/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ አባታችን ከሞተበት ከ1983 ዓ.ም እስካሁን ድረስ 30 አመት ሙሉ ቆይተው ያቀረቡት የወራሽነት አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ የቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(2) የተደነገገውን ያለአግባብ በመተርጎም ከዘር ሀረግ የወረደ ርስት ይርጋ የለውም በማለት ያቀረብነውን መቃወሚያ በብይን ውድቅ ማድረጉ፤ ይህን ብይን የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ አቅርበን መጽናቱ ስህተት በመሆኑ እንዲሻርልን በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ክርክሩ ንብረት የርስት ስለሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(2) በይርጋ የሚታገድ አይደለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ርስት የሚለው ሀሳብ በአሁኑ ሰአት ተግባራዊ ሊደረግ የሚቻል ነው ወይ የሚለውን ነጥብ ተጠሪዎች ባሉበት መጣራት ያለበት መሆኑ ታምኖበታል ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በቀን 18/08/2013 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ክርክር ውሳኔ ባልተሰጠበት እና ጉዳዩን የያዘው የስር ቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ማስረጃ ቃል ለመስማት በመዝገቡ ላይ ቀጠሮ ሰጥቶ ባለበት ሁኔታ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አመልካቾች በብይኑ ላይ ያቀረቡት አቤቱታ ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ ወድቅ እንዲደረግ፤ በሌላም በኩል ሟች ከሞቱ በኋላ የሟች መኖሪያ ቤት እና ቤቱ ያለበት ይዞታ አመልካቾች እና ተጠሪዎች በጋራ ስናስተዳድር ቆይተን አሁን የድርሻ ድርሻችንን ለማስተዳደር የወስን ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ያቀረብን ስለሆነና የክርክሩ ንብረት የዘር ሀረግ ተከትሎ የመጣ በመሆኑ የአመልካቾች የይርጋ መከራከሪያ በብይን በመታለፉ የህግ ስህተት ያልተፈጸመ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ

እንዲጸናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በተሰጠ ብይን ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ የመቅረቡን ስነ ስርዓታዊነት በቅድሚያ መመልከቱ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው ይህንኑ መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በህጉ በሌላ ሁኔታ እንዲፈፀም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ማለት የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ክርክሩን በሚሰማበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን ሲሰጥና ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት በሚሰጠው በማናቸውም ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማለት ወይም የሰበር አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም፡፡ ይኸው የሥነ ሥርዓት ህግ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320 (1) (3) እና (4) ስር ተመልክቷል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ያሳለፈው ብይን ላይ ዋናው ክርክር ሳያልቅ ይግባኝ/የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት አይገባም ተብሎ ይግባኙ/የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ሲገባ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ ባሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ መታየቱ እና በዚህ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪም የይርጋ መቃወሚያው ውድቅ የመደረጉ ጉዳይ በጭብጥነት ተይዞ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ መደረጉ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ በዋናው ፍሬ ጉዳይ ላይ ክርክር ለመስማት ቀጠሮ መለወጡ ብቻ ከስረነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም፡፡ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ወይም እልባት ተሰጥቷል ሊባል የሚችልም አይደለም፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ አመልካቾች ቅሬታ ካላቸው በስረ-ነገሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ መቃወሚያው በመታለፉም ያላቸውን ቅሬታ ጨምረው በአንድ ላይ በማጠቃለል ይግባኙን/የሰበር አቤቱታውን ያቀርባሉ እንጂ ክርክሩ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ በመቃወሚያ በተሰጠ ብይን ላይ ይግባኝ ማቅረብ እነደማይችሉ ከሥነ ሥርዓት ህግ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳብ እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ሰ/ህ/ቁ 320(3) ሥር በግልጽ ከተመለከተው ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ይግባኝ ሰሚ እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ ዋናው ክርክር ሳያልቅ ይግባኝ የማይፈቀድበት ነው በማለት ቅሬታውን ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው መርምረው ትዕዛዝና ውሳኔ ማሳለፋቸው የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 47822 በቀን 12/06/12 ዓ.ም፤ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33354 በቀን 02/07/2012 ዓ.ም፤ እንዲሁም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 33561 በቀን 28/03/2011 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝና ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች የቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10475 በቀን 18/05/2012 ዓ.ም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ባሳለፈው ብይን ያላቸውን ቅሬታ በስረ-ነገሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ መቃወሚያው በመታለፉም ያላቸውን ቅሬታ ጨምረው በአንድ ላይ በማጠቃለል ይግባኙ/የሰበር አቤቱታቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ ብለናል፡፡

3. በስር ፍርድ ቤት የተጀመረው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ ሰኔ 2/2013 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 213074

ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ሩቂያ መሀመድ - ጠበቃ ኸይሩ ሲርጋጋ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1ኛ. ወ/ሮ አይሻ በያን

2ኛ. አቶ ሸምሱ መሀመድ } አልቀረቡም

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 18/12/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የቡታጀራ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 11707 በቀን 24/06/2012 ዓ.ም፣ የደ/ብ/ብ/ህ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15065 በቀን 15/12/2012 ዓ.ም እንዲሁም የደ/ብ/ብ/ህ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 15199 በቀን 24/10/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ጉዳዩ የጋብቻ ንብረትን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በስር የቡታጀራ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተዋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በቀን 18/01/2010 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ከሳሽና ተከሳሽ በጋብቻ በጋራ ያፈራነው በማለት አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰ ይዞታና በይዞታው ላይ 48 ቅጠል ቆርቆሮ ክዳን ውስጥ ለውስጥ 3 ክፍል መኖሪያ ቤት በግል ገንዘቤ በ2007 ዓ.ም አሰርቼ አብረን የኖርንበት ሲሆን ቤቱ የተሰራበት መሬት ከወላጅ እናቱ ከወ/ሮ አይሻ በያን ለጎጆ መውጫ የተሰጠ ቦታ ላይ የሰራሁት ስለሆነ የጋራ ንብረታችን ነው እኩል እንድካፈል ይወሰንልኝ በማለት ከሌሎች ንብረቶች ጋር ዝርዝር በማቅረብ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሰጡት መልስ ከሳሽ የጠቀሰችው ቦታና ቤት በተመለከተ ቦታውም ሆነ ቤቱ ከሳሽና ተከሳሽ በጋብቻ ወቅት ያፈራነው ሳይሆን በእናቴ ወ/ሮ አይሻ በያን ስም የሚገበርበት ቦታ ሲሆን ቤቱንም የሰራችው ኩዌት ሀገር የነበረችው ልጅዋ ወ/ሮ ሲትያ መሐመድ የተባለችው በላከችላት ገንዘብ ነው፤

በኪራይ ቤት ከምትቀመጡ እህትህ እስክትመጣ በማለት በግዜያዊነት እንድኖርበት የሰጠችኝ ቤት ነው እንጂ የጋብቻ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጣልቃ ገብ ወ/ሮ አይሻ በያን በበኩላቸው ወደ ክርክሩ ገብተው ከሳሽ ጠቅሳ ያቀረበችው ይዞታ ወሰን ከእኔ ንብረት ጋር የማይገናኝ ቢሆንም የእኔ ወሰን በሰሜን ካሳ ከምሲ በደቡብ መሐመድ ሀሰን፣ በምስራቅ ሼፍ ኡመር፣ በምዕራብ መንገድ ሲሆን የጋራ ንብረት ነው ብለው የሚከራከሩበት ቤት በራሴ ይዞታ ላይ የሚገኝ ከመሆኑ በስተቀር ከሳሽ እንደጠቀሰችው አይደለም፤ ልጄ ፈትያ መሐመድ ከውጭ ሀገር ሰርታ በላከችልኝ ገንዘብ የሰራሁት ቤት እንጂ የከሳሽና ተከሳሽ የጋራ ንብረት አይደለም፤ ተከሳሽ ልጄ በመሆኑ ከከሳሽ ጋር አብረው በአቶ አብደላ ሻፊ ኪራይ ቤት ውስጥ ሲኖሩ ቆይተው በጎርፍ ምክንያት ተፈናቅለው የሚገቡበት በማጣታቸው ቤት እስኪያገኙ ድረስ በጊዜያዊነት በግል ቤቴ ውስጥ እንዲቀመጡ ካደረኩ በኋላ ባለመግባባት ምክንያት ፍቺ ፈጽመው የግል ንብረት የሆነው የቆርቆሮ ቤት እንደ ግል ንብረታቸው በማድረግ የቀረበው ክርክር ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የክርክር መነሻ የሆነው ቦታና ቤት የጣ/ገብ የግል ንብረት ተብሎ እንዲወሰን በማለት ጠይቀዋል፡፡

በጣ/ገብ አቤቱታ ላይ ከሳሽ በሰጡት መልስ የጣ/ገብ አቤቱታ መብቴን ለማጣበብ ከተከሳሽ ጋር በመመሳጠር የቀረበ አቤቱታ ነው ምክንያቱም ጣ/ገብ ጠቅሳ ያቀረበችው ቤትና ይዞታ ከሳውዲ አረቢያ ከ2003-2005 ዓ.ም ሰርቼ ከመጣሁ በኋላ በ2006 ዓ.ም ከተከሳሽ ጋር ትዳር መስርተን ስንኖር እንደ አካባቢው ባህል ለጎጆ መውጫ ይዞታው ተሰጥቶን ከአረብ አገር ሰርቼ ባመጣሁት ብር ለጎጆ መውጫ ተብሎ በተሰጠን ይዞታ ላይ ከወራቂ መሐመድ የቤት መስሪያውን እቃ በብድር በመውሰድ ያሰራነው መሆኑን ፍ/ቤት ማረጋገጥ ይችላል፤ በተጨማሪም የ05 ቀበሌ አስተዳደር እኔና ባለቤቴ መስራታችንን ማረጋገጥ የሚችል መሆኑ ታውቆ በደብዳቤ በመጠየቅ እንዲረጋገጥ፤ ጣ/ገብ አመልካች ያለማንም አስገዳጅ ይዞታውን ከሰጠችኝ በኋላ ቤት መስራቴን እያወቀች ከተከሳሽ ጋር ባለመስማማታችን ትዳራችን ሲፈርስ ተከሳሽን ለመጥቀም ያቀረበችው አቤቱታ ነው፤ ጣ/ገብ ያቀረበችው የሰነድ ማስረጃ ሀሰተኛ ነው ምክንያቱም ሰነዱ የተሰራው ባለቤቷ እንዳለ በማድረግ ሲሆን የጣ/ገብ ባለቤት በ2003 ዓ.ም እንደሞተ እንዲታወቅልኝ እና የጣ/ገብ አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት አቅርበዋል፡፡ ተከሳሽም መልሱን በማጠናከር የጣ/ገብ አቤቱታ ላይ ተቃውሞ እንደሌለው ገልጿል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ቃል በመስማት፣ ከአስተዳደሩ ማስረጃ በማስቀረብ እንዲሁም ከማዘጋጃ ቤት ባለሙያ ጋር ቤትና ቦታውን ተመልክቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ከስር መሰረቱ የጣልቃ ገብ ስለመሆኑ በከሳሽም ያልተካደች ቢሆንም የከሳሽ ክርክር ለጎጆ መውጫ የተሰጠ ይዞታ መሆኑና ጣ/ገብ ሳትቃወም ቤቱ የተሰራና የተሰራበትም ወጪ በከሳሽ የተሸፈነ ነው የሚል ሲሆን ጣ/ገብ ደግሞ አረብ አገር የምትኖረው ልጄ በምትልከው ገንዘብ የተሰራ የግል ንብረት ነው የሚል ነው፡፡ የከሳሽ ምስክሮች ከጣ/ገብ ምስክሮች በተሻለ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ አከራካሪው ቤት በከሳሽ ገንዘብ የተሰራ መሆኑን ይዞታውም ከሳሽና

ተከሳሽ ትዳር በመሰረቱበት ጊዜ ለጎጆ መውጫ የተሰጠ ስለመሆኑ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በይዞታው ላይ የተሰራው የቆርቆሮ ክዳን ቤት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ ስለመኖሩ በንብረት ህግ ቁጥር 1179 መሰረት የጋራ ነው፡፡ ከይዞታው መጠን ጋር ተያይዞ የክ/ከተማው ማዘጋጃ ቤት በላከው ምላሽ መሰረት የክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ መጠን ትክክለኛ መረጃ ተገኝቶ ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ ቦታውን በአካል ከማዘጋጃ ቤት ባለሙያ ጋር በመሄድ በመመልከት ቤቱ ያረፈበትን ጨምሮ 1000 (አንድ ሺህ) ካ.ሜ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሁለቱም ወገኖች የየበኩላቸውን ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ከሳሽ በመ/ቁ 11686 ለከፍተኛው ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ  ክርክር የተነሳበት ቤትና ይዞታ መጠኑ 2852.85 ካ.ሜ ሆኖ የስር ፍ/ቤት 1000 ካ/ሜ እኩል ይካፈሉ ማለቱ ስህተት ነው በማለት አቅርበው ፍ/ቤቱም አከራካሪውን ይዞታ መጠን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ቦታውን ተመልክቶ ከማዘጋጃ ቤትም በቀረበው ማስረጃ መጠኑ 2852.85 ካ.ሜ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ፍ/ቤቱ ለምን 1000 ካ/ሜ አድርጎ እንደወሰነ በግልጽ ያላብራራውና ከቀረበው ማስረጃም ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት የይዞታው መጠን 2852.85 ካ/ሜ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ጣ/ገብ በመ/ቁ 11707 ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

ጣ/ገብ በዚህ መልኩ ሁለት አይነት ውሳኔ መሰጠቱን በመቃወም እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበው ፍ/ቤቱም በከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 11707 በቀን 15/04/2011 ዓ.ም እና በመ/ቁ 11686 በቀን 4/11/2010 ዓ.ም የተወሰኑትን ውሳኔዎች በመሻር መዝገቦቹ ተጣምረው ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ለከፍተኛው ፍ/ቤት መልሷል፡፡ በመለሰው መሰረት ከፍተኛው ፍ/ቤት አጣምሮ ተመልክቶ በመ/ቁ 11707 በሰጠው ውሳኔ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የስር ከሳሽና ተከሳሽ ቤቱ በተሰራበት ግዜና ተሰርቶም ይኖሩበት በነበረ ግዜ ጣ/ገብ ያለመቃወሚ በመረጋገጡ በአከራካሪው ይዞታ ላይ የተሰራው መኖሪያ ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ቤቱ ያረፈበትን ይዞታ በተመለከተ የገጠር ይዞታ የነበረው ወደከተማ እየተካለለ በመሆኑና አንድ እድሜው ለአቅመ አዳም የደረሰ ወጣት የገጠር ይዞታ ወደ ከተማ ሲከለል ሊያገኝ በሚችልበት አግባብ ለከሳሽና ተከሳሽ መውጫና መግቢያ ባገናዘበ መልኩ 400 (አራት መቶ) ካ/ሜ ብቻ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ሊሆን ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝና የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 18/12/2013 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ አከራካሪው መሬት አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ጋብቻ እንደፈጸምን የ2ኛ ተጠሪ ወላጆች ለጎጆ መውጫ ሰጥተውን እህል እየዘራን ስንጠቀምበት ረጅም ግዜ ቆይተን ልጅ ወልደን አብረን ኖረንበታል፤ 1ኛ ተጠሪ ከ5 ጥማድ በላይ መሬት አላት፤

ይሁንና ለጎጆ መውጫ ሰጥተውን አካባቢው እየተሻሻለ ሲመጣ 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን አሳምና እኔን ለማፈናቀል ተመካክረው ጋብቻው እንዲፈርስ ተደርጎ አረብ አገር ሰርቼ ባገኘሁት ገንዘብ የሰራሁትን ቤት ክደው ተከራክረዋል፡፡ በስር ፍ/ቤት አከራካሪ የነበረው በተጠቀሰው አዋሳኝ ላይ ያለው ይዞታና ቤት በጋብቻ ግዜ የተፈራ መሆን አለመሆኑ እንጂ የአዋሳኝ የመጠን ጉዳይ አልነበረም፡፡ የይዞታው መጠን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ለጎጆ መውጫ ይዞታና በላዩ ላይ የሰራነውን ቤት ለሁለት እኩል እንድንካፈል በጠየኩት ዳኝነት መሰረት ማስረጃ አቅርቤ አረጋግጫለሁ፡፡ ተጠሪዎች የይዞታውን መጠን በተመለከተ ክርክር አላደረጉም፡፡ የከተማው ፍ/ቤት የመሬቱ መጠን 1000 ካ/ሜ ከእነ ቤቱ የጋራ ንብረት እንዲሆን የወሰነበት ተገቢ ባለመሆኑ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቤ ጉዳዩን የያዙት ዳኛም ከማዘጋጃ ባለሙያ ጋር በመሆን ግራ ቀኛችን በተገኘንበት የይዞታው መጠን 2852.85 ካ/ሜ መሆኑን በአካል አረጋግጦ የወሰነው ማስረጃን መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ይዞታው ለጎጆ መውጫ ሲሰጠን መሬቱን ያለማና የከተማው ልማት በአካባቢው ባልተስፋፋበት ግዜ የገጠር መሬት ለጎጆ መውጫ ሲሰጥ እንደ አቅም በጥማድ ወይም በሶማ እና መሬቱ ያለበት አካባቢ ተጠቅሶ እንጂ ካ/ሜ አይታወቅም፡፡ የስር ከተማ ፍ/ቤትም በአዋሳኝ ከተጠቀሰው ቀንሶ 1000 ካ/ሜ ያለበት አግባብና ከፍተኛው ፍ/ቤት 400 ካ/ሜ በማለት የወሰኑበት አግባብ ተገቢነት የለውም፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት የመስክ ምልከታ ሳያደርግ የመሬቱ መጠን 400 ካ/ሜ እንዲሆን ሲወስን መሰረት ያደረገው በከተማ ክልል ውስጥ ያለውን ሁኔታ እንጂ በገጠር ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 11707 የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ተብሎ ውድቅ እንዲደረግና በመ/ቁ 11686 የወሰነው ውሳኔ እንዲጸና በማለት የቅሬታ ማመልከቻቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሆኖ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ 1000 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን ቤትና ይዞታ እንዲከፋፈሉ ውሳኔ ሲሰጥ ግራ ቀኙ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ሁለቱም መዝገቦች በተለያየ ችሎት ሳይጣመሩ በመታየታቸው በሁለቱም መዝገቦች የተለያየ ውሳኔ ስለተሰጠባቸው ጉዳዩን የክልሉ ሰበር አይቶ መዝገቦችን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 11 መሰረት አጣምሮ እንዲያይ ለከፍተኛው ፍ/ቤት በመመለስ ውሳኔ ሲሰጥ ጉዳዩ የተመለሰለት ፍ/ቤት ሁለቱን መዝገቦች አጣምሮ አይቶ ግራ ቀኙ 400 ካ/ሜ ይዞታ ላይ ያለውን ቤት እንዲከፋፈሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የይዞታው መጠን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት በአካል በቦታው ድረስ በመሄድ ያረጋገጠው 1000 ካ/ሜ መሆኑን ድምዳሜ ላይ ደርሶ ባለበት ፍ/ቤቱ ይህን ሊያስለውጥ የሚችል ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ 400 ካ/ሜ ላይ ያለውን ይዞታ እንዲከፋፈሉ መወሰኑ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በቀን 11/04/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ በተገቢው መንገድ ተጣርቶ 400 ካ/ሜ የተወሰነ እንጂ አመልካች እንደምትለው ያለምንም ማስረጃ የተወሰነ ባለመሆኑ በውሳኔው የተፈጸመበት የህግ

ስህተት የለም ተብሎ እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው ክርክሩ የቤተሰብ /የፍትሐብሄር/ በመሆኑ ሊመራ የሚገባው በቤተሰብ ህጉ እና በፍትሐብሄር ሥነ ስርዓት ህጉ አግባብ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራከራዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባቀረቡት ወይም በግልጽ ባመለከቱት ጉዳይ ላይ ተመስርቶ በህጉ አግባብ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህን ውሳኔ ለማሻሻልና ለመሻር እንዲችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) ስልጣን የተሰጠው ሲሆን ውሳኔውን ሲሽርም ሆነ ሲያሻሽል ግን በህግና በማስረጃ የተደገፈ ምክንያት ሊሰጥ ይገባል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተው አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ሲፈጽሙ ለጎጆ መውጫ የተሰጣቸውን ይዞታና በጋብቻ ጊዜ በገንዘባቸው ተሰራ የሚሉትን ቤት አዋሳኝ እና መጠን ጠቅሰው ድርሻቸውን እኩል ለመካፈል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ምስክሮች ከተጠሪ ምስክሮች በተሻለ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ አከራካሪው ቤት በአመልካች ገንዘብ የተሰራ መሆኑንና ይዞታውም ለጎጆ መውጫ የተሰጠ ስለመሆኑ ሚዛን በሚደፋ መልኩ ማስረዳታቸውን በማረጋገጥ በይዞታው ላይ የተሰራው የቆርቆሮ ክዳን ቤት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት እንደሆነ፤ የይዞታው መጠን ግን የክ/ከተማው ማዘጋጃ ቤት በላከው ምላሽ ስለ ይዞታ መጠን በትክክል ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ ቦታውን በአካል ከማዘጋጃ ቤት ባለሙያ ጋር በመመልከት ቤቱ ያረፈበትን ጨምሮ 1000 (አንድ ሺህ) ካ.ሜ የባልና ሚስት የጋራ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በበኩሉ በመጨረሻ በሰጠው ውሳኔ የገጠር ይዞታ የነበረው ወደከተማ እየተካለለ በመሆኑ ጉዳዩ አንድ እድሜው ለአቅመ አዳም የደረሰ ወጣት የገጠር ይዞታ ወደ ከተማ ሲከለል ሊያገኝ በሚችልበት አግባብ ሊታይ ይገባል በማለት አመልካችና 2ኛ ተጠሪ መውጫና መግቢያ ባገናዘበ መልኩ 400 (አራት መቶ) ካ/ሜ ብቻ የባልና ሚስት የጋራ ሆኖ ሊካፈሉ ይገባል በማለት በማሻሻል ወስኗል፡፡

ይሁንና የገጠር ይዞታ የነበረ መሬት ወደ ከተማ ሲካለል ባለይዞታዎች የሚኖራቸው መብት እና የሚደርሳቸው የይዞታ መጠን እንዲሁም ካሳ ራሱን ችሎ የሚታይ እና በሌላ ህግ አግባብ የሚስተናገድ እንጂ አሁን በተያዘው የባልና ሚስት ንብረት ክርክር ውሳኔ የሚያገኝ ጉዳይ አይደለም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተመልሶለት መዛግብቱን አጣምሮ እንዲወስን ሲደረግ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ከማስረጃቸው በመውጣት በራሱ ልኬት 400 (አራት መቶ) ካ/ሜ ብቻ የባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸው ሆኖ ሊካፈሉ ይገባል በማለት መወሰኑ ከፍሲል በተጠቀሰው ህግ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ ግራቀኝ የጠየቁትን የይግባኝ የዳኝነት ጥያቄ ፤ ክርክሩ የሚመራበት የሥነ ሥርዓት ህግ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን የዳኝነት ስልጣን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው የሚነቀፍ ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የቡታጀራ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 11707 በቀን 24/06/2012 ዓ.ም፣ የደ/ብ/ብ/ህ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15065 በቀን 15/12/2012 ዓ.ም እንዲሁም የደ/ብ/ብ/ህ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 15199 በቀን 24/10/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የቡታጅራ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 15202 ሚያዚያ 24/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የቆርቆሮ ክዳን ቤት እና ቤቱ ያረፈበትን ጨምሮ 1000 ካ.ሜ ቦታ የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት በመሆኑ በተሻሻለው የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 101 መሰረት እኩል እንዲካፈሉ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. የዕግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ 208253

ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ብርቄ ታደሰ

2ኛ. ወ/ሮ የሺ ታደሰ

3ኛ. ወ/ሮ ፅጌ ታደሰ

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሴ ታደሰ

አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በቀን 25/09/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 374650 በቀን 03/09/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በጅልዱ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሲሆን የአሁን 3ኛ አመልካች እንዲሁም በዚህ ሰበር ክርክር የሌሉት አቶ ሽፈራው ግርማ እና እጅጋየሁ ታደሰ ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በቀን 19/03/2012 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ አባታችን ታደሰ ተ/ጻድቅ በ2006 ዓ.ም የሞቱ ሲሆን ሰባት ልጆች አሏቸው፤ አባታችን በህይወት እያለ ይዞታው የነበረውና ከሞተ በኋላ በተከሳሽ እጅ የገቡ በሶስት ቦታ የሚገኙ ይዞታ መሬቶች የውርስ ድርሻችንን እንዲያካፍለን ይወሰንልና በማለት የመሬቱን አዋሳኝ እና መጠን ጠቅሰው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጣ/ገቦች በበኩላቸው በቀን 11/06/2012 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ከሳሾች ያቀረቧቸውን ይዞታዎች በተመለከተ እኛም የሟች ወራሽ ስለሆን የሚገባን ድርሻ እንዲያካፍሉን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በቀን 06/04/2012 ዓ.ም በከሳሾች ላይ እንዲሁም በቀን 17/06/2012 ዓ.ም በጣ/ገቦች ላይ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አውራሽ የሞቱት በ2006 ዓ.ም ሳይሆን በ2005 ዓ.ም በመሆኑና በወራሾች መካከል የሚደረግ የውርስ ክርክር በ3 አመት ውስጥ መቅረብ ያለበት በመሆኑ፤

እንዲሁም የያዝኩት ይዞታ ቢኖር እንኳ ከ7 አመት በኋላ ሊጠይቁኝ ስለማይችሉ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በተመለከተ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ መሬት ወራሾች በስምምነት አካለ መጠን ያልደረሰ ወንድማቸው ትምህርቱን ተምሮ እስኪያጠናቅቅ ድረስ በተከሳሽ እጅ ይቆይ በማለት የተስማሙ መሆኑን የከሳሾች ምስክሮች ሲያረጋግጡ የተከሳሽ ምስክሮች ግን በ2006 ዓ.ም መሬቱ እጁ መግባቱን እንጂ በምን ሁኔታ እንደገባ አናውቅም ስላሉ የከሳሾችን ምስክሮች ቃል አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም የይዞታ መሬቶቹ አውራሽ ከሞተ በኋላ በስምምነት በተከሳሽ እጅ የገባ እንጂ ተከሳሽ እንደዚሁ የያዘው ስላልሆነና ስምምነቱ መኖሩ ለወደፊት እንካፈላለን በሚል በመሆኑ የይርጋ ጊዜውን ቀሪ የሚያደርግ ነው በማለት በተከሳሽ የተነሳውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም በክሱ በ3ኛ ተ.ቁ ላይ የሚገኘው ይዞታ መሬት የክርክሩ አካል ባልሆነው 3ኛ ወገን እጅ (በአቶ ደክሲሳ ገመቹ) ያለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በተ.ቁ 1 እና 2 ላይ የተገለጹት ይዞታ መሬቶች ግን የውርስ ሀብት መሆኑ ያላከራከረ በመሆኑና ይዞታ መሬቶቹን ተከሳሽ የተከራካሪዎች አባት ከሞቱ ከ2006 ዓ.ም በኋላ ውርስ ሳይካፈሉ በተከሳሽ እጅ ለግዜው እንዲቆዩ በተስማሙት መሰረት የያዘ እንጂ የተከሳሽ የግሉ እንዳልሆነ የከሳሾች እና የጣ/ገብ ማስረጃዎች አስረድተዋል፤ የተከሳሽ ምስክሮች ግን ይህን አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ በእጁ ያለውን በተ.ቁ 1ኛ እና 2ኛ ላይ ከተገለጸው ይዞታ መሬት የከሳሾች እና 3ኛ ጣ/ገብ ድርሻ የሆነውን ይልቀቅ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሽ ይግባኝ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አውራሽ ሲሞቱ የተከራካሪዎች ወንድም ደረጀ ታደሰ ትምህርት ላይ ስለነበር ትምህርቱን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ተከሳሽ እነሱን ረድቶ በመሬቱ እንዲጠቀምበት ወራሾች በመስማማት በተከሳሽ እጅ እንደተውት የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ መሬቱን ወራሾች እንዲካፈሉ መወሰኑ ስህተት ያለው ሆኖ አልተገኘም በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዘዋል፡፡

በመጨረሻም ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የቀረቡት ምስክሮች ለክርክር ምክንያት የሆነውን ይዞታ መሬት ወራሾች በስምምነት ወንድማቸው ደረጀ ታደሰ እንዲማርበት በተከሳሽ እጅ ትተዋል በማለት ቃላቸውን ከመስጠታቸው ውጪ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ወራሽነታቸውን በማረጋገጥ ወንድማቸው እንዲማርበት ስለማድረጋቸው ያቀረቡት ማስረጃም ሆነ የፅሁፍ ውል የለም፤ የውርስ ይዞታ መሬት ሳይከፋፈሉ እንዲቆይ መስማማታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች በሰው ምስክር ላይ ብቻ በመመስረት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ ያደረጉበት ሁኔታ ስህተት ነው፡፡ በአጠቃላይ አከራካሪውን መሬት ተከሳሽ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ 7 አመት የተጠቀመበት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ያቀረበው

የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበት ሁኔታ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ከሳሾች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ በፍ/ሕ/ቁ 1000(1) መሰረት በ3 አመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔ በመሻር በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት መሬቱ ወንድማቸው እንዲማርበት ብለው የቆየ መሆኑ በማስረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ሽሮ በይርጋ ይታገዳል ያለበት አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 10/02/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር መሬቱን ለመጠየቅ በህግ በተወሰነ ግዜ ውስጥ መጠየቅ ሲገባቸው ሳይጠይቁ ቀርተው በይርጋ መታገዳቸው አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ቅሬታው ውድቅ ተደርጎ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አወሳሰንን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 245(1) እና (2) እንደተደነገገው ተከሳሽ ለክሱ መቃወሚያ ባቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተውን ማስረጃ በመመርምር የቀረበው መቃወሚያ በተገቢና በቂ በሆነ ማስረጃ የተደገፈ መሆን አለመሆኑን ፍሬ ነገርን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በማረጋገጥ ይወስናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ለክሱ ባቀረቡት መቃወሚያ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም በመቃወሚያው ላይ ግራቀኙ ያደረጉትን ክርክር ተመልክቶ ለጉዳዩ አወሳሰን ይረዳል ያለውን ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በህጉም ተቀባይት የለውም ያልተባለን ማስረጃ ተቀብሎ መርምሮና መዝኖ የግራቀኙ አውራሽ እንደሞቱ ወራሾች ስምምነት በማድረግ ወንድማቸው ደረጀ ታደሰ ትምህርቱን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ተጠሪ እየረዳው በውርስ መሬቱ እንዲጠቀምበት በመስማማት በተጠሪ እጅ መሬቱን እንደተዉት በማረጋገጥ የይርጋ ክርክሩን ውድቅ

በማድረግ ወስኗል፡፡ ይህን ተከትሎ በውርስ የሚተላለፍ መሆኑ ያላከራከረውን ይዞታ መሬት ወራሾች እንዲካፈሉት ወስኗል፡፡ ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ እና ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ችሎቶችም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በአንጻሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃውን መዝኖ ከወረዳው ፍርድ ቤት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ድረስ ያሉ ችሎቶች አግባብነትና ተቀባይነት ያለው በማስረጃ ተቀብለው በመመዘን አረጋግጥን ከሚሉት የፍሬ ነገር መደምደሚያ በመውጣት አመልካቾች ወራሽነታቸውን በማረጋገጥ ወንድማቸው እንዲማርበት ስለመስማማታቸው ያቀረቡት ማስረጃም የለም፤ የውርስ ይዞታ መሬት ሳይከፋፈሉ እንዲቆይ መስማማታቸውን የሚያሳይ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ስለሌለ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ማስረጃውን በተመለከተ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በመጨረሻ ተቀብለው የሰጡትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

እንደሚታወቀው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ) እንዲሁም በክልሉ ህገ መንግስት እና በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ማስረጃ በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ከማረም ስልጣኑ ውጭ በመሆኑ የሚነቀፍ ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 374650 በቀን 03/09/2013 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የጀልዱ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 71594 በቀን 26/05/2013 ዓ.ም፤ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 34508 በቀን 02/06/2013 ዓ.ም፤ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 342485 በቀን 21/07/2013 ያሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# ውል

የሰ.መ.ቁ.188102

ጥቅምት 25 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡-1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፊይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- መይ ሪል ስቴት ዴቨሎፕመንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቆች ውቤ አለና እና ሰለሞን ገ/ሚካኤል - ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡-1. አቶ ፋሲል ጌታቸዉ

2. ዶ/ር ሐና እስክንድር

3. ካፒቴን አዲሱ ፊጠና

4. አቶ ነብዩ ሳሙኤል

5. ወ/ሮ ትዕግስት ሀብቴ

6. ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ብርሐኔ

7. አቶ አምሴ አካለወርቅ

8. ወ/ሮ ሒሩት አካለወርቅ

9. ወ/ሪት ወይንሸት አበበ

10. ወ/ሮ ትርሲት አካለወርቅ

11. ዶ/ር አሰፋ በቀለ

12. ፕ/ር አየነዉ እጅጉ

13. ወ/ሮ ዝማምነሽ አዳሙ

14. ዶ/ር ዉብሸት አየነዉ

15. አቶ ተዋበ አየነዉ

**ለሁሉም ተጠሪዎች ጠበቆች ቁምላቸው ዳኜ እና ደረጀ ኢቲቻ ቀርበዋል**

16. አቶ ዩሀንስ ክፍሌ
17. ወ/ሮ የምስራች ፈለቀ
18. አቶ ጥሩነህ ስንሻዉ
19. ወ/ሮ ሔለን እስክንድር
20. ካፒቴን አበበ አባተ
21. አቶ መኮንን ቀጸለ
22. ወ/ሮ ገነት ቀጸለ
23. ካፒቴን አምሐ ቀጸለ
24. ወ/ሮ ኢያሩሳሌም ተፈራ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የቤት ግንባታ ዉል ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.162150 መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የሥር ከሳሽ (የአሁን አመልካች) ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ከተከሳሾች ጋር ቀድሞ በነበረን ክርክር በመካከላችን ባለ የግንባታ ውል መሰረት ያልተከፈልን ገንዘብ ካለ መጠየቅ እንደምችል መብቱ ተጠብቆልኝ የተወሰነ በመሆኑና በዚህ የግንባታ ውል መሰረትም መክፈል የሚገባቸውን የተለያየ መጠን ያላቸውን ቀሪ ክፍያዎች፤ ከሌሎች የህንፃው ተጠቃሚዎች ጋር በጋራ ለሚጠቀሙበት መሰረታዊ መጠቀሚያዎች ከሳሽ ያወጣውን ወጪ፤ የተ.እ.ታ ክፍያዎች ፤ በሰበር ችሎት(በቀድሞው ክርክር) ተከሳሾች የህንፃዎቹን የባንክ መያዣ ኃላፊነት እንወስዳለን ያሉ በመሆኑና ከሳሽ ህንጻውን ከብድር መያዣ ለማስለቀቅ የከፈለውን የባንክ የብድር ወለድ እኩል መጠን ያላቸውን የቦታ ሊዝ ክፍያዎችን ፤ተከሳሾች በድርሻቸው መክፈል ከነበረባቸው ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9 % ወለድና በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉኝ በማለት የሰውና ሰነድ ማስረጃን በማያያዝ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፤

ተከሳሾች በበኩላቸው ከሳሽ ክሱን ያቀረበው ከተከሳሾች ጋር ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም ባደረገው ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ባላቸው የግንባታ ውሎች መሰረት ሲሆን; በዚህ ውል መሰረት

ተከሳሾች በአራት ዙር ለከሳሽ ክፍያ መፈፀም ያለባቸው ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ዙር ክፍያ የሚከፈለው ውሉ ሲፈረምና ግንባታው ሲጀመር በመሆኑ ሁሉም ተከሳሾች ከፍለውታል፡፡ 3ኛ ዙር ክፍያ የሚከፈለው የህንጻዎቹን ግንባታ አጠናቆ ሲያስረክብ ሲሆን 4ኛ ዙር ክፍያ ደግሞ ከሳሽ የህንፃ ክፍሎቹን ስመ ሀብት በተከሳሾች ስም አዘዋውሮ የባለቤትነት ማስረጃ ሲሰጥ በመሆኑና ከሳሽም ይህን ግዴታውን በቅድሚያ ያልተወጣ በመሆኑ የመክፈያ ጊዜው አልደረሰም/አልበሰለም፤ ክፍያ እንዲፈፀምለት የሰጠው ማስጠንቀቂያ ባለመኖሩ ክስ የማቅረብ መብት የለውም ተብሎ መዝገቡ እንዲዘጋላቸው የመጀ/ደ/መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን; በአማራጭነት በፍሬ ጉዳይ ላይ ደግሞ

ከሳሽ በውላችን የውሉ አካል እንዲሆኑ በተስማማንበት ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን(የፊኒሽንግ ማቴሪያሎች፤የክፍሎቹን ስፋትና የዋጋ ዝርዝር ያካተተ) መሰረት ግዴታውን በመወጣት ያላስረከበ በመሆኑ ወለድና ወጪ ሊጠይቅ ካለመቻሉሙ በላይ ርክክብ ሲደረግ ለተገኙ ጉድለቶች ማለትም የኩሽና እቃዎች፤የመብራት አምፖሎችና ባልኮኒ ማስገባት ሲኖርበት ያላስገባ መሆኑ፤ወለሉና የሽንት ቤት እቃዎች ጥራት ባላቸው የጣልያን እቃዎች መሰራት ሲኖርባቸው ተመጣጣኝነት በሌላቸውና የጥራት ደረጃቸውና ዋጋቸው ዝቅተኛ በሆኑ እቃዎች የተሰሩ ከመሆኑም በላይ ያልተሰራ ወለል መኖሩ፤ ባለሶስት መኝታ ማስረከብ ሲገባው ባለ ሁለት መኝታ ማስረከቡ(ፓርትሽን ያልተሰራለት)፤ጣሪያና ግድግዳው በልሰና ላይ ያለ ቀለም ያልተቀባ በር ያልተገጠመላቸው መሆኑ እና አጠቃላይ የአፓርትመንቱ ስፋት በመቀነሱ ለከሳሽ ቀሪ ክፍያ የሚፈፀመው እነዚህ የተገኙ ጉድለቶችን ሲያስተካክል አልያም ለማስተካከያ የሚያስፈልገው ወጪ ተቀናሽ ከተደረገ በኃላ የሚቀር ካለ የሚከፈል ነው፡፡

በውላችንና የውላችን አካል በሆኑ የዋጋ ዝርዝር መሰረት የሊዝና የተ.እ.ታ ክፍያ በቤቶቹ ጠቅላላ ዋጋ ላይ የሚካተት ነው ፤ከቤቱ ጠቅላላ ዋጋ አካል አይደሉም ቢባል እንኳን መክፈል የሚገባን ለተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ከሆነ በኃላ ያለውንና ለመንግስት የተከፈለውን የሊዝ መጠን ለባለቤቶቹ በማካፈል ነው፡፡የጋራ መገልገያ ናቸው የተባሉት ለቤቶቹ የግድ የሚያስፈልጉ በመሆናቸው የቤቱ አካል ሆነው በቤቱ ጠቅላላ ዋጋ ላይ የሚካተት ነው; ባይሆንም ለመስራት ፍቃዳችንን ባለመጠየቁ ልንጠየቅ አይገባም፡፡በከሳሽና በባንክ መካከል ላለው ግዴታ ተከሳሾች በወልም ይሁን በውሳኔ ለከሳሽ የባንክ ክፍያ ኃላፊነት የምንወስድበት አግባብ የለም በማለት የመከላከያ መልሳቸውን ሰጥተው የቃል ክርክርም አድረገዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተከሳሾች ያቀረቡትን የመ/ደ/መቃወሚያን ባለመቀበል ብይን ከሰጠ በኃላ በውላቸው መሰረት ግንባታው መከናወኑንና አለመከናወኑን ከነዋጋቸው እንዲያጣራ ባለሙያ የመደበ ሲሆን ከሳሽ በባለሙያው ገለልተኝነት ላይ ያነሳውን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ የምርመራውን ውጤት የመዝገቡ አካል እንዲሆን አድርጎታል፡፡ተከሳሾች ቤቶችን በፍርድ የተረከቡ መሆኑና ቀሪ ክፍያም

ያለ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ከሳሽ በውላቸው መሰረት ግንባታውን አካሂዶ ያስረከበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት የሰው ማስረጃና የባለሙያ ማስረጃ ያጠናከረ ሲሆን፡

የከሳሽ የሰው ምስክሮች ቤቶቹ ለነዋሪዎች ምቾት (በተሻለ ሁኔታ እንዲጠቀሙበት) ሲባልና በቤት ገዢዎቹም ተስማምተው ባለሶስት መኝታ ቤትን ወደ ባለሁለት መኝታ ቤት እንዲቀየር ተደርጎ በፀደቀ ዲዛይንና በስፔስፍኬሽኑ ከተገለፀው በተሻለ ሁኔታ የተሰሩ መሆናቸውን፤የቤቶቹ ወለል በኤም ዲ ኤፍ የተሰራ መሆኑንና የፔንት ሀውሶቹ ወለል በፐርኬ ያልተሰራ መሆኑን፤የኩሽና እቃዎች በተጨማሪ ዋጋ የሚሰሩ መሆናቸውን ሲመሰክሩ፣

የተከሳሾች የሰው ምስክሮች በበኩላቸው ቤቶቹን በፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት ተከሳሾች ሲረከቡ ቤቶቹ ቀለም ያልተቀቡ፤የበር እጀታ የሌለው፤ወለሉ በጣልያን ፐርኬ መሰራት ሲኖርበት በጥራትና በዋጋ አነስተኛ ኤም ዲ ኤፍ የተሰራ ከመሆኑም በላይ ያልተሰራም መኖሩን፤ያለ ፍቃዳቸው ከባለ ሶስት መኝታ ወደ ባለሁለት መኝታ ዝቅ ማለቱ፤ የቤቱ ስፋትም የቀነሰ በመሆኑና የኩሽና እቃዎች ያልተገጠሙና ያልተሟሉ በመሆናቸው በመካከላቸው ባለው የውል ድዛይንና ስፔስፊኬሽን መሰረት ተገንብቶ ያልተጠናቀቀ መሆኑንና ተጨማሪ የጋራ መገልገያዎችንም እንደሚያሰሩላቸው በከሳሽ እንደተነገራቸው መስማታቸውን መስክረዋል፡፡ የባለሙያ ሪፖርትም በውላቸው መሰረት ወለሉ በጣልያን ፐርኬ መሰራት ሲኖርበት ተመሳሳይ ጥራት በሌለውና በደረጃም ሆነ በዋጋ ዝቅተኛ በሆነ ኤም ዲ ኤፍ የተሰሩ ሲኖሩ የፔንት ሀውሶቹ ወለል ያልተሰራላቸው መሆኑን፤በር ያልተገጠመላቸው ያሉና የተገጠመላቸውም በውላቸው ካለው የኦክ እንጨት ውጪና ዝቅተኛ ጥራት ያለው መሆኑን፤ ቀለምና ኮርኒስ ተሰርቶ ያልተጠናቀቀ ሲሆን የኤሌክትሪክ ስራው ደግሞ በዲዛይኑና ስፔስፊኬሽኑ መሰረት ያልተሰራ መሆኑን ገልጧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ውል፤የሰው የባለሙያ ማስረጃን በመመርመር የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል;

1.በከሳሽና ተከሳሽ መካከል በተደረገው የግንባታ ውል መሰረት ከሳሽ ክፍያ ለመጠየቅ በቅድሚያ ቤቶቹን በውላቸው መሰረት ገንብቶ ማስረከብ ያለበት ሲሆን ከውሉ ውጪ የተፈጸመውን ጉድለት በራሱ ለማስተካከል አልያም ለማስተካከል የሚያስፈልገውን ወጪ የመተካት ኃላፊነት አለበት፤ ይሁንና ከሳሽ ከውላቸው ውጪም ቢሆን ግንባታውን አከናውኖና ተከሳሾችም የተረከቡትን በውላቸው ላይ ካለው ዋጋ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ሊያዝለት የሚገባ ሲሆን ከዚህ የሚቀረው ዋጋና ከሳሽ ሙሉ ለሙሉ ያልሰራቸው ስራዎች ዋጋ ተከሳሾች መክፈል ካለባቸው ቀሪ ክፍያ (3ኛ ዙር ክፍያ) ላይ ተቀናሽ ሊሆን ይገባል፡፡ ተቀናሽም የሚደረገውም የወለል፣ የኮርኒስ፣ የበርና የኤሌክትሪክ ስራዎች ዋጋን ብቻ እንጂ ሌሎች ከዚህ ውጪ ያሉ በውሉ መሰረት አልተሰሩም ተብለው የቀረቡትን ወጪዎች የማያካትት ነው ተብሏል፡፡

ምክንያቱም ግራ ቀኙ ሊገደዱ የሚችሉት የውላቸው አካል እንደሆኑ በተስማሙባቸው ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን እንጂ የውሉ አካል ባልሆኑት የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ (የቤቱ ዋጋ የሊዝ ዋጋ

እንደሚያካትት የሚገልጽ)፤ የመዝናኛና የኩሽና እቃዎች በተጨማሪ ዋጋ እንደሚሰሩ (price add ons) የሚገልጸው አይደለም፣ ቢፈረምም አይገደዱበትም፤ ከሶስት መኝታ ወደ ሁለት መኝታ የተቀየረው በስምምነት በመሆኑና ዲዛይኑም በመፅደቁ የውሉ አካል ነው;ይህም በሰው ማስረጃም የተደገፈ በመሆኑ የተከሳሾች አቤቱታ ውድቅ ነው፡፡

የመጨረሻውን (4ኛውን) ዙር ክፍያ ከሳሽ ለመጠየቅ በውላቸው መሰረት የቤቱን ማስረከብና ስመ ሀብቱንም በተከሳሾች ስም የማዘዋወር ግዴታ ያለበትና ያልፈፀመ በመሆኑ ይህንን ግዴታውን ሲወጣ ክፍያውን እንዲከፍሉት የመጠየቅ መብቱ ተጠብቆለታል፡፡

2.በውላቸው ላይ የሊዝ ዋጋንና ተ.እ.ታ የመንግስት ግብርን (ተ.እ.ታ በወቅቱ አለመመዝገቡ ይህን ግዴታ ቀሪ የማያደርገው በመሆኑ) ከቤቱ ዋጋ በተጨማሪነት ለመክፈል በግልፅ ስለተስማሙ በስምምነታቸው መሰረት ሊከፍሉ ይገባል፡፡

3. ከሳሽ ከውላቸው ውጪ ለተጨማሪ የጋራ መገልገያ ወጪ ማውጣታቸውና ሌሎች የቤት ገዢዎችም እየከፈሉ መሆኑን ባቀረቧቸው የሰነድና የሰው ማስረጃ ያስረዱ ስለሆነ ተከሳሾች በድርሻቸው በባለሙያ ተሰርቶ በቀረበው ግምት ልክ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡

4.በሰበር ክርክር ወቅት ተከሳሾች ከሳሽ ከባንክ ላለበት ብድር ከሳሽን ተክተን እንከፍላለን ያላሉና እንዲከፍሉም ያልተወሰነባቸው በመሆኑ፤ከሳሽ እነዚህንና ሌሎች ቤቶችን ማስያዣ በማድረግ ከባንክ ተበድሮ የከፈለውን ግዴታ ተከሳሾች እንዲተኩ የሚያስገድድ ህግ የሌለ በመሆኑ የከሳሽን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ተከሳሾች ሊከፍሉ አይገባም በማለት ውሳኔ አሳልፏል፡፡

5. ለከሳሽ የሚከፈሉት ክፍያዎች ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9 ወለድ ጋር ነው፡፡በክሱ ምክንያት ከሳሽ ያወጣውን ወጪ ተከሳሾች ሊተኩለት ስለሚገባ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር አቅርቦ የመጠየቅ መብቱ ተጠብቋል በማለት ውሳኔ ተላልፏል፡፡

የሥር ከሳሽ እና ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ፣

1.ከውላቸው ውጪ ከደረጃ በታች ለተሰሩ ስራዎች ኃላፊነቱን ሊወስድ የሚገባው ከውል ውጪ የሰራው እንጂ የሥር ተከሳሾች እንዲከፍሉ የማይገደዱ ባለመሆኑ ከቀሪ ተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ መሆን አለበት በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በዚህ ረገድ ሽሮታል፡፡

2. በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለው የግንባታ ውል (ያልተገነባ ቤት) ሲሆን በውሉ ላይ የተጠቀሰው ዋጋ ለምን ምን ስራ እንደሆነ አከራካሪ በመሆኑ ፤በድርድር ወደ ስምምነት የወሰዷቸው የዋጋ ማቅረቢያና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች; በሪል ስቴት ኢንዱስትሪው

የተለመደ ቢዝነስ አሰራርና ሌላም ተገቢ የሆነ ማስረጃ በመስማት ዋጋውም የኩሽና እቃዎችን ማካተትና አለማካተቱን የተዋዋዮቹ ሃሳብ ምን እንደነበር ሳይጣራ መወሰኑ አግባብ አይደለም፡፡

3. የሊዝ ክፍያን ገገርዎች ለመንግስት መክፈል እንዳለባቸው በውላቸው በግልፅ የተስማሙት በመሆኑ፤ ለመንግስት ቢከፍሉ ሕንጻው ላረፈበት ቦታ ለህንጻው ነዋሪዎች ተካፍሎ በመሆኑ፤ ገንቢውም ይህን የሊዝ ክፍያ ከከፈለ ውሉን መሰረት አድርጎ እንዲተካለት መጠየቅ የሚችል በመሆኑ ይህ ገንቢው ለሊዝ ለመንግስት የከፈለው መጠንና ምን ያህል ቤቶች እንዳሉ ሳይጣራ በውሉ የተመለከተውን ገንዘብን ይክፈሉ ማለቱ አግባብ አይደለም፡፡

4. የሥር ከሳሽ የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ከመሆኑ በፊት ለተደረጉ ግብይቶች መ/ሰጪዎች ሁሉንም የመንግስት እዳ ለመክፈል በመስማማታቸው ብቻ እንዲከፍሉ መወሰኑ በወቅቱ የነበረውን ሀሳባቸውን ያላጤነ ሲሆን የሥር ከሳሽ ለተ.እ.ታ ከተመዘገበ በኋላ ግን እሱም ታክሱን የመሰብሰብ ግዴታ ሲኖርበት የሥር ተከሳሾችም የመክፈል ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ መቼ ምዝገባ እንደተደረገና ስንት መክፈል እንዳለበት ሳይጣራ መወሰኑ አግባብ አይደለም፡፡ በተጨማሪም 4ኛውን ዙር ክፍያ እንዲከፍሉ ሳይወሰን ተ.እ.ታ እንዲከፍሉ መወሰኑ አግባብ አይደለም፡፡ ለከፈሉትም ደረሰኝ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

5. ለጋራ መገልገያዎች ከውል ውጪ መሰራቱ በመረጋገጡና ገንቢውም ከውሉ ውጪ የመስራት ኃላፊነት ስለሌለበትና ሌሎች ገገርዎችም ስለከፈሉ የሥር ተከሳሾች ወጪውን መተካት ቢኖርባቸውም ሁሉም ነዋሪዎች እኩል የሚጠቀሙባቸው እንደመሆኑ መጠን እኩል ክፍያ መጠየቅ ሲገባው በቤቶቹ ስፋት መጠየቁ አግባብ አይደለም፡፡

6. በውላቸው መሰረት ግንባታው መከናወኑን /አለመከናወኑን ያጣራው ባለሙያ ላይ የሙያ ስነምግባር ግድፈት እንዳለበት በቃለ መሀላና በማንኛውም ማስረጃ ማስረዳት ቢቻልም የስር ፍ/ቤት ይህንን ማስረጃ ሰምቶ በገለልተኛነቱ ላይ ውሳኔ ማሳለፍ ሲገባው በማለፍ መወሰኑ አግባብ አይደለም ፤በሂሳብ ስሌት ላይ የቀረበው ቅሬታም ከዚሁ ጋር የሚፈታ ነው፡፡

7. 4ኛውን ዙር ክፍያ ይ/ባይ ስመ ሀብቱን በተጠሪዎች ስም ሲያዘዋውር መሆኑ በውላቸው የተገለፀና በዚሁ መሰረት የሚፈፀም ቢሆንም ይ/ባይ በውል የተጣለበትን ግዴታ ከተወጣ አዲስ ክስ በማቅረብ እንዲጠይቅ ማድረጉ ለተጨማሪ ወጪና ጊዜ ብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ግዴታውን እንደተወጣ ከተ.እ.ታ ጋር ሊከፍሉት ይገባል፡፡

8. ወጪና ኪሳራን በተመለከተ እንደገና እንዲወሰን ወደ ስር ፍ/ቤት በመመለሱ እንደገና የሚታይ በመሆኑ ቀሪ ሆኗል በማለት በእነዚህ ጉዳዮች የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ፡፡

አመልካች ታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ተጠሪዎች በቀደመው ክርክራችን የማጠናቀቂያ ክፍያ ጠይቀው ባለማስረዳታቸው ውድቅ ተደርጎና ህንጻው የቀረው እንደሌለ ባመኑት መሰረት ባለበት እንድናስረክብ የተወሰነውንና በዚህ ውሳኔ ያጡትን መብት አሁን ካለብን እዳ ይቀነስ ማለታቸው ዳግመኛ ዳኝነት መጠየቃቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሰረት ተቀባይነት የሌለዉ ሆኖ ሳለ፤ የኩሽና እቃዎችና የሊዝ ክፍያ በውላችን ላይ በግልጽ ከቤቱ ዋጋ ውጪ እንደሆነ የተስማማነውን እና የውላችን አካል ያልሆኑትን የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድንና ተጨማሪ ክፍያን (price add ons) ከግምት በማስገባት በውላችን ላይ የግራ ቀኙን ሀሳብ ምን እንደነበር ሊተረጎምና መጠኑም ሊቀነስ ይገባል መባሉ፤ የታክስ አዋጅ ቁ.285/86 አመልካች ለተ.እ.ታ መመዝገብ ያለበት ከሆነ ተመዘገበም አልተመዘገበም ታክስ አዋጁ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ መክፈል ያለበት በመሆኑ፤ በውላችን ላይ ተመሳሳይነት ባላቸው እቃዎች ግንባታ ማካሄድ እየቻልን ይህ ከግምት ሳይገባ የተወሰነ በመሆኑ፤ በቀደመው ክርክር የባንክ እዳን ኃላፊነት እንወስዳለን ያሉ በመሆኑ አመልካች ይህንን እዳ ባይከፍል ሊከፍሉ እንደሚገደዱ ከግምት ውስጥ ሳይገባ የተወሰነ በመሆኑ፣ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልንና በጠየቅነዉ ዳኝነት መሰረት እንዲወሰንልን አመልክተዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱም፣ ጉዳዩን በማየት ፤በዚህ ጉዳይ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር በከፍ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ያለ ማስረጃ የቀረበ ክስ ነው ተብሎ የተዘጋባቸውና እስከ ሰበር በፀናበት ሁኔታ አመልካች ተጠሪዎች ቀሪ ክፍያ እንዲከፍሉ ባቀረቡት ክስ መዝገብ በፍርድ ያጡትን መብት በስር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ያገኘበት አግባብነት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.5 አንጻር ፤የስር ፍ/ቤቶች በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለውን አስገዳጅ ውል በአግባቡ መተርጎማቸውና አለመተርጎማቸውን ከመሰረታዊ የውል ህግ መርህ አንጻር እና ቤቶቹ የሚሰሩባቸውን እቃ በአማራጭ የተዋዋሉትን ውል በአግባቡ መተርጎማቸውና አለመተርጎማቸውን፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች መስከረም 8 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ በቀድሞው ለግንባታው የሚያስፈልገው ዋጋ የይከፈለን ክርክር ከሳሾች ተጠሪዎች የነበሩ ሲሆን ለአሁን ይግባኝ መሰረት የሆነው በውላችን መሰረት ለገነባሁት ግንባታ ክፍያ የይከፈለኝ ክርክር ከሳሽ አመልካች ነው፡፡ ቤቶቹን በፍርድ በተቀበልንበት ወቅት ለተረጋገጠ ጉድለት በውላችን መሰረት (በግንባታ ህጎች) ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ ጉድለቱን እንዲያስተካክል መጠየቃችን ዳግመኛ ዳኝነት አይደለም፤ የአመልካች ክስ መሰረትም ውላችን እንጂ የቀድሞው ውሳኔ ባለመሆኑ ፤ማስረጃም ሊሆነው ስለማይችል ፤የቀድሞው ውሳኔ አመልካች ላልሰራው ስራ ክፍያ እንዲጠይቅ መብት ያልሰጠው በመሆኑና የእኛንም የመከላከል መብት የማይነካ በመሆኑ፤ በውላችን የኩሽና እቃዎች የአመልካች ግዴታ አለመሆኑን በግልጽ ያላስቀመጠ በመሆኑ ግልፅነት የጎደለው ነው ይሁን እንጂ የውሉ አካል በሆኑ ሰነዶችና በ9ኛ ተጠሪ ውል ጭምር ይህ ወጪ የቤቱ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ እንደሚካተት የተስማማንበት

በመሆኑ፤ price add ons የሚለው ራሱ በጠቅላላው ላይ የሚጨመር ይሁን ከሱ ውጪ ያለ ወጪ መሆኑን ግልጽ ባለመሆኑ፤ ቤቶቹም በውላችን መሰረት ተመሳሳይነት ባላቸው እቃዎች እንዳልተሰሩ በባለሙያ ተረጋግጦ ሳለ አመልካች በባለሙያው ላይ ቅሬታ አቅርቦ ተቀባይነት በማግኘቱ እንደገና እንዲታይ የተባለ በመሆኑ የመጨረሻ ውሳኔ ካለማግኘቱም በላይ የማስረጃ ክርክር በመሆኑ በሰበር ሊቀርብ አይችልም፤ ውል በፈጸምንበት ወቅት አመልካች የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ያልነበረ በመሆኑ በውላችን ያልተካተተ ሲሆን ቀድሞ ለከፈልነው ዋጋና እንድንከፍል ላልተወሰነብን ዋጋ የምንከፍልበት አግባብ የለም፤በውላችን መሰረት የቤት መስሪያ ዋጋን እየከፈልን የአመልካችን ብቻ የሚመለከት እዳን የምንከፍልበት አግባብ የለም፤ እኛ የተረከብነው ቤት ማስያዣ ከፍሎ አስለቀኩ ያለው ዝርዝር ውስጥ ካለመኖሩም በላይ አላስረዳም በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

አመልካች ባቀረበዉ የመልስ መልስ አመልክች ለተ.እ.ታ የተመዘገበው ውል ከመግባቱ በፊት በ1997 ዓ.ም ነው፤በቤቶቹ ላይ በዕዳ ምክንያት ለሚመጣ ኃላፊነት እንወስዳለን በማለት የተስማሙ ስለሆነና ተረክበው ስመ ሀብቱም የዞረላቸው በመሆኑ ሊከፍሉ ይገባል በማለት አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ አመልካች እና ተጠሪዎች መካከል የአፓርትመንት ቤቶችን ገንብቶ ለማስረከብ የግንባታ ዉሎች የእነዚህ ዉሎች አካል እንዲሆኑ የተስማሙባቸዉ ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን መኖራቸዉ ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ ዉል ተዋዋይ ወገኖች ወደዉና ፈቅደዉ በተስማሙበት አግባብ መፈጸም እንዳለበት፣ ዉሉን የመፈጸም ግዴታ ያለበት ወገን በዉሉ መሰረት ያልፈጸመ እንደሆነ ጉድለቱን የማስተካከል ካልሆነ ለጉድለቱ ላስከተለዉ ጉዳት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት እንደሚኖርበት ስለዉሎች በጠቅላላዉ የተመለከቱት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ እንዲሁም የሕንጻ ሥራን የሚመለከቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3019-3040 ድንጋጌዎች የሕንጻ ግንባታን በተመለከተ እንደአግባብነታቸዉ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች የአፓርትመንት ቤቱን ገንብቶ ለተጠሪዎች ማስረከብ ያለበት እና ተጠሪዎችም ደግሞ ክፍያዎችን መፈጸም የሚገባቸዉ በግንባታ ዉሎቹ የዉሎቹ አካል እንዲሆኑ የተስማሙባቸዉ ዲዛይንና እስፔስፊኬሽን እንዲሁም ከፍ ሲል የተጠቀሱት አግባብነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች መሰረት መሆን እንዳለበት ግልጽ ነዉ፡፡

ይሁን እንጂ ከዚህ ቀደም የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች እና የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሁኖ በነበራቸዉ ክርክር፣ ከሳሾች በጠየቁት ዳኝነት ተከሳሽ በግንባታ ዉሉ መሰረት ግዴታዉን በመፈጸም ቤቱን እንዲያስረክባቸዉ፣ ርክክቡ በመዘግየቱ ምክንያት ለደረሰባቸዉ ጉዳት ካሳ

እንዲከፈላቸዉ፣ እንዲሁም ግንባታቸዉን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገዉን ወጪ ተከሳሽ እንዲከፍላቸዉ የጠየቁ ሲሆን፣ ተከሳሽም ተገቢ ነዉ ያለዉን ክርክር ካቀረበ በኋላ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ ያሳለፉ ሲሆን፣ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰ.መ.ቁ.95780 መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች ለክርክር መነሻ የሆኑትን ቤቶች ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ፣ አመልካች ደግሞ ተጠሪዎች አልከፈሉኝም የሚለዉን ክፍያ በሕግ አግባብ መጠየቅ እንደሚችል በመወሰን፣ ተጠሪዎች የቤቶቹ ርክክብ በመዘግየቱ የደረሰብን ካሳ እና ግንባታዉን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገዉን ወጪ አመልካች እንዲከፍለን በማለት የጠየቁት ዳኝነት ማለፉን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን ዉሳኔ ተከትሎ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክስ ከተጠሪዎች ጋር ባደረግነዉ የግንባታ ዉሎች መሰረት ያልከፈሉትን ክፍያዎች እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን እና እስከዚህ ችሎት በክርክር ላይ መሆናቸዉን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም አሁን በግራ ቀኛቸዉ መካከል ላለዉ ክርክር እልባት ለመስጠት እና ተጠሪዎች ለአመልካች ሊከፍሉት የሚገባቸዉ ክፍያዎች ምን እንደሆኑ ለመለየት የግንባታ ዉሎቹን የዉሉ አካል እንዲሆን የተስማሙበትን ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መሆን አለበት፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ለክርክር መነሻ የሆኑትን አፓርትመንት ቤቶችን ባሉበት ሁኔታ እንዲያስረክባቸዉ እና አመልካች ደግሞ ተጠሪዎች ሊከፍሉኝ ይገባል የሚላቸዉን ክፍያዎች መጠየቅ ይቻላል በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ ይዘትና ዓላማ አሁን ከቀረበዉ ክርክር አንጻር ያለዉን አንድምታ ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡ የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ መዝገብ ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ ተብሎ መወሰኑ፣ አመልካች ቤቶቹን በግንባታ ዉሎቹና የዉሎቹ አካል እንዲሆን በተስማሙበት ዲዛይንና ስፔስፊኬሽ መሰረት አጠናቅቋልና ተጠሪዎች እንዲረከቧቸዉ ማለት ነዉን? ተጠሪዎች ደግሞ በዉሉ ላይ የተመለከተዉን ሙሉ ክፍያዎችን ለአመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑን ያመለክታልን? ወይስ ቤቶቹ በተሰሩት መጠን ማለትም በጥራትም ሆነ በመጠን ባሉበት ደረጃ ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ እና ተጠሪዎች ደግሞ ተሰርቶ ለተረከቡት ሥራ ተገቢዉን ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚያመለክት ነዉ? የሚሉት ጥያቄዎች ተገቢዉን ምላሽ የሚሹ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.95780 መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈዉ ዉሳኔ ይዘትና ዓላማ ሲታይ የአሁን አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች እንዲያስረክባቸዉ ሲል አመልካች የሰራቸዉን ሥራዎች ባሉበት ሁኔታ እንዲያስረክብ ከሚያመለክት በስተቀር አመልካች ቤቶቹን በግንባታ ዉሎቹና የዉሎቹ አካል እንዲሆን በተስማሙበት ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን መሰረት መጠናቀቁን በማስረጃ መረጋገጡን ገልጾ ርክክቡ

የተፈጸመ መሆኑን ድምዳሜ ላይ ደርሶ ዉሳኔ ማሳለፉን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ይህ ችሎት አመልካች ቤቶቹን በዚህ አግባብ ሙሉ ለሙሉ ገንብቶ ያጠናቀቀና ለተጠሪዎችም ያስረከባቸዉ ስለሆነ በዉሉ መሰረት ሊከፈለዉ የሚገባዉን ሙሉ ክፍያዎችን ከተጠሪዎች መጠየቅ ይችላል የሚል አንድምታ የለዉም፡፡ አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች እንዲያስረክባቸዉ መባሉ አመልካች ላልሰራቸዉ ሥራም ጭምር በግንባታ ዉሎቹ መሰረት ሙሉ ክፍያዎችን ከተጠሪዎች መጠየቅ ይችላልና አሁን ለቀረበዉ ክስ ምንም ዓይነት መከላከያና መከራከሪያ ሳያቀርቡ ላልተሰራም ሥራ ጭምር ሙሉ ክፍያዎችን ለአመልካች ለመክፈል ይገደዳሉ የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የዉሳኔዉ አዉድ አያመለክትም፡፡ አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች እንዲያስረክባቸዉ ማለት የቤቶቹ ግንባታ በደረሱበት ደረጃ የቀረ የግንባታ ሥራ ቢኖርም እንኳን አመልካች ቀሪዉን የግንባታ ሥራ መቀጠል ሳይጠበቅበት ቤቱን እንዲያስረክብ የሚያስችል ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ እንዲረከቡ መወሰኑና ርክክቡ ለዘገየበት የጠየቁት ካሳ እና ቤቶቹን ገንብቶ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገዉን ወጪ እንዲከፈላቸዉ ጠይቀዉ ተቀባይነት ማጣቱ፣ ተጠሪዎች ላልተሰራ ሥራ ሁሉ በግንባታ ዉሎቹ ላይ የተመለከተዉን ሙሉ ክፍያ ለአመልካች እንዲከፍሉ፤ አመልካችም የተሰራዉና ያልተሰራ ሥራ ሳይጣራና ሳይለይ ሙሉ ክፍያዎችን ጠይቆ መቀበል ይቻላል ማለት አይደለም። አመልካች ይህ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ ተከትሎ ለተጠሪዎች ያስረከባቸዉ ቤቶች የተሰሩት ሥራዎች መጠን ከግንባታ ዉሎቹና የዉሎቹ አካል እንዲሆኑ በተስማሙባቸዉ ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን መሰረት ምን ያህል ነዉ የሚለዉ በብቁና ገለልተኛ ባለሙያ ተለክቶ ተገምቶ ሲታወቅ፣ ተጠሪዎች ደግሞ የቀረበዉን ግምት መሰረት በማድረግ በዉላቸዉ መሰረት ቀሪ ክፍያ የሚከፍሉ ይሆናል ማለት ነዉ። አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ማስረከብ ማለት ተሰርቶ የተጠናቀቀ ወይም ያልተጠናቀቀ ሥራዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ይህን ማለት የሚቻለዉ በባለሙያ በማስረጃ በማጣራት ነዉ። በመሆኑም አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች ሲያስረክባቸዉ ቤቶቹን በተመለከተ የተሰሩ ሥራዎችንና ግንባታዉ የደረሰበት ደረጃ በባለሙያ ሳይጣራና በተጠሪዎች በኩል ምንም ዓይነት ክርክር ሳይነሳበት በግንባታ ዉሎቹ መሰረት ሙሉ ክፍያዎች ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም።

በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ ግራ ቀኙ መካከል በተደረጉት የግንባታ ዉሎች መሰረት ተጠሪዎች ለአመልካች ሊከፍሉት የሚገባቸዉ ክፍያዎች ምንድን ናቸዉ? የሚለዉ ነዉ። በግራ ቀኛቸዉ መካከል ከተደረገዉ የግንባታ ዉል አንቀጽ 2 መረዳት እንደሚቻለዉ ተጠሪዎች ለአመልካች ክፍያዎችን የሚፈጽሙበት በአራት ዙር ሲሆን 1ኛዉ ዙርና 2ኛዉ ዙር ክፍያዎችን በተመለከተ ተጠሪዎች ለአመልካች የከፈሉአቸዉ መሆናቸዉ ያላከራከረ ጉዳይ ሲሆን፣ አከራካሪ የሆነዉ 3ኛ ዙር እና 4ኛ ዙር ክፍያዎች መሆናቸዉን መረዳት ይቻላል። በግንባታ ዉሉ መሰረት 3ኛዉ ዙር ክፍያ የሚከፈለዉ የቤቶቹ ግንባታ ተጠናቅቆ ርክክብ ሲፈጸም ሲሆን፣ 4ኛ ዙር ክፍያ ደግሞ የቤቶቹን ስመ ሀብት በተጠሪዎች ስም እንዲመዘገብ ሲደረግና የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ሲሰጥ መሆኑን ያስገነዝባል።

በዚህ መሰረት 3ኛ ዙር ክፍያ የሚፈጸመዉ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች ሲያስረክባቸዉ በመሆኑ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች ያስረከባቸዉ በመሆኑ፤ 3ኛ ዙር ክፍያዎች መጠየቁ ተገቢ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች ያስረከባቸዉ በመሆኑ፣ የቤቶቹ ግንባታ ሥራ መጠን ምን ያህል ነዉ ለዚህ ለተሰራዉ ሥራ ደግሞ ከግንባታ ዉሉ አንጻር ተጠሪዎች ለአመልካች መክፈል ያለባቸዉ ክፍያዎች ምን ያህል ነዉ የሚሉት ነጥቦች በማስረጃ ነጥረዉ ተጣርቶ ዉሳኔ ሊስጥባቸዉ የሚገቡ ናቸዉ፡፡ በግንባታ ዉሉ መሰረት ለአመልካች ሊከፈለዉ የሚገባዉ 3ኛ ዙር ክፍያ ለተሰራዉ ሥራ እስከሆነ ድረስ፤ የተሰራዉን ሥራ በብቁና ገለልተኛ ባለሙያ በማስገመት ከግንባታ ዉሉ አንጻር ተጠሪዎች ለአመልካች 3ኛ ዙር ክፍያ ዉስጥ ምን ያህል መክፈል እንዳለባቸዉ አጣርቶ መወሰኑ ተገቢ ነዉ፡፡ አመልካች ላልሰራቸዉ ሥራዎች ተጠሪዎች ክፍያ የሚከፍሉበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች ቤቶቹን ለተጠሪዎች እስካስረከባቸዉ ድረስ ለተሰሩት ሥራዎች ከተጠሪዎች ክፍያዎች መቀበል መብት እያለዉ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከደረጃና ከጥራት በታች ለተሰሩት ሥራዎች ተጠሪዎች ክፍያ ሊከፍሉ አይገባም በማለት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ከዚህ አንጻር አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪዎች ከዚህ ቀደም ላልተሰራ ሥራ ለማስጨረስ የሚያስፈልገዉ ወጪ እንዲከፈለን ብለዉ ዳኝነት ጠይቀዉ ዉድቅ የሆነባቸዉ ስለሆነ አሁን ይህን ክርክር ድጋሚ ማንሳት አይችሉም ክርክራቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሰረት ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ከዚህ ቀደም ግራ ቀኛቸዉ መካከል በነበረዉ ክርክር ተጠሪዎች ግንባታዉን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገዉን ወጪ አመልካች እንዲከፍላቸዉ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ጥያቄአቸዉ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች እንዲያስረከብ መወሰኑ የሚታወስ ነዉ፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ መሰረት ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች ካስረከበ በኋላ ተጠሪዎች ቀሪ ክፍያዎችን እንዲከፍሉት ባቀረበዉ ክስ ላይ ተጠሪዎች ለአመልካች ክፍያዎችን መፈጸም ያለበት ለተሰሩት ሥራዎች እንጂ ላልተሰሩት ሥራዎች መሆን የለበትም ብለዉ መከራከራቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 (1) መሰረት ከዚህ ቀደም ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ነዉና አሁን ማንሳት አይችሉም የሚያስብል ስላልሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያነሳዉ መከራከሪያ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡ እንግዲህ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ አመልካች ቤቶቹን ባሉበት ሁኔታ ለተጠሪዎች አስረከበ ማለት የግንባታ ሥራዎቹ የተጠናቀቁ እና ያልተጠናቀቁ ሊኖሩ ስለሚችሉ፣ ይህን መለየት የሚቻለዉ ደግሞ በማስረጃ በባለሙያ በማጣራት መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት ባለሙያ ተመድቦ እንዲያጣራ ማድረጉ ተገቢ አካሄድ ነዉ፡፡ ነገር ግን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰራዉን ሥራ ገምቶ እንዲያቀርብ የተመደበዉን ባለሙያ አሬት ኮንሰልተንት በተመለከተ አመልካች ከባለሙያዉ ገለልተኛነት ጋር በተያያዘ ያነሳዉ ክርክር በግራ ቀኙ ማስረጃ ነጥሮ ዉሳኔ

ሊሰጥበት ይገባል ያለዉን አስመልክቶ የቅሬታ ነጥብም ስላልሆነ ይህ ችሎት ይህን የዉሳኔ ክፍል አልነካዉም፡፡

ሌላዉ ግራ ቀኛቸዉን ያከራከረዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን የሚመለከት ነዉ፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 2 (13 (5))፣ 3 (1፣ ሀ)፣ 7 (1)፣ 16፣ 17፣ 18 መሰረት ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናዉን ሰዉ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 (1) ሥር እንደተመለከተዉ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለሚመለከተዉ ለግብር አስገቢ ባለስልጣን ለማስረከብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆኖ ለሚሰበስባዉ የተጨማሪ እሴታ ታክስ ደረሰኝ መስጠት ሲችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተመለከተ አመልካች ለተጨማሪ እሴት ታክስ መቼ እንደተመዘገበ ተለይቶ ከታወቀ በኋላ ተገቢ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት የለዉም ብለናል፡፡

ግራ ቀኛቸዉን ያከራከራቸዉ ሌላዉ ጉዳይ የሊዝ ክፍያ ጉዳይ ነዉ፡፡ የሊዝ ክፍያ ጉዳይ ሊስተናገድ የሚገባዉ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እንዲሁም አዋጁን ተፈጻሚ ለማድረግ በወጡት ደንብ መሰረት እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ የሊዝ ክፍያ የሚከፈለዉ ለሚመለከተዉ የመንግስት አስተዳደር አካል ነዉ፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ በግንባታ ዉሎቻቸዉ ላይ ያመለከቱት ነገር ቢኖርም በተጨባጭ ለመንግስት ሊከፍል የሚገባዉ የሊዝ ክፍያ ምን ያህል ነዉ የሚለዉ ጉዳይ በማስረጃ ነጥሮ ከታወቀ በኋላ ተጠሪዎች ሊከፍሉት የሚገባቸዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሊዝ ክፍያን በተመለከተ በማስረጃ ተጣርቶ ከታወቀ በኋላ ተጠሪዎች በድርሻቸዉ እንዲከፍሉት በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከቀረበዉ ማስረጃ አንጻር መርምሮ የኩሽና ዕቃዎችን፣ የጋራ መገልገያ ወጪ አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤት እነዚህን ነገሮች አጣርቶ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት የመለሰዉ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት ስላልተገኘ፣ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ ባለመቀበል፣ ዉሳኔዉን አጽንተነዋል፡፡

በሌላ በኩል 4ኛ ዙር ክፍያን በተመለከተ ተጠሪዎች በምን አግባብ ለአመልካች መክፈል እንደሚገባቸዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከዉላቸዉ አንጻር መርምሮ የደረሰበት ድምዳሜ እና ከዚህ ክፍያ ጋር በተያያዘ ተ.እ.ታ በተመለከተ ያሳለፈዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ አይተዉ መወሰን ሲገባዉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.179592 ሰኔ 4 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.162150 መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የግንባታዉን ሥራ ሰርቶ እያለ ከደረጃና ከጥራት በታች ስለሆኑ ተጠሪዎች ክፍያዎችን ሊከፍሉ አይገባቸዉም ያለዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ አመልካች ቤቶቹን ባስረከበበት ወቅት የተሰሩት ሥራዎች ምን ያህል እንደሆኑ በባለሙያ በማስረጃ ከተጣራ በኋላ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ ተጠሪዎች 3ኛ ዙር ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸዉ ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን፣ የሊዝ ክፍያን፣ የጋራ መገልገያ ወጪን፣ የ4ኛ ዙር ክፍያን፣ የባንክ ብድር ወለድን፣ የኩሽና ዕቃዎችን፣ አፌት ኮንሰልታንት ሙያዊ ሥነ-ምግባርን በተመለከተ ያስተላለፈዉ የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. ይህ ዉሳኔ ህዳር 3 ቀን 2014 ዓ.ም ተነቧል፡፡**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

**የሰ/መ/ቁ.** 201665

ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ-- ነ/ፈጅ ቀርበዋል

**ተጠሪ-** አቶ ኤፍሬም ደሳለኝ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበዉ ክስ አመልካች ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሠረት የተለያዩ እቃዎችን ለማቅረብ ጨረታውን አሸንፌ የተወሰኑ እቃዎችን አቅርቤ ክፍያ ተፈፅሞልኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብዛቱ 1750 የሆነ መፅሔት አንዱን በብር 562.00 ለመስራት ጨረታ አሸንፌ መፅሔቱን ካዘጋጀሁ በኋላ ሰኔ 25 ቀን 2010 ዓ.ም ለርክክብ በአመልካች ዩኒቨርሲቲ የተገኘሁ ሲሆን ርክክቡ ሳይፈፀም የአመልካች ተማሪዎች በኃይል እና በጉልበት መጽሔቶቹን ተከፋፍለዋል፤ የአመልካች የፀጥታ ሰራተኞች እና ፖሊሶች ድርጊቱን እንዲያስቆሙ ጥያቄ ባቀርብም ክልከላ ብናደርግ ሌላ ችግር ይፈጠራል በማለት ድርጊቱን ሳያስቆሙ ቀርተዋል፡፡ አመልካችም የመፅሔቱን ክፍያ እንዲፈፅምልኝ ስጠይቅ የሂሳብ ወጪና ገቢ ባልተሰራበት ለመክፈል አንችልም የሚል ምላሽ የሰጠኝ በመሆኑ የመፅሔቶቹን ጠቅላላ ዋጋ ብር 983,500.00 ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ ተጠሪ እቃዎቹን በ45 ቀናት ውስጥ የማስረከብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህም ጊዜ እስከ ሰኔ 15 ቀን 2010 ዓ.ም ነው፤ ሆኖም ግን ተጠሪ መጽሔቱን ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ከማቅረቡም በላይ ጥራቱ በውሉ ላይ በተገለፀው አግባብ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፤ መፅሔቱ እና ፎልደሩ የሚሰራው የተማሪዎችን ምርቃት ለማድመቅ ሲሆን ተጠሪ ግን አቅርቦት የፈፀመው ተማሪዎች ከተመረቁ እና ወደ ቤተሰቦቻቸው ከተበታተኑ በኋላ ነው፤ ከዚህም ባለፈ አመልካች መፅሔቱን ያልተረከበ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ግራ ቀኙ ግንቦት 01 ቀን 2010 ዓ.ም ያደረጉት ውል ተጠሪ እቃውን በ45 ቀናት ውስጥ ያማያቀርብ ከሆነ እና ይህ ጊዜ ካለፈ የውሉ ገንዘብ መጠን 10 ፐርሰንት እስከሚደርስ ድረስ በእያንዳንዱ ቀን 0.1 ፐርሰንት እንደሚቀጣ፣ አመልካችም የእቃው መዘግየት ዕቃውን ለተፈለገው ዓላማ የማይደርሰው ከሆነ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ለማቋረጥ እንደሚችል የሚያመለክት ሲሆን አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን አላቋረጠም፤ በዚህም ምክንያት መቀጮ ከመጠየቅ በስተቀር ውሉን ማፍረስ አይችልም፤ የመፅሔቶቹን ጥራት በባለሞያ በማረጋገጥ የመረከብ ኃላፊነት ያለበት እራሱ አመልካች ነው፤ ነገር ግን ይህንን ሳያደርገ መፅሔቶቹ ተማሪዎች በጉልበት እንዲወስዱት ያደረገ በመሆኑ ተጠሪ ግዴታውን አልተወጣም ለማለት አይቻልም በማለት ተጠሪ ከዚህ በፊት ሰርቶ ሳስረከበው ባይንደር የተከፈለው ብር 498,750.00 የውል ግዴታ ከተገባበት ጠቅላላ ገንዘብ ብር 1,366,440.00 ተቀናሽ ተደርጎ የሚመጣውን ብር 867,690.00 ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም አቤቱታው ተሠርዞበታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች ጥር 21 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያላቸውን ስህቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል። የአቤቱታው ይዘትም አጠር ባለ መልኩ በውል ስምምነታችን መሠረት የአከፋፈል ሁኔታን በሚመለከት ተጠሪ በጨረታው ስፔሲፊኬሽን ላይ በተገለፀው የጥራት መጠን ልክ ሲያቀርብ አመልካች ደግሞ እቃው በውሉ ላይ በተጠቀሰው መጠን እና አይነት መቅረቡን በማረጋገጥ በሞደል 19 ገቢ እንዲሆኑ ካደረገ በኋላ ክፍያ እንደሚፈፅም ተስማምተን እያለ እቃዎቹን በዚህ አግባብ ባልተረከብንበት እንደተረከብን ተቆጥሮ ክፍያ ፈጽሙ መባሉ፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በገባው የውል ግዴታ መሠረት በ45 ቀናት ውስጥ እቃውን ሳያቀርብ ተማሪዎች ተመርቀው ወደ ቤተሰቦቻቸው ከተመለሱ በኋላ ሳስረክብ መጥቼ ተማሪዎች በጉልበት ወስደውብኛል ሲል ያቀረብነውን አቤቱታ ተቀብሎ የግራ ቀኙን ውል እና የህጉን ዓላማ ያለገናዘበ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነዉ።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ግራ ቀኙ ባደረጉት የውል ስምምነት መሠረት ተጠሪ መጽሔቶቹን ለአመልካች ማስረከቡ ባልተረጋገጠበት አመልካች ተረክቧል ተብሎ ዋጋውን እንዲከፍል የተወሰነበት አግባብ ግራ ቀኙ ካደረጉት ውል አንፃር ተጠሪ ባለበት መመርምር ያለበት መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ሰበር የሰሚ ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ግንቦት 25 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሱ ሰኔ 25 ቀን 2010 ዓ.ም መፅሔቶቹን በመኪና ጭኜ ወደ አመልካች ዩኒቨርሲቲ ገብቼ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የተማሪዎች ህብረት አመራሮች ጋር ስደውል በፈተና ምክንያት ፀብ ተፈጥሮ ከግቢ ውጪ መሆናቸውን የገለፀልኝ እና የሳይንቲፊክ ዳይሬክተሩን እንዳነጋገር ከገለጹልኝ በኋላ በመካከል በግቢው ውስጥ የነበሩት የአመልካች ተመራቂ ተማሪዎች የመኪናውን ረዳት በመደብደብ መጽሔቱን የወሰዱ ሲሆን አመልካች

ሊያስቆማቸው አልቻለም፤ ይህም የአመልካች ችግር ሲሆን መፅሔቱም ጥራት እንዳለው በማስረጃ ያረጋገጥኩ ሲሆን አመልካች ግን ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ አላቀረበም፤ የመፅሔቶቹን ብዛት እና ጥራት አረጋግጦ የመረከብ ግዴታ እያለበት ያልተረከበ በመሆኑ ጥፋቱ የራሱ ነው፤ የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ግንዛቤ በመውሰድ አመልካች ክፍያውን እንዲፈፅም ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ለማስቀረብ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብበነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ በመካከላቸዉ በተደረገዉ የተማሪዎች የምረቃ መጽሔት አቅርቦት ዉል መሰረት አመልካች መክፈል የሚገባዉን የመጽሔቶቹን ዋጋ አለመክፈሉን ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ በመካከላቸዉ መጽሔት አቅርቦት ዉል መደረጉን ሳይክድ አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ መጽሔቶቹን በዉሉ ላይ በተመለከተዉ ጊዜ እና ሁኔታ መሠረት ያላስረከበ እና ርክክቡ ሳይደረግ አመልካች የመጽሔቶቹን ዋጋ ለመክፈል የማይገደድ መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪም ቢሆን በዉሉ በተመለከተዉ አግባብ የርክክብ ሥርዓት አለመፈጸሙን ሳይክድ አመልካች ክፍያዉን የመፈጸም ኃላፊነት ይኖርበታል በማለት የሚከራከረዉ መጽሔቶቹን ወደ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ከወሰደ በኋላ ተማሪዎች በጉልበት ቀምተዉ የተከፋፈሉ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በዉሉ መሠረት ርክክብ አለመደረጉን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች የመጽሔቶቹን ዋጋ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት ከድምዳሜ ላይ የደረሰዉ መጽሔቶች ወደ ግቢ መግባታቸዉንና አመልካች የመጽሔቶቹን ጥራት አረጋግጦ የመረከብ እና ተማሪዎችን የመቆጣጠር ግዴታ እያለበት ይህን ባለማድረግ ተማሪዎች በጉልበት እንዲወስዱት አድርጓል የሚል ምክንያት በመጥቀስ ነዉ፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ መሰረታዊ ጭብጥም የቀረበዉ ክስ ዉልን መሰረት ያደረገ እንጂ አመልካች ተማሪዎችን ባለመቆጣጠሩ ምክንያት የሚኖርበትን ኃላፊነት የሚመለከት ባልሆነበት እና አመልካች መጽሔቶቹን በዉሉ አግባብ ባልተረከበበት ሁኔታ አመልካች የመጽሔቶቹን ዋጋ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት የተሰጠ ዉሳኔ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ ነዉ፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቀዳሚነት እንዲያከናዉን ከሚጠበቁበት ተግባራት ዉስጥ አንዱ እና መሠረታዊዉ ለቀረበለት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉ የህግ ክፍል የመለየት ተግባር (identification of applicable law) ነዉ፡፡ አስቀድሞ ይህን ማድረግ የቀረበዉ ክስ የክስ ምክንያት ያለዉ መሆን አለመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን እና ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ካሉ አስቀድሞ በመለየት መርምሮ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉ ሲሆን፣ ጉዳዩ ወደ ሙሉ የክርክር ሂደት (full scale trial) የሚገባ ከሆነም በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉን ጭብጥ ይዞ ክርክሩን በመምራት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን ድንጋጌ በአግባቡ ለይቶ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት ያስችላል፡፡ በአጠቃላይ አስቀድሞ በጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ክፍል መለየት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከክርክር አመራር ሥርዓት ጋር በተያያዘ በሥ/ሥርዓት

ህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና ድንጋጌዎች መሠረት ባደረገ መልኩ ክርክሩን ይመራ ዘንድ ያስችለዋል። የክርክር አመራርን አስመልክቶ በህጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ጉዳዩን መምራት፣ የክርክር አመራሩ ፍትሐዊ እና ሚዛናዊ እንዲሆን በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብት እንዲከበር በማድረግ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ እንዲረጋገጥ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፤ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ፣ ተቀባይነት እና አግባብነት ያለዉን ማስረጃ ለይቶ በማስቀረብ እና በመመርመር ወሳኝ የሆኑ ፍሬ ነገሮች ነጥሮ እንዲወጡ በማድረግ ብሎም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ድንጋጌ ለይቶ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ ያስችላል። በክስ አቤቱታ ላይ የሚገለጹ ነገሮችን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 222 ላይ ከሳሽ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮችን እንዲሁም ተከሳሽ ለክሱ ምክንያት በሆነዉ ነገር ላይ በኃላፊነት የሚጠየቅበትን ሁኔታ ከሳሽ በግልጽ በክሱ ማካተት እንዳለበት፤ እንዲሁም የሚጠየቀዉ ዳኝነት በግልጽ መመልከት እንዳለበት በአንቀጽ 224 በአስገዳጅ መልክ ከደነገገባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ክፍል አስቀድሞ እንዲለይ ለማስቻል እንደሆነ ይታመናል።

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ ተጠሪ ለክሱ መሰረት ያደረገዉ አመልካች በዉሉ መሰረት የሚጠበቅበትን የመጽሔቶችን ገንዘብ የመክፈል ግዴታዉን አለመወጣቱን ነዉ። የተጠሪ ክስ ይህ ከሆነ አመልካች እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት ክርክርም ተጠሪ በዉሉ መሠረት እንዲያቀርብ የሚጠበቅበትን መጽሔት በዉሉ ላይ በተመለከተዉ አግባብ ያቀረበ መሆን ያለመሆኑ ነዉ። አመልካች ያቀረበዉ ክርክርም ይህንኑ መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ መዝገቡ ያሳያል። ተጠሪ በክሱ የግቢዉ የጥበቃ አካላትና ፖሊሶች ባለመከላከላቸዉ ተማሪዎች መጽሔቱን በጉልበት ተከፋፍለዉ ወስደዋል በሚል የገለጸ ቢሆንም ከዚህ ጋር በተያያዘ ተማሪዎች በሚፈጽሙት ጥፋት አመልካች ከዉል ዉጭ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የጠቀሰዉ ነገር ባለመኖሩ አመልካች ይህን አስመልክቶ ክርክር እና ማስረጃ አቅርቦ አልተከራከረም፤ ይህን እንዲያቀርብም የተጠሪ የክስ ምክንያት አይፈቅድለትም። ይህ በሆነበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካች ዩኒቨርሲቲ በግቢዉ ዉስጥ ያሉትን ነገሮች የመቆጣጠርና ተማሪዎች መጽሔቶቹን ሲወስዱ የማስቆም ኃላፊነት አለበት በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ከተጠሪ የክስ ምክንያት ዉጪ በመሆኑ አመልካች ክርክር እና ማስረጃ አቅርቦ ያልተከራከረበትን ፍሬ ነገር መሠረት ያደረገ እና በዚህም ምክንያት የአመልካችን የመሰማት መብት ከግምት ዉስጥ ያላስገባ መሠረታዊ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል።

ይልቁንም ከግራ ቀኝ ክርክር አኳያ ተጣርቶ እልባት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ጉዳይ ተጠሪ በዉሉ መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ መወጣት አለመወጣቱ ነዉ። እንደሚታወቀዉ ዉል ተዋዋይ ወገኖች ስለ እራሳቸዉ ጉዳይ በእራሳቸዉ ለመወሰን ያላቸዉን ነፃነት በመጠቀም የሚያደርጓቸዉ ስምምነቶችን የሚመለከት ሲሆን፣ በህግ የተመለከቱትን አስገዳጅ ድንጋጌዎችን የሚፃረር እስካልሆነ ድረስ ተዋዋዮች

የሚያደርጓቸዉ ስምምነቶች የህግ ኃይል ተሰጥቶአቸዉ ግራ ቀኝን የሚያስገድዱ ስለመሆኑ በዉል ህግ ተቀባይነት ያገኘ መርህ ሲሆን፣ በፍትሐብሔር ህጋችን አንቀጽ 1711 እና 1731 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ናቸዉ፡፡ በዚህ መልኩ የህግ ደረጃ የተሰጠዉ ተግባር በመሆኑም አመሠራረቱ፣ አፈፃፀሙ እና ዉጤቱ የሚወሰነዉ ስለጉዳዩ በሚደነግገዉ ህግ ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት በተለይም ስለዉል አፈፃፀም እና ዉጤቱ የሚደነግገዉ የአገራችን የፍትሐብሔር ህግ ተዋዋይ የተዋዋለበትን ግዴታ በዉሉ መሠረት ለሌላኛዉ ተዋዋይ የመፈጸም ኃላፊነት እንዳለበት፣ በዉሉ መሠረት በበኩሉ የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ ተዋዋይ ሌላኛዉ ተዋዋይ በዉሉ አግባብ ግዴታዉን ያልተወጣ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ይህን ግዴታዉን በፍርድ ኃይል ተገዶ እንዲፈጽም አሊያም ዉሉ እንዲሰረዝ ወይም/እና ካሳ እንዲከፈለዉ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል (የህጉ አንቀጽ 1757 እና 1771 ድንጋጌዎች ይመለከቷል)፡፡ ይህ እንደ አጠቃላይ ሆኖ ስለ የሽያጭ ዉል በተለይ የሚደነግጉትን የህጉን ድንጋጌዎች ስንመለከት ሻጭ በዉሉ ዉስጥ የተመለከተዉን ነገር ለገዥዉ በዉሉ በተመለከተዉ አግባብ የማስረከብ ኃላፊነት እንዳለበት፣ በዉል በልዩ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር የማስረከቢያ ቦታም ዉሉ ሲደረግ በነበረ መስሪያ ቤት መሆን እንዳለበት፣ ገዥዉም የገዛዉን ንብረት የመረከብ እና ዋጋዉንም ለሻጭ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት፣ በዚህ መልኩ ያልተፈጸመለት ተዋዋይ እንደነገሩ ሁኔታ ዉሉን በማስገደድ በፍርድ ኃይል ለማስፈጸም ወይም ለማሰረዝ ወይም/እና ካሳ እንዲከፈለዉ ዳኝነት መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በአንቀጽ 2274፣ 2279፣ 2303፣ 2329-2359 እና 2360 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ ሻጭ ለተሸጠዉ ንብረት ዋጋዉን ከገዥ መጠየቅ የሚችለዉ እና ገዥም ንብረቱን የገዛበትን ዋጋ ለሻጭ ለመክፈል የሚገደደዉ ንብረቱን በዉሉ በተመለከተዉ አግባብ ከተረከበ ወይም ያለበቂ ምክንያት ንብረቱን ለመረከብ ፍቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ብቻ መሆኑን፣ ገዥዉ ንብረቱን ተረክቦ ወይም መረከብ ሲገባዉ ያለ በቂ እና ህጋዊ ምክንያት ሳይረከብ ቀርቶ የንብረቱን ዋጋ ለሻጭ ያልከፈለዉ እንደሆነ ሻጭ ገዥዉ ገንዘቡን ተገዶ እንዲከፍል ወይም ዉሉ እንዲሰረዝ ወይም/እና ካሳ እንዲከፈለዉ ዳኝነት መጠየቅ የሚችል መሆኑን እና ሻጭ ይህን ዳኝነት ለመጠየቅ ግን በበኩሉ በዉሉ መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ መሆኑን ወይም ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ ስምምነት መሠረት አመልካች የመጽሔቶቹን ዋጋ ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደደዉ ተጠሪ በጨረታዉ ስፔስፍኬሽን መሠረት ዉሉ ላይ በተገለጸዉ ጥራት መሠረት ሲያቀርብ አመልካች የቀረቡት መጽሔቶች በዉሉ መሰረት ሙሉ በሙሉ በዓይነትና በመጠን መቅረባቸዉን ቆጥሮ በማረጋገጥ በሞዴል 19 መጽሔቶቹን ገቢ ያደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ በዉሉ አንቀጽ 16.1 ላይ የተመለከተ መሆኑን አመልካች ጠቅሶ የሚከራከር ሲሆን፣ ተጠሪ ይህን የዉሉን ይዘት ክዶ አይከራከርም፡፡ ተጠሪ መጽሔቶቹን በዉሉ ላይ በዚህ መልኩ በተመለከተዉ አግባብ ለአመልካች ያላስረከበ ስለመሆኑ ግራ ቀኝን ያላከራከረ ጉዳይ ሲሆን፣ መጽሔቶቹን ተጠሪ በመኪና ጭኖ በአመልካች ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ካስገባ በኋላ ተማሪዎች በጉልበት ወስደዉ መከፋፈላቸዉ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ

ተጠሪ መጽሔቶቹን በብዛት እና በጥራት በዉሉ በተመለከተዉ አግባብ ለአመልካች አለማስረከቡንና ርክክብም አለመፈጸሙን ነዉ፡፡ ይህ በመሆኑም ተጠሪ መጽሔቶቹን በዉሉ መሠረት የማስረከብ ግዴታዉን ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ተጠሪ በዉሉ መሠረት ግዴታዉን ካልተወጣ ደግሞ አመልካች ገንዘቡን በዉሉ መሠረት ለመክፈል የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ሲጠቃለልም ለዉሉ ምክንያት የሆኑትን መጽሔቶች አመልካች በብዛት እና በጥራት በዉሉ ላይ በተመለከተዉ አግባብ መቅረባቸዉን አረጋግጦ ርክክብ ባልተፈጸመበት ሁኔታ በዉሉ መሠረት ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት የለበትም፡፡ ተማሪዎቹ ለሚፈጽሙት ህገ ወጥ ተግባር የአመልካች ዩኒቨርሲቲ ከዉል ዉጪ ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ በተጠሪ የክስ ምክንያት ሆኖ ክርክር አልተደረገበትም፡፡ በመሆኑም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ተማሪዎቹ ለሚፈጽሙት ህገ ወጥ ተግባር አመልካች የፍትሐብሔር ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ለክስ ምክንያት ሆኖ ክርክር ባልቀረበበት ሁኔታ ይህን በመጥቀስ አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-49370 የካቲት 05 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 191818 ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 203358

ቀን፡- የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- 1. አቶ ደልቦ ደንድሬ -- ወኪል 2ኛ አመልካች ቀረቡ

2. ወ/ሮ መለሱ አንዳርጌ -- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ደጀኔ ጌታነህ -- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የዉል ማፍረሻ ምክንያቶችን የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ በቀን 08/01/2012 ዓ/ም ከአመልካቾች ጋር በብር 830,000.00 በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር B127/22 የቤት ሽያጭ ዉል ፈጽመናል፡፡ በዉሉ መሰረት ቃብድ ብር 20,000.00 ለአመልካቾች ከፍያለሁ፡፡ አመልካቾች እስከ ቀን 05/02/2012 ዓ/ም ድረስ በዉሉ መሰረት ቀሪ ገንዘብ ተቀብለው ቤቱን ሊያስረክቡኝ ስምምነት ብናደርግም በተባለዉ ጊዜ አላስረከቡኝም፡፡ በመሆኑም በዉሉ ምክንያት የከፈልኩት ቃብድ እና ቅጣቱን ብር 70,000.00 አመልካቾች እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ ሁለት የሽያጭ ውል አስፈርሞናል፡፡ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ፊት አልተደረገም፡፡ ባንክ ገንዘቡን ስላልፈቀደልኝ ቀብዱን መልሱልኝ ያለን ተጠሪ እንጂ እኛ ውሉን አልፈጽምም አላልንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪ ገንዘቡን ይዞ ሲመጣ እስከ 05/02/2012 ዓ/ም ድረስ አመልካቾች ቤቱን የሚመለከቱ ሠነዶች ሳያቀርቡ ቀርተው ከ06/02/2012 ዓ/ም በኋላ በማቅረባቸው እንደውሉ ያልፈጸሙት አመልካቾች ናቸው በማለት በማስረዳታቸው በውሉ በተቀመጠው ጊዜ ተገቢውን ኃላፊነት ያልተወጡት አመልካቾች በመሆናቸው ገንዘቡን ከመቀጫ ጋር ብር 70,000.00 ሊመልሱ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካቾች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

ይሕ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ውሉን የተወው ተጠሪ ነው፤ ውሉን ከተወ ቃብድ የመጠየቅ መብት የለውም፡፡ ክሱ ሲቀርብ እንደውሉ ለመፈጸም ዝግጁና ፈቃደኛ መሆናችን ገልጸን ተከራክረናል፡፡ ሠነድ በሚሟላት ግዴታችን ተወጥተናል፡፡

ዉሳኔው ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ባንክ ለተጠሪ የቤት ግዥ ዋጋ ለመክፈል መተማመኛ በሰጠበትና አመልካቾች ተፈላጊውን ሠነድ አቅርበው እያለ ቃብድና መቀጫ እንዲከፍሉ መወሰኑ አግባብነቱን ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ቤቱን አመልካች ለተጠሪ መሸጣቸው የሚካድ ነገር የለውም፡፡ ውሉን በውልና ማስረጃ ለማድረግ ተስማምተን በተፈጠረው የቃል አለመግባባት የተነሳ ውሉ ቀሪ ሆኗል፡፡ በተጠሪ በኩል የተደረገ የውል ጥሰት የለም፡፡ ውሉ የፈረሰው በአመልካቾች አለመተማመን ነው፡፡ አመልካቾች ተፈላጊውን ሠነድ በጊዜው አላሟሉም፡፡ እንደውሉ እንዲፈጸም ያልጠየቅሁት ለአመልካቾች ትዳር ብዬ ነው፤ ውሉን አመልካቾች ስላፈረሱ የቃብድ ገንዘቡንና መቀጫውን መጠየቄ ተገቢ ነው፡፡ ውሳኔው ሊጸና ይገባል በማለት ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጸመ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ መወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ በቀን 08/01/2012 ዓ/ም ከአመልካቾች ጋር በብር 830,000.00 በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር B127/22 የቤት ሽያጭ ዉል ፈጽመናል፡፡ በዉሉ መሰረት ቃብድ ብር 20,000.00 ለአመልካቾች ከፍያለሁ፡፡ አመልካቾች እስከ ቀን 05/02/2012 ዓ/ም ድረስ በዉሉ መሰረት ቀሪ ገንዘብ ተቀብለው ቤቱን ሊያስረክቡኝ ስምምነት ብናደርግም በተባለዉ ጊዜ አላስረከቡኝም፡፡ በመሆኑም በዉሉ ምክንያት የከፈልኩት ቃብድ እና ቅጣቱን ብር 70,000.00 አመልካቾች እንዲከፍሉኝ የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ባንክ ገንዘቡን ስላልፈቀደልኝ ቃብዱን መልሱልኝ ያለን ተጠሪ እንጂ እኛ ውሉን አልፈጽምም አላልንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንደሚታወቀዉ ተዋዋዮች የመዋዋል ነጻነታቸዉን ተጠቅመዉ ግዙፋዊም ሆነ ግዙፋዊ ያልሆኑ መብትና ጥቅሞቻቸዉን በተመለከተ በዉል ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ወይም ለማስተላለፍ በዉል በሚስማሙት አኳኋን መብትና ግዴታዎችን ለማቋቋም ይችላሉ፡፡ በዚህ አግባብ ተዋዋዮች ሕግ የወሰናቸዉንና የከለከላቸዉን ነገሮች በማክበርና በመጠበቅ የመዋዋል ነጻነታቸዉን ተጠቅመዉ ዉል በማቋቋም የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸዉ ሊወስኑ እንደሚችሉ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1711 አጠቃላይ መርህ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ዉል በፀና አኳኋን ተደርጓል ሊባል በሚችል አኳኋን በተዋዋዮች ፈቃድ እና ችሎታ ላይ ፣የዉሉ ጉዳይ የሚቻል፣ሕጋዊና ሞራላዊ ከመሆን አኳያ እና በሕግ ከተደነገገዉ ፎርም አንጻር ጉድለት ሳይኖርበት የተደረገ እንደሆነ ዉሉን የሚያፈርስ ምክንያት ስለማይኖር ሊፈጸም ይገባል(የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808 ይመለከቷል)፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በቀጥታ

ውሉ እንዲፈርስ የሚል ዳኝነት ባያቀርቡ በውሉ መሠረት ያልተፈጸመልኝ ስለሆነ ቃብድና መቀጫ አመልካቾች ይክፈሉኝ የሚለው ዳኝነት ውሉ እንዲፈርስና የውል መፍረስ ውጤት የሆነውን የከፈሉትን ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበ ክስ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ ዉሉ እንዲፈርስ የጠየቁት እነዚህ የዉሉ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች (Essential Elements of Contract) ጉድለት አለበት የሚል ክርክር ያላቀረቡ በመሆኑ ከዚህ አኳያ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ዉል የሚያስፈርስ ምክንያት የለም፡፡

ተጠሪ ዳኝነት ሲጠይቁ በግልጽ ውሉ እንዲፈርስ በክስ ማመልከቻቸው ላይ ያላመላከቱ ቢሆንም የከፈሉት ገንዘብ እንዲመልስ የሚለው ዳኝነት ውጤት የሚያገኘው ውሉ ሲፈርስና ወደነበሩበት ሲመለሱ በመሆኑ አመልካቾች በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ የቤቱን ስመ ሀብት ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችንና ቤቱን ለተጠሪ ለማስረከብ የገቡትን ግዴታ አለመወጣታቸዉ የቤት ሽያጭ ዉሉን ሊያስፈርስ የሚችል ምክንያት መሆን አለመሆኑ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ በቁጥር 1731/1 ስር እንደተደነገገዉ በሕግ አግባብ የተደረጉ ዉሎች በቋቋሚቸዉ ሰዎች ላይ ሕግ ነዉ፡፡በዚሁ የፍትሐ ብሔር ሕግ የዉል አለመፈጸም(non-performance of contract) ስለሚያስከትለዉ ዉጤት በሚደነግገዉ ክፍል በቁጥር 1771 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር እንደተመለከተዉ ከተዋዋዮቹ አንዱ የዉሉን ግዴታ ያልፈጸመ እንደሆነ የዉል ግዴታዉን ለተወጣዉ ሌላዉ ወገን እንደ ነገሩ ሁኔታ እንዲጠቀምበት ሕጉ ሦስት መፍትሔዎችን (Remedies) ይሰጠዋል፡፡ እነዚህም (1) ሌላኛዉ ወገን ተገዶ እንደ ዉሉ እንዲፈጸምለት (forced enforcement/performance) እንዲጠይቅ፣ (2) በሕግ ወይም በዉል በአንድ ወገን ብቻ ዉል የሚያሰርዙ ምክንያቶች ተደርገዉ የሚቆጠሩ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ(unilateral cancellation of contract based on conditions under the contract and laws) ዉሉ መሰረዙን እንዲገልጽ ወይም ዉሉ በፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲሰረዝ (Cancellation of contract by the Court) መጠየቅ እና (3) የጉዳት ካሳ (Damages) መጠየቅ የሚሉ ናቸዉ፡፡ በዚሁ ክፍል በቁጥር 1785/2 ስር እንደተደነገገዉ በዉሉ ላይ ዐይነተኛ የሆነ ዉል መጣስ ተግባር (Fundamental Breach of Contract) ካልተፈጸመ በቀር ዳኞች ዉሉ እንዲሠረዝ መወሰን እንደማይችሉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ዓላማ ተዋዋይ ወገኖች መሠረታዊ ያልሆኑ ምክንያቶችን መነሻ በማድረግ ዉል መሠረዝ እንዳይችሉ ማድረግና ዳኞችም ዉሉ እንዲሠረዝ ከመወሰናቸዉ በፊት ዉሉ ባይሠረዝ ከፍ ያለ ችግር የሚያስከትል መሆኑን እንዲያመዛዝኑ ኃላፊነት በመጣል በሕግ አግባብ ለተደረጉ ዉሎች ጥበቃ ማድረግና በተቻለ መጠን እንደዉሉ እንዲፈጸም ማድረግ ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ እየጠየቁ ያሉት አመልካቾች በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ግዴታቸዉን አልተወጡም በሚል ምክንያት በመሆኑ የዉል ግዴታ ከመወጣት ጋር በተያያዘ መጠየቅ የሚቻለዉ ዳኝነት ሌላዉ ተዋዋይ ወገን ተገዶ ዉሉን እንዲፈጽም ወይም ዉሉ እንዲሠረዝ ወይም/እና ሌላዉ ወገን ግዴታዉን ባለመወጣቱ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ካሳ መጠየቅ እንጂ ዉሉ እንዲፈርሰ መጠየቅ አይደለም፡፡አመልካቾች በዉሉ ላይ የቤቱን ስመ ሀብት ለማዞር አስፈላጊ የሆኑትን ሰነዶችና ቤቱን ለተጠሪ በውሉ በተወሰነው ጊዜ አለመስጠታቸዉ የቤት ሽያጭ ዉሉን

ሊያሠርዝ የሚችለዉ *ዐይነተኛ የሆነ የዉል መጣስ ተግባር* የሚያስከትል ነዉ ሊባል የሚችል ሲሆን እና በዉሉ የተመለከተዉ የአንድ ወር ጊዜ *ቁርጠኛ የሆነ የዉል መፈጸሚያ ጊዜ* ነዉ ሊባል የሚችል ሲሆን ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ የዉሉ ጉዳይ ቤት በሽያጭ ማስተላለፍ (መግዛት) በመሆኑ ዐይነተኛ የሆነ የዉል መጣስ ተከስቷል ሊባል የሚችለዉ ወይም በዉሉ የተመለከተዉ ጊዜ ቁርጠኛ የሆነ የዉል መፈጸሚያ ጊዜ ነዉ ሊባል የሚችለዉ የአንድ ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈጸም ማድረግ (አመልካች ሰነዶቹን አሟልተዉ አቅርበዉ የቤቱን ስመ ሀብት ወደ ተጠሪ እንዲዞር ማድረጉ) ቤቱን ለመግዛት የተፈለገበትን ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡ከዚህ አንጻር ተጠሪ አመልካቾች የቤቱን ስመ ሀብት በስሜ ለማዛወር የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ስላላስረከቡኝ ቤቱን ለመግዛት የፈለግሁበት ዓላማ ሳይሳካ ስለቀረ ከዚህ በኋላ እንደዉሉ እንዲፈጸም ማድረግ ጥቅም የለዉም በማለት በማስረጃ በማስደገፍ በስር ፍርድ ቤት አልተከራከሩም፡፡ በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ አመልካቾች የዉል ግዴታቸዉን ያልተወጡ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ሆኖም በዚህ ምክንያት የዉል ግዴታ መፈጸሚያ ጊዜ በመዘግየቱ ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ ተጠሪ ተገቢዉን ኪሳራ እንዲጠይቁ መብት ሊሰጣቸዉ ከሚችል በስተቀር በዉሉ የተመለከተዉን ጊዜ አለማክበር ዐይነተኛ የሆነ የዉል መጣስ ወይም ቁርጠኛ የሆነ የዉል መፈጸሚያ ጊዜ ተጥሷል የሚባል ባለመሆኑ ዉሉ እንዲሰረዝ የሚያደርግ ምክንያት አይደለም፡፡

ተጠሪ የቤት ሽያጭ ዉሉ በፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲፈርስላቸዉ ባቀረቡት ክስ ላይ የጠቀሱት ምክንያት ዉሉን ለማስፈረስ የሚያስችል ምክንያት አይደለም፡፡ በተጨማሪም በዉሉ የተመለከተዉን ግዴታ አመልካቾች አለመፈጸማቸዉ ዐይነተኛ የሆነ የዉል መጣስ ወይም ቁርጠኛ የሆነ የዉል መፈጸሚያ ጊዜ ተጥሷል የሚያስብል አይደለም፡፡ ስለሆነም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ዉል የሚያስፈርስና የሚያሰርዝ ምክንያት የለም፡፡ አመልካቾች በዉሉ መሰረት ስመ ሀብቱን ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ለማስረከብና እንደዉሉ ለመፈጸም ዝግጁ መሆናቸዉን በማረጋገጥ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ተከራክረዋል፡፡ ስለሆነም ዉሉን ሊያስፈርስ የሚችል የሕግ ድጋፍ ያለዉ ምክንያት በሌለበት የስር ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስና ለቃብድ የተከፈለ ብር 20,000.00 እንዲመለስ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ግራቀኙ መስከረም 08 ቀን 2012 ዓ/ም ያደረጉት የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ያደረጉ ስለመሆኑ የተማመኑ ሲሆን ውሉ በቃብድ ላይ የተመሰረተ ውል ካለመሆኑም በላይ በውላቸው ላይ ብር 20,000.00 የተከፈለው ለቅድመ ክፍያ ስለመሆኑ በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ክፍያው ቃብድ ተደርጎ መወሰዱም ውሉን ያገናዘበ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የዉል ግዴታቸዉን በጊዜው ባለመፈጸማቸዉ ምክንያት ጉዳት ደርሶብኛል በማለት ተጠሪ መቀጫ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1890(2) እንደተመለከተው ኪሣራውን የተዋዋሉት ለውሉ አፈጻጸም መዘግየት ስለመሆኑ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ሊፈጸም የሚችል ውል ላይ ኪሣራ ለመጠየቅ አይቻልም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች የውል ግዴታቸውን አለመወጣታቸውን ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ቢሆንም ውሉ ከላይ በተመለከተው

አግባብ ሊያስፈርስ የሚችል ምክንያት ባለመኖሩ፣ ውሉ ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ እና ግራቀኙ ያደረጉት ውል ላይ መቀጫው በግልጽ ለመዘግየት እንደሚከፈል ያልተመለከተ በመሆኑ ተጠሪ መቀጫ እንዲከፈላቸው ያቀረቡትን ዳኝነት ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉን በማፍረስ ለተጠሪ አስቀድመው የከፈሉት ገንዘብ ብር 20,000.00 እና መቀጫ ብር 50,000.00አመልካቾች እንዲከፍሉ የሠጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 89300 የካቲት 09 ቀን 2012 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 248652 ሕዳር 30 ቀን 2013ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የቤት ሽያጭ ዉል ሊያስፈርስ የሚችል ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ቅድመ ክፍያና መቀጫ ሊከፍሉ አይገባም ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጪ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 89300 ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መ/ቁ/207371

ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ኤልባን ጌት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪ፡- ዋቻሞ ዩንቨርሲቲ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የሽያጭ ውል አፈጻጸም የሚመለከት ነዉ፡፡ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ፡- የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪ ላይ መጋቢት 01 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ ተጠሪ ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚውሉ የህክምና ዕቃዎችን ግዥ ለመፈፀም በ2011 በጀት ዓመት ባወጣው ጨረታ ተወዳድረን ግምታቸው ብር 7,311,800.00 ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የላብራቶሪ ዕቃዎችን ለማቅረብ ጨረታውን በማሸነፍ ሶስት ምስክሮች ባሉበት በ17/05/2011 ዓ.ም በጽሁፍ ውል ፈጽመናል፡፡ በገባነው የውል ግዴታ መሰረት ስለ ዕቃዎቹ ልዩ አዋቂ ባለሙያዎችና ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አስተያየት መስጫ ቅጽ ላይ አረጋግጠው በ12/07/2011 ዓ.ም በንብረት ገቢ ደረሰኝ በሞዴል-19 ሙሉ በሙሉ ገቢ አድርገን ተጠሪም ክፍያ እፈጽማለሁ በማለት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቁጥር 0016 የብር 7,209,100.00 ቆርጠን ሰጥተነዋል፤ ተጠሪ ዕቃውን ከተረከበ በአንድ ሳምንት ውስጥ ክፍያውን መፈፀም እንዳለበት የውሉ አንቀጽ 3 እና ልዩ ሁኔታዎች በሚለው ስር ግዴታ ያለበት ቢሆንም ግዴታውን አልፈፀመም፣ ስለዚህ ተጠሪ በዕቃዎቹ ላይ ምንም ቅሬታ ሳያቀርብ ለመልካም ስራ አፈፃፀም የተያዘውን ዋስትና ብር 731,180.00 እንዲለቀቅ በ28/07/11 ዓ.ም በዋስትና ወረቀቱ ጀርባ ላይ ፈርሞ በዩንቨርሲቲው ማህተም አረጋግጦ ለዋስትና ያስያዝነው ገንዘብ ተቀብለናል፡፡ግዴታችንን 99% ከተወጣን በኋላ ብር 102,700 ዋጋ ያላቸውን ቀሪ እቃዎች በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ብናቀርብም ባለሙያዎች በሌላ መልክ ይቀየርልን በማለታቸው ለዕቃዎቹ መፈለጊያ አንድ ወር እንዲራዘም ጠይቀን በተራዘምልን ጊዜ ውስጥ ዕቃዎቹን በማስረከብ ማረጋገጫ ተቀብለናል፡፡ተጠሪ ለተረከበው ዕቃ በውሉ መሰረት ክፍያ እንዲፈጽም በተለያዩ ጊዜ ተጠይቆ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ለተረከበው ዕቃ አጠቃላይ ዋጋ የብር 7,311,800.00 ከህጋዊ ወለድ፣የጠበቃ እና ሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፍል እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በቀን 07/12/2012 ዓ.ም ጽፎ በሰጠው

መልስ አመልካች ከዕቃዎች ውስጥ አብዛኛውን ዕቃ በውሉ መሰረት ቢያቀርብም በተ.ቁ.50 ላይ ያለውን ባዮ-ሜዲካል ላብ የተባለው ዕቃ በተመለከተ በተጠሪ በተዘጋጀ ዝርዝር ሁኔታ መስፈርት መሰረት መልቲ ሄድድ ማይክሮስኮፕ ሆኖ ፋይፍ ሄድድ ማይክሮስኮፕ የተባለውን ማቅረብ ሲገባው ባይናኩላር ኦሎምፐስ ማይክሮስኮፕ የተባለውን ስላቀረበ በውሉ መሰረት እንዲያስተካክል ቢጠየቅም ፍቃደኛ አልሆነም፣ስለዚህ እንደውሉ ሳይፈጽም ስለክፍያ ክስ ማቅረብ ስለማይችል አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታ ሳይወጣ ተጠሪ ክፍያ ሊፈጽም አይችልም ተብሎ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲወሰንልን በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ያቀረበው ዕቃ ባይናኩላር ማይክሮስኮፕ እንጂ በውል የተጠቀሰው ኦሎምፐስ ፋይፍ ሄድድ ማይክሮስኮፕ የሚባለውን አለመሆኑ ተረጋግጧል፣ አመልካች ለተጠሪ ያስረከበዉ እቃ በውሉ ዝርዝር ሁኔታ የተቀመጠውን መስፈርት ያሟላ ባለመሆኑ በውሉ መሰረት ግዴታውን ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፣ ስለዚህ በውሉ የተመለከተ ግዴታውን ሳይወጣ ገንዘብ ይከፈለኝ የሚል ጥያቄ ማንሳቱ አግባብነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል እንዲታረምልን በማለት ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡-ተጠሪ የመደባቸው ጥራት አረጋጋጭ እና ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የእቃውን ትክክለኛነት አረጋግጠው መጋቢት 12 ቀን 2011 ዓ.ም በሞዴል-19 ገቢ አድርገው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና እንዲለቀቅ ተጠሪ ለኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ የፃፈው ደብዳቤ እና የፌደራል መንግስት ግዥ አስተዳደር ኤጀንሲ በውላችን አንቀጽ 28/4 መሰረት ስህተት ካለ ወዲያውኑ ማሳወቅ ሲገባው ከስምንት ወር በኋላ ተሳስቻለሁ በሚል ውል እንዲፈርስ ጥያቄ ሊያቀርብ አይገባም በማለት የግዥ አስተደደር ኤጀንሲ አመልካች ጥፋተኛ አይደለም በማለት የሰጠውን ሪፖርት ጭምር አቅርበን እያለ የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ስህተት በመሆኑ፤ የተጠሪ ምስክሮች ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ስለዕቃው እውቀት የላቸዉም የሚለው ቃል በጫና የሰጡት መሆኑ፤ ፍርድ ቤቱም ክሱን ውድቅ ማድረጉ የማስረጃ ምዘና መርህ የተከተለ አይደለም፤ አመልካች ገቢ ያደረገው ዕቃ እና በውሉ የተመለከተው እቃ መካከል መሰረታዊ ልዩነት አለ ወይስ የለም? የተጠየቀው እቃ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ በገበያ ላይ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ከሚመለከተው አካል ወይም በባለሙያ ሳያረጋግጥ እንዲሁም አመልካች ውል ከመግባቱ በፊት በሁለቱ መካከል መሰረታዊ ልዩነት የሌለ መሆኑን እና የተፈለገው ዕቃ በኢትዮጵያ ገበያ አለመኖሩን ጥር 17 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ገልፆ እያለ ይህ በዝምታ መታለፉ አግባብነት

የለውም፡፡ በውላችን አንቀጽ 10 መሰረት ዕቃዎች ላይ ጉድለት ወይም መሰረታዊ ስህተት ካለበት ወይም ቴክኒክ ኮሚቴው በስህተት የተቀበለውን ከሆነ በ28 ቀናት ውስጥ ቅሬታ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የማቅረብ መብቱን ሳይጠቀም ከ8 ወር በኋላ የአመልካችን ክስ ተንተርሶ እንደውሉ አልተፈፀመም ዉሉ ይፍረስ የሚለዉ ክርክር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23895 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪ ዕቃውን ከተረከበ በኋላ ገንዘብ አልከፍልም ማለቱን አግባብነት እና የኢ.ፌዲሪ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በቀን 25/09/2012 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ጥፋተኛ ከተደረገበት ዉሳኔ አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 09/10/2013ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በውሉ መሰረት ለማቅረብ ተስማምቶ የነበረዉ የባዮ ሜዲካል ዕቃ መልቲ ሄድድ ማይክሮስኮፕ የምርት ስያሜም ኦሎምፐስ የተባለው መሆኑን ነገር ግን አመልካች በርክክብ ወቅት ያቀረበው ባይናኩላር ማይሮስኮፕ በአንድ ጊዜ አንድ ሰው ብቻ ሊጠቀምበት የሚችል በዋጋም ሆነ በአገልግሎታቸው ሰፊ ልዩነት አላቸው፤ አመልካች ከመነሻውም በጨረታ ሰነድ ዝርዝር የተገለፀውን አቀርባለሁ ብሎ ጨረታ ካሸነፈ በኋላ ውል ለመዋዋል በቀረበ ጊዜ ዕቃውን ማግኘት አስቸጋሪ እንደሚሆን ገልጾ ባይናኩላር ለማቅረብ ጠይቆ ነገር ግን ተጠሪ በዝርዝር ከተመለከተው ውጭ እንደማይዋዋል ሲገልጽ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፀውን ለማቅረብ ተስማምቶ ውል የተዋዋለ መሆኑን፤ ርክክብ ሲፈፀምም አመልካች ከቅን ልቦና ውጪ የባለሙያዎች የልምድ እና የእውቀት ውስንነት በመጠቀም ባለሙያዎችን በማሳሳት በውል ከተስማማው ዕቃ ውጪ ብራንዱ ኦሎምፐስ በመሆኑ ብቻ እና በተጠሪ ተቋምም ከዚህ በፊት ያልነበረ በመሆኑ የትምህርት ክፍሉ ባለሙያዎችም አስፈላጊ ናቸው እንረከባቸው በማለት የሰጡትን አስተያየት እና ከባለሙያዎች ኮሚቴ የቀረበለት አስተያየት በዕቃ ርክክብ ወቅት በተፈጠረው ስህተት ምክንያት የተረከበ መሆኑን፤የተሻለ እውቀት ያላቸው መምህራን ለፈተና ከተመደቡበት ሀዋሳ ዩንቨርሲቲ ሲመለሱ ዕቃው ሰፊ ልዩነት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ ክፍያ እንዳይፈፀም ታግዶ ቆይቷል፡፡ ተጠሪም ይህንን እውነታ ለአመልካች ሲገለጽላቸው እንደውሉ ትክክለኛ እቃ ለማቅረብ በወቅቱ ሀገር ውስጥ የማይገኝ በመሆኑ ዕቃዎቹን ለማስገባት ጊዜ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ገልፀው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው መግባባት አመልካች እቃው በትክክለኛ እቃ እስከሚተካ ክፍያ እንደማይፈፀም ተስማምተን ቆይተናል፤ አመልካች ይህንን ክዶ ያልተከራከረ በመሆኑና ዕቃው ሀገር ውስጥ የለም የሚለው ክርክር በውሉ ከተመለከተው ውጪ እንዲያቀርብ የተሰጠው ፍቃድ የለም፡፡ የኢ.ፌዲሪ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተጠሪ እቃውን ትክክለኛ ነው ብሎ መረከቡን እና ጉድለትም በጊዜ ማሳወቅ ነበረበት የሚሉ ነጥቦች መሰረት በማድረግ መሆኑን፤ አመልካችም

በትክክለኛ እቃ እተካለው በማለት ተጨማሪ ጊዜ ስለጠየቀና የድርጅቱ ባለቤት በደም ካንሰር በከፍተኛ ታሞ ስለነበረ ዕቃዎቹን ፈልገው በትክክለኛ ዕቃ ይተካሉ በሚል በትዕግስት እየጠበቅን ባለበት ሁኔታ ክፍያ ጥያቄ ማቅረቡ እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ያላስገባ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የላቦራቶሪ የእቃ አቅርቦትና ሽያጭ ዉል መሰረት ለመማር ማስተማር (የባዮ ሜዲካል ላብ) አገልግሎት የሚዉሉ እቃዎችን አመልካች ለተጠሪ ማስረከቡ አላከራከረም፡፡ ሆኖም ተጠሪ እቃዎቹን ከተረከበ በኋላ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ተገዶ ክፍያ እንዲፈጽም እንዲወሰንለት አመልካች ካቀረበዉ ዳኝነት አንጻር በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መከራከሪያ አመልካች ካስረከባቸዉ እቃዎች ዉስጥ በተራ ቁጥር 50 ላይ የተገለጸዉ እቃ በዉሉ የተገለጸዉን ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ (specification) ያሟላ ባለመሆኑ ክፍያ ለመፈጸም አልገደድም የሚል ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም እቃዉ እንደዉሉ አልቀረበም በሚል ተጠሪ ክፍያ ለመፈጸም አይገደድም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ እቃውን እንደተረከበ ጉድለት ስለመኖሩ በጊዜ አላስታወቀም ወይም መቃወሚያ አላቀረበም፤ ጉድለቱም መሰረታዊ መሆን አለመሆኑ አልተጣራም በማለት ነዉ፡፡

ጉዳዩ የእቃ ሽያጭ ውልን የሚመለከት እንደመሆኑ የተከራካሪዎቹ ወገኖች መብትና ግዴታ መታየት ያለበት ስለ ልዩ ውሎች በሚል በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ(Title) አስራ አምስት ሥር ከቁጥር 2266 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሻጩን መብትና ግዴታ እና ገዢውም መብትና ግዴታ የሚዘረዝሩ ሲሆን ከዚህም ዉስጥ ገዥዉ እቃውን እንደተረከበ ሊወስዳቸው የሚገባ እርምጃዎች ምን እንደሆኑ ያመለክታሉ፡፡ ሻጩ በውሉ በተመለከተው መሠረት ትክክለኛውን እቃ ለገዢው የማስረከብ ኃላፊነት እንዳለበት እንደተደነገገው ሁሉ ገዢም እቃው በውሉ መሠረት የተሟላ አይደለም ወይም ጉድለት ያለበት ነው የሚል ከሆነ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመመርመርና የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ሕግ/ቁ/2287፣2288፣2291እና2292) ይመለከታል፡፡

እቃዉ ጉድለት አለበት የሚባለዉ ሻጩ ከሸጠዉ ነገር አንዱን ክፍል ብቻ የሰጠ እንደሆነ ወይም ሻጩ ሊሰጥ በዉል ቃል ከገባበት ልክ አብልጦ ወይም አሳንሶ የሰጠ እንደሆነ ወይም በዉሉ የተመለከተዉ ሳይሆን ሌላ ነገር ወይም ዓይነቱ ሌላ የሆነዉን ነገር የሰጠ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2288 ድንጋጌ ይዘት ያሣያል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ የመረመረዉ የስር ፍርድ ቤት በዉሉ ዝርዝር መግለጫ (specification) መሰረት አመልካች ማቅረብ የሚገባዉ (multi 5 headed Olympus micro-scope) መሆን ሲገባዉ አመልካች ያቀረበዉ (binocular Olympus microscope) መሆኑን አረጋግጦ ይህንኑ ምክንያት መሰረት በማድረግ አመልካች እንደዉሉ ግዴታዉን ሳይወጣ ክፍያ መጠየቅ አይችልም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ይህ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች የሚከራከረዉ በአንድ በኩል እቃዉ ጉድለት እንደሌለበት ተጠሪ በራሱ ባለሙያዎች እና ቴክኒክ ኮሚቴ አረጋግጦ መረከቡ፤በሌላ በኩል ጉድለት ስለመኖሩም በዉሉ በተገለጸዉ አግባብ በ28 ቀናት ዉስጥ ያላስታወቀ መሆኑን በመግለጽ ነዉ፡፡ ሻጭ የሸጠዉ ነገር እንደዉሉ ትክክል ካልሆነ ወይም ጉድለት ካለዉ ሻጭ ኃላፊነት እንዳለበት ግልጽ ነዉ፡፡ ገዥዉም የተረከበዉን እቃ በተቻለ ፍጥነት መርምሮ ጉድለቱን ለሻጭ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

ገዥዉ እቃዉ እንደዉሉ ትክክል አይደለም ወይም ጉድለት አለበት በማለት እንዲሟላ ወይም ጉድለቱ እንዲስተካከል ለመጠየቅ ያለዉ መብት በጊዜ የተገደበ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2291(1) እና 2292 ላይ እንደተመለከተዉ ገዥ የተረከበዉን እቃ ባጭር ጊዜ ዉስጥ መመርመር እና ልዩነት ካለም ባጭር ጊዜ ዉስጥ ማስታወቅ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡በእቃዉ ላይ ጉድለት መኖር አለመኖሩን ለማስታወቅ የሚቻልበት ጊዜ በስምምነት የተወሰነ ከሆነ ገዥዉ በዉል በተወሰነዉ ጊዜ ውስጥ የማስታወቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2294 ይመለከታል፡፡ ይህ ሳይፈጸም ቀርቶ እንደሆነ ገዥ በዚህ ረገድ የሚኖረዉን መብት ያጣል፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2293 ይመለከታል፡፡ ከዚህ ሁሉ ማየት የሚቻለዉ ገዥዉ የተረከበዉ እቃ ጉድለት ወይም እንደዉሉ ትክክል መሆን አለመሆኑን ባጭር ጊዜ ዉስጥ የመመርመር እና ጉድለቱን ለሻጩ የማስታወቅ ግዴታዉን ካልተወጣ በጉድለት ምክንያት የሚያነሳዉን የመብት ጥያቄ ሊያጣ እንደሚችል ህጉ ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ አኳያ የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች አጥብቆ የተከራከረዉ ተጠሪ እቃዉን ከተረከበ በኋላ ጉድለት መኖሩን በዉሉ በተገለጸዉ ጊዜ ዉስጥ አላስታወቀም በማለት ሲሆን ለዚህም በማስረጃነት የፌደራል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጄንሲ የሰጠዉን ዉሳኔ ዋቢ በማድረግ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ እቃዉ እንደዉሉ ትክክል አለመሆኑ የታወቀዉ ባለሙያዎች ከሃዋሳ ዩንቨርሲቲ ተመልሰዉ ከመረመሩ በኋላ መሆኑን እና ቀደም ሲል የተረከቡት የኮሚቴ አባላት በቂ እዉቀትና ልምድ ስለሌላቸዉ አመልካች ከቅን ልቦና ዉጪ በማሳሳት ያደረገዉ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር አኳያ እልባት የሚሻዉና መጣራት ያለባቸዉ ጭብጦች ፡-

1ኛ/ተጠሪ የተረከበዉን እቃ ትክክለኛነት የመረመረዉ ጊዜዉን ጠብቆ ነዉ ወይስ አይደለም?

2ኛ/የምርምራዉን ዉጤት ለአመልካች በዉል በተገለጸዉ ጊዜ ዉስጥ አስታዉቋል ወይስ አላስታወቀም? ተጠሪ በዉሉ በተገለጸዉ ጊዜ ካላስታወቀ ዉጤቱ ምንድነዉ?

3ኛ/እንደዉሉ ትክክል አይደለም የተባለዉ እቃ ጉድለት ሊስተካከል የሚችል መሆን አለመሆኑ?

4ኛ/ጉድለቱን ማስተካከል የማይቻል ከሆነስ ዉጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉ ናቸዉ፡፡በእነዚህ ጭብጦች ዙሪያ ግራቀኙ አለን የሚሉትን ክርክርና ማስረጃ አቅርበዉ ካሰሙ በኋላ ጉዳዩ ከግራቀኙ ዉል እና አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር ተገናዝቦ እልባት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ነዉ፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልከተዉ ተገቢዉን ጭብጥ ይዘዉ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸዉ ጉድለት መኖሩ ተመስክሯል በሚል ምክንያት ብቻ የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ዉድቅ ማድረጋቸዉ የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሣያል፡፡ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በተሟላ ሁኔታ ሳይሰማ እና ሳይጣራ የሚሰጥ ዉሳኔ የክርክር አመራር ጉድለት ብቻ ሳይሆን የተከራካሪ ወገኖችን እኩል የመሰማት መብት እና አንጻራዊ እዉነትን ከማረጋገጥ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ሊታረም እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች የሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ረገድ በሰበር መ/ቁ/37105፣ 29861፣47551፣49660 እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሰጠውን ዉሳኔ መመልከት ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ለተጠሪ ካቀረባቸዉ እቃዎች ዉስጥ 50ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተመዘገበዉ እቃ እንደዉሉ ትክክል ባለመሆኑ ተጠሪ ክፍያ ሊፈጽም አይገደድም በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ አጠቃላይ የክርክሩን ይዘት እና በግራቀኙ የተደረጉትን ስምምነት እንዲሁም አግባብነት ያላቸዉን ጭብጦች እና ማስረጃ በተሟላ ሁኔታ የተመለከተ ባለመሆኑ በሰበር ችሎት የተሰጡትን አስገዳጅ ዉሳኔዎች የሚቃረን ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4-ሐ/ሸ/ እና 10(1 /ለ) ድንጋጌዎች መሰረት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 252027 በቀን 25/05/2013ዓ.ም የሰጠዉን ፍርድ በማጽናት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/203515 ላይ በቀን 28/08/2013ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ፍርድ ቤቱን የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በተገለጸዉ ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እና በማስረጃ አጣርቶ ተቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡ይጻፍ

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰበር መ/ቁ/208266

ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ስሜነህ ዘሪሁን - ጠበቃ አለባቸው - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡1ኛ/ አቶ ጀማል ሰይድ

2ኛ/ አቶ ወንዱ ጣፊያ

3ኛ/ ወ/ሮ ኤዱጋ ድምና

} አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በዚህ ችሎት እንዲታረም በሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደተመለከትነው ክርክሩ የተጀመረው በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆን የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ገቦች ሲሆኑ የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡1ኛ ተጠሪ ባቀረበው ክስ አመልካች በ225 ካ.ሜ ላይ የተሰራውን ቤት በብር 150,000 ሸጦልኝ የስመ ንብረት የዞረልኝ ቢሆንም የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቤቱን አለቅም ስላሉ ቤቱን አስለቅቆ እንዲያስረክበኝ ወይም ውሉ ፈርሶ ገንዘቡን ከነቅጣቱ እንዲከፍል እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች ባቀረበው መልስ እኔ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ የሸጥኩት እና ስመ ሀብቱም የተላለፈለት በመሆኑ ቤቱን ያለአግባብ የያዙት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ተገደው እንዲወጡ ክስ ከማቅረብ ውጭ እኔ ልጠየቅ አይገባም፤ ቤቱን የገዛው ስም ሳይዞር ነው፤አሁን ስም ስለዞረለት ሊጠይቀኝ አይችልም በማለት የተከራከረ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ቤቱን አልሸጥንም፤ 1ኛ ተጠሪም ለመሸጥ

የሚያስችለው መብት የለውም፤በስሙ የተመዘገበው ከማዘጋጃ ቤት ሰራተኛ ጋር በመመሳጠር ነው በማለት ቤቱን ለማስረከብ አንገደድም ሲሉ መከራከራቸውን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የሸጠውን ቤት በአመልካች ስም ያልተመዘገበ እና የራሱ ያልሆነውን የሸጠ ስለሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1715(2) መሰረት ውሉ ፈራሽ ስለሆነ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ የተቀበለውን ገንዘብ ብር 150,000 የመመለስ ግዴታ አለበት በማለት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815 ምርኩዝ በማድረግ ወስኗል፡፡በ1ኛ ተጠሪ እና በጣልቃ ገቦች (2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች) መካከል ያለው የቤት ሽያጭ ውል የፀና ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን መዝገቡ ያሣያል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞበታል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም በማለት አቤቱታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት በሚመለከት አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ ጥቅምት 10/2009 ዓ.ም በተፃፈው ውል ብር 70,000 መግዛቱን፤ይህንኑ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ ብር 150,000 ጥር 14 ቀን 2009 ዓ.ም በተፃፈ ውል በሽያጭ ማስተላለፉን ፤ስመ ሀብቱ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲዞር አመልክቼ ተቃዋሚ እንዲቀርብ ማስታወቂያ ተለጥፎ ስመ ሀብቱ ለ1ኛ ተጠሪ ተላልፏል፤ይህም በስር ፍ/ቤት በተከራካሪዎች የታመነ እና ስም የተዛወረበት ሰነድም መቅረቡን፤ ስለሆነም በህጉ መሰረት የተፈፀመ ሽያጭ ውል እና ስመ ሀብቱ የዞረ እና አከራይቶ ሲጠቀም የቆየው ውሉ ይፍረስ ማለቱ ከፍተኛ መሰናክል የሚፈጥር እና የሰበር ሰሚ ውሳኔ በሰ/መ/ቁ 43424፣ 37725፣ 39540 እንዲሁም በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 36(4) የተደነገገውን የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ተፈፅሟል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በስሙ የተላለፈውን ቤት በተመለከተ ይፀናል በማለት መወሰኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የተቀበለውን ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲመለስ መወሰኑ አመልካች ሁለት ጊዜ እንዲቀጣ የሚያደርግ እና 1ኛ ተጠሪ ሁለቴ እንዲጠቀም የሚያደርግ በመሆኑ ተከራካሪዎች በህግ ዘንድ እኩል የመታየት እና ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አላግባብ ቤቱን ይዘው የሚገኙ ከሆነ በህግ እንዲለቁ ክስ ከማቅረብ ውጭ አመልካች የሚጠየቅበት እና ውሉ ከተፈፀመ ከ4 ዓመት በኋላ እንዲፈርስ እና ገንዘብ እንዲመለስ የሚደረግበት አግባብ የሌለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ እንዲታረም የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ስመ ሀብት ወደ 1ኛ ተጠሪ በዞረበት እና ቀሪ ገንዘቡንም ለአመልካች የከፈላቸው ስለመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታቸው ላይ ጠቅሰው እያለ የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ አመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ እንዲመልሱና የሚፈፀም የስም ዝውውር አይኖርም በሚል የተወሰነበት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ

ነጥቦች መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ አመልካች ይህንን ቤት ለ1ኛ ተጠሪ መሸጡንና ገንዘብ መቀበሉ እና የስም ዝውውር ለ1ኛ ተጠሪ መደረጉ ያልተካካዱ ጉዳይ መሆኑን ነገር ግን አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የሸጠው ቤት ላይ ህጋዊ መብት አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለው በስር ፍ/ቤት በጭብጥነት ተይዞ በማስረጃ ሲጣራ ተጠሪ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ በሚሸጥበት ጊዜ ቤቱ በራሱ ስም ያልተመዘገበ የንብረቱ ባለቤት በ2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ እና 2ኛ ተጠሪም ሆነ ባለቤታቸው 3ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲሸጡ ውክልና ያልሰጧቸው መሆኑ ተረጋግጧል፤አመልካች ይህንን ለማስተባበል በቂ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ አመልካች መብት ሳይኖረው በአየር ላይ በቀን 14/05/2009 ዓ.ም የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ መደረጉ የህግ ስህተት የለውም፡፡ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ከተባለ በስር ፍ/ቤት በአማራጭ የጠየኩትን ዳኝነት አመልካች ቤቱን ከማንኛውም 3ኛ ወገን ነፃ በማድረግ እንዲያስረክበኝ ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት ተከራክረዋል፡፡1ኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ ላይ አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መጥሪያ የደረሳቸው ቢሆንም መልስ ያላቀረቡ በመሆኑ የፅሁፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበት ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብ ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበነው 1ኛ ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀው አመልካች የሸጠለትን ቤት ነፃ በማድረግ እንዲያስረክብ ወይም ውል እንዲፈርስ የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ቤቱን ያለአግባብ የያዙ ሰዎችን ከሚጠይቅ በስተቀር ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የተከራከረ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ክርክር የተነሳበት ቤት በሽያጭ አለማስተላለፋቸውን እንዲሁም አመልካች ለመሸጥ የሚያስችለው መብት እንደሌለው እና ቤቱ የግል ንብረታቸው መሆኑን ገልጸው መከራከራቸውን መዝገቡ ያሣያል፡፡ ፍርድ ቤቱም የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈጸም ይችላል ወይስ አይችልም አሊያም ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ በማስረጃ አጣርቶ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል መብት እንደሌለው በማረጋገጥ ውሉ ፈርሶ ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሰጠው ውሳኔ በክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ያጸና በመሆኑ በዚህ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ስልጣን ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው የሰበር ስርዓት በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ

መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመልክት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለው ትርጉም መስጠቱ (አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል) ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የውሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የሚያስችል ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

በተለይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለውን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳው የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ውጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ውሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ግራቀኙን ያከራከረው በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ በመሰረቱ የውለታዉ ጉዳይ የሚቻል፣ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ካልሆነ እና ተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ወይም ችሎታ ጉድለት የሌለበት እንዲሁም በህግ የተደነገገውን የውል አደራረግ ስርዓት ተከትሎ ተዋዋይ ወገኖች ወደውና ፈቅደው የሚያደርጉት ውል ህግ ሆኖ የሚያስገድዳቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1678 እና 1731/1 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ እንደውሉ ያልተፈጸመለት ወገን አንድም ውሉ እንዲፈጸምለት ወይም ውሉ እንዲሰረዝና ኪሳራ እንዲከፈለዉ መጠየቅ ይችላል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1771 ይመለከታል፡፡ ዉሉ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ የሚደረገው አንድም በህግ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለማሟላቱና የዉሉ አደራረግ ጉድለት ያለበት ሲሆን ወይም ውሉ እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሰናክል ሲፈጠር አሊያም አንደኛዉ ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ለመወጣት የማይችል መሆኑ በማያጠራጥር ሁኔታ ሲረጋገጥ ወይም የውሉ አይነተኛ ጉዳይ የተነካ ከሆነ ወይም በሌላ ምክንያት በተዋዋይ ወገኖች

ስምምነት የተደረሰበት ከሆነ ነው፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808፣1784 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች ይመለከታል)፡፡ በህግ አግባብ የተቋቋመ ውል በተቻለ መጠን እንዲፈጸም ማድረግ የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነዉ፡፡

በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በ14/05/09ዓ.ም የቤት ሽያጭ ውል መደረጉ አላከራከረም፡፡ ይሁንና ቤቱ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይዞታ ስር መሆኑ ብቻ ሳይሆን አመልካቹም ቤቱን ከእነዚህ ተጠሪዎች የገዛ መሆኑንና ስመ ሀብቱ በስሙ ሳይመዘገብ ለ1ኛ ተጠሪ አሳልፎ የሸጠ መሆኑን ገልጾ የተከራከረ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ቤቱን ለአመልካች አለመሸጣቸውን ይልቁንም ቤቱን ሳይጨምር ከመሬት ይዞታቸዉ ላይ ቆርሰው መሸጣቸውን ገልጸው በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈጸም እንደማይችል ተከራክረዋል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች አከራካሪውን ቤት በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት ያለው መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡፡በፍ/ብ/ህ/ቁ 2281 እና 2282 መሰረት ሻጭ ለገዥው የሸጠውን ነገር የማያስነካ መብት ለገዥው ማስተላለፍ እና የእኔ ነው ባይ ሲመጣ ዋቢ የመሆን ግዴታ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ቤቱ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ንብረት እንደነበር ያላከራከረ እና አመልካችም ቤቱን ከእነዚሁ ገዝቻለሁ ከማለት ውጪ ቤቱን በስሙ ያስመዘገበበት ሁኔታ ስለመኖሩ የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ሌላ ህጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ የሚያስረዳ ማስረጃ አለማቅረቡን የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረው የቤቱ ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ መመዝገቡ ተረጋግጦ እያለ ውሉ ሊፈጸም አይችልም ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነው በማለት ነው፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በማወቅ በአስተዳደር አካል ማስረጃ የተሰጠው ሰው የዚሁ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ የህግ ግምት የሚወሰድ ቢሆንም ይህ የህግ ግምት ሊስተባበል እንደሚችል የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1196 ድንጋጌ ይዘት ያመላክታል፡፡ አመልካች እና ተጠሪን ያከራከረው ጉዳይ በሽያጭ የተላለፈው ቤት ስመሀብት በተጠሪው ስም የተመዘገበ ቢሆንም ቤቱን በይዞታቸው ስር አድርገው እየተጠቀሙበት ያሉት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉንም ሆነ ስመ ሀብቱ በ1ኛ ተጠሪ የተመዘገበበት ሁኔታ ተገቢነት እንደሌለዉ የበኩላቸውን ክርክር በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱም የተረጋገጠው ፍሬ ነገር የቤቱ ስመ ሀብት በአመልካች ባልታወቀበት ሁኔታ አመልካች ግዴታውን ለመፈጸም እንደማይችል በማረጋገጥ ውሉ እንዲፈርስ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን መገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ቤቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ ከውል ወይም ከህግ የመነጨ መብት ያለው መሆኑን የማስረዳት ሸክም ባልተወጣበት ሁኔታ ስመ ሀብቱ በ1ኛ ተጠሪ ስም መመዝገቡን ብቻ መሰረት አድርጎ ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ ስህተት ነው የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡

ሌላኛው የአመልካች አቤቱታ ነጥብ የስር ፍርድ ቤት በአንድ በኩል ውሉ ፈራሽ ነው ገንዘቡን ለ1ኛ ተጠሪ እንዲመልስ ወስኖ እያለ ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ ስም እንደተመዘገበ ይጸናል ማለቱ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ እና

ተጠሪው ሁለቱ እንዲጠቀም ያደረገ ነው የሚል ነው፡፡ ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባው በተጠየቀው ልክ እና አግባብብ ብቻ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 182 በግልጽ ደንግጓል፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ሰበር መ/ቁ/86510 ቅጽ 15 እና ሌሎች መዝገቦችን መመልከት ይቻላል፡፡ መዝገቡ እንደሚያሣየው የ1ኛ ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ቤቱን እንዲያስረክብ ይህ ካልተቻለ ውሉ ፈርሶ ገንዘቡን እንዲመልስለት የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካች የራሱ ያልሆነ ቤት መሸጡን በማረጋገጥ ውሉ ሊፈጸም ስለማይችል አመልካች ገንዘቡን ለ1ኛ ተጠሪ ይመልስ ካለ በኂላ የቤቱ ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ ስም እንደተመዘገበ ይጸናል ማለቱ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ መሆኑን ያሣያል፡፡ ከዚህም ሌላ በክርክሩ ሂደት እንደተገለጸው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የሸጡት ቤቱን ሳይሆን ከይዞታቸዉ ላይ መሬት ቆርሰው መሸጣቸውን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ በተለይም በቀን 13/02/08ዓ.ም እና በ10/02/09 የተደረጉ ውሎች ለስር ፍርድ ቤት ስለማቅረባቸዉ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይሁንና 1ኛ ተጠሪን እና አመልካችን ያከራከረው በቀን 14/05/2009ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አፈጻጸም እና ውሉ የሚፈርስ ከሆነ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት እንጂ ሌሎቹን ውሎች በሚመለከት የተጠየቀ ዳኝነት ስለመኖሩ መዝገቡ አያሣይም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች በሌላ አግባብ ያላቸውን የውል ወይም ሌላ የህግ ምክንያት መሰረት አድርገው የሚጠይቁትን መብት በማይነካ ሁኔታ መወሰን ሲገባው የቤቱ ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ እንደተመዘገበ ይቀራል ማለቱ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በቀን 14/05/2009ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል መብት የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ ውሉ ሊፈጸም የማይቻል ነው በማለት እንዲፈርስ እና አመልካች ገንዘቡን ለ1ኛ ተጠሪ እንዲመልስ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ጉድለት ያልተገኘበት ሲሆን በሌላ በኩል ግን የቤቱ ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ እንደተመዘገበ ይረጋል በማለት የሰጠው ውሳኔ ክፍል ዳኝነት ያልተጠየቀበት በመሆኑ እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 182 እንዲሁም የሰበር ችሎቱን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ሸ/ እና 10/1/ሐ መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1ኛ/ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ/11260 ላይ በቀን በ15/08/2013ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በቀን 14/05/2009ዓ.ም የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ እና አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ እንዲመልስ የተሰጠው ፍርድ ክፍል ባለበት ጸንቷል፡፡

3ኛ/ የቤቱ ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ እንደተመዘገበ ይረጋል በማለት የተወሰነው ከተጠየቀው ዳኝነት ዉጭ ስለሆነ ተሽሯል፡፡

4ኛ/ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5ኛ/ በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 11/10/2013ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰበር መ/ቁ/211204

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ጌታሁን ኪዳነማርያም - ጠበቃ ቴድሮስ ጌታቸው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ/ ወ/ሮ አሰለፈች በቀለ

2ኛ/ አቶ በላይነህ በቀለ

3ኛ/ ወ/ሪት የትምወርቅ በቀለ

4ኛ/ ወ/ሪት ሰናይት በቀለ

5ኛ/ አቶ ግሩም ከበደ

6ኛ/ ወ/ሪት መሰረት በቀለ

(1ኛ–6ኛ) ጠበቃ ኤልያስ አበበ - ቀረቡ

7ኛ/ ወ/ሮ ተዋበች በቀለ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ የካቲት 11 ቀን 2009 ዓ.ም በተደረገው የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ተጠሪዎች ከወላጅ እናታቸው ወ/ሮ አዛለች በየነ በውርስ ያገኙትን በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የሚገኝ ቁጥሩ 978 የሆነ ቤት በስማቸው ተዛውሮ የካርታ ቁጥር የካ/179211/05 በቀን 27/09/2005 ዓ.ም በስማቸው ተመዝግቦ የቦታ ስፋት 1396 ካ.ሜ ላይ ያረፈው ቤት በብር 11,000,000 ለአመልካች ሸጠው ውሉ ሲፈረም ብር 3,000,000 የተከፈላቸው ሲሆን ቀሪው ብር የቤቱን ስመ-ሀብት ወደ አመልካች በማዛወር ቤቱን ከሙሉ ሰነዱ ጋር ሲያስረክቡ ለመክፈል ተስማምተናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ለመፈፀም ስለዘገዩ ግዴታቸዉን እንዲወጡ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻቸው ፍቃደኛ አልሆኑም፤ውሉ የተደረገው በህጉ አግባብ በመሆኑ የማይፈጽምበት ምክንያት የለም፣ስለዚህ ተጠሪዎች ቤቱ እና ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶች እንዲያስረክቡ፤ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት እና መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርበዉ የቤቱን ስመ ሀብት ለአመልካች እንዲያዛውሩ እና ቀሪ ገንዘቡን እንዲቀበሉ፤ነገር ግን የሽያጭ ውሉ ተቀባይነት የሚያጣ ከሆነ በቀብድነት የወሰዱትን ገንዘብ አጠፌታ ብር 6,000,000 እንዲሁም የውል ቅጣት

ብር 100,000 እና ለደላላ የተከፈለው ብር 60,000 በድምሩ ብር 6,610,000 ከተከፈለበት 11/06/2009 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ፣ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ ከ1-6 ያሉት ተጠሪዎች ለአመልካች የመኖሪያ ቤት አልሸጥንም፤ውሉን አልፈረምንም፤አመልካች ከ7ኛ ተጠሪ ጋር አደረጉት የተባለው የሽያጭ ውልም ህግ በሚፈቅደው መሰረት ስርዓቱን ተከትሎ በውልና ማስረጃ ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ ያልተመዘገበና ገና በሂደት ላይ የነበረ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል አይደለም፤ስለዚህ ውሉ በህጉ መሰረት ያልተመዘገበ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው እንዲባልልን፤ ተወካይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ሲፈልግ የወካዮቹ የጥቅም ግጭት ሊፈጠር የሚችል ሁኔታ ካለ የወካዮችን ጥቅም በቅድሚያ ማሳወቅ እንዳለበት በህጉ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ 7ኛ ተጠሪ ብቻ በማስፈረም የተደረገው ውል የተከሳሾች መብትና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ በማሳሳትና በህገ ወጥ የተደረገ የመንደር የቤት ሽያጭ ውል ሊፀና አይገባም እንዲባልልንና በፍ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ወደነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰን፣ አጠፌታ እንዲከፈልልኝ የተባለው አጠፌታ ክፍያ ለመክፈል ያልተስማሙ በመሆኑ ህገ ወጥ ነው፤ የደላላውም ሆነ የቅጣት ክፍያ የሚከፈልበት አግባብ የለም፣ 2ኛ ተጠሪ የአዕምሮ ህመምተኛ እና 3ኛ ተጠሪ በዕድሜ የገፉ አዛውንት እና ሌሎች ተጠሪዎች ከሀገር ውጭ ያሉትን የወራሽነት ጉዳይም ሳይጠናቀቅ 7ኛ ተጠሪ ብቻውን ያደረገው የሽያጭ ውል ህገ ወጥ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት የተከራከሩ መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የሽያጭ ውሉ የተደረገው የማይንቀሳቀስ ንብረት ቤት ላይ መሆኑን፤ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስም ሆነ በክርክር ሂደት ውል መኖሩን አምነው አልተከራከሩም፣እንዲሁም ባቀረቡት መልስ ከ1 እስከ 6 ያሉት ተጠሪዎች ለአመልካች መኖሪያ ቤት አልሸጥንም በማለት የተከራከሩ መሆኑን፤ ውሉ የተደረገው በፍ/ህ/ቁ 1723 የተመለከተውን ድንጋጌ አሟልተው አይደለም፣ስለሆነም በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል በፍ/ህ/ቁ 1678(ሐ)፣ 1719(2) እና 1723 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተከትሎ የተደረገ ስምምነት ባለመሆኑ በህግ ፊት ዋጋ ያለው ሊፀና የሚችል ባለመሆኑ ቤቱን ያስረክቡኝ ወይም ስመ ሀብቱ ያዙሩልኝ በማለት ያቀረቡት ተቀባይነት የለውም፡፡ በአማራጭ ያቀረቡትን ዳኝነት የተከፈለውን ገንዘብ ወይም ቀብድ አጠፌታ ይከፈለኝ የተባለው ውሉ ረቂቅ በመሆኑ የተከፈለው ገንዘብ ቅድመ ክፍያ እንጂ ቀብድ አለመሆኑን

ሰነዱ ያስረዳል፤ስለዚህ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት የተቀበሉትን ቅድመ ክፍያ ብር 3,000,000 ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ ተጠሪዎች የመንደር ውሉን ክደዉ የተከራከሩ መሆኑን ጠቅሶ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 የሚያሟላ ውል ስላልሆነ ውሉ ፈራሽ ነው ሲል የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡የአመልካቹ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- ተዋዋይ ወገኖች ውል ስለመኖሩ ባልተካካዱበት ሁኔታ ውሉ ፎርሙን አልጠበቀም በሚል የህግ ውጤት የለውም ሲል የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የውሉ ፎርም አልተሟላም በሚል ውል ይፍረስ የሚል ክስ ዳኝነት ተከፍሎ ክስ ሳይቀርብለት፣ ፎርም አልተሟላም በሚል ውል ይፍረስ ተብሎ የሚሰጡ ውሳኔዎች ስህተት ናቸው በሚል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 43825፣ 53328 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ሁኔታ እያለ የስር ፍ/ቤቶች ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፡፡7ኛ ተጠሪ ከሌሎች 6ቱ እህቶችና ወንድሞቹ ህጋዊ ውክልና መሰረት ውሉን መፈፀማቸውን በግራ ቀኙ የታመነ ነው፤ተጠሪዎቹም ውክልና አልሰጠንም፣ ወኪላችን ውል አልፈፀመም፣ አልተዋዋለም የሚል ክርክር ባላቀረቡበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻር እና እንደ ውሉ እንዲፈፀምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ከ1ኛ እስከ 6ኛ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የክርክር መነሻ የሆነውን ቤት እንዲሸጡ ለ7ኛ ተጠሪ ውክልና የሰጧቸው ስለመሆኑና በተሰጠው ውክልና መሰረት የሽያጭ ውል ስለመደረጉ ባልተካደበት ውሉ ያልተመዘገበ በመሆኑ እንዲፈረስና ተጠሪዎች ከአመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ እንዲመልሱ የተወሰነበት አግባብነት ከፍ/ህ/ቁ.1723(1) እና የሰ/መ/ቁ 36887 እንዲሁም ተያያዥ ነጥቦች መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት መዝገቡ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

የተጠሪዎች ጠበቃ በቀን 01/02/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ተደርጓል ተብሎ የቀረበው የቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊ ስርዓቱን

ተከትሎ የተደረገና የሚፀና ውል የለም፣ ምክንያቱም ከ1ኛ እስከ 6ኛ ተጠሪዎች ቤቱን ለተጠሪ አልሸጥንም፣ የሽያጭ ውልም አልተዋዋልንም፣ የሽያጭ ገንዘብም አልተቀበልንም፡፡ አመልካች ከ7ኛ ተጠሪ ጋር አደረጉት የተባለው የቤት ሽያጭ ውልም ቢሆን ህግ በሚፈቅደው መሰረት ሥርዓቱን ተከትሎ በውልና ሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ ያልተመዘገበና ገና በሂደት ላይ የነበረ በመሆኑ ውሉ በህጋዊ መንገድ ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡የቤት ሽያጭ የለም እንጂ አለ እንኳን ቢባል ከመጀመሪያ ህጋዊ ባለመሆኑና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል መስፈርት ጠብቆ ያልቀረበ ጉድለት ያለበት በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰጠቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ተፈጽሟል የተባለው ውል በተንኮል የተቀነባበረ የመንደር ውል ከቅን ልቦና ውጭ የተጠሪዎች መብት የሚጎዳና ህግን የሚፃረር በመሆኑ ሊፀና አይገባም፡፡ውል እንዲፈርስ አልጠየቁም የተባለው በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ ክርክር እና ውል መኖሩም እኛ አናውቅም ግማሾችን ከሀገር ውጭ የምንኖር፣ 1ኛ ተጠሪ እድሜያቸው ከ80 ዓመት በላይ የሆኑ ውል ለማዋዋል የማይችሉ፣ 2ኛ ተጠሪ የአእምሮ ህመምተኛ በአማኑኤል የሚታከሙ በመሆኑ መቃወሚያ ማቅረብ አልተቻለም፡፡የስር ፍ/ቤት ውሉ ፈራሽ ነው ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ የማይነቀፍ በመሆኑ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ከሰበር ችሎት ዉሳኔዎች ጋር መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት ዋና ዓላማ በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እና አተገባበር እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን ቀደም ሲል ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች መሰረታዊ የህግ ስህተት ምንነት አመላካች ዉሳኔዎች መስጠቱ የሚታወቅ ሲሆን ጥር 13 ቀን 2013ዓ.ም የጸደቀዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013

በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ ወይም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለው ትርጉም ሰጥቷል፡፡(አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል)፡፡በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር ከሀ-ሸ እንደተዘረዘረው በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚችል የመጨረሻ ውሳኔ፣ፍርድ፣ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ህግን አለ አግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ህግ የሚጠቅስ፤ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፣በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋና ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፣ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ውሳኔ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ ውሳኔ ጉዳይ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ስለዚህም ለሰበር የቀረበው ጉዳይ ከእነዚህ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ግራቀኙን ያከራከረው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል በፍርድ ሃይል ሊፈጸም የሚችል የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡ ከስር መዝገብ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪዎች ቤት አልሸጥንም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በ7ኛ ተጠሪ እና በአመልካች መካከል ተደርጓል የተባለው ውልም ተገቢውን ስርዓት ተከትሎ አልተደረገም፤ የጸና የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት በዝርዝር መከራከራቸውን ያሣያል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ከተጠሪዎች ክርክር በመነሳት ተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ውል ክደዋል፤ ውሉም የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1678፣1719(2) እና 1723 ድንጋጌዎች መሰረት የተደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች ውሉን አምነዋል፤ የፎርማሊቲ ጉዳይ ማንሳታቸዉ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰበር ችሎቱ ውሳኔና ህጉን የሚቃረን ነው በማለት ነው፡፡

ግራቀኙን ያከራከረው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል አፈጻጸም ጉዳይ ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ወይም ሌሎች መብቶችን ለማስተላለፍ ወይም ለማቋቋም የሚደረግ ውል በጽሁፍ እና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት መደረግ እንዳለበት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723/1/ ድንጋጌ ይዘት ያሥገነዝባል፡፡እንደውለታው ዓይነት ወይም በህግ የተደነገገው የጽሑፍ

ውል አደራረግን ሥርዓት አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 (ሐ)፣ 1719(2) እንደተመለከተው በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል አስፈላጊ የሆነውን የውል አደራረግ ሥርዓት አሟልቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡በዚህ አግባብ ያልተደረገ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል እንደረቂቅ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1720(1) እና 1723 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡የምዝገባው ሂደት ባልተሟላበት ሁኔታ ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ሕጋዊ ነዉ ሊባል እንደማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.21448 ግልጽ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በሌሎችም መሰል ክርክሮች ላይ ተመሳሳይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ሰበር መ/ቁ/34803 ቅጽ8፣ መ/ቁ/ 78398 ቅጽ14 እና ሌሎች መዝገቦች መመልከት ይቻላል፡፡የሰበር ችሎት ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡(መ/ቁ21448 ይመለከታል)፡፡ይኸውም የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲረጋገጥ (authentication) የማድረጉ አስፈላጊነት በተዋዋይ ወገኖች መካከል የፀና ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ወይም ለማስረዳት ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ (registration) ዓላማ ደግሞ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረዉ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡በሌላ በኩል ሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ/36887 በሰጠዉ ውሳኔ ላይ እንዳመላከተው በሰበር መ/ቁ/ 21448 ላይ የተሰጠው ትርጉም ተከራካሪ ወገኖች በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን አምነው በውልና ማስረጃ አካል ባለመመዝገቡ ብቻ ውል የለም በሚል የሚቃወሙ ተከራካሪዎችን የሚያመለከት አይደለም በማለት ውሉ ተፈጻሚ ሊደረግ እንደሚችል ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡የዉሳኔው መነሻ ምክንያት በፍ/ብ/ህግ ቁ/1723/1/ መሰረት የሚከናወነው ውሉን ማረጋገጥ ዋና አላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ በማስረጃነት እንዲያገለግል በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የተያዘዉን ክርክር ስንመለከት ተጠሪዎች በስር ፍርድ በሰጡት መልስ ‹‹**<u>ቤቱን አልሸጥንም</u>**›› ካሉ በኋላ ሌሎች የውል ፎርማሊቲ ክርክር ማቅረባቸው የሽያጭ ውሉን ማመናቸውን ያሣያል በማለት አመልካቹ የሚከራከር ቢሆንም የተጠሪዎች ዝርዝር መልስ ይዘት እንደሚያሣየው የሽያጭ ዉል የለም፤የቀረበው ሰነድም ረቂቅ ነው በማለት በግልጽ መከራከራቸዉ ውሉን ማመነቸውን የሚያሳይ አይደለም፡፡ይልቁንም የቤት ሽያጭ ውል አለመፈጸማቸውን ክደው መከራከራቸውን ያሣያል፡፡በውክልና ስልጣን ተዋውለዋል የተባሉት 7ኛ ተጠሪ ውሉን በግልጽ ስለማመናቸው አያሳይም፡፡ተጠሪዎች ቤቱን አልሸጥንም፤የቀረበው ሰነድም ረቂቅ ነው ብለው ክደው ስለተከራከሩ ውል እንዲፈጸምለት

የጠየቀው አመልካች የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን ማስረዳት የሚችለው በህጉ ቅቡልነት ያለውን በአዋዋይ ፊት የተረጋገጠ ሰነድ በማቅረብ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723(1) እና የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 21448 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ ስለዚህም ይህ ሰበር አጣሪ ችሎት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት በሰበር መ/ቁ/ 36887 ላይ የሰጠው ውሳኔ እንደሆነ አድርጎ የያዘው ጭብጥ በክርክሩ የተረጋገጠውን ፍሬነገር ያገናዘበ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ውሉን በግልጽ ባላመኑበት ሁኔታ አመልካች ውሉ በጽሁፍ መደረጉን ብቻ ሳይሆን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተረጋገጠ ሰነድ ባለማቅረቡ የጸና የቤት ሽያጭ ውል የለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

በሌላ በኩል ውሉ ረቂቅ ነው አመልካቾች ተገደው የሚፈጽሙት የቤት ሽያጭ ውል የለም ከተባለ ግራ ቀኙ ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ተገቢ ነው፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው አማራጭ የዳኝነት ጥያቄ ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ይሁንና አመልካች በአማራጭ የጠየቀው ዳኝነት ተጠሪዎች የተቀበሉትን ገንዘብ አጠፌታ እንዲሁም ቅጣት እና ደላላ ወጪን ጨምሮ ገንዘቡን ከተቀበሉበት 11/06/2009ዓ.ም ጀምሮ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት የጠየቀ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ክርክራቸውን እና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪዎች የተቀበሉት ሶስት ሚሊዮን ብር መሆኑንና ገንዘቡም ቀብድ ሳይሆን የሽያጭ ዋጋ ከፊል (ቅድሚያ) ክፍያ መሆኑን አረጋግጧል፡፡አመልካቾች የተቀበሉት ቀብድ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የተቀበሉትን ገንዘብ ያህል መመለስ እንጂ አጠፌታ እንዲከፍሉ አይገደዱም፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1885(2) እና 1815(1) ድንጋጌ ይዘት ይህንኑ ያመላክታል፡፡ቀብድ ነው ቢባል እንኳን ተጠሪዎች ውሉ አለመደረጉን ክደው በተከራከሩበት እና ውሉ መደረጉን የሚያሳይ በህግ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ውሉ ውጤት ሊኖረው የማይችል በመሆኑ እና ቀብድ እና ውጤቱን አስመልክቶ በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በህግ አግባብ የሚደረግ ውልን ታሳቢ አድርገው የተቀረጹ ከመሆናቸው አንጻር ግራቀኙ የተቀባበሉትን ገንዘብ ከመመለስ ባሻገር አጠፌታ ለመመለስ አይገደዱም፡፡ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ሶስት ሚሊዮን ብር ብቻ እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡ወለዱን የማይከፍሉበት ምክንያት ስለመኖሩ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ምክንያት የለም፡፡ገንዘቡ የተከፈለው ውሉ እንዲፈጸም በሚል እንደመሆኑ ምንም እንኳን ተጠሪዎች ገንዘቡን ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ወለድ እንዲታሰብ አመልካች የጠየቀ ቢሆንም ገንዘብ ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ወለድ ሊታሰብ የሚችልበት ምክንያት የለም፤ በመሆኑም

ተጠሪዎች ገንዘቡን ይዘዉ በመቆየታቸዉ ያለአግባብ ሊበለጽጉበት ስለማይገባና ውሉ ባለመፈጸሙ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ወለድ እንዲታሰብ ማድረግ ፍትሃዊ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለል የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የሚደረግ ውል በህግ የተወሰነውን ፎርም ተከትሎ እንዲደረግ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ ወይም ጠቀሜታ እንዲሁም ባህርይ አንጻር ጥበቃ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ይታወቃል፡፡የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 1723 ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ የተቀረጸ ነው፡፡ስለሆነም ውሉ በጽሁፍ መደረጉ ብቻ ሳይሆን በሚመለከተው አካል ዘንድ እንዲረጋገጥ ማድረግ የተዋዋይ ወገኖች ግዴታ በመሆኑ ይህ ባልተፈጸመበት ሁኔታ ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለዚህም ሰበር ችሎት ውሉ መደረጉ በግራቀኙ ከታመነ (መ/ቁ/ 36887 እና ሌሎች መሰል መዝገቦችን ይመለከታል) ህጋዊ ዉጤት እንደሚያስከትል ትርጉም የሰጠ ቢሆንም የትርጉሙ ወሰን የድንጋጌውን ዓላማ(አንቀጽ 1723) ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡የድንጋጌው ዓላማ የጸና ውል ስለመኖሩ የሚቀርብ ማስረጃ በውል አዋዋይ ፊት የተረጋገጠ ሰነድ መሆን እንዳለበት ያሣያል፡፡ሰበር ችሎቱ የሰጠው ዉሳኔ ተፈጻሚ የሚሆነው የቤት የሽያጭ ውሉ መደረጉን በግልጽ አምነው የፎርም ክርክር የቀረበ ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የውሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ከዚህ ትርጉም አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ውሉ መደረግ አለመደረጉን አስመልክቶ መታየት ያለበት ጉዳይ ተከሳሽ ውሉን በግልጽ አለመካዱ ሳይሆን ውሉን በግልጽ ማመኑ ነዉ፡፡ስለዚህም ውሉ በአንቀጽ 1723 መሰረት ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ ባይሆንም ውሉ ህጋዊ ዉጤት የሚኖረው ተከሳሽ ውሉን በግልጽ ካመነ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

በዚህ ጉዳይ ተጠሪዎች ቤቱን አልሸጥንም፤ውሉም ረቂቅ ነው ብለው መከራከራቸው ውሉን አምነዋል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶችም ተጠሪዎች ውሉን ክደው መከራካራቸዉን በማረጋገጥ የሰጡት ውሳኔ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል አደራረግ ስርዓት በሚመለከት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723/1/ የተደነገገውን እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 21448 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10(1ለ) መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ ዉሳኔው ላይ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ/201863 ላይ በቀን 13/09/2013ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/ተጠሪዎች በረቂቅ ውሉ መሰረት የተቀበሉትን ብር ሶስት ሚሊዮን በስር ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡

3ኛ/ በዚህ ችሎት የተደረገውን ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በ16/11/2016 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**አ/ኃ**

የሰ/መ/ቁ. 216155

ቀን፡- ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ጉታ፡- ጠበቃ አበበ ጉታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

2. የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ

3. የጅግጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት

} ዓ/ሕግ መሀመድ ሁሴን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ለመስራት ውል ገብቼ በርካታ ማሽነሪዎችና ዕቃዎችን ወደግንባታ ቦታው ወስጃለሁ፡፡ ለግንባታው ለሚጠይቀው ከፍተኛ ገንዘብ ሲባል በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን በማስያዝ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና መጋዘን፣ ወርክሾፕና የሌሎች ሰዎችን ንብረት በማስያዝ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ገንዘብ በመበደር የግንባታ ፕሮጀክቶችን በመፈጸም ከፍተኛ የሆነ ብደርና ዕዳ ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያለምንም ጥፋት የግንባታ ሥራ ውሉን በመቋረጥ ለመረጧቸው ሌሎች የኮንስትራክሽን ድርጅቶች በንዑስ ግንባታ የሥራ ውል አስተላልፈዋል፡፡ ማሽነሪዎች፣ መኪናዎች እና ዕቃዎች ከሶማሌ ክልል እንዳይወጡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሰጡት ሕገ-ወጥ የዕግድ ትዕዛዝ ከማገዳቸውም በተጨማሪ ንብረቶችን እያከራዩ በሕገ-ወጥ መንገድ ሲጠቀሙባቸው ነበር፡፡ 1ኛ ተጠሪ መፍትሔ እንዲሰጠኝ ብጠይቅም ምላሽ ሊሰጠኝ አልቻለም፡፡ ስለሆነም፡-

1. ከ1991 ዓ/ም እስከ 2006 ዓ/ም ማሽነሪዎችና መኪናዎች ባከራይ ላገኘው የምችለው ገቢ ስለተቋረጠ የኪራይ ገንዘብ ብር 127,938,480.00 እና ወለድ ብር 15,890,976.14 በድምሩ ብር 143,829,456.14 እንዲከፍሉ፣

2. ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን የሸጠው በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 32,000,000.00 እንዲከፍሉ፣
3. ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ መጋዘን፣ ወርክሾፕና ቢሮ የሸጠ በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 14,650,000.00 እንዲከፍሉ፤
4. በሪቴንሽን የተያዘ ገንዘብ ብር 176,566.40 በድምሩ ብር 192,457,377.62 እንዲከፍሉ እንዲወሰን የሚል ነው።

ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ አመልካች ውል ያደረጉት ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ሊከሰስ አይገባም። ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው። ክሱ በይርጋ የታገደ ነው። ውሉ የተቋረጠው በአመልካች ጥፋት ነው። የተበደሩት ለፕሮጀክቱ አይደለም። ማሽነሪዎችና ዕቃዎች ከሕግ ውጭ አልተያዙም፣ የተያዙት አመልካች እንደ ውሉ ያልፈጸመው መኖሩን እስኪረጋገጥና በፍርድ ቤት እግድ ነው። የተጠየቀው የጉዳት ካሳ የተጋነነ ነው፤ ለክሱ ኃላፊነት የለብንም ብለዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ውደቅ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ የተከሰሰው የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የበላይ አካልና ተቆጣጣሪ ከመሆኑም በላይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የፈጸሙት ተግባር መፍትሔ እንዲሰጥ ሲጠየቅ ምላሽ ያልሰጠ በመሆኑ በሕግ ያለበትን ኃላፊነት አልተወጣም በመባሉ ስለሆነ ክሱ በእርሱ ላይ መቅረቡ ተገቢ ነው። የአመልካች ንብረት የሆኑትን ማሽነሪዎች ተጠሪዎች በመያዝ አመልካች ጥቅም ያጡ በመሆኑ ቢያከራዩ ሊገኝ የሚችለው ገቢ ብር 96,447,600.00 እንዲሁም ሪቴንሽን ገንዘብ ብር 176,566.40 ተጠሪዎች ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል። ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የሚከፈል በመሆኑና አመልካች ማሽነሪዎች በተጠሪዎች ተይዘው ለቆዩበት ጊዜ የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው ስለተወሰነ በባንክ የተሸጡ ንብረቶች ዋጋ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ከደረሰባቸው ጉዳት በላይ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል። አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባለመቀበል ሠርዟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ማሽነሪዎች በተጠሪዎች መያዛቸው አከራይቼ አገኝ ከነበረው ገቢ በተጨማሪ ተደራራቢ በገንዘብ ሊተመን የሚችል እና ሊተመኑና ዋጋ ሊወጣላቸው የማይችል ተደራራቢ ጉዳቶች ደርሰዋል። ማሽነሪዎች በመያዛቸው ሰርቼ ብደሩን መክፍል እንዳልችል አድርገው ንብረቴ የተሸጠ በመሆኑ በባንክ የተሸጡትን ንብረቶች የገበያ ዋጋ ብር 46,650,000.00 ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች በባንክ ዕዳ ንብረቴ ተሸጦ ጉዳት ደርሶብኛል በማለት የጠየቁት

ዳኝነት ውድቅ መደረጉ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከፍ/ሕ/ቁ. 2091 አንጻር ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ይዘትም ለክሱ ኃላፊነት የለብንም፣ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተወሰነው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 204625 አቅርበን በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ አመልካች ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ካሣ እንዲከፈለው ስለተወሰነ በሐራጅ ለዕዳው በባንክ የተሸጡ ንብረቶችን ዋጋ ልንከፍል አይገባም፡፡ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ ከ1991 ዓ/ም እስከ 2006 ዓ/ም ማሽነሪዎችና መኪናዎች ባከራይ ላገኘው የምችለው ገቢ ስለተቋረጠ የኪራይ ገንዘብ ብር 127,938,480.00 እና ወለድ ብር 15,890,976.14 በድምሩ ብር 143,829,456.14፣ ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን የሸጠው በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 32,000,000.00፣ ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ መጋዘን፣ ወርክሾፕና ቢሮ የሸጠ በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 14,650,000.00፤ በሪቴንሽን የተያዘ ገንዘብ ብር 176,566.40 በድምሩ ብር 192,457,377.62 ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ለክሱ ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር የውል ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በክስ ማመልከቻ የጠቀሱ በመሆኑ የቀረበው ዳኝነት በውል ግንኙነት መሠረት የተያዘ ገንዘብ ክፍያ እንዲፈጸም እና የውል ጉዳት ኪሣራን የሚመለከት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አመልካች የውል ግንኙነት የሌላቸው ሲሆን ክሱ በ1ኛ ተጠሪም ላይ የቀረበው አመልካች ውል የወሰዱበትን ሥራ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ለ3ኛ ወገን በማስተላለፍ ሂደት ላይ በመሳተፍና ለደረሰብኝ ጉዳት መፍትሔ እንዲሰጠኝ ስጠይቀው ካለበት ኃላፊነት አንጻር ተገቢውን ምላሽ ባለመስጠት ጉዳት እንዲደርስበኝ አድርጓል በሚል ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት ያደረገ ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ክሱ ሁለት የክስ ምክንያቶች ተጣምሮ የቀረበበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ የአመልካች ንብረት የሆኑትን ማሽነሪዎች ተጠሪዎች በመያዝ አመልካች ጥቅም ያጡ በመሆኑ ቢያከራዩ ሊገኝ የሚችለው ገቢ ብር 96,447,600.00 እንዲሁም ሪቴንሽን ገንዘብ ብር 176,566.40 ተጠሪዎች ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል፤ ካሣ ከደረሰው

ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የሚከፈል በመሆኑና አመልካች ማሽነሪዎች በተጠሪዎች ተይዘው ለቆዩበት ጊዜ የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው ስለተወሰነ በባንክ የተሸጡ ንብረቶች ዋጋ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ከደረሰባቸው ጉዳት በላይ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ ኃላፊነት አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚለው ጉዳይ ተጠሪዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 204625 ያቀረቡት ይግባኝ መዝገብ ላይ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ለዚህ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከማሽነሪዎች ሊገኝ ከሚችለው የተቋረጠ ገቢ በተጨማሪ በባንክ ዕዳ ለተሸጡ ንብረቶች የገበያ ዋጋም ተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል የሚል ነው፡፡ ውል ያልፈጸመ ወገን በፍ/ሕ/ቁ. 1790 እና 1791 እንደተመለከተው ያልተፈጸመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውል ያልፈጸመው ወገን የደረሰውን የጉዳት ኪሣራ መክፈል አለበት፡፡ የሚከፈለው ኪሣራ ተዋዋዮች በፍ/ሕ/ቁ. 1889 መሠረት አስቀድመው የወሰኑት ከሆነ በውሉ የተመለከተውን መጠን ሲሆን ተዋዋዮች አስቀድመው ኪሣራውን ካልወሰኑ በክርክር ሂደት ፍርድ ቤት ኪሣራውን በማስረጃ አጣርቶ የሚወሰነው ይሆናል፡፡ ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት ያደረገ ሲሆን ካሣ በፍ/ሕ/ቁ. 2090(1) እንደተመለከተው ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ ወይም ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት መርህ ተቀምጧል፡፡ ሕጎቹ የተለያዩ ቢሆኑም ልዩነቱ ካሣው የሚከፈልበት ግንኙነት መሠረት እንጂ ዓላማቸው ተመሳሳይ ነው፤ እርሱም ጉዳት የደረሰበትን ሰው መካስ ነው፡፡ ሕግ አውጪው ሕግ ሲያወጣ ጉዳት የደረሰበት ሰው ከጉዳቱ እንዲያተርፍ ታሳቢ አድርጓል ሊባል አይችልም፡፡

አመልካች ንብረቶቻቸው ከውል እና ከሕግ ውጭ በተጠሪዎች ተይዘዋል በሚል በንብረቶች ሊያገኙት ይችሉት የነበረው ገቢ ታስቦ በሥር ፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ አመልካች በብድር ለወሰዱት ገንዘብ ባለመክፈላቸው ንብረታቸው ተሸጦ ዕዳው መከፈሉን በመጥቀስ ማሽነሪዎች በተጠሪዎች ባይያዙ ኖሮ ዕዳውን ሰርቼ በመክፈል ንብረቶችን ማስቀረት እችል ስለነበር ለጉዳቱ ተጠሪዎች ካሣ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ንብረታቸው በሐራጅ የተሸጠው ለወሰዱት ዕዳ ክፍያ በመሆኑ እንደጉዳት የሚታይ ካለመሆኑም በላይ አመልካች ማሽነሪዎቹ በእጃቸው ቢቆዩ ከገቢው ቀንሰው ለዕዳው ክፍያ ሊያውሉት የሚችሉ በመሆኑና በሥር ፍርድ ቤት የ14 ዓመት ሙሉ ገቢ የተወሰነላቸው በመሆኑ፤ ለተሸጠው ንብረት ዋጋ በተጨማሪነት ከታሰበላቸው ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝና ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚለውን መርሕ የሚጥስ ትርፍ ክፍያ ስለሚሆን የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን የገበያ ዋጋው ብር 32,000,000.00 የሆነ እና በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ መጋዘን፣ ወርክሾፕና ቢሮ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 14,650,000.00 ተጠሪዎች ሊከፍሉ አይገባም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 204961 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 236316 የካቲት 18 ቀን 2013 ዓ/ም በባንክ ዕዳ ለተሸጡ ንብረቶች ዋጋ ተጠሪዎች የመክፈል ኃላፊነት የለባቸውም በሚል የሠጡት ውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰበር መ/ቁ/215762

ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡-1ኛ/ አቶ ጳውሎስ ኦርጂኖ

2ኛ/ ወ/ሮ አመለወርቅ ሁሴን } አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ኤጌዶ- ተወካይ ታደሰ ኤጌዶ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በዚህ ችሎት እንዲታረም በሚል ነዉ፡፡

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል አፈጻጸም የሚመለከት ጉዳይ ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- ክርክሩ የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በአሁኑ አመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካቾች በዱራሜ ከተማ ውስጥ በ460.6 ካ.ሜ ላይ ያላቸውን መኖሪያ ቤት በብር 2,250,000.00 በቀን 24/01/2012 ዓ.ም በተደረገው ውል ሽጠውልኝ ቀብድ ብር 1,000,000 መቀበላቸዉን እንዲሁም የተጠሪ ወኪል በ1ኛ አመልካች የባንክ ሂሳብ ብር 800,000.00 ገቢ በማድረጋቸው በአጠቃላይ ብር 1,800,000.00 የተቀበሉ መሆኑን ገልጸ አመልካቾች በውሉ መሰረት ቤቱን እንዲያስረክቡ እንዲወሰን ይህ ካልሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1885(2) መሰረት የተቀበሉትን ቀብድ አጠፌታ እና ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ህጋዊ ወለድ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸዉ ባቀረቡት መልስ የቤት ሽያጭ ውል ሲደረግ ቀብድ መሆኑ በውሉ ስላልተገለጸ ቀብድ ነው በሚል አጠፌታ መጠየቅ ተገቢ ስላለመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 26996 አስገዳጅ የህግ ትርጉም መስጠቱን፤በውልም ሆነ በወኪላቸው ገንዘብ ያልተቀበሉ ከመሆኑም በላይ የሽያጭ ውሉ በሚመለከተው አካል ፊት ያልተደረገ እና ያልተመዘገበ የማይፀና ረቂቅ ውል በመሆኑ ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለብንም፤የቀብድ ውል የሌለና የባንክ ሰነድ ቀብድ መሆኑን የሚገልጽ አይደለም፤ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መከራካራቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል በቀን 24/01/2012 ዓ.ም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑን፣1,000,000.00 ብር ቀብድ ሳይሆን ለቤቱ ሽያጭ የተከፈለ መሆኑን፣ብር 800,000ለቤት ሽያጭ የተከፈለ አለመሆኑን፣በሽያጭ ከተዋዋሉበት ዋጋ ቀሪውን ብር ተጠሪ ለአመልካቾች ከፍሎ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል እንዲታረምልኝ በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ከመረመረ በኋላ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህንን ዉሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፡-የሽያጭ ውል ነዉ የተባለዉ 2ኛ አመልካች በሌለሁበት እና ባልፈረምኩበት ድርሻዬን በሚመለከት ልዩ ጥንቃቄ አድርጎ መወሰን ሲገባው እና ተጠሪ የጠየቀው የቀብድ አጠፌታ እንዲመለስ የሚል ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ ከተጠየቀው የዳኝነት ውጪ የቀብድ ውል የለም ካለ በኋላ የሽያጭ ውል አለ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት ነዉ፣ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል የለም፣የስር ፍ/ቤት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት ተመዝግቦ ማረጋገጫ ያገኘ መሆን አለመሆኑን ሳያረጋግጥ የውሉ ሰነድ ከረቂቅ ያለፈ የህግ ጥበቃ የሚያገኝ ሰነድ ስለመሆኑ ሳይመረምር ውል አለ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲሻር በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካቾች የቤት ሽያጭ ውሉን በግልፅ ክደው ተከራክረው እያለ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ፣ተጠሪ ቀሪውን ገንዘብ ከፍሎ ቤቱን ይረከብ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ በአዋጅ ቁ/1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 15/04/2014ዓ.ም ባቀረበው መልስ በቀብድ ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የአመልካቾች አይደለም በማለት ክደው የተከራከሩትን የስር ፍ/ቤት በፎረንሲክ ምርመራ ፊርማው የአመልካቾች መሆኑ ከማረጋገጡ በተጨማሪም የቤት ሽያጭ ውል መኖሩና በእማኞች ፊት ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑ አሳማኝ እና በቂ በሆነ መልኩ በሰውና በሰነድ ተረጋግጦ ይህንን ሊያስተባብል የሚችል ማስረጃ አመልካቾች ስላላቀረቡ የተወሰነ እንጂ አንዳችም መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ

ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ አመልካቾች የተቀበሉትን ቀብድ አጠፌታ እንዲመልሱ ወይም በዉሉ መሰረት የሸጡትን ቤት እንዲያስረክቡ የሚል ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸዉ ቤት ሽያጭ ዉል የለም፣ቀብድ አልተቀበልንም በማለት መከራከራቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሽያጭ ዉል መደረጉን ያስረዳል የተባለዉ ሰነድ ላይ ያለዉን ፊርማ በባለሙያ አስመርምሮ እና ዉሉ ሲደረግ እማኝ ነበሩ የተባሉትን ሰዎች ምስክርነት ቃል ሰምቶ የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩ ተረጋግጧል በማለት አመልካቾች ቀሪ ገንዘብ ተቀብለዉ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በቅደም ተከተል በይግባኝ ሰሚ ችሎት እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ በመሆኑ በዉሳኔዉ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ ስልጣን ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የሰበር ስርዓት በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢ.ፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም መሰጠቱ (አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል) ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ አገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የሚያስችል ነዉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

በተለይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር

ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ግራቀኙን ያከራከረዉ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል በፍርድ ሃይል ሊፈጸም የሚችል የቤት ሽየጭ ዉል አለ ወይስ የለም የሚለዉ ነዉ፡፡አመልካቾች አጥብቀዉ የሚከራከሩት የቤት ሽያጭ ዉል የለም፤የቀረበዉ ሰነድም ረቂቅ ነዉ በማለት በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ታልፎ ዉል መኖሩ ተረጋግጧል፤ተገደዉ ሊፈጽሙ ይገባል ተብሎ በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔና ህጉን የሚቃረን ነዉ በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ የዉለታዉ ጉዳይ የሚቻል፣ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ካልሆነ እና ተዋዋይ ወገኖች ፈቅድ ወይም ችሎታ ጉድለት የሌለበት እንዲሁም በህግ የተደነገገዉን የዉል አደራረግ ስርዓት ተከትሎ ተዋዋይ ወገኖች ወደዉና ፈቅደዉ የሚያደርጉት ዉል ህግ ሆኖ የሚያስገድዳቸዉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር1678 እና 1731/1 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ እንደዉሉ ያልተፈጸመለት ወገን አንድም ዉሉ እንዲፈጸምለት ወይም ዉሉ እንዲሰረዝና ኪሳራ እንዲከፈለዉ መጠየቅ ይችላል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1771 ይመለከታል፡፡ ዉሉ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ የሚደረገዉ አንድም በህግ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለማሟላቱና የዉሉ አደራረግ ጉድለት ያለበት ሲሆን ወይም ዉሉ እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሰናክል ሲፈጠር አሊያም አንደኛዉ ተዋዋይ ወገን ግዴታዉን ለመወጣት የማይችል መሆኑ በማያጠራጥር ሁኔታ ሲረጋገጥ ወይም የዉሉ አይነተኛ ጉዳይ የተነካ ከሆነ ወይም በሌላ ምክንያት በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰበት ከሆነ ነዉ፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808፣1784 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች ይመለከታል)፡፡

የተያዘዉ ጉዳይ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል አፈጻጸም የሚመለከት ነዉ፡፡የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ወይም ሌሎች መብቶችን ለማስተላለፍ ወይም ለማቋቋም የሚደረግ ዉል በጽሁፍ እና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መደረግ እንዳለበት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723/1/ ድንጋጌ ይዘት ያሥገነዝባል፡፡እንደውለታው ዓይነት ወይም በህግ የተደነገገዉ የጽሑፍ ውል አደራረግን ሥርዓት አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 (ሐ)፣ 1719(2) እንደተመለከተው በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል

አስፈላጊ የሆነውን የውል አደራረግ ሥርዓት አሟልቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡በዚህ አግባብ ያልተደረገ የሽያጭ ዉል እንደረቂቅ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1720(1) እና 1723 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡የምዝገባው ሂደት ባልተሟላበት ሁኔታ ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ሕጋዊ ነዉ ሊባል እንደማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.21448 በሰጠው ግልጽ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በሌሎችም መሰል ክርክሮች ላይ ተመሳሳይ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ሰበር መ/ቁ/34803 ቅጽ8፣መ/ቁ/ 78398 ቅጽ14 እና ሌሎች መዝገቦች መመልከት ይቻላል፡፡የሰበር ችሎት ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 ያላቸውን ልዩነት በግልጽ አስፍሯል፡፡(መ/ቁ21448 ይመለከታል)፡ይኸውም የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲረጋገጥ (authentication) ሂደት የማድረጉ አስፈላጊነት በተዋዋይ ወገኖቹ መካከል የፀና ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ (registration) ዓላማ ደግሞ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረዉ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡በሌላ በኩል ሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ/36887 በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንዳመላከተዉ በሰበር መ/ቁ/ 21448 ላይ የተሰጠዉ ትርጉም በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን አምነው በውልና ማስረጃ አካል ባለመመዝገቡ ብቻ ውል የለም በሚል የሚቃወሙ ተከራካሪዎችን የሚያጠቃልል አይደለም ምክንያቱም በፍ/ብ/ህግ ቁ/1723/1/ መሰረት የሚከናወነው የምዝገባ ዋና አላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የቤት ሽያጭ ውል ለመኖሩ በማስረጃነት እንዲያገለግል በመሆኑ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ክርክር አመልካቾች በስር ፍርድ በሰጡት መልስ የቤት ሽያጭ ዉል የለም፤የቀረበዉ ሰነድም ረቂቅ ነዉ በማለት በግልጽ ተከራክረዋል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የቤት ሽያጭ ዉል አለመፈጸማቸዉን ክደዉ መከራከራቸዉን ያሣያል፡፡አመልካቾች የቤት ሽያጭ ዉል አልፈጸምንም ብለዉ ክደዉ ስለተከራከሩ ዉል እንዲፈጸምለት የጠየቀዉ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩን ማስረዳት የሚችለዉ በህጉ ቅቡልነት ያለውን ሰነድ በማቅረብ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723(1) እና ከላይ የተጠቀሱት የሰበር ችሎቱ የሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ ያስገነዝባል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 36887 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ሳይሆን በመ/ቁ/ 21448 እና ሌሎች መሰል ዉሳኔዎች ናቸዉ፡፡በመሆኑም አመልካቾች የቤት ሽያጭ ዉሉን ክደዉ በመከራከራቸዉ ተጠሪ በበኩሉ ዉሉ በጽሁፍ መደረጉን ብቻ ሳይሆን ዉል ለማዋዋል ስልጣን ባለዉ አካል ፊት የተረጋገጠ ዉል በማቅረብ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ተጠሪ ያቀረበዉ ሰነድ በዚህ አግባብ የተረጋገጠ አለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡በዚህ አግባብ ስርዓቱን ተከትሎ የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ባልቀረበበት ሁኔታ ረቂቅ ነዉ የተባለዉ ሰነድ ላይ ያለዉን ፊርማ እና የምስክሮች ቃል መሰረት አድርጎ በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩ ተረጋግጧል በሚል የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ መታረም የሚገባዉ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በሌላ በኩል ዉሉ ረቂቅ ነዉ አመልካቾች ተገደዉ የሚፈጽሙት የቤት ሽያጭ ዉል የለም ከተባለ ግራ ቀኙ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ተገቢ ነዉ፡፡ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ አማራጭ የዳኝነት ጥያቄ ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡ይሁንና ተጠሪ በአማራጭ የጠየቀዉ ዳኝነት አመልካቾች የተቀበሉትን ገንዘብ አጠፌታ እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ክርክራቸዉንና ማስረጃ መርምሮ አመልካቾች የተቀበሉት አንድ ሚሊዮን ብር መሆኑንና ገንዘቡም ቀብድ ሳይሆን የሽያጭ ዋጋ ከፊል ክፍያ መሆኑን አረጋግጧል፡፡አመልካቾች የተቀበሉት ቀብድ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የተቀበሉትን ገንዘብ ያህል መመለስ እንጂ አጠፌታ እንዲከፍሉ አይገደዱም፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1885(2) እና 1815(1) ድንጋጌ ይዘት ይህንኑ ያመላክታል፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾች የቤት ሽያጭ ዉል ክደዉ ተከራክረዉ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ሽያጭ ዉል መደረጉ ተረጋግጧል በሚል አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጡት ዉሳኔ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል አደራረግ ስርዓት በሚመለከት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723/1/ የተደነገገዉን እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 21448 የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4-ሸ/ እና 10(1ሐ) ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ ዉሳኔዉ ላይ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/የደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በማጽናት በመ/ቁ/17102 ላይ በቀን 10/02/2014ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል ረቂቅ ዉል እንጂ አመልካቾች ቤት እንዲያስረክቡ የሚገደዱበት በህግ አግባብ የተቋቋመ የቤት ሽያጭ ዉል የለም ብለናል፡፡

3ኛ/አመልካቾች በረቂቅ ዉሉ መሰረት የተቀበሉትን ብር አንድ ሚሊዮን ክሱ በስር ፍርድ ቤት ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡

4ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገዉን ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

5ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በ22/03/2014ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ እግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

# ንብረት

**የሰ/መ/ቁ.** 184596

ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** አቶ ጫላ ያኢ ፉሪ - ቀርበዋል

**ተጠሪ-** የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታዉን ለለቀቀ ባለይዞታ ሊከፈል የሚገባዉን ካሳ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በጀመረበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅ እና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበት ክስ በውርስ ከተላለፈልኝ መሬት ውስጥ መጠኑ 98,463 ካ.ሜ የሚሆነውን የእርሻ መሬት ተጠሪው በ1997 ዓ.ም የወሰደ ሲሆን 35,000 ካ.ሜ የእርሻ፣ 64,460 ካ.ሜ ደግሞ የግጦሽ በሚል ከፋፍሎ ካሳ ብር 5,273,572.20 ቢከፈለኝም ካሳው በአግባቡ አልተሰላም፡፡ የማፈናቀያ ካሳ፣ ለተደረገው ቋሚ ማሻሻያ እና የጎርፍ መቀልበሻ እና መከላከያ፣ ቁጥቋጦ ያስነቀልኩበት እና ያስመነጠርኩበት የጉልበት ዋጋ እና በመሬቱ ላይ ለነበረው ባህርዛፍ ካሳ ያልተከፈለኝ በመሆኑ ቀሪ ብር 9,216,506.29 እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

ተጠሪ የተለያዩ የመጀመሪያ መቃወሚያዎችን በማስቀደም ለክሱ በሰጠው መልስ በኤጀንሲው በተሰራ ግምት እና በወቅቱ በነበረው የካሳ ስሌት መሠረት ለአመልካች ካሳ የተከፈላቸው ሲሆን በዚህ ላይ ቅሬታ ካላቸዉ በ30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ሲገባቸዉ አላቀረቡም፡፡ ለመንገድ እና ጋራጋንቲ ስራ ተወስዷል በሚል የተጠየቀዉም ካሳ የተከፈለበት ሲሆን የባህርዛፍ ግምቱን በሚመለከት ሊከፈላቸው አይገባም እንጂ ሊከፈላቸው ይገባል እንኳን ቢባል የመፈናቀያ ካሳ ነጠላው በ10 ተባዝቶ ሳይሆን መሬቱን እንዲለቁ ከመደረጉ በፊት በነበሩት አምስት ዓመታት ውስጥ ያገኙ የነበረው ዓመታዊ ገቢ በ10 ተባዝቶ ነው፤ በአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተወስዶ ለደን ተከላ የዋለ 27,226.09 ካ.ሜ መሬት ካሳን በሚመለከት የቀረበውን ጥያቄ ተጠሪን የማይመለከተው ሲሆን ቦታውም ለልማት ተነሺ በሚል ስም በተጠሪ ያልተጠና እና ተነሺነቱ እውቅና ያልተሰጠው በመሆኑ ጥያቄው የተጠሪን ጽ/ቤት አይመለከትም

በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ አመልካች የተሰራላቸውን ካሳ ተቀብለው ቦታውን ለልማት እንዲያስረክቡ ቢነገራቸውም ፍቃደኛ ስላልሆኑ ካሳው በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ መደረጉን፤ አመልካች በተደጋጋሚ ቅሬታቸውን ለመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ ጽ/ቤቱ እና ለክንቲባ ጽ/ቤት ቢያቀርቡም በወቅቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው የካሳ ጉዳዮች እና ምትክ ቦታ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንዳላቀረቡ፤ የከንቲባው ጽ/ቤት ጉዳዩ በድጋሚ ታይቶ ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ ሰጥቶ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ የተደረገው ብር 452,784.16 የሆነው የካሳ መጠን ተሻሽሎ ብር 5,273,572.00 እንዲከፈላቸው ተወስኖ በቀን 12/05/2009 ዓ.ም ክፍያውን መቀበላቸውን፤ የድንጋይ ካባ እና በአካባቢ ጥበቃ ተወስዶብኛል የሚሉትን መሬት በሚመለከት በአቤቱታው ውስጥ የተካተተ እና ከክፍያው በፊት የተቋጨ እንደሆነ አመልካች እንዳልካዱ፤ ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ለመጀመሪያ ጊዜ አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 21/05/2009 ዓ.ም የተሰጣቸውን መልስ መሠረት በማድረግ እንደሆነ፤ እንዲሁም ጉዳዩ በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንደተቋጨ በመግለጽ የከንቲባው ጽ/ቤት በፍትህ እና በርትዕ መፍትሔ ያበጀለትን ጉዳይ እንደገና መርምሮ መወሰን አግባብነት የለውም፤ አመልካች አሁንም ተጎድቻለው የሚሉ ከሆነ በተጀመረው አኳኋን ቅሬታቸውን ለከንቲባው ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ ሲል አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኝ ከተከራከሩበት በኋላ ጉባኤው አመልካች ካሳው በህጉ አግባብ ተሰልቶ አልቀረበም፣ የተከፈለኝ ካሳም በቂ አይደለም በሚል ያቀረቡትን ቅሬታ እና የተጠሪን መልስ በማስረጃ አጣርቶ ሳይመረምር ለአመልካች የተከፈለው ካሳ የሚጠቅመው እንጂ የሚጎዳው አይደለም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት በመሆኑ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን መልሶ ልኮለታል፡፡ በዚሁም መሠረት ጉባኤው የተመለሰለትን ጉዳይ ከመረመረ በኋላ በመመሪያ ቁጥር 19/2006 መሠረት በወቅቱ ከእርሻ ማሳው ላይ የተሰበሰበው ዓመታዊ ምርት በ10 ተባዝቶ እንዲከፈላቸው፤ የድንጋይ ካባ መሬት ካሳ ክፍያን በሚመለከት የመንገዶች ባለስልጣን በተደጋጋሚ ጊዜ በፃፈው ደብዳቤ መሠረት ካሳ የተከፈላቸው በመሆኑ አሁን በድጋሚ ሊከፍላቸው አይገባም፤ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ወሰደ የተባለውን መሬት በሚመለከት ጽ/ቤቱ ይዞታውን ከመንግስት የወሰደ ስለመሆኑ በደብዳቤ ስለገለጸ ተጠሪ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች አሁንም በዚህ ባለመስማማት ለከተማ አስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት የያዘውንና የካባ ድንጋይ መሬትን እንዲሁም ወጪና ኪሳራን በሚመለከት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ለጋራጋንቲ ስራ ለካባ ድንጋይ የተወሰደዉን ተጠሪ የ10,097.54 ካ.ሜ. ካሳ በመመሪያ ቁጥር 19/2006 እና በ2009 ዓ.ም በወጣው የካሳ ክፍያ ስሌት መሠረት ካሳው መከፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች እንዲከፍል፣ በአካባቢ ጥበቃ የተያዘዉን የአመልካች ይዞታ አስመልክቶ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤዉ መርምሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት፤ ጉባኤው አመልካችን

ባለመብት አድርጎ በሰጠው ውሳኔ ላይ ወለድ እና ወጪና ኪሳራን በሚመለከት አመልካች ዝርዝር እንዲያቀርቡ በማድረግ በማስረጃ ካጣራ በኋላ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ መልሶ ልኮለታል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታውን ለከተማ አስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የካባ ድንጋይ መሬቱን በሚመለከት ጉባኤው በማስረጃ አረጋግጦ የሰጠውን ውሳኔ ያለበቂ ምክንያት መሻሩ፤ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት የያዘውን መሬት በሚመለከት የመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ ቦታው ለልማት ተነሺነት ያጠናውና እውቅና ያልሰጠው መሆኑ፣ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በራሱ አጥሮ የሚያስጠብቀውና ከመንግስት የወሰደው ይዞታ መሆኑ በተረጋገጠበት ለአመልካች ካሳ ሊከፈለው ይገባል፤ ስሌቱን በሚመለከት መመሪያውን ተመልከቶ ይወስን በማለት ጉዳዩን ለጉባኤው መመለሱ ተገቢነት የለውም በማለት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የጉባኤውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 11/02/2012 ዓ.ም በተፃፈ 07 ገጽ የሰበር አቤቱታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት እና በይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ለመንገድ ስራ ገረጋንቲ ማውጫ የተወሰደው መሬቴ ጠቅላላ ስፋቱ 46,448.50 ካ.ሜ ሲሆን ተጠሪ በሪፖርቱ ላይ የተከፈለኝ ለ39,902.29 ካ.ሜ መሆኑን ቢገልጽም የ13,471.01 ካ.ሜ መሬት ካሳ አልተከፈለኝም፤ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ስለመክፈሉም በማስረጃ ባላረጋገጠበት ለጠቅላላው መሬት  እንደከፈለ ተቆጥሮ ጥያቄዬ ውድቅ መደረጉ፤ ይዞታው ላይ የንብረት ካሳ ተከፍሎታል እንኳን ቢባል ጉባኤው የመፈናቀያ ካሳ እንዲከፈለኝ ሊወስንልኝ ሲገባ ያለፈውና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ እንዲከፈለኝ የወሰነልኝን ሰበር ሰሚ ችሎቱ መሻሩ፤ በተጠሪ ምክንያት ለክርክሩ ለዳኝት የተከፈለውን ጨምሮ ከፍተኛ ወጪ አውጥቼ እያለ ወጪና ኪሳራ የየራሳችሁን ቻሉ፤ እንዲሁም በተጠሪ ችግር ምክንያት ተገቢው ካሳ ሳይከፈለኝ በመቆየቱ ወለድ እንዲከፈለኝ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተወሰነልኝን ውሳኔ ሰበር ሰሚ ችሎቱ መሻሩ መሠረታዊ ስህተት በመሆኑ ካሳው በመመሪያ ቁጥር 19/2006 አንቀጽ 10(16) እና በ2011 ዓ.ም ሲሰራበት በነበረው የካሳ ስሌት ቀመር መሠረት ተሰልቶ መከፈል ከነበረበት ጥር 12 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለአመልካች ሊከፈላቸው የሚገባው ካሳ ስሌቱ መሰራት ያለበት በ2006 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሠረት ነው? ወይስ በ2009 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሠረት ነው? የሚለው መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ ተጠሪም መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ በቀን 25/01/2013 ዓ.ም ጽፎ በሰጠው መልስ አመልካች ካሳ ተከፍሏቸው ቦታውን ለልማት እንዲለቁ የተወሰነው በ1997 ዓ.ም ሲሆን በወቅቱም የተሰራላቸውን የካሳ ገንዘብ ለመውሰድ ፍቃደኛ አልነበሩም፤ በዚህም የተነሳ ለተለያዩ አስተዳደር አካላት ቅሬታ አቅርበው የካሳው መጠን ተሻሽሎ ብር 5,273,572.02 ተከፍሏቸው በ2009 ዓ.ም ተቀብለዋል፤ ካሳው የተሰራውም በዚሁ በ2009

ዓ.ም በነበረው ዋጋ በመመሪያ ቁጥር 19/2006 ዓ.ም መሠረት ነው፤ አመልካች በ1997 ዓ.ም እንዲለቁ በተደረገው መሬት ላይ በ2009 ዓ.ም በነበረ ዋጋ ካሳው የተሰራላቸው አንሶ በ2011 ዓ.ም በነበረ ዋጋ ይሰራልኝ ማለታቸው ተገቢ አይደለም፤ በመሬቱም ላይ ለእርሻ ማሳ ቋሚ ማሻሻያ እና በመሬቱ ላይ ለነበሩ ባህርዛፎች ካሳ አልተከፈለኝም የሚል ክርክር ቢያቀርቡም በማስረጃ አላረጋገጡም፤ በ1999 ዓ.ም በተደረገው የመጨረሻ የቦታው ልኬትም የተስማሙ ሲሆን በጊዜው በመሬቱ ላይ ምንም አይነት ባህርዛፍ በስፍራው ላይ አልነበረም፤ ተጠሪም እነዚህ ንብረቶች የወሰደ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ለአመልካች ካሳ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በራሱ ስህተት ነበረ፤ ለመንገድ ስራ ጋራጋንቲ ማምረቻ ተወሰደብኝ የሚሉትን 46,448.50 ካ.ሜ በሚመለከት በአራት የተለያዩ ጊዜያት በጠቅላላው ብር 627,013.79 የተከፈላቸው ሲሆን ስለመከፈሉም በማስረጃ አረጋግጠን ተገቢው ውሳኔ አርፎበታል፤ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ካሳ ሳይከፍለኝ 27,226.09 ካ.ሜ ቦታ ወስዶብኛል ቢሉም ቦታው ለልማት የሚፈለግ ስለመሆኑ ለተጠሪ ቀርቦ ያልተጠና በመሆኑና መሬቱ በአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ስር እያለ ተጠሪ ካሳ የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ከጠየቃቸዉ የተለያዩ ክፍያዎች ዉስጥ ለልማት የተለቀቀዉ የእርሻ እና የግጦሽ ይዞታ 98,800 ካ/ሜትር መሆኑ ተረጋግጦ በወቅቱ ከእርሻ ማሳ ላይ የተሰበሰበዉ የዓመት ምርት በ10 ተባዝቶ ለአመልካች እንዲከፈል የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ወስኗል፡፡ በዚህ ላይ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ የክርክር ነጥብ ለጋራጋንቲ የካባ ድንጋይ፣ ለአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ወለድን አስመልክቶ የቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ መደረጉ ነዉ፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህን አስመልክቶ በየደረጃዉ የተሰጡትን ዉሳኔዎች አግባብነት እንደሚከተለዉ ተመልክቶታል፡፡

ለጋራጋንቲ ስራ ለካባ ድንጋይ ተወሰደ የተባለዉን ይዞታ አስመልክቶ ይህ መሬት ከአመልካች የተወሰደ ስለመሆኑ ተጠሪ ክዶ አይከራከርም፡፡ በዚህ ምክንያት ከአመልካች የተወሰደዉ የይዞታ መጠንም 46448 ካ/ሜትር ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ተጠሪም ይህን ሳይክድ የሚከራከረዉ ካሳ ተከፍሎታል በማለት ነዉ፡፡ አመልካች የሚከራከረዉ የተከፈለኝ የ 36,350 ካ/ሜትር ብቻ ነዉ በማለት ይከራከራል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤዉ በዚህ ረገድ የቀረበዉን የአመልካች ክርክር ዉድቅ ያደረገዉ አመልካች ከመንገዶች ባለስልጣን በተፃፈላቸዉ የካሳ ክፍያ ደብዳቤ መሠረት ካሳ ስለመዉሰዳቸዉ ከማህደራቸዉ መረጋገጡን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪ በዚህ ለጋራጋንቲ እና ለካባ ድንጋይ ሲባል ለተወሰደዉ መሬት ካሳ ከፍያለሁ በማለት የሚከራከር ቢሆንም በዚህ ምክንያት ለተረከበዉ መሬት ስፋት ልክ በመመሪያዉ እና በካሳ አከፋፈል ስሌት መሠረት ካሳ ስለመክፈሉ ተጠሪ አላስረዳም በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ

የቀሪዉን የ10097 ካ.ሜትር መሬት ካሳ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የወሰነ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን የይግባኝ ሰሚዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሲለዉጥ የጠቀሰዉ ምክንያት አመልካች ካሳ የወሰደ ስለመሆኑ በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ተረጋግጧል በማለት ነዉ፡፡ በመሠረቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ በተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 42(2) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከጭብጥ አያያዝ እንዲሁም ከመሠረታዊ የማስረጃ አቀራረብ እና የምዘና መርህ ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ስህተት ካልሆነ በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት ከፍሬ ነገር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተለይም ማስረጃን መዝነዉ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ባላቸዉ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር በድጋሚ መመርመርን እና መመዘንን እንደማያካትት የሚታወቅ ሲሆን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በበርካታ መዛግብት ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ነዉ፡፡ በመሆኑም ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን የተሰጠዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት በካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠዉን ዉሳኔ ይዘት መርምሮ ተጠሪ ከአመልካች በተወሰደዉ መሬት ልክ በካሳ አወሳሰን እና አሰላል መመሪያ መሠረት ካሳ ስለመክፈሉ አልተረጋገጠም በሚል የደረሰበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ በድጋሚ በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ ስልጣኑን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአካባቢ ጥበቃ ተወሰደ የተባለዉን ይዞታ አስመልክቶ በአመልካች ለተጠየቀዉ ዳኝነት ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረዉ መሬቱ ለልማት ተነሺ በሚል ስም በመመሪያዉ መሠረት ያልተጠና እና ዕዉቅና ያልተሰጠዉ ከመሆኑም በላይ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት አጥሮ የሚያስጠብቀዉ ይዞታ ከመሆኑ ዉጪ ለልማት ያልተፈለገ በመሆኑ ተጠሪ ሃላፊነት የለበትም በማለት ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ በአመልካች የቀረበዉን ዳኝነት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤዉ ዉድቅ ያደረገዉ በልማት ምክንያት ተነሺ መሆን ያለመሆኑን አስመልክቶ የቀረበ ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ይዞታዉን የወሰደዉ ከመንግስት ስለመሆኑ ተረጋግጧል በማለት ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይህን በጭብጥነት ይዞ የመረመረ ሲሆን፤ በዚህም መሠረት የንፋስ ስልክ ላ/ክ/ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት፣ የክ/ከተማዉ መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት፣ የክ/ከተማዉ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት፣ የከተማ አስተዳደሩ መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ በተለያዩ ጊዜያት የተፃፃፉአቸዉን ደብዳቤዎች በዋቢነት በመጥቀስ እነዚህኑ ከጉባኤዉ ዉሳኔ እና ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በማገናዘብ መጠኑ 27,226.09 ካ/ሜትር የሆነዉ የአመልካች ይዞታ በአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት የተወሰደበት መሆኑን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ አመልካች መሬቱ የተወሰደባቸዉ ካሳ ያልተከፈላቸዉ ከሆነ ተጣርቶ ካሳ እንዲከፈላቸዉ ለን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት እና ለክ/ከተማዉ የአካባቢ ጽ/ቤት በጽሑፍ ያሳወቀዉ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ ካሳዉን የመክፈል ኃላፊነት አለበት በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በአንፃሩ የከተማዉ አስተዳደር

ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን የይግባኝ ሰሚዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሻረዉ ይዞታዉ በመመሪያ መሠረት በልማት ተነሽነት ተይዞ ዕዉቅና ያልተሰጠዉ ከመሆኑም በላይ የአካባቢ ጥበቃ ከመንግስት ተሰጥቶት አጥሮ የያዘ መሆኑ መረጋገጡን በመጥቀስ ነዉ፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የአመልካች እንደነበረ፣ ካሳ ሳይከፈልበት በክ/ከተማዉ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ታጥሮ እንደተያዘ እንዲሁም ተጣርቶ ካሳ ሊከፈለዉ እንደሚገባም በሚመለከተዉ አካል እንደታመነበት ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን በተሰጠዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ መሆኑን ሲሆን ጉባኤዉም ሆነ የከተማ አስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ ላለመቀበል የጠቀሱት መሠረታዊ ምክንያት ቦታዉ በልማት ተነሺነት ተጠንቶ ዕዉቅና ያልተሰጠዉ መሆኑን ነዉ፡፡

በመሠረቱ እንደሌሎች መሠረታዊ መብቶች ሁሉ ለንብረት መብት ከፍተኛ ግምት የሰጠዉ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 40 ላይ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ እንደሚከበርለት፣ በህግ መሠረት ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም፣ የሌሎች ሰዎችን መብት ሳይቃረን ንብረትን የማስተላለፍ መብቶችን ያጎናጸፈዉ ሲሆን የንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ብቻ ለንብረቱ ባለቤት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን መዉሰድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነዉ የሚለዉ ይህ ህገ መንግስት ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባዉ ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገዉ ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለዉ ይደነግጋል (አንቀጽ 40/3 እና 7 ይመለከቷል)፡፡ የሥነ ህግ ሳይንስ (jurisprudence) መብትና ግዴታዎች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች (two sides of one coin) መሆናቸዉን ይነግረናል፤ ይህም ማለት ግዴታ በሌለበት መብት ገቢራዊ ሊሆን ስለማይችል መብት ባለበት ሁሉ ግዴታ ሊኖር ግድ ይላል፡፡ በመሆኑም መንግስት ከላይ ለተመለከቱት የንብረት መብቶች በህገ መንግስቱ ዕዉቅና ሲሰጥ መብቶችን ለማክበር እና ለማስከበር ጭምር ግዴታ በመግባት ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከንብረት መብት ጋር በተያያዘ መንግስት ሁለት መሠረታዊ ግዴታዎች ያሉት ሲሆን አንድም ዜጎች በንብረት መብቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በህግ እና በተቋማት ጥበቃ ማድረግ ሲሆን ሁለትም የንብረት ባለቤትነት መብትን ሊጋፉ የሚችሉትን ተግባራት ከመፈጸም የመታቀብ ግዴታ ነዉ፡፡ ስለሆነም መንግስት የሰዎችን የንብረት ባለቤትነት መብት ሊገድብ ከሚችል ወይም በመብታቸዉ እንዳይጠቀሙ ሊያደርግ ከሚችል አግባብ ካልሆነ ተግባር የመታቀብ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ ንብረቱን ወይም ንብረቱ የሚገኝበትን ቦታ ለጠቅላላዉ ህዝብ ጥቅም (general public interest) የሚፈልግ ከሆነም ንብረቱን ወይም ንብረቱ የሚገኝበትን ቦታ በእጁ ከማስገባቱ በፊት አስቀድሞ ለባለንብረቱ ካሳ የመክፈል ግዴታ አለበት የሚለዉ መርህ ከንብረት መብት መርሆዎች አንዱ በመሆን በዓለማችን ዕዉቅና ያገኘ ስለመሆኑም የሚታወቅ ነዉ፡፡ መንግስት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመዉሰድ እንደሚችል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት

አንቀጽ 40(8) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ይህንኑ መነሻ ያደረገ ሲሆን፣ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የግል ንብረትን መዉሰድ የሚቻልበትን አግባብ የሚደነግግ አዋጅ ቁጥር 455/97 ወጥቶ በስራ ላይ ይገኛል፡፡

ይህ አዋጅ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና የንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/97 በመባል የሚታወቅ ነዉ፡፡ ይህ አዋጅ የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል ለህዝብ ጥቅም ሲባል በመንግስት አካላት፣ በግል ባለሀብቶች፣ በህብረት ስራ ማህበራት ወይም በሌሎች አካላት የተሻለ ልማት ሊካሄድበት ይገባል ብሎ ያመነበትን የገጠር ወይም የከተማ መሬት በቅድሚያ ካሳ እንዲከፈል በማድረግ የማስለቀቅ ስልጣን እንዳለዉ የሚያስገነዝብ ሲሆን (አንቀጽ 3/1/ ይመለከቷል) የማስለቀቂያ ሥርዓቱ እንዲሁም የካሳዉ መጠን እና ዓይነት ምን እንደሆነም በዝርዝር ይደነግጋል፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ መንግስት የአንድ ሰዉ ንብረት ያረፈበትን ቦታ ለልማት ሲፈልግ ግለሰቡን ከመሬቱ ከማስለቀቁ በፊት አስቀድሞ ካሳ (እንደ ሁኔታዉ ምትክ ቦታ ወይም የማፈናቀያ ካሳ ሊሆን ይችላል / የአዋጁ አንቀጽ 7 እና 8 ይመለከቷል) መክፈል ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም ለልማት ዓላማ መሬቱ ወይም በመሬቱ ላይ የሚገኘዉ ንብረቱ በመንግስት የተወሰደበት ሰዉ መንግስት እንደአግባብነቱ ምትክ ቦታ እንዲሰጠዉ ወይም ከመሬቱ ላይ ለተነሳዉ ንብረት የማፈናቀያ ካሳ እንዲከፍለዉ የመጠየቅ መብት ያለዉ ሲሆን መንግስትም ይህን የማድረግ ግዴታ ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ ይህ ካልሆነ በህገ መንግስቱ ለመሬትም ሆነ በመሬት ላይ ለሚፈራ ሀብት የተደረገ ጥበቃ ዋጋ ያጣል፡፡ ስለሆነም መንግስት ቦታዉን ለልማት በመፈለጉ ምክንያት ንብረቱ የተወሰደበት ወይም ከቦታዉ እንዲነሳ የተደረገ ሰዉ የሚያቀርበዉ የካሳ ይገባኛል ጥያቄ ይህን ሁሉ ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ አመልካች ባህር ዛፍ ነበረበት የሚለዉ ይዞታዉ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት እጅ ታጥሮ የሚገኝ ሲሆን ጽ/ቤቱ አጥሮ ሊይዝ የቻለዉም ከመንግስት ስለተላለፈለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የጠየቀዉም ለዚሁ የማፈናቀያ ካሳ እንዲከፈለዉ ነዉ፡፡ ምንም እንኳ በህገ መንግስቱ መሠረት መሬት የህዝብና የመንግስት በመሆኑ መንግስት ለመሬቱ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ባይኖርበትም አመልካች በመሬቱ ላይ ባለማዉ ባህርዛፍ ላይ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40(7) መሠረት የባለቤትነት መብት ያለዉ በመሆኑ እና መሬቱንም በቋሚነት የለቀቀ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 8(1) መሠረት የማፈናቀያ ካሳ ሊከፈለዉ የሚገባዉ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ባህርዛፍ ነበረበት የሚለዉን ይዞታ እንዲለቅ ተደርጎ ባህርዛፉም የመንግስት አካል በሆነዉ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተይዞ የሚገኝ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ቦታዉ በተነሽነት አለመመዝገቡ እና ዕዉቅና ያልተሰጠዉ መሆኑ መንግስት ለልማት ዓላማ ከግለሰቦች መሬት ሲወስድ አስቀድሞ ካሳ እንዲከፍል የሚጠበቅበትን ግዴታ እንዳይወጣ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ እንዲሆን መፍቀድ ለዜጎች በህገ መንግስቱ ጥበቃ የተደረገለትን የንብረት ባለቤትነት መብት ጥያቄ ዉስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 36 መሠረት ለአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዉስጥ አንዱ የተለያዩ ዕፅዋት የሚተከሉበትን ቦታ እና የሚሰጡትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና፣ አካባቢያዊ ጠቀሜታ በማጥናት እንዲሆኑ ማድረግ፣ በከተማዉ መሪ ፕላን ለመናፈሻ፣ ለደን፣ ለወንዝ ዳርቻና ለሌላ አረንጓዴ ልማት በተከለሉ ቦታዎች ላይ የሚተከሉትን ዕፅዋት የማማከር ተግባር ሲሆን፤ ለከተማዉም ሆነ ለክ/ከተማዉ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ (ጽ/ቤት) ከተሰጡት ስልጣን እና ተግባራት ዉስጥ አንዱ ቦታን ማስለቀቅና አግባብ ባለዉ አካል በሚወሰነዉ መሠረት ምትክ ቦታ መስጠት፣ ካሳ እና ሌሎች ክፍያዎችን መፈጸም ስለመሆኑም ከአዋጁ አንቀጽ 21 (6 እና 9) እና አንቀጽ 38(23) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም የአካባቢ ጥበቃ ለሚፈልጋቸዉ ቦታዎች እንዳስፈላጊነቱ ምትክ ቦታ በመስጠት ወይም ካሳ በመክፈል ባለይዞታዉን አስለቅቆ የሚያስረክበዉ ተጠሪ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የክ/ከተማዉ በእጁ አድርጎ ለአረንጓዴ ልማት እየተጠቀመበት ለሚገኝ እና በአግባቡ ካሳ ያልተከፈለበት የአመልካች ይዞታ ካሳ የመክፈል ኃላፊነቱ የተጠሪ በመሆኑ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች በአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት እጅ ይገኛል ለተባለዉ ይዞታ ተጠሪ ኃላፊነት እንዳለበት ከድምዳሜ ላይ በመድረስ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤዉ በመመሪያዉ መሠረት አጣርቶ የካሳ ክፍያዉን አስልቶ እንዲወስን መመለሱ በአግባቡ ሆኖ እያለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ ያላግባብ በመሻር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ካሳዉ በመመሪያ ቁጥር 19/2006 መሠረት መሰላት እንዳለበት ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ አመልካች ለከተማዉ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በቀጥታ/በመስቀለኛ አቤቱታ ያላቀረበ ሲሆን ይህን ሳያደርግ ካሳዉ በመመሪያ ቁጥር 19/2009 መሠረት ሊሰላ ይገባል በማለት ለዚህ ችሎት የሚያቀርበዉ ቅሬታ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበዉን አቤቱታ ይህ ችሎት አልተቀበለዉም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 30477 በቀን 09/12/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29562 በቀን 09/07/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.201741

ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- ወ/ሮ ፅጌ ቀለመወርቅ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አረጋይ ከበደው

**ይህ መዝገብ ከመ/ቁ/ 205748 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍርድ</u>**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪ ይዞታን እና የቤት ኪራይ ገቢን አስመልክቶ በአመልካች ላይ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 33893 በሆነው ከሣሽ፣ በመ/ቁ/ 33695 በሆነው ተከሣሽ በመሆን ተከራክረው ሁለቱ መዛግብት ተጣምረው ተመርምረው በተሰጠው የአሁን አመልካች የሚያከራክረውን ይዞታ እንዲለቁ እና የቤት ኪራይ ገንዘብም እንዲከፍሉ በሚል የተሰጠው ውሣኔ በይግባኝም ሆነ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያልተለወጠ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ የተፈፀመውን መሠረታዊ የህግ ስህተት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ አመልካች አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ላየው የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ቀርቦ በመ/ቁ/ 33893 በሆነው መዝገብ እንደቀረበው በሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 03 ውስጥ በሚገኝ በስተሰሜን፣ በምዕራብ እና በምሥራቅ መንገድ እና በደቡብ የበርታ ሀሰን እና የወ/ሮ ድርቤ መኮንን ቤት የሚያዋስነውን የቦታ ስፋቱ 555 ካ.ሜ. የሆነ ላይ የሚገኝ በሟች ባለቤቴ በአቶ ቀለመወርቅ ብርሃኔ ስም በአስተዳደሩ ተመዝግቦ ያለ የመሬት ይዞታ እና ቤት ተሰርቶበት የሚገኘው የድሮ ይዞታ ስለሆነ በደርግ ስርዓት ከአቶ ሙባረክ ዲኖ፣ታምሩ አበበ እና አቶ በየነ ሽዋ ከሚባሉት ላይ ሟች ባለቤቴ አቶ ቀለመወርቅ ብርሃኔ ጎን እና ጎን ያለ መሬት የቦታው ስፋት 2000 ካ.ሜ በመግዛት የያዘው እንደገበሬ የመንግሥት ግብር እየተገበረበት በእርሻ እየተጠቀመበት የቆየ ሲሆን እኔ ከዚህ ባለቤቴ ጋር

በ1994 ዓ.ም. ተጋብተን እዚህ መሬት ላይ የተለያዩ ቤቶች በመሥራት ሌላውን ደግሞ በእርሻ እየተጠቀምንበት በመሆኑ አካባቢው በሰበታ ከተማ አስተዳደር ስር ሲታቀፍ ይህ መሬት በእጃችን ስለቀረ ካርታ እንዲሰጠን ጠይቀን እየጠበቅን ያለን መሆኑ የከተማው የውስጥ ለውስጥ መንገድ በሚሰራበት ጊዜ የመሬት ይዞታችን መንገድ ወጥቶበት ለሁለት ቦታ ያካፈለው ሲሆን፣ ሁለቱም ጊቢ በውስጥ የሚገኙ በባለቤቴ ስም ተመዝግቦ የመብራት ሀይል ቆጣሪ ገብቶልን በሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 03 የቤ/ቁ/ 2046 ተሰጥቶ 13 ክፍል ቤቶች በተለያዩ ጊዜ በላዩ ላይ ተሰርቶ ያለን በማከራየት እየተጠቀምንበት የነበረ ባለቤቴ በቀን 09/12/2008 በሞት ከዚህ ዓለም የተለየ ሲሆን እኔ የልጆች ሞግዚትነት እና ሚስትነቴን አሳውጄ ማስረጃ ተሰጥቶኛል፡፡

አመልካች በህግ የተሰጣት አንዳችም መብት ሳይኖራት የባልና ሚስት ንብረት የሆነውን ከሚች ጋር በጋራ አፍርቼ ያለኝን አመልካች ቤቱ የእኔ ነው ብላ በጉልበት የያዘችው የቤቱንም ኪራይ ከልክላኛለች ስለሆነም አመልካች የሟች ባለቤቴ አቶ ቀለመወርቅ ብርሃኔ ንብረት እና አብረን ያፈራነውን እና የልጆቼ የውርስ ንብረት የሆነውን እንድትለቅ ወጪና ኪሣራም እንድትከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ ተሻሽሎ ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ የሚያከራክረው ቤትና ይዞታ ከባለቤቴ ጋር ያፈራነውና የተጋባንበት ነው፡፡ እስካሁንም ድረስ በሟች ባለቤቴ ስም ግብር የምንገብርበት ሲሆን መብራት እና ውሃም በሟች ስም ገብቷል፡፡ ይዞታው ወደከተማ ሲካለል የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሲወጣ ሁለት ቦታ የተካፈለ 600 ካ.ሜ. በአንድ በኩል ከ600 ካ.ሜ. በላይ የሚሆን ደግሞ በዚህ በኩል ያለውን ቤቶች ሰርተን እያከራየን እየተጠቀምንበት ያሉ መሆኑን፣ ሟች ባለቤቴ እና የአሁን ተከሣሽ አባት በቀን 09/12/2008 ከሞተ በኋላ ወ/ሮ ጽጌ ቀለመወርቅ የእኔ ነው ብላ የመሬት ይዞታ እና እነዚህን ቤቶች የያዘችው ቢሆንም አንዳችም መብት እንኳን ሳይኖራት በሀሰት ምስክር በመመርኮዝ የእኔ ነው ብላ የተከራከረች ቢሆንም በደርግ ስርዓት ውስጥ ቀበሌው ከመሬት ክፍፍል አልፎ የመሬት ስጦታ ውል ሊያረጋግጥ የማይችል መሆኑን፣ እሷ ለምስክርነት ያቀረበችው ደረሰኝ የውሸት እና ከዚህ ጉዳይ ጋር የማይገናኝ መሆኑን እኔ 20 ክፍል ቤቶች እያከራየሁ በወር ብር 19200.00 ታገኛለች ያለችውም ውሸት መሆኑን፣ ቤቶቹ ፈራርሰው ከጥቅም ውጭ ስለሆኑ የተወሰኑት ክፍሎች ብቻ እየተከራዩ የሚገኙና ገቢ እና ትንንሽ ልጆች እና ከሟች ጋር አብረን ያፈራናቸው እየተጠቀሙባቸው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም/የስር ተከሣሽ/ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- ወ/ሮ አረጋይ ከበደው እነዚህ ቤቶች ንብረት በባለቤታቸው በአቶ ቀለመወርቅ ብርሃኔ ስም አለ ትበል እንጂ ከአቶ ታምሩ አበበ ላይ በስጦታ ያገኘችው መሆኑን እና የከራቡ ሁርቡ ቀበሌ የማህበራዊ ፍርድ ቤት በቀን 21/12/1982 ዓ.ም. የተሰጠ ውሣኔ በተከሣሽ ስም ግብር እንደምትገብርበት ቤትም እላዩ ላይ እንድትሰራበት እና ማንኛውንም ንብረት በላይ ላይ እንድታፈራበት የተወሰነላት መሆኑን የመንግሥት ግብር በስሟ እየገበረች ቤቶች እላዩ ላይ

ሰርታ እየተጠቀመችበት መቆየቷን እሷ ውጪ ሀገር ለስራ ከመሄዷ በፊት የመሬት ይዞታ እና እላዩ ላይ የተሰሩት ቤቶች አባቷ አቶ ቀለመወርቅ ብርሃኔ በውክልና ቁጥር 2116/1/98 ነሐሴ 3/1998 ዓ.ም. ሰጥታው እሱም በዚህ ውክልና በመመርኮዝ በራሷ ገንዘብ የተለያዩ ቤቶች በተጨማሪነት በመሬቱ ላይ ሰርቷል ይሁን እንጂ ይህ የመሬት ይዞታ እና እነዚህ ቤቶች በ1999 ዓ.ም. ውስጥ በሰበታ ከተማ ቀበሌ 03 ውስጥ ታቀፈ ሲባል የሰበታ ከተማ አስተዳደር የውስጥ ለውስጥ መንገድ በሚያወጣበት ጊዜ የመሬት ይዞታዬን ሁለት ቦታ እንዲከፈል ሆኗል፡፡

በዚህም ምክንያት ይህ ክርክር የተነሳበት መሬት ስፋቱ 555 ካ.ሜ. የሆነ በእኔ እጅ የቀረ ሲሆን በግምት ከ600 ካ.ሜ. በላይ የሚሆን መሬት ትልቅ ቤት እና 20 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የሆኑት አብረው የተቆረጡ ከሣሽ/የአሁን ተጠሪ/ በሚች አባታችን በማመካኘት ግማሹን በጉልበት የያዘችባት መሆኑን እና ይህ ቤት ንብረት እንደምትለው የአሁን ተጠሪዋ ሳይሆን የአሁን አመልካች መሆኑን እና በስሟ ያለ እና የቤት ቁጥር 3686 የሚል ተሰጥቶት የሚገኝ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲሆንላት ጠይቃለች፡፡

የአሁን አመልካች የተሻሻለ ክስ በ14/03/2011 ዓ.ም. በመ/ቁ/ 33893 ላይ ያቀረበች መሆኑን፣ ይዘቱም ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት የስጦታ ውል በቀን 12/12/1982 ዓ.ም. ያገኘሁት በላዩ ላይ ቤት ሰርቼ ያለው ተጠሪ የእኔን ንብረት ለ24 ወራት ከህግ ውጭ ለሰዎች እያከራየች እየተጠቀመችበት በመሆኑ የቤቶቹ ግምት ብር 250000.00 /ሁለት መቶ ሀሣሳ ሺ/ እንድትለቅልኝ እና የ20 ሰርቪስ ቤቶችን ኪራይ ደግሞ የአንድ ወር ብር 19200.00/ አስራ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ / እና 9 በመቶ ወለድ ብር 127944.00/ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ አራት ብር/ በአጠቃላይ ብር 588744.00/ አምስት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ ሰባት መቶ አርባ አራት / ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ እና የጠበቃ አበል እንዲሁም ወጪና ኪሣራ እንድትከፍል ይወሰንልኝ በማለት አቅርባለች፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ እና መዝገቡን አጣምሮ በሁለቱም መዛግብት ላይ የቀረበውን ክርክር በማጠቃለል ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ምስክሮች አዳምጧል፡፡ የቀረበውን ክርክር ለማጣራት ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ መስጠቱን እና ምላሽ መምጣቱን ተመልክተናል፡፡

የቀረቡት ምስክሮች የሰጡትን ቃል፣በግራ ቀኙ በቀረበው ክርክር የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎችና እና ፍ/ቤቱ ጠይቆ የቀረበለትን ማብራሪያ መመርመሩን እና በተጠሪ በኩል በመ/ቁ/ 33893 በሆነው መዝገብ ቀርቦ የነበረውን ክስ አስመልክቶ ከሣሽ/ተጠሪ የመክሰስ መብት የላትም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 33/2 መሠረት ውድቅ ያደረገ ሲሆን፣ አመልካችም አቅርባው የነበረውን ክስ መኖሪያ ቤቱ ሟቹ እና ተጠሪዋ በጋብቻ ወቅት አብረው ያፈሩት ነው በሚል ውድቅ ያደረገ እና በአብላጫ ድምጽ የወሰነ መሆኑን የውሣኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን ያቀረቡ እና በመ/ቁ/ 322203 በሆነው የተከፈተና የተመረመረ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና

ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የአሁን አመልካች ለክርክር መነሻ በሆነው የመኖሪያ ቤት ንብረት ባለቤት መሆኗ ስላልተረጋገጠ ሰበታ ከተማ ቀበሌ 03 ውስጥ አዋሳኙ በሰሜን፣በምዕራብ እና በምሥራቅ መንገድ፣ በደቡብ በርታ ሃሰን ቤት እና ወ/ሮ ድርቤ መኮንን መካከል ተዋስኖ የሚገኝ በግምት 555 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ሰፍሮ የሚገኘው መኖሪያ ቤት የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ እንድትለቅ እና አመልካች ወላጅ አባቷን ለመውረስ የምታቀርበውን መብት የሚያግድ አይደለም ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በመቃወም ይግባኝ ያለች ሲሆን ይግባኛቸው በመ/ቁ. 322114 ላይ ተመርምሮ ውድቅ መደረጉን፣ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ በመ/ቁ/ 333945 በሆነው አቅርበው ውድቅ ተደርጓል፡፡

ከዚህ የምንረዳው አመልካች በአንድ በኩል ተጠሪ በሌላ በኩል የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መዛግብቱን አጣምሮ ባየው ጉዳይ በየፊናቸው ይግባኝ ማለታቸውን እና በተለያየ መዝገብ መስተናገዳቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በየፊናቸው አቤቱታ ማቅረባቸውን እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉን ነው፡፡

አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ በመሆኑ ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን አመልካች መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- የሚያከራክረው ይዞታ የተጠሪ ባለቤት የገዛው ነው በሚል ተጠሪ ትከራከር እንጂ በስር ፍ/ቤት የሽያጭ ውል ያላቀረበች መሆኑን፣ በማስረጃነት የተያያዘው አቶ ታምሩ አበበ ለአመልካች ስጦታ የሰጡበት ማስረጃ መሆኑን፣ አባቴ በይዞታው ላይ መብት የለውም እንጂ መብት ያለው ቢሆን እና በግዢ አግኝቶት ህጋዊ ለማድረግ የተፈለገ ቢሆን ኑሮ ስጦታው ለአባቴ እንጂ ለእኔ ሊሰጥ አይገባም ነበር፣ የስጦታ ውሉንም ሚች መፈፀም ነበረበት፣ አባቴ በይዞታው ላይ መብት ያለው ቢሆን ኑሮ ለምን በአባቴ ስም የስጦታ ውሉ አልተፈፀመም፣ የስጦታ ውሉ ባልተሻረበት ንብረቱ ያንቺ አይደለም ተብሎ ሊወሰን የሚገባው ባልሆነበት፣ አባቴና እናቴ ጋብቻ የፈፀሙት በ1994 ዓ.ም. በመሆኑ ንብረቱ በጋብቻ ውሉ ላይ ሊቆጠር ይገባው ነበር፣ የወላጅ አባቴ ሀብት ከሆነ የራሱን ሀብት እንዴት ከእኔ ውክልና ወስዶ ሊያስተዳድር ይችላል የሚሉና ሌሎች ዝርዝር ነጥቦችን በማንሳት የሚያከራክረው ይዞታና ቤት የእኔ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሊሻር የሚገባው ነው በማለት አቤቱታ አቅርባለች፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በሰ/መ/ቁ/ 204748 በሆነው ክርክር የተነሳበት ይዞታ ለአመልካች በስጦታ ተላለፈ የተባለው በ1982 ዓ.ም. ሆኖ በተጠሪ እና በሚች መካከል ጋብቻ የተፈፀመው በ1994 ዓ.ም. መሆኑና ስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ በተመለከተበት ሁኔታ ስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ

በማድረግ የመወሰኑን አግባብ ለመመርመር በሚል ጭብጥ የተያዘ ሲሆን፣ በሰ/መ/ቁ/ 201741 በሆነው ደግሞ የአሁን አመልካች ይዞታውን በስጦታ አግኝታ ለአባቷ ውክልና ሰጥታ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤት ገንዘብ በመላክ የሠራችው እና ግብርም እየገበረችበት የነበረው ቤት ለአመልካች አይገባትም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ሁለቱም መዛግብት ለችሎቱ የቀረበ ሲሆን መጥሪያም ለተጠሪ ተልኮላቸው ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ በሰ/መ/ቁ/ 205748 በሆነው ላይ ያቀረቡት ጥቅምት 1 ቀን 2014 ዓ.ም. በተፃፈ ያቀረቡት መልስ በአጭሩ፡- አመልካች በስጦታ አገኘሁ ያለችውን በተመለከተ በራሷ በኩል ቀርበው የነበሩ የፍርድ ሸንጎ ፀሐፊ የነበሩት ግለሰብ በሰጡት ምስክርነት ስጦታ ተሰጠ በተባለ ጊዜ አመልካች ህፃን ልጅ የነበረችና የምትኖረውም በአዲስ አበባ ለገሃር አካባቢ ከእናቷ ጋር የነበረ መሆኑን ስጦታ ተደረገ በተባለበት ቦታም በጊዜው ያልነበረች እና ስጦታ አረጉ የተባሉት አቶ ታምሩ አበበንም የማታውቅ መሆኑን፣ ይልቁንም ስጦታ ተባለ እንጂ አቶ ቀለመወርቅ ከኪሣቸው ገንዘብ የከፈሉና ኩታ ገጠም የሆኑ ይዞታዎችን የገዙ መሆኑን፣ አመልካች ከውጭ አገር ገንዘብ እየላኩ ተሰራ ያለችው ሀሰት መሆኑን እና የትኛው ቤት ሲሰራ ገንዘብ እንደላከች በመግለጽ ያለመከራከሯን፣ ባለቤታቸው አስቀድሞ ገዝተውት ለእርሻ ሲጠቀሙበት የነበረውን ይዞታ በ1994 ዓ.ም. ተጠሪን ካገቡ በኋላ ቤቶች እየተሰሩበት ሲጠቀሙ የቆዩ የጋራ ንብረት እንጂ የግል ንብረት አለመሆኑን፣ በስር ፍ/ቤት መዝገቡ ተጣምሮ በአንድ ላይ ጭብጥ ተመስርቶበት የተከራከሩ መሆኑን በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግን ስለተጠሪ እና የአመልካች አባት ጋብቻን በተመለከተ ያልተነሳውን እና ክርክር ያልተካሄደበትን በመያዝ ተጠሪን መልስ ማሰጠት ተገቢ አለመሆኑን፣ የይዞታው አመጣጥም አቶ ቀለመወርቅ ኩታ ገጠም የሆኑ የእርሻ ይዞታዎችን ከተለያዩ ሰዎች በ1982 ዓ.ም. ገዝተው ቤት እየሰሩ እያረሱ መልሰው እየሰሩ ሲጠቀሙበት የቆዩ እና ወደ ከተማ ሲካለል በመንገድ ምክንያት ለሁለት የተከፈለ እና አቶ ቀለመወርቅ በ2008 ዓ.ም. ሲሞቱ አመልካች በጉልበት የያዘችው እንጂ በስጦታ ያገኘችው አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ በሰ/መ/ቁ/ 201741 በሆነው ላይ ግንቦት 9 ቀን 2013 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ በቀዳሚው መዝገብ ያቀረቡትን ክርክር የሚያጠናክር እንጂ የተለየ ሆኖ ባለመገኘቱ መመዝገብ አላስፈለገም፡፡ አመልካችም የቀደመውን የሰበር አቤቱታቸውን በማያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ በሁለቱም መዛግብት በማቅረብ እና ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚሁ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልስ ከስር ፍ/ቤት አጠቃላይ ክርክር እና ውሣኔ እንዲሁም በአጣሪው በሁለቱም የሰበር መዛግብት ላይ ከተያዘው ማስቀረቢያ ጭብጥ አንፃር ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በሁለቱም ለሰበር የቀረቡ መዛግብት የክርክር መነሻቸው በስር ወረዳ ፍ/ቤት ተጣምረው የታዩ በሂደት ሁለት ቦታ የተከፈለ ሆኖ ነገር ግን በአንድ ንብረት ላይ የተደረገ ክርክር

ሲሆን፣ በሰ/መ/ቁ/ 205738 በሆነው አመልካች የቤቶቹ ግምት ብር 250000.00/ሁለት መቶ ሀሣሳ ሺ/ እንድትለቅልኝ እና የ20 ሰርቪስ ቤቶችን ኪራይ ደግሞ የአንድ ወር ብር 19200.00/ አስራ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ / እና 9 በመቶ ወለድ ብር 127944.00/ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ አራት ብር/ በአጠቃላይ ብር 588744.00/ አምስት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ ሰባት መቶ አርባ አራት / ከወለድ ጋር ተጠሪ እንድትከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ክስ ያቀረበች መሆኑን፣ በሰ/መ/ቁ/ 201741 በሆነው መዝገብ ደግሞ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በሟች ባለቤቴ በአቶ ቀለመወርቅ ብርሃኔ ስም በአስተዳደሩ ተመዝግቦ ያለ የመሬት ይዞታ እና ቤት ተሰርቶበት የሚገኘው የድሮ ይዞታ ይዞታችን መንገድ ወጥቶበት ለሁለት ቦታ ያካፈለው ሲሆን፣ ሁለቱም ጊቢ በውስጥ የሚገኙ በባለቤቴ ስም ተመዝግቦ የመብራት ሀይል ቆጣሪ ገብቶልን በሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 03 የቤ/ቁ/ 2046 ተሰጥቶ 13 ክፍል ቤቶች በተለያዩ ጊዜ በላዩ ላይ ተሰርቶ የምንጠቀምበትን አመልካች በጉልበት ይዛ እየተጠቀመች ስለሆነ እንድትለቅ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርባለች፡፡

የስር ፍ/ቤትም ሁለቱንም መዛግብት አጣምሮ ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ የግራ ቀኙን ክስ ውድቅ ያደረገ በመሆኑ ግራ ቀኙ ይግባኝ የጠየቁ በመሆኑ የአመልካች ይግባኝ ውድቅ ተደርጐ እስከ ክልሉ ሰበር የፀና ሲሆን፣ ተጠሪ ያቀረበችው ይግባኝ ግን ተቀባይነት አግኝቶ አመልካች ይዞታውንና ቤቱን እንድትለቅ የወራሽነት ድርሻ አለኝ የምትል ከሆነ መጠየቅ እንደምትችል በማመላከት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ ተወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔ በሰበር ያልተለወጠና የፀና መሆኑን የክርክሩ አመጣጥ ያሳየናል፡፡

ከአጠቃላይ ክርክሩ እና ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር የስር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔን አግባብነት መመርመር ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ይዞታና ቤት አመልካች ለእኔ በስጦታ የተሰጠኝ እና ለአባቴ ውክልና ሰጥቼ በገንዘቤ ያስገነባሁት እንጂ ተጠሪ እንደምትለው አይደለም በማለት የምትከራከር ሲሆን ይህን ለማረጋገጥ የቀረበውም አቶ ታምሩ አበበ የተባሉ ግለሰብ ለአመልካች ይዞታውን በስጦታ የሰጧት መሆኑን እንደሆነ የስጦታ ውሉም በማህበራዊ ፍ/ቤት የፀደቀ መሆኑን እና ለወላጅ አባቷም ውክልና የሰጠች ፣ ቤቶቹን ተጠሪ እያከራየች እየተጠቀመች በመሆኑ ኪራዩን እንድትከፍለኝ የሚል ነው፡፡

እነዚህን ፍሬ ነገሮች አስመልክቶም በስር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክር የሚያከራክረውን ይዞታ አቶ ታምሩ አበበ የተባሉ ግለሰብ ለአመልካች ስጦታ መስጠታቸውን የሚያረጋግጥ ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀ የስጦታ ውል የቀረበ ስለመሆኑ፣ አመልካች ለአባቷ ንብረቱን እንዲያስተዳድርላት ውክልና የሰጠች መሆኑ፣ ሟችም የሚያከራክረው ይዞታ ላይ ቤቶችን መገንባቱን፣ ይዞታውም በአመልካች ስም በባህር መዝገብ ተ.ቁ. 3686 በሆነው ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ እንዲሁም ተጠሪ ሟች አቶ ቀለመወርቅን ያገቡት የሚያከራክረው ይዞታና ቤት ተገዝቶ እና ቤቶቹም በላዩ ላይ ከተገነቡ በኂላ ስለመሆኑ ማስረጃን የማረጋገጥ ፍሬ ነገርን የመለየት ሥልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለሀብትነት በማወቅ የመመዝገብ ሥልጣን ባለው አካል ይዞታን አመልካች ከአቶ ታምሩ አበበ በስጦታ ያገኘች መሆኑን አረጋግጦ በባህር መዝገብ መዝግቦ ያለ በመሆኑ አመልካች የዚህ ይዞታና ቤት ባለቤት መሆኗ በሚመለከተው አካል ፊት የተረጋገጠ መሆኑን እንዲሁም የእሷ አይደለም የሚል ወገን ቢመጣም መቃወሚያ እንዳሆን የሚያደርግ ህጋዊ ሂደቱ ተጠብቆ በህግ ጥበቃ እየተደረገለት ያለ መብት እንደሆነ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይህ ይዞታ በህግ አግባብ ለአመልካች የተላለፈ እና ሟች አባቷም ይህንኑ ንብረት ህጋዊ ውክልናን በመያዝ ሲያስተዳድርላት የቆየ መሆኑ የማያሳይ ሆኖ እያለ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይዞታውን እንድትለቅና በውርስ መጠየቅ እንደምትችል በመግለጽ መወሰኑ የበላይ ፍ/ቤትም ይህን ስህተት ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ሊሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ ተከትሎ የቀረበውን መዝገብ አስመልክቶ አጣሪ ችሎቱ የያዘው ጭብጥ ከላይ ውሣኔ ያገኙትን ቤቶች እና ይዞታን መሠረት አድርጐ በመሆኑ በጭብጥም ያልተያዘ አመልካችም ይህ የኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ በማለት ያቀረበችውን ክርክር አመልካች ራሷ የሰራችውን ቤት ተጠሪ እያከራየች የምትጠቀም ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃም ያልተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ማድረጉና በበላይ ፍ/ቤቶችም ውሣኔው ያለመለወጡ ተገቢ እንጂ የሚነቀፍና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊባል የሚገባው አይደለም ብለን አቤቱታውን ውድቅ አድርገን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1) የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 334609 ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/. 322203 ህዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2) የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 333945 ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 322114 በ15/7/2012 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 33695 በ11/03/2012 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
3) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

በዚህ መዝገብ በዛሬው ቀን የተሰጠው ውሣኔ ግልባጭ በመ/ቁ/ 201741 በሆነው የሰበር መዝገብ ላይ ተገልብጦ እንዲያያዝ ታዟል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.201894

መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- ቢላድ አህመድ ከሊፋ

ተጠሪ፡- አንበር አህመድ ኡመር } አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካችና በሰበር ያልተጠራ መሀመድ ሃሰን በተባለ ግለሰብ ላይ ይዞታን አስመልክቶ አቅርበውት የነበረው ክስ ተቀባይነት አግኝቶ የውሃ ቤርካ ያለበት ይዞታ እና 39.40 በ38.20 ካ.ሜ. ይዞታ የተጠሪ ነው ቀሪው ግን የአሁን አመልካች ነው ሲል የሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ላየው የሶማሌ ክልል የቆራሄ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ አቅርበውት የነበረው ክስ በአጭሩ፡- በቀብሪደሀር ከተማ 03 ቀበሌ የሚገኝ 550 ሺ. የሚገመት እና 2257.50 ካ.ሜ. በሆነው ይዞታ የአሁን ተጠሪ 500ካ.ሜ. ላይ ቪላ ቤት ገንብቷል፣ ሆኖም ዝምድና ስላለን እንዲጠብቅልኝ አድርጌ ሽማግሌ ገብቶ 5000. ዶላር እንድትከፍል ተጠይቃ አልከፈልም ስላለኝ 2ኛ የስር ተከሣሽም ወንድሟ ስለሆነ እየረዳት ስለሆነ ከስሻለሁ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ ይዞታው የእኔ ነው፣ ወንድሜ መሬቱ ላይ እንድትኖር ስላደረገ አይቻት ትቼ ዝም ብዬ ነበረ፣ መሬቱ ብዙ ነው፣ ያጠረሸውም አሁን ልቀቂ አልላትም የሚያከራክረውን መሬት

ግን ከተንበር ሠርታ ዘግታለች እናት በመሆኗ አልጠየኳትም በሚል አቅርባለች፡፡ 2ኛ ተጠሪ ከክስ ውጭ ስለሆነ መልስ አላቀረበም፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ አከራካሪው ይዞታ ባለበት ቦታ ሄዶ የተመለከተ ሲሆን፣ ከይዞታው ላይ 38.20 በ39.40 ካ.ሜ. የሆነው ይዞታ የከሣሽ መሆኑን ግራ ቀኙ የተማመኑ መሆኑን፣ ውሃ ቤርካ የተገነባበት ስፋቱ 11.40 ሜትር መሆኑን፣ ሌላው በግል የታጠረው ቤትም የተሰራበት 17.ሜ በ26.70 የይዞታ መጠን ላይ ነው ሲል በመግለጽ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው 11.40 እና 17 X 26.70 የማን ነው የሚል ጭብጥ በመያዝ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማድረጉን ማዘዙን፣ ቀጥሎም ክርክሩ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በመሆኑ የሰው ምስክር የማያስፈልግ መሆኑን፣ የስር ከሣሽ ያቀረቡትን የይዞታ ማረጋገጫን የሚመለከተው አካል አረጋግጦ ለፍ/ቤቱ እንዲልክ ትዕዛዝ መስጠቱን እና ምላሽ መቅረቡን ክርክሩ ያሳያል፡፡

በዚሁ መሠረት የአሁን ተጠሪ ያቀረበችው የይዞታ ማረጋገጫ ያልተመዘገበ መሆኑን የሚመለከተው አካል መግለጫ የሰጠ ስለሆነ፣ 5000 ዶላር ተጠሪ ልትከፍል ተስማምታለች የተባለውን በተመለከተም በጽሁፍ የተደረገ ውል ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለ መሆኑን፣ የሚያከራክረው 39.40 x 38.20 የሆነው ይዞታ የውሃ ቤርካ ያለበት ይዞታ የተጠሪ ነው፣ ሌላው ግን የቢላድ አህመድ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና የግራ ቀኙን ምስክሮች አስቀርቦ ሰምቶ የሚያከራክረው ይዞታ የአሁን ተጠሪ መሆኑ በምስክር ተረጋግጧል፣ በመሆኑም በይዞታው ላይ የተሰራው ቤት በአሁኑ ዋጋ ተገምቶ ለአሁን አመልካች ትክፈል ሲል የስር ፍ/ቤት ውሣኔን አሻሽሎ ወስኗል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኙ ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔን በመቃወም ሲሆን፣ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረበችው ማስረጃ ህገወጥ መሆኑም ሆነ ከሚመለከተው አካል ያልተሰጠ ሆኖ እያለ፣ ባለቤት መሆኗንም የሚያረጋግጥ ሳይሆን፣ ክርክሩንም እንደ ሁከት ክርክር በመቁጠር እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1168 መሠረት ለ15 ዓመት ያህል የተከፈለ የመሬት ግብር የተገበረበት ባልቀረበበት፣ ባለእጅ ይዞታ ናችሁ በማለት የሰጠው ውሣኔ ባልተጠየቀ ዳኝነት በመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 182/2/ ድንጋጌ አንፃር በሚቃረን መልኩ ባልተጠየቀ ዳኝነት አስቀድሞ በሰበር በመ/ቁ/ 30956 ከሰጠው ውሣኔ ጋር የሚቀረን ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም መሬት አይሸጥም አይለወጥም የሚለውን የህገ መንግሥት ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ፣ ይዞታው ላይ ግንባታ ሳከናውን ምንም ተቃውሞ ሳይቀርብ የተገነባ ሆኖ እያለ፣ ተጠሪም ከእኔ የተሻለ መብት እንደሌላት በተረጋገጠበት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጨማሪ

ምስክሮችን ሰምቶ አመልካች ከሟች እናቴ በውርስ መቀበሌን አስረድተው እያለ ተጠሪ መሬትን በህገወጥ መንገድ ሽያጭ ማግኘቷን ያስረዱትን ምስክሮች በመቀበል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ስላልሆነ ስህተቱ ሊታረም ይገባል ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የመሬት ግዢና ሽያጭ መሠረት ዋጋ ተገምቶ ቤት የገነባችበት መሬት ግምት እንድትከፍል በማለት የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 አኳያ ለመመርመር ሲባል ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ መዝገቡ የቀረበ ሲሆን መጥሪያም ለተጠሪ ተልኮላቸው ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ በጠበቃቸው አማካይነት መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ.ም. በተፃፈ በሰጡት መልስ የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 40/3 መሬት የህዝብና የመንግሥት በመሆኑ አይሸጥም አይለወጥም የሚለው መርህ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይሁንና በተያዘው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት መሬት ይሸጣል ወይም ይለወጣል የሚል ጭብጥ ተይዞ የተደረገ ክርክር እንዲሁም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠ ውሣኔ የለም፡፡ ከዚህ ባሻግር የሁከት ይወገድልኝ ክስ ቀርቦ የባለቤትነት ክስን መሠረት በማድረግ የተሰጠ ውሣኔም የለም፡፡ ተሰጥቶም ከሆነ ሥነ ሥርዓታዊ ክርክር በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ የሚቀርብ ክርክር አይደለም፡፡

ተጠሪ ከ20 ዓመት በፊት ከአሁን ተጠሪ ወንድም መግዛታቸውን፣ ቤት ገንብተውበታል፣የባለቤትነት ካርታም አውጥተውበት ህጋዊ ሆነዋል፣ ካርታውም የተሰጣቸው በ1996 ዓ.ም. ነው፣ ካርታው ህገ ወጥ ነው ከማለት በቀር ያቀረቡት ተጨባጭ ማስረጃ ስለሌለ የሚሰጥ ውሣኔ አይኖርም፡፡

አመልካች በሚያከራክረው ይዞታ ላይ ሊገኙ የቻሉት ተጠሪ ወደ ውጭ አገር በሄዱበት ወቅት አመልካች እና ባለቤታቸው/ማለትም የአሁን ተጠሪ ወላጅ አባት ጋር በአደራ ለመጠበቅ ስምምነት ላይ ደርሰው መሆኑን፣ አመልካችም ሲጠብቁ ቆይተው የተጠሪ ወላጅ አባት ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኂላ የተጠሪን አስቀድሞ የነበረን ቤት በማፍረስ በተጠሪ ይዞታ ላይ ያለተጠሪ እውቅና እና ፈቃድ አዲስ ግንባታ ገንብተው ለቅቀው ንብረቱን እንደያስረክቡ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ነው፡፡

በመሆኑም በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 መሠረት ንብረት ማፍራት የሚቻለው በህግ አግባብ ሲሆን በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ግንባታ ከገነቡ በኂላ ህጋዊ ነኝ ማለት ግን ቅንነት የጎደለው እና አለአግባብ ለመበልፀግ የሚደረግ ጥረት ነው፣ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ መገንባታቸውን ያልካዱ፣ ተጠሪም ንብረታቸውን በአደራ እንዲጠበቅላቸው አደራቸውን ከማስቀመጥ ባሻገር በይዞታው ላይ ግንባታ አመልካች እንዲገነቡ ፈቃዳቸውን ያልሰጡ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ በመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ አቅርበዋል፣ አመልካችም የቀደመው የሰበር አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቀርበው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልስ ከስር ፍ/ቤት አጠቃላይ ክርክር እና ውሣኔ እንዲሁም በአጣሪው ከተያዘው ማስቀረቢያ ጭብጥ አንፃር ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ አጠቃላይ ሂደት መገንዘብ የቻልነው ቀርቦ የነበረው ክስ የአሁን አመልካች 500ካ.ሜ. ላይ ቪላ ቤት ገንብቷል፣ ሆኖም ዝምድና ስላለን እንዲጠብቅልኝ አድርጌ ሽማግሌ ገብቶ 5000. ዶላር እንድትከፍል ተጠይቃ አልከፍልም ስላለኝ 2ኛ የስር ተከሣሽም ወንድሟ ስለሆነ እየረዳት ነው በሚል ክስ ማቅረባቸውን፣ አመልካች በበኩላቸው ይዞታው የራሳቸው እንደሆነ መከራከራቸውን ነው፡፡

በአጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የመሬት ሽያጭ ውሉ ከህገመንግሥቱ አንቀጽ 40/3/ አንፃር ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት የመወሰን አለመወሰኑን አግባብነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ /3/ "የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡" በሚል ይደነግጋል፡፡

ተጠሪ የሚያከራክረውን ይዞታ ከአመልካች ወንድም ከ20 ዓመት በፊት ገዝተው ቤት ሰርተው እየኖሩበትና ግብርም እየገበሩ የይዞታ ማረጋገጫም በስማቸው አውጥተው እየተጠቀሙ ያሉ መሆኑን በማንሳት የሚከራከሩ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው የሚያከራክረው ይዞታ ከእናታቸው በውርስ የተላለፈላቸው መሆኑን አንስተው የመሬት ሽያጭና ግዢ ውል ህገ ወጥ ነው በማለት ነው፡፡

ነገር ግን ተጠሪ ክስ ሲያቀርቡ ከላይ እንደተመለከትነው በይዞታቸው ላይ ተጠሪ ቤት ገንብተውበት ሽማግሌ ገብቶ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኗ፣ በሽማግሌ የተወሰነውንም 5000 ዶላር ለመክፈል ፈቃደኛ አይደለችም በሚል ሲሆን፣ ተጠሪ አንስተው የተከራከሩት ደግሞ ይዞታው የእኔ ነው፣ ወንድሜ መሬቱ ላይ እንድትኖር ስላደረገ አይቻት ትቼ ዝም ብዬ ነበረ፣ መሬቱ ብዙ ነው፣ ያጠረችውም አሁን ልቀቂ አልላትም የሚያከራክረውን መሬት ግን ከተንበር ሥርታ ዘግታለች እናት በመሆኗ አልጠየኳትም በሚል በመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተደርጐ የነበረው ክርክር የሚያሳየው የመሬት ሽያጭና ግዢ ተነስቶ ክርክር አለመደረጉን ይልቁንም አመልካች አጥረው የያዙትን ይዞታ ልቀቂ ማለት እንደማይፈልጉና ልቀቂ የሚሉት ሌላ አጥረው ከተምበር ሰርተው የዘጉትን ቦታ መሆኑን ነው፡፡

የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መስመር ለማስያዝ በማሰብ ከሚያከራክረው ይዞታ ድረስ በመሄድ እና የሚያከራክረውን ይዞታ በመለየት የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ከአጠቃላይ የግራ ቀኙ ይዞታ ለክርክሩ መሠረት መሆን የሚገባው ይዞታ 11.40 እና 17 X 26.70 የማን ነው የሚል ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሚያከራክረው 39.40 x 38.20 የሆነው ይዞታ የውሃ ቤርካ ያለበት ይዞታ የተጠሪ ነው፣ ሌላው ግን የቢላድ አህመድ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የህገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች አንፃር የሚያከራክረውን ይዞታ ተጠሪ አገኘሁት የሚሉት በሽያጭ እንደሆነ ምንም እንኳን በስር ፍ/ቤት ክርክር የተደረገበት መሆኑን የሚያሳይ ነገር ባይኖርም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ራሳቸው በሰጡት ምላሽ አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም በድንጋጌው መሠረት የመሬት ሽያጭ በህገ መንግሥቱ የተከለከለ በመሆኑ ተጠሪ ይዞታውን ያገኙበት መንገድ ህገ ወጥ በመሆኑ ለተጠሪ ሊፀናላቸው የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ይልቁንም በስር ፍ/ቤት የሚያከራክረውን ይዞታ ከክርክሩ መለየት ባለመቻሉ ችሎቱ በአካል ተመልክቶ እና ግራ ቀኙ የሚተማማኑበት የቱ እንደሆነ የሚከራከሩበት የቱ ይዞታ እንደሆነ ተለይቶ በሚያከራክራቸው ይዞታ ላይ ተከራክረው ማስረጃም ቀርቦ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ የተወሰነ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግን በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ወደ ጐን በመተው የይዞታው መተላለፊያ መንገድን ሳይመረምር እና ህጋዊነቱንም ከህገ መንግሥቱ ስለመሬት ማስተላለፊያ መንገዶች በህጋዊ መንገድ ስለመተላለፍ ሳያረጋግጥ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች የመሬቱን የአሁን ዋጋ ግምት እንዲከፍሉ ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የስር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ላይ የተፈፀመውን ስህተት ሳያርም ማለፉ ተገቢ አይደለም ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 05-01-122/13 ጥር 10 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 05-01-183/12 የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሶማሌ ክልል የቆራሄ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ msgo/m5/012 በቀን 19/06/2012 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርከር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. በዚህ መዝገብ የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በቆራሄ ከፍተኛ ፍ/ቤት አፈፃፀም ችሎት በመ/ቁ/ msgo/m/1/13 ላይ የተሰጠው እግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

<u>መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ</u>

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ 197183

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ደበርማዊ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. አለማየሁ ቶሎሳ - አልቀረቡም

2. በሻቱ ወጌ - ተወካይ ደረጀ ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ቤተክርስቲያን ነሐሴ 17 ቀን 2012 ዓ.ም በተወካይዋ አማካኝነት ተጽፎ በቀረበ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 222444 የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 332958 ነሐሴ 14 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቧ ነው፡፡

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መነሲቦ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን 1ኛ ተጠሪ እና በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ አላዛር ተረፈ የተባሉ ግለሰብ እንደቅደምተከተላቸው ተከሳሾች፤ የአሁን 2ኛ ተጠሪ እና አረጋሽ ነጋሳ የተባሉ ግለሰብ ደግሞ ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡ አመልካች ቤተክርስቲያን በሥር ፍ/ቤት ያቀረበችው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አዋሳኙ በክሱ የተገለጸው እና በመንዲ ከተማ 04 ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ለጥምቀት አገልግሎት ስትጠቀምበት የነበረ መሆኑን፤ 1ኛው ተጠሪ ከዚህ በፊት ይዞታዋን አልፎ ግንባታ በመፈጸሙ ምክንያት ጉዳያቸው በሽማግሌ ታይቶ በቀን 23/05/2010 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት በሕገ-ወጥ መንገድ የሰራው ግንባታ ተትቶለት ሁለተኛ ወደ አመልካች ይዞታ አልፎ እንዳይገባ የተስማሙ መሆኑን፤ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ ስምምነቱን በማፍረስ በምስራቅ በኩል ሰርቶ የሚገኘውን የመኖሪያ ቤት በማለፍ በግምት 400 ካ.ሜ የሚሆን ይዞታ ላይ በፍልጥ ቤት የሰራ መሆኑን፤ አስተዳደሩ አላግባብ የሰራውን ቤት እንዲያነሳው ደብዳቤ የጻፈለት ቢሆንም ፈቃደኛ አለመሆኑን፤ የስር 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ በምስራቅ አቅጣጫ ወደ ምንጭ ውሃ አካባቢ

የሚገኘውን በግምት 600 ካ.ሜ የሚሆን ይዞታ በመያዝ አጥር የሰራበት መሆኑን በመግለጽ አላግባብ የሰሩትን ግንባታ አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁ ይወሰንላት ዘንድ ዳኝነት መጠየቋን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች የመሬቱ ባለይዞታ መሆንዋን የሚያሳይ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ አላቀረበችም፤ በቀን 23/05/2010 ዓ.ም ተፈጸመ የተባለው የውል ስምምነት የቦታውን አዋሳኝ ለይቶ አይገልጽም፤ ከአመልካች ጋር ከዚህ በፊት ይዞታውን በሚመለከት አለመግባባት ተፈጥሮ መታረቃችን አይካድም፤ ቤት የተሰራበት መሬት ለአቶ ጆብር አለማየሁ በሕጋዊ መንገድ የተሰጠው ይዞታ ሲሆን ለሕዝብ ተከልሎ ከሚገኘው ይዞታ ውጪ በመሆኑ ክሱ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር 2ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ፡- የአሁን 2ኛ ተጠሪ በቡና ችግኝ አጥር ስራልኝ ብላኝ አጥር መስራት ስጀምር አመልካች ሰዎችን ልኮ ከቦታው አባሮኛል በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩለት ጠይቋል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት ክርክር አከራካሪ የሆነው ይዞታ የመንግስት ግብር የሚከፍሉበት ይዞታቸው መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ ክርክሩ የሚመለከታቸው መሆኑን በመግለጽ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ የጠየቁ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ያቀረቡትን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ውድቅ ያደረገው መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች እና ተጨማሪ ምስክሮች ከሰማ እና የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ አጥርቶ እንዲልክለት ካደረገ በኋላ ክርክር ያስነሳው መሬት በቀን 23/05/2010 ዓ.ም በተፈጸመው የእርቅ ውል ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ አይደለም፤ 1ኛ ተጠሪ የጆብር አለማየሁ ይዞታ ነው በማለት ቤት የሰራበት መሬት በአመልካች ክስ ላይ በተጠቀሰው አዋሳኝ የሚካተት ሲሆን አመልካች ክስ ያቀረበችበት ይዞታ የአመልካች ይዞታ ስለመሆኑ ከተሰጣት የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ላይ መገንዘብ ተችሏል፤ 1ኛ ተጠሪ ከልጃ ጆብር አለማየሁ ሕጋዊ ውክልና ሳይሰጠው ጆብር አለማየሁን በመወከል ለመከራከርም ሆነ እላዩ ላይ ቤት ለመስራት አይችልም፤ ለአቶ ጆብር አለማየሁ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው በአመልካች እና በአቶ ጆብር አለማየሁ መካከል ክርክር ቢነሳ ኖሮ ነበር፤ 1ኛ ተጠሪ በአከራካሪው መሬት ላይ ቤት መስራቱን ያልካደ እና ቤት የሰራውም ከአቶ ጆብር አለማየሁ ሕጋዊ ውክልና ሳይወስድ እና አመልካች ቤተክርስቲያን የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ በወሰደችበት ይዞታ ላይ አመልካች እየተቃወመችው የሰራ በመሆኑ ግምቱን የመጠየቅ መብት ሳይኖረው በራሱ ወጪ አፍርሶ መሬቱን ለአመልካች ሊለቅ ይገባል፤ በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ የገባቸው ከባለቤትዋ በውርስ እየተላለፍ መጥቶ በባለቤትዋ ተስፋዬ ቶሎሳ ላይ በደረሰ ይዞታ ላይ ነው፤ የከተማው አስተዳደር ይህን ይዞታ ለአመልካች ቤተክርስቲያን ሰጥቷል፤ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ የባለቤትዋ ልጆች ሕጋዊ ውክልና ሳይሰጥዋት እንደግል ንብረትዋ ለመከራከር መብት የላትም፤ መብት አላት ቢባል እንኳን አግባብነት ባላቸው መመሪዎች መሰረት

አስተዳደሩን በመጠየቅ መብቷን ከምታስከብር በቀር ጣልቃ ገብታ መከራከርዋ አግባብ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታቸውን በትዕዛዝ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪዎች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪው ይዞታ ከድሮ ጀምሮ የ1ኛ ተጠሪ ቤተሰብ እንደሆነ እና በኋላ ላይ የ1ኛ ተጠሪ ልጅ ለሆነው ጆብር አለማየሁ ለተባለ ሰው እንደተሰጠ፤ 2ኛ ተጠሪም ይዞታውን ከባለቤቷ ቤተሰብ በውርስ እንዳገኘች እና ከእጇ ወጥቶ እንደማያውቅ በስር ፍርድ ቤት ከቀረቡት ማስረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፤ አመልካች ሳይት ፕላን አለኝ ከማለት በቀር ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ከባለይዞታው ተወስዶ የተሰጣት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፤ ስለሆነም ይዞታው የአመልካች መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪዎች ይዞታውን እንዲለቁ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም ሲል ሽሮታል፡፡

አመልካች በተራዋ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበች ቢሆንም አቤቱታዋ በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ነሐሴ 17 ቀን 2012 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ይዘቱም፡- አከራካሪ የሆነው ይዞታ ከ2003 ዓ.ም በፊት ለጥምቀት በዓል ስጠቀምበት የነበረ ሲሆን በ 2003 ዓ.ም ደግሞ በከተማው መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ሳይት ፕላን ተሰጥቶኛል፤ 1ኛ ተጠሪ በሕገ ወጥ መንገድ ይዞታዬ ውስጥ በመግባቱ ጉዳያችን በሽማግሌ ታይቶ 400 ካ.ሜ ተትቶለታል፤ 1ኛ ተጠሪ እንደገና በግምት 400 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ የልጄ የጆብር አለማየሁ ነው በማለት በሕገ ወጥ መንገድ ቤት የገነባበት ስለመሆኑ እና 2ኛ ተጠሪም 600 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ በመያዝ አጥር ያጠረችበት ስለመሆኑ በወረዳው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ ተጠሪዎች ይዞታውን ሊለቁ አይገባም በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የተሰጣት መሆኑን መሠረት በማድረግ 1ኛ ተጠሪ በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት እንዲያፈርሱ በከተማ አስተዳደሩ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ባለበት እና 2ኛ ተጠሪ ባለይዞታ ስለመሆናቸው ባልተገለጸበት ተጠሪዎች ይዞታውን ሊለቁ አይገባም በሚል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- 1ኛ ተጠሪ የተከሰሰኩበት ይዞታ የቤተሰቦቻችን ነባር ይዞታ ሲሆን ልጄ ጆብር አለማየሁ በ1998 ዓ.ም ከመንዲ ከተማ አስተዳደር

በሕጋዊ መንገድ ያገኘው እና የግንባታ ፈቃድ የወሰደበት ነው፤ አከራካሪው መሬት በአመልካች ሳይት ፕላን ውስጥ እንደማይገኝም ተረጋግጧል፤ 2ኛ ተጠሪም ስፋቱ 600 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ በውርስ ወደ ባለቤቱ ተስፋዬ ቶሎሳ ተላልፎ የቡና ተክል እንዳለኝ እና የመንግስት ግብር እንደምገብርበት ተረጋግጧል፤ ስለሆነም ይህን መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈፀምን ማናቸውም ድርጊት እንዲቆም ወይም ተገቢው መብት እንዲመለስለት ሕጉ ከዘረጋቸው መንገዶች አንዱ የይዞታ ክስ ስለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1149/1 ድንጋጌ የሚያስገነዝብ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረውና ይህንኑ በሀይል ሲነጠቅ ወይም በይዞታዉ ስር ባለ ንብረት ላይ የመጠቀም መብቱን የሚያዉክ ተግባር ሲፈጸም ሲሆን ማረጋገጥ ያለበትም ንብረቱ በሕግ አግባብ በይዞታው ሥር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የሀይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጥር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ለአመልካች ቤተክርስቲያን በአከራካሪው ይዞታ ላይ ሳይት ፕላን የተሰጣት መሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪ የልጇ የአቶ ጆብር አለማየሁ ይዞታ ነው በማለት ቤት የሰራበት ይዞታ ለአመልካች በተሰጣት ሳይት ፕላን ውስጥ የሚገኝ መሆኑን፤ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ቀደም ሲል በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት በቀን 23/05/2010 ዓ.ም በተፈጸመው የእርቅ ስምምነት አከራካሪው ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ አለመሆኑ፤ 1ኛ ተጠሪ ከልጁ ጆብር አለማየሁ ይዞታውን በሚመለከት የተሰጠው ውክልና አለመኖሩ፤ 2ኛ ተጠሪ አጥራ የያዘችው ይዞታም ለአመልካች በተሰጣት ሳይት ፕላን ውስጥ የሚገኝ መሆኑን በወረዳው ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ ችለናል፡፡

1ኛ ተጠሪ ቤት የሰራበት እና 2ኛ ተጠሪም አጥራ የያዘችው አከራካሪ የሆነው ይዞታ ለአመልካች ቤተክርስቲያን በተሰጣት ሳይት ፕላን ውስጥ የሚገኝ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች በዚሁ ይዞታ ውስጥ ተፈጥሯል የምትለው የሁከት ተግባር እንዲወገድ ያቀረበችው ክስ በሕጉ አግባብ የቀረበ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በሳይት ፕላን ተረጋግጦ በተሰጣት ይዞታ ውስጥ የተፈጠረው የሁከት ተግባር እንዲወገድ እና ተጠሪዎች ይዞታውን እንዲለቁ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ከባለይዞታው ተወስዶ የተሰጣት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የሰጡት ውሳኔ ስለሁከት

ክስ አቀራረብና ሁከት እንዲወገድለት ክስ የሚያቀርብ ወገን ማስረዳት ስለሚጠበቅበት ፍሬ ነገር አስመልክቶ የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

6. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 222444 የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 332958 ነሐሴ 14 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
7. የመነሲቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 16830 በቀን 06/12/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 42961 ጥር 05 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
8. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

## የልዩነት ሀሳብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 የተመለከተው የችሎቱ ዳኛ አብላጫው ድምፅ የአመልካችንና 1ኛ ተጠሪን ክርክር አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ የምስማማ ሲሆን 2ኛ ተጠሪን አስመልክቶ ግን አብላጫው ድምፅ የስር ወረዳ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመቀበል በደረሰበት መደምደሚያ የማልስማማ በመሆኑ ለልዩነት መነሻ የሆኑኝን ምክንያቶች እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ መሃል ያለው ክርክር የይዞታ ይገባኛል የመፋለም ክርክር ሲሆን አመልካች ለይዞታው የተሰጣትን ሳይት ፕላን መሰረት በማድረግ በይዞታው ላይ የተረጋገጠ መብት ያላት መሆኑን በመግለፅ አላዛር ተረፈ በተባለ በወቅቱ አጥር በአከራካሪው ይዞታ ላይ ሲያጥር በነበረ ሰው ላይ ክስ አቅርባ የነበረ ቢሆንም ይህ ተከሳሽ አጥሩን የሚያጥረው ለ2ኛ ተጠሪ መሆኑን ገልፆ በመከራከሩ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ገብተው ይዞታው ለባለቤታቸው በውርስ ተላልፎላቸው አብረው ሲጠቀሙበት የነበረና ግብር በስማቸው የሚገብሩበት መሆኑን በመጥቀስ በይዞታው ላይ በህግ የተረጋገጠ መብት ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ መከራከራቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

አከራካሪው ይዞታ የቶሎሳ በቸሬ መሆኑን አቶ ቶሎሳ በቸሬ ከሞቱ በኋላ የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት አቶ ተስፋዬ ቶሎሳ በውርስ አግኝቶት ሲጠቀምበት ቆይቶ ሲሞት 2ኛ ተጠሪ አሁን ድረስ

የሚጠቀሙበት መሆኑን፤የ2008 ዓም ግብርም በስማቸው መክፈላቸው በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡የስር ፍርድ ቤት የ2ኛ ተጠሪን ክርክር ውድቅ ለማድረግ በመነሻነት 2ኛ ተጠሪ ከልጆቿ ውክልና ሳይኖራት ሙሉውን ለመጠየቅ መብት አላት? ወይስ የላትም? የሚለው በውርስ ህግ ታይቶ የሚወሰን ነው ካለ በዚህ አግባብም ተጣርቶ እና ድርሻ ተለይቶ ከቀረበ በኋላ የመፋለም ክርክሩ እንዲቀጥል ሊያደርግ ሲገባ 2ኛ ተጠሪ ለመከራከር መብት የላቸውም ካለ በኋላ በዚህ አግባብም ከውርስ እና ውክልና ስልጣኑ ጋር በተያያዘ ያሉት ነጥቦች ጠርተውና ተረጋግጠው ሲቀርቡ የመፋለም ክርክሩ የሚቀጥልበትን አግባብ ሊያመለክት ሲገባ ይዞታውን አስመልክቶ የመከራከር መብት የላቸውም ካለ በኋላ በፍርድ ቤቱ አረዳድ 2ኛ ተጠሪ በሌላቸው የመከራከር መብት ያቀረቡትን ክርክር በመመርመር ለጉዳዩ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የክርክር አመራር ስህተት መፈፀሙን ያሳያል፡፡

በፍሬ ጉዳዩ ላይ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔም አስመልክቶም የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ በአከራካሪው ይዞታ ላይ መብት አላቸው የሚል መነሻ ሳይኖረው የልማት ተነሺነት የሚሰጠውን መብትና ጥቅም የጠየቁት ከ8 አመት በኋላ ነው በማለት የ2ኛ ተጠሪን የይዞታ የይገባኛል ክርክር ውድቅ ማድረጉ አግባብ ነው ብዬ ስለማላንምን ይህ ውሳኔ በስራ ባልደረቦቹ መፅናቱም ከላይ ከተመለከቱት ነጥቦች አንፃር ምክንያታዊ ነው ብዬ ስለማላምን ከዚህ ይልቅ ጉዳዩ ለስር ፍርድ ቤት ተመልሶለት 2ኛ ተጠሪ በአከራካሪው ይዞታ ላይ ክርክር ለማቅረብ የሚያስችል መብትና የተሟላ ውክልና አላቸውን?አላቸው ከተባለስ አከረካሪው ይዞታ ለአመልካች የተላለፈው በህጉ አግባብ የ2ኛ ተጠሪና ሌሎች ወራሾች የካሳና ምትክ ቦታ ጥያቄዎች በአግባቡ ተመልሰው ነው ወይስ አይደለም የሚሉትና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦች ተጣርተው ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት ሊሰጠው ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረባዎቼ በሀሳብ ተለይቼያለሁ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ.202845

ጥቅምት 29/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ በላይ ማሞ ከጠበቃ አቶ ግሩም አየለ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ነ/ፈጅ አቶ ደምሰው ተፈራ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የሁከት ይወገድልኝ ክስን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/258880 ላይ ጥር 05/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/281986 ላይ መጋቢት 29/2012 ዓ.ም የተሰጠውን ብይን የሚነቀፍበት ጉድለት የለበትም በማለት በአሁን አመልካች የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ የሰረዘበት የመጨረሻ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን ቤት ወላጅ አባታቸው በህይወት እያሉ ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ ከአሁን ተጠሪ ተከራይተው በ1998 እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ከአባታቸው ጋር በቤቱ ውስጥ ሲኖሩ የነበረ መሆኑን፤ ወላጅ አባታቸው ከሞቱ በኋላ አቶ ወሰን ማሞ ከተባሉት ወንድማቸው ጋር ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የቤቱ የተከራይነት መብት እንዲተላለፍላቸው ለአሁን ተጠሪ ጥያቄ ሲያቀርቡ የተከራይነት ስሙ በሁለቱ ወራሾች አልያም በአንዳቸው ስም ሊሆን እንደሚችል በተጠሪ የተገለፀላቸው በመሆኑ ውሉ በወንድማቸው ስም እንዲደረግ ተስማምተው በዚሁ መሰረት የኪራይ ውሉ ተፈፅሞ ሁለቱም በቤቱ ውስጥ ሲኖሩ የቆዩ መሆኑን፤ ወንድማቸው በሌላ ክፍለ ከተማ ቤት የደረሳቸው በመሆኑ የተከራይነት ስሙ በስማቸው እንዲዞርላቸው ተጠሪን ሲጠይቁ “ቤቱን የተከራየው ሰው ግዴታውን አልተወጣም!” በሚል ምክንያት ቤቱን ለቀው እንዲወጡ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው መሆኑን በመግለፅ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ እንዲወገድላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ የመቃወሚያው ይዘትም ክስ የቀረበበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ክርክር የሚደረግበት ሳይሆን በአስተዳደራዊ መፍተሔ እልባት የሚያገኝ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለውም፤ ጥያቄውም በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የቤቶች አስተዳደር በመመሪያ ቁጥር 02/2010 አንቀፅ 56(1(ሀ)) በሚያዘው መሰረት በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፤ ከሳሹም ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት የሌለው በመሆኑ ክስ ለማቅረብ አይችልም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ብይን የቀረበው ክስ በይዞታ ላይ የተፈጠረ ሁከት ይወገድልኝ የሚል በመሆኑ ከሳሽ በንብረቱ ላይ የይዞታ መብት ያለው መሆኑ ወይም የንብረቱ አያያዝ ህጋዊ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1149 የሚፈቅድለት በመሆኑ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የለውም ሊባል አይችልም፤ ሆኖም አመልካች ጥያቄውን ለተጠሪም ሆነ ለፍርድ ቤት ያቀረበው በመመሪያ ቁጥር 02/2010 አንቀፅ 56(1(ሀ)) ስር ከተመለከተው ሶስት ወር በኋላ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል፤ የቤቱ የተከራይነት መብትም በአመልካች ወንድም ስም የነበረ ስለመሆኑ ተገልጿል፤ የቤቱ የተከራይነት መብት በአመልካች እና በወንድሙ አልያም በአንዳቸው ስም ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል ስለመገለፁ የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ አመልካች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት የለውም በማለት ክሱውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁን አመልካች በዚሁ ውሳኔ ላይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የይግባኝ አቤቱታውን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ዘግቷል፡፡ የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 08/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ብይን እና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ነሐሴ 03/2010 ዓ.ም ወራሽነታቸውን በማረጋገጥ መስከረም 07 እና 28 ቀን 2011 ዓ.ም ለክርክር መነሻ በሆነው ቤት በተከራይነት ለመቀጠል ለተጠሪ ጥያቄ አቅርበው እያለ የቀረበው አቤቱታ በይርጋ ይታገዳል በሚል ውድቅ የተደረገበት አግባብነት ከመመሪያ ቁጥር 02/2010 አንቀጽ 56(1(ሀ)) አንጻር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከአመልካች የሰበር ቅሬታ፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ አመጣጥ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው የአመልካች የክስ አቤቱታ ውድቅ የተደረገው በሁለተ ምክንያት ነው፡፡ የመጀመሪያ ክስ የቀረበበት ጉዳይ ለተጠሪም ሆነ ለፍርድ ቤት በመመሪያ ቁጥር 02/2010 አንቀፅ 56(1(ሀ)) ስር በተመለከተው የሶስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተከራይነት ስም በሌላ ሰው ስም ያለ በመሆኑ አመልካች ቤቱን አስመልክቶ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት የለውም የሚል ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ነጥቦች በሚከተለው መልኩ በተናጠል ታይተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የቤቶች አስተዳደር በመመሪያ ቁጥር 02/2010 አንቀፅ 56(1(ሀ)) ስር የተመለከተው የይርጋ ጊዜ በተከራይ መሞት ምክንያት የተከራይነት መብቱ ሊተላለፍልኝ ይገባል የሚል አካል ወራሽነቱን በፍርድ ቤት ካረጋገጠ በኋላ ጥያቄውን ለቤቱ አከራይ አስተዳደር አካል የሚያቀርብበትን ጊዜ የሚመለከት እንጂ በፍርድ ቤት የክስ ማቅረቢያ ጊዜን የሚመለከት አይደለም፡፡ የፍርድ ቤት ክርክርን አስመልክቱ ከሁከት ክስ ጋር በተያያዘ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ የተመለከተው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1149(2) ስር ነው፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ለአስተዳደር አካል የመብት ጥያቄ ማቅረቢያ ጊዜ እና ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረቢያ ጊዜን ቀላቀሎ ማየቱ ስህተት ነው፡፡ እናም የአመልካች ጥያቄ በእርግጥም በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ለማጣራት ለመብቱ መጠየቅ መሰረት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበትን እና ለአስተዳደር አካሉ እና ለፍርድ ቤት የመብት ጥያቄው የቀረበበትን ጊዜ በአግባቡ ማየት ያስፈልጋል፡፡

በፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ በተመለከተ ለክሱ መሰረት የሆነው የሁከት ተግባር ተፈፅሟል የተባለው ህዳር 25/2012 እና ታህሳስ 06/2012 ዓ.ም ሲሆን የሁከት ይወገድልኝ ክስ የቀረበው ደግሞ ታህሳስ 13/2012 ዓ.ም መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ የሁከት ይወገድልኝ ክስን አስመልክቶ ለክስ ማቅረቢያ የተቀመጠው ጊዜ የሁከት ተግባሩ ከተፈጠረበት አልያም ንብረቱ በሁከት ምክንያት ከተወሰደብት ጊዜ አንስቶ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በፍርድ ቤት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረቡት "የሁከት ተግባር ነው" የተባለው ድርጊት በተፈፀመ በቀናት ልዩነት በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡

ሆኖም ለአስተዳደር አካሉ የመብት ጥያቄ ማቅረቢያ ጊዜን አስመልክቶ የቀረበው ክርክር በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ወራሽነቴን ያረጋገጥኩት ነሓሴ 03/2010 ዓ.ም ሲሆን የስም ዝውውር እንዲደረግልኝ ለተጠሪ ጥያቄ ያቀረብኩት መስከረም 07 እና 28 ቀን 2011 ዓ.ም በመሆኑ በመመሪያ የተመለከተው የሶስት ወር ጊዜ አላለፈም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች ነሓሴ 03/2010 ዓ.ም ወራሽነታቸውን በፍርድ ቤት አረጋግጠው የስም ዝውውር እንዲደረግላቸው መስከረም ወር 2011 ዓ.ም ለተጠሪ ጥያቄ ስለማቅረባቸው የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በራሱ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ባቀረቡት የክስ ዝርዝር ውስጥ የቤቱ ተከራይ

የነበሩት ወላጅ አባታቸው በ1998 ዓ.ም እንደሞቱ አመልካች እና ወንድማቸው ወራሽነታቸውን በፍርድ ቤት አረጋግጠው ተመሳሳይ የተከራይነት ስም ዝውውር አቅርበው የነበረ መሆኑን፤ በወቅቱም የተከራይነት ስሙ በሁለቱ አልያም በአንዳቸው ሊሆን እንደሚችል በተጠሪ በኩል በመገለፁ የተከራይነት ስሙ በአመልካች ወንድም ስም እንዲሆን የተደረገ ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ በክሱ ውስጥ በተገለፀው አኳኋን አመልካች ቀደም ብለው ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ከሆነ ነሓሴ 03/2010 ዓ.ም በድጋሚ ወራሽነት ማረጋገጥ የተፈለገበት እና የተቻለበት ምክንያትም ግልፅ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር በስር ፍርድ ቤት የተደረገ ማጣራት ስለመኖሩም የቀረበው የመዝገብ ግልባጭ የሚያሳይ ነገር የለውም፡፡ እናም አመልካች ለተጠሪ ያቀረቡት የተከራይነት ስም ይዛወርልኝ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን አለመሆኑ ላይ አቋም ከመያዙ በፊት ከቀረበው ክስ እና ክሱን ለማረጋገጥ በአስረጂነት ከቀረበው ማስረጃ ይዘት አኳያ አመልካች በትክክል ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት ጊዜ በአግባቡ ሊጣራ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር ተገናዝቦ እልባት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የአመልካች ክስ ውድቅ የተደረገው ክስ ባቀረቡበት ቤት ላይ ከውልም ሆነ ከህግ የመነጨ መብት እና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ የፍትሓ ብሔር ሥነ ሥረዓት ህጉ በሁለተኛው መፀሓፍ ስለ ጠቅላላ ደንቦች በሚደነግገው ምዕራፍ አንድ ቁጥር 33 ስር በአንድ የፍትሓ ብሔር ክርክር ማናቸውም ሰው ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ላይ ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ክስ ማቅረብ የማይፈቀድለት መሆኑን፤ እንዲሁም ከተከሳሽ ላይ የሚጠይቀውን ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታ ካላቀረበ በቀር በማናቸውም ሰው ላይ ክስ ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ዓላማ ለክርክር ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ ትክክለኛ ጥቅም ያለውን ወገን(Real party in the interest) መለየት ነው፡፡ ክርክር በተነሳበት ጉዳይ ላይ ትክክለኛ ጥቅም ያለውን ወገን መለየት ያስፈለገው በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ስለመሆኑ በዚሁ ዙሪያ ከተፃፉት የጥናት ፅሁፎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት በአንድ ሰው መብት/ጥቅም ላይ ሌሎች ሰዎች ክስ እንዳያቀርቡ መከላከል(to prevent suit by a person who wants to litigate someone else's claim against the defendant) የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ ያለው መብት/ጥቅም ለሌላ ሰው ተላልፎ ከሆነ ተከሳሹ ወገን በአንድ ጉዳይ በሁለት የተለያዩ ሰዎች ሊቀርብበት ከሚችለው ሁለት ክስ መከላከል(to prevent two suits against the defendants for a single wrong where the interest in the subject matter has been transferred) የሚል ነው፡፡

እናም በአንድ የፍትሓ ብሔር ክርክር ጉዳይ ወደ ክሱ ሥረ ነገር ክርክር ሳይገባ ክሱን ያቀረበው አካል ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የለውም በሚል ምክንያት አቤቱታውን ውድቅ ለማድረግ

ከላይ ከተመለከቱት መመዘኛዎች አንፃር ክስ ያቀረበው አካል በእርግጥም መብት እና ጥቅም የሌለው ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አኳኋን አቋም ለመውሰድ የሚያስችል ግልፅ ማሳያ ከሌለ በቀር ክሱን ያቀረበው አካል የሚኖረው መብት እና ጥቅም በሥረ ነገር ክርክር ወቅት በማስረጃ የሚረጋገጥ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 33 መሰረት አቤቱታን ውድቅ ከማድረግ ሊቆጠቡ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ክስ ያቀረቡት የተከራይነት መብቱ በውርስ ሊተላለፍልኝ የሚገባውን እና እየኖርኩበት ያለሁትን ቤት ተጠሪ ሊያስለቅቀኝ እንቅስቃሴ የጀመረ በመሆኑ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ ሊወገድልኝ ይገባል በሚል ነው፡፡ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ንብረቱን በተመለከተ በህግ ከተረጋገጡለት መብቶች ውስጥ አንዱ በሀብቱ ላይ የተፈጠረው ህገ ወጥ ሁከት እንዲወገድለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ ክስ የሚያቀርብ ሰው ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት መሆኑን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1140፣ 1146 እና 1149 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ ለቀረበው ክስ ተጠሪ በሰጡት መልስ የተከራይነት ስሙ በአመልካች ስም የሌለ በመሆኑ ልከሰስ የሚችልበት ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ ምክንያት የለም በማለት ሞግቷል፡፡ ከተጠሪ መከራከሪያ በግልፅ መረዳት የሚቻለው ስለ ቤቱ አያያዝ ህጋዊነት ከሚከራከሩ በቀር ቤቱ በአሁን አመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን እና ይህንኑ ቤት ለማስለቀቅ ሂደት መጀመሩን አልካደም፡፡

የሁከት ይወገድልኝ ክስ በቀረበበት ወቅት ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በአመልካች እጅ መኖሩ ካልተካደ ሁኔታው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ በቂ መብት የሚፈጥር በመሆኑ አመልካች በመጀመሪያው የክርክር ምዕራፍ ላይ መብት እና ጥቅም የላቸውም ሊባሉ አይገባም፡፡ የቤቱ አያያዝ ህጋዊነት፣ በህግ ረገድ ስለሚኖረው ውጤት እና ተያያዥ ጉዳዮች በክርክር ሂደት ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት የተሟላ ክርክር እና ማስረጃ ነጥሮ የሚወጣ ጉዳይ እንጂ ክስ ለማቅረብ ከሚኖር መብት እና ጥቅም ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የተሟላ ክርክር እና ማስረጃን ሳይሰማ በክርክር ሂደት በማስረጃ ሊጣራ የሚገባን ነጥብ መዝዞ አመልካች ክርክር በተነሳበት ንብረት ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይህንኑ አቋም መቀበሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33 እና የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1149 ድንጋጌዎችን መሰረታዊ ዓላማ ከግንዛቤ ያላስገባ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም እና አረዳድ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/258880 ላይ ጥር 05/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/281986 ላይ መጋቢት 29/2012 የተሰጠውን ብይን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ፡-
   2.1. ከቀረበው ክስ እና ማስረጃ አኳያ አመልካች ወራሽነታቸውን በፍርድ ቤት ያረጋገጡበት ትክክለኛ ጊዜ መቼ እንደሆነ፤ በክሱ ዝርዝር እንደተመለከተው አመልካች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት በ1998 ዓ.ም ወላጅ አባታቸው እንደሞቱ ከሆነ ነሐሴ 03/2010 ዓ.ም በድጋሚ ወራሽነት ማረጋጥ የተቻለበት ምክንያት እና ህጋዊ ውጤቱ ምን እንደሆነ በመለየት አመልካች በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የቤቶች አስተዳደር በመመሪያ ቁጥር 02/2010 አንቀፅ 56(1(ሀ)) ስር በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄያቸውን ለአሁን ተጠሪ አላቀረቡም በማለት በቀረበው መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ብይን እንዲሰጥ፤
   2.2. የቀረበው መቃወሚያ በምክንያት የሚታለፍ ከሆነ በክሱ ሥረ ነገር ክርክር ላይ የግራ ቀኙን የተሟላ ክርክር እና ማስረጃን በመስማት የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት ጉዳዩ ይመለስለት፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የሰ.መ.ቁ 203882

መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ብርሃኑ ሻይ

2. ወ/ሮ ምህረት ሻይ

3. ሲ/ር እየሩሳሌም ሻይ

4. ወ/ት አለምጸሐይ ሻይ

(1-4) አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ ነብያት ግርማ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

2. የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ቤቶች አስተዳደር - ዐ/ህግ ለታ ባይሳ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 276300 መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 254780 በቀን 01/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማ ቤት ሁከት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በቀድሞ አጠራር ወረዳ 05 ቀበሌ 15 በአሁኑ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የሚገኝ ቁጥሩ 1141 የሆነ ቤት ከወላጆቻቸው በውርስ የተላለፈላቸው እና በቀን 24/05/2008 ዓ.ም በስማቸው ካርታ የተሰጣቸው መሆኑን፤ በዚሁ ቤት ግቢ ውስጥ አውራሾቻቸው በሕይወት እያሉ የዋናው ቤት አካል ሆኖ የሚጠቀሙበትን ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት ያለ መሆኑን፤ ወላጆቻቸው በሕይወት እያሉ ማድቤቱን በችግር ላይ ለነበረች ሴት ለጊዜው ሰጥተዋት የነበሩ መሆኑን፤ ሆኖም አዋጁ ሲታወጅ

የሴትየዋ ልጅ በወቅቱ ቀበሌ ይሰራ ስለነበር ስልጣኑን ተጠቅሞ ቤቱን እንደተከራየ አድርጎ ቁጥር 1140 የሚል ቁጥር ያሰጠው መሆኑን፣ ግለሰቧም ቤቱን ለቃ ለአውራሻቸው ሳታስረክብ የሄደች መሆኑን፣ አመልካቾች በይዞታቸው ስር አድርገው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን፣ ሆኖም 1ኛው ተጠሪ በሰጣቸው ካርታ ላይ ይህንኑ ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት የመንግስት ብሎ በመስራት፣ 2ኛ ተጠሪም ቤቱ የራሴ ነው በማለት ሁከት እየፈጠሩባቸው የሚገኙ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ የአመልካቾች አውራሾች ክስ የቀረበበትን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አስረክበዋል፣ 2ኛ ተጠሪ ቀደም ሲል ቤቱን ለአቶ ወርጃ አበዙ አከራይቶ ኪራይ ሲሰበስብበት የቆየ ነው፣ ተከራይ ቤቱን በምን አግባብ እንደለቀቀ ሳይታወቅ አመልካቾች ክስ የቀረበበትን ቤት ቀላቅለው ይዘዋል፣ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ፣ ቁጥራቸው 1140 እና 1141 የሆኑትን ቤቶች ማሕደሮች አስቀርቦ ከተመለከተ እና ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲላክለት ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ካርታ ያቀረቡ ቢሆንም አከራካሪው መጸዳጃ ቤት እና ማዕድ ቤት በይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ውስጥ የማይካተት መሆኑ ተረጋግጧል፣ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በሰጠው መልስ ቁጥሩ 1140 የሆነው ቤት መጸዳጃ ቤት እንደሆነ እና አመልካቾች የያዙት ቢሆንም በሲአይኤስ ላይ የቀበሌ ቤት በሚል የተገለጸ ነው የሚል ምላሽ ልኳል፣ 2ኛ ተጠሪ የመንግስት ነው የሚለው ቤት አመልካቾች ለመጸዳጃ ቤት የሚገለገሉበት እና 2ኛ ተጠሪም ይህን ቤት እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ሲያከራየው የነበረ ነው፣ 2ኛ ተጠሪ ቤቱ በምን አግባብ ከእጁ ሊወጣ እንደቻለ አላስረዳም፣ የአመልካቾች ምስክሮች አመልካቾች ቤቱን ሲገለገሉበት እንደነበረ ያስረዱ ቢሆንም ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ስለሌለ አከራካሪው ቤት የአመልካቾች አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ፍርድ ቤት ከቀረበለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ጭብጥ ወጥቶ የባለቤትነት ፍርድ መስጠቱ አግባብ አይደለም፣ ሁከት እንዲወገድ በሚል በሚቀርብ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት የለውም፣ አመልካቾች ወደፊት ለክርክሩ መነሻ በሆነው መኖሪያ ቤት ላይ የምናነሳውን የባለይዞታነት ክርክር በሚገድብ መልኩ የተሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሁከት ይወገድ የሚል ክስ አቅርበው ሳለ አከራካሪው ቤት የአመልካቾች የግል ሀብት አይደለም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር

ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የአመልካቾች መሆን አለመሆናቸው ጭብጥ ተይዞ ውሳኔ የተሰጠው አመልካቾች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን በመግለጽ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ስላቀረቡ ነው፤ የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አስፈላጊ የሆነውን ጭብጥ በመያዝ እና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በማስቀረብ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት 1ኛው ተጠሪ በሰጣቸው ካርታ ላይ አከራካሪ የሆነውን ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት የመንግስት ብሎ በመስራት፤ 2ኛ ተጠሪም ይህንኑ ቤት የራሴ ነው በማለት ሁከት የፈጠሩብን በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድልን የሚል ነው፡፡ ሆኖም የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ሁከት ይወገድልን የሚል ቢሆንም ይህንኑ ዳኝነት ሊጠይቁ የቻሉት አከራካሪ የሆነው ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት ከአውራሾቻቸው የወረሱት ቤት አካል መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ ይህም አመልካቾች የአከራካሪው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት ባለቤት መሆናቸውን በመግለጽ በዚሁ ቤት ላይ ተፈጠረ የሚሉት ሁከት እንዲወገድ ክስ ያቀረቡ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች አከራካሪ የሆነው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት የቀበሌ ቤት መሆኑ እና 2ኛ ተጠሪም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ሲያከራየው የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት በአከራካሪው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት ላይ በተጠሪዎች ተፈጥሯል የሚሉት ሁከት እንዲወገድ የሚል ቢሆንም ይህንኑ ዳኝነት ሊጠይቁ የቻሉት አከራካሪ የሆነው ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት ከአውራሾቻቸው የወረሱት ቤት አካል መሆኑን እና የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን በመግለጽ በመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አጣርቶ አመልካቾች የአከራካሪው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት የአመልካቾች የግል ሐብት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካቾች ለጠየቁት ዳኝነት ምላሽ የሰጠ

እና በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 276300 መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 254780 በቀን 01/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ሚያዝያ 05 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ማ/አ**

የሰ/መ/ቁጥር 218309

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ቂስ ቀፀላጊዮርጊስ ደስታ

ተጠሪዎች፡- 1) አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ፅ/ቤት

2) አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቤቶች አስተዳደር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደደር የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 35011 ታሕሳስ 7ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠው ትእዛዝ የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምላቸው አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጀመረው የሁከት ክርክር የሰበር አመልካች ከሣሽ፣ የሰበር አንደኛ ተጠሪ ተከሣሽ፣የሰበር ሁለተኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ግንቦት 2ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ ክሣቸው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 648 የሚታወቀው ቤት የግል ቤታቸው መሆኑን፤ የቤት ቁጥር 649 ደግሞ የአስተዳደሩ ሆኖ አመልካች የግል ቤታቸው ስለጠበባቸው በኪራይ እንዲሰጣቸው ሕዳር 21ቀን 1985 ዓ/ም ጠይቀው በቃለ-ጉባኤ ተሰጥቷቸው እንዲሁም ቤቱ ወንዝ ዳር በመሆኑ በወንዙ የተወሰደውን የቤቱን ክፍል በራሣቸው ወጪ አድሰው ኪራይ እየከፈሉ በይዞታቸው አድርገው እስካሁን እየተጠቀሙበት መሆኑንና ውል እንዲይዝላቸው ኪራይም እንዲቀበላቸው ሲጠይቁት ይጠብቁ ሲላቸው ከቆየ በኂላ ሚያዚያ 28ቀን 2013ዓ/ም የግል ቤታቸውን ጨምሮ ማሸጉን ዘርዝረው የፈጠረባቸው ሁከት እንዲቆም የቤቱንም ኪራይ እንዲቀበል እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የቀበሌው አስተዳደር አከራካሪውን ቤት የሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል የተባለ ቃለ-ጉባኤ፣ በመዝገብ ቁጥር 648/91 የተሰጠ ውሣኔና የአፈፃፀም ችሎቱ የሰጠውን ትዕዛዝ በማስረጃነት ስለማቅረባቸው የስር ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ያስገነዝባል፡፡

አንደኛ ተጠሪ የመልስ ክርክሩን እንዲያቀርብ ታዞ አላቀረበም፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ሆኖ ለክርክሩ መንስዔ የሆነውን ቤት ማሸጉን ሣይክድ ነገር ግን አመልካች በክፍለ ከተማው ወረዳ 03 ውስጥ የግል ቤት ያላቸው ስለሆነና የግል ቤት እያላቸው የመንግስት ቤትን በኪራይ መያዝ ስለማይችሉ ቤቱ መታሸጉ በሕግ የተሰጣቸውን ሀላፊነት መወጣታቸውን እንጅ ሁከት ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የግል ቤታቸውና ግማሹ በጎርፍ የተወሰደው የተጠሪው ቤት በአንድ ጣራ ስር መሆናቸውን በ1985 ዓ/ም ስራ ላይ የነበረው የቀበሌ አስተዳደር ቤቱን በኪራይ የሰጣቸው የግል ቤታቸው በመጥበቡ መሆኑን፣ ቀደም ሲል በፍርድ ቤት ሲከራከሩ ቆይተው ስለተወሰነላቸው መረከባቸውን በመጥቀስ ለዚህ ጉዳይ መመሪያው ተፈፀሚነት ሊኖረው አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ክስና የመልስ ክርክር ከሰነድ ማስረጃ ጋር አጣምሮ ከመረመረ በኋላ አመልካች የግል ቤት ያላቸው ስለመሆኑ አለመካዱን በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 10(8) መሰረት የግል ቤት ያለው ሰው የቀበሌ ቤት የያዘ ከሆነ የቀበሌ ቤቱን መመለስ እንደሚገባው የሚደነግግ በመሆኑ ተጠሪው የፈፀመው ድርጊት ሁከት አይደለም ሲል የአመልካችን ክስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(2) ድንጋጌን በመጥቀስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት አመልካች የይግባኝና የሰበር አቤቱታቸውን በየደረጃው ለሚገኙት የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ያቀረቡ ቢሆንም ስለተሰረዘባቸው ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች ታሕሳስ 16ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታቸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከቀድሞው ወረዳ 6 ቀበሌ 13 አስተደደር ፅ/ቤት መጀመሪያም በቃለጉባኤ ተሰጥቷቸው በኋላም በፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 648/2011 በተደረገው ክርክር ውሣኔ አግኝቶ ውሳኔው እንዲፈፀም በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ግንቦት 27 ቀን 1994ዓ/ም ስለመረከባቸው በሰነድ ማስረጃ በተረጋገጠበት፤ የቤት ቁጥር 649 የሆነውን የተከራዩት የግል ቤት እያላቸው ነገር ግን ችግራቸው ታይቶ ከ17 ዓመት በፊት መሆኑ በተረጋገጠበት የግል ቤት ሣይኖራቸው የተከራዩት በማስመሰልና በመገንዘብ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራውን መመሪያ ቁጥር 5/2011 በመጥቀስ ተጠሪው ሁከት አልፈጠረም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሣኔ የቤት ቁጥር 648ን በሚመለከት የቀረበውን ክርክር መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን፤እንዲሁም የቤት ቁጥር 649ን በሚመለከት የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 820/94 መጋቢት 9ቀን 1994 ዓ/ም የሰጠውን የአፈፃጸም ትዕዛዝ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑ እንዲመረመር ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪው በበኩሉ የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አመልካች የቤት ቁጥር 648 ተብሎ የሚታወቅ የግል ቤት ያላቸው ስለመሆኑ ባለመካዱ መመሪያ ቁጥር 5/2011 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ውሣኔ

መሆኑን፣ በወረዳ አስተዳደር ለዚያውም መመሪያን በመጣስ የግል ቤት ላለው ሰው የመንግስት ቤት መስጠትም ሆነ መያዝ ሕገ ወጥ መሆኑን ገልፆ የስር ፍርድ ቤቱ ውሣኔ እንዲፀና ተከራክሯል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ሲሆን የስር ፍርድ ቤቱ ተጠሪው ቤቱን ማሸጉ ሁከት አይደለም ሲል በመወሰኑና በየደረጃው የሚገኙት ፍርድ ቤቶችም ይህን ውሣኔ በማፅናታቸው የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን በጭብጥነት ተይዞ ጉዳዩ ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረው የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ ይዘት በወቅቱ የቀበሌን ቤት ያስተዳድር በነበረው የመንግስት አካል የቤት ቁጥር 648 የግል ቤታቸው መሆኑን እያወቀ ነገር ግን ቤታቸው በመጥበቡ ችግራቸውን ለማቃለል ሲባል የመንግስት ቤት የሆነውን 649 በኪራይ እየከፈሉ እንዲኖሩበት የተሰጣቸው መሆኑን በኋላም በዚሁ ቤት ላይ በፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር ቤቱ ለአመልካች እንደሚገባ ተወስኖላቸው በአፈፃፀም ከተረከቡ በኋላ በራሳቸው ወጪ አድሰው ኪራይ እየከፈሉ እስካሁን ድረስ ሲጠቀሙ የቆዩ ቢሆንም ሚያዚያ 28ቀን 2013ዓ/ም አንደኛ ተጠሪው የግል ቤታቸውን ጨምሮ ቤቱን በማሸጉ ሁከት ነው ተብሎ ሁከቱ እንዲወገድ የቤቱን የኪራይ ዋጋም እንዲቀበላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ቀርቦ የከተማ አስተዳደሩን የመንግስት ቤቶች ለማስተዳደር የወጣው መመሪያ ቁጥር 5/2011 በሚደነግገው መሰረት አመልካች የግል መኖሪያ ቤት እያላቸው የመንግስትን ቤት በኪራይ መያዝ ስለማይችሉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ማሸጉ ሁከት አይደለም ሲል መከራካሩን የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያስገነዝባል፡፡

እንደሚታወቀው ከሣሽ የሆነ ወገን ተገቢነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ የክስ አቤቱታ አቅርቧል ለማለት የሚቻለው ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ንብረት በእጅ አድርጎ የሚገኝ እና ንብረቱ ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጭበረበረና በማኛቸውም መንገድ ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ ያልያዘው መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ፣ በዚህ መሰረት ክስ የቀረበበት ተከሣሽ ድርጊቱን እንዲፈፅም የተፈቀደለት መብት ወይም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በማይታበይ ሁኔታ ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1140ና 1149 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በቀረበልን ጉዳይ ክሱ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በኪራይ የያዙት የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀፅ 10(8) ድንጋጌን በመጣስ የግል ቤት እያላቸው ነው ካለ በኋላ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(2) ጠቅሶ ውደቅ አድርጓል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33 በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን በሚደነግገው የስነ ስርዓት ሕጉ ሁለተኛ መፅሐፍ ስር የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው ክስ ሊያቀርብ የሚችለው ወይም የሚገባው ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ መረጋገጥን ከከሣሽነት መመዘኛዎች መካከል አንዱ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓላማም በአከራካሪው ንብረቱ ወይም

መብት ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ጥቅም የሌለው ሰው ክስ እያቀረበ የተከራካሪ ወገኖችን እና የፍርድ ቤቱን ጊዜ እንዳያባክን፣ ተገቢነት ለሌለው የገንዘብ ወጪ ምክንያት

እንዳይሆን ታስቦ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤቱ ለሰጠው ውሣኔ መሰረት ያደረገው የከተማ አስተደደሩን መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀፅ 10(8) ድንጋጌን ነው፡፡ ይህ አንቀፅ ንብረትነታቸው የቀበሌ ወይም የመንግስት የሆኑ መኖሪያ ቤቶች ለተከራይ ነዋሪዎች የሚሰጡበትን መመዘኛዎች የሚደነግግ ነው፡፡ ከእነዚህ መመዘኛዎች መካከል የግል ቤት ወይም ሌላ በማናቸውም ምክንያት የተገኘ መኖሪያ ቤት አለመኖር አንዱ ሊሆን እንደሚገባና የግል ወይም በማኛቸውም መንገድ የተገኘ መኖሪያ ቤት ያለው ሰው የቀበሌ ቤት የያዘ ከሆነ የቀበሌውን ቤት ሊመልስ እንደሚገባ የአንቀፁ ንዑስ አንቀፅ 8 ይደነግጋል፡፡ የመመሪያው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ  የሚሆኑት ከነሐሴ 10ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ አንቀፅ 60 ይደነግጋል፡፡ በዚህ አንቀፅ ላይ የተደነገገው የተፈፃሚት ጊዜና የመመሪያውን አስፈላጊነት ለማስገንዘብ በመግቢያው ላይ የተዘረዘሩት ምክንያቶች ጣምራ ንባብ መመሪያው ተግባራዊ እንዲሆን ከተገለፀው ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ታስቦ የወጣ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም ማለት ይህ መመሪያ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ንብረትነቱ የመንግስት የሆነን መኖሪያ ቤት ለግሰቦች በኪራይ መስጠትም ሆነ መያዝ የሚቻለው ተከራዩ የግል ወይም በማናቸውም መንገድ የተገኘ ሌላ መኖሪያ ቤት የሌለው መሆነን በማረጋገጥ ሊሆን እንደሚገባ የሚደነግግ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ  በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች የግል ቤት ያላቸው መሆኑ እየታወቀ ቤቱን ሲያስተዳድር በነበረው የመንግስት አካል በ1985 ዓ/ም በሕጋዊ መንገድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ፤ ከዚህ በኂላም  በፍርድ ቤት ውሣኔ ቤቱን መረከባቸውን፤ ከ1985 ዓ/ም ጀምሮ ኪራይ እየከፈሉ በይዞታቸው አድርገው ሲጠቀሙበት መቆየታቸው በመዘርዘር የሚያቀርቡትን ክርክር ተጠሪው በግልጽና በዝርዝር ክዶ የተከራከረ መሆኑን መዝገቡ አያመላክትም፡፡ ተከሣሽ የተከሰሰበትን ነገር መካድ የሚችለው በከሣሹ የቀረቡትን ነገሮች ሁሉ በዝርዝርና በግልጽ ክዶ በመቃወም ሊሆን እንደሚገባና የቀረበውን ነገር በዝርዝርና በግልጽ ያለመካድ ያልተካደውን ነገር በከፊልም ሆነ በሙሉ አምኖ እንደመቀበል የሚያስቆጥር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 83 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አመልካች አከራካሪውን ቤት ያገኙት የግል ቤት ያላቸው ስለመሆኑ በአስተዳደር አካሉ ታውቆና ችግራቸው ታምኖበት ተሰጥቷቸው በኂላም በፍርድ ቤት ውሣኔ አፈፃፀም ቤቱን ተረክበው ኪራይ እየከፈሉ ሲገለገሉበት መቆየታቸው ካልተካደ አመልካቹ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1140 በሚደነግገው መሰረት ተከራይ ባለይዞታ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በወቅቱ አከራካሪውን ቤት ሲያስተዳድር በነበረው የመንግስት አካል የቤቱን ኪራይ እየከፈሉ አመልካች እንዲኖሩበት በሠጣቸው ጊዜ የግል መኖሪያ ቤት እንዳላቸው እውቅና አልነበረም የሚል ክርክር ባልቀረበበትና ባልተረጋገጠበት፤ እንዲሁም ቤቱ ለአመልካች በተሰጠበት ወቅት በማናቸውም

መንገድ የተገኘ ሌላ መኖሪያ ቤት እያለው የመንግስት ቤት በኪራይ መስጠትም ሆነ መያዝ ክልከላ የነበረ ስለመሆኑ በተጠሪው ክርክር ባልቀረበበት ከነሐሴ 10ቀን 2011ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ታስቦ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 5/2011 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ የተጠሪው ድርጊት ሁከት አይደለም ተብሎ መወሰኑ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረት ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1) የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 35011 ታሕሳስ 7ቀን 2014ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 34909 ህዳር 22ቀን 2014ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጣቸው ትዕዛዞች እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 040732 ሕዳር 6ቀን 2014ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2) አመልካች ከግል ቤታቸው ጋር የተያያዘውን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የቀበሌ ቤት አመልካች ኪራይ እየከፈሉ እንዲኖሩበት መጀመሪያ በአስተዳደሩ ተወስኖ ተሰጥቷቸው በኋላም በፍርድ ቤት ውሣኔ አፈፃፀም የተረከቡትን የመኖሪያ ቤት ከነሐሴ 10ቀን 2011ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ታስቦ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 5/2011 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ተጠሪው ማሸጉ የሁከት ድርጊት በመሆኑ እንዲወገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተወስኗል፡፡
3) ይህ ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

አ/መ　　　　　　　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# ውርስ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 202027

ጥር 23 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

| | | |
|---|---|---|
| አመልካች፡- | ወ/ሮ አስማረች ጀምበሬ | የቀረበ |
| ተጠሪ፡- | አቶ አዕምሮ አወቀ | የለም |

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ መምህር አወቀ ሽፈራው ከሞቱ ከ24 ዓመት በኋላ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት ማግኘቱ፤ ተጠሪ የሟች ልጅ ስላልሆነ ልጅነቱ በደም ምርመራ እንዲረጋገጥ የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ መታለፉ፤ ተጠሪ የጠየቀው ዳኝነት ቤት መካፈል ወይንም የቤቱ ግምት እንዲሰጠው እንጂ ቦታው የጋራ ነው ባላለበት ሁኔታ ሟች በሞቱበት ጊዜ ቦታው ያልተሰጠ ሆኖ እያለ ቦታው የተጠሪ አባት በሕይወት እያሉ የተገኘ ነው ቢባል እንኳን ቤት እና መሬቱን በመነጣጠል አከራካሪው ቤት ከሟች ሞት በኋላ በአመልካች ጥረት መፈራቱ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም ተጠሪ የግንባታ ወጪውን ተጋርቶ ቤቱን ግራ ቀኙ እኩል ይካፈሉ በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የፍትሐ ብሔር ሕጉ እና የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ የሚቃረን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች የካቲት 1 ቀን 2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መዝገቡ ለችሎቱ ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በባህርዳር ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ አመልካች ከሳሽ ፣ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በስር ክሳቸው አመልካች እና ወላጅ አባቴ መምህር አወቀ ሽፈራው በአካባቢው ባህል መሰረት ተጋብተው ሲኖሩ፣ ወላጅ አባቴ ባደረባቸው ህመም ምክንያት የካቲት 12 ቀን 1991 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ሟች አባቴ እና አመልካች በጋራ በትዳር እያሉ በባህርዳር ከተማ መገናኛ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው በአመልካች ስም ገንዘብ ሲቆጥቡ ቆይተው ፣ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 11 ውስጥ በማህበሩ ቦታ ተመርተው ህዳር 4 ቀን

1990 ዓ/ም የማህበር የቦታ ካርታ ተሰርቶላቸው ቦታውንም በአመልካች ስም ተረክበው፣ የካቲት 4 ቀን 1990 ዓ/ም ከቀድሞው የባህር ዳር ልዩ ዞን መስተዳደር ጋር አመልካች ውል ገብተው፣ ሟች እና አመልካች በተመሩት ስፋቱ 250 ካሬ ሜትር በሆነ ቦታ ላይ ግንቦት 1990 ዓ/ም በብሎኬት ቤት ሰርተውበታል፡፡ አባቴ ከመሞቱ በፊት በካርኒ ቁጥር 70210 በ1997 ዓ/ም ለባህርዳር ከተማ ማዘጋጃ ቤት በማህበሩ ስም የከተማ ቦታ ግብር ከፍሎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ በአሁኑ ሰዓት ዕድሜዬ 22 ዓመት ሲሆን ወላጅ አባቴ ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩበት ወቅት አካለመጠን ያልደርስኩ በመሆኑ እና ቤቱም በአመልካች መያዙን ያወቀኩት ጥቅምት ወር 2011 ዓ/ም በመሆኑ መብቱን ሳይጠይቅ መቆየቱን ገልፆ ፤ይህ ግምቱ 6,000,000.00(ስድስት ሚልዮን) የሆነው ቤት የግምቱ ግማሽ እንዲከፈለው ወይንም በሕጉ ላይ በተመለከተው የክፍፍል ሥርዓት ድርሻው እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡

አመልካች በመልሳቸው ሟች አቶ አወቀ ሽፈራው የአመልካች ባለቤት መሆኑ እና በ1991 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ መሆኑን አምነው ፣ ተጠሪ የሟች ልጅ አለመሆኑን ፣ የሟች ልጅ ታምራት አወቀ መሆኑ በፍርድ መረጋገጡን፣ የሟች ልጅ ነው ቢባል እንኳን ሟች ከሞቱ ከ21 ዓመት በኋላ ያቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ፣ ሟች ከሞቱ በኋላ በጋራ ለማህበሩ የከፈሉትን 5,000.00 (አምስት ሺ) ብር ግማሹን 2,500.00 (ሁለት ሺ አምስት መቶ) ብር እና የቤት ቁሳቁስ ግማሹን ለሟች ልጅ ታምራት አወቀ በሞግዚቱ አማካኝነት የተሰጠ በመሆኑ የቀረ የጋራ ንብረት አለመኖሩን፣ ክስ የቀረበበትን ቤት ሟች ከሞቱ አንድ ዓመት በኋላ በግል ገንዘባቸው በሀምሌ ወር 1992 ዓ/ም የቤቱን መሰረት አውጥተው፣ ጥቅምት ወር 1993 ዓ/ም ግንባታ ጀምረው፣ ታህሳስ ወር 1993 ዓ/ም 40 ቆርቆሮ ገዝቶ በማልበስ፣ መጋቢት ወር 1993 ዓ/ም የላሜራ በር አስገጥሞ ገብቶበት በ1997 ዓ/ም የቤቱን ግድግዳ ሊሾ አድርጎ፣ ህዳር 18 ቀን 2000 ዓ/ም ካርታ አሰርተው መረከባቸውን ፣ ከ2005-2008 ዓ/ም ባለው ጊዜ ከራሳቸው እና በብድር በተገኘ ገንዘብ አጥር አጥረው እና ተጨማሪ ክፍሎች፣ የውሃ ታንከር እና ሻወር ሰርተው ግብሩም ሟች ከሞቱ ከስድት ዓመት በኋላ የተከፈለው በአመልካች ስም ስለሆነ ሟች ያልሰራው እና ግብር ያልከፈለበት ቤት እና ቦታ በትዳር ውስጥ የተፈራ ነው ሊባል ስለማይገባ ክሱ ውድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ሊጣሩ ይገባቸዋል ያላቸውን ጭብጦች በመለየት የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ሰምቶ እና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳው ዘንድ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም እንዲጣራ አድርጎ መዝገቡን እንደመረመረው በአመልካች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ወድቅ አድርጎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት እና ቦታ የሟች እና የአመልካች መሆኑ በምስክሮች እና በሰነድ ማስረጃ ስለተረጋገጠ አመልካች የሟች ድርሻ የሟች ሕጋዊ ወራሽ ለሆነው ተጠሪ ልታካፍል ይገባል በማለት በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በይግባኝ ለማሳረም ለአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪም ክርክሩን ያቀረበው በጠበቃ ሆኖ እያለ ይቻቻሉ መባሉን በመቃወም ይግባኝ አቅርቦ ፤ ፍርድ ቤቱም ሁለቱንም መዝገቦች በማጣመር እንደመረመረው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተሰራበት ቦታ በ1990 ዓ/ም ተመርተው ፕላኑ በ1991 ዓ/ም ተሰጥቶ ግንባታው

ከሟች ሞት በኋላ የተሰራ መሆኑን የአመልካች ምስክሮች ያስረዱ ሲሆን፤ የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት እምነት የሚጣልበት ባለመሆኑ የተጠሪ አባት የጉልበትም ሆነ የገንዘብ አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑ ሳይረጋገጥ ለክርክሩ መነሻ የሆነ ቤት የሟች እና የአመልካች የጋራ ሀብት ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃን ያገናዘበ አይደለም በማለት የባህርዳር እና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር፤ አከራካሪው ቤት በአመልካች ጉልበት እና ገንዘብ የተሰራ መሆኑ ስለተረጋገጠ የሟቹ አስተዋጽኦ የሌለበትን ቤት ተጠሪ ሊካፈል አይገባም በማለት በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡ የልዩነት ሃሰቡም ለክርከሩ መነሻ የሆነው ቤት የተሰራው ሟች እና አመልካች በጋራ ተደራጅተው ባገኙት ቦታ ላይ መሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ፤ ተጠሪ ቦታውን የመውረስ መብት ያለው በመሆኑ ቤቱን ለመስራት የወጣውን ወጪ በድርሻው እንዲተካ ማድረግ ሲገባ በቦታው ላይ ያለውን የውርስ ድርሻ ጠቅላላ አመልካች እንድትወርሰ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ ተጠሪው በውሳኔው ባለመስማማት ባቀረቡት አቤቱታ ጉዳዩን ያየው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎትም፡- በስር ፍርድ ቤት የተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች የክርክሩን ቦታ አመልካች እና ሟች በጋራ የተመሩት መሆናቸውን ያረጋገጡ ሲሆን አመልካችም በሰጠችው የምስክርነት ቃል ቦታው ለማህበሩ የተሰጠው በ1990 ዓ/ም አመልካች እና ሟች ባልና ሚስት በነበሩበት ጊዜ መሆኑን ያረጋገጠች ሆኖ መምህር አወቀ ሽፈራው የሞቱትም ቦታው ለማህበሩ ከተሰጠ በ1991 በኋላ ዓ/ም በመሆኑ፤ ቦታው ሟች እና አመልካች በባልና ሚስትነት እያሉ የተሰጠ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ ሟች በባዶ ቦታው ላይ ያለው የባለ ይዞታነት መብት ወራሹ እና ልጁ ለሆነው ተጠሪ የሚተላለፍ ሆኖ እያለ አመልካች ቤቱን በግል ገንዘቧ ሰርታለች በማለት ተጠሪ በባዶ ቦታው ላይ ያለውን መብት እንዲያገኝ ማድረግ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ፤ ቦታው እና ቤቱ እኩል ለሁለት ተከፍሎ ግራቀኙ እኩል የሚካፈሉት ሆኖ ለተጠሪ በሚደርሰው ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ለመስራት የዋለው የቤቱ ወጪ ግምት በባለሞያ ተጠንቶ ተጠሪ ለአመልካች እንዲተካ በማድረግ፤ ይህ ካልተቻለ አጠቃላይ በቦታው ላይ የተሰራውን ቤት ለመስራት የወጣው ወጪ በባለሞያ ተጠንቶ ፤ የወጪውን ግምት ግማሽ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍላት ተደርጎ ቤት እና ቦታውን እኩል እንዲካፈሉ በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት አመልካች ያቀረቡትን በፍርዱ መግቢያ ላይ የተገለፀውን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተሰራበትን መሬት አመልካች የቤት ሥራ ማህበሩ የተረከበው እና አመልካችም በመሬቱ ላይ ቤት የሰራች መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያስረዳ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔን በመሻር ቦታው ለሁለት ተከፍሎ ለተጠሪ በሚደርሰው ቦታ ላይ ያለውን ቤት ለመስራት የወጣ ወጪ በባለሙያ ተገምቶ ለአመልካች እንዲከፈል በሚል የወሰነበትን አግባብነት በሰበር መዝገብ ቁጥር 55081 ላይ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ለሰበር ይቅረብ በማለቱ ተጠሪ

ተከታዩን መልስ ሰጥቷል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተሰራበትን ቦታ ሟች እና አመልካች በባልና ሚስትነት በማህበር ተደራጅተው በአመልካች ስም የተመሩት እንጂ አመልካች በስሟ ብቻዋን ያገኘችው አለመሆኑ አመልካች እና ሟች ቦታውን ለመቀበል ከባህርዳር ከተማ ልዩ ዞን አስተዳደር ጋር የካቲት 4 ቀን 1990 ዓ/ም ውል የያዙ መሆኑን ቦታውን ለመቀበል ከባህዳር ልዩ ዞን መስተዳድር ጋር የተደረገ ውል፣ የማሕበሩ ካርታ ፣ የባህርዳር ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ፣ የቦታ ምርት ካርኒ እንዲሁም በሥር ፍርድ ቤት የተሰሙት የሰው ምስክር ያረጋገጡትን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ እያለ አመልካች ቦታውን በግሏ ከሟች ሞት በኋላ እንደተመራችው ሁኖ የቀረበው ቅሬታ እና የተያዘው ጭብጥ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፤ የስር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት አከራካሪውን ቤት አመልካች በግል ገንዘቧ ሰርታለች በማለት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመቃወም በመዝገብ ቁጥር 203279 ላይ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሰበር አቤቱታ አቅርቦ በቀጠሮ ላይ መሆኑን ገልፆ ፤ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ አግባብ ነው ቢባል እንኳን ቦታው በምሪት የተገኘው ሟች በሕይወት እያለ በመሆኑ ተጠሪ የግንባታ ወጪውን ሸፍኖ በቤቱ ላይ እኩል ባለመብት እንዲሆን የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆኑን፤ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች ልጅ አይደለም በሚል ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም የሟች ልጅ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በአመልካች ባለመስተባበሉ እንዲሁም ይርጋን በተመለከተም ተጠሪ አካለመጠን ካደረሰ በኋላ የሟች አባቱ ንብረት በአመልካች መያዙን አውቆ ክስ እስከመሰረተበት ያለው ጊዜ ሲሰላ ያቀረበው ክስ በይርጋ የማይታገድ መሆኑ ተረጋግጦ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የስር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ዋናውን አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን የሥር ፍርድ ለቤት መሥሪያ የተሰጠውን የከተማ ይዞታ እና በይዞታው ላይ የተሰራውን ቤት በመለያየት አመልካች በግል ጥረታቸው ያፈሩት ቤት ቤቱ ያለበትን ይዞታ አይጨምርም በማለት የሰጡት ውሳኔ ህጉን ያገናዘበ መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው ተመርመሯል፡፡ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ሟች እና አመልካች በጋራ ያፈሩት በመሆኑ የሟች ድርሻ በውርስ እንዲተላለፍለት ላቀረበው ክስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በማስቀደም በፍሬ ነገር መልሳቸው አከራካሪውን ቤት ከሟች ሞት በኋላ በግል ጥረታቸው ያፈሩት በመሆኑን ተከራክረዋል፡፡ በአመልካች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ አጣርቶ የደረሰበት የፍሬ ነገር መደምደሚያን ችሎቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ አከራካሪው ቤት የተሰራበት ይዞታን አመልካች እና ሟች በጋራ የተመሩት መሆኑ እና ቤቱ ከሟች ሞት በኋላ አመልካች የሰሩት መሆኑ ማስረጃን የመመዘን እና የመመርመር ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን፤ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት

አመልካች በግል ገንዘቧ ሰርታለች በማለት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመቃወም በመዝገብ ቁጥር 203279 ላይ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም። አመልካች እና ሟች በጋራ የተመሩት ቦታ የከተማ ይዞታ ሆኖ ቦታው የተሰጠው የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ነው። አመልካች እና ሟች በጋራ ቤት ለመሥራት ቦታውን ቢወስዱም ፤ መምህር አወቀ ሽፈራው ስለሞቱ አመልካች በቦታው ላይ በገነቡት ቤት ላይ በሕገ መንግስቱ 40(7) ድንጋጌ መሰረት ሙሉ መብት ያላቸው ሲሆን ይህ የባለሀብትነት መብትም የሚገደበው በህግ በተመለከተው አግባብ ብቻ መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1204 ድንጋጌ ያመለክታል። አመልካች በቤቱ ላይ ያላቸው የባለሀብትነት መብት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1131 ድንጋጌ መሰረት በይዞታውም ላይ የሚዘረጋ ሲሆን ፤ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1132 ድንጋጌ ላይ እንደተመለከተው ቤቱ የመሬቱ አንድ አቋም ተደርጎ ስለሚቆጠር አመልካች በቤቱ ላይ ያላቸው ባለሀብትነት መሬቱንም የሚጨምር ሆኖ እያለ ፤ አመልካች እና ሟች አከራካሪው ቤት የተሰራበትን የከተማ ይዞታ አብረው ስለተመሩ ብቻ በአመልካች ጥረት የተፈራውን ቤት ሟቹ ያልነበረውን መብት ተጠሪ እንዲወርስ የተሰጠው ውሳኔ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 826(2) የሚፃረር በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል።

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03 - 96106 ታህሳስ 13 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርደ እና ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 51857 የካቲት 4 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል።
3. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸዉን ይቻሉ።'
4. በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው ዕግድ ተነስቷል።

**መዝገቡ ዉሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 216298

ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ አስቴር ለማ
2. ተማሪ አቤል ስዩም
3. አቶ ዳንኤል ስዩም

} ጠበቃ ሙሉጌታ ታደሰ - ቀርቧል

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ሜሮን ስዩም
2. ወ/ሮ ሀናን ስዩም

} ጠበቃ ሳባ እሸቱ

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ተጠሪዎች ሟች ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፈርስ የጠየቁት የሥር ፍርድ ቤት እንዳለው በንብረቶቹ ላይ ጉዳት ይደርሳል በሚል ሳይሆን በመንፈስ መጫን የተደረገ ነው በሚል በመሆኑ ኑዛዜው የተደረገው በመንፈስ መጫን ነው ወይስ አይደለም ከሚለው መከራከሪያ አንፃር መታየት ሲገባው በተከራካሪዎች ያልተነሳን መከሪከሪያ ለውሳኔ መሠረት መደረጉ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 182(2) ድንጋጌን የሚጥስ መሆኑን ፣ ኑዛዜው በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሆኖ በንብረቱ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ከተባለም የኑዛዜው ተጠቃሚዎች ዋስትና እንዲጠሩ ማድረግ ሲገባ ኑዛዜው ፈራሽ መባሉ ፣ ኑዛዜው የተደረገው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በመሆኑ ሟች ኑዛዜውን ሲያደርጉ ከተጽኖ ነፃ እንደነበሩ የሚገመት ሆኖ ኑዛዜው በመንፈስ መጫን የተደረገ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ ሲገባው ኑዛዜው በመንፈስ መጫን የተደረገ ነው በማለት ድምዳሜ ላይ መደረሱ ፣ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው በኑዛዜው 200 ካ.ሜ የቤት መሥሪያ ቦታ ስላገኙ ከውርስ ያልተነቀሉ ሲሆን ኑዛዜው ከሩብ በላይ ጉዳት ስላደረሰብን ከውርስ ነቅሎናል በማለት ያቀረቡት ክርክር ሳይኖርና ውርሱ ተጣርቶ ከሩብ በላይ ጉዳት ያደረሰባቸው መሆኑ ሳይጣራ ከሩብ በላይ ጉዳት ያደረሰባቸው በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሸሮ ሟች አቶ ስዩም ለማ ግንቦት 4

ቀን 2012 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ሊፃና ይገባል ተብሎ እንዲወሰን አመልካቾች ህዳር 8 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ጉዳዩ ኑዛዜ እንዲሰረዝ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በከሳሽነት አመልካቾች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ተጠሪዎች ከሟች አቶ ስዩም ለማ የቀድሞ ሚስት የሚወለዱ ልጆች እና የሟች ወራሾች መሆናቸውን ገልፀው ሟች ግንቦት 4 ቀን 2012 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ቁጥሩ 590 የሆነውን ቤትና የቤት ቁሳቁስ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች እንዲጠቀሙበትና እነሱ በሕይወት እስካሉ ድረስ ተጠሪዎች እንዳይጠይቁ በማለት ያደረጉት ኑዛዜ በመንፈስ መጫን የተደረገ ፣ የተጠሪዎችን በውርስ ሀብቱ የመጠቀም መብታቸውን የጣሰ ለሕግ ተቃራኒ የሆነና በዝምታ ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው መሆኑን ፣ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-33759 አ.አ የሆነውን ተሽከርካሪ የኑዛዜው ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ያልተገለፀ በመሆኑና በኦሮሚያ ክልል አስጎሪ አካባቢ የሚገኘው 1600 ካ.ሜ ቦታ ለተጠሪዎች ሰጥቻለሁኝ የሚለው የኑዛዜው ክፍልም ሊፈፀም የሚችል ባለመሆኑ ሟች ግንቦት 4 ቀን 2012 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም ለክሱ በሰጡት መልስ፡- ተጠሪዎች በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው ይዞታ ተሰጥቷቸው እያለ ተነቅለናል ማለታቸው ተገቢ አለመሆኑንና የድርሻ ማነስ ከሆነ በክፍፍል ጊዜ የሚታይ መሆኑን ፤ ማስታመምና መንከባከብ ኑዛዜ ለማድረግ የሚያነሳሱ ምክንያቶች እንጂ የመንፈስ መጫን መኖሩን የሚያሳዩ አለመሆናቸውንና ለሕግ ተቃራኒ አለመሆኑን ፣ ገደብ ያለበት ኑዛዜ ማድረግን ሕጉ ስለሚፈቅድ ኑዛዜው ተጠሪዎችን መብት ያሳጣ አለመሆኑንና የተሽከርካሪው ተጠቃሚም በኑዛዜው መገለፁን ፣ የባሌበትነት መብትም መተላለፉንና ለአፈጻጸምም አስቸጋሪ ባለመሆኑ ኑዛዜው የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ተብሎ የተጠሪዎች ክስ ወድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ ይዞ መዝገቡ እንደመረመረው፡- ቤቱንም ሆነ ቁሳቁሱን አመልካቾች በሕይወት እስካሉ ድረስ ይጠቀሙ የሚለው የኑዛዜው ክፍል ሲታይ ቁሳቁሱ በመገልገል የተነሳ ከአገልግሎት ውጪ የሚሆንበት ሁኔታን ስለሚፈጠር ወራሾች በውርስ መብት እንዳይሰሩበት የመከልከል ውጤት ያለው ሲሆን የእርጅና እና የለውጥ ወጪም ለሌላ አከራካሪ ሁኔታ የሚዳርግ ሆኖ ሟች የሰፋ መብት ለአመልካቾች መስጠታቸው በመንፈስ መጫን የተደረገ የሌሎች ወራሾችን መብት የሚጎዳ ሲሆን ፣ ተሽከርካሪውንም የኑዛዜው ተጠቃሚ እስከመቼ እንደሚጠቀም ስላልተገለፀ ወራሾችን በውጤቱ ከውርስ የነቀለ እና ይዞታውም በወራሾች የድርሻ መጠን ላይ መብታቸውን የሚጎዳ ሆኖ ስለተገኘ ኑዛዜው ሊፍርስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረቡት ይግባኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረዙ በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልከቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ኑዛዜው የተደረገው በመንፈስ መጫን ነው የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካቾች በንብረቱ ሲጠቀሙ ቢጎዳ ለጥገና ቢያወጡ

ለሌላ ክርክር የሚጋብዝ ነው በሚል ኑዛዜው ይፍረስ ብሎ የመወሰኑን አግባብነት መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ፡- የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተጠሪዎች ኑዛዜው ፈራሽ የሚሆንበትን በርካታ ምክንያቶች በመጥቀስ ያቀረቡትን ክርክር መሠረት ያደረገ መሆኑን ፣ ውሳኔው መሠረት ያደረገው የመንፈስ መጫንን ሆኖ የመንፈስ መጫን መኖሩ የሰፋ መብት ለአመልካቾች መሰጠቱ በኑዛዜው ሰነድ ተረጋግጦ እና ውጤቱም ከውርስ መንቀል መሆኑ ተጣርቶ መወሰኑ አግባብ መሆኑን ፣ ንብረቱን አመልካቾች እየተጠቀሙ በሄዱ ቁጥር በተጠሪዎች የንብረት መብት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ለክርክር የሚጋብዝ በመሆኑ ውሳኔው በተከራካሪዎች ያልተነሳ ክርክርን መሠረት ያደረገ ነው የሚያስብል አለመሆኑን ፣ በኑዛዜው የተሸከርካሪው ተጠቃሚ ሌላ ሰው ሆኖ እያለ አመልካቾች ከተሸከርካሪው አንፃር ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ክርክሩ ተቀባይነት አለው ቢባል እንኳን 200 ካ.ሜ ይዞታ የተባለው በየትኛውም አቅጣጫ መንገድ የሌለው ፣ በኑዛዜው መሠረት ለመካፈል የከተማ አስተዳደሩ ፕላን የሚፈቅድ መሆኑ ባልተረጋገጠበት እና ባዶ መሬት ከጠቅላላው የውርስ ንብረት አንፃር ከሩብ በታች ሆኖእያለ ኑዛዜው መፍረስ የለበትም መባሉ አግባብ አለመሆኑንና ከወርስ መንቀል የተባለውም ከውርስ ሃብቱ ከሩብ በታች ድርሻ ደርሶናል የሚለውን መከራከሪያ የያዘ መሆኑንና በተጠሪዎች እጅ የገባ ንብረት አለመኖሩ በዝምታ ከውርስ መንቀል በመሆኑና ኑዛዜው በመንፈስ መጫን መደረጉ የተጠሪዎችን መብት የሚጎዳ በመሆኑ ኑዛዜው እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር ቅሬታቸውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ መዝገቡ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ኑዛዜ በነፃ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡ የኑዛዜ ተጠቃሚ ወይንም ማንኛውም ሰው በተናዛዡ ላይ ባለው ከመጠን ያለፈ መንፈስ መጫን በመርህ ደረጃ ኑዛዜ ሊፈርስ እንዳማይችል የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 868 የሚያመለክት ሲሆን ፤ በቁጥር 869 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በሕጉ ውስጥ ለተዘረዘሩት ሰዎች የተደረገውን ኑዛዜ በህጉ የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቶ ሲገኝ ዳኞች ሊቀንሱ ወይንም ሊሽሩ ይችላሉ፡፡ ሟች በፊት ካደረገው ጋብቻ የተገኙ ልጆች ያሉት እንደሆነ ለኋለኛው ባል ወይንም ሚስት ጥቅም የተደረገ ኑዛዜን ለመቀነስ ወይንም ለመሻር እንደሚችሉ ፣ በዚህ አግባብ የተደረገን ኑዛዜ እንዲቀነስ ወይንም እንዲሻር መጠየቅ የሚችሉት የሟች ተወላጆች መሆናቸውና በህጉ የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቶ በተገኘ ጊዜ ኑዛዜ ለማፍረስ ወይንም ለመቀነስ ዳኞች ምክንያት ማስቀመጥ እንዳለባቸው ከቁጥር 872 , 874 እና 875 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ከወራሽነት የመንቀል አይነቶች በግልፅ ፣ በዝምታና በተዘዋዋሪ ሊሆን

እንደሚችል እንደዚሁም ከውርስ ሊነቀሉ የሚችሉ እና የማይችሉ ሰዎች ፣ ከውርስ መንቀል የሚቻልበት የህግ አግባብ ከፍትሐ ብሔር ሕጉ 937 — 940 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ሟች አቶ ስዩም ለማ ግንቦት 4 ቀን 2012 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በመንፈስ መጫን የተደረገና ከሟቹ የቀድሞ ሚስት የሚወለዱ ተጠሪዎችን በዝምታ ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለት ተጠሪዎች ላቀረቡት ክስ አመልካቾችም በመልሳቸው ተጠሪዎች በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው ይዞታ ተሰጥቷቸው እያለ ተነቅለናል ማለታቸው ተገቢ አለመሆኑንና የድርሻ ማነስ ከውርስ አለመነቀል መሆኑንና ማስታመምና መንከባከብ ኑዛዜ ለማድረግ የሚያነሳሱ ምንክያቶች እንጂ የመንፈስ መጫን መኖሩን ስለማያሳይ ኑዛዜው የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ግራቀኙ ክርክራችንን ያስረዳልናል ያሉትን የሰው ምስክር የቆጠሩ ሲሆን የሰነድ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን በጭብጥነት የያዘ ቢሆንም ተጠሪዎች ኑዛዜው በመንፈስ መጫን የተደረገ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክርክር አመልካች የመንፈስ መጫን የለም በማለት ክዶ ተከራካሮ እያለ ኑዛዜው የተደረገው በመንፈስ መጫን መሆን አለመሆኑን እንዲሁም የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ ተጠሪዎች ከውርስ መነቀል አለመነቀላቸውን ሳያጣራ ግራቀኙን ባላከራከረ ጉዳይ አመልካቾች የውርስ ሀብቱን በተገለገሉ ቁጥር በእርጅና እና የለውጥ ወጪ ወደፊት ሊያከራክር ይችላል የሚል ምክንያንት ለኑዛዜው ማፍረሻነት መጠቀሙ ተገቢነት የለውም፡፡ ተናዛዡ የኑዛዜ ተጠቃሚዎች እንዳያበላልጥ በህግ የተቀመጠ ክልከላ ሳይኖር ሟች የሰፋ መብት ለአመልካቾች መስጠታቸው ኑዛዜው በመንፈስ መጫን የተደረገ የሌሎች ወራሾችን መብት የጎዳ ማለቱ እንዲሁም ውርሱ ተጣርቶ የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻው ሳይታወቅ በውጤቱ ወራሾችን ከውርስ የነቀለ በመሆኑ ሊፍርስ ይገባል ማለቱም የህግ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ሟች አቶ ስዩም ለማ ግንቦት 4 ቀን 2012 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በመንፈስ መጫን የተደረገ ተጠሪዎች ከውርስ የነቀለ መሆኑን አለመሆኑ ተጣርቶ ፤ በመንፈስ መጫን የተደረገና ተጠሪዎችን ከውርስ የነቀለ ከሆነ ውጤቱ ምን መሆን አለበት የሚለው በጭብጥነት ተይዞ ተገቢ በሆነ መንገድ ተጣርቶ ውሳኔ አለመስጠቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 246, 247 ,249 ,257 እና 264 ድንጋጌዎች የሚጥስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 270611 ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 81125 መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት **ተሽሯል**፡፡

2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 81125 በማንቀሳቀስ በፍርድ ሀተታው ውስጥ በተገለፀው መሠረት ሟች አቶ ስዩም ለማ ግንቦት 4 ቀን 2012 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በመንፈስ መጫን የተደረገ መሆን አለመሆኑ እንዲሁም ተጠሪዎችን ከውርስ መንቀል አለመንቀሉ ፤ በመንፈስ መጫን የተደረገ ከሆነ ወይንም ተጠሪዎችን ከውርስ የነቀለ ከሆነ ውጤቱ ምን መሆን አለበት የሚለውንና ተያያዥ ጭብጦችን ተገቢ ነው በሚለው መንገድ አጣርቶ እንዲወስን መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ላይ ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡
4. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ.ቁ.199901

መስከረም 27/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ዘውዴ እረዳ

2ኛ. ወ/ሮ ጥሩወይ በላይ እረዳ

3ኛ. አቶ ጌታሁን ተረፈ እረዳ

4ኛ. ወ/ሮ እመቤት አማረ እረዳ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሹምነሽ ስዩም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን አመልካቾች በሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ጥቅምት 14/2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ ከአያታቸው ቄስ ረዳ ተክለሃይማኖት በውርስ የተላለፈላቸውን ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን በ245.8 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ አንድ ህድሞ ክብ ቤት የአሁን ተጠሪ ከነበረባቸው የቤት ችግር በመነሳት እንዲኖሩበት ፈቅደዉላቸው በኋላም በቤቱ ላይ በ2007 ዓ.ም በወራሾች ስም ካርታ አስወጥተው ለመከፋፈል ተጠሪ እንዲለቁላቸው ሲጠይቋቸው ያለምንም መብትና ጥቅም አለቅም ብለው ይዘው የሚገኙ መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ ጥቅምት 23/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ መቃወሚያውም ሁለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ቄስ ረዳ ተ/ሓይማት ከሞቱ በኋላ 1ኛ አመልካች፣ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት አመልካቾች ወላጆች እና ወላጅ እናቴ ወ/ሮ ውዴ ረዳን ጨምሮ በሰባት ወራሾች መካከል

የውርስ ሀብት ክፍፍል ተደርጓል፤ በክፍፍሉም ወላጅ እናቴ ቀድሞኑም ከአባቸው ቄስ ረዳ ጋር ክስ በቀረበበት ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን አባታቸውን ጦረው፣ ሲታመሙም አስታመው፤ ከሞቱ በኋላ ደግሞ አስፈላጊውን ሃይማኖታዊ ስርዓት ሁሉ የፈፀሙላቸው መሆኑ ከግንዛቤ ገብቶ አሁን ክስ የቀረበበት ቤት ለእናቴ በክፍፍል እንዲደርስ እና ቀሪውን ንብረት ሌሎች ወራሾች እንዲካፈሉት በአስማሚ ሽማግሌዎች ፊት ስምምነት ፈፅመዋል፤ በስምምነቱ መሰረት ወላጅ እናቴ ክስ የቀረበበትን ቤት ለ25 ዓመታት ኖረውበት እርሳቸው ከሞቱ በኋላም በውርስ ተላልፎልኝ ለ7 ዓመታት ስጠቀምበት የነበረ ነው፤ በመሆኑም ክሱ በወራሾች መካከል በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የውርስ ሀብት ክፍፍል ከተደረገ ከሶስት ዓመት በኋላ ክስ/መቃወሚያ ሊቀርብበት የማይችል በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ በአማራጭ የስረ ነገር ክርክር ደግሞ ክስ የቀረበበት ንብረት ከእናቴ በውርስ የተላለፈልኝ ሆኖ እያለ አመልካቾች በመመሳጠር ሆን ብለው የተጠሪን የውርስ ሃብት አካተው ካርታ ያወጡበት በመሆኑ ልለቅ አይገባም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክሱ የቀረበው በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ ነው? ወይስ አይደለም? በሚል ጭብጥ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ሰምቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የውርስ ክፍፍል ስምምነቱን መርተዋል የተባሉት ሽማግሌዎች መሆናቸውን፤ በሰጡት ቃልም የግራ ቀኙ አያት በሞቱ ጊዜ የግራ ቀኙን ወላጆች ጨምሮ በሰባት ወራሾች መካከል በስምምነት የውርስ ሀብት ክፍፍል ያደረጉ መሆኑን፤ በስምምነቱ መሰረትም አሁን ክስ የቀረበበትን ቤት ለአሁን ተጠሪ ወላጅ እናት እንዲደርስ እና የተቀረውን የውርስ ሀብት ሌሎች ወራሾች ለመካፈል ተስማምተው በዚሁ መሰረት ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ ስለመሆኑ ሲመሰክሩ በአመልካቾች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ደግሞ ክፍፍል መደረጉን አናውቅም በማለት የተናገሩ ስለመሆኑ መዝግቦ በሰጠው ብይን “የክፍፍል ስምምነቱ በቃል የተደረገ ቢሆንም በግራ ቀኙ ወላጆች መካከል የውርስ ሀብት ክፍፍል ስምምነት የተደረገ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ የውርስ ሀብት ክፍፍልን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ ፎርማሊቲ የለም፤ ክሱም በስምምነት በተጠናቀቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው” በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህንኑ ብይን በይግባኝ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ስምምነቱ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ ሲሆን የፍ/ብ/ህ/ቁ/1567፣ 1568 እና 1723 በሚደነግገው መሰረት በፅሁፍ የቀረበ ስምምነት ባለመኖሩ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ በይርጋ መቃወሚያው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ እንዲወስን፤ ክሱ በይርጋ የማይታገድ ከሆነ በክሱ ስረ ነገር ክርክር ላይ አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን በነጥብ መልሷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በተራቸው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ለውርስ ሀብት ክፍፍል ስምምነት በህግ ተለይቶ የተቀመጠ ልዩ ፎርማሊት የለም፤ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠቀሱት

የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1567፣ 1568 እና 1723 የውል ጉዳይን እንጂ የውርስ ጉዳይን የሚመለከቱ ባለመሆናቸው ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም በማለት የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ብይን አፅንቷል፡፡ ይኸው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ህዳር 30/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም አመልካቾች የሟቹ ወራሽ ስለመሆናችን የወራሽነት ማረጋገጫ በማውጣት እነ ቄስ ተረፈ እረዳ በሚል በ2007 ዓ.ም በስማቸው በማዞር ካርታ አሰርተው እስከ 2012 ዓ.ም ግብር እየገበሩ በጋራ የያዙት እና ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ስለመሆኑ የሰነድና የሰው ማስረጃ አቅርበው አሰምተው እያለ በአግባቡ ሳይታይ የወረዳው ፍ/ቤት በብይን መዝጋቱ ትክክል ነው በሚል መወሰናቸው አግባብ አይደለም፤ ተጠሪ ቤት ስለሌላቸው ቤቱን እየጠበቁ እንዲኖሩበት የተደረገ እንጅ ከቤቱ ላይ መብት የላቸውም፤ ተደረገ የተባለው ስምምነትም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ ሲሆን ስምምነቱን የሚገልፅ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፤ ይህ በሌለበት ወንድም እና የአባታቸውን ወገን አቅርበው ስምምነት ነበር በመባሉ ብቻ ጉዳዩ በስምምነት ያለቀ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ምክንያት ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚሁ አግባብ ተጠሪ መጋቢት 22/2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ፍሬ ነገሩን በማንኛውም የማስረጃ አይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/47551 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፤ የውርስ ሀብት ክፍፍል ስርዓትን አስመልክቶ በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት ብቻ ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1079 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር ከመገለፁ ውጭ ክፍፍሉ ሊፈፀም ስለሚገባበት የተለየ ፎርማሊቲ አልተመለከተም፤ የአያታችን የውርስ ሀብት ክፍፍል አስመልክቶ ወላጆቻችን በራሳቸው በመረጧቸው ሽማግሌዎች ስምምነት ተደርጎበት ክስ የቀረበበት ንብረት ለወላጅ እናቴ ስለመድረሱ የወረዳው ፍርድ ቤት በማስረጃ አረጋግጦ ወስኗል፤ ስለ ውርስ ሀብት ክፍፍል በህግ ተለይቶ የተመለከተ ፎርማሊቲ በሌለበት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን እና ስለ የማይንቀሳቀስ ሀብት ርስት ምዝገባ የተመለከቱትን የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1567 እና 1568 ድንጋጌዎችን ጠቅሶ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ አግባብ ባለመሆኑ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ተረድተው በማረማቸው የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፤ አመልካቾች ክስ ያቀረቡት የውርስ ሀብት ክፍፍሉ ከተደረገ ሶስት ዓመት በኋላ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1106 መሰረት ከመነሻው በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው

ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በመስጠት ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክስ በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በሚል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ አመጣጥ መረዳት እንደሚቻለው የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ በወራሾች መካከል የውርስ ሀብት ክፍፍል ስምምነት ሊፈፀም የሚገባበትን ፎርማሊትን አስመልክቶ ነው፡፡ በመሰረቱ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት፣ በወራሾቹ መካከል ስምምነት ከሌለ ደግሞ ከእነርሱ መካከል አንዱ ተግቶ ያሰናዳውን የክፍያ ሐሳብ ለዳኞች አቅርቦ በማፀደቅ ሊከናወን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1079 ይደነግጋል፡፡ በእርግጥ ህጉ የውርስ ሀብት ክፍፍል በዚህ መልኩ ሊከናወን እንደሚችል ከመደንገጉ ውጭ በወራሾች መካከል የሚደረገው የክፍፍል ስምምነት ሊፈፀም ስለሚኖርበት ፎርማሊቲ በግልፅ አላስቀመጠም፡፡ እናም ስለክፍፍሉ የተለየ ፎርም አለመቀመጡ የስምምነቱ ፎርም አፈፃፀም ለወራሾች የተተወ ነፃነት ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ የሚደረገው ስምምነት በተስማሚዎቹ መካከል መብትና ግዴታን የሚፈጥር ውል እንደመሆኑ መጠን የስምምነቱ ፎርማሊቲ ስምምነት ከሚደረግበት ንብረት ዓይነት እና ባህሪ አኳያ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

በዚሁ አግባብ በፍትሐብሔር ህጉ አምስተኛ መፅሓፍ ውስጥ ስለልዩ ውሎች የተደነገገው ልዩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ የሚመነጭ ማናቸውም ስምምነት በፍትሐብሔር ህጉ አራተኛ መፀሀፍ ውስጥ ስለውሎች በጠቅላላው በተደነገገው መርህ መሰረት የሚመራ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1677 ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ ስለውሎች በጠቅላላው ከሚደነግገው የህጉ ክፍል ውስጥ ከተመለከቱት መሰረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ በቁጥር 1719 ስር የውል ፎርማሊቲን አስመልክቶ የተቀመጠው መርህ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በህግ በልዩ ሁኔታ የውል ፎርም ካልተመለከተ በቀር ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በተስማሙበት አኳኋን ሊፈፅሙ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡ የተዋዋይ ወገኖች የስምምነታቸውን ፎርማሊት የመወሰን ነፃነት ከሚገደብበት ልዩ ሁኔታ ወይም በስተቀር ውስጥ አንዱ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ስምምነትን አስመልክቶ ስለመሆኑ በቁጥር 1723 ስር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ አግባብ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስምልክቶ የሚደረግ የክፍፍል ወይም የማዛወር ስምምነቶች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት መደረግ እንደሚገባው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1723(2) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስምልክቶ የሚደረግ ስምምነት በዚህ አይነቱ ጥብቅ የአፈፃፀም ስርዓት መሰረት እንዲመራ የተፈለገበት የራሱ ህጋዊ እና አስተዳደራዊ ምክንያት እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ከህግ አኳያ ንብረቱ በተፈጥሮው ዘለቄታዊ ባህሪ ያለው በመሆኑ ምክንያት በእንደዚህ ዓይነት ንብረት ላይ የሚፈጠር ማናቸውም መብት የሶስተኛ ወገኖችን መብት እንዳይጎዳ ተገቢውን ቁጥጥር እና ጥንቃቄ ለማድረግ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ከአስተዳደር አንፃር ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም የማይንቀሳቀስ ንብረት በህግ አግባብ በተቋቋመ መንግስታዊ አስተዳደር ክፍል ዘንድ መመዝገብ ያለበት እና በንብረቱ ላይ የሚደረግ ማናቸውም የመብት መለዋወጥ መረጃዎች ሁሉ በሰነድ መደራጀት ያለበት ስለመሆኑ ስለ የማይነቀሳቀስ ንብረት መዝገብ በሚደነግገው የፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀፅ 10 ከቁጥር 1553 ጀምሮ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በእርግጥ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀፅ 10 ስራ ላይ የሚውልበት ቀን በነጋሪት ጋዜጣ እስኪታወጅ ድረስ ተፈፃሚ እንደማይሆን በፍ/ብ/ህ/ቁር 3363(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ እስከሚሆን ድረስም በምትኩ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 3364 - 3367 ድረስ የተመለከቱት ልማዳዊ ደንቦች ተግባራዊ የሚደረጉ ስመሆኑ በቁጥር 3363(2) ስር ተመልክቷል፡፡ በጊዜ ሂደትም መሬትን እና ሌሎች የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ምዝገባ እና አስተዳደር የሚመለከቱ የአስተዳደር መዋቅሮች በህግ እንዲቋቋሙ ተደርጎ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ስምምነቶች ላይ አስተዳደራዊ ቁጥጥር እየተደረገበት ያለ ለመሆኑ በችሎት ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ አግባብ ያላቸው የአስተዳደር አካላት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገን ስምምነት ተቀብለው ለመመዝገብ እና በስምምነቱ መሰረት በንብረቱ ላይ ተጓዳኝ መብት ለመፍጠር ስምምነቱ በህጉ በተመለከተው ልዩ ፎርም ተፈፅሞ ሊቀርብላቸው ይገባል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ከ1ኛ አመልካች አባት እንዲሁም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት እና ከተጠሪ አያት በተዋረድ የመጣ የውርስ ሀብት ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁም የሚከራከሩት ንብረቱን አስመልክቶ በወራሾች መካከል የተደረገ የክፍፍል ስምምነት ስለመኖሩ ላይ ነው፡፡ የተጠሪ መከራከሪያ ክስ የቀረበበት ቤት የአያታችን የውርስ ሀብት ቢሆንም የውርስ ሃብቱን አስመልክቶ በወራሾች መካከል በቃል ስምምነት ክፍፍል ተደርጎ ቤቱ ለእናቴ ደርሷቸው ከእናቴ የተላለፈልኝ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ስምምነት ስለመኖሩ ክደዋል፡፡ እንዲያውም በንብረቱ ላይ በወራሾች ስም በጋራ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አውጥተው ግብርም በስማቸው እየገበሩ የሚገኙ መሆኑን ገልፀው ይከራከራሉ፡፡ እንግዲህ ተጠሪ የሚጠቅሱት ስምምነት የተደረገው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በመሆኑ ከላይ በተሰጠው የፍርድ ትችት መሰረት ስምምነቱ ቢያንስ በፅሁፍ የተዘጋጀ እና በሚመለከታቸው ወራሾች የተፈረመበት ሊሆን ይግባል፡፡ በዚህ መልኩ የቀረበ ስምምነት በሌለበት እና ስምምነት ስለመኖሩም ከሌሎች ባለመብቶች ጭምር መከራከሪያ ቀርቦ ባለበት በህግ ረገድ እውቅና የሚሰጠው እና ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ስምምነት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ ክስ

የቀረበበትን ንብረት አስምልክቶ ቀድሞ የተደረገ እና ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ስምምነት ከሌለ ደግሞ በዚሁ ምክንያት የአመልካቾች ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚዘጋበት አግባብ የለም፡፡

ጉዳዩ ይህ በሆነበት የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መዝጋቱ እና የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ መቀበላቸው ስምምነት ተደርጎበታል የተባለውን የውርስ ሀብት ባህሪ እና ከዚያው አኳያ የተቀመጠውን ተጓዳኝ አስገዳጅ የህግ ፎርማሊቲን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/03-27166 ላይ ጥቅምት 18/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳዳር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01037 ላይ ጥር 29/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 191393

ቀን፡- ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ቴዎድሮስ ምሕረት

አበባ እምቢአለ

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- 1. አቶ ሰይፈ ላቀው

2. ወ/ሮ አስካለ ላቀው

ተጠሪዎች፡- አቶ አሸናፊ ተክሉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ከሳሾች፤ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በቀይት ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካቾች በ09/07/2011 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የሟች እናታችንና አባታችን ወራሾች መሆናችንን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 መሰረት ወራሽነታችንን አሳውጀናል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ሌላኛውን የስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ወ/ሮ ዘነበች ላቀውን ጨምሮ ያለ ህግ አግባብ የወላጆቻችንን መሬት ከጥር ወር 2011 ዓ.ም ጀምሮ ልዩ ቦታው ስርጥ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘውን 4 ጥማድ መሬት፣ ልዩ ቦታው ግመሎ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘውን ½ ጥማድ መሬት፣ ልዩ ቦታው ዳዲስ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘውን ¼፣ ሌሎች 2 ቦታ የሚገኙ 1/8 ጥማድ መሬት፣ ልዩ ቦታው ዋደር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘውን 1/8 ጥማድ መሬትና ልዩ ቦታው አፋሳሽ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ¼ ጥማድ መሬት የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ ለቀው እንዲያስረክቡን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪን የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽም በ20/07/2011 ዓ/ም ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ተጠሪ የሚች ሙሉነሽ አስፋው ወራሽ በአዋጅ ቁጥር 133/98 ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/7/ለ ተወስኖልኝ ቀድሞ በስራ ላይ በነበረው አዋጅ መሰረት የቀደምትነት መብት ስላለኝ ከተራ ቁጥር 1-3 በክሱ ላይ በተዘረዘሩት የሙሉነሽ አስፋው ድርሻ ተላልፎልኝ፣ በስሜ ተመዝግቦ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶኝ፣ በስሜ እየገበርሁ የያዝኩት ስለሆነ አመልካቾች ሊጠይቁኝ አይገባም፡፡ አመልካቾች የሚች ቤተሰቦቻቸው ልጆች ቢሆኑም በቀድሞው አዋጅ መሰረት የውርስ ቅደም ተከተልን መሰረት በማድረግ በተጠሪ ቀድመው የመውረስ መብት ወይም መካፈል የሚያስችል ስላልነበራቸው የውርስ መሬቱን አልጠየቁም፡፡ አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 57 በቀድሞው አዋጅ መሰረት የተገኙ መብቶች የሚጸኑ መሆናቸውን ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በውርስ ያገኘሁትን መሬት ላካፍል ወይም ላስረክብ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ አሁን በተያዘው ክርክር ያልተካተተች ስለሆነ ክርክሯን መመዝገቡ አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ ታልፏል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤቱም መዝገቡን መርምሮ በአመልካቾች አቤቱታ ላይ የተጠቀሱትን መሬቶች ተጠሪዎች ለአመልካቾች ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ምስክሮች አስቀርቦ ሰምቷል፡፡ ወላጆቻቸው መሞታቸውን ተረጋግጧል፤ አመልካቾች የሚቾች ወራሾች መሆናቸውን በፍ/ብ/መ/ቁ 07245 በ15/07/2011 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 መሰረት አረጋግጠዋል፤ በተጨማሪም በቅደም ተከተል በፍ/ብ/መ/ቁ 07266 በ06/07/2011 ዓ/ምና በፍ/ብ/መ/ቁ 07035 በ22/12/2011 ዓ/ም በአማራ ክልላዊ መንግስት የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 መሰረት ያሳወጁ መሆናቸውን 2 የወራሽነት ማስረጃ ከመዝገቡ ተያይዟል፡፡ ተጠሪ ደግሞ በፍ/መ/ቁ 06174 በ02/02/2009 ዓ/ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 16/5ና በደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/7/ለ መሰረት ያሳወጀውንና በ05/12/2010 ዓ/ም የወ/ሮ ሙሉነሽ አስፋውን መሬት በወረዳው መሬት አስተዳደር በኩል ተላልፎለት በይዞታ መለያ ቁጥር Am/11/6/5/1450 ያወጣውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በማስረጃነት ያያያዘ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ በዚህ መዝገብ ተከራካሪ ስላልሆነ ማስረጃውን መመዝገቡ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ መሬቱን ሊይዝ የቻለው የሚቾች የቤተሰብ አባል በመሆኑ ወራሽነቱን አረጋግጦ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የአመልካቾች ምስክሮች አመልካቾች የሚቾች ልጆች ከመሆናቸው ውጪ የተለየ ያስረዱት ነገር የለም፡፡

ክርክር ያስነሳው የሚቾች መሬት ተጠሪና የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያወጡበት መሆኑን አመልካቾች ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም የወረዳው መሬት አስተዳደር በቁጥር ባ/ወ/ወ/7/ወ/አስ/አጠ/5451/30/28 በ11/08/2011 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ ተጠሪ የሚች ሙሉነሽ አስፋው የገጠር መሬት ይዞታ ወራሽ መሆኑን በቀያት ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/መ/ቁ 06174 አስወስኖ ይዞታዋ እንዲተላለፍለት አመልክቶ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ማስታወቂያ ተለጥፎ ባለመቅረቡ በውርስ የገጠር መሬት ይዞታ የሚተላለፍበት ፎርማሊቲ ተሟልቶ ውርስ እንዲተላለፍለት ተወስኖ

ተላልፎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በደ/መ/ቁ Am/11/6/5/1450 ተመዝግቦ እንዳገኘ በመግለጽ መሬት አስተዳደር ማስረጃ ልኳል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከላይ ከተጠቀሱት ማስረጃዎች የሚቾች መሬት ህጉን በጠበቀ መልክ ለተጠሪና ለ2ኛ የስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ተላልፏል፡፡ ተጠሪና የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያወጡበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ መሬቱን ለቆ ያስረክበን ከማለት ውጪ በተጠሪ ስለቀረበው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የገለጹት ነገር የለም፡፡ የአማራ ክልል የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 35/2 የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የባለ ይዞታው በህግ የተጠበቀ ማስረጃ መሆኑንና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እያለ ዳኞች ሌሎች የሰነድም ሆነ የሰው ማስረጃዎችን ቅደሚያ ሰጥተው ሊቀበሉና ሊመለከቱ እንደማይችሉ ሲገልጽ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ስር ደግሞ ይህንን የሚቃረን ጠንካራ የጽሑፍና አብልጦ የሚያሳምን ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ህጉ ደንግጎ ይገኛል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶ የተሰጠው ሰው መሬቱ የእሱ አይደለም የሚል ክርክር የሚያቀርብ ግለሰብ ጠንካራ የጽሑፍ ማስረጃና አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ አለበት፡፡ በመሆኑም በሰው ምስክር ብቻ ተጠሪ ማረጋገጫ ደብተር አውጥተው የያዙትን መሬት የሚለቁበት የህግ አግባብ ስለሌለ ሊለቁ አይገባም በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተጠሪን አስመልክቶ የቀረበውን ይግባኝ የሰረዘው ሲሆን በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ሰርዞታል፡፡

የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች የካቲት 18 ቀን 2012 ዓ/ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ የአሁን ተጠሪ በቀድሞው አዋጅ መሰረት የመሰረተው መብት የለውም ምክንያቱም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 996 መሰረት የወራሽነት ማስረጃ ብቻ በመያዝ በአውራሹ ንብረቶች ላይ መብት መመስረት አይችልም፡፡ መሬቶቹን በመዘርዘር በመሬት ይዞታው ላይ እኔ ነኝ ወራሽ በማለት ተከራክረናል፡፡ ተጠሪ በቀድሞው አዋጅ ቁጥር 133/1998 መሰረት መሬቱን አልተረከበውም፤ በእጁ አላደረገውም ስለዚህ በቀድሞው አዋጅ መሰረት የተመሰረተ መብት የለውም፡፡ ስለዚህ ውሳኔ መሰጠት የነበረበት በአዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የሟች ልጆች ስለሆንን በአዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት ወራሾች ነን፡፡ ተጠሪ በመሬቱ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ያገኘው በ05/12/2010 ዓ/ም ሲሆን ይዞታውን የተረከበው በጥር ወር 2011 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ የቤተሰብ አባል ነው እንኳን እንዳይባል ፍርድ ቤቱ የቤተሰብ አባል ነው በማለት ውሳኔ አልሰጠም፤ በቤተሰብ አባልነቱ መብት አልመሰረተም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በቀድሞው አዋጅ መሰረት ህጋዊ መብት የሌለው ስለሆነ በስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የህግ ትርጉም ስህተት የተፈጸመበት ውሳኔ ነው፡፡

መሬቱ የማን ይዞታ ነው ወይም የእኔ ይዞታ ነው የሚል ክርክር አልተነሳም፤ ፍርድ ቤቱም ይህንን ጉዳይ በጭብጥነት አልያዘውም፤ መሬቱ የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አስፋው መሆኑን ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም፤ በመሆኑም ተከራካሪዎች የተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 35/2/ እና /5/ ተፈጻሚነቱ ክርክር በተነሳበት የይዞታ መሬት ላይ ህጋዊ ባለይዞታ ማነው የሚመለከተውን ክርክር በተመለከተ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቱ ይህን ድንጋጌ መሰረት አድርጎ የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በጭብጥነት ሊያዝና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው የወራሽነት መብት ያለው ማነው የሚለው ጭብጥ ነው፡፡ ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ ልጅ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት የሟች ሙሉነሽ አስፋው ልጅ ነው በማለት የተሰጠው ማስረጃ የሀሰት በመሆኑ፣ ያገኘው የመሬት ማረጋገጫ ደብተር ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተንተርሶ ነው፣ የአዋጁን አንቀጽ 34/5 የሚጥስ ነው፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎችን መንፈስና የክርክርን ሂደት የሚጻረር ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ይዞታው በአጠቃላይ የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አስፋውና የሟች አቶ ላቀው ሙሉጌታ የጋራ የይዞታ መሬት ነው፡፡ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአባታችን ድርሻ እኩል እንድንካፈል ተወስኗል፡፡ የሟች እናታችን ድርሻ መሬት ተጠሪ ለቀው ሊያስረክቡን ይገባል የሚል ነው፡፡

የሠበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ከግራ ቀኙ ክርክር የአሁን አመልካቾች የሟቾች ወራሽ መሆናቸው አከራካሪ ባልሆነበትና የአመልካቾች ክስ/አቤቱታ/ በይርጋ ይቋረጣል ባልተባለበት ሁኔታ የአመልካቾች የውርስ ሀብት ጥያቄ ውድቅ ተደርጎ በስር ፍርድ ቤቶች የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብሎ ተጠሪ የመከላከያ መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ክርክር በሚደረግበት ይዞታ ላይ መብት አቋቁሜበታለሁ፣ በመሬት አስተዳደር ተመዝግቧል፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች በነበረን ክርክር መብት መቋቋሙ በማስረጃ ተረጋግጦ የሙሉነሽ አስፋው ድርሻ አይገባችሁም የላቀው ሙሉጌታን ድርሻ ተካፈሉ ተብለው ተካፍለዋል፡፡ አመልካቾች ወራሽነቱ በሀሰት የተገኘ ነው ይሰረዝልን የሚል ክስ በወረዳው ፍርድ ቤት አቅርበው በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ታይቶ ወራሽነት አይሰረዝም ተብሎ ስለተወሰነ ራሱን አስችሎ ክርክር አቅርቦበት ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ችሎት ክርክር ሊቀርብበት አይገባም፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ በይዞታው ላይ መብት የተቋቋመበት ስለመሆኑ በቂና ተአማኒ የሆነ ማስረጃ ነው፡፡ አመልካቾች አዲስ አዋጀ ሲወጣ ልጆች ነን በሚል መብት የተቋቋመበት ይዞታ ከተጠሪ ላይ ሊወስዱ አይችሉም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን በአግባቡ መዝኖ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች የሙሉነሽ አስፋው ውርስ ይገባናል ሲሉ ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 28 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጡት የመልስ መልስ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 99567፣ 121822፣ 183645፣ 86089 የሰጠውን ውሳኔ ወደጎን በመተው የሰጡት ውሳኔ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ውሳኔ ነው፡፡ በአዋጅ

ቁጥር 252/2009 መሰረት አመልካቾች የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አስፋው ልጆች ስለሆኑ በዚህ አዋጅ መሰረት የመውረስ መብት ያላቸው አመልካቾች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ወራሽ ሳይሆን መውረሱ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አስፋው ብቸኛ ወራሾች አመልካቾች ብቻ ናቸው፡፡ ተጠሪ በቀድሞው አዋጅ መሰረት በወረዳው መሬት አስተዳደር ወራሽ መሆኑን አረጋግጦ አላስመዘገበም መሬቱን አልተረከበም በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ለውርስ ክርክሩ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ የትኛው ነው የሚለውን በመያዝ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ክስ ያቀረቡት የውርስ መሬት ለመረከብ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የቤተሰብ አባል በመሆኑ የውርስ መሬቱ ወራሽ መሆናቸውን እና አውራሻቸው በሞቱበት ጊዜ በሥራ ላይ በነበረው ሕግ መሠረት ቀዳሚ ወራሽ መሆናቸውን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ በአምስተኛው አንቀጽ (Title) አገሪቱ የውርስ ስርዓት እንዴት እንደሆነ ዝርዝር የሆኑ ደንቦችን የያዙ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ስለ ውርስ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አቀራረጽ ስንመለከት በአንድ በኩል የውርስ ሕግ ጠቅላላ መሪ ደንቦች የሆኑ ጠቅላላ የሕግ ድንጋጌዎች ያሉት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሟች ውርስ በኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ የሚተላለፍበትን መንገድ በዝርዝር የሚያስቀምጡ ስለ ውርስ ንብረት አስተዳደር እና የውርስ ንብረት እንዴት ለወራሾች እንደሚከፋፈል የሚዘረዝሩ ልዩ የሕግ ድንጋጌዎች ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ ውርስ ስለሚከፈትበት ጊዜና ስፍራ ለወራሾች ሊተላለፉ ስለሚችሉ የሟች መብትና ግዴታዎች እና ሟችን ለመውረስ ስለሚያስፈልግ ችሎታ ከፍ/ሕ/ቁ. 826-841 የተደነገጉት የሕግ ድንጋጌዎች ጠቅላላ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸው በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ውርስ ሞትን መሰረት አድርጎ መብትና ግዴታ ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው የሚተላለፍበት የሕግ ሁኔታ ነው፡፡ የፍ/ሕ/ቁ. 1 መሰረት ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከሞተበት ቀን ድረስ የሕግ መብት አለው፡፡ ስለዚህ በሞት ምክንያት አንድ ሰው ያለው መብት የሚቋረጥ ስለሆነ በተለይ ከንብረት ጋር የተያያዘው ጥቅም የማን ሆኖ ይቀጥላል የሚለው እንዲሁም በሞት በእንጥልጥል የሚቀረው መብት ምን ይሆናል ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የምናገኘው ከውርስ ሕግ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 826/2/ መሰረት በሟች ሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆነ በስተቀር በውርስ ውስጥ የሚገኙ የሟች የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች ለወራሾችና ለኑዛዜ ባለስጦታዎች ይተላለፋሉ፡፡ የነዚህ መብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ የውርስ መከፈትን ወይም መጀመርን የግድ ይላል፡፡ የሟች ውርስ ተከፈተ የምንለው ሟች በሞት ሲለይ በሕይወት ዘመኑ ሲኖር በነበረው መብቱ ተጠቅሞ ያፈራው ንብረት ባለቤት በማጣቱና ለሟች ግዴታም ተጠያቂ የሚሆን ባለመኖሩ የአንዲት አገር ሕግ የሟችን መብትና ግዴታ ለሌሎች ሰዎች /ወራሾች/ ለማስተላለፍ ስለ ሟች ውርስ አስተዳደር ትኩረት ሰጥቶ ጥበቃ ማድረግ መጀመሩን የምናመለክትበት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕግ በዚህ ላይ ያለውን አቋም ስንመለከት አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ በሞተበት ጊዜ

ዋና መኖሪያ ሥፍራ በሆነበት ቦታ የሟች ውርስ ይከፈታል በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁር 826/1/ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ የምንረዳው የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ስለ ሟች ንብረትና የውርስ አስተዳደር ትኩረት መስጠትና ጥበቃ ማድረግ የሚጀምረው ሟቹ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት የጊዜ ክፍተት ሳይተው መሆኑን ነው፡፡ ሟች ህይወቱ ማለፉ ከተረጋገጠበት ቅጽበት ጀምሮ የሟች ውርስ ይከፈታል፡፡ የሟች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ በሕግ መወሰኑና ግልጽ በሆነ ድንጋጌ ማስቀመጡ ሟችን የሚወርሰው ሰው ሟች ከሞተ በኋላ በስንት ጊዜ በህይወት የኖረ ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በሌላ አነጋገር የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ ለማረጋገጥ መርዳቱ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕጋችን ሟችን ለመውረስ ሟች ሲሞት በህይወት መኖር አስፈላጊ መሆኑ በፍ/ሕቁ.830 ተደንግጓል፡፡ የሟች ውርስ የሚከፈተው ሟች በሞተበት ቅጽበት በመሆኑ ሟች ከሞተ በኋላ በውስን ጊዜም ዘግይቶ የሞተ ሰው ሟችን ወርሶ እንደሞተ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ የሟች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ ትኩረት ሰጥቶ የሕጉ ድንጋጌ በግልፅ ማመልከቱ የወራሽነት ችሎታን እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የተደነገጉትን የሕግ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም ይረዳል፡፡ የሟች ውርስ መከፈት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሟች በህይወት እያለ የነበረው የፍትሐብሔር መብትና ግዴታ የተቋረጠና የሟች ንብረት በፍ/ሕ/ቁ.942 በተደነገገው መሠረት እንደ አንድ ልዩ ንብረት ተቆጥሮ /estate/ ሕግ ጥበቃ ማድረግ መጀመሩን የሚያመለክትና ይህም የሟች ህይወት ያለፈበት ቅጽበት ጀምሮ የሚከናወን መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከአመልካቾች የክስ አቤቱታ እንደተረዳነው አውራሾቻቸው የሞቱት እንደ ቅደም ተከተላቸዉ አባታቸው አቶ ላቀው ሙሉጌታ የካቲት 30 ቀን 1996 ዓ/ም ሲሆን ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ ሙሉነሽ አስፋው ደግሞ ነሀሴ 04 ቀን 2009 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የአባታቸውን የውርስ ድርሻ መሬት ያገኙ መሆኑ እና ተጠሪ የያዙት የእናታቸውን የውርስ ደርሻ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪም ከስር ጀምሮ የሚከራከሩት የሟች ሙሉነሽ አስፋው የቤተሰብ አባልና ወራሽ መሆናቸውን በመግልጽ በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11(7)(ለ) መሠረት ቀዳሚ ወራሽ ነኝ በማለት ነው፡፡ አመልካቾች ጉዳዩ በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 252/2009 መሠረት ሊገዛ እንደሚገባ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የዉርስ ጉዳይ የገጠር መሬትን የሚመለከት ሲሆን፣ የወራሽነት መብት የሚተላለፍላቸዉን ሰዎች ማንነት አስመልክቶ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉጭ (ይህ በልዩ ሁኔታ በገጠር መሬት አዋጅ የተመለከተ በመሆኑ) ያሉት ሌሎች ከዉርስ ጋር በተያያዘ በፍትሐብሔር ህጉ ላይ የተመለከቱ ደንቦች እና መርሆዎች ከገጠር መሬት ወራሽነት ጋር በተያያዘም እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት እንዳላቸዉ የሚታወቅ ነዉ፡፡ ዉርስ የሚከፈትበትን ሁኔታ አስመልክቶ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 826(1) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉ ዉርስ የሚከፈተዉ አዉራሹ በሞተበት ጊዜ እና ቦታ መሆኑን ነዉ፡፡ መብት የሚመነጨዉ ከህግ መሆኑም እሙን ነዉ፡፡ ስለሆነም አንድ ሰዉ

የሟች ወራሽ መሆን ያለመሆኑ የሚረጋገጠዉ ሟች በሞተበት ጊዜ በስራ ላይ ያለዉን ህግ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡ የወራሽነት ማረጋገጫ፣ ከስሙም መገንዘብ እንደሚቻለዉ፣ በህግ የተገኘን መብት ለማረጋገጥ የሚሰጥ እንጂ በእራሱ መብት የሚሰጥ አለመሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ለዚህ ጉዳይም ሆነ በተለያዩ የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ለተነሳው ጭብጥ መሰረት የሆነው የትኛው ሕግ የተከራካሪ ወገኖችን መብት ለመወሰን መዋል አለበት የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በአጠቃላይ የውርስ ሕግን መሰረት በማድረግ የውርስ ጉዳይ እልባት ለመስጠት ቢሞከር ብያኔው መሰረት የሚያደርገው በሕግ የታወቀን ዝምድና/ግንኙነትን ነው፡፡ አመልካቾች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996 መሰረት አድርገው መብት እንዳገኙ የተከራከሩ ሲሆን የተጠቀሰው የምስክር ወረቀት የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ የፍ/ሕ/ቁ. 997 ወራሹ በምስክር ወረቀቱ እንደተገለጸው ወራሽ እንደሆነ ግምት ይወሰዳል፡፡ ሆኖም በሕጉ ታሳቢ የተደረገው የምስክር ወረቀቱ ወራሽ መሆንን ከማረጋገጥ ባለፈ የወራሹን ድርሻ የሚያመለክት መሆኑን እንደሆነ ከቁጥር 996 ንባብ መረዳት የሚቻል ቢሆንም በአሰራር ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ማረጋገጫ ዝምድናን መሰረት አድርጎ ወራሽ መሆንን ከማወቅ የዘለለ አይደለም፡፡ በፍ/ሕ/ቁ.946 እና ተከታዮቹ መሰረት ተጠሪን ባሳተፈ መልኩ ወርስ ተጣርቶ የወራሾች ማንነትና የወራሾች የዉርስ ሀብት ድርሻ ተለይቶ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 996 መሰረት ተገልጾ የተሰጠ የወራሽነት ምስክር ወረቀት ባለመሆኑ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃዉን በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክር የሚሰጣቸዉ የተለየ መብት የለም፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር ለውርስ መብቱ መሰረት የሆነው ሕግና ጉዳዩ የተከሰተበትን ውርሱ የተከፈተበትን ጊዜ ከግምት በማስገባት አግባብበነት ያለውን ህግ መለየት ያስፈልጋል፡፡ አመልካቾች ጉዳዩ በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት የመብት ጥያቄ የሚያነሱ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 133/1998 መሠረት ቀዳሚ ወራሽ ነኝ በማለት ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ ተጠሪ ወራሽ መሆናቸው እንደተረጋጋጠ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዳላቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች የመብት ጥያቄ የሚያነሱት በአዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት በመሆኑ ጥያቄው የሚሆነው ይህ አዋጅ ከመወጣቱ በፊት የተከናወኑ ተግባራት እና የተገኘ መብት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን መቻሉን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጉዳይ ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተለያየ አቋም የተያዘ በመሆኑ የተነሳውን የሕግ ጥያቄ በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል፡፡

በመርሕ ደረጃ ሕጎች የሚኖራቸው ውጤት የወደፊት ነው፡፡ በኢፌድሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደማይሰራ ስለተደነገገ የወንጀል ጉዳዩችን በተመለከተ ወደ ኋላ ተፈጻሚ የሚሆን ሕግ ኢ-ሕገመንግስታዊ ይሆናል፡፡ የፍትሐብሔር ጉዳዩችን በተመለከተ ምንም እንኳ ከልካይ የሕገ መንግስት ድንጋጌ ባይኖርም ተቀባይነት ያለው የሕግ አስተምሮ ሕጎች ተፈጻሚ መሆን

ያለባቸው ወደፊት ብቻ እንጂ አስቀድሞ የተገኙ መብቶችን መቀየር የለባቸውም የሚል ነው። ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም ከሚለዉ አጠቃላይ መርህ (the principle of non-retroactivity of laws) አንፃር ስንመለከተውም ሕግ በዜጎች መካከል ያለዉን ግንኙነት ለመቆጣጠር ሲባል በሕግ አዉጪዉ አካል የሚወጣ ነዉ። ህግ የሚወጣዉም ህጉ በስራ ላይ ባለበት ወቅት በዜጎች መካከል ያለዉን ወይም ወደ ፊት የሚፈጠረዉን ግንኙነት ለመቆጣጠር ወይም ለመዳኘት በመሆኑ ህጉ ከመዉጣቱ በፊት ወይም ከተሻረ በኋላ በተፈጠረ/በሚፈጠር ግንኙነት ላይ ተፈፃሚ ማድረግ አይቻልም። ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለዉም መርህ ከዚሁ የመነጨ ሲሆን፣ መሠረተ ሃሳቡም አንድ ህግ ተፈፃሚ የሚሆነዉ ህጉ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለተፈጠረ መብትና ግዴታ ወይም ፍሬ ነገር ነዉ የሚል ነዉ። በሌላ አገላለጽ አንድ ህግ ተፈፃሚ መሆን የሚጀምርበትን ጊዜ አስመልክቶ በህግ አዉጪዉ ከተደነገገዉ ቀን በፊት ለተፈጠሩት ክስተቶች ወይም መብትና ግዴታዎች ተፈፃሚነት አይኖረዉም የሚል ሃሳብ ያለዉ ነዉ። ይህ መርህ ከህግ የበላይነት መገለጫዎች ዉስጥ አንዱ ነዉ። ስለሆነም አንድ መሠረታዊ ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ህግ አዉጪዉ እራሱ በልዩ ሁኔታ ካላመላከተ በስተቀር፣ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ለያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉን መሠረታዊ ህግ (substantive law) ሲወስን መሠረት ሊያደርግ የሚገባዉ ወይም መሠረት እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በተፈጠረበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረዉ ህግ ሊሆን ይገባል። ስለሆነም ድርጊቱ ወይም መብትና ግዴታ በተፈጠረበት ጊዜ የነበረዉ ህግ በሌላ ህግ የተተካ ሆኖ ሲገኝ እና ክርክሩ ለፍርድ ቤት ወይም ለዳኝነት ሰጪ አካል የቀረበዉ አዲሱ ህግ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መምራት እና ዉሳኔ መስጠት ያለበት በተሻረዉ ህግ መሠረት ይሆናል፤ ክርክሩ አዲሱ ህግ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለፍርድ ቤት መቅረቡ ጉዳዩ በአዲሱ ህግ መሠረት እንዲመራ ምክንያት ሊሆን አይገባም። ይህን ማድረግ ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለዉን የህግ መርህ የሚጥስ ከመሆኑም በላይ የህግ የበላይነት እንዳይረጋገጥ ወይም እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በተያዘው ጭብጥ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል የተለያየ አቋምን የያዘ ትርጉም የሰጠ ሲሆን በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 189013፣ 163796 እና ሌሎች መዛግብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ውርሱ በተከፈተበት ጊዜ በሥራ ላይ በነበረው ሕግ እንጂ በክርክሩ ጊዜ አዲስ ሥራ ላይ በዋለው ሕግ አይደለም በማለት ትርጉም ሰጥቷል። በሌላ በኩል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥሮች 86089፣ 99587፣ 121822፣ 183645 እና በሌሎች መዛግብት ላይ በሰጠው ትርጉም ለውርስ ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ሟች በሞተበት እና ውርሱ በተከፈተበት ጊዜ የነበረው ህግ ሳይሆን ክርክሩ በቀረበ ጊዜ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት ሊሆን ይገባል በማለት ትርጉም መስጠቱ በአንድ ጭብጥ ላይ የተለያየ እና የሚቃረን ትርጉም በመሆኑ ወጥ የሆነ ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ነው። ከላይ በፍርድ ሐተታው እንደተገለጸው ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥሮች 86089፣ 99587፣ 121822፣ 183645 የሰጠው ትርጉም ሕግ ወደኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለው መርሕ እና በፍ/ሕ/ቁ. 826(1) አግባብ የተመለከተው ዉርስ የሚከፈተዉ አዉራሹ በሞተበት ጊዜ እና ቦታ መሆኑን የሚለውን

ያላገናዘበ በመሆኑ ትርጉሙ ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የውርስ ክርክር ወራሾቹ ሆነ ቀዳሚ ወራሾች እነማን ናቸው የሚለው ሊወሰን የሚገባው አውራሽ በሞተበት ጊዜ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ወ/ሮ ሙሉነሽ አስፋው ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩበት ወቅት በ2009 ዓ/ም በክልሉ ስራ ላይ የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 133/98 ነዉ፡፡ የመሸጋገሪያ ድንጋጌን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 57 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ በሌሎች ህጎች የተቋቋሙ መብቶች እና ግዴታዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተጋጩ ድረስ ተፈፃሚነታቸዉ እንደሚቀጥል እንዲሁም አዋጁ ከመዉጣቱ በፊት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ እልባት እንደሚያገኙ የሚደነግግ ቢሆንም፣ ከዉርስ ጋር በተያያዘ ለሚነሳ ክርክር ይህ አዋጅ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደሚሰራ አያመላክትም፡፡ በአመልካች የተነሳው ጥያቄ ተጠሪ በቀድሞው አዋጅ መሰረት መሬቱን አልተረከበውም፤ በእጁ አላደረገውም ስለዚህ በቀድሞው አዋጅ የተመሰረተ መብት የለውም እንዲሁም ተጠሪ በመሬቱ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ያገኘው በ05/12/2010 ዓ/ም ሲሆን ይዞታውን የተረከበው በጥር ወር 2011 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት መሆኑን በተመለከተ የተነሳው ክርክር መሬቱን መረከብ በመሬት ላይ ለሚኖር መብት መሰረት ባለመሆኑና ተፈጻሚ የሚሆነውን ሕግ ለመወሰን ስለማይረዳ ይህ ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ልጆች ስለሆንን ተጠሪ ደግሞ የቤተሰብ አባል ስላልሆነ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት አመልካቾች ወራሾች ነን በሚል የሚቀርበው ክርክር ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው ይህ የሚወሰነው አግባብ ባለው ሕግ እንጂ አንዱ ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ መሰረት ባደረገው ሕግ ባለመሆኑ አግባብነት የለውም፡፡

ስለሆነም አመልካቾች ሟችን ለመዉረስ መብት ያላቸዉ መሆን ያለመሆኑ የሚወሰነዉ በአዋጅ ቁጥር 133/98 መሠረት ይሆናል፡፡ ተጠሪ የሟች ሙሉነሽ አስፋው ልጅ ባይሆኑም የቤተሰብ አባል እና ወራሽ ስለመሆናቸው መረጋገጡን የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በፍርድ ሀተታው አስፍሯል፡፡ ይህም ተጠሪ በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11(7)(ለ) መሠረት ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን አመልካቾች የሟች ልጆች ሲሆኑ ራሱን ለማስተዳደር የግል መሬት ያለው ወራሽ የሆነ ልጅ በደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11(7)(ሐ) መሠረት ወራሽ ነው፤ ነገር ግን በአወራረስ ቅድመተከተል ተጠሪ ቀዳሚ ወራሽ በመሆናቸው ተጠሪ በውርስ የያዙትን መሬት ሊለቁ አይገባም ተብሎ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-11116 ሕዳር 22 ቀን 2012 ዓ/ም፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0130745 ሰኔ 19 ቀን 2011 ዓ/ም

እና የቀይት ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07293 ሰኔ 05 ቀን 2011 ዓ/ም ተጠሪን አስመልክቶ የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥሮች 86089፣ 99587፣ 121822 እና 183645 ላይ ለውርስ ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ሟች በሞተበት እና ውርሱ በተከፈተበት ጊዜ የነበረው ህግ ሳይሆን ክርክሩ በቀረበ ጊዜ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት ሊሆን ይገባል በማለት የሰጠው ትርጉም ተለውጧል፡፡

3. የውርስ ክርክር ወራሾቹ ሆነ ቀዳሚ ወራሾች እነማን ናቸው የሚለው ሊወሰን የሚገባው አውራሽ በሞተበት ጊዜ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት ሊሆን ይገባል በማለት ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

የሰ/መ/ቁ. 144359

የካቲት 14 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካቾች፡-** 1ኛ. አቶ መስፍን እንደሬ

2ኛ. አቶ ተፈራ እንድሬ

3ኛ. ወ/ሮ የሻረግ እንድሬ

4ኛ. አቶ እንዳል እንድሬ

ጠበቃ ማረን ወንዴ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፦** 1ኛ. ወ/ሮ ብዙነሽ እሸቴ - ተወካይ አይተነው እንድሬ - ቀረቡ፡፡

2ኛ. አቶ ሙስጠፋ እንድሬ - ጠበቃ አገኘሁ አይናለም - ቀረቡ፡፡

በዚህ መዝገብ እና በሰ/መ/ቁ. 144360 ያለ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ከመሆናቸው በላይ የቀረበው የህግ ክርክርና የነገረ ጭብጥም አንድ በመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 11/1/ መሠረት ሁለቱም መዝገቦች በማጣመር ጉዳዩን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

**ጉዳዩ፦** የውርስ ሀብት ክርክርን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሻሽመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ፍርድ ቤቱ በ24/4/2009ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ እና በ17/6/2009ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመቃወም የአሁን አመልካቾች ከሌሎች 2 አመልካቾች ጋር ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የስር ከሳሽ በስር ተከሳሽ እናታችን ላይ ባቀረቡት ክስ ፍርድ ቤቱ ሲያከራክር ቆይቶ የክርክሩን ንብረት ከሳሽ እና ተከሳሽ ብቻ እንዲካፈሉ የሰጠው ውሳኔ የሟች አባታችን የአቶ እንድሬ ወርቁን ንብረትም ጭምር በመሆኑ እኛም የአባታችን ወራሽ መሆናችንን ያረጋገጥን በመሆኑ ውሳኔው የኛን መብት የሚነካ ስለሆነ ይህ ውሳኔ ተሰርዞ ድርሻችንን ማግኘት እንድንችል ይወሰንልን በማለት በ21/6/2009ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ለሰ/መ/ቁ. 144360 አቤቱታ ምክንያት የሆነው የአሁን አመልካቾች ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ሲደረግባቸው አዲስ ክስ ለሻሽመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ 61715 በቀን 9/8/2009 ዓ.ም

በዋለው ችሎት ክሳቸው ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች አቤቱታ ቢያቀርቡም በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆነ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ነው፡፡ በሁለቱ በዚህ መዝገብ እና በሰ/መ/ቁ. 144360 ያለ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ከመሆናቸው በላይ የቀረበው የህግ ክርክርና የነገረ ጭብጥም አንድ በመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 11/1/ መሠረት ሁለቱም መዝገቦች በማጣመር ጉዳዩን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ ቤቱም የመቃወም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ በመጀመሪያው ክርክር ጊዜ ተከሳሽን ወክሎ ይከራከሩ የነበሩት ከፍርድ መቃወሚያ አቅራቢዎች መካከል አቶ አይተነው እንድሬ የተባሉት ግለሰብ በመሆናቸው እና የአሁን ፍርድ መቃወሚያ አቅራቢዎች የስር ተከሳሽ ልጆች በመሆናቸው ክርክሩን አያውቁትም ነበር ለማለት የማያስችል በመሆኑ በወቅቱ በክርክሩ ገብተው ለመከራከር የማያስችል በቂ ምክንያት የነበረ ስለመሆኑ አላስረዱም በማለት አትቶ የአሁን አመልካቾች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ለሰ/መ/ቁ. 144360 አቤቱታ ምክንያት የሆነው የአሁን አመልካቾች ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ሲደረግባቸው አዲስ ክስ ለሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ 61715 በቀን 9/8/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክሳቸው ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች አቤቱታ ቢያቀርቡም በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆነ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም መዝገቦች በማጣመር ጉዳዩን መርምረናል፡፡

አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት በነዚህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም፦ የመቃወም ተጠሪዎች ባደረጉት ክርክር እኛ ባልተከራከርንበት የተሰጠው ውሳኔ እኛ ከሟች አባታችን ማግኘት የሚገባን ድርሻችንም ጭምር ውሳኔ ያረፈበት እና የፍትሐ ብሄር ስነ-ስርዓት ህጉም በሌለበት የተሰጠ ፍርድ መብቱ የሚነካበት ሰው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት የፍርድ መቃወሚያ ሊያቀርብ እንደሚችል ተደንግጎ እያለ ይህ ሁሉ ታልፎ ያቀረብነውን የፍርድ መቃወም አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት ቅሬታው ተጠሪዎችን ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሁፍ መልስ እና የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረገው ክርክር እና ማስረጃ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም የአመልካቾች ክርክር አሁን ክርክር የተነሳበት ንብረት እኛም የአባታችን ድርሻ ያለበት ስለሆነ እኛ የክርክሩ ተካፋይ ያልተደረግንበት ውሳኔ መብታችንን ስለሚነካ ተሰርዞ የድርሻችንን እንድንካፈል ይወሰንልን በማለት ያቀረብነው የመቃወሚያ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ላይ እንደተመለከተው ማንኛውም በፍርዱ ተካፋይ ሊሆን የሚገባው ሰው ተካፋይ ባልሆነበት ሁኔታ የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካ ከሆነ ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ሊያቀርብ እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የሱን መብት የሚነካ ክርክር መኖሩን ያወቀ ማንኛውም ሰው ፍርድ መሰጠቱን ሳይጠብቅ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ጠይቆ ገብቶ ተከራክሮ መብቱን ሊያስጠብቅ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 41 ላይ ደንግጎ ይገኛል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካቾች የስር የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ የተደረገው አመልካቾች አስቀድመው ክርክሩን ያውቁት ስለነበር አሁን ፍርድ እስከሚያልቅ ድረስ ጠብቀው ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ በእርግጥም አስቀድሞ መብቱን የሚነካ ክርክር መኖሩን ያወቀ አካል ክርክሩ አብቅቶ ውሳኔውን ከመስማቱ በፊት ወደ ክርክሩ ሊገባ እንደሚገባ ከላይ በተመለከተው የህግ ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡበት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በነበረው ክርክር ላይ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካቾች እናትን ወክሎ ይከራከር የነበረው ከፍርድ መቃወሚያ አቅራቢዎች አንዱ የሆነው የስር ተከሳሽ ልጅ እና የአሁን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢዎች ወንድም መሆኑ በስር በግራ ቀኙ ከተደረገው ክርክር መረዳት ችለናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢዎች በስር ወንድማቸው እና እናታቸው መካከል የነበረውን ክርክር በተለየ ሁኔታ እንደማያውቁ ካላስረዱ በስተቀር ክርክሩ መኖሩን አያውቁም ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ሲሰጥ ጠብቀው በመምጣት የተሰጠው ፍርድ ይነሳልኝ በማለት አቤቱታ ማቅረብ የፍት/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ላይ የተመለከተውን የህግ ድንጋጌ አላማ የሚያሳካ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ ለውርስ ሀብት ክርክርን በተመለከተ ተፈፃሚነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ እንኳን የውርስ ሀብቱ ሳይከፋፈል ቀርቶ ከተከፋፈለ በኂላም በሌለበት የውርስ ሀብቱ የተከፋፈለበት አካል በሚያቀርበው አቤቱታ ክፍፍሉ ሊፈርስ እና እንደገና ክፍፍል ሊደረግ እንደሚገባ በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 1080 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን አመልካቾች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አስቀድሞ የነበረውን ክርክር በሚያውቁበት ሁኔታ ቢሆንም የፍርድ መቃወሚያ የቀረበበት ክርክር የውርስ ሀብትን መሰረት ያደረገ ከሆነ የውርስ ሀብቱ ክፍፍል ከተደረገ በኂላም ቢሆን የሚቻል ክርክር በመሆኑ የአመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አመልካቾች አስቀድመው ክርክሩን ያውቁት ነበር በማለት ውድቅ በማድረግ የሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በትእዛዝ በማጽናት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58636 በቀን 1/7/2009 ዓ.ም እና የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29010 በቀን መጋቢት 5 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ

በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 263073 ሚያዝያ 8 ቀን 2009 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ መነሻነት ክርክር ባቀረቡበት የውርስ ሀብት ላይ አመልካቾች ድርሻ አላቸው? ወይስ የላቸውም? የሚለውን ጭብጥ በማስረጃ አጣርቶ ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት ለስር የሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት ይላክ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ለዚህ ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁ. 144360 ይያያዝ ብለናል፡፡

**መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

**የሰ/መ/ቁ.** 236246

ሰኔ 26 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች፡** ወ/ሮ ገነት ጉልላት- ከጠበቃ ኤሊያስ ጥላሁን ጋር - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ተቋመወርቅ በለጠ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ በፍርድ ቤት የተሰጠ የወራሽነት ማረጋገጫ የሚሰረዝበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት ማመልከቻ ተጠሪ አዉራሽ አያታቸዉ ወ/ሮ አዛለች አወቀ በ1981 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ ወራሽነት ሳይጠይቁ ቆይተዉ ከ33 ዓመት በኋላ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ መዉሰዳቸዉ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰዉ የተሰጣቸዉ የወራሽነት ማረጋገጫ ዉሳኔ እንዲሰረዝ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸዉ ተጠሪ በመ/ቁጥር 111123 ላይ ወራሽነታቸዉን ባረጋገጡበት መዝገብ ላይ አመልካች መቃወሚያ አቅርበዉ ዉድቅ ተደርጎ ዉሳኔዉ የጸና መሆኑን እና ሌሎች የመጀመሪያ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚሏቸዉን ክርክሮች በመጥቀስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ የአያታቸዉ ወ/ሮ አዛለች አወቀን ሀብት ለመዉረስ ያቀረቡት የወራሽነት ጥያቄ በሦስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) እና በመ/ቁጥር 120841 ላይ የተሰጠዉን የሰበር ዉሳኔ በዋቢነት በመጥቀስ አስቀድሞ ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረዉን የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ በመሰረዝ ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መዉሰድ በይርጋ የማይታገድ በመሆኑ ተጠሪ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የወሰዱት መብታቸዉ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ ነዉ በሚል የወራሽነት ማስረጃዉን በመሰረዝ የተሰጠ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የከተማዉ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡ አመልካች ጥቅምት 12 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ የሆነዉ ዉሳኔ

መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፣ የሰበር አቤቱታቸዉ መሠረታዊ ይዘትም በአጭሩ ሟች አባታቸዉ በህይወት በነበሩበት ወቅት ያላረጋገጡትን የሟች ወ/ሮ አዛለች አወቀ ወራሽነት ተጠሪ በምትክ ወራሽነት ከ33 ዓመት በኂላ ያስጡት የወራሽነት ማረጋገጫ ዉሳኔ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የወራሽነት ማስረጃዉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት የሰጡት ዉሳኔ የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 1000(1)፣ 1677(1)፣ 1845 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 25567 እና 57114 ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ መሠረት ያላደረገ ነዉ የሚል ነዉ።

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡትን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል። በዚህም መሠረት ተጠሪ ታህሳስ 20 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የተሰጣቸዉ የወራሽነት ማስረጃ በይርጋ ምክንያት ሊሰረዝ እንደማይገባ ተጠቅሶ የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመጥቀስ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ተከራክረዋል። አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካች በስር ለከተማዉ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረዉ የወራሽነት ማረጋገጫ እንዲሰረዝ ነዉ። የሟች ወራሽ ላልሆነ ሰዉ የተሰጠ የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰረዝ መብት ያለዉ ሰዉ ክስ ማቅረብ እንደሚችል እና ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ማስረጃዉ የተሰጠዉ ሰዉ ወራሽ አለመሆኑ ከተረጋገጠ የሰጠዉን የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ መሰረዝ እንደሚችል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 997-999 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የምንገነዘበዉ ነዉ። የአመልካች አቤቱታም በዚሁ መሠረት የቀረበ ስለመሆኑ ከማመልከቻዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ ክስ የሚያቀርብ ሰዉ ተከሳሹ የወራሽነት መብት የሌለዉ መሆኑን በክሱ የማሳየት እና ይህንኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ተጠሪ አባታቸዉን ተክተዉ የሟች ወ/ሮ አዛለች አወቀ ህጋዊ ወራሽ ስለመሆናቸዉ አመልካች ክደዉ አይከራከሩም፤ ተጠሪ ሟችን የማይወርሱበት ሌላ ህጋዊ ምክንያት ስለመኖሩም ጠቅሰዉ አይከራከሩም። ከላይ እንደተገለጸዉ ለተጠሪ የተሰጠዉ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ ዳኝነት ሲጠይቁ አመልካች የጠቀሱት ምክንያት የወራሽነት ማስረጃዉን አዉራሽ ከሞተ ከ33 ዓመት በኂላ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ። ወይም በሌላ አገላለጽ ለተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ የተሰጣቸዉ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000 ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኂላ ነዉ የሚል ምክንያት ነዉ። ስለሆነም ተጠሪ አባታቸዉን

ተክተዉ ሚችን እንዳይወርሱ የሚከለክል በህግ የተመለከተ የጊዜ ገደብ አለ ወይ? የሚል ነጥብ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ ከፍትሐብሔር ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሦስት የይርጋ ዓይነቶች ያሉ ሲሆን፤ የመጀመሪያዉ በህግ የተወሰነ ጊዜ ካለፈ በኋላ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ክስ ወይም ዳኝነት ተቀባይነት እንዳይኖረዉ የሚከለክል የይርጋ ዓይነት ወይም በእንግሊዝኛዉ "period of limitation" በመባል የሚታወቅና በፍትሐብሔር ህጋችን አንቀጽ 1845 ላይ የተመለከተዉ ዓይነት ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ዓይነት ይርጋ አንድን ንብረት በህግ ለተወሰነ ጊዜ በመያዝ ወይም በመጠቀም በንብረቱ ላይ የባለቤትነት ወይም የባለይዞታነት መብት የሚገኝበትና በእንግሊዝኛዉ "acquisitive prescriptive" በመባል የሚታወቅ ሆኖ በፍትሐብሔር ህጋችን አንቀጽ 1168 ላይ የተመለከተዉ ዓይነት ሲሆን፣ ሦስተኛዉ በህግ ለተወሰነ ጊዜ ንብረትን ይዞ ባለመገኘት ወይም በንብረቱ ባለመጠቀም ወይም በህግ በተሰጠ መብቱ ባለመጠቀም የባለቤትነት ወይም የባለይዞታነት ወይም በአንድ ነገር የመጠቀም መብትን የሚያሳጣና በእንግሊዝኛዉ "extinctive prescriptive" በመባል የሚታወቅ ሆኖ በህጋችን አንቀጽ 1192 ላይ የተመለከተዉ ዓይነት ይርጋ ነዉ፡፡ ይህም በአጭሩ ሲቀመጥ የመጀመሪያዉ ይርጋ ዓይነት የተወሰነ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ማቅረብን የሚከለክል ሲሆን፣ በሁለተኛ እና ሦስተኛ ላይ የተመለከቱት ግን በህግ የተወሰነ ጊዜ ካለፈ በኋላ መብትን የማግኘት ወይም የማጣት ዉጤትን የሚያስከትሉ ናቸዉ፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች የተጠሪ መብት በይርጋ ታግዷል በማለት የሚከራከሩት የወራሽነት ማስረጃዉን የወሰዱት በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ መሆኑን ሲሆን፣ ይህ የይርጋ ደንብ የወራሽነት ማስረጃን ለማስረዝ ወይም ህጋዊ መብት በሌለዉ ሰዉ የተያዘ የዉርስ ንብረት እንዲለቀቅ የሚቀርብ ክስ የሚቀርብበትን ጊዜ የሚመለከት ነዉ፡፡ ይህም በባህሪዉ ክስ እንዳይቀርብ የሚከለክል (limitation of actions) ነዉ፡፡ አመልካች በጠቀሷቸዉ መዛግብት ላይ ይህ ሰበር የሰጣቸዉ ዉሳኔዎችም ይህንኑ መሠረት ያደረጉ ናቸዉ፡፡ ይሁንና በአመልካች ላይ የቀረበ ክስ ባለመኖሩ አመልካች ይህን እንደመከራከሪያ ሊያነሱ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በሌላም በኩል አንድ ሰዉ የወራሽነት ማስረጃን በተወሰነ ጊዜ ዉስጥ ከፍርድ ቤት ካልወሰደ ወይም ወራሽነቱን ካላሳወጀ የመዉረስ መብት እንደሚያጣ (extinctive prescriptive) በህግ የተመለከተ ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ የተሰጠ ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ የጠየቁት ዳኝነት ተቀባይነት የሌለዉ ሆኖ እያለ የስር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 1000(1) እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 120841 ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ ያለቦታዉ በመጥቀስ ማስረጃዉን በመሰረዝ የሰጠዉ ዉሳኔ በእርግጥም የህግ ስህተት በመሆኑ፣ የከተማዉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቱ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የሰጡት ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 36434 ላይ ነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ብ/ም**

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ 215583

ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ምስራቅ ሞገስ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገብረጻዲቅ አባይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262273 በቀን 02/09/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 275310 በቀን 28/11/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የጋብቻ ንብረት ክፍፍልን የተመለከተ ሲሆን ከአሁን በፊት እስከዚህ ሰበር ችሎት ደርሶ ችሎቱ በመ/ቁ 182455 በቀን 24/01/2013 ዓ.ም ባሳለፈው ውሳኔ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተዘጋውን የመ/ቁ 262273 አንቀሳቅሶ በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በተጠሪ ስም በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር የተቀመጠ ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሀምሳ ሺ.ህ) በግራቀኙ አለመግባባት ተፈጥሯል ከተባለበት ግዜ አንስቶ ያለውን ሙሉ የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርት በማስቀረብ ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም መዋል አለመዋሉን አጣርቶ የመሰለውን እንዲወስን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የተመለሰለት የስር ፍርድ ቤት አለመግባባት የተፈጠረው መቼ ነው የሚለውን ለማጣራት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቷል፡፡ ከባንኩ የተላከውን መግለጫም ተመልክቷል፡፡

በመጨረሻም በሰጠው ውሳኔ አመልካች አለመግባባቱ የተፈጠረው ከጥቅምት 2010 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን የገለጹ እና የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ከሚያዚያ 16/2010 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ከጥቅምት/2010 ዓ.ም በኋላ አለመግባባቱ መፈጠሩን ቢገልፁም በዚህ ጊዜ ስለመፈጠሩ በጉዳዩ ልክ አላስረዳችም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከሳሽ ክስ የመሰረተችው ሚያዚያ

17/2010 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ አለመግባባቱ የተፈጠረው ክስ በተመሰረተበት ከሚያዚያ 17 ቀን 2010 ዓ.ም ነው፡፡ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በጻፈው ደብዳቤም ከቀን 18/08/2010 ዓ.ም በኋላ የወጣ ገንዘብ የሌለ መሆኑን ገልጿል፡፡ በመሆኑም ከቀን 18/08/2010 ዓ.ም በኋላ የወጣ ገንዘብ የሌለ መሆኑ በመረጋገጡ በጋብቻ ወቅት እያሉ በተለያየ ጊዜ ወጪ የተደረገው ጥሬ ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ውሏል በማለት ፍርድ ቤቱ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የአዋሽ ባንክ በቀን 19/03/2011 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤም ከቀን 18/08/2010 ዓ.ም በኋላ የወጣ ገንዘብ የሌለ መሆኑን ገልጾ ያለው ተቀማጭ ገንዘብ ብር 505.00 (አምስት መቶ አምስት) መሆኑን የገለጸ ሲሆን ይህም የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 02/02/2014 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የስር ፍ/ቤት በአመልካች የቀረቡትን የሰው ምስክሮች ምስክርነት ሙሉ ይዘትና በፍ/ቤት ትዕዛዝ ከአዋሽ ባንክ ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ጋር በማገናዘብ በጥልቀት መርምሮ ውሳኔ ያለመስጠቱ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ነው፡፡ በአመልካች በኩል ሶስት ምስክሮች ቀርበው ሁለቱ ምስክሮች የተጠሪ የቅርብ ጓደኞች በመሆናቸው ገለልተኛ ምስክርነት መስጠት ስላልቻሉ እንጂ አመልካች ከተጠሪ ጋር ከሚያዚያ 2010 ዓ.ም በፊት በነበረን አለመግባባት ሽምግልና ሲቀመጡ የነበሩና በመካከላችን ያለውን አለመግባባት በቅርበት የሚያወቁ ሆነው እያለና ከ3ኛ ምስክር ምስክርነት እና ከተጠሪ ክርክር አኳያ ሲመዘን እምነት የማይጣልበት ስለሆነ የምስክሮቹ ቃል ሙሉ ይዘት ተጨምቆ ሲታይ ቢያንስ 3ኛው ምስክር በመካከላችን ከጥር ወር የጥምቀት በአል አካባቢ ጀምሮ ከባንክ ቡክ መደበቅ ጋር በተያያዘ መግባባት እንዳልቻልን መመስከሩ ከተጠሪ ጋር የነበረን አለመግባባት ምክንያት በባንክ ካለው ገንዘብ ጋር ተያይዞ እንደሆነ የተረጋገጠ ከመሆኑም በተጨማሪ ያለመግባባቱ ተጠሪ እንደሚለው ከሚያዚያ 16/2010 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን ከዚህ በፊት ቢያንስ ከጥር ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪም አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረብኩት የፍቺ አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስ በተደጋጋሚ በመካከላችን ግጭት እንደነበርና በሽማግሌ ስንፈታ መቆየታችንና መጋቢት 27/2010 ዓ.ም በድጋሚ ሽማግሌ ጠርተን ለማስማማት መቀመጣቸውን መግለጹ የሚያሳየው በእርግጥም አለመግባባቱ ተጠሪ እንደሚለው ከሚያዚያ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ሳይሆን ከዚያ በፊት እንደሆነ አመልካችም አለመግባባቱን ቀድሜ በሽምግልና ለመፍታት ሳደርግ የነበረውን ጥረት የሚያረጋግጥ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት የወሰነው ውሳኔ ክርክራችንና ማስረጃን መሰረት ያላደረገ ነው፡፡ ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አኳያ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 261(2) አግባብ በቅድሚያ ምስክርነቴን እንድሰጥ ቢደረግ ኖሮ አለመግባባቱ መች፣ በምን ምክንያት እንደሆነ፣ ችግሩን በሽምግልና ለመፍታት ያደረኩትን ጥረት እና በተጠሪ የተደረገው ወጪ ለትዳር ጥቅም እንዳልዋለ ማስረዳት ስችል ፍ/ቤቱ ጥያቄዬን አለመቀበሉ ሳያንስ አለመግባባቱ ከሚያዚያ ወር 2010 ዓ.ም በፊት ጀምሮ እንደነበርና አለመግባባቱንም በሽምግልና ለመፍታት ያደረኩት ጥረት እንዳልነበር

በማተት የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ነው፡፡ ከአዋሽ ባንክ የቀረበውም ማስረጃ ባቀረብኳቸው የሰው ምስክሮች በተረጋገጠው እንኳ አለመግባባቱ ከተፈጠረበት ከጥር ወር 2010 ዓ.ም በኋላ ያለው እንቅስቃሴ ሲታይ ወጪ ብቻ እንጂ ገቢ የማያሳይ ከመሆኑ በተጨማሪ የካቲት 06/2010 ዓ.ም ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) ወጪ አድርጎ በድጋሚ መጋቢት 20/2010 ዓ.ም ላይ 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ብር በአንድ ግዜ ወጪ ማድረጉ እንዲሁም በዚሁ መዝገብ ቀድሞ ከአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ በቀረበው የባንክ ስቴትመንት ላይ በተመሳሳይ መጋቢት 20/2010 ዓ.ም 690,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ሺህ) ብር ከሂሳቡ ላይ ወጪ መደረጉ ተደምሮ ሲታይ ካለን የኑሮ ወጪ አንጻር ሁለት ወር ባልሞላ ግዜ ውስጥ ይህን ያህል ከፍተኛ ወጪ ሊያስወጣ የሚችልበት ሁኔታ በሌለበት የስር ፍ/ቤት ለተጠሪ በማስረጃ ያልተደገፈ መከራከሪያ ክብደት በመስጠት የሰጠው ውሳኔ ማስረጃዎችን በሙሉ ይዘት ያልመረመረው መሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የተጠሪን ገንዘብ የማሸሽ ተግባር ያረጋገጠ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ከባንኩ በቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ አስተያየት እንድሰጥ ሳያደርግና በጉዳዩ ላይ ምስክርነቴን እንድሰጥ ሳያደርግ ውሳኔ መስጠቱ ኢ-ህገመንግስታዊና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ቢያንስ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 182455 በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ከሚያዚያ 17 ቀን 2010 ዓ.ም በፊት በተጠሪ ከአዋሽ ባንክ ወጪ የተደረገው 750,000.00 (ሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ) ብር ለትዳር ጥቅም አልዋለም ተብሎ የዚህን ገንዘብ ግማሹን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያካፍል እንዲወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል አለመግባባት የተፈጠረው ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ መሆኑን በመውሰድ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 25/06/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል አለመግባባት የተፈጠረው ከ17/08/2010 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ከዚህ ግዜ በፊት በጋብቻ ውስጥ እያሉ የወጣው ገንዘብ ለጋራ የትዳር ጥቅም ውሏል በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው፤ ከፍተኛው ፍ/ቤትም ቀደም ሲል ሰበር ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ 182455 ጭብጥ ይዞ በመለሰው መሰረት አለመግባባቱ የተፈጠረበትን ግዜ በምስክሮች አረጋግጦና አለመግባባቱ ከተፈጠረ አንስቶ ከባንክ ወጪ የተደረገ ገንዘብ አለመኖሩን ባንኩ በላከው ሰነድ ማስረጃ አጣርቶና መርምሮ ውሳኔውን ማጽናቱ አግባብ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል አለመግባባት የተፈጠረው ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ መሆኑን የወሰደው ከዚያ በፊት በሰላም አብረን እንኖር እንደነበርና ክስ ከቀረበበት ግዜ ጀምሮ አለመግባባት የተፈጠረ ስለመሆኑ አመልካች በቆጠሯቸው ምስክሮች በመረጋገጡ እንዲሁም አለመግባባቱ ከመፈጠሩ በፊት ጋብቻችን ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ለጋራ ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠርና የህግ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት አለመግባባት የተፈጠረበትን ጊዜ በመውሰድ ውሳኔ መስጠቱ አግባብ

በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሰረቱ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(1) ስር በግልጽ እንደተመለከተው ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኙት ገቢ ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል፡፡ ስለሆነም በጋብቻው ጊዜ ያገኙት ገቢና ያፈሩት ንብረት የጋራ መሆኑ አከራካሪ አይሆንም፡፡ ከዚህም ሌላ በርከት ያለ ገንዘብ በትዳር ጊዜ በአንደኛው ተጋቢ መውጣቱ ሳይካድ እና ይኸው ገንዘብ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉ ክርክርና ማስረጃ በሌላኛው ወገን ሲቀርብ ገንዘቡ በሙሉ ለትዳር ጥቅም ውሏል የሚል ወገን የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ማስተባበል ይጠበቅበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ እስከዚህ ሰበር ችሎት የዘለቀው የጋብቻ የንብረት ክፍፍል ጥያቄን አስመልክቶ አስቀድሞ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ፍቺና የንብረት ክፍፍል ከተጠየቀበት ጥቂት ቀናት አስቀድሞ በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በተጠሪ ስም በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር ተቀምጦ የነበረውና ወጪ የሆነው ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ) በግራቀኙ አለመግባባት ተፈጥሯል ከተባለበት ጊዜ አንስቶ ያለውን ሙሉ የሂሳብ እንቅስቃሴ በማየት ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም መዋል አለመዋሉን ተጣርቶ ይወሰን ተብሎ ተመልሷል፡፡ አመልካች ባቀረቧቸው ምስክሮች በተለይ በ1ኛ ምስክሯ ከጥር ወር ጀምሮ በሂሳብ ደብተር የተነሳ (የሂሳብ ደብተር ስለደበቀባት) አለመግባባት መኖሩን፤ እንዲሁም በሌሎቹም ምስክሮች በሽምግልና መታየታቸውን አስረድተዋል፡፡

በአንጻሩ ተጠሪ ገንዘቡ በባንክ እንደነበር እና በእርሳቸው መውጣቱን ክደው ያልተከራከሩ በመሆኑ ይኸው በርከት ያለ ገንዘብ በርግጥም ለትዳር ጥቅም መዋሉን ክርክርና ማስረጃ በማቅረብ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁንና ተጠሪ አለመግባባቱ የተፈጠረው ፍርድ ቤት ክስ ሲቀርብ (ከሚያዚያ 16/2010 ዓ.ም ጀምሮ) ነው እንዲሁም አለመግባባቱ ከመፈጠሩ በፊት ጋብቻችን ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ለጋራ ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠርና የህግ ግምት የሚወሰድበት ነው በማለት ከመከራከራቸው በቀር የተጠቀሰው ገንዘብ ለትዳር ጥቅም መዋሉን አላሳዩም፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው እንደተያዘው ጉዳይ አይነት በርከት ያለ ገንዘብ በትዳር ጊዜ በተጠሪ መውጣቱ ሳይካድ እና ይኸው ገንዘብ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉ ክርክርና ማስረጃ በአመልካች በኩል ሲቀርብ ገንዘቡ በሙሉ ለትዳር ጥቅም ውሏል የሚሉት ተጠሪ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ማስተባበል ይጠበቅባቸዋል፡፡ በአንፃሩ አለመግባባቱ የተፈጠረው የፍቺ ክስ በቀረበበት ቀን ነው ከዚህ ቀን ቀደም ብሎ በጥቂት ቀናት ውስጥ ከባንክ የወጣው ገንዘብ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ይገመታል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህጉን ትክክለኛ ይዘትና መንፈስ የተከተለ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ሙሉ ክርክሩንና የቀረበውን ማስረጃ ከህጉ ጋር አገናዝቦ ሳይመረምር እንዲሁም በዚህ ሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ በመሸሽ ተጠሪ በአጭር ጊዜ ከባንክ ያወጣው ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ስለማዋሉ ማስረጃ አቅርቦ የአመልካችን ክርክር ባላስተባበለበት ሁኔታ ባንኩ ከቀን 18/08/2010 ዓ.ም በኋላ የወጣ ገንዘብ የሌለ መሆኑን አረጋግጧል እንዲሁም በጋብቻ ወቅት እያሉ በተለያየ ጊዜ ወጪ የተደረገው ጥሬ ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ውሏል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ እና ያሳለፈው ውሳኔ የሚነቀፍ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህን ሳያርም ማለፉ አላግባብ ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262273 በቀን 02/09/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 275310 በቀን 28/11/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ፍቺና የንብረት ክፍፍል ከተጠየቀበት ጥቂት ጊዜ አስቀድሞ በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በተጠሪ ስም በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር ተቀምጦ የነበረውና ወጪ የሆነው ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ) የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት በመሆኑና ተጠሪም ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም አለማዋሉን በተመለከተ የቀረበባቸውን ክርክርና ማስረጃ ስላላስተባበሉ የዚህን ገንዘብ ግማሽ ብር 375000.00 (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ) ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ.መ.ቁ 196814

ጥቅምት 3 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ሃዲያ ያሲን ሽዩቦ - ጠበቃ በቃሉ ለማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሁሴን ሰኒ ኢብራሂም - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ/ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት በመ.ቁ 62149 በ24/7/11ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 243190 በ14/11/12ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ9/2/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት አቤቱታ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 በተጠሪ ስም የተገዛ በሻጭ አቶ ደረጀ ደበበ ስም የተመዘገበ ቤት እንዲሁም የቤት ቁሳቁሶችን በመዘርዘር እንድንከፋፈል እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካች የጋራ ሀብት ነው በማለት የጠቀሱት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነው ቤት አመልካች ትዳራቸውን ጥለው በሄዱበት ከ1996ዓ.ም እስከ 2008ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ከሁለተኛ ባለቤቴ ጋር ያፈራሁት ነው፡፡ አመልካች የጋራ ነው ባሉበት ቤት ላይ ያደረጉት አስተዋጽኦ የሌለ ስለሆነ ድርሻ ሊኖራቸው አይገባም በማለት እንዲሁም የቤት ቁሳቁሶችንም በተመለከተ መልስ ከሰጡ በኋላ በአመልካች አቤቱታ ውስጥ ያልተካተቱ በማለት የቤት ቁሳቁሶችን በመዘርዘር እንድንካፈል እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የምስክሮችንም ዝርዝር አቅርበዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ዘርዝረው ያቀረቡትን የቤት ቁሳቁሶች በተመለከተ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ አቅርበዋል፡፡ መቃወሚያው በብይን ታልፏል፡፡

በስር ጣልቃገብ (አሁን ሰበር ክርክሩ ላይ የሌሉት ወ/ሮ ነፊሳ ስሩር) ባቀረቡት የጣልቃገብነት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በ2001ዓ.ም ጋብቻ ከመሰረትን በኋላ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነ ቤት ተጠሪ በ29/1/03ዓ.ም ገዝተዋል፡፡ ቤቱ የተፈራው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረን ባለንበት ግዜ ስለሆነ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያፈሩት ንብረት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ለጉዳዩ አግባብ ናቸው ያላቸውን ጭብጦች በመያዝ አከራካሪውን በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነውን ቤት በተመለከተ በክስ መሰማት ወቅት አመልካች ይህ ቤት በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 ወይራ በሚባል ቦታ የነበረን የጋራ ቤት በመሸጥ ከተገኘው ገንዘብ ላይ ተጠሪ ብር 200,000.00 ሰጥተው እንዲሁም አመልካች ከውጭ ሀገር ብር 130,000.00 በመላክ ከወንድማቸው ብር 30,000.00 ተበድረው በመጨመር የተገዛ ስለሆነ የጋራ ነው፤ ገንዘቡን የላኩት በእህቴ በኩል ነው ሲሉ መከራከራቸውን እንዲሁም ተጠሪ በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 ወይራ በሚባል ቦታ የነበረንን ቤት የሸጡት የአመልካች እህት ናቸው፤ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ የደረሰኝ የለም፡፡ አመልካች ከ1996ዓ.ም እስከ 2008ዓ.ም ድረስ ባህር ማዶ የነበሩ በመሆናቸው በቤቱ ላይ ምንም አስተዋጽኦ አላደረጉም፤ ስለሆነም ድርሻ የላቸውም በማለት መከራከራቸውን በመግለጽ እንዲሁም አመልካች ከ1996ዓ.ም እስከ 2008ዓ.ም ድረስ ባህር ማዶ የነበሩ ስለመሆናቸው ክርክር ያልተነሳበት መሆኑን ከገለጸ እና አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ እንዲሁም የግራቀኙ የጋራ ሀብት እንደነበረ የተገለጸው በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 ውስጥ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ይገኝ የነበረው ቤት ማህደር ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ትእዛዝ ሰጥቶ ትእዛዙ ለተገቢው አካል ባለመድረሱ ማህደሩ ሊቀርብ ባለመቻሉ በማለት ትእዛዙን ካለፈ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አከራካሪው በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 በሆነው ቤት ላይ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑን በሰውም ሆነ በሰነድ ማስረጃ አላረጋገጡም በማለት ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረግ እንዲሁም የቤት ቁሳቁሶችን በተመለከተም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው አከራካሪውን በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነውን ቤት በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 327(3) መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የሌለው መሆኑን እንዲሁም የተጨማሪ ማስረጃ ላቅርብ ጥያቄን በተመለከተ አመልካች የጠየቁትን ማስረጃ በስር ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት ስላለማግኘቱ አልተረጋገጠም በማለት፤ ማስረጃውም ለተያዘው ጉዳይ ተገቢ ሆኖ አለመገኘቱን በመግለጽ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች በመቃወም ሲሆን ይዘቱም አከራካሪውን በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነውን ቤት በተመለከተ በአመልካች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ቤቱ የተገዛው ቀደም ሲል አመልካች እና ተጠሪ በትዳር እያለን ያፈራነው

በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 ልዩ ስሙ ወይራ ሰፈር በተባለው የነበረንን ቤት በብር 280,000.00 ሸጠን ብር 80,000.00 ተጠሪ አጥፍቶ ቀሪው ብር 200,000.00፤ አመልካች ከውጭ ሀገር ብር 130,000.00 ልኬ ብር 37,000.00 ከአመልካች ወንድም ተወስዶ በብር 367,000.00 የተገዛ መሆኑን በተመሳሳይ ሁኔታ አስረድተዋል፡፡ ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃ አላስተባበለም፡፡ አመልካች በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤ.ቁ አዲስ የሆነውን ቤት የሸጥን መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ከኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር እንዲቀርብልኝ ትእዛዝ ተሰጥቶ የወረዳው አስተዳደርም ፋይሉን አላገኘሁም ግዜ ይሰጠኝ በማለት ጠይቆ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ የስር ፍ/ቤቱ ለኮ/ቀ/ክ/ከተማ ይዞታና አስተዳደር የሽግግር ግዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ዴስክ ትእዛዝ እንዲሰጥልኝ አቤቱታ አቅርቤ አቤቱታውን ባለመቀበል አልፎታል፡፡ የአመልካች ምስክሮች በበቂ ሁኔታ ያስረዱ መሆኑን የስር ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ አትቶ እና ከባንክ የቀረበለትን ማስረጃ ባለመመልከት አመልካች በቤቱ ላይ አስተዋጽኦ አላደረገችም በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንንም የይግባኝ ሰሚው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ማጽናቱ የቤተሰብ ህግ አ/ቁ 213/92 አንቀጽ 62(2) ድንጋጌ ውጪ ስለሆነ ሊታረም ይገባል፡፡ ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆኑ አመልካች የጋራ የሆነው ንብረት ላይ አስተዋጽኦ አላደረገችም በማለት በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አመልካች አከራካሪውን በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነውን ቤት በጋራ አፍርታለች፤ ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ግዜ የተፈራ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ተከራካሪ ወገኖች በትዳር ውስጥ ባሉበት ግዜ የነበራቸው የጋራ ቤት ተሽጦ የተገዛ ስለመሆኑ በተገለጸበት አመልካች በቤቱ ላይ አስተዋጽኦ ያላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ4/8/13ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ2/9/13ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ አመልካች አቤቱታ ያቀረበችበት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነውን የመኖሪያ ቤት አመልካች ትዳሯን ጥላ በሄደችበት ከ1996ዓ.ም እስከ 2008ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ከሁለተኛ ባለቤቴ(በስር ፍ/ቤት ጣልቃገብ የነበሩት ወ/ሮ ነፊሳ ስሩር) ጋር በጋራ ጥረታችን ያፈራነው ንብረት እንጂ አመልካች ምንም አይነት አስተዋጽኦ ያላደረገችበት እና ትዳሩን ጥላው በሄደችበት ግዜ ያፈራነው ንብረት ነው፡፡ አንድ ተጋቢ ጥሎ በሄደበት እና ምንም አስተዋጽኦ ያላደረገበትን ንብረት በተመለከተ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 43988 (ቅጽ 11) ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንጻር አመልካች በቤቱ ላይ ያደረገችው አስተዋጽኦ የሌለ እና በሰነድም ሆነ በሰው ማስረጃ ያላስረዳች በመሆኑ ከዚህ አንጻር በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

አመልካች በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤ.ቁ አዲስ የሆነውን ቤት በተመለከተ በስር ፍ/ቤት እንዳያቀርቡ የተከለከሉት ማስረጃ የለም፡፡ ይልቁንም አመልካች ማስረጃውን ከሚመለከተው አካል እንዲያቀርቡ በችሎት በተደጋጋሚ ግዜ ታዘው ትእዛዙን ወደ ጎን በመተው ትእዛዝ ላልተጻፈለት አካል በማድረሳቸው

ችሎቱ ትእዛዙን ማለፉ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ማስረጃው ለተያዘው ጉዳይ ተገቢነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በ19/9/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች አከራካሪውን በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነውን ቤት በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አከራካሪው በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነው ቤት የተገዛው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያልተቋረጠ ጋብቻ በነበረበት ወቅት እንዲሁም ተጠሪ እና በስር ክርክር ጣልቃገብ የነበሩት ወ/ሮ ነፊሳ ስሩር በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ወቅት ስለመሆኑ የክርክሩ ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በዚህ አከራካሪው ቤት ላይ አመልካች አስተዋጽኦ የሌላቸው ስለመሆኑ ማስረጃዎችን የመስማት፤ የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን የተሰጠው የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍሬነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊታይ የሚገባው ነጥብ አመልካች ከላይ በተገለጸው ቤት መፈራት ላይ አስተዋጽኦ የለሽም መባላቸው ቤቱን በተመለከተ በአመልካች ላይ የሚያመጣው ውጤት ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡

በስር ክርክር ጣልቃገብ ሆና የተከራከረችው የተጠሪ ባለቤት ወ/ሮ ነፊሳ ስሩር የተጠሪ ሚስት በመሆኗ እና አከራካሪው ቤት የተገዛው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ወቅት በመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አ/ቁ 213/92 አንቀጽ 62(2) ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው እንደሚሆን ከደነገገው አንጻር የቤቱ ግማሽ (50%) ድርሻ ባለመብት የምትሆን ሲሆን አመልካች ደግሞ ቤቱ በተፈራበት ወቅት ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ያልተቋረጠ የነበረ በመሆኑ በቤቱ መፈራት ላይ አስተዋጽኦ የላትም መባሉ የቤቱ ቀሪ ግማሽ ድርሻ(50%) ከሆነው የተጠሪ ድርሻ ውስጥ ግማሹን (25%) ድርሻዋን የሚያሳጣት አይሆንም፡፡

ስለሆነም ከላይ በተገለጸው ምክንያት የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ከተጠሪ የቤቱ ግማሽ ድርሻ(50%) ላይ ግማሽ ድርሻ(25%) አላት በማለት ውሳኔ መስጠት ሲገባው አመልካች በቤቱ ላይ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ከላይ በተገለጸው መልኩ ሊያርም ሲገባው ውሳኔውን በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ/ምድብ ችሎት 2ኛ ቤተሰብ ችሎት በመ.ቁ 62149 በ24/7/11ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ/ምድብ ችሎት 2ኛ ቤተሰብ ችሎት በመ.ቁ 62149 በ24/7/11ዓ.ም አመልካች በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 በሆነው ቤት ላይ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 243190 በ14/11/12ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 327 የሆነው ቤት ግማሽ (50%) የተጠሪ ድርሻ ላይ ግማሹ (25%) የአመልካች በመሆኑ ከተቻለ የቤቱ 25% ለአመልካች በአይነት ሊሰጣቸው፣ ካልተቻለ የቤቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ የግምቱን 25 % ለአመልካች ሊሰጣቸው እና ተጠሪ ቤቱን እንዲያስቀሩ፣ይህ ካልተቻለ ቤቱን አመልካች እና ተጠሪ በስምምነት ሸጠው ከሽያጩ ገንዘብ ውስጥ 25% ለአመልካች ሊሰጥ፣ ይህም ካልተቻለ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ ውስጥ 25% ለአመልካች ሊከፈላቸው ይገባል በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተወስኗል፡፡
4. ከላይ በውሳኔው ክፍል ተራ ቁጥር 1፣2 እና 3 ላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች ውጪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ/ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት በመ.ቁ 62149 በ24/7/11ዓ.ም በሌሎች ንብረቶች ላይ የሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
7. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ/መ/ቁጥር 212845

ቀን 22/9/2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ገነት ገለቱ ከጠበቃ ተስፋዬ አድማሱ ጋር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዮሀንስ ዛቲ ጠበቃ ጌትነት ገሰሰ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 271488 ግንቦት 16 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 61476 የካቲት 4 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት የጋራ ንብረታችን ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የጋራ ንብረት አይደለም ተብሎ መወሰኑ፣ 3 ቀርጥ መሬት የጋራ ንብረት ሊባል እንደሚገባ ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ አምኖ መልስ ሰጥቶ እያለ በልማት ምክንያት በመንግስት ተወስዷል ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበችው ክስ በከሳሽ እና ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በ21/7/2009 ዓ/ም በፍቺ ቀሪ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ከተከሳሽ ጋር በጋራ ያፈራነው 1. በተከሳሽ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ በቀድሞ አጠራር ፈጨ ቀበሌ በኋላ ወረዳ 13 ውስጥ የሚገኝ በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ቤት 2. የእርሻ መሬታችን ለልማት በመወሰዱ ምክንያት መንግስት የሰጠን የመሬት ካሳ ተጣርቶ ድርሻ ይካፈለኝ 3. በአመልካችና ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ 3 ቀርጥ

የእርሻ መሬት ግማሹን እንዲያካፍለኝ 4. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በዳሽን ባንክ አቃቂ ቅርንጫፍ፣ በህብረት ባንክ፣ በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ በአቢሲኒያ ባንክ በተከሳሽ ስም ያለ ገንዘብ ተጣርቶ ድርሻዬ ይካፈለኝ 5. የእርሻ መሬታችን በመንግስት በመወሰዱ በምትክ የተሰጠን ባለ 3 መኝታ ኮንዶሚኒየም እና ለቤት ማደሻ የሚሰጠው ገንዘብ ድርሻዬን ያካፍለኝ 6. የሲሚንቶ ማቡኪያ፣ ጋሪ ከነ ፈረሱ ድረሻዬን ያካፍለኝ ስትል ጠይቃለች፡፡ ተከሳሽም ከሳሽ ትዳራዋን ትታ የሄደችው በ1992 ዓ/ም ሲሆን እስከ ሄደችበት ጊዜ ድረስ በጋራ ያፈራነው የቤት ቁሳቁስ ብቻ ነው፡፡ አንድ ተጋቢ የትዳር ግንኙነት ትቶ በሄደበት ወቅት የተፈራ ንብረት ለመካፈል መብት የሌለው ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 43988 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በተከሳሽ ስም የሚገኝ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ በ500 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው የመኖሪያ ቤት ከወላጅ አባቴ በውርስ ያገኘሁትና ካርታ ፕላን የተሰጠኝ በ2001 ዓ/ም ሲሆን የግል ንብረቴ ነው፡፡ የእርሻ መሬታችን በልማት በመወሰዱ የተከፈለ ካሳ ድርሻዬ ይከፈለኝ ያለችው መሬቱን በውርስ ያገኘሁት ነው፡፡ ከሳውም የተከፈለው በ1992 ዓ/ም ነው፡፡ አሁን ያለው መሬት 2 ቀርጥ ሲሆን በወታደርነት ባበረከትኩት አገልግሎት የተሰጠኝ ነው፡፡ ያገኘሁትም ከከሳሽ ጋር ሳንጋባ በፊት በ1983 ዓ/ም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለው የሂሳብ ቁጥር የተከፈተው ከሳሽ በ1992 ዓ/ም ትዳርዋን ትታ ከሄደች በኋላ በ1997 ዓ/ም ነው፡፡ የአቢሲኒያ ባንክ የተከፈተው በ2011 ዓ/ም ነው፡፡ ባለ 3 መኝታ ኮንዶሚኒየም ቤት ከቤት ማደሻ ገንዘብ ጋር የጠየቀችውን በተመለከተ ከወላጆቼ በውርስ ባገኘሁት መሬት የተሰጠ ካሳ በመሆኑ ልትካፈል አይገባም፡፡ የሲሚንቶ ማቡኪያ እና የፈረስ ጋሪ የሉም፣ አሉ ከተባለም ደርሻ የላትም በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 61476 የካቲት 4 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር በጋራ ያፈሩት ስለመሆኑ አላስረዳችም ተከሳሽ ይዞታው የአባቱ፣ ቤቱ የወንድሙ መሆኑን አስመስክሯል በመሆኑም የጋራ ንብረት አይደለም፡፡ 2 ቀርጥ መሬት በተመለከተ ተከሳሽ ከውትድርና ስመለስ የተሰጠው መሆኑ የተከሳሽ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ ይሁንና በትዳር ባሉ ጊዜ የተገኘ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው፡፡ ይህ መሬት በልማት ምክንያት የተወሰደ በመሆኑ የሚካፈሉት መሬት የለም፡፡ በልማት ምክንያት ለተጠሪ የተከፈለ ካሳ ከጽ/ቤቱ የቀረበው ሪፖርት የተከፈለው ካሳ ተነሽ አርሶ አደሩ ከ3 ልጆቼ ጋር ተመዝግቦ የተከፈለ ሲሆን ከሳሽ በባለቤትነት ያልተመዘገበችና ተከሳሽ ጋብቻ የሌለው መሆኑ ማስረጃ ቀርቦ ኮንዶሚኒየም የተሰጠው ሲሆን በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት በመሆኑ የካሳ ገንዘቡና ኮንዶሚኒየም ቤቱ የጋራ ንብረት ነው፡፡ ከሳሽና ተከሳሽ ፍቺ የፈጸሙት በ21/7/2009 ዓ/ም ሲሆን ከሳሽ አረብ ሀገር የሄደችና እየመጣች የጋራ ኑሮዋቸውን የምትደግፍ መሆኑ የተመሰከረ ሲሆን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለው ገንዘብ ፍቺ እስከተፈጸመበት 2009 ዓ/ም ያለው የጋራ ንብረታቸው ነው፡፡ በሌላ ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ የለም፡፡ የሲሚኒቶ ማቡኪያ እና የጋሪ ፈረስ ስለመኖራቸው በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ታልፏል ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በመ/ቁጥር 271488 ግንቦት 16 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት

በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኝዋን ውድቅ አድርጎል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርባለች፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የአሁን አመልካች በማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 145 እንዲቀርብላት የጠየቀችው ማስረጃ አስቀርቦ ሳያጣራ እንዲሁም መሬት ልማት ማኔጅመንት በ21/5/2013 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ 500 ካ/ሜ ይዞታ በተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑ እየተገለጸ በማስረጃ አላስረዳችም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሚያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት እና በአመልካችና ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ከሳሽ 3 መሬት ቀርጥ የምትለው ተከሳሽ 2 ቀርጥ መሬት ከውትድርና ስመለስ የተሰጠኝ ነው የሚለው የእርሻ መሬት በተመለከተ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ባቀረበችው ክስ በተከሳሽ ስም ተመዝግቦ ያለና በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ በቀድሞ አጠራር ፈጨ ቀበሌ በኳላ ወረዳ 13 ውስጥ የሚገኝ በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ቤት 2. የእርሻ መሬታችን ለልማት በመወሰዱ ምክንያት መንግስት የሰጠን የመሬት ካሳ 3. በአመልካችና ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ 3 ቀረጥ የእርሻ መሬት ድርሻዬን ያካፍለኝ የሚል ሲሆን **ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ ደግሞ** በተከሳሽ ስም የሚገኝ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ በ500 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው የመኖሪያ ቤት ከወላጅ አባቴ በውርስ ያገኘሁትና በ2001 ዓ/ም ካርታ ፕላን የተሰጠኝ የግል ንብረቴ ነው፡፡ የእርሻ መሬታችን በልማት በመወሰዱ የተከፈለ ካሳ ድርሻዬ ይከፈለኝ ያለችው መሬቱን በውርስ ያገኘሁትና ካሳውም የተከፈለው በ1992 ዓ/ም በመሆኑ የሚካፈላት ካሳ የለም፡፡ አሁን ያለው መሬት 2 ቀርጥ ሲሆን በወታደርነት ባበረከትኩት አገልግሎት የተሰጠኝ በመሆኑ ልትካፈል አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር በጋራ ያፈሩት ስለመሆኑ አላስረዳችም ተከሳሽ ይዞታው የአባቱ፣ ቤቱ የወንድሙ መሆኑን አስመስክሯል በመሆኑም የጋራ ንብረት አይደለም፡፡ 2 ቀርጥ መሬት በተመለከተ ተከሳሽ ከውትድርና ስመለስ የተሰጠው መሆኑ የተከሳሽ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ ይሁንና በትዳር ባሉ ጊዜ የተገኘ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው፡፡ ይህ መሬት በልማት ምክንያት የተወሰደ በመሆኑ የሚካፈሉት

መሬት የለም ሲል ወስኗል፡፡ **የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 37106 ላይ በሰጠው ውሳኔ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ ሳይደረግ የሚሰጥ ውሳኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡** ግራ ቀኙን ያከራከራቸው በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ቤት በተመለከተ የአሁን አመልካች በጠየቀችው ዳኝነት በአሁን ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ፣ የአሁን አመልካችና ተጠሪ በትዳር እያሉ ሲጠቀሙበት የነበር መሆኑን በመጥቀስ የጋራ ንብረት ስለሆነ ያካፍለኝ ብላለች፡፡ ከሳሽ ይህን ቤት የጋራ ንብረት ነው ስትል ላቀረበችው ዳኝነት፣ ያጋራ ንብረት ነው ያለችበት ምክንያት በትዳር ውስጥ ስላፈሩት ነው ወይስ የግል ንብረት የነበረውን በጋብቻቸው ጊዜ የጋራ ያደረጉት ስለመሆኑ መለየት ያለበት ጭብጥ ነው፡፡ የጋራ ንብረት ነው ያለችበት ምክንያት በትዳራችን ወቅት አፍርተናል የሚል ከሆነ የተሻሻለው **የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ድንጋጌ አንጻር የአሁን አመልካች የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የህግ ግምት የሚወሰድ እና የአሁን ተጠሪ የግል ንብረት ነው የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ የግል ንብረቱ ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ነው፡፡** ከሳሽ የአሁን አመልካች የግል ንብረቱ የነበረውን በጋብቻቸው የጋራ ንብረት ሆኗል የሚል ምክንያት ካላት ደግሞ ከሳሽ የግል ንብረት የጋራ ሆኗል የምትልበት ክርክር የማስረዳት ግዴታ የሚጠበቅባት ነው፡፡ የፌደራል የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 63(1) አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት አንደሆነ ይቆጠራል ሲል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ይሄው አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 86(1) ባልና ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን መልሶ የመውሰድ መብት እንደሚኖረው ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ያከራከረው በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ የግሌ ነው ሲል ላቀረበው ክርክር የግሉ ስለመሆኑ ማስረዳት የሚጠበቅበትና የግል ንብረት መሆኑን ካሳየ ከሳሽ የአሁን አመልካች የግል ንብረቱ የጋራ ሆኗል ክርክር ካላት ይህን ለማስረዳት የሚጠበቅባት ነው፡፡ ይሁንና የስር ፍ/ቤቶች ያከራከረው ቤት በተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ስም ተመዝግቦ ያለ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በትዳር ባሉበት ጊዜ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ባልተካደበት የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የተቀመጠውን የህግ ግምት የአሁን ተጠሪ የግል ንብረቱ መሆኑን በማስረጃ ማስረዳት እየተገባው ከሳሽ የአሁን አመልካች የጋራ ንብረት መሆኑን አላስረዳችም መባሉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተከሳሽ ከወላጆቹ በውርስ ያገኘሁት ነው የሚል ክርክር አቀርቦም እያለ የአባቱና የወንድሙ ንብረት መሆኑ ተመስክሯል በሚል የተሰጠው ውሳኔ የግራ ቀኙን ክርክርና የባልና ሚስት ንብረት የቤተሰብ ህግ ደንጋጌን ያልተከተለ ግልጽ ያልሆነ ውሳኔ መሆኑን መረዳት የሚቻል ነው፡፡

ሌላው የአሁን አመልካች የጋራ ንብረታቸን ነው ስትል እንዲከፈላት የጠየቀችው ካሳ የተከፈለበት የመሬት ይዞታ እና በክርክራቸው ወቅት የነበረ የእርሻ መሬትን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም ካሳ የተከፈለበት የእርሻ መሬት በውርስ ያገኘሁት ነው፣ ይካፈለኝ ያለችው የመሬት ይዞታ ደግሞ

ከውትድርና ስመለስ ላደረኩት አገልግሎት የተሰጠኝ የግል ንብረቴ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ከግራ ቀኙ ክርክር የምንረዳው ሁለት ቦታ ያሉ የመሬት ይዞታዎች አንዱ ካሳ የተከፈለበት አንዱ ደግሞ በክርክራቸው ወቅት ያለ መሆኑን ነው፡፡ **ይሁንና የስር ፍ/ቤቶች በነዚህ የመሬት ይዞታዎች ላይ ግልጽ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር በተገቢው ማስረጃ ሳያጣሩ ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ከውትድርና ስመለስ ተሰጠኝ የሚለውንና መኖሩን የገለጸውን የመሬት ይዞታ ካሳ ተከፍሎበታል ከተባለው መሬት ጋር አንድ በማድረግ ካሳ ተከፍሎበት በመንግስት በመወሰዱ የምትካፈለው መሬት የለም ሲል** የሰጠው ውሳኔ ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ የተሰጠ ውሳኔ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 271488 ግንቦት 16 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 61476 የካቲት 4 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1. በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ የሚገኝ በ500 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን ቤት በተመለከተ ከሳሽ የጋራ ንብረት ነው ስትል ላቀረበችው ዳኝነት የጋራ ንብረት ነው ያለችበት ምክንያት በትዳር ውስጥ አፍርተናል ነው ወይስ የግል ንብረት የጋራ ሆኗል የሚል ስለመሆን አለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር በመለየት፣ የጋራ ንብረት ነው ያለችበት ምክንያት በትዳራችን ወቅት አፍርተናል የሚል ከሆነ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ድንጋጌ አንጻር የአሁን አመልካች የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የህግ ግምት የሚወሰድ እና የአሁን ተጠሪ የግል ንብረት ነው የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ የግል ንብረቱ ስለመሆኑ ባቀረበው ማስረጃ እንዲያስረዳ በማድረግ፣ ከሳሽ የአሁን አመልካች የግል ንብረቱ የጋራ ንብረት ሆኗል የሚል ምክንያት ክርክር ካላት ደግሞ ከሳሽ የግል ንብረት የጋራ ሆኗል የምትልበት ክርክሯን ባቀረበችው ማስረጃ እንድታስረዳ በማድረግ እንዲሁም ተገቢውን ማስረጃ በማስቀረብ አጣርቶ እንዲወስን፣ 2. የአሁን አመልካች የጋራ ንብረታቸን ነው ስትል እንዲካፈላት የጠየቀችው ሁለት ቦታዎች ያሉ ካሳ የተከፈለበት የመሬት ይዞታ እና በክርክራቸው ወቅት የነበር የእርሻ መሬት መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን የአሁን ተጠሪም ካሳ የተከፈለበት የእርሻ መሬት በውርስ ያገኘሁት ነው፣ ይካፈለኝ ያለችው የመሬት ይዞታ ደግሞ ከውትድርና ስመለስ ላደረኩት አገልግሎት የተሰጠኝ የግል ንብረቴ ነው የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ እነዚህን የመሬት ይዞታዎች በመለየት ባቀረቡት ማስረጃና ከተገቢው አካል በማጣራት ካሳ የተከፈለበት የመሬት ይዞታ በተመለከተም ግልጽ ውሳኔ መስጠት እንዲሁም በክርክራቸው ውቅት አለ የተባለውንም የመሬት ይዞታ በተመለከተም እንዲሁ አጣርቶ ግልጽ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ሌላው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.215383

ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡.......1. ወ/ሮ አርሴማ ኤልያስ } ጠበቃ አበበ ዘበነ - ቀርበዋል፡፡

2. የርገን ቫንድራ ቬድ

ተጠሪ፡...............የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የጉዲፈቻ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር አመልካቾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ በመ.ቁ.274588 በ22/11/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ 1ኛ አመልካች እና 2ኛ አመልካች ባልና ሚስት ሲሆኑ፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች የማትወለደውን ህጻን ልጃቸውን ህጋዊ ባለቤታቸው ለሆነው ለ2ኛ አመልካች በጉዲፈቻ ለመስጠት ያደረጉትን ስምምነት እንዲጸድቅላቸዉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ አመልካች (ሚስት) ጉዲፈቻ ሰጪ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ስትሆን 2ኛ አመልካች (ባል) ጉዲፈቻ ተቀባይ የውጪ አገር ዜጋ መሆናቸዉ ከቀረበዉ አቤቱታ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች የማትወልዳትን ልጅ በጉዲፈቻ ዉል ስምምነት ለ2ኛ አመልካች ለመስጠት የተፈራረሙ ቢሆንም ጉዲፈቻ ለዉጭ አገር ዜጋ በአዋጅ ቁ.1070/2010 መሰረት የተከለከለ መሆኑ የቀረበዉን የጉዲፈቻ ውል ስምምነት ፍ/ቤቱ ውድቅ አድርጎታል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾች ጥቅምት 16 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ጉዲፈቻ ሰጪ ኢትዮጵያዊ  የሆኑና ጉዲፈቻ ተቀባይ የደች ዜግነት ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ጋብቻቸውን በመፈፀም ሕጋዊ ባልና ሚስት ሆነን ኢትዮጵያ ውስጥ ልጅ ወልደው እየኖርን ያለን በመሆኑ፤ ጉዲፈቻ ተሰጪ ሕጻንም ከእናቷ ጋርና ከእንጀራ አባቷ ጋር እየኖረች በስሙም እየተጠራች አብረው የሚኖሩ በመሆኑ፤ ጉዲፈቻዉም አባትነትን እንጂ እናትነትን በተመለከተ ወላጅ እናቷን የማይነካ በመሆኑ፤ ጉዲፈቻዉ ከዉጭ ዜጋዉ ከተወለደዉ ወንድሟ ጋር እኩል በማድረግ በጉዲፈቻ ተደራጊዋ ህጻን አእምሮ ሊፈጠር የሚችለውን አሉታዊ  ተፅዕኖ ለማስቀረት ለህጻኗ ጥቅም የታሰበ ሆኖ ሳለ፣ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የጉዲፈቻ ዉል ስምምነቱን በልዩ ሁኔታ በማየት ከተለያዩ ሕጎችና አዋጆች አንጻር እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 1070/2010 ዓላማና መንፈስ አንጻር በመረዳት መወሰን ሲገባቸዉ፣ የሥር ፍ/ቤቶች የጉዲፈቻ ዉሉን በመከልከል የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን፣ አመልካቾች ያደረግነዉ የጉዲፈቻ ዉል ስምምነት እንዲጸድቅልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በዚህ ጉዳይ ጉዲፈቻ ሰጪ እና ጉዲፈቻ ተቀባይ ባልና ሚስት መሆናቸው ከመረጋገጡ አንፃር ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 የሚሸፈን መሆን አለመሆኑ አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት አዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት ይህን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉ ጉዳይ ሲታይ 1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊት ስትሆን፣ 2ኛ አመልካች የደች የዉጭ አገር ዜጋ ሲሆን፣ ግራ ቀኛቸዉ ሕጋዊ ጋብቻ ፈጽመዉ አንድ ልጅ ወልደዉ አብረዉ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት መሆናቸው፤ እንዲሁም ሕጻን አቪያ ቫንድራ ቬድ 1ኛ አመልካች የተወለደችና ከ2ኛ አመልካች ያልተወለደች ልጅ ከግራ ቀኙና ከጋራ ልጃቸዉ ጋር በአንድ ቤት እየኖረች እና አሁንም በ2ኛ አመልካች ስም የምትጠራ መሆንዋን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካቾች

በትዳር አብረዉ እየኖር ያሉ በመሆናቸው፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር ያልወለዱትን ልጅ 2ኛ አመልካች የልጅቷ እንጀራ አባት በመሆኑ፣ በጋራ ከወለዱትና ካላቸዉ ልጅ ጋር ይህችን ልጅ እኩል ለማሳደግ ሲባል 1ኛ አመልካች የልጅቷ እናትነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ 2ኛ አመልካች በጉዲፈቻ ስምምነት መሰረት የልጅቷ የጉዲፈቻ አባት ለመሆን፣ የጉዲፈቻ ስምምነት ፈርመዉ፣ ይህም ስምምነት በፍ/ቤት እንዲጸድቅላቸዉ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ይህ ከሆነ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ የፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አግባብነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች ናቸዉ ወይስ ይህን የተሻሻለዉን የቤተሰብ ሕግ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 በምዕራፍ አሥር ከአንቀጽ 180–196 ድንጋጌዎች ሥር ስለጉዲፈቻ የሚመለከቱ መሆናቸውን ማየት ይቻላል፡፡ በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት የጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 180 ሥር ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ ያገባ ሰዉ የሚያደርገዉን የጉዲፈቻ ስምምነት በተመለከተ በዚህ ሕግ አንቀጽ 187 ሥር በተደነገገዉ አግባብ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የጉዲፈቻ አድራጊዉ ያገባ በሚሆንበት ጊዜ፣ ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁን የጉዲፈቻ ልጃቸዉ የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ እንደማይቻል የሚደነግግ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የጉዲፈቻዉ ልጅ፣ የጉዲፈቻዉ ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈጻሚነት እንደማይኖረዉ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ባልና ሚስት በጋራ የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ የሌላ ሰዉ ልጅን በጉዲፈቻ ማሳደረግ እንደሚችሉ፣ እንዲሁም በጋራ ያልወለዱትን የባል ወይም የሚስት የሆነዉን ልጅ ባል ወይም ሚስት በጉዲፈቻ ስምምነት ማሳደግ እንደሚችሉ ነዉ፡፡ የጉዲፈቻዉ ልጅ የባል ወይም የሚስት በሆነ ጊዜ ሌላኛዉ ተጋቢ በጉዲፈቻ ስምምነት የአንደኛዉን ልጅ በጉዲፈቻ ስምምነት ማሳደግ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ ይህ ድንጋጌ የባል ወይም የሚስት የዜግነት ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ ያስቀመጠዉ ክልከላ የለም፡፡ ነገር ግን ባል ወይም ሚስት የኢትዮጵያ ዜጎች ብቻ መሆን አለባቸዉ፤ ከመካከላቸው አንዳቸዉ የውጭ አገር ዜጋ ሊሆን አይችልም የሚያስብል ሁኔታ የለም፡፡ ምክንያቱም ባል ወይም ሚስት ከሁለቱ አንዳቸው የውጭ ዜጋ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በውጭ አገር ጋብቻቸውን በሕግ አግባብ ፈጽመው በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር አይችሉም በማለት በሕግ የተጣለ ግልጽ ክልከላ የለም፡፡

በሌላ በኩል የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለማሻሻል አዋጅ ቁጥር 1070/2010 ወጥቶ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 መሰረት የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193 የተሻረ መሆኑን፣ የአዋጁ አንቀጽ 194 (3፣ መ) ተሰርዞ ነባሩ ፊደል ተራ (ሠ) ፊደል ተራ (መ) ሆኖ መሸጋሸጉን፣ እና የአዋጁ አንቀጽ 194 (4) መሰረዙን ይደነግጋል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚመለከቱት በውጭ አገር ዜጋ የሚደረግ የጉዲፈቻ ጉዳይ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193 ድንጋጌ የጉዲፈቻ አድራጊዉ የውጭ አገር ዜጋ በሚሆንበት ጊዜ የጉዲፈቻ ስምምነቱ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልበትን አግባብ የሚያመለክተው ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 አንቀጽ 2 (1) ድንጋጌ መሻሩን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 194 (3፣ መ) እና (4) ድንጋጌዎች የጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ የሚመለከቱ በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሰረዛቸውን ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከአዋጅ ቁጥር 1070/2010 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የጉዲፈቻ አድራጊዉ የውጭ አገር ዜጋ የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ አንድ ኢትዮጵያዊ/ዊት ልጅን በጉዲፈቻ መዉሰድ እንደማይቻል ያሳያል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች እና ተጠሪ ባልና ሚስት ሆነዉ፣ 1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊት ዜጋ ስትሆን፣ 2ኛ አመልካች የደች አገር ዜጋ ሲሆን፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ያልወለደችውን ልጅ፣ የእርሷ እናትነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ 2ኛ አመልካች የልጅቷ የጉዲፈቻ አባት እንዲሆን ለማድረግ፣ በትዳራቸው በጋራ ካገኙት ልጃቸው ጋር ይህችንም ልጅ ለማሳደግ በማሰብ 2ኛ አመልካች የጉዲፈቻ አባት እንዲሆን ለማስቻል፣ የጉዲፈቻ ስምምነት ፈርመዉ ፍ/ቤቱ እንዲያጸድቅላቸዉ ያቀረቡ መሆናቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ የሆነችዉ የ1ኛ አመልካች ልጅ፣ አመልካቾች በትዳራቸው ውስጥ ከወለዱት ልጃቸው ጋር እያሳደጓት ያሉ እና ይህች ልጅ አሁንም በ2ኛ አመልካች ስም እየተጠራች በአመልካቾች ዘንድ የምትኖር መሆንዋ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዚህም በላይ አመልካቾች የሚኖሩት በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ አመልካቾች ሕጋዊ ጋብቻ ፈጽመው በትዳር አብረዉ በመኖር ልጅ ማፍራት የሚከለችላቸው ሕግ እስከሌለ ድረስ፣ ከትዳራቸዉ በፊት የባል ወይም የሚስት ልጅ የሆነዉን ሌላኛዉ ተጋቢ በጉዲፈቻ ስምምነት መዉሰድ አይችልም የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 1070/2010 አንቀጽ 2 መሰረት የአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193፣ 194 (3፣ መ) እና (4) ድንጋጌዎች መሰረዛቸዉን እንጂ የአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 187 ድንጋጌ መሰረዙን ወይም መሻሻሉን የሚያመለክት አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ የሚገባዉ የአዋጅ ቁጥር 1070/2010 ሳይሆን የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አግባብነት ያላቸዉ ደንጋጌዎች ናቸዉ፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኞቸውን የባልና ሚስት ግንኙነት፣ አንድ ልጅ በትዳራቸው ወልደው ያላቸዉ መሆናቸዉን፣ 1ኛ አመልካች የጉዲፈቻ ተደራጊዋ ልጅ እናት መሆንዋ

እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አመልካቾች የጉዲፈቻ ተደራጊዋን ልጅ አሁንም አብረዉ እያሳደጓት እና በኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ መሆናቸውን ከግምት ዉስጥ ሳያስገቡ፣ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 መሰረት ጉዲፈቻ ለዉጭ አገር ዜጋ ተከልክሏል በማለት አመልካቾች የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲጸድቅላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን ግንኙነት ከግምት ዉስጥ ሳያስገቡ ጉዲፈቻ ለውጭ አገር ዜጋ ተክልክሏል በማለት ያሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.127142 በ9/9/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.274588 በ22/11/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆናቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታው በተመለከተው አግባብ አመልካቾች የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲጸድቅላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. አመልካቾች በዚህ ችሎት በነበረው ክርክር የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡**

**ማ/አ** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ.መ.ቁ 198277

ቀን፡- ጥቅምት 2 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ቶላ - ጠበቃ ገናነው ተሾመ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰጉ ፈዬ - ጠበቃ ሀ/ማርያም አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 323353 በ26/2/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 336621 በ9/3/13ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ14/3/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በስር የደገም ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክፍቺ በኋላ የንብረት ክፍፍል ክስ ከአመልካች ጋር የጋራችን የሆነ አከራካሪውን በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ በ200 ቆርቆሮ የተሰራ 8 ክፍል ቤት ግምቱ ብር 2,000,000.00 የሆነ በ600ካ.ሜ ላይ ያለ አዋሳኞቹ በክሱ ውስጥ የተጠቀሱ አመልካች በ9/4/09ዓ.ም በፈረመልኝ ውል መሰረት እንዲያካፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት መልስ ተጠሪ ከቤቱ ጋር በተገናኘ የገለጸችው ውል በጋብቻ ውስጥ የተፈረመ ሲሆን ይህ የኦሮሚያ ቤተሰብ ህግ አ/ቁ 69/95 እና 83/96 አንቀጽ 89 ከደነገገው አንጻር በፍርድ ቤት ያልጸደቀ እና ስልጣን ባለው አካል ስላልተረጋገጠ በህግ ተቀባይነት ስለሌለው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ፤ ይህን ቤት ከእህቴ ወ/ሮ አሰፋ ቶላ የወረስኩት በመሆኑ የኦሮሚያ ቤተሰብ ህግ አ/ቁ 69/95 እና 83/96 አንቀጽ 73 በውርስ የተገኘ ንብረት ከክርክር ውስጥ እንዲወጣ የደነገገ በመሆኑ ከዚሁ ንብረት ጋር በተያያዘ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆንልኝ፡፡ በ9/4/09ዓ.ም የተደረገው ውል በደፈናው በውርስ ያገኘሁትን ቤት በጋራ ተጠቀምንበት የሚል እንጂ ቤቱ እንዴት አይነት እንደሆነ፤ ስፋቱ፤ አዋሳኞቹ እነማን እንደሆኑ ግልጽ ባለመሆኑ ውሉ በህግ ተቀባይነት

የለውም፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበው ተጠሪ ለዚሁ ክስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን ጭብጦች በመያዝ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ባልና ሚስት ጋብቻ ሲፈጽሙ በግላቸው ያለውን ንብረት ወይም ከዚያ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በግላቸው ያገኙትን የግላቸው ሆኖ እንደሚቀር የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አ/ቁ 69/85 እና 83/96 አንቀጽ 73 ደንግጓል፡፡ በሀምቢሶ ከተማ የሚገኘውን ከላይ የተገለጸውን ተጠሪ በ2009ዓ.ም አመልካች ፈረመልኝ በማለት የገለጸችው ቤት አመልካች ከእህቱ ወ/ሮ አሰፋ ቶላ በውርስ ያገኘ ስለመሆኑ የቀረበው ክርክር እና የግራቀኙ ማስረጃ የሚያስረዳ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ባልና ሚስት ተጋብተው አብረው በሚኖሩበት ግዜ በመካከላቸው ያደረጉት ውል በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ በቀር ውጤት እንደሌለው በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 89 ተደንግጓል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በሽማግሌዎች ተስማምተው በውርስ የተገኘውን ይዞታ መሬት እና ንብረት ስለመፈራረማቸው ከቀረበው ክርክር እና ከግራቀኙ ምስክሮች ለመረዳት የሚቻል ነው፡፡ ሆኖም ይህ ውል በፍርድ ቤት የተረጋገጠ ስለመሆኑ የቀረበ የሰውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም በተጠሪ ክስ የቀረበበት በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘውን በ600ካ.ሜ ላይ ያረፈውን አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰውን ቤት በተመለከተ በ9/4/09ዓ.ም የተደረገው ውል ያልጸደቀ እና በውርስ የተገኘ ንብረት ነው በማለት በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 73 እና 89 መሰረት የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በአመልካች የቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ክስ ባቀረቡበት በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን ቤት በተመለከተ ከላይ በተገለጸው በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በዚሁ ላይ ተጠሪ ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በሀምቢሶ ከተማ የሚገኘውን ቤት በተመለከተ ግራቀኙ በባልና ሚስትነት በመኖር ላይ ሳሉ አመልካች በውርስ ያገኘ መሆኑን ግራቀኙ አልተካካዱም፡፡ በጋብቻ ውስጥ በውርስ ንብረት ያገኘው ወገን ንብረቱ የግሉ እንደሚሆን የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 73 የደነገገ ሲሆን፤ በግሉ ወረሰ የሚባለው በስጦታ ውል ወይም በኑዛዜ ቃል ወይም በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በቀር በውርስ የተገኘ ንብረት የተጋቢዎች ነው፡፡ አመልካች ለብቻው መውረሱን የሚገልጽ የስጦታ ውል ወይም በኑዛዜ ቃል የወረሰበትን አላቀረበም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በ9/4/09ዓ.ም በፈጸሙት ውል ክርክር ያስነሳውን ቤት የጋራቸው ንብረት አድርገው ነበር፡፡ ይህ ውል የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 89 በደነገገው መሰረት ስላልተመዘገበ ተቀባይነት ቢያጣም ተጠሪ አስቀድማ በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 78(3) መሰረት ያገኘችውን መብት የሚያሳጣት አይደለም፡፡ በግለሰቦች መካከል የተደረገ ውል በአዋጅ የተሰጠውን መብት የሚከለክል አይደለም በማለት በስር ፍ/ቤት ቤቱን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ቤቱን ተጠሪ ከአመልካች ጋር እንድትካፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ እና ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ አከራካሪውን በሀምቢሶ ከተማ የሚገኘውን ቤት ያገኘሁት ያለኑዛዜ ከወንድሞቼ ጋር ተከራክሬ በፍ/ቤት ውሳኔ በውርስ ነው፡፡ አመልካች ቤቱን ያለኑዛዜ በፍ/ቤት ውሳኔ መውረሴን በስር የወረዳው ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ባልካደችበት፤ ቤቱን በኑዛዜ ወይም በስጦታ ውል መውረሴን ተጠሪ ባልተከራከረችበት እና በማስረጃም ባላስረዳችበት የስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች አመልካች ቤቱን በግሉ ስለመውረሱ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የስር የወረዳውን እና የከፍተኛውን ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ በመሻር የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የስር የወረዳው እና የከፍተኛው ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ እንዲጸናልኝ፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አከራካሪው በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ 600ካ.ሜ የሆነው ቤት እና ይዞታ አመልካች በውርስ ያገኘው ንብረት ሆኖ ሳለ በጋብቻ ውስጥ የተገኘ ውርስ ነው በሚል የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ ልትካፈል የሚገባው የጋራ ንብረት ነው ያለውን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያጸናበት ከኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አ/ቁ 69/95 አንቀጽ 73 አንጻር ለመመርመር ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ18/3/13ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ9/4/13ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው እና ትእዛዙ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በ23/4/13ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር የደገም ወረዳ ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡበት አከራካሪውን በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘውን በ200 ቆርቆሮ የተሰራ ባለ 8 ክፍል ግምቱ፤ ስፋቱ እና አዋሳኞቹ በክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን ቤት አመልካች እና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ አመልካች ከእህቱ ከወ/ሮ አሰፌ ቶላ

በውርስ ያገኘው ስለመሆኑ አመልካች እና ተጠሪ ያልተካካዱት እና በስር የደገም ወረዳ ፍ/ቤት እንዲሁም በይግባኝ ሰሚው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬጉዳይ ነው፡፡

የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 73 ባልና ሚስት ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ ደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን ቤት ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ እያሉ ከእህቱ ወ/ሮ አሰፌ ቶላ በውርስ ያገኘው ስለመሆኑ ያላከራከረ እና የተረጋገጠም ጭምር በመሆኑ ይህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተገለጸው የህግ ድንጋጌ መሰረት ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት ሆኖ የሚቀር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የስር የደገም ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘውን ቤት አመልካች ያካፍለኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ እና በዚሁ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመሻር ቤቱን ተጠሪ ከአመልካች ጋር እንድትካፈል በማለት የሰጠውን ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናት የሰጠውን ትእዛዝ ይህ የሰበር ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 323353 በ26/2/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 336621 በ9/3/13ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የደገም ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 41770 በ7/5/12ዓ.ም በሀምቢሶ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘው በ200 ቆርቆሮ የተሰራ 8 ክፍል የሆነ ግምቱ ፤ ስፋቱ እና አዋሳኞቹ በክሱ ውስጥ የተገለጹትን ቤት አመልካች ያካፍለኝ ሲሉ ተጠሪ ያቀረቡትን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በዚሁ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 72333 በ10/6/12ዓ.ም በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ከላይ በውሳኔው ክፍል ተራ ቁጥር 2 ስር ከተገለጸው ነጥብ ውጪ የደገም ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 41770 በ7/5/12ዓ.ም በሀረርጌ ዞን ዶባ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘውን ግምቱ፤ መጠኑ እና አዋሳኞቹ በአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውስጥ የተገለጸውን ቤት በተመለከተ የሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሠ/መ/ቁጥር 208197

መጋቢት 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ዓለማየሁ አባተ(ዶ/ር)፡- ጠበቃ ዘፋኒያህ ዓለሙ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መዕዜት ዓይነኩሉ፡ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለው የፍርድ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንደኛው ተጋቢ የፈጸመውን የብድር ውል ሌላኛዉ ተጋቢ አውቋል ሊባል የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ በመሰረቱት ክስ ከአመልካች ጋር ተጋብተው እየኖሩ ቆይተዉ በቀን 03/06/2009ዓ/ም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ጋብቻዉ ፈርሷል፡፡ አመልካች በጋራ ንብረት ክፍፍል ክርክር መልሳቸው ላይ በአማራ ክልል ባህር ዳር ከተማ በካርታ ቁጥር 32394/97 በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት የተሰራው ከስር 2ኛ ተከሳሽ በተገኘ ብድር እና እዳውም አልተከፈለም በማለት መልስ የሰጠ ቢሆንም የብድር ውሉ ተጠሪ ሳያውቁት የተደረገ ነው፡፡ በቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 68(1/መ) መሰረት ከብር 500 በላይ ለማበደርም ሆነ ለመበደር የተጋቢዎች የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል፡፡ ተጠሪ የብድር ውል ስለመኖሩ አላውቅም፡፡ በብድር ተገኘ የተባለውም ገንዘብም ለትዳር ጥቅም አልዋለም፡፡ ውሉ ከቅን ልቦና ውጪ ተጠሪን ለመጉዳት የተደረገ በመሆኑ የብድር ውሉ ሊፈርስ ይገባል እንዲሁም የብድር ውሉ ተጠሪ ላይ የሚያመጣው ግዴታ የለም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም ለክሱ በሰጡት መልስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለውም፡፡ተጠሪ ክስ የመሰረቱበት የብድር ውል ስለመኖሩ ስለሚያውቁ ውሉ መኖሩን ካወቁ ከስድስት ወር በኋላ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብታቸው በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው በማለት ተቃውመዋል፡፡ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ባህርዳር ከተማ ያለ ቤት ስሰራ የገንዘብ ችግር

ገጥሞኝ ተጠሪ ብድር ማግኘት ባለመቻሏ የብድር ገንዘብ ፈልገን እኔ እንድበደር ተነጋግረን ተበድሬ ቤቱን ሰርቻለሁ፡፡ በዚህ አግባብ የተገኘው ገንዘብ በባህርዳር ከተማ ያለውን መኖሪያ ቤት መስሪያ መዋሉንና የብድር ውል መኖሩን ተጠሪ ታውቃለች፡፡ ከተበደርነው ገንዘብ ብር 110,000.00 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ከፍዬ ብር 340,000.00 እንደሚቀር ተጠሪ ያውቃሉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የብድር ውሉ እሷን ለመጉዳት በማስመሰል እንደተደረገ አድርገው ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ በማስረጃ ያልተደገፈ እና የሕግ መሰረት የሌለው ስለሆነ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 63059 ላይ በቀን 10/03/2011ዓ/ም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አስመልክቶ በሰጠው ብይን ይርጋን በሚመለከት የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተ ተጠሪ ብድሩ መኖሩን ካወቀች 6 ወር አልፏል የሚለውን አመልካች ባቀረቡት ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል፡፡ ሆኖም የብድር ውል የተደረገው በቀን 07/10/2007ዓ/ም ሲሆን ተጠሪ ክስ የመሰረቱት ደግሞ የብድር ውል ግዴታ ከተገባ ሁለት አመት ሳይሞላው በቀን 28/09/2009ዓ/ም ነው፡፡ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 69/2 ስር በተደነገገው የሁለት አመት አማራጭ ይርጋ መሰረት የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ አልሆነም በሚል በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በመቀጠልም ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ምስክሮች ሰምቶና መርምሮ በቀን 17/04/2012ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በብድሩ ላይ አልፈረሙም፡፡አመልካች ባቀረቧቸው ምስክሮች ብድር ስለመኖሩ እንደተነገራቸው ከመመስከራቸው ዉጪ ስለብድሩ እዉቅና ያላቸው ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በምስክርነት ቃላቸው ቤቱ የተሰራው ከአመልካች ጋር ባፈሩት የጋራ ገንዘብ መሆኑን አስረድተዋል፡፡በተጨማሪም መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት እየሰሩ ደመወዝ በወር 80,000.00 ሲከፈላቸዉ እንደነበር ገልጸው ቤቱ የተሰራው በዚህ ገንዘብ ጭምር መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የአመልካች ምስክሮች ብድር ስለመኖሩም አመልካች ነግሮናል በማለት ውሉ ሲፈጸምም ሆነ አመልካች ብሩን ሲበደሩ እንዳላዩ አስረድተዋል፡፡በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 71/ሐ በክሱ ላይ የተደረገው ውል ተጠሪ የማያዉቁትና ገንዘቡም ለትዳር ጥቅም ያልዋለ በመሆኑ በአመልካችና በስር 2ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገው የብድር ዉል በአንቀጽ 69/1 መሰረት ፈርሷል ሲል ወስኗል፡፡
አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 251127 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 06/06/2013ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የአመልካች ምስክሮች ቃል ላይ እንደተመለከተው አመልካች ብድሩን እንደወሰዱ እንደነገራቸው እንጂ በእርግጥ የብድር ውሉ መኖሩን በግልጽ አላስረዱም፡፡ በመሆኑም በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2 ስር የተመለከተውን የይርጋ ጥያቄን ለማንሳት ተጠሪ ስለብድሩ እውቅና እንዳላቸው በግልጽ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በ6 ወር ዉስጥ ክሱ አልቀረበም ብሎ በይርጋ ውድቅ ማድረግ ተገቢ ስለማይሆን የስር ፍርድ ቤት ከዚህ አንጻር የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው፡፡ እንዲሁም ባህርዳር ከተማ ውስጥ ያላቸው ቤት የተሰራዉ ተጠሪ ገንዘብ እየላኩ በጋራ ገንዘባቸው እንደሆነ ተጠሪ አስረድተዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ቤቱ የተሰራው በግራ ቀኙ የጋራ ገንዘብ እንዳልሆነ በማስተባበል አላስረዱም፡፡ በመሆኑም የብድር ገንዘቡ

ለትዳር ጥቅም አልዋለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የብድር ውሉ እንዲፈርስ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቷል፡፡

አመልካች በቀን 23/09/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ከላይ በተመለከተው መሰረት በተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸው ይዘት በአጭሩ፡- የብድር ውል ግዴታ የተገባው በ07/10/2007 ዓ/ም ነዉ፡፡ ተጠሪ በቀን 28/09/2009ዓ/ም ክስ የመሰረቱት ብድሩ መኖሩን ካወቁ ከስድስት ወር በኋላ መሆኑን አመልካች ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ አስረድቻለሁ፡፡ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2 ስር የተደነገገዉ የ6 ወር ይርጋ ራሱን ችሎ የቆመ ይርጋ እንጂ ከሁለት አመት ፍጹማዊ ይርጋ ጋር ግንኙነት የሌለው ሆኖ እያለ ጉዳዩን ከሁለት አመት ይርጋ አንጻር በማየት የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ አልታገደም በሚል አለአግባብ የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ስህተት ማረም ሲገባው አለአግባብ ማስረጃ ምዘና ዉስጥ በመግባት ብድር ዉል ግዴታ መገባቱን ተጠሪ ልታዉቅ አትችልም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሰጠው ውሳኔ የክርክር አመራር በተመለከተ በሰ/መ/ቁጥር 36979 የተሰጠውን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ በብድር ውሉ ላይ በግልጽ ገንዘቡ በብድር የተወሰደው በባህር ዳር ከተማ ለምናስገነባው ቤት ለማዋል እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ በብድር ውሉ ላይ ተመልክቶ እያለ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2006/1 ስር የተደነገገውን በሚቃረን አኳኋን በምስክሮች ለማረጋገጥ የተደረገው የክርክር አመራር ስህተት ቢሆንም አመልካች በምስክሮች ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ አስረድቻለሁ፡፡ ተጠሪ ግን ገንዘብ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን በማስረጃ ማስረዳት አልቻሉም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የብድር ውሉ መኖሩን አታዉቅም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱት በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ወደጎን በመተው በመሆኑ ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም ዉሏል ተብሎ እንዲወስንላቸው እና የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመጠየቅ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ያደረጉት የገንዘብ ብድር ውል መኖሩን ተጠሪ ካወቁ ከስድስት ወር በኋላ የብድር ውሉ እንዲፈርስ ክስ እንዳቀረቡ የስር ፍርድ ቤት በቀን 10/03/2011 ዓ/ም በሰጠው ብይን ላይ በገለፀበት ሁኔታ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ከቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 69/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 07/03/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

የቀረበውን የይርጋ ክርክር በተመለከተ ግራ ቀኙ በነበራቸው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ክስ ወቅት ለዚህ ክስ መነሻ የሆነውን የብድር ውል አመልካች የባልና የሚስት የጋራ እዳ መሆኑ ተረጋግጦ

እንዲወሰንላቸው ክርክሩን ሲመለከት ለነበረው የስር ፍርድ ቤት በሚያዚያ 18/2009 ዓ/ም አቅርበው ተጠሪም የጋራ እዳ እንዲባል የቀረበው የብድር ውል ስለመደረጉ የሚያውቁት ነገር ባለመኖሩ ምክንያት ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት የብድር ውል መደረጉን ባወቁ በስድስት ወር ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ በመጠየቅ ክስ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃ መዝነዉ የብድር ዉል መደረጉን እንደማላውቅ ድምዳሜ ላይ የደረሱ ስለሆነ በሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚታይ አይደለም፡፡ እንዲሁም የብድር ውል መደረጉን ዉሉ በተደረገ በስድስት ወራት  ውስጥ አውቅ እንደነበር አመልካች አላረጋገጡም፡፡ የገንዘብ ብድሩ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉ በስር ፍርድ ቤት በቀረቡት ማስረጃዎች ተረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም በቤተሰብ ጉዳይ ችሎት በብድር የተወሰደው ገንዘብ የጋራ እዳ እንዲባልላቸው ጠይቀው የነበረ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ እዳው የጋራ እዳ ነዉ ተብሎ የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡ በዚህ አግባብ ብድሩ ለትዳር ጥቅም የዋለ ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው የጠየቁት ተቀባይነት ባላገኘበት ተጠሪ የብድር ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት በጠየቁበት መዝገብ ላይ ብድሩ ለትዳር ጥቅም የዋለ ነዉ ተብሎ እንዲወሰንላቸው ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡  አመልካችም በቀን 01/04/2014 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ማስቀረቢያ ጭብጥ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 68/መ ስር እንደተደነገገው በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከብር 500.00(አምስት መቶ ብር) በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰዉ ዋስ ለመሆን የተጋቢዎቹ ስምምነት ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ የሕግ ግዴታ ባለማክበር አንዱ ተጋቢ የውል ግዴታ ገብቶ የተገኘ እንደሆነም ሌላኛው ተጋቢ ግዴታው እንዲፈርስ ክስ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን በሕጉ አንቀጽ 69/1 ላይ ተመልክቷል፡፡ የክስ ማቅረቢያ ጊዜም ግዴታው መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ በ6 ወር ውስጥ መሆን እንዳለበት ወይም በሌላ በማንናቸውም ሁኔታ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ከሆነ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ አንቀጽ ላይ የተመለከተው ሁለቱም አይነት የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነቱ ያለአንደኛው ተጋቢ ተሳትፎ በሌላኛው ተጋቢ የተገባ ግዴታ እንዲፈርስ በስምምነቱ ተካፋይ ያልሆነዉ ተጋቢ ሲጠይቅ ነዉ፡፡ እንዲሁም በዚህ ድንጋጌ ላይ የተመለከተው ሁለት አይነት የይርጋ ጊዜ ሲሆን አንደኛዉ የስድስት ወር የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነቱ በሕጉ ከአንቀጽ 68(ሀ-መ) ስር የተጋቢዎቹ የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል ተብለው በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ አንዳኛው ተጋቢ የሌላኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር የውል ግዴታ መገባቱን ያወቀ ተጋቢ ውሉ እንዲፈርስ ክስ ማቅረብ ያለበትን ጊዜ የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው በዚሁ ድንጋጌ የተመለከተው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ

ደግሞ በማንኛውም ሌላ ምክንያት በሕጉ ከአንቀጽ 68(ሀ-መ) ስር የተጋቢዎቹ የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል ተብለው በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ አንዳኛው ተጋቢ የሌላኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር የውል ግዴታ መገባቱን በመቃወም ውሉ እንዲፈርስ ክስ የሚያቀርብበትን ፍጹማዊ(absolute) የሆነ የይርጋ ጊዜ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ አግባብ የይርጋ ጊዜያትና ለእያንዳንዱ የይርጋ ጊዜ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ አመላካች ምክንያቶች ተለይቶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 ስር ከተመለከተው በተለየ ሁኔታ የተደነገገበት ምክንያት የተጋቢዎችን ልዩ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ጥቅማቸውን ለማስከበር እና በዉል ግንኙነት ለተፈጠረዉ ግብይት ጥበቃ (security of transaction) በማድረግ ተወዳዳሪ ጥቅሞችን ለማስከበር ነው፡፡

ሌላው የዚህን ችሎት ትርጉም የሚሻው ነጥብ በአንደኛው ተጋቢ የውል ግዴታ ሲገባ ተካፋይ ያልሆነ ተጋቢ ግዴታው መገባቱን አወቀ የሚባለው መቼ ነው? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 69/2 ስር የተጠቀሰው የ6 ወር የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነው የውል ግዴታ በአንደኛው ተጋቢ መገባቱን ለሚያውቅ ተጋቢ ነው፡፡ ጊዜውም ያጠረበት ምክንያትም ያለእሱ ተሳትፎ ግዴታ መገባቱን እስካወቀ ድረስ ሁለት ዓመት እስኪሆን መጠበቅ ሳያስፈልግ ግዴታ ያመጣው ውል እንዲፈርስ መጠየቅ ይችላል በሚል እምነት ነው፡፡ እንግዲህ ይህ ይርጋ ውል ይፍረስልኝ በሚል ክስ የማቅረብ መብት ቀሪ የሚያደርግ እስከሆነ ድረስ በስምምነቱ ተሳታፊ ያልሆነ[ው]ችው ተጋቢ ውል ይፍረስልኝ ክስ ለማቅረብ በሚያስችል ልክ ስለውሉ መኖር የተሟላ እዉቀት ሊኖረው(ልኖራት) ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት በአንደኛው ተጋቢ የተደረገ የገንዘብ ብድር ውል መኖሩን ሌላው/ዋ ተጋቢ አወቀ/አወቀች ሊባል/ልትባል የሚችለው/የምትችለው ቢያንስ የገንዘብ ብድር ውሉ ከማን ጋር እንደተደረገ፣ የምን ያህል ገንዘብ ብድር ውል እንደሆነ፣ መቼ የተደረገ የብድር ውል እንደሆነ ማወቅ ሲችል/ስትችል ነው፡፡ እነዚህን ፍሬ ነገሮች ያላወቀ ተጋቢ የገንዘብ ብድር ዉሉ ይፍረስልኝ ክስ አዘጋጅቶ ለማቅረብ ይቸገራል፡፡ ምክንያቱም የገንዘብ ብድር ውል ይፍረስልኝ ዳኝነት በመጠየቅ ክስ የሚያቀርበው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ የብድር ውል ግዴታ መገባቱን በጥቅሉ ከማወቅ ባለፈ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በቁጥር 33(2 እና 3) ፣ 80(2-4)፣85 እና 222/1 እንደተደነገገው የተከሳሹን ማንነት እና የክሱን ምክንያት (ለክሱ አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮችን) በክሱ እንዲገልጽ ሕጉ ስለሚያስገድደው ሌላኛው ተጋቢ ከማን ጋር የምን ያህል ገንዘብ ብድር ውል እንደተዋዋለ እና የብድር ውሉ መቼ እንደተደረገ ማወቅና በክስ አቤቱታዉ ላይ በፍሬ ነገር ደረጃ መግለጽ ስለሚኖርበት እና ሥልጣን ያለዉን ፍርድ ቤት ከብድሩ ገንዘብ መጠን አንጻር ለይቶ ገልጾ ክሱን ማቅረብ ስለሚኖርበት ነው፡፡

እንዲሁም አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክምን ከሚመለከተው መሠረታዊው መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለው አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ብሎ የሚከራከር ሰው ፍሬ ነገሩ መኖሩን በማስረጃ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 258-260 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001/1 ይመለከቷል)፡፡ በዚህ መሰረት ግዴታ መገባቱን አውቋል ብሎ

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2 ስር የተደነገገውን የ6 ወር የይርጋ ጊዜ አንስቶ የሚከራከር ተከራካሪ (ተጋቢ) ሌላኛው ተጋቢ ግዴታው መገባቱን እንዴትና መቼ እንዳወቀ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ይፈርስ ዘንድ ዳኝነት በመጠየቅ በስር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ ክስ የመሰረቱበት የገንዘብ ብድር ውል አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ዉስጥ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ተዋውለዋል የተባለውን ውል ነው፡፡ በዚህ የብድር ውል ላይ ተጠሪ በተዋዋይነት አለመሳተፋቸው እና ከክርክሩ እንደተገነዘብነውም የብድር ግዴታ የተገባበት የገንዘብ መጠን ብር 450,000.00 መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች የገንዘብ ብድር ውል ግዴታ መገባቱን ተጠሪ ክሱ ከመቅረቡ ከ6 ወር በፊት ታውቅ ነበር ያሉትን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ቃል አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ብድር እንደተበደሩ ለተጠሪ ነግረዋቸዋል የሚል እንደነበር የስር ፍርድ ቤቶች በሕግ የተሰጣቸውን የምስክሮችን ቃል የመመዘን ሥልጣን በመጠቀም ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ በዚህ መልኩ አመልካች በምስክሮቻቸዉ በጥቅሉ ያስረዱት አመልካች ከማን ጋር ምን ያህል ገንዘብ ለመበደር መቼ በተደረገ የብድር ውል እንደተዋዋሉ ተጠሪ ውል ይፍረስልኝ ክስ ለመመስረት በሚያስችላቸው በተሟላ መልኩ አውቀዋል የሚያሰኝ ማስረጃ ወይም ምስክርነት ቃል አይደለም፡፡

እንደሚታወቀው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያርም ነው፡፡ ችሎቱ በዚህ ሥልጣኑ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ውስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነው የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጣን ለችሎቱ አልተሰጠውም፡፡ ሆኖም የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም መርህ (Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence)እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standard of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ተጥሶ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ሲኖር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሚሆን በሰበር ሰሚ ችሎት የሚታረም ይሆናል፡፡ በዚህ በያዝነው ጉዳይ ከላይ እንደተመለከተው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ የተሰጠውን ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን በመጠቀም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መዝኖ አመልካች በምስክሮቻቸው ቃል ብድሩን እንደወሰዱ ለተጠሪ እንደነገሯቸው እንጂ በእርግጥ የብድር ውሉ መኖሩን በግልጽ ለተጠሪ አላስረዱም በማለት የደረሰበት የፍሬ ነገር ድምዳሜ ከማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርህ አተገባበር አንጻር ጉድለት ያለበት አይደለም፡፡ አንደኛው ተጋቢ ገንዘብ ተበድሬያለሁ ብሎ ለሌላኛው ተጋቢ ተናግሯል መባሉ ብቻ መብት ለማስከበር በሚያስችል ሁኔታ የብድር ውል ግዴታ መገባቱን ሌላኛው ተጋቢ አውቋል ብሎ ለመደምደም አያስችልም፡፡

በሌላ በኩል የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ አልሆነም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ከውጤት አንጻር ተገቢ ቢሆንም ተጠሪ የብድር ውል መገባቱን ከ6 ወር በፊት እንደሚያውቁ አመልካች በማስረጃ አስረድተዋል ካለ በኋላ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2 መሰረት የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜን እንደአማራጭ ይርጋ ጊዜ በመቁጠር የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ አልታገደም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በድንጋጌው የተመለከተውን የይርጋ ጊዜያት ትክክለኛ አፈጻጸም ያላገናዘበ ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የታየውን የይርጋ ጊዜያት አተገባበር ጉድለት አለማረሙ ስህተት ነው፡፡ እንዲሁም በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68/መ እና 69/1 መሰረት የገንዘብ ብድር ውል ሲደረግ ያልተሳተፈ ተጋቢ የብድር ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ምክንያት ሊያደርግ የሚገባውና ውሉ እንዲፈርስ ከመወሰኑ በፊት በፍሬ ነገር ደረጃ ሊረጋገጥ የሚገባው በገንዘብ ብድር ውል ግዴታዉ በተዋዋይነት አለመሳተፉን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ውል ይፍረስልኝ በሚል ከሚቀርብ ክስ ጋር በተያያዘ በብድር ተገኘ የተባለው ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ዉሏል ወይስ አልዋለም በሚለው ጭብጥ ላይ ማከራከርና ውሳኔ መስጠት አይቻልም፡፡ ይህ አይነት ክርክር ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ፍቺ ተከትሎ በሚደረገው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የብድር ውል ይፍረስልኝ ተብሎ በቀረበ ክስ ክርክር ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው በብድር ተገኘ የተባለዉ ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ውሏል ወይስ አልዋለም የሚለውን ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙን አከራክረው መወሰናቸው ሊታረም የሚገባው የክርክር አመራር ጉድለት ነው ብለናል፡፡

ሲጠቃለል ለክሱ መነሻ የሆነው የገንዘብ ብድር ውል የተደረገዉ በቀን 07/10/2007ዓ/ም ሲሆን ተጠሪ ክስ የመሰረቱት ደግሞ የብድር ውል ግዴታ ከተገባ ሁለት አመት ሳይሞላው በቀን 28/09/2009ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር የገንዘብ ብድር ውል ሲያደርጉ ተጠሪ በተዋዋይነት እንዳልተሳተፉ ከመረጋገጡም በተጨማሪ ተጠሪ ክስ ከማቅረባቸው ከ6 ወር በፊት የገንዘብ ብድር ውል ግዴታ መገባቱን ተጠሪ ከላይ በተመለከተው አግባብ በተሟላ መልኩ እንደሚያውቁ አመልካች አለማስረዳታቸው ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የ6 ወር ይርጋ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተመለከተው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተለያዩ ጉድለቶች ቢኖሩም ተጠሪ ክስ የመሰረቱት በተዋዋይነት ያልተሳተፉት ወይም ፈቃዳቸውን ያልገለጹበት ውል እንዲፈርስላቸው ከመሆኑ አንጻር ሲታይ እና በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2 መሰረት የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ መሰረት በማድረግ ሲታይ የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት በሰጡት ውሳኔም ሆነ ከተጠሪ አንጻር የብድር ውሉ እንዲፈርስ (ተጠሪን አይመለከታቸዉም ሲሉ) በሰጡት ውሳኔ ከውጤት አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 63059 ላይ በቀን 10/03/2011ዓ/ም የሰጠው ብይን እና በቀን 17/04/2012ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ

ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 251127 ላይ በቀን 06/06/2013ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪ የየራሳቸውን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸው፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 198553

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ እሸቴ አድኔ ጠበቃ ዋና ኢንስፔክተር ሐየሎም አስረስ -- ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስናቀች ለውጤ -- አልቀረቡም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 244609 ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54761 ጥቅምት 20 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት በሰበር ለማሳረም ህዳር 18 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በመባሉ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ ሰኔ 7 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በክ/መ/ቁ 201536 በተሰጠ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ የቀረበ የንብረት ክርክር ሲሆን ክሱ በቀረበበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች በሥር ክሳቸው ከተጠሪ ጋር በትዳር በነበሩበት ወቅት በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥሩ አ.138 የሆነ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ድርሻቸውን ተጠሪ ለማካፈል ፈቃደኛ ባለመሆን እየኖሩበት እና ከሚኖሩበት ከፍል ውጪ ያለውን ተጨማሪ ክፍል ብቻቸውን አከራይተው እንደሚጠቀሙበት ገልፀው ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት ምላሽ በግራቀኙ መካከል በነበረው የባልና ሚስት ክርክር የጋብቻ ውሉ ሀሰተኛ ነው በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 54761 ሐምሌ 3 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ቅር በመሰኘት ያቀረቡት ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 201353 የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙ የጋብቻ ውል ሀሰተኛ ነው በማለት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ከጥር 18 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ጋብቻ

መኖሩን አረጋግጦ ሰኔ 7 ቀን 2010 ዓ/ም እንዲፈርስ የወሰነ ሲሆን የክፍፍል ጥያቄ የቀረበበት ቤት መንግስት አቅመ ደካማ ለሆኑ ሰዎች ባደረገው ድጎማ(እገዛ) በብር 8,000(ስምንት ሺ) በግራቀኙ መካከል ጋብቻ ከመደረጉ ሶስት ዓመት አስቀድሞ ከአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ የቤት ማስተላለፍ ጽ/ቤት ባደረጉት ውል የተላለፈላቸው በ60.5 ካ.ሜትር ላይ ያረፈ የጋራ መኖሪያ ቤት የጋራ ንብረት ባለመሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት ተብሎ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ያየው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት በግራ ቀኙ መካከል ጋብቻ አለ ተብሎ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተወሰነበት ጊዜ ውስጥ መፈራት/አለመፈራቱን በጭብጥነት ይዞ መዝገቡን እንደመረመረው የክፍፍል ጥያቄ የቀረበበት ቤት ሰኔ 6 ቀን 1993 ዓ/ም ለተጠሪ ከተሰጠ በኋላ የቤቱ ሽያጭ በውል ቁጥር ገ/ቤሽ/0250/1998 ከአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቤት ማስተላለፍ ጽ/ቤት ጋር በተደረገው የቤት ማስተላላፍ ስምምነት ለተጠሪ ለመተላለፉ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ገልፆ ፤ ይህ ጊዜ በግራቀኙ መካከል የጋብቻ ግንኙነት መኖሩን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መኖሩን ካረጋገጠበት ጥር 18 ቀን 2001 ዓ/ም በፊት የተገኘ መሆኑን ከማስገንዘቡም በላይ የተጠሪ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት ቃል ካዛንቺስ አካባቢ ነዋሪ የነበሩት ሰዎች በልማት ምክንያት የነበረው ቤት ሲፍርስ አከራካሪውን ቤት በመንግስት ተሰርቶ ለተጠሪ ተሰጥቷቸው ሲኖሩ ቆይተው ከመንግስት ጋር በገቡት ውል በብር 8000ሺ የቤቱ ካርታ የተሰጣቸው መሆኑና በዚህ ጊዜ አመልካች ከተጠሪ ጋር አብረው የማይኖሩ መሆኑን ያስረዱ ፤ ሲሆን የአመልካች ምስክሮች አከራካሪውን ቤት ከተጠሪ ጋር ማፍራታቸውን እና ተጠሪ ቤቱ በተረከቡበት ጊዜ ግራቀኙ አብረው መኖራቸውን እንደክርክራቸው ያላስረዱ በመሆኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት ያፈሩት በመሆኑ የግራቀኙ የጋራ ንብረት ሊባል አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ከተጠሪ ጋር ከ1982 ዓ/ም ጀምሮ ህጋዊ የሆነ ጋብቻ የነበራቸው መሆኑን እና በዚህ ጊዜ ውስጥ የተፈራው ንብረትም የጋራ ነው በማለት ሲከራከሩ ፤ ተጠሪ በ1982 ዓ/ም የተመሰረተ ጋብቻ አለመኖሩ በፍርድ መረጋገጡንና ንብረቱንም ከጋብቻ በፊት እንዳገኙት መከራከራቸውን ገልፆ ፤ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙ ጋብቻ በ1982 ዓ/ም እንደተመሰረተ የቀረበውን ማስረጃ በተመለከተ ውሉ የተዘጋጀው ጥር ወር 2001 ዓ/ም ቢሆንም ልጃቸው በጋብቻ ውስጥ እንደተወለደ ለማስመሰል ጋብቻው በ1982 ዓ/ም እንደተፈፀመ የተዘጋጀ እንጂ የግራቀኙ ጋብቻ በ2001 ዓ/ም መመስረቱን የወሰነ በመሆኑ ፣ የግራቀኙ ጋብቻ በ1982 ዓ/ም ተፈጽሟል የተባለው የምስክር ወረቀት ለመውሰድ ስለተፈለገ እንጅ ሕጋዊ ጋብቻ የመሰረቱት በ2001 ዓ/ም በመሆኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከጋብቻ በፊት በተጠሪ የተፈራ የግል ንብረቷ ነው በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ሆኖ ይዘቱም፡- በግራቀኙ መካከል ጥር 18 ቀን 2001 ዓ/ም የተመሰረተ ጋብቻ መኖሩ ተረጋግጦ ሰኔ 7 ቅን 2010 ዓ/ም እንዲፈርስ በተላለፈው ውሳኔ መሰረት አመልካች በጋብቻ ወቅት በላኩት ገንዘብ የተገዛ የጋራ

ንብረት 50% ድርሻቸውን ተጠሪ ሊያካፍሉ ሲገባ የሥር ፍርድ ቤት ጋብቻ መኖሩን እያወቀ እና እየተረዳ ወደጎን በመተው በጋብቻ ውስጥ የተፈራን ንብረት የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መወሰኑና እና ይግባኝ ሰሚው የሥር ፍርድ ቤትም ውሳኔውን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ በጋብቻ ውስጥ የተፈራው ንብረት ድርሻቸው እንዲወስኑላቸው ጠይቀዋል።

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻ የመሰረቱት ጥር 6 ቀን 1982 ዓ/ም ሲሆን በክብር መዝገብ ላይ የተመዘገበ ብሔራዊ ጋብቻ የፈፀሙት ጥር 18 ቀን 2001 ዓ/ም የጋብቻ የምስክር ወረቀት የሚያስረዳ በመሆኑ አከራካሪው ቤት በግራቀኙ ጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ወቅት የተፈራ መሆን/አለመሆኑን ለማጣራት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- በግራቀኙ መካከል የተደረገው ጋብቻ ጥር 18 ቀን 2001 የተደረገ ሲሆን ጥር 6 ቀን 1982 ዓ/ም ተፈረመ ተብሎ ለክብር መዝገብ ሹም የቀረበው ሰነድ ወደኋላ ተደርጎ ከግራቀኙ የሚወለደውን ልጅ እስራኤል ሀገር ወስጄ ላስተምር አመልካች በማለታቸው መሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት በአመልካች ባለመስተባበሉ ፣አመልካች በአባወራነት በዕድር ፣ በማኅበራዊ እና በቤተሰብ አባልነት ቅጽ የማይታወቁ እና የጋብቻ ሰነዱም የቤተሰብ ሕጉ ካስቀመጠው ዓላማ እና ግብ አንፃር ያልተዘጋጀ ትዳር መኖሩን የማያስረዳ በመሆኑ የግራቀኙ ጋብቻ የተመሰረተው ጥር 2001 ዓ/ም መሆኑን ተረጋግጦ የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ከጋብቻ በፊት የተፈራው የተጠሪ የግል ንብረት የጋራ ነው በማለት አመልካች የሚያቀርቡት ቅሬታ ተገቢ ባለመሆኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ ፀንቶ ኪሳራ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና ግራቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር እንደሚከተለው መርምሮታል። የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94 መሰረት ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ ጋብቻ በተፈፀመ ዕለት ወይንም ከዚያ በኋላ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ በሚሰጥ የምስክር ወረቀት መሆኑን ያመለክታል። አንቀጽ 28 እና ተከታዮቹ የጋብቻ ምዝገባን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ሲሆኑ በአንቀጽ 28(3) ድንጋጌ መሰረት ጋብቻ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ውጤት እንደሚኖረው ተመላክቷል። የጋብቻ መዝገብ ጋብቻ የተመዘገበበት እና የተፈፀመበትን ቀን እንደሚያመለክት አንቀጽ 30(ሐ) ይደነግጋል። በተያዘው ጉዳይ የግራቀኙ ክርክር የጋብቻ ፍቺን ውጤት የሆነ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ቤት ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ላቀረቡት ክስ ተጠሪ ጋብቻው የተመሰረተው ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም ሲሆን በጋብቻ ምስክር ወረቀቱ ላይ ጋብቻ በ1982 ዓ.ም እንደተደረገ መገለፁ ከቤተሰብ ሕጉ ዓላማ ውጭ የግራቀኙ የጋራ ልጅ በጋብቻ ውስጥ እንደተወለደ አድርጎ ወደ እስራኤል ሀገር ለማውጣት መሆኑ ተከራክረዋል። በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ጋብቻ የተፈፀመው ጥር 18 ቀን

2001 ዓ/ም መሆኑ እና ጋብቻው ከጥር 18 ቀን 2001 እስከ ሰኔ 7 ቀን 2010 ዓ/ም ፀንቶ ቆይቶ ሰኔ 7 ቀን 2010 ዓ/ም በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ መፍረሱ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገቡ ቁጥር 201353 ላይ የተሰጠ የፀና ውሳኔ ያለ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ሰኔ 6 ቀን 1993 ዓ/ም ለተጠሪ በልማት ተነሽነት ተሰጥቷቸው በ1998 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቤት ማስተላለፍ ጽ/ቤት ጋር በተደረገው ስምምነት ያገኙ የግል ንብረታቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 57 መሰረት የተጠሪ የግል ንብረት የሆነውን ቤት ለመካፈል አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ መሆኑ በህጉ አግባብ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 244609 ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54761 ጥቅምት 20 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት **ፀንቷል**፡፡
2. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ውጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**የሰ/መ/ቁጥር 205579**

**ቀን 25/4/2014 ዓ/ም**

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ፍቃዱ ገብሬ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እመቤት ኃይሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 257855 የካቲት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 113997 ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ በአመልካችና ተጠሪ መሀል በህግ የሚታወቅ ጋብቻ እያለ በመንግስት ሥራ ምክንያት ወደ ሀዋሳ የሄድኩና ከማገኘው ደሞዝ ቤተሰቦቼን እየረዳሁ የቆየሁ ሆኖ ሳለ በከሳሽና ተከሳሽ መሀከል ጋብቻ የለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ ከተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ጋር በ1990 ዓ/ም ተጋብተናል፡፡ በትዳር ውስጥ በጋራ ያፈራናቸው ንብረቶች አሉን፡፡ ይሁንና ተከሳሽ በመሀላችን በተፈጠረ አለመግባባት ከቤት ያስወጣችን በመሆኑ ጋብቻችን ፈርሶ በጋራ ያፈራነው ንብረቶችን ታካፍለኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሽም ከከሳሽ ጋር ተጋብተን 3 ልጆች መውለዳችን እውነት ነው፡፡ ይሁንና ከሳሽ 2000 ዓ/ም ትቶን ሄዷል፡፡ አድራሻው እንኳ አይታወቅም፡፡ ልጆቻችንን ምንም ሳይረዳኝ ያሳደኩት እኔ ነኝ፡፡ አሁን ንብረት ለመካፈል ፍለጋ የመጣና ከሄደ ከ12 ዓመት በኃላ የመጣ በመሆኑ ጋብቻቻን ፈርሷል፡፡ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥታለች፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 113997 ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የኢፌዴሪ የተሻሸለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 53(1 እና 2) ተጋቢዎች አብረው የመኖርና መደበኛውን የጋብቻ ግዴታ መፈጸም እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይሁንና ከሳሽና ተከሳሽ

በ2000 ዓ/ም ጀምሮ በተለያዩ ቦታዎች በመኖር ላይ ያሉ መሆኑ የተሰሙት ምስክሮች ያስረዱና የጋብቻ ግዴታዎችን ከሳሽ አለመወጣቱን የሚያሳይ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 31891 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተጋቢዎች ተለያይተው ለረጅም ጊዜ መኖር እና በየፊናቸው የየራሳቸውን ህይወት መምራት በህጋዊ መንገድ ጋብቻ ተቋርጧል የሚያስብል መሆኑን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከሳሽና ተከሳሽ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው በመኖር በየፊናቸው የየራሳቸውን ህይወት መኖራቸው በምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ እና ጋብቻቸው የተቋረጠ በመሆኑ በዚህ ፍ/ቤት የሚፈርስ ጋብቻ የለም ሲል የከሳሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ከሳሽ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 257855 የካቲት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በአመልካችና ተጠሪ መካከል ያለው ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ስትል ተከራክራለች፡፡ አመልካችም መስከረም ወር 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 75 ስለ ጋብቻ መፍረስ በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ እንደሆነ ደንግጎ ይገኛል፡፡ በስር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለን ጋብቻ እንዲፈርስልኝ ሲል ላቀረበው ክስ ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ከአመልካች ጋር ተለያይተው የኖሩ በመሆኑ ጋብቻችን ፈርሷል ስትል ላቀረበችው ክርክር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካችና ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው የየራሳቸውን ኑሮ መስርተው ይኖሩ የነበሩ መሆኑ በመረጋገጡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 31891 ባልና ሚስት በመለያየት ሀሳብ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው የየራሳቸውን ኑሮ መስርተው የሚኖሩ ከሆነ ጋብቻ በሁኔታ የፈረሰ መሆኑን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በሰጠው መሰረት የአሁን አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ሲል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አያስቀረብም ብሎታል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ሲሉ ውሳኔ የሰጡት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 14290፣ 31891 እና ሌሎችም መዝገቦች ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት አድርገው ቢሆንም የኢፌዲሪ የፌደሬሽን ም/ቤት በመ/ቁጥር 50/10 መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ/ም 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ አምስተኛ ዓመት፣ አንደኛ መደበኛ ስብሰባ ይህን ውሳኔ ህገ መንግስታዊ ባለመሆኑ

ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ባልና ሚስት ተለያይተው ስለኖሩ ብቻ ከፍ/ቤት ውሳኔ ውጪ የጋብቻ ፍቺ አለ ለማለት የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ ድንጋጌ መሰረት በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ስለመፍረሱ የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር የስር ፍ/ቤቶች በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

# ት እ ዛ ዝ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 257855 የካቲት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 113997 ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሻረ በመሆኑ የአሁን አመልካች ባቀረበው የጋብቻ ፍቺ ክስ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር 205500

ቀን 24/5/2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - ወ/ሮ አሰለፈች ዘነበ - ጠበቃ ግርማ ጌታቸው

ተጠሪ - አቶ ቀጸላ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መጋቢት 26 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-91413 የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋራ ያፈራሁትን የጋራ ንብረት የተጠሪ የግል ንብረት የሚያደርገውንና የግል ንብረቴን የጋራ የሚያደርገውን በወረዳ ፍ/ቤት የጸደቀው ስምምነት መብቴን የሚጎዳ ለህሊናና ለሞራል ተቃራኒ ሆኖ እያለ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 3316 መሰረት ፈራሽ መሆን ሲገባ ስምምነቱ መፍረስ የለበትም ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሁም የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 0391413 እና 03-94947 ላይ በአንድ ጉዳይ የተለያዩ ውሳኔዎች በመስጠቱ ውሳኔዎቹ የሚቃረኑና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበችው አቤቱታ ከአሁን ተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ ፈርሶ በ8/4/2010 ዓ/ም ያደረግነው ስምምነት በ12/4/2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የጸደቀው 1. በክሴ ላይ ያልጠየኩትን ከጋብቻ በፊት በግሌ ያፈራሁትን ንብረት ዳኝነት ሳይጠየቅበት በስምምነቱ የጋራ ንብረት እንዲሆን የተደረገ በመሆኑ 2. በክሴ ላይ የገለጽኩትን ንብረቶች ላይ ምንም ሳይባል ፍ/ቤቱ የእርቅ ስምምነቱን በማጽደቅ መዝገቡን መዝጋቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ስለሆነ ይፍረስልኝ ስትል በ25/10/2010 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ ጠይቃለች፡፡ የአሁን ተጠሪም በ8/4/2010 ዓ/ም ፈቅደን በመረጥነው ሽማግሌዎች የንብረት

ከፍፍል ተደርጎ ስምምነቱ የጸደቀ በመሆኑ እና ይህ የጸደቀው ስምምነት ባልተሻረበት ሁኔታ የጸደቀ ስምምነት ይሻርልኝ ስትል ያቀረበችው አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ በጅምር ላይ ያለ ቤት ተጠናቆ እንድንካፈል የተስማማነው ህጋዊ አይደለም የሚያስብል ባለመሆኑ አቤቱታዋ ውድቅ ይሁንልኝ ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡ የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት አከራክሮ በ19/2/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ ቀርቦ የጸደቀው ስምምነት ሊፈርስ አይገባም ሲል የአሁን አመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ አከራክሮ በመ/ቁጥር 0128524 ታህሳስ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የወረዳ ፍ/ቤት በ19/2/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በ8/4/2010 ዓ/ም በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለው ስምምነት ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ እንዲወስን ለወረዳ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 0111057/10 ጥር 13 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በ8/4/2010 ዓ.ም ግራ ቀኙ ያደረጉት ስምምነት የጋራ ንብረት ነው በማለት የተማመኑበትን ቤት ተጠሪ የጋራ ንብረታቸው የሆኑትን 3 ፈረሶች ሸጠ ቤቱን በመጨረስ በ30/4/2011 ዓ/ም ሊካፈሉት ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪ የጋራ ንብረት ናቸው ብላ ዘርዝራ ያቀረበችውንና  የልጅ አስተዳደግ ላይም ምንም ሳይልበት መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 274(2) እርቅ ወይም ግልግል ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻልና የፍ/ብ/ህግ 3307 እስከ 3324 የተደነገጉት ካልተሟላ እርቅ ወይም ግልግል መፍረስ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 3309 መብት መተው የሚዳርጉ የግልግል ቃሎች በጠባቡ ሊተረጎሙ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 101(1) የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለእኩል መካፈል እንዳለበት ይደንግጋል፡፡ ተጠሪ በመልሱ የጋራ ንብረት መሆኑን ያመነውን ከጋራ ንብረት ውጪ ማድረጉ የሴቶችን ህገ መንግስታዊ የእኩልነት መብት የሚጋፋ ነው፡፡ በመሆኑም በ8/4/2010 ዓ/ም የተደረገው ስምምነት ከፍትህ አንጻር ለህግና ለሞራል የሚቃረን በመሆኑ ፈራሽ ነው፡፡ ግራ ቀኙ በቀድሞ ክስ መሰረት ክርክር እንዲቀጥሉ ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 0129718 መጋቢት 11 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁን ተጠሪ ለአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ አከራክሮ በመ/ቁጥር 03-91413 የካቲት 15 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 3309 እና ተከታዮቹ መሰረት በሽማግሌ የእርቅ ስምምነት ውሉን ከመጽደቁ  በፊት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ መሆን አለመሆኑ መመርመር ሲገባ ታልፏል የሚል ሆኖ በወረዳ ፍ/ቤት የጸደቀ የእርቅ ስምምነት ሊሻር አይገባም ሲል መጀመሪያ ሰጥቶ የነበረው ብይን በአግባቡ ነው፡፡ ነገር ግን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦለት ተመላሽ ማድረጉና የወረዳ ፍ/ቤት ሊፈርስ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት አያስቀርብም ማለቱ ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች ያደረኩት ስምምነት መጽደቁና መዝገቡ መዘጋቱ ተገቢ አይደለም

ካለች ይግባኝ በማለት ማሳረም አንጂ የጸደቀ እርቅ እንደ ውሳኔ ስለሆነ በእራሱ ሊሽረው ስለማይገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ እና የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በወረዳ ፍ/ቤት በ8/4/2010 ዓ/ም የጸደቀው እርቅ ሊሻር አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርባለች፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካችና ተጠሪ መካከል የተፈጸመው የእርቅ ስምምነት በፍ/ቤት የጸደቀ በመሆኑ በይግባኝ ከማሻር በስተቀር ሊፈርስ አይችልም ሲል የወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ቀደም ብሎ ከአሁን ተጠሪ ጋር በነበራቸው የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በ8/4/2010 ዓ/ም የተጻፈ የንብረት ክፍፍል ስምምነት በአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ በ12/4/2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት አጽድቋል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን የወረዳው ፍ/ቤት በ12/4/2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት ስምምነታቸውን በማጽደቅ የሰጠውን ትእዛዝ ይፍረስልኝ ስትል በ25/10/2010 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ ጠይቃለች፡፡ የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤትም በ19/2/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት አቤቱታዋን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባበት አከራክሮ በመ/ቁጥር 0128524 ታህሳስ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት በ19/2/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔን በመሻር በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል በ8/4/2010 ዓ/ም የተደረገው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ስምምነት ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ ይዞ አከራክሮ እንዲወስን ለወረዳ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ አንድ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 6፣ 78፣ 358 ውጪ ውሳኔው ፍትሐዊ አይደለም በሚል በሚቀርብለት አቤቱታ የራሱን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሽርበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ይሁንና ይህን የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦበት ያላሻረውና ውሳኔው እንደጸና የሚገኝ፣ የአሁን ተጠሪ ይህን የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ተቀብሎ አንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት ተመልሶ የከፍተኛ ፍ/ቤት በመለሰው ጭብጥ መሰረት ተከራክሮ ወረዳው ፍ/ቤትም በተመለሰለት ጭብጥ መሰረት አከራክሮ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ በኋላ ያለው ክርክር የአሁን አመልካችና ተጠሪ

ያደረጉትን የንብረት ክፍፍል ስምምነት ተቀብሎ የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት በማጽደቅ የሰጠው ውሳኔ ሊሻር ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ሳይሆን በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል የተደረገው ስምምነት ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ክርክር ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ብሎ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0128524 ታህሳስ 12 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በፍሬ ነገር አከራክሮ የሰጠውን ውሳኔና ይግባኝ ባልተባለበት ባለቀ ጉዳይ ተጠቅሞ በኋላ የከፍተኛ ፍ/ቤት ጭብጥ ይዞ በመለሰው መሰረት ተጣርቶ የተሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ሥነ ሥረዓታዊ ሆኖ ባለመገኘቱ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል ታህሳስ 8 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ ስምምነት የተደረገውን የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተመለከተ የአማራ ብ/ክ/መ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 97(1) ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን ንብረት መልሶ የመውሰድ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 101 ከዚህ በላይ የተመለከቱት የባልና ሚስት ሀብትን በስምምነት ስለመከፋፈል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም ተጋቢዎች እኩል የሚከፋፈል እንደሚሆን ደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን አመለካችና ተጠሪ ያደረጉት ስምምነት የጋራ ንብረት የሆነውን የግል የሚያደርግና የግል የሆነውን ንብረት የጋራ የሚያደርግ ስምምነት በክልሉ የቤተሰብ ህግ በተጠቀሰው መሰረት ለህጉ ተቃራኒ ሆኖ የሚገኝ ነው፡፡ በመሆኑም የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል ታህሳስ 8 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ስምምነት ውድቅ ማደረጉ ተገቢ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ውሳኔ**

1. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-91413 የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0129718 መጋቢት 11 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የአንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0111057 ጥር 13 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ማ/አ　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁጥር 190729

የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ አያልነህ ገ/ማርያም ጠ. መንግስተአብ ይልማ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ክብነሽ ጎሹ ጠ. ዳንኤል ብርዬ - ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ሮዳ ሁሴን - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ክርክሩ የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የቀረበ ክስን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተመጀረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች 1ኛ ተከሳሽ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የሚገኝ ስፋቱ 700 ካሬ ሜትር የሆነ የመኖሪያ ቤት ከአመልካች ጋር አብረን ስንኖር በጋራ ያፈራን ሲሆን በመካከላችን በተፈጠረ አለመግባባት በ2004 ዓ.ም ተለያይተናል፡፡ ይህ የጋራ ንብረት ተሽጦ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እንድንከፋፈል በዚሁ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 90477 ክስ መስርቼ ክርክር ላይ እያለን 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ ያልጸደቀ የሽያጭ ውል በብር 400,000 ከ1ኛ ተጠሪ መግዛታቸውን በመግለፅ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብ በመሆን ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም ካቀረቡት አቤቱታ ቤቱ መሸጡን ያወቅኩ ስለሆነ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ክሳቸውን ያቀረቡት ውሉ ከተደረገ ከ3 ዓመት 11 ወር በኂላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፤ ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በተደረገ የንብረት ክፍፍል ስምምነት 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸው የባለቤትነት መብት ቀሪ ስለሆነ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የላቸውም፤ በዚህ ስምምነት ቤቱ ለአመልካች የደረሰኝ እና ጉዳዩ በሽምግልና ያለቀ ስለሆነ ክሱ ተገቢነት የለውም በማለት

የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያቸውን አቅርበዋል፡፡ በአማራጭ ባቀረቡት መልስ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እንደ ባልና ሚስት አብረን ስንኖር የተጠቀሰውን ንብረት በጋራ ያፈራን ቢሆንም ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም የንብረት ክፍፍል አድርገን ግንኙነታችን በመቋረጡ እና በየግል የያዝነውን ንብረት ለ3ኛ ወገን ያስተላለፍኩ ስለሆነ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በኩላቸው አመልካች ካቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በተጨማሪነትም ግራ ቀኝ በመ/ቁጥር 90477 ላይ ክርክር እያደረግን ስለሆነ እና በሁለቱ መዝገቦች ላይ የሚያዘው ጭብጥ ተመሳሳይ ስለሆነ ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2)(ሐ) መሰረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በአማራጭ ባቀረቡት መከራከሪያ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መስማማት ባለመቻላቸው ሰኔ 12 ቀን 2002 ባደረጉት የመለያየት ውል ቤቱን አመልካች እንዲወስዱ ተስማምተዋል፡፡ በዚህ መነሻነት 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በብር 400,000 ገዝቼ ተጨማሪ ግንባታ ያከናወንኩበት ስለሆነ ወደ ነበረበት ሊመለስ አይችልም፡፡ ውሉም በአዋዋይ ፊት ያልተፈፀመው አመልካች እና ተጠሪ በ1993 ዓ.ም ቤቱን ሲገዙ ባልፀደቀ ውል ስለሆነ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመቃወሚያው ላይ በሰጠው ብይን በመ/ቁጥር 90477 1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት እንዲካፈሉ እንዲወስንላቸው ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የተጠየቀው ዳኝነት የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ የሚል የተለያየ ጭብጥ ስለሆነ በፍ/ሥ/ስ/ሕ/ቁጥር 244(2)(ሐ) መሰረት የቀረበው መቃወሚያ ተገቢነት የለውም፡፡ ውሉን ለማፍረስ የሚያስችል የክስ ምክንያት አለ ወይስ የለም የሚለውም በፍሬ ነገር ክርክር የሚጣራ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የውሉን መኖር ያወኩት ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም ነው በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ስላልተቃወሙ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት እስከተጠየቀበት ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም ያለው ግዜ 6 ወር ያልሞላው በመሆኑ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 69(2) መሰረት ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት መቃወሚያውን አልፎታል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው ውሳኔ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በስምምነት ክፍፍል ስለማድረጋቸው የቀረበው ውልና በዚህ ውል መሰረት ቤቱን በሽያጭ ስለማስተላለፋቸው አመልካች ያቀረቡት ውል በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድ መሆኑ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁጥር 161234 ተረጋግጦ አመልካች በወንጀል ተቀጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔም በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁጥር 164836 ጸንቷል፡፡ በመሆኑም በክፍፍል በተገኘ ንብረት ላይ የተደረገ ሽያጭ ነው በማለት የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይት የለውም፡፡ 2ኛ ተጠሪ የመጀመሪያው ውል ያልጸደቀ መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ ቢሆንም የውሉ መፅደቅ ክርክር ያልተነሳበት እና በነበረ ውል ግንኙነት የተገኘው መብት አሁን ላይ ክርክር የተነሳበትና ያልፀደ ስለሆነ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በውሉ ፈቃዳቸውን ያልሰጡ እና በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድን መሰረት አድርጎ የተፈጸመ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በቦታው ላይ ላደረጉት ተጨማሪ ግንባታ 1ኛ ተጠሪን ከሰው ከማስከፈል በስተቀር ወደ ነበርንበት ልንመለስ አይገባም በማለት የቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡

አመልካች የካቲት 10 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ይህን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ሽያጭ ውል የተፈፀመው ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ በፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 69(2) መሰረት አንደኛው ተጋቢ ውሉ መደረጉን ካወቀ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ክሱን ማቅረብ ያለበት እና በማንኛውም ሁኔታ ከ2 ዓመት በኋላ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የተቀመጠውን ፍፁም ይርጋ ያለአግባብ በመተርጎም 1ኛ ተጠሪ ውሉ መኖሩን ያወቁት ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ የ6 ወር ጊዜው አላለፈም በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተደረገው የንብረት ክፍፍል ስምምነት ላይ ያለውን ፊርማ በመካዳቸው ፍ/ቤቱ ፊርማው እንዲመረመር ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ መዝገቡ የተዘጋ ቢሆንም እንደገና እንዲንቀሳቀስ ሲደረግ ፊርማው በፎረንሲክ እንዲመረመር አለመደረጉ ወይም ትዕዛዙ ቀሪ ስለመደረጉና ቀሪ የተደረገበት ምክንያት ሳይገለፅ መታለፉ አግባብ አይደለም፡፡ ውሉ እንዲፈርስ ሲወስንም ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሚያስችል ምክንያት አለ ወይስ የለም፤ በውሉ መፍረስ አንደኛው ወገን የሚበለፅግ እና ሌላው ወገን የሚጎዳ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ሊታይ የሚገባው ሚስት የንብረቱን መሸጥ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ነው? ወይስ ውሉ ከተደረገበት ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም? ጀምሮ የሚለውን ከቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌ አንፃር ለመመርምር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

2ኛ ተጠሪ መጥሪያው ደርሷቸው ስላልቀረቡ መልስ የማቅረብ መብታቸው የታለፈ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ 2ኛ ተጠሪ እና አመልካች አባት እና ልጅ ሲሆኑ አመልካች ክፍፍል ያልተደረገበትን ሰነድ አልባ ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የንብረት ክፍፍል አድርጌበታለው በማለት በሀሰት ባዘጋጀው የክፍፍል ስምምነት መነሻነት የተደረገውን የመንደር የሽያጭ ውል መኖሩን ካወኩበት ሕዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 69 መሰረት በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት የጠየኩ ስለሆነ የይርጋ መቃወሚያው መታለፉ ተገቢ ነው፡፡ ለሽያጭ ውሉ መነሻ የሆነው የስምምነት ክፍፍል በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑ ተረጋግጦ አመልካች በወንጀል የተቀጣ በመሆኑ በወንጀል ድርጊት መነሻ የተፈፀመን ከመነሻው የሌለ ውልን ሊፈርስ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ተገቢ አይደለም፡፡ የክፍፍል ውሉ ላይ 1ኛ ተጠሪ ያልፈረምኩ እና የማላውቀው መሆኑ በፎረንሲክ ተረጋግጦ አመልካች በወንጀል የተቀጡ በመሆኑ ሰነዱ በፎረንሲክ አልተመረመረም በማለት የሚያነሱት ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡ ውሉን አመልካች

ንብረቱን ከ1ኛ ተጠሪ ለማሸሽ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር የፈፀሙት እና ያልተመዘገበ ሕገ ወጥ ውል በመሆኑ የደረሰባቸው ጉዳት የለም፡፡ በተጨማሪም ወደ ነበሩበት ላለመመለስ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ዳኝነት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የተፃፈ የመልስ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከሩት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተደረገ የስምምነት ውል መሰረት ክርክር የተነሳበት ቤት የአመልካች ድርሻ እንዲሆን ተስማምተን፤ ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ያስተላለፍኩ በመሆኑና እንዲሁም በ1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ክስ የቀረበው ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም ስለሆነ በፌደራል የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 69(2) መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የቀረበው መቃወሚያ መታለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ በአንፃሩ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ሰኔ 12 ቀነ 2002 ዓ.ም የንብረት ክፍፍል ስምምነት አለመፈራረማቸውን፤ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም የሽያጭ ውል ማድረጋቸውንም ያወቁትም ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑን፤ ከዚህም ጊዜ ጀምሮ የስድስት ወር ጊዜ ሳያልፈው ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም ውሉ እንዲፈርስ ክስ የመሰረትኩ እና የሽያጭ ውሉም ያልተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጦ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጋራ የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ፣ ለማከራየት፣ በመያዣነት ለመስጠት ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ሌሎች ሰዎች በንብረቱ ላይ መብት እንዲያገኙ ለማድረግ የተጋቢዎቹ የጋራ ስምምነት እንደሚያስፈልግ፤ ከዚህ በተቃራኒ አንደኛው ተጋቢ የውል ግዴታ የገባ እንደሆነ ፍቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ ግዴታው መገባቱን ካወቀበት ግዜ ጀምሮ በ6 ወር ውሰጥ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ግዴታው በተገባ በ2 ዓመት ውስጥ ግዴታው እንዲፈርስ ሊጠይቅ እንደሚችል በፌደራል የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 68(1) እና 69 ላይ ተመላክቷል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪ የሆነውን ቤት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እንደ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ በ1993 ዓ.ም በጋራ የገዙት ሲሆን አመልካችም ይህ ንብረት ከመነሻውም የጋራ ንብረት አይደለም በማለት የሚያቀርቡት መከራከሪያ የለም፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር የንብረት ክፍፍል ማድረጋቸውን በዚህም መነሻነት ቤቱ የአመልካች ድርሻ እንዲሆን ተስማምተው የሽያጭ ውሉ ሰኔ 5 ቀን 2003 ዓ.ም ከተደረገ በኋላ በ2007 ዓ.ም ውሉ እንዲፈርስ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውል መኖሩን ያወቁት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የጋራ

ንብረት ክፍፍል ክስ በኮ/መ/ቁ 90444 መስርተው ክርክር ላይ እያሉ ሕዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም 2ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉን መሰረት አድርገው በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ካቀረቡት አቤቱታ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ ሲሆን አመልካችም ሆነ 2ኛ ተጠሪ ይህን በመቃወም ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ ከዚህም ሌላ 1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ አለመመዝገቡን ጠቅሰው ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካችም ሆነ 2ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ መመዝገቡን ገልጸው ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ ይልቁኑም 2ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ ያልተመዘገበው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ቤቱን በ1993 ዓ.ም የገዙት ባልተመዘገበ ውል በመሆኑ ከአመልካች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውልም ያለመመዝገቡን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ይህም የሽያጭ ውሉ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተፈፀመ እንደመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 1723 በሚደነግገው አግባብ ስልጣን ባለው ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ፅ/ቤት አለመመዝገቡን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ እንዲሁም በፍ/ሕ/ቁጥር 2878 መሰረት ውሉ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት በሚገኝበት አከባቢ በሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት መመዝገቢያ የባህር መዝገብ ላይ አለመመዝገቡን ያሳያል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች ምዝገባ አላማም በተዋዋዮች መካከል ውሉን የተመለከቱ አከራካሪ ሁኔታዎች ቢነሱ ጉዳዩን በቀላሉ እልባት ለመስጠት ለማስቻል እንዲሁም በንብረቱ ሽያጭ ላይ መብት ጠያቂ ሶስተኛ ወገኖች ካሉ ውሉ ስለመደረጉ አውቀው ተገቢውን መፈጸም እንዲችሉ ለማስቻል ነው፡፡ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ውሉን መዋዋላቸው ባይካካዱም ይሕ የሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁጥር 1723 እና 2878 መሰረት ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ የተደረገውን የሽያጭ ውል አውቀው መቃወሚያ ሊያቀርቡበት የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡ በአንፃሩ 1ኛ ተጠሪ ይህ የሽያጭ ውል መኖሩን ያወቁት ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑ እና ውሉ እንዲፈርስ በፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንደሚታወቀው የይርጋ ድንጋጌዎች አላማ መብቱን የሚጎዳ ነገር መፈጸሙን እያወቀ በመብቱ ሳይሰራ የሚቆይን ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብት መገደብ እንጂ መብቱ ስለመነካቱ የማያውቅ ወይም ማወቅ የሚችልበት እድል የሌለውን ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብት መገደብ አይደለም፡፡ የሽያጭ ውሉ ባልተመዘገበበት እና በሌላ ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ ስለሽያጭ ውሉ መደረግ አወኩ ካሉበት ጊዜ በፊት ስለማወቃቸው በአመልካች የቀረበ ክርክር የሌለ ከመሆኑም በላይ 1ኛ ተጠሪ ውሉ አውቀዋል ወይም ማወቅ ነበረባቸው ተብሎ የሚገመተው ውሉ የተመዘገበ ቢሆን ኖሮ ነበር፡፡ ይህ ባልሆነበት ውሉ በተደረገበት በ2 ዓመት ውስጥ ክስ ማቅረብ ነበረባቸው የሚለው የአመልካች ክርክር የቤተሰብ ህጉን አንቀጽ 69 አላማ እና መንፈስ ያላገናዘበ ከመሆኑም በተጨማሪ ከተጋቢዎች አንዱ የሌላኛውን ፍቃድ ሳያገኝ ውል እየተዋዋለ የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ እስኪያልፍ ደብቆ በማቆየት በውሉ ላይ ፍቃደኝነቱን ያልገለጸውን ተዋዋይ ወገን ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብቱን አላግባብ እንዲያጣ የሚያደርግ ነው፡፡ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረጉ ውሎች በሚመለከተው አካል እስካልተመዘገቡ ድረስ የውል ይፍረስልኝ ክስ ማቅረቢያ የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ መቆጠር መጀመር ያለበት በውሉ ላይ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ የውሉን መደረግ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም ማለት በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 69 በማንኛውም ሁኔታ ውሉ ከተደረገበት ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ የውል ይፍረስልኝ ክስ መቅረብ አለበት የሚለው ድንጋጌ ተፈጻሚ መሆን

ያለበት እንዲፈርስ የሚጠየቀው ውል በሚመለከተው የመንግስት አካል የተመዘገበ ከሆነ ወይም ባይመዘገብ እንኳን በሌላ አግባብ ስለውሉ መደረግ በሚያውቅ ተጋቢ ላይ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ በቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 69 ላይ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ መቆጠር መጀመር ያለበት 1ኛ ተጠሪ ውሉ መደረጉን ካወቁበት ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ መሆን ስለሚገባው እና 1ኛ ተጠሪም የሽያጭ ውሉ መደረጉን ካወቁበት ጀምሮ ክስ እስከ መሰረቱበት ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም 6 ወር ሳይሞላው ክስ የመሰረቱ በመሆኑ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ በኩል የተነሳው የይርጋ መከራከሪያ መታለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም፡፡

በመቀጠልም የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ስንመለከት አመልካች አከራካሪውን ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት መሆኑን ሳይክዱ ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተደረገ የክፍፍል ስምምነት የአመልካች ንብረት እንዲሆን 1ኛ ተጠሪ የተስማሙ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ነገር ግን ሰኔ 12 ቀን 2012 ዓ.ም የንብረት ክፍፍል ተደርጎበታል በተባለው ሰነድ ላይ 1ኛ ተጠሪ አለመፈረማቸው እና አመልካች ሰነዱን በሐሰት ያዘጋጁት መሆኑ ተረጋግጦ አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 161234 በወንጀል የተቀጡ ሲሆን ይህ የጥፋተኝነት ውሳኔም በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁ 164836 በተሰጠ ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ይህ የወንጀል ውሳኔ በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ እንዳለ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ (Conclusive Evidence) በመሆኑ አመልካች በስር ፍ/ቤት ፊርማው በፎረንሲክ ሳይመረመር የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሚያነሱት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የንብረት ክፍፍል ስምምነት በሀሰት የተዘጋጀ በመሆኑ እንዲሁም በሽያጭ ውሉ 1ኛ ተጠሪ ፍቃዳቸውን ያልሰጡ መሆኑ በመረጋገጡ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡

አመልካች በይዞታው ላይ ከሽያጭ ውሉ በኋላ በ2ኛ ተጠሪ ተጨማሪ ግንባታ መደረጉን በመግለፅ ተዋዋዮችን ወደ ነበርንበት መመለስ አይቻልም፤ ውሉ እንዲፈርስ ሲወሰንም አንደኛው ወገን ያለአግባብ የሚበለፅግ መሆን አለመሆኑ ከግምት ውስጥ ሳይገባ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ይህ መከራከሪያ ሊቀርብ የሚገባው በ2ኛ ተጠሪ በመሆኑ እና 2ኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ስለማቅረባቸው ወይም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክር መጥሪያ የደረሳቸው ቢሆንም ቀርበው ይህን ገልፀው ያቀረቡት መከራከሪያ እና የመስቀለኛ የሰበር አቤቱታ ስለሌለ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 100686 የካቲት 22 ቀን 2008 እና ሚያዝያ 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ብይንና ፍርድ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁጥር

237723 ታህሳስ 7 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝብ ቤት**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 203209

ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች** - አቶ ስንታየሁ አባተ

**ተጠሪ** - ወ/ሮ ታድፋለች ገላዬ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ የተሰጠ ፍርድ የሚፈጸምበትን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የጉዳዩም አመጣጥ በባህር ዳር ከተማ ግሽ አባይ ክ/ከተማ በ500 ካ/ሜትር ቦታ ለይ የሚገኘዉ ቤት የጋራ ነዉ በማለት ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 03-21833 ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት የድርሻቸው እንዲሰጣቸው ግራ ቀኝ ያቀረቡትን የአፈፃፀም አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የመኖሪያ ቤቱ በአይነት መከፈል የማይችል መሆኑ በባለሞያ ተረጋግጧል በማለት በጨረታ ተሸጦ ገንዘቡን ግራ ቀኙ ይካፈሉ በማለት ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ቅር የተሰኙት አመልካች ቤቱ ያረፈው በ500 ካ.ሜ ይዞታ ላይ በመሆኑ ክፍለ ከተማው ካርታ ከተሰራለት ስሙ-ንብረት ማዞር እንደሚቻል ያረጋገጠልን ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጊዜ ሰጥቶን

ካርታ ካሰራን በኂላ እኩል እንዲከፈል ማድረግ ሲገባው ቤቱ በኃራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ መስጠቱ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ለባህር ዳር እና አካባቢው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይት አላገኘም፡፡ አመልካች አሁንም በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይህም አቤቱታ ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 18/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው የጠየቁ ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት በባህርዳር ከተማ ግሽ አባይ ክ/ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የክፍለ ከተማው ከተማ ልማትና ቤቶች ኮንስትራክሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ካርታ ለመስጠት ጊዜ ይሰጠኝ በማለት ጠይቆ እያለ የኃራጅ ሽያጪ ሂደት ቅደም ተከተል ሳይጠበቅ፣ ግምቱን እየተቃወምኩ፣ ካርታ ከተሰራለት ለሁለት መከፈል እንደሚችል ተረጋግጦ እና ግራ ቀኞችን ተስማምተን በገበያ ዋጋ ለመሸጥ እድል ሳይሰጠን በኃራጅ ይሸጥ ተብሎ ትዕዛዝ መሠጠቱ መሠረታዊ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አከራካሪው ይዞታና ቤት የግራ ቀኙ በሆነበትና በፍርዱም ላይ ከተቻለ በአይነት እንዲካፈሉ ተብሎ እያለ የስር ፍርድ ቤት በቀጥታ ወደ ጨረታ ሂደት የገባበት አግባብ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 20/07/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው የሰበር ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ ከአንድ ዓመት በፊት በባህር ዳር እና አካባቢው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 03-21833 ውሳኔ የተሰጠበትና ይዘቱም ቤቱ በጨረታ እንዲሸጥ የታዘዘበት ሲሆን አመልካች ይህንን ውሳኔ ሳያሽሩ ተጠሪ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትዕዛዝ መነሻ በማድረግ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፤ የስር ፍርድ ቤቶችም ቤቱ በኃራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጡት በዓይነት መከፈል እንደማይችል አረጋግጠው ስለሆነ የሰጡት ትዕዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የግራ ቀኝ የጋራ ንብረት የሆነዉ እና ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ቤት በባህር ዳር ከተማ በግሽን ክ/ከተማ በ500 ካ/ሜትር ላይ የሚገኝ ቤት ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህ ቤትና ይዞታ ካርታ ከተሰራለት በኂላ በዓይነት መካፈል እንደሚቻል ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ቤቱ በሃራጅ ሊሸጥ ይገባል በሚል ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉን ትዕዛዝ የሰጠዉ ቀደም ሲል በጨረታ ይሸጥ

በተባለዉ ላይ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽናቱንና ወደ ኃላ ተመልሶ ካርታ በቅድሚያ ካርታ ይሰራ የሚል ትዕዛዝ መስጠት የማይችል መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 79/95 ከአንቀጽ 101-103 ባሉት ድንጋጌዎቹ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት በዓይነት እንዲከፋፈል ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባዉ የክፍፍል ሥርዓት መሆኑን እና በግራ ቀኝ ስምምነት ለአንደኛዉ ተጋቢ ንብረቱ እንዲሰጥ የማይደረግ ከሆነ ንብረቱ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚደረገዉ ንብረቱን በዓይነት ማካፈል እንደማይቻል ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰዉ ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባዉ የክፍፍል ሥርዓት ሲሆን በዚህ መልኩ እኩል ማከፋፈል የማይቻል የሆነ እንደሆነ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ በማድረግ ክፍፍሉን መፈጸም እንደሚገባ በህጉ አንቀጽ 102 (1 እና 2) ላይ ከተመለከቱት ግልጽ ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ህጉ የአከፋፈል ሥርዓቱ በዚህ ቅደም ተከተል እንዲከናወን ሲደነግግ መሠረት ያደረገዉ አንድም ንብረቱ በተቻለ መጠን ከተጋቢዎች እጅ እንዳይወጣ ጥበቃ ለማድረግ ሁለትም የክፍፍሉን ፍትሐዊነት በማረጋገጥ ባልና ሚስት በጋራ ንብረቶቻቸዉ ላይ ያላቸዉን የእኩልነት መብት እዉን ለማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ከባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ የሚነሳን ክርክር በተመለከተ የሚሰጥ ዉሳኔም ይህን ሁሉ ከግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነዉን ቤትና ይዞታ በተመለከተ በዓይነት ማካፈል አይቻልም የተባለዉ ከክፍፍሉ በፊት ካርታ ሊሰራበት ይገባል በሚል ምክንያት ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ ቤቱን ለሁለት እኩል ማካፈል እንደማይቻል ሌላ የተለየ ምክንያት አልቀረበም፡፡ ክፍፍሉ በዓይነት ከተደረገ በኋላ ግራ ቀኝ በየበኩላቸዉ በደረሳቸዉ የይዞታ መጠን ልክ ካርታ እንዳይሰጥ የሚያደርግ ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ካርታ የሚሰጥበትን ጊዜን መጠበቅ ሳያስፈልግ ይዞታዉን ከላዩ ላይ ካለዉ ንብረት ጋር በዓይነት ማካፈል ይቻላል፡፡ በመሆኑም ካርታ በይዞታዉ ላይ አለመሠራቱ ወይም ዘግይቶ የሚሰራለት መሆኑ ግራ ቀኝ የጋራቸዉ መሆኑ ተረጋግጦ ፍርድ ያረፈበት እና በ500 ካ/ሜትር ይዞታ ላይ ያረፈ ቤት ግራ ቀኝ በዓይነት ለሁለት እንዳይካፈሉ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ የሰጠዉ ትዕዛዝ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል የሚፈጸምበትን ሥርዓት እና ቅደም ተከተል አስመልክቶ በክልሉ የቤተሰብ ህግ ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላዉ የተጠሪ ክርክር ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ አስቀድሞ በወረዳዉ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለፀና በድጋሚ የቀረበ ነዉ የሚል ነዉ፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በመቃወም የቀረበለትን ይግባኝ ዉድቅ ያደረገዉ ይህንኑ ምክንያት በመጥቀስ ስለመሆኑ መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመሠረቱ አፈፃፀም በፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን በተሰጠዉ አካል የሚሰጥ ፍርድ ወደ ተግባር የሚቀየርበት ሥርዓት በመሆኑ ፍርድ እንዲያስፈጽም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ፣ ማለትም በፍርዱ ላይ በተመለከተዉ ላይ ሳይጨምር ወይም ሳይቀንስ፣ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ዳኝነት ያላግባብ የተወሰደ ንብረት ወይም ሀብት እንዲመለስ ወይም

ገንዘብ እንዲከፈል ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ በሚሰጥ ዉሳኔ የፍርድ ባለመብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ በተሰጠ ፍርድ መሠረት የተፈጸመለት እንደሆነ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ጉዳይ የሚፈጀዉ ጊዜ እንደ የጉዳዩ ዓይነትና ባህርይ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም፣ ክስ ከቀረበበት ጀምሮ እስከ ዉሳኔ ድረስ ያለዉ ሂደት የተወሰነ ጊዜ መዉሰዱ አይቀሬ ነዉ፡፡ በዚህም ሂደት የፍርድ ቤት ብሎም የተከራካሪ ወገኖች ጊዜይባክናል፤ ወጪና ድካም ይኖራል፡፡ ስለሆነም ፍርድን እንደ ፍርዱ ማስፈጸም ይህን ሁሉ ሂደት በማለፍ የተሰጠ ፍርድ ፍሬ አልባ እንዳይሆን የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ፍርድ ተፈፃሚነቱ ተገማች እንዲሆን ያስችላል፡፡ የፍት/ብ/ሥነ ሥርዓት ህጋችን ሰባተኛ መጽሐፍ ከአንቀጽ 371 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎቹ የፍርድ አፈፃፀም የሚመራበትን ሥነ-ሥርዓት ይደነግጋል፡፡ የፍርድ አፈፃፀም የቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ የመጽሐፉ ክፍል እንዲሁም ስለአፈፃፀም አስመልክቶ በሌላ ህግ የተመለከተም ካለ በዚህ መልኩ የተዘረጋዉን ስርዓት በመከተል ድንጋጌዎቹን እንደየአግባብነታቸዉ ተግባራዊ በማድረግ አፈፃፀሙን በመምራት እንደ ፍርዱ የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡ የፍርድ አፈፃፀም ዓላማ ፍርድ ወደ ተግባር እንዲለወጥ ማድረግ በመሆኑ አፈፃፀሙን የያዘ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ክርክርን አስመልክቶ የተቀረጹትን የፍት/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን ድንጋጌዎች መከተል ሳያስፈልገዉ ከአፈጻጸም ጋር ተያይዞ የተዘረጋዉን ሥርዓት መሠረት በማድረግ አፈፃፀሙን የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 394-403 ባሉት ድንጋጌዎቹ ስለ አፈፃፀም ሥርዓት (Modes of Execution) የሚደነግግ ሲሆን፣ እነዚህም ድንጋጌዎች በፍርዱ የተሰጠዉን ዳኝነት ዓይነት መሰረት በማድረግ የሚፈጸሙ ስለመሆናቸዉ ከየድንጋጌዎቹ ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነዉ የባልና ሚስት ንብረትን አስመልክቶ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ በፍርዱ መሠረት ተፈጽሟል ለማለት የሚቻለዉ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል አስመልክቶ በክልሉ የቤተሰብ ህግ ላይ በተመለከተዉ አግባብ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ክፍፍሉ የተደረገ እንደሆነ ነዉ፡፡ አፈፃፀሙ ይህን ተከትሎ የተደረገ አለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ቀደም ሲል በጉዳዩ ላይ ይግባኝ መቅረቡ ፍርድ ቤቱ አፈፃፀሙ ፍርዱን እና ህጉን የተከተለ መሆን ያለመሆኑን አይቶ በህጉ አግባብ አፈፃፀሙን መርቶ ፍርዱን እንዳያስፈጽም ምክንያት አይሆንም፡፡ በመሆኑም ይህን አስመልክቶ ተጠሪ ያቀረበዉ ክርክር የክርክሩን መሠረታዊ ባህርይ ከግምት ዉስጥ ያላስገባ በመሆኑ ይህ ችሎት አልተቀበለዉም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1. የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 41017 በቀን 09/03/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን፣ የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0324545 በቀን 23/04/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ፍርድ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 101268 በቀን 09/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

2. የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤትና ይዞታ ለግራ ቀኝ እኩል እንዲካፈሉ በማድረግ እንዲያስፈጽም ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 26/06/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# የዳኘነት ስልጣን

**የሰ/መ/ቁ.** 204107

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች** - ብዙነህ ቢሌ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ

**ተጠሪ** - ሲ.አር.ሲ.ሲ ጋምቤላ አቦቮ ፑኚዶ መንገድ ስራ ፕሮጀክት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በጋምቤላ ክልል አኙዋክ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ውል ለአስፋልት ስራ የሚውል ጠጠር በጥራትና በብዛት በወር አስር ሺ ሜትር ኩብ በጠቅላላ መቶ ሀምሳ ሺ አምርቶ እንዲያቀርብ ግዴታ ቢገባም ያመረተው ግን ጥራቱን ያልጠበቀ አስራ አምስት ሺ ሜትር ኩብ ብቻ ነው፤ አመልካች በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ በሚፈለገው ጥራትና መጠን ጠጠሩን ባለማቅረቡ በአማካሪ ድርጅቱ ማስጠንቀቂያ ሲሰጠው ምርቱን እንደማሻሻል ስራውን አቋርጦ ሔዷል፤ በዚህም ምክንያት በተጠሪ ላይ የብር 5,700,21000.00 ኪሳራ የደረሰብኝ በመሆኑ አመልካች ይህንን ገንዘብ ለተጠሪ ይክፈል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቆ ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው የሚሉ መቃወሚያዎችን ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ ደግሞ በገባነው የውል ግዴታ መሠረት ማሽን እና ተሽከርካሪ ወደ ሳይት በማስገባት ስራ የጀመርን ሲሆን ያመረትነው ጠጠር የጥራት ችግር እንዳለበት አልተገለፀልንም፤ ስራውንም ያቆምነው በተጠሪ ጥፋት በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገ ሲሆን ፍሬ ነገሩን በሚመለከት ደግሞ አመልካች በውሉ ላይ የገባውን ግዴታ ያላከበረ በመሆኑ ውሉ እንዲሠረዝ፣ አመልካች በተጠሪ ሳይት ላይ የተከለውን ክሬሸር እንዲያነሳ እና ስራ በመዘግየቱ ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰው ኪሳራ በባለሞያ ተሰልቶ ኪሳራ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ የተከራከሩበት ሲሆን ፍርድ ቤቱም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ የሰጠውን

ውሳኔ በማሻሻል አመልካች ተጠሪ በክሱ ላይ እንዲከፈለው የጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍለው፣ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ያመረተው 10,000 ሜትር ኪዩብ ጠጠር እንዲረከብና ሂሳቡን እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህም ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 07/07/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን እንደሌለው ጠቅሼ ያቀረብኩት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት እና የፌደራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ መሠረት ያላደረገ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፣ እንዲሁም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ደረሰ የተባለውን ኪሳራ በሚመለከት በባለሞያ ተጣርቶ ይከፈል ያለውን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የባለሞያ አስተያየት ሳይሰማ ዳኝነት የተጠየቀበትን ገንዘብ እንድንከፍል መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪ የጠየቀው ገንዘብ በባለሞያ ተጣርቶ ሳይቀርብ አመልካች እንዲከፍል የወሰነበትን አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት በቀን 30/07/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በሁለት ወራት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያላቀረበ በመሆኑ አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ደግሞ CRCC 21 ጋምቤላ-አቦቦ-ፑኝዶ መንገድ ስራ ፕሮጀክት አዲስ አበባ ካለው CRCC 21 የተለየና የተጠሪ አድራሻ በጋምቤላ ክልል ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤ አመልካች በውሉ ላይ የተቀመጠውን ግዴታ ባለመወጣቱ በተጠሪ ላይ ለደረሰው ኪሳራ በውሉ መሠረት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ሰበር ሰሚዉ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም የሚል ትዕዛዝ መስጠቱ ከአመልካች አቤቱታ ጋር ተያይዞ ከቀረበዉ የትዕዛዙ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአቤቱታዉ የማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ ነዉ

በሚል አቤቱታዉን ዉድቅ እንዳደረገ በመጥቀስ ተጠሪ በዚህ ችሎት የሚያቀርበዉ ክርክር የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ትክክለኛ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት አልተቀበለዉም፡፡

በመቀጠል መታየት ያለበት ነጥብ የጋምቤላ ክልል የአኙዋ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህን ጉዳይ ተቀብሎ የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን ያለመሆኑ ነዉ፡፡ አመልካች ነዋሪነቱ አዲስ አበባ ከመሆኑም በላይ ተጠሪም በቻይና አገር የተቋቋመ ድንበር ተሻጋሪ የኮንስትራክሽን ድርጅት መሆኑ የሚታወቅ ነዉ፡፡ ይህ መሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ስልጣን ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2/ እና 4) መሠረት ጉዳዩን የማየት ስልጣኑን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያደርገዋል፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2 እና 4) የክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፣ በቅደም ተከተል፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን በዉክልና የማየት ስልጣን እንዳላቸዉ የሚደነግግ ሲሆን ይሄዉ ህገ መንግስት በአንቀጽ 78 (2) ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትንም ሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል ማደራጀት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን በተወሰኑ ክልሎች ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ቁጥር 322/95 በተወሰኑ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲደራጁ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ሲሆን በዚህ አዋጅ መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተደራጀባቸዉ ክልሎች ዉስጥ አንዱ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣንን የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉክልና የማየት ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡

በሌላ በኩል፣ ምንም እንኳ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በዉክልና ለማየት ያለዉ ስልጣን ያልተነሳ ቢሆንም፣ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ጉዳይ ከገንዘብ መጠን አንፃር ሲታይ ከብር 500,000.00 በላይ በመሆኑ ክርክሩ በተጀመረበት ወቅት በስራ ላይ በነበረዉ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 14 መሠረት ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን በላይ በመሆኑ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዉክልና ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለዉም፡፡ እንደሚታወቀዉ አንድ የፍትሐብሔር ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቅድሚያ እንዲያከናዉን ከሚጠበቁበት ተግባራት ዉስጥ አንዱ የቀረበለት ክስ ህጋዊ ብቃት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን የማረጋገጥ ተግባር ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 231 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህን ሲያረጋግጥ መሰረት የሚደርገዉም በከሳሽ የቀረበዉን ክስ መሠረታዊ ይዘት እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን ማንነት እና አድራሻ መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ የቀረበዉ ክስ ህጋዊ ብቃቱን ያሟላ መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ ግምት ዉስጥ መግባት ካለባቸዉ ሁኔታዎች ዉስጥም አንዱ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን ያለመሆኑ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 231 (1/ለ) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የህጉ አንቀጽ 9 ድንጋጌም ይህንኑ የሚስገነዝብ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቶች ክርክሮችን በዘፈቀደ ሳይሆን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ

የተዘረጉትን ደንቦች እና መርሆችን መሠረት በማድረግ ሊሆን እንደሚገባ መገንዘቡም ተገቢ ነዉ፡፡ የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ከተከራካሪ ወገኖች ማንነት አንፃር ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ሆኖ ዳኝነት ከተጠየቀበት የገንዘብ መጠን አንፃርም ሲታይ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን በላይ በመሆኑ ክርክሩን ተቀብሎ የማየት ስልጣኑ በማንኛዉም ሁኔታ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር ሊወድቅ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ በመሆኑም ከአኙዋክ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያለ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ይህን ባለማድረግ ክርክሩን ተቀብሎ ዉሳኔ መስጠቱም ሆነ በክልሉ በየደረጃዉ ያሉ ፍርድ ቤቶችም ይህን ማረም ሲገባቸዉ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ያለ ስልጣኑ የሰጠዉን ዉሳኔ መሠረት በማድረግ በዋናዉ ጉዳይ ላይ አከራክረዉ በየበኩላቸዉ የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የአኙዋ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02258 በቀን 20/02/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02809/2013 በቀን 02/04/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00988/2013 በቀን 22/06/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. የአኙዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለዉም፡፡
3. ተጠሪ መብቱን ለማስከበር ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት የሚያቀርበዉን ክስ ይህ ዉሳኔ አይከለክልም፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 09/07/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ. 220566

መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**1. ብርሃኑ አመነዉ

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. በዕዉቀት በላይ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ሌሊሴ ደሳለኝ

6. ተሾመ ሽፈራዉ

7. ኑረዲን ከድር

**አመልካች**.....ሐጂ መሀመድ እስማኤል

**ተጠሪ**......1. የድሬዳዋ አስተዳደር ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ

2. አቶ ጌታቸዉ ረጋሳ ካባ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሊዝ ዉልን መነሻ ያደረገ ክርክር የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.17839 በ14/3/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በሕግ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ከሲራክ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር በዕዳ ምክንያት ወርሶ በጨረታ የሸጠልኝ ስፋቱ 11410 ካ.ሜ የሆነዉን በማዕድን ዉሃ ማምረቻ ፋብሪካ በስሜ እንዲመዘገብ በጠየቅኩኝ መሰረት በካርታ ቁጥር መል/ሊ/3095 በስሜ ተመዝግቦልኝ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የሊዝ ዉል ተዋዉለን ሥራዉን ለማስቀጠል የዉሃ ጉድጓድ ለማስቆፈር በዝግጅት ላይ እያለሁኝ፤ 1ኛ ተከሳሽ ከተሰጠኝ ይዞታ ዉስጥ 8620 ካ.ሜ ቦታ ቀንሶ ለ2ኛ ተከሳሽ በሊዝ ዉል የሰጠዉ በመሆኑ፤ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ያደረኩኝ የሊዝ ዉል ሊሰረዝ የሚችልበት ምክንያት ስለሌለ 1ኛ ተከሳሽ ከዉላችን ዉጭ ቀንሶ ለ2ኛ ተከሳሽ በካርታ ቁጥር መል/ሊ/5455 የሰጠዉ የ8620 ካ.ሜ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰረዝልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተከሳሽ (የአሁን 1ኛ ተጠሪ) በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ይህ ጉዳይ በቀጥታ ክስ በመደበኛ ፍ/ቤት የሚታይ ባለመሆኑ ክሱ ዉድቅ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ በፍሬ

ነገር ክርክር 1ኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ቦታ ቀንሶ ለ2ኛ ተከሳሽ የሰጠዉ በተደረገዉ የሊዝ ዉል እና በሕግ መሰረት ከሳሽ በቦታዉ ላይ ምንም ሥራ ባለመስራቱ እና ላለመስራቱም ከአቅም በላይ ችግር የገጠመዉ ስለመሆኑ በሊዝ ዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ያላሳወቀዉ በመሆኑና አምስት አመቱም የተጠናቀቀ በመሆኑ፣ ከዚህ በላይ ጊዜ ሊሰጠዉ የማይችል በመሆኑ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተከሳሽ (የአሁን 2ኛ ተጠሪ) በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የከሳሽ የሊዝ ዉል በሊዝ አዋጁ፣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ተሰርዞ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ግንቦት 24 ቀን 2009 ዓ.ም ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ያደረገዉ በመሆኑ፤ ፍ/ቤቱ ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለዉም፡፡ በፍሬ ነገር ክርክር ከሳሽ በተሰረዘና በሌለ ዉል ክስ ማቅረብ አይችልም፤ ክሱ እኔን አይመለከተኝም፤ ከሳሽ መከራከር ካለበት ዉሉን ካደረገዉና ከሰረዘዉ አካል ጋር እንጂ ከእኔ ጋር መሆን የለበትም፤ ለእኔ ካርታ የተሰጠኝ ሕጉን ተከትሎ በመሆኑ ሊሰረዝ የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠዉ ትዕዛዝ ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ከሳሽ ለክሱ ምክንያት ያደረገዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመከና መሆኑን ስላረጋገጠ፣ ይህ ደግሞ የከሳሽን ክስ ቀሪ የሚያደርግ በመሆኑ፣ በክርክሩ ሂደት ለክሱ መነሻ የሆነዉ ነገር ተቋርጧል በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ከሳሽ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከረ ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ ያደረኩኝ የሊዝ ዉል እያለ 1ኛ ተከሳሽ ከዉላችን ዉጭ በመሰረዝ እና በሊዝ ካገኘሁት ይዞታ ላይ ቀንሶ ለሌላ ሰዉ መስጠቱ ሕጋዊ አይደለም የሚል በመሆኑ፣ የከሳሽ የዳኝነት ጥያቄ የሊዝ ዉል አፈጻጸምን የሚመለከት በመሆኑ፤ ይህ ጉዳይ በፍ/ቤት መታየቱ ተገቢ ቢሆንም ከከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት እና ከመደበኛ ፍ/ቤት መካከል በየትኛዉ ፍ/ቤት መታየት አለበት የሚለዉ ነጥብ ምላሽ የሚፈልግ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33 (1) (ሀ) እና (መ) መሰረት የከተማ አስተዳደር ዉሎችን በተመለከተ እና የከተማዉን መዋቅራዊ ፕላን አስመልክቶ በሚነሱ ክርክሮች ላይ አከራክሮ ለመወሰን የሥረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆኑን ስለሚያስገነዝብ፤ የሊዝ ዉል ደግሞ ከሊዝ አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ ከወጡ ሕጎች እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132 መሰረት የአስተዳደር ዉል መሆኑን ስለሚያመለክት፤ የሥር ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ተቀብሎ የማከራከር የሥረ-ነገር ስልጣን የድሬዳዋ ከተማ ፍ/ቤት ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ25/5/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረግነዉ የሊዝ ዉል 1ኛ ተጠሪ ከሕግ ዉጭ በመሰረዝ ከይዞታዉ ቀንሶ ለ2ኛ ተጠሪ መስጠቱ

ሕገወጥ ተግባር መሆኑን በመግለጽ ክስ ያቀረብኩኝ በመሆኑ፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰ.መ.ቁ.150925 በ27/10/2010 ዓ.ም በሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ ከድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/96 አንቀጽ 33 እና 3132 መሰረት የድሬዳዋ ከተማ ፍ/ቤቶች ከሊዝ ዉል ጋር ተያይዞ የሚቀርበዉን ዳኝነት አይተዉ ለመወሰን የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን እንደሌላቸዉ እና ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆናቸዉን የወሰነ ሆኖ ሳለ፣ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ፤ ጉዳዩ ወደሥር ፍ/ቤት ተመልሶ በፍሬ ነገር ክርክር ታይቶ ዉሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ተቀብሎ የማከራከር የሥረ-ነገር ስልጣን የለዉም በሚል የወሰነበትን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 416/1996 እና የሰ.መ.ቁ.150925 ላይ ከተሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት 1ኛ ተጠሪ በ20/8/2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የዳኝነት ስልጣን የለዉም፣ ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በ20/8/2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የዉሳኔ ምክንያት በመለወጥ እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠዉ ምክንያት፣ ዉሳኔዉ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር በ8/9/2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር 1ኛ ተጠሪ በሊዝ ዉል ያገኘሁትን ይዞታ ከሊዝ ዉሉ ዉጭ በመቀነስ ለ2ኛ ተጠሪ በሊዝ ዉል የሰጠ በመሆኑ፣ የ1ኛ ተጠሪ ተግባር ከሕግ ዉጭ በመሆኑ በሊዝ ዉል ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ እንዲሰረዝልኝ የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ደግሞ አመልካች በሊዝ ዉል የተሰጠዉን ይዞታ በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ስላልሰራበት በሕግ አግባብ ይዞታዉ የተወሰደ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህ ጉዳይ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር እያየ እያለ የአመልካች ካርታ መሰረዙ ስለተገለጸ ክስ የቀረበበት ምክንያት ቀሪ ሆኗል በማለት መዝገቡን የዘጋ ሲሆን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ ክርክሩን በማየት ይህ ጉዳይ የሊዝ ዉል አፈጻጸምን የሚመለከት ስለሆነ

ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት መሆኑን በማመልከት የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የላቸዉም በማለት መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት የግራ ቀኙ ክርክር የሊዝ ዉል አፈጻጸምን የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ነዉ ወይስ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸዉ? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካቾች በእነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ባለስልጣን ሁለት ሰዎች እና በተጠሪ ድንቅ ስራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል የነበረዉን ክርክር በመመርመር በሰ.መ.ቁ.54697 መስከራም 24 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ጉዳዩ የሊዝ ዉልን መሰረት አድርጎ ለአንድ ሰዉ የተሰጠ ቦታ ለሌላ ሰዉ ሲሰጥ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለዉ አካል የትኛዉ ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ፣ የሥር ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የአመልካቾችን መከራከሪያ ነጥቦችን በመመርመር ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በማለት መወሰኑን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ይህን የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻር ጉዳዩን የማየት ሥረ-ነገር ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸዉ በማለት የወሰነዉን በመመርመር፣ ይህ ጉዳይ በፍ/ቤት የሚታይ ነዉ መባሉ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ስልጣን ያላቸዉ ፍ/ቤቶች የትኞቹ ናቸዉ (የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ወይም የፌዴራል ፍ/ቤቶች)፣ የተጠሪ ክስ መሰረቱ የሊዝ ዉል ሆኖ ዉሉ ተጥሷል በሚል ዳኝነት የጠየቁ በመሆኑ፣ የተጠሪ ጥያቄ የክፍለ ከተማ አስተዳደር ከሕግ ዉጭ በሊዝ የተወሰደ ቦታ ለመዉሰድ ካርታና የምስክር ወረቀት በመሰረዝ ሕገወጥ እርምጃ ፈጽሟል በማለት በሊዝ ዉል ያገኙት የንብረት መብታቸዉ (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (6) ይመልከቷል) በፍርድ እንዲጠበቅላቸዉ የሚጠይቅ በመሆኑ በፍ/ቤት ሊያስተናግድ የሚገባዉ እና ዉሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ በመሆኑ እና መታየት ያለበትም በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤቶች በመሆኑ፣ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 (1) (ሀ) እና (መ) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንጻር ሕጋዊ ሆኖ አግኝተናል በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔን በማጽናት መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች በድሬዳዋ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማንጅመንት ቢሮ እና በተጠሪዎች በእነ አቶ ደጉ ወ/ሚካኤል ሁለት ሰዎች መካከል በነበረዉ ክርክር በሰ.መ.ቁ.150925 ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም በሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ አመልካች በሊዝ ዉል መሰረት የተሰጠኝን ይዞታ በተመለከተ የሊዝ ዉልን በማቋረጥ ካርታዉን በማምከን፣ ለ2ኛ ተጠሪ ይዞታዉን በሊዝ ዉል በመስጠት ካርታ የሰጠ በመሆኑ፣ የ1ኛ

ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የሊዝ ዉል እንዲጸናልኝ እና ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የተደረገዉ የሊዝ ዉል እንዲሰረዝ የሚጠይቅ መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ፤ የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33 መሰረት የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶችን ስልጣን የሚያመለክት ቢሆንም ከዚህ የአዋጁ ደንጋጌ እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132 አንጻር ሲታይ 1ኛ ተጠሪ የእኔ የሊዝ ዉል እንዲጸናልኝ እና ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የተደረገዉ የሊዝ ዉል እንዲሰረዝልኝ በማለት ያቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ የአስተዳደር ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቅ ሆኖ አልተገኘም፤ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ ሰምተዉ ለመወሰን የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የላቸዉም በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር መወሰኑን ያመለክታል፡፡

በመሆኑም ከፍ ሲል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.54697 በሰጠዉ ዉሳኔ የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጦብኛል በዉሉ ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ በማለት የሚቀርበዉ የዳኝነት ጥያቄ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሥር እንደሚወድቅ የሚል ሲሆን፣ በሰ.መ.ቁ.150925 በሰጠዉ ዉሳኔ ደግሞ የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጦብኛል በዉሉ ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ በማለት የሚቀርበዉ የዳኝነት ጥያቄ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የላቸዉም በማለት መወሰኑን ያሳያል፡፡ ምንም እንኳን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር ራሳቸዉን የቻሉ ከተሞች ቢሆኑም ሁለቱም ከተሞች በቻርተር የሚተዳደሩና ተጠሪነታቸዉ ለፌዴራል መንግስት በመሆኑ፤ የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 (1) (ሀ) እና (መ) እና የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33 (1) (ሀ) እና (መ) ተመሳሳይ ይዘትና ዓላማ ያላቸዉ ድንጋጌዎች መሆናቸዉን ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህ የአዲስ አበባ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር ድንጋጌዎች ተመሳሳይ ይዘትና ዓላማ ያላቸዉ ሆኖ ሳለ፣ የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋረጦብኛል መብቴ እንዲከበርልኝ በማለት የሚቀርበዉን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ በአዲስ አበባ አስተዳደር በከተማዉ አስተዳደር ፍ/ቤቶች እንደሚታይ፣ እና በድሬደዋ አስተዳደር ደግሞ በከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች እንደማይታይና የፌዴራል ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሥር እንደሚወድቅ መወሰኑን ያመለክታል፡፡ እነዚህ ሁለቱ የሰበር ዉሳኔዎች እርስ በእርሳቸዉ የሚቃረኑ በመሆናቸዉ እና ተከራካሪ ወገኖችን ላልተፈለገ ክርክር የሚዳርጉና ችሎቱም ወጥና ተመሳሳይ የህግ ትርጉም እንዳይሰጥ እንቅፋት የሚሆኑ በመሆናቸዉ፣ እነዚህን ዉሳኔዎች አንድ ላይ አድርጎ አንድ ወጥ የሆነ የህግ ትርጉም እንዲኖር ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ህዳር 28 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት በሰ.መ.ቁ.54697 እና 150925 በሆኑት መዛግብት ላይ የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጧብኛል መብቴ እንዲከበርልኝ በማለት የሚቀርበዉን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ ከፍ/ቤቶች ስልጣን አንጻር ዉሳኔዎቹ መካከል ቅራኔ ወይም ግጭት መኖሩን ስለሚያመለክት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች ለሚሰየሙበት ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት እንዲቀርብ

በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26 (1) መሰረት አዟል፡፡ በዚህ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 26 (2) መሰረት ጉዳዩ በሰባት ዳኞች እንዲታይ በ07/4/2015 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ አግባብ ይህ ጉዳይ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት አመልካች ባቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ 1ኛ ተጠሪ የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ በመሰረዝ በዉሉ ያገኘሁትን ይዞታ በመቀነስ ለ2ኛ ተጠሪ በሊዝ ዉል በመስጠት ካርታ የሰጠዉ በመሆኑ ይህ የ1ኛ ተጠሪ ድርጊት ከሕግ ዉጭ በመሆኑ ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰረዝልኝ በማለት መጠየቁን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አመልካች የሊዝ ዉልን ሊያሰርዝ ወይም ሊያቋርጥ የሚችል ምንም ዓይነት ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር በሊዝ ዉሉ ያገኘሁት ይዞታ ተቀንሶ ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ይዞታ ከሕግ ዉጭ ስለሆነ በሊዝ ዉል ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ በማለት የጠየቀዉ ዳኝነት ከሊዝ ዉል አፈጻጸም ጋር የተያያዘ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀዉ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 2 (1) መሰረት ‹‹ሊዝ›› ማለት በጊዜ በተገደበ ዉል መሰረት የከተማ ቦታ የመጠቀም መብት የሚገኝበት የመሬት ይዞታ ሥሪት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 (1) እንደሚያመለክተዉ የከተማ ቦታ በሊዝ እንዲይዝ የተፈቀደለት ሰዉ አግባብ ካለዉ አካል ጋር የሊዝ ዉል መፈራረም እንደሚኖርበት ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለዉ የሊዝ ዉል የከተማ ቦታን በሊዝ በመያዝ የመጠቀም መብትን የሚፈጠር ውል መሆኑን ነዉ፡፡ የከተማ ቦታን በሊዝ በመያዝ እንዲጠቀም የሊዝ ዉል ያደረገዉ ሰዉ በዉሉ መሰረት ይዞታዉን የተጠቀመ እንደሆነ እስከዉሉ ጊዜ ገደብ ድረስ በይዞታዉ የመጠቀም መብቱ የተረጋገጠለት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የመንግስት አስተዳደር መስሪያ ቤቶች በሕግ የተጣለባቸዉን ኃላፊነት ለመወጣት የአስተዳደር ዉሎችን ለመዋዋል እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3131 ሥር ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132 ሥር እንደተመለከተዉ አንድ ዉል እንዳስተዳደር መሥሪያ ቤት ዉል ሆኖ የሚቆጠረዉ፡ ሀ) ሕግ ወይም ተዋዋዮቹ ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ዉል ነዉ ያሉት ሲሆን፣ ለ) ዉሉ ከሕዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር የተያያዘና ለሥራዉም አፈጻጸም የተዋዋዩን የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱን ሥራ ተካፋይነት ሳይቋረጥ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሐ) በዉሉ ዉስጥ ለጠቅላላ ጥቅም አስቸኳይ በመሆናቸዉ ብቻና የግል ሰዎች በሚያደርጓቸዉ ዉሎች ዉስጥ የማይገኙ አንድ ወይም ብዙ ዉለታዎች ያሉበት ሲሆን ነዉ በማለት ይደነግጋል፡፡

እንግዲህ የሊዝ ዉል በሕግ በግልጽ የአስተዳደር ዉል ነዉ ተብሎ ባልተመለከተበት እና የከተማ ቦታን በሊዝ ዉል በመያዝ የመጠቀም መብት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132 ድንጋጌ አንጻር ሲታይ በድንጋጌ

ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ባለመሆኑ የአስተዳደር ዉሎች ሥር የሚወድቅ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ከሊዝ ዉል አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ማለትም የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጧል በዉሉ ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ፣ እንዲወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 (1) (ሀ) እና (መ)፣ በአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33 (1) (ሀ) እና (መ) ሥር የሚወድቅ ጉዳይ መሆኑን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ እንዲሁም ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 (1)፣ 79 (1) እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.4 ድንጋጌዎች የጣምራ ንባብ ይዘትና ዓላማ ሲታይ ሕግ በቀጥታ ወይም በግልጽ ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል ካልሰጠ በቀር በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ሰምቶ ለመወሰን ስልጣን ያላቸዉ መደበኛ ፍ/ቤቶች በመሆናቸዉ፣ የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ስለተቋረጠ በዉሉ ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ በማለት ከሊዝ ዉል አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚቀርበዉን ክስ ተቀብሎ ሰምቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆናቸዉን ያስገነዝባል፡፡ በዚህ መሰረት የአዲስ አበባም ሆነ የድሬዳዋ ከተማ የአስተዳደር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የላቸዉም፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.54697 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ቀሪ ሊደረግ የሚገባዉ እና በሰ.መ.ቁ.150925 ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተፈጻሚነት ሊቀጥል የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ሆነ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የሊዝ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጦብኛል በዉሉ ያገኘሁት መብት እንዲከበርልኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ከሊዝ ዉል አፈጻጸም ጋር የሚያያዙትን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የሚቀርበዉን ክስ ሰምቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸዉ ብለናል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከተዉ 1ኛ ተጠሪ የሊዝ ዉልን ለማቋረጥ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ በቂ ምክንያት ሳይኖር በሊዝ ያገኘሁትን ይዞታ በመቀነስ ለ2ኛ ተጠሪ በሊዝ ዉል የሰጠና ካርታ እንዲሰጠዉ ያደረገዉ ከሕግ ዉጭ በመሆኑ ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ እንዲሰረዝልኝ በማለት ያቀረበዉን ክስ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ አግባብ አጣርቶ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ በክርክር ሂደት ላይ እያሉ የአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መሰረዙ ስለታወቀ አመልካች ክስ ያቀረበበት ጉዳይ የክስ ምክንያት ተቋርጧል በማለት መዝገቡን መዝጋቱ የህግ መሰረት የለዉም፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረበዉ ክስ የጠቀሰዉን የዳኝነት ጥያቄ ለማየት፣ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆናቸዉን ተገንዝቦ የግራ ቀኙን ክርክር አጣርቶ መወሰን ሲገባዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የላቸዉም፣ ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸዉ የከተማዉ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ናቸዉ በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ የህግ ድጋፍ የሌለዉ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኛቸዉን ክርክር በሕግ አግባብ መርምሮ መወሰን ሲገባቸዉ የአመልካችን የክስ አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.77574 በ6/7/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.17839 በ14/3/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ የግራ ቀኙን ክርክር በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ፅ/ወ

# ንግድና ኢንሹራንስ

የሰ/መ/ቁ 216384

ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡-1ኛ. አቶ ሰለሞን እሸቱ

2ኛ. አቶ ብርሃኑ ወርቅነህ — ቀረቡ

3ኛ. ወ/ሮ አብዮት ደሳለኝ

ተጠሪ፡- ሰዓዳ ጌቱ እና ጓደኞቻቸው ሻወርና መፀዳጃ ህ/ሽ/ማህበር - ስራ አስኪያጅ ፍሬህይወት ጉርሜሳ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 09/03/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 291552 በቀን 01/10/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 275453 በቀን 24/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክስ የተጠሪ ማህበር መስራች አባል መሆናቸውን ገልፀው ነገር ግን ማህበሩ 1ኛ አመልካችን የካቲት 2 ቀን 2013 ዓ.ም ፣ 2ኛ አመልካችን መጋቢት 2 ቀን 2013 ዓ.ም እንዲሁም 3ኛ አመልካችን የካቲት 6 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከማህበር አባልነት አሰናብቷል፡፡ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም ውስጠ ደንብ መሰረት ማህበሩ ፈጽማችኋል ያላቸውን ተግባሮች ያልፈፀምን ሲሆን ተፈጽመዋል ቢባል እንኳን ከአባልነት እንደሚያሰናበቱ አልተደነገገም፡፡ በመሆኑም ስንብቱ ህገወጥ በመሆኑ ተከሳሽ ማህበር ወደ አባልነታችን እንዲመልሰን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ በአመልካቾች ላይ የተወሰደው እርምጃ የማህበሩን መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በ29/08/2011 ዓ.ም በሌሎች የማህበሩ አባላት ላይ የስድብ፣ ዛቻና ማስፈራራት እንዲሁም የማህበሩን ስራ ትተው የመሄድ ተግባር ፈጽመዋል፤ ግንቦት 2 ቀን 2011 ዓ.ም ሁከትና ዛቻ በመፍጠራቸው ለፖሊስ ቀርቦ ጉዳዩ በይቅርታ ተፈቷል፡፡ 3ኛ

አመልካች በማህበሩ ውስጥ ዝቅተኛ የስራ ተነሳሽነት ያላቸው እንዲሁም ያለ በቂ ምክንያት ለረጅም ግዜ ከስራ ጠፍተው በመምጣት ጥር 1 ቀን 2012 ዓ.ም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ 2ኛ አመልካችም በአባላት ስብሰባ የማይገኙ እና የተለያዩ ጥፋቶችን የሚፈጽሙ በመሆናቸው የገንዘብ ቅጣት ተጥሎባቸዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ 2ኛ አመልካች ለ 2 ወራት ሙሉ የስአት መቆጣጠሪያ ላይ ሳይፈርሙና የማህበሩን ገንዘብ ገቢ ሳያደርጉ እየሰሩ የሚገኙ በመሆናቸው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እና የ 2 ወር ደሞዝ ቅጣት ተላልፎባቸዋል፡፡ በዚህም ስራቸው ሊታረሙ ባለመቻላቸው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የማህበሩን ገንዘብ ብር 6050.00 ገቢ ሳያደርጉ በመቅረታቸው እና ሲጠየቁም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከማህበሩ አባላት ብር 450 ነጥቀው በመውሰዳቸው ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አድርጎ አሰናብቷቸዋል፡፡ የማባረር እርምጃ መወሰዱ የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ተከትሎ የተደረገ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ ማህበር ውስጠ ደንብ አንቀጽ 24 ማንኛውም አባል የማህበሩን ንብረት በአግባቡ መያዝ እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 20 መሰረት ተከሳሽ ማህበር አባላቱን የማባረር ስልጣን አለው፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች በተመሳሳይ ቃል ከሳሾች የማህበሩን ገንዘብ ለማህበሩ ገቢ አለማድረጋቸውን አስረድተዋል፡፡ ከሳሾች በምስክርነት ቃላቸው ገንዘቡን ገቢ ያላደረጉት በወቅቱ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ባለመኖሩ መሆኑን ቢያስረዱም የማህበሩን ገንዘብ በማግስቱም ሆነ በቀጣዮቹ ጊዜ ገቢ ማድረግ የነበረባቸው እና የሙብት ጥያቄ ካላቸውም ማህበሩን ከሚጠይቁ በቀር ገንዘቡን ለራሳቸው ለማድረግም ሆነ ለሙብት ማስከበሪያ መጠቀም አይችሉም፡፡ በምስክርነታቸው ከሳሾች ገንዘቡን ለግላቸው አለማዋላቸው ቢገለጽም ገንዘብ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ በእጃቸው ካደረጉ በህግ ንብረታቸው እንደሆነ የሚቆጠር ሲሆን ለማህበሩ ገቢ አለማድረጋቸው ለግላቸው በማዋል ሀሳብ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል፡፡ ከዚህ ባለፈ ተከሳሽ በመልሱ የጠቀሳቸውን ተግባራት ሲፈጽሙ እንደነበር የተከሳሽ ምስክሮች በአግባቡ ሲያስረዱ ከሳሾች ግን ይህን አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም ከሳሾች በውስጠ ደንቡ እንዲሁም በንግድ ህግ አንቀጽ 292 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የማህበሩን ጥቅም ለራሳቸው በማድረጋቸው፣ በማህበሩ ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረሳቸው እንዲሁም አባላት ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ሁከት መፍጠራቸው በመረጋገጡ በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 20 መሰረት ማህበሩ ለማባረር ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ከሳሾች ጥር 22 እና መጋቢት 2 ቀን 2013 ዓ.ም በተደረጉ ጠቅላላ ጉባኤዎች መሰናበታቸው በአግባቡ በመሆኑ ማህበሩ ያስተላለፈው የስንብት ውሳኔ እንዲነሳ በሚል የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ አመልካቾች በተጠሪ ማህበር ውስጥ የማህበሩ መስራችና አባል ስንሆን ተጠሪም ምንም የህግ ምክንያት ሳይኖረው ከማህበሩ አባልነታችን በማሰናበቱ በስር ፍ/ቤት ወደ አባልነታችን እንዲመልሰን ክስ አቅርበን በሰጠነው ምስክርነት አመልካቾች የሰበሰብነውን ገንዘብ ወደ አካውንቱ ልናስገባ ስንሄድ በባንኩ ማስገባት አትችሉም በመባላችን ምክንያት ያላስገባን ስለመሆኑና ገንዘቡም በ1ኛ ከሳሽ ሂሳብ ውስጥ የሚገኝና ለግል ጥቅማችን ያላዋልነው ስለመሆኑ እንዲሁም ተከሳሽ የጠቀሰውን ተግባር ያልፈጸምን ስለመሆኑ በማስረጃ አስረድተን እያለና የማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 20 በግልጽ ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሰርቅ እጅ ከፍንጅ የተያዘን የሚመለከት በመሆኑ ተከሳሽ በዚህ ረገድ ክርክር ባላቀረበበትና በቀረቡት ምስክሮችም ይኸው ስለመሆኑ ሳይረጋገጥብን ከውስጠ ደንቡ ውጭ ገንዘቡ በእጃችን ያለና ለግል ጥቅማችን ያላዋልን ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በፍርዱ ሀተታ ላይም ተመልክቶ እያለ ገንዘቡ በእጃቸው መሆኑ ንብረታቸው እንደሆነ የሚቆጠር ስለሆነና ለማህበሩ ገቢ አለማድረጋቸው ለግላቸው ለማዋል ሀሳብ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው በማለት ፍርድ ቤቱ የተሳሳተ ግምት በመውሰድ በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 20 ን ተላልፈዋል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘናና የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ባቀረብነው ምስክር በፈረቃ እንደማንገናኝ በመልሳቸው ላይ ጠቅሰው ያቀረቡትን ተግባር ያልፈጸምን ስለመሆኑ አስረድተን እያለ በተጠሪ የተመሰከረባቸውን አላስተባበሉም በማለት የደረሰበት መደምደሚያም የተሳሳተ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ያለውን ተግባር ያልፈጸምን ስለመሆኑ በአግባቡ ያስረዳን ከመሆኑም በላይ የማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 20 በዚህ ምክንያት ሊያሰናብት እንደሚችል ባልተደነገገበት ሁኔታና የተጠሪ ምስክሮች ይህን ባላስረዱበት ሁኔታ ከአባልነታችን ማሰናበቱ ተገቢ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግም ሆነ የማስረጃ ድጋፍ የሌለው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን በማለት ቅሬታቸው አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ መተዳደሪያ ደንቡ የማህበሩ ገንዘብ ስርቆት መፈጸም እንደሚያሰናብት የሚገልጽ ሲሆን የአሁን አመልካቾች የማህበሩ ገንዘብ ያዥ እንዲቀበላቸው ጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆኑ በእጃቸው መቆየቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ለግላቸው ለማዋል ሀሳብ እንዳላቸው ተገንዝቤያለሁ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 10/06/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካቾች የተጠሪ ማህበርን ህልውና የሚጎዳ ተግባር በየግዜው ከመፈጸማቸው በተጨማሪ 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከጥር 01 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰበሰቡትን ብር 6050.00 ለተጠሪ ገንዘብ ያዥ ገቢ እንዲያደርጉ እየጠየቅናቸው በእንቢተኛነት ወደ ራሳቸው አካውንት ገቢ ለማድረግ ጠይቀው ባንኩ ስላልተቀበላቸው 1ኛ አመልካች አካውንት ውስጥ ማስገባታቸው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ መሆኑን ስለሚያረጋግጥ፤ 2ኛ አመልካች ደግሞ የማህበሩን ብር 450.00 ከማህበሩ አባላት ነጥቆ መውሰዱ በተጠሪ የውስጥ ደንብ አንቀጽ 20 መሰረት ከስራ ስለሚያሰናብት ተጠሪ የወሰደው የስንብት እርምጃ በአግባቡ ነው፤ የስር

ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔም መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ክስ ለማቅረባቸው ቀዳሚ ምክንያት የሆነው የተጠሪ ጠቅላላ ጉባኤ ያሳለፈው የስንብት ውሳኔ ሲሆን ለውሳኔውም ምክንያት የሆነው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የማህበሩን ገንዘብ ብር 6050.00 ገቢ ሳያደርጉ መቅረታቸው እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከማህበሩ አባላት ብር 450.00 ወስደዋል መባሉ ነው፡፡ ከዚያ በፊት በአመልካቾች ተፈጽመዋል ለተባሉ የተለያዩ ግድፈቶች የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችም ተያይዘው በመከራከሪያነት ቀርበዋል፡፡

የማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 24 ማንኛውም አባል የማህበሩን ንብረት በአግባቡ መያዝ እንዳለበት የሚደነግግ መሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ማህበሩም በደንቡ አንቀጽ 20 መሰረት አባላትን የማባረር ስልጣን ቢኖረውም ይኸው ስልጣን በበቂ ምክንያትና ማስረጃ ላይ ተደግፎ ሊተገበር የሚገባ ነው፡፡

ለስንብት ምክንያት የሆነውን የማህበሩን ገንዘብ አመልካቾች ገቢ ያላደረጉት በወቅቱ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ባለመኖሩ መሆኑን፤ በባንክም ሄደው በአካውንት ለማስገባት ሞክረው በባንኩ ማስገባት አትችሉም በመባላቸው ምክንያት ገቢ ስላለመሆኑና ገንዘቡም ተጠቃሎ በ1ኛ አመልካች የሚገኝና ለግል ጥቅማቸው ያላዋሉት ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር በማስረጃዎቻቸው የተደገፈ ስለሆኑ የስር ፍርድ ቤት ካሳለፈው ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን ፍሬ ነገርና ማስረጃ ተቀብሎ ነገር ግን ገንዘብ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ በእጃቸው ካደረጉ በህግ ንብረታቸው እንደሆነ የሚቆጠር ነው ለግላቸው ለማዋል ሀሳብ እንዳላቸውም ግንዛቤ ይወሰዳል በማለት የደረሰበት የግምት መደምደሚያ የግራቀኙን ክርክርና ህጉን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላም በኩል ተጠሪ በተለያየ ጊዜ በአመልካቾች ተፈፀሙ ለሚላቸው ቀላል ጥፋቶች በይቅርታ መታለፋቸውን እንዲሁም በማህበሩ መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት  ማስጠንቀቂያና የገንዘብ ቅጣት ተጥሎባቸው መታለፋቸውን ከተጠሪም ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ አሁን ላደረገው ስንብት ህጋዊነት በድጋሚ በመከራከሪያነት ማቅረቡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤትም አስቀድሞ ማስጠንቀቂያና መሰል ቅጣት ተሰጥቶባቸው የታለፉ ጉዳዮችን ለስንብቱ እንደምክንያት ተቀብሎ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካቾችን ከተጠሪ ሕብረት ሽርክና ማህበር ለማሰናበት የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ አመልካቾች ከማህበሩ አባላት ጋር ተስማምተው ለመስራት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የሚቻል ሲሆን በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ አብሮ የመስራት ፍላጎት ባልጠፋበት ህጉ ካስቀመጣቸው አማራጮች መካከል የመጨረሻ አማራጭ የሆነውን ከማህበር ማሰናበት መወሰን ተቀባይነት የለውም፡፡ የሕብረት ሽርክና ማህበር የሚመሰረተው በአባላት መካከል ባለው መተማመን እና አብሮ የመስራት ፍላጎት ላይ ሲሆን ይህ ማለት ግን በሁሉም የማህበሩ አባላት መካከል ያለመስማማት አይፈጠርም ወይም አነስተኛ ጥፋቶች ሁሉ ለስንብት ያበቃሉ ማለት አይደለም፡፡

ስለሆነም የአመልካቾች ተግባር የማህበሩን ህልውና ለማስቀጠል እንደማይችል ተደርጎ ከማህበሩ እንዲሰናበቱ መወሰኑ የንግድ ህጉንም ሆነ የማህበሩን ደንብ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 291552 በቀን 01/10/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 275453 በቀን 24/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ማህበር አመልካቾችን ወደ አባልነታቸው እንዲመልስ ወስነናል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁጥር 194796

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ገ/ስላሴ በየነ - ጠበቃ ብርሃኑ ተሻገር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በዋነኛነት የመድን ሽፋን ለተሰጠው ከቀረጥ ነጻ የገባ ተሽከርካሪ ጉዳት ሲደርስበት የመድን ሽፋን ሰጪው ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ቀረጥ እና ታክስ ለመንግስት ቢከፍል የከፈለውን ቀረጥ በጉዳቱ ኃላፊነት ያለበት ወገን እንዲተካለት መጠየቅ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ፤ አቶ ተስፋዬ ገብረመድህን 2ኛ ተከሳሽ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት 3ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም. አሻሽሎ ባቀረበው ክስ ሰኔ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. የተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በነበሩት በ2ኛ ተከሳሽ ጥፋት በደንበኛዬ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ የጉዳቱ መጠን በባለሙያ ሲገመት 57.62 በመቶ የነበረ በመሆኑ ተሽከርካሪው ሙሉ ውድመት(total loss) እንደደረሰበት በመቁጠር መድን ከተገባለት አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ብር 1,300,000 የአደጋ ተቀናሽ ብር 65,000 ሲቀነስ የካሳው መጠን ብር 1,235,000 ይሆናል፡፡ አመልካች ካሳውን ከተሽከርካሪው ለሚፈለግ ቀረጥ እና ታክስ ብር 283,363.43 ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን እንዲሁም ብር 951,636.57 ደንበኛዬ ለሆነው ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ባለቤት ከፍያለሁ፡፡ የተሽከርካሪው ቅሪት አካል ብር 489,288.67 የተሸጠ በመሆኑ ይህ ገንዘብ ለካሳ ከተከፈለው ገንዘብ ላይ ሲቀነስ የሚቀረው ብር 745,711.33 ይሆናል፡፡ በመሆኑም ለጉዳት ገማች የተከፈለ ብር 2,593.25 እና ለመኪናው ከአደጋ ቦታ ማስነሻ የተከፈለ ብር 1,545 ጨምሮ በድምሩ ብር 749,849.58 ተጠሪ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ የስር 3ኛ ተከሳሽም ለተጠሪ ተሽከርካሪ በሰጠው የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን መጠን ልክ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ ጉዳቱ የደረሰው በ2ኛ ተከሳሽ ጥፋት መሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም። የጉዳት መጠኑ ተጠሪን ሳያሳትፍ መሰራቱ ከህግ ውጪ ነው። ካሳ መከፈል ያለበት አደጋው በደረሰ ወቅት ባለው የተሽከርካሪ ዋጋ ልክ ነው። ተሽከርካሪው ጉዳት በደረሰበት ወቅት ከቀረጥ ነጻ የገባ በመሆኑ እና አመልካች ሊከፍል የማይገባውን ቀረጥ እና ታክስ የከፈለ በመሆኑ ተጠሪ ለቀረጥ እና ታክስ የተከፈለውን ገንዘብ የመተካት ግዴታ የለብኝም። የአደጋ ተቀናሽም አጠቃላይ የመድን ሽፋን ከተሰጠው 1,400,000 ብር 5 በመቶ 70,000 ሊሆን ሲገባ አመልካች ብር 65,000 ብቻ ተቀናሽ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል። የስር 2ኛ ተከሳሽ በጋዜጣ ተጠርተው ያልቀረቡ በመሆኑ ክርክሩ በሌሉበት ታይቷል። 3ኛ ተከሳሽ በበኩሉ ለተጠሪ ተሽከርካሪ እስከ ብር 200,000 የመድን ሽፋን መስጠቱን፤ ከዚህ ላይ ብር 8,406 ለኢትዮ ቴሌኮም መክፈሉን እና የሚቀረው ብር 191,593.66 ብቻ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ጉዳቱ የደረሰው በ2ኛ ተከሳሽ ጥፋት መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሻሽ በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው። አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው ተሽከርካሪ አደጋ በደረሰበት ወቅት የገበያ ዋጋው ግምት በባለሙያ ተሰልቶ በቀረበው መሰረት ካሳው ብር 1,275,000 ሊሆን ይገባል። አደጋ መነሻ መሰላት ያለበት አጠቃላይ የመድን ሽፋን በተሰጠው የገንዘብ መጠን ላይ ሊሆን ስለሚገባ ተቀናሽ ሊደረግ የሚገባው ብር 70,000 ነው። አመልካች የተሽከርካሪውን ቀረጥና ታክስ ለመንግስት እንዲከፍል ግዴታ የሚጥልበት ህግም ሆነ ውል  በሌለበት የከፈለ በመሆኑ ይህ ገንዘብ ለአመልካች ሊተካ አይገባም። አመልካች ለጉዳት ገማች እና ለተሽከርካሪው ማስነሻ የከፈለው ገንዘብ ሊተካለት ይገባል። በመሆኑም ከተሽከርካሪው የገበያ ዋጋ ብር 1,275,000 ላይ የአደጋ ተቀናሽ ብር 70,000፤ ቅሪተ አካል በመሸጥ የተገኘው ብር 489,288.67 እና አመልካች ለግብር የከፈለው ብር 283,363.43 በድምሩ ብር 842,652,10 ተቀናሽ ተደርጎ ብር 436,486.48 ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ይክፈሉ። የስር 3ኛ ተከሳሽም 191,593.66 ተጠሪን ተክቶ ለአመልካች ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች ለቀረጥ እና ታክስ የከፈለው ገንዘብ ሊተካለት አይገባም መባሉን እና የአደጋ ተቀናሽ ብር 70,000 ሊሆን ይገባል መባሉን በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ቀረጥና ታክስን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 52/2003 አንቀጽ 5/1 ማንኛውም መድህን ሰጪ ከቀረጥ ነጻ ለገባ ተሽከርካሪ የመድን ዋስትና ሲሰጥ የተገባው ዋስትና ለቀረጡ ጭምር መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት እና የመድን ውሉ የማያረጋግጥ ከሆነ ግን ለቀረጥ እና ታክሱ አከፋፈል መድህን ሰጪው ተጠያቂ እንደሚሆን ተመልክቷል። አመልካች ታክስን ጨምሮ የመድህን ሽፋን ለመስጠቱ በውሉ ላይ ያላረጋገጠ በመሆኑ ቀረጥና ታክስ መክፈሉ ተገቢ አይደለም። አደጋ ተቀናሽም በመድን ፖሊሲው መሰረት መታሰብ ያለበት የመድን ሽፋን ከተገባለት አጠቃላይ ዋጋ ላይ ሊሆን ስለሚገባ ተቀናሽ መደረግ ያለበት 70,000 ነው መባሉ ተገቢ ነው በማለት

የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል። አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም የሚከተለውን የሰበር ቅሬታ አቅርቧል።

አመልካች በነሀሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ በመድን ውሉ ላይ ሽፋን የሰጠሁት የተሽከርካሪውን ቀረጥ እና ታክስ ጨምሮ መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል። የአደጋ ተቀናሽም በመድን ውሉ መሰረት ሊታሰብ የሚገባው ከሚከፈለው የካሳ መጠን ላይ በመሆኑ ብር 65,000 ተቀናሽ ማድረጌ ተገቢ ሆኖ እያለ ብር 70,000 ሊቀነስ ይገባል መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ጠይቋል።

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ አመልካች ለደንበኛው ካሳ የከፈለው የመድህን ፖሊሲውን ተከትሎ ነው አይደለም? የሚለውን ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል።

ተጠሪም በታህሳስ 27 ቀን 2013 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች የመድን ውሉ የተሽከርካሪውን ቀረጥ ይጨምራል በማለት ያቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። የኢንሹራንስ ፖሊሲው የተሽከርካሪው ግምት የመለዋወጫ እቃን የሚጨምር መሆኑን ከመግለጹ ውጪ ቀረጥና ታክስን የሚጨምር ስለመሆኑ አያመለክትም። አደጋ ተቀናሽም ሊሰላ የሚገባው የመድን ሽፋን ከተሰጠው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ላይ ሊሆን ይገባል መባሉ የመድን ውሉን የተከተለ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል።

አመልካችም በጥር 17 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል።

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነው ጉዳት የደረሰበት የአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነጻ የገባ መሆኑ፤ ተሽከርካሪው ጉዳት ከደረሰበት በኋላ አመልካች ለደንበኛው ከሚከፍለው የካሳ መጠን ላይ ተቀናሽ በማድረግ ለመንግስት ቀረጥ እና ታክስ የከፈለ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ይህ ከቀረጥ ነጻ የገባ ተሽከርካሪ ጉዳት ሲደርስበት ቀረጥና ታክሱ በአመልካች ለመንግስት መከፈል ነበረበት ወይስ አልነበረበትም የሚለው ነው? ለዚህ ነጥብ ምላሽ ለመስጠት ከቀረጥ ነጻ መብት ያስፈለገበትን አላማ እና የመብቱ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ መመርመሩ ተገቢ ነው። በጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 129 እና 130 ስለቀረጥና ታክስ ነጻ መብት አሰጣጥ እና ከቀረጥ ነጻ በገባ ተሽከርካሪ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገባ የተፈቀደለት አካል ብቻ መሆኑን

ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ከቀረጥ ነጻ የገባ እቃ የጠፋ ወይም ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ አስመጪው ለባለስልጣኑ ይህንኑ ማሳወቅ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 130/3 ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህ የማሳወቅ ግዴታ በአስመጪው ላይ የተጣለበት አላማ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የገባ ተሽከርካሪ ጠቅላላ ጉዳት ደርሶበት ከጉዳት አድራሹ ወይም ከመድን ሰጪው ካሳ ሲከፈለው የሚከፈለው ካሳ ቀረጥ እና ታክስን ጨምሮ የተሽከርካሪውን የገበያ ዋጋ ይከፈለዋል ተብሎ ስለሚታሰብ በቀረጥ ነጻ መብት ተሽከርካሪውን ያስገባው ሰው በካሳ መልክ ቀረጥ እና ታክስን አብሮ በመቀበል አላግባብ እንዳይበለጽግ ለመከላከል ብሎም ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብት ከታለመለት አላማ ውጪ እንዳይውል ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ አስመጪው ከቀረጥ ነጻ የገባው ተሽከራካሪ ጉዳት ደርሶበት ከመድን ሰጪው ካሳን ሲቀበል የካሳው መጠን ግብር እና ታክሱንም የሚጨምር በመሆኑ ለጉዳት ኃላፊ የሆነ ወገን ቀረጥ እና ታክሱን ለመድህን ሰጪው ለመተካት ከህግ የመነጨ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች የቀረጥ እና ታክስ አከፋፈል ሁኔታ ለመወሰን በሚኒስቴሩ መመሪያ ቁጥር 52/2003 ወጥቶ በስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5/1 ከቀረጥ ነጻ ለገባ ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን ሲሰጥ የመድን ሽፋን ዋስትናው ቀረጥ እና ታክሱን የሚጨምር መሆኑን በመድን ውሉ ላይ መገለጽ እንዳለበት እና በመድን ውሉ ላይ ካልተገለጸ የመድን ሽፋን ሰጪው ለተሽከርካሪው ቀረጥ እና ታክስ ኃላፊ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው የመድን ሽፋን ውሉ በተሽከርካሪው ባለቤት እና በኢንሹራንስ ዋስትና ሰጪው መካከል የሚደረግ በመሆኑ ስለቀረጥና ታክሱ በመድን ውሉ ላይ ሳይገለጽ በመቅረቱ ኢንሹራንሱ የተሽከርካሪውን ቀረጥ እና ታክስ ከጉዳት ካሳ ወይም ከተሽከርካሪው ዋጋ ላይ ተቀናሽ ሳያደርግ ለደንበኛው ቢከፍል ለቀረጥ እና ታክሱ መድን ሰጪው ለመንግስት ተጠያቂ እንደሚሆን አመላካች ነው፡፡ መድን ሰጪው ለደንበኛው ከሚከፍለው የካሳ መጠን ላይ ግብር እና ታክሱን ተቀናሽ አድርጎ ለመንግስት ከከፈለ በመድን ውሉ ላይ ስለቀረጥ እና ታክስ መጠቀስ አለመጠቀሱ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ በሌላ አባባል በመድን ውሉ ላይ የመድን ሽፋኑ የተሽከርካሪውን ቀረጥ እና ታክስ የሚጨምር መሆኑን መግለጽ ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት ግብር ሰብሳቢው አካል በቀላሉ ከተሽከርካሪው የሚፈለገውን ግብር ካሳ በሚከፈልበት ጊዜ ከመድን ሰጪው መሰብሰብ እንዲያስችለው እንጂ በመድን ውሉ ላይ ካልተገለጸ በተሽከርካሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት ያለበት ወገን ለመድን ሰጪው ግብር እና ታክሱን የመተካት ግዴታ ያስቀርለታል ማለት አይደለም፡፡ በተጠቀሰው መመሪያ አንቀጽ 14/1 ከቀረጥ ነጻ የገባ ተሽከርካሪ ሙሉ ለሙሉ እንዲወድም ምክንያት የሚሆነው ሰው ለቀረጥ እና ታክሱ ኃላፊነት እንዳለበት መገለጹ ለቀረጥ እና ታክሱ ክፍያ የመጨረሻ ኃላፊነት ያለበት ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነው ሰው መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ በመሆኑም በመድን ውሉ ላይ ስለቀረጥ እና ታክስ ባይገለጽም እንኳን የመድን ዋስትና ሰጪው ከቀረጥ ነጻ ለገባው ተሽከርካሪ ቀረጥ እና ታክሱን ጉዳት ከደረሰበት ተሽከርካሪ የገበያ ዋጋ ላይ በመቀነስ መክፈሉ

እስከተረጋገጠ ድረስ ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለበት ወገን መድህን ሰጪው የከፈለውን ቀረጥ እና ታክስ የማይተካበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ጉዳት የደረሰበት የአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ አደጋ በደረሰበት ወቅት የገበያ ዋጋው ምን ያክል እንደሆነ ታክስን ጨምሮ እና ታክስን ሳይጨምር ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ታክስን ጨምሮ የቀረበውን ግምት ብር 1,235,000 መቀበሉን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ የተሽከርካሪው አጠቃላይ ግምት ላይ አመልካች ግብር እና ታክሱን ለሚመለከተው የመንግስት አካል ቀረውን ለደንበኛው መክፈሉ ከላይ በተጠቀሰው መመሪያ የተጣለበትን ግዴታ መወጣቱን ከሚያሳይ በስተቀር ግዴታ ሳይኖርበት ከፍሏል የሚያስብል አይደለም፡፡ አመልካች ከደንበኛው ጋር በገባው የመድን ውል ላይ ስለቀረጥ እና ታክሱ ቢገለጽም ባይገለጽም አመልካች ቀረጥ እና ታክሱን መክፈሉ መረጋገጡ በቂ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተጠሪ የመድን ውሉ ቀረጥ እና ታክስ ይጨምራል የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያላነሳው በመሆኑ በዚህ ሰበር ደረጃ ሊነሳ አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በእርግጥ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ የፍሬ ነገር ክርክር በይግባኝ ወይም በሰበር ደረጃ ሊነሳ እንደማይችል በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 329/1 ላይ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው በተሽከርካሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ወገን ለቀረጥ እና ታክሱም ኃላፊነት እንዳለበት በጉምሩክ አዋጁ እና በመመሪያ የተደነገገ በመሆኑ በመድን ውሉ መገለጽ አለመገለጹ ከጉዳት አድራሹ አንጻር የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ቀረጥ እና ታክስ የመክፈል ግዴታ ሳይኖርበት የከፈለ በመሆኑ በተጠሪ ሊተካለት አይገባም ማለታቸው መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም እና አተገባበር ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሌላው የአመልካች የቅሬታ ነጥብ የአደጋ መነሻ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው 5 በመቶ የአደጋ መነሻ መሰላት ያለበት የመድን ሽፋን ከተሰጠው አጠቃላይ የተሽከርካሪ ዋጋ ላይ ነው ወይስ አደጋው በደረሰ ወቅት ባለው የተሽከርካሪ ዋጋ ላይ ነው የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ነጥብ እልባት ለመስጠት የውሉን ይዘት መመልከት ተገቢ ነው፡፡ የአደጋ መነሻ ክፍያን በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ “birr 5000 or 5/100 0f the repair cost in the case of partial loss or 5/100 of the sum insured or the market value in case of total loss, whichever is higher” በሚል ተቀምጧል፡፡ ይህም ማለት ተሽከርካሪው አጠቃላይ ውድመት(total loss) ከደረሰበት የአደጋ መነሻ 5/100 የሚታሰበው የመድን ሽፋን በተሰጠው አጠቃላይ ገንዘብ እና አደጋው በደረሰ ሰአት በተገመተው የተሽከርካሪ የገበያ ዋጋ መካከል ከፍተኛ ከሆነው ላይ እንደሆነ አመላካች ነው፡፡ ይህም ማለት በተያዘው ጉዳይ የመድን ሽፋን የተሰጠው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ብር 1,400,000 ከተሽከርካሪው የገበያ ዋጋ የሚበልጥ በመሆኑ የተቀናሽ ክፍያው መታሰብ ያለበት ከዚሁ ከአጠቃላይ የገንዘብ መጠን ላይ ነው፡፡ በዚህ የገንዘብ መጠን ላይ ሲታሰብ 5/100 ብር 70,000 ይሆናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የአደጋ መነሻ ብር 70,000 መቀነስ ነበረበት በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የመድን ውሉን መሰረት ያደረገ ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 190712 በ12/04/2011 ዓ.ም. እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 170449 በ29/07/2012 ዓ.ም. የሰጡት ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2ኛ. አመልካች ጉዳት ለደረሰበት ተሽከርካሪ የከፈለውን ቀረጥ እና ታክስ ብር 283,363.43 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሶስት ሺ ሶስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከአርባ ሶስት ሳንቲም) ተጠሪ ለአመልካች ሊተኩ ይገባል ብለናል፡፡ ሌላው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አልተነካም፡፡

3ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጎ

**የሰ/መ/ቁ.** 203888

የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

**ተጠሪዎች-** 1. ቃልኪዳን ተስፋዬ

2. ላኮመንዛ የሽማቾች ህብረት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርዱ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት ደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ እንዲሁም አመልካች ጣልቃ-ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ግንቦት 06/09/2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ2ኛ ተጠሪ የሆነው እና የሰሌዳ ቁጥሩ አአ 3-A17891 የሆነ ኤፍ.ኤስ.አር ተሽከርካሪ ነሐሴ 27 ቀን 2008 ዓ.ም ወደ ኋላ በመንሸራተት በደሴ ከተማ ሆጤ ክፍለ ከተማ ዉስጥ ያለኝን የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ እና የቁልፍ ስራ ድርጅቴን ጉዳት ያደረሰበት በመሆኑ ጉዳት ለደረሰበት ንብረቴ ብር 158,297.00 እንዲሁም ከነሐሴ 27 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 17 ቀን 2009 ዓ.ም ሰርቼ አገኝ የነበረውን በቀን ብር 1000.00 በጉዳቱ ምክንያት ያጣሁ በመሆኑ የ25 ቀን ብር 25,000.00 እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ በተሽከርካሪዉ ምክንያት ጉዳቱ መድረሱን ሳይክድ የ1ኛ ተጠሪ የንግድ ፍቃድ የቁልፍ ስራ እና የአትክልትና ፍራፍሬ ችርቻሮ ንግድ ሲሆን የሸቀጣሸቀጥ ንግድ እንደሚሰሩ አስመስለው ክስ ማቅረብ አይችሉም፤ የቀረበው የንብረት ግምት እና የቀን ገቢ የተጋነነ ነው፤ ጉዳት አድርሷል የተባለው ተሽከርካሪም የመድን ሽፋን ያለው በመሆኑ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ወደ ክርክሩ በመግባት መልስ እንዲሰጥ ይታዘዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ወደ ክርክሩ በመግባት ባቀረበዉ መልስ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ ሌላ ግለሰብ ክስ አቅርቦ በክርክር ላይ ያለ በመሆኑ መዝገቦቹ ይጣመሩልኝ፤ ጉዳት ደርሶባቸዋል የተባሉት ንብረቶች እና ኮንቴይነሩን ለማሰራት ወጣ የተባለው ወጪ ግምት የተጋነነ

በመሆኑ በገለልተኛ ገማች እንዲገመትልን ይደረግ የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጠው መልስ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ የንግድ ፍቃድ ያወጡበት ዘርፍ እና ጉዳት ደርሶባቸዋል የተባሉት ንብረቶች አይገናኙም፤ ፍቃድ ላላወጡባቸው ንብረቶች ካሳ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው እና ሙሉ ለሙሉ ውድመት ላልደረሰበት ኮንቴይነር ካሳ መጠየቅ ተገቢ አይደለም፤ ከሱቁ ውስጥ ጠፋ የተባለው ጥሬ ገንዘብም በስፍራው የነበረ ስለመሆኑ የሚታምን አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የ1ኛ ተጠሪ የስራ ዘርፍ ንግድ ስራ ስለመሆኑ በምስክርም ጭምር ተረጋግጧል፤ የንብረቱን ግምት በተመለከተ አስራ ሶስት ከሚሆኑ የእቃ አይነቶች ውጪ የሌሎቹን ግምት ማስገመት ያልተቻለ ሲሆን አመልካችም ለማስገመት ተገቢውን ጥረት አላደረገም፤ የተገመቱት ንብረቶች ዋጋም 1ኛ ተጠሪ ካቀረቡት ግምት ቢበልጥም አመልካች ገምተው ያቀረቡትን ግምት ተቀብለናል፤ ከሱቅ ጠፍቷል የተባለውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ ስለመጥፋቱ ያስረዳች ሲሆን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አላስተባበሉም ካለ በኋላ የአመልካችን የኃላፊነት መጠን በሚመለከት አመልካች በዚሁ ተሽከርካሪ ምክንያት በተመሳሳይ ሰዓት ጉዳት ለደረሰበት ሌላ ግለሰብ በሌላ መዝገብ ተከስሼ ብር 100,000.00 እንድከፍል የተወሰነብኝ በመሆኑ በአንድ አደጋ ምክንያት ከብር 100,000.00 በላይ ካሳ ልከፍል አይገባም ቢልም አደጋው የደረሰው በተለያዩ ሰዎች ንብረት ላይ በመሆኑ ኃላፊነት አለበት፤ ስለሆነም አመልካች ብር 100,000.00 እንዲከፍል፣ ቀሪውን ብር 83,279.00 ደግሞ 2ኛ ተጠሪ ከጠበቃ አበል እና ለዳኝነት ከተከፈለ ወጪ ጋር እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የኃላፊነት መጠን 2ኛ ተጠሪ ክዶ ባልተከራከረበት ግልጽ የሆነውን የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1)(ሐ) "ን" ያለአግባብ በመተርጎም መድን የተገባለት ተሽርካሪ በአንድ ጊዜ በተለያዩ ግለሰቦች ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ ለእያንዳንዳቸው ግለሰቦች እስከ ብር 100,000.00 ድረስ ካሳ መክፈል አለበት ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች በአንድ ድርጊት በሁለት ግለሰቦች ንብረት ላይ ጉዳት ደርሶ እያለ አመልካች ለእያንዳንዳቸው ካሳ ሊከፍል ይገባል የመባሉ አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(3)(ሐ) አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በሚል መጥሪያ ተልኮላቸው 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ተቀብለው መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

2ኛ ተጠሪ ግን መጋቢት 23 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ተሽርካሪያችን ጉዳት በንብረታቸው ላይ ጉዳት ያደረሰባቸው 1ኛ ተጠሪ እና አቶ ከሪም ሁሴን የተባሉት ግለሰቦች የየራሳቸው ንብረት ያላቸው በመሆኑ የአንዳቸው መብት ከአንዳቸው ጋር ሳይቀላቀል ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ሊከፈላቸው ይገባል፤ የስር ፍርድ ቤቶችም በዚሁ አግባብ ካሳ እንዲያገኙ መወሰናቸው ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር በ2ኛ ተጠሪ መልስ ላይ የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው ንብረትንቱ የ2ኛ ተጠሪ የሆነዉ የሠሌዳ ቁጥር አ.አ. 3-17891 በአመልካች ድርጅት ላይ አድርሷል ለተባለዉ የንብረት ጉዳት ብር 183,297.00 ለመክፈል 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት አለበት በሚል ከተወሰነዉ ዉስጥ አመልካች የሦሥተኛ ወገን መድን ሰጪ እንደመሆኑ ብር 100,000.00 እንዲከፍል የተወሰነ ሲሆን፣ አመልካች ከስር ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረዉ በተመሳሳይ አደጋ ምክንያት በሌላ ሦስተኛ ወገን ላይ በደረሰ ጉዳት በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36764 ላይ ክስ ቀርቦበት ብር 100,000.00 እንዲከፍል የተወሰነበት መሆኑን ጠቅሶ በአንድ አደጋ ምክንያት ከብር 100,000 በላይ መክፈል የለብኝም በማለት ነዉ፡፡ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ ያደረጉት በጉዳት ምክንያት የሦስተኛ ወገን መድን ሰጪ የሚከፍለዉን የክፍያ መጠን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1-ሐ) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ የብር 100,000.00 የክፍያ ጣሪያ በአንድ ሰዉ ላይ ለሚደርስ ጉዳት መድን ሰጪዉ ከዚህ የገንዘብ መጠን በላይ ለመክፈል እንደማይገደድ የሚገልጽ እንጂ በአንድ ጉዳት በብዙ ሰዎች ላይ ጉዳት የደረሰ ቢሆንም የመድን ሰጪዉ የኃላፊነት ጣሪያ ከብር 100,000.00 ሊበልጥ አይገባም የሚል ይዘት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡

በንግድ ሕግ አንቀጽ 685 እና ተከታዮቹ መሠረት መድን ገቢ እና መድን ሰጭ ስለ ኃላፊነት ኢንሹራስ ውል ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉ የተመለከተ ሲሆን ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 ዓ/ም አንቀጽ 15(1) ደግሞ ተሽከርካሪ ከሚያደርሰው ግጭት የሚመነጭ ኃላፊነትን መድን ገቢው የመድን ሽፋን እንዲኖረው የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የመድን ሰጭው የኃላፊነት መጠን ጣሪያውም በሕግ ተዘርዝሯል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1)(ሐ) መሠረት በንብረት ላይ ለሚደርስ ኪሣራ የኃላፊነት ጣሪያው ከብር 100,000.00 ያልበለጠ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

አሁን ያከራከረው ይህ ጣሪያ ተፈጻሚነቱ ንብረቱ ላይ ጉዳት በደረሰበት ለእያንዳንዱ ሠው ነው ወይስ በጠቅላላ ሁሉም ንብረት ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው 3ኛ ወገኖች የሚለው ነው፡፡ የኃላፊነት መጠኑን የደነገገው የአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1) ለ3ኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ (ሠረዝ የተጨመረ)

ማለቱ የኃላፊነት ጣሪያው በዋነኛነት የተጎጂውን ቁጥር ሳይሆን ጣሪያው የተወሰነው አደጋ በደረሠ ጊዜ እና የኃላፊነት ጣሪያው የደረሠን አደጋ የሚከተል እንደሆነ ያሳያል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1)(ሀ) እና (ለ) ላይ በሠው ላይ ለሚደርስ የአካል ጉዳት ወይም ሞት የኃላፊነት ጣሪያው በተጎጂው ሠው ቁጥር ልክ መሆኑ በሕጉ በግልጽ ተመላክቶ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1)(ሐ) መሠረት በንብረት ላይ ለሚደርስ ኪሣራ ግን የኃላፊነት ጣሪያው ከብር 100,000.00 ያልበለጠ ተብሎ መደንገጉ፤ ጉዳት በንብረት ላይ በሚደርስ ጊዜ ጉዳት የደረሠባቸው የባለንብረቶች ቁጥር ግምት ውስጥ ሳይገባ በጠቅላላው አንድ ጊዜ ለተከሠተ አደጋ በንብረት ላይ ለሚደርስ ኪሣራ የተገለጸ ጣሪያ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በአንድ ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ በተከሠተ አደጋ በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት፤ አደጋው በብዙ ባለንብረቶች ላይ ወይም በአንድ ሠው ንብረት ላይ ያደረሠው ኪሣራ ከ100ሺ በላይ ከሆነ መድን ሰጭው የመሸፈን ኃላፊነት ያለበት እስከ ብር 100,000.00 ድረስ ብቻ መሆኑን የሕጉ አነጋገር ያስረዳል፡፡ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰ/መ/ቁጥር 170340 ጨምሮ በሌሎች መዝገቦች ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ለ2ኛ ተጠሪ ክስ መነሻ በሆነው አደጋ ምክንያት በሌላ ሰዉ ላይም ጉዳት መድረሱን ተከትሎ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 35458 ላይ ክስ ቀርቦበት ብር 100,000.00 አመልካች እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ ተጠሪዎች ክደዉ አይከራከሩም፡፡ አመልካች በዚሁ አደጋ ምክንያት በሌላ ሰዉ ላይ ለደረሠው ጉዳት ብር 100,000.00 ከ2ኛ ተጠሪ ክስ አስቀድሞ የከፈለ በመሆኑ በአንድ ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ በተከሠተ አደጋ በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ያለበትን ከፍተኛ የኃላፊነት ጣሪያ ስለከፈለ ድጋሜ ክፍያ ሊጠየቅ አይገባም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የንብረት ጉዳት ካሣውን ለ2ኛ ተጠሪ ሊከፈል ይገባል በማለት መወሰናቸው የአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1) (ሐ) የተመለከተውን ያላገናዘበ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

## ውሳኔ

1. አመልካች ብር 100,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36764 የካቲት 04 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0110086 ታህሳስ 29 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ብር 100,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. 2ኛ ተጠሪ ብር 83,279.00 (ሰማኒያ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤቶች ከተወሰነዉ በተጨማሪ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

4. የሰበር አጣሪ ችሎት መጋቢት 06 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.124957

ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ዓሊ መሐመድ

2. ተኽሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ /አ.ማ/ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ መብራቱ ፈንታሁን - ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ሰምለም ወርቁ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ በተሽከርካሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት በመድን ዉል መሰረት ካሳ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.01-00223 በ29/06/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች፣ የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ ከሳሾች ባቀረቡት ክስ የከሳሾች ንብረት የሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-06060 አ.ማ ሚኒባስ ተሽከርካሪ በ5/7/2006 ዓ.ም ከጎንደር ወደ መተማ እየሄደ እያለ ከሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-17800 ኤፍ.ኤስ.አር ተሽከርካሪ ጋር ተጋጭቶ ሙሉ ጉዳት ደርሶበታል፣ የጉዳቱ መንስኤዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-17800 ተሽከርካሪ እንደሆነ የተረጋገጠ ሲሆን፣ በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ከተከሳሽ ጋር የብር 300,000 የመድን ዋስትና ገብተናል፣ የደረሰዉን አደጋ ለተከሳሽ አሳዉቀናል ነገር ግን በመድን ዉሉ መሰረት ስላልከፈለን ይህን ገንዘብ እንዲከፈለን በጊዜ ባለመክፈሉ የተቋረጠብን ጥቅም ብር 100,000 እንዲከፍለን፣ ለወደ ፊትም በየወሩ 12,000 እንዲከፈለን በማለት ከሷል፡፡

ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ የከሳሾች ተሽከርካሪ በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ከተፈቀደለት የመንገደኞች ቁጥር በላይ ጭኖ ሲጓዝ ጉዳት የደረሰበት ስለሆነ በመድን ዉሉ መሰረት ካሳ ሊከፈላቸዉ

አይገባም፣ አዳጋ ያደረሰዉን ተሽከርካሪ ሊጠይቁ ይገባል እንጂ ተከሳሽ መጠየቅ የለባቸዉም፣ በተሽከርካሪዉ ጉዳት ምክንያት ለሚደርስ የጥቅም ማጣት የመድን ዋስትና ያልሰጠን ስለሆነ ልንከፍል አይገባም፣ ይህ የሚታለፍ ከሆነ የተከሰስንበትን ገንዘብ መጠን የአደጋ መነሻ 5% ተቀናሽ ተደርጎ ሊከፈል ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ በከሳሾች እና በተከሳሽ መካከል በተደረገዉ የመድን ዉል መሰረት ተከሳሽ በከሳሾች የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-06060 ሚኒባስ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ሙሉ ለሙሉ ጉዳት በገባዉ ግዴታ መሰረት 5% ተቀንሶ ለብር 250,000.00 ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ ለከሳሾች ይክፈል፤ ይህን ገንዘብ ፍርድ ከተሰጠ ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከ9% ወለድ ይክፈል፤ ከሳሾች ካሳዉ ባለመከፈሉ የተቋረጠብን ጥቅም ተከሳሽ እንዲከፍለን ያሉትን በተመለከተ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም፣ ተከሳሽ የመኪናዉን ቅሪት ይረከብ በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ5/7/2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት በአጭሩ፡--የተጠሪዎች ሚኒባስ ተሽከርካሪ አደጋዉ ሲደርስ 7 ሰዎች ትርፍ ጭኖ ሲያንጉዝ የነበረ በመሆኑ በመድን ዉልም ሆነ በትራንስፖርት ደንብ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር የጉዳት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ሳይኖርብን እንድንከፍል መወሰኑ እና ጉዳት አድርሷል የተባለዉን ተሽከርካሪ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ጠይቀን ሳይገባ ዉሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣የተጠሪዎች መኪና አደጋ በደረሰበት ጊዜ ትርፍ ሰዉ መጫኑ ያልተካደ እስከሆነ ድረስ በመድን ፖሊሲዉ ተጠቃሚ ይሆናሉ ወይስ አይሆኑም? ለጉዳቱ ኃላፊ ነዉ የተባለዉ ተሽከርካሪ ባለቤት ጣልቃ እንዲገባ የተጠየቀዉን ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በታዘዘዉ መሰረት በ28/8/2008 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የቀረበዉ ቅሬታ ዉድቅ ተደርጎልን የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች ቀጠሮ እያወቀ በመቅረቱ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉ ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርመሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች እና ተጠሪዎች ለተጠሪዎች ንብረት ለሆነዉ ሚኒባስ ተሽካርካሪ በተመለከተ የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ መዋዋላቸዉ ያላከራከረ ጉዳይ ሲሆን፣ አመልካች በዚህ ተሽከርካሪ ላይ ለሚደርሰዉ ሙሉ ዉድመት ከብር 300,000 ዉስጥ 5% ተቀናሽ ተደርጎ ለተጠሪዎች ለመክፈል መስማማታቸዉን የሥር

ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ እንዲሁም በግራ ቀኛቸዉ መካከል በተፈረመዉ የኢንሹራንስ ዉል ፖሊስ ክፍል 3 እንደተመለከተዉ ተጠሪዎች በተሽከርካሪ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ላይ ከተመለከተዉ የተሣፋሪ ቁጥር በላይ የተጫነ እንደሆነ ለሚደርሰዉ ጉዳት ኃላፊ እንደማይሆን ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በፖሊስዉ ክፍል 10 ተራ ቁጥር 1 /ሀ/ ሥር እንደተመለከተዉ ተሽከርካሪዉ ትርፍ ሰዉ በመጫኑ ኃላፊ የማይሆነዉ የተፈጠረዉ የግጭት ወይም በተሽከርካሪዉ ላይ ለደረሰዉ አደጋ መንስኤዉ ትርፍ ሰዉ በመጫኑ እንደሆነ ነዉ፡፡ ይህ የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ደግሞ በንግድ ሕጉ በተመለከተዉ እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1711 እና 1731 /1/ በሚደነግገዉ አግባብ በግራ ቀኛቸዉ መካከል ሕግ ነዉ፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች ተሽከርካሪ ትርፍ ሰዉ መጫኑ ለአደጋዉ መንስኤ የሆነ እንደሆነ አመልካች በዉሉ መሰረት የጉዳት ካሳ ለመክፈል ከኃላፊነት ነጻ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በተጠሪዎች ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት መንስኤዉ ትርፍ ሰዉ ጭኖ መገኘቱ ያልሆነ እንደሆነ አመልካች በመድን ዉል ፖሊሲዉ መሰረት ከኃላፊነት ነጻ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡

ከዚህ አንጻር በሥር ፍ/ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ በተጠሪዎች ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት መንስኤዉ ትርፍ ሰዉ ጭኖ በመጓዙ ሳይሆን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-17800 ኤፍ.ኤስ.አር ተሽከርካሪ የቀኝ መስመሩን ለቆ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች በተጠሪዎች ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ምክንያት የሆነዉ ተሽከርካሪዉ ትርፍ ሰዉ በመጫኑ ሳይሆን በሌላ ተሽከርካሪ ጥፋት እንደሆነ ስለተረጋገጠ የአሁን አመልካች በመድን ዉል ፖሊሲ መሰረት ለተጠሪዎች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔዎች በሕጉ አግባብ የተሰጡ ናቸዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ለማለት አይቻልም፡፡

በቀጣይነት መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካች የጉዳት አድራሽ ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነዉ ሰዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.43 መሰረት ወደ ክርክር እንዲገባለት ጠይቀዉ የመታለፉን አግባብነት ነዉ፡፡ በእርግጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.43 /1/ እንደሚደነግገዉ ተከሳሽ ለተከሰሰበት ነገር የክርክሩ ተካፋይ ያልተደረገ ሰዉ ከእኔ ጋር ድርሻ ካሳዉን መክፈል አለበት የሚልበት ምክንያት ካለ ይኼንኑ አስተካክሎ ይህ ሶስተኛ ወገን ወደ ክሱ እንዲገባ ማመልካቸዉን ለፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚችልና ፍ/ቤቱም ይህ ሶስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባ የፈቀዳ እንደሆነ ክርክሩን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች መድን ሰጪ ሲሆን በደንበኛዉ መኪና ላይ ለደረሰዉ ጉዳት የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-17800 የሆነ ተሽከርካሪ ባለቤት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ካሳ ድርሻዉን መክፈል አለበት የሚል ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ አግባብ ይህን ሶስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባ ከማድረግ የሚከለክላዉ ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን በዚህ ድንጋጌ አግባብ ለጉዳቱ ምክንያት ነዉ የተባለዉ ሶስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባ አለመደረጉ አመልካች የሚያጣዉ መብት አለ ወይ? ከሚለዉ ነጥብ ጋር በማገናዘብ መታየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ በንግድ ሕግ አንቀጽ 683 /1/ እንደሚደነግገዉ መድን ሰጪ ለኢንሹራንስ ገቢዉ /ለደንበኛዉ/ በከፈለዉ የገንዘብ መጠን ጉዳት እንዲደርስ ባደረጉት ሶስተኛ ወገኖች በከፈለዉ ገንዘብ መጠን ባሉት መብቶችና ክሶች በደንበኛዉ ምትክ ሆኖ መጠየቅ

እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ከሆነ የአሁን አመልካች ለተጠሪዎች በከፈለዉ የገንዘብ መጠን ባሉት መብቶች በተጠሪዎች እግር ተተክቶ ወይም በምትክነት ለጉዳቱ መንስኤ ነዉ የተባለዉን ተሽከርካሪ ከሶ ከመጠየቅ የሚያግደዉ ነገር የለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በተጠሪዎች ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት መንስኤ ነዉ የተባለዉን ተሽከርካሪ ባለቤት ወደ ክርክሩ እንዲገባ አለማድረጋቸዉ የአመልካችን መብት የሚነካበት ሁኔታ ስለሌለ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያስብል ስላልሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**ዉ ሳ ኔ**

1. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-20431 በ26/4/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.01-00223 በ29/6/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

# አፈፃፀም

የሰ/መ/ቁ. 199094

ቀን፡- ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ መንግስቱ የሺጥላ - ጠበቃ ጓንጉል ተሻገር - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ቢ.ኤንድ ዋይ ፖልትሪ ፋርም ኃ/የተ/የግል ማሕበር- ጠበቃ ወይንዓለም ወ/ሰንበት - ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው ክርከሩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን አመልካች እና ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 253220 ክርክር ሲያደርጉ ቆይተው ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ/ም የእርቅ ሥምምነት ያደረጉ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የእርቅ ሥምምነቱን ሐምሌ 23 ቀን 2010 ዓ/ም ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ አመልካች ጥቅምት 05 ቀን 2012 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በእርቅ ሥምምነቱ መሠረት ተጠሪ ማስተላለፍ የሚገባውን ንብረት አላስተላለፈልኝም በማለት ሥመ-ሀብቱን ተጠሪ ተገዶ እንዲፈጽም እና ግዴታውን ባለመወጣቱ ስለደረሰው ጉዳት በአዲስ ክስ የመጠየቅ መብት ይጠበቅልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው የጽሁፍ መልስ በእጁ የሚገኙ ንብረቶች ለአመልካች እንዳስረከበና አመልካች እየተጠቀመባቸው እንደሚገኝ፣ በፍራንኮ ቫሎታ ከታክስ ነጻ ወደ አገር የገቡትን ንብረቶች እ.ኤ.አ. በ05/12/2018 በተደረገ ሥምምነት ወደአመልካች ተዛውረዋል፡፡ አመልካች ለሚፈለገው ሰው ውክልና በመስጠት ሆነ የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ በአካል በመገኘት ሥመ-ንብረት ለማዛወር ቢሞክሩም አመልካች ንብረቱ ሲዛወርለት የሚሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እንደገኘ እንዲከፍል ሲጠየቅ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ዝውውሩ ሊፈጸም አልቻለም፡፡ በአፈጻጸም ማመልከቻ ወደፊት ክስ የማቅረብ መብቱ ይጠበቅልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ጥቅምት 10 ቀን 2012 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በዕርቅ ሥምምነቱ መሠረት አመልካች ለተጠሪ ብር 8,000,000.00 የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ ገንዘቡን በየወሩ ተከፋፍሎ

የሚከፈል ሲሆን አመልካች ጊዜውን እያሳለፈ ሲከፍል ቆይቶ ከሐምሌ ወር 2011 ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ አቋርጧል፡፡ ስለሆነም እስከ ጥቅምት 20 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ሊከፈል የሚገባውን ብር 930,010.65 ተገዶ እንዲከፍልና ቀሪውን በእርቅ ሥምምነቱ መሠረት እንዲከፍል በቂ መያዣና ዋስትና እንዲያቀርብ ጠይቋል፡፡ አመልካች ባቀረበው መልስ ተጠሪው መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ቀጠሮ በፍርድ ቤት ያልታዘዘና በሬጅስትራር ያላለፈ ክስ ይዞ ሊቀርብ አይገባም፡፡ ንብረቶችን ለማዛወር ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው ክፍያ ያቋረጥነው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጨምረን ስለከፈልን ድጋሚ ልንከፍል አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የተጠሪ ማመልከቻ በሬጅስትራር ተመርቶ የቀረበ ስለሆነ ሊመረመር የሚገባው ነው ካለ በኋላ የሂሳብ ባለሙያ መድቦ ካሰራ በኋላ በእርቅ ሥምምነቱ መሠረት አመልካች ያልከፈለውን ብር 930,010.65 ከ8% ወለድ ጋር እና እስከ ታህሳስ 2012 ዓ/ም ድረስ የዋጋ ግሽበት ያመጣውን ብር 128,173.96 ለተጠሪ በ30 ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ አዟል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ በእርቅ ሥምምነቱ ማን ሊከፍል እንደሚገባ ያልተመለከተ በመሆኑና ንብረቱ የሚዛወረው ለአመልካች ስለሆነ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎች መሠረት ከታክሱ መርሕ አኳያ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እንደመሆኑ መጠን የታክስ ክፍያው በገዢ (በመጨረሻ ተጠቃሚው) ሊከፍል የሚገባ ስለሆነ ሥመ-ሀብቱ ሲዛወር አመልካች ሊከፍል ይገባል፡፡ ተጠሪ ተገቢውን ትጋት በማድረግ ሥመ-ሀብቱን ወደአመልካች እንዲያዛውርና ስመ-ሀብቱ ሲዛወር አመልካች ክፍያውን ያለማቋረጥ የሚከፍሉ ስለመሆኑ ቅድሚያ ቀሪ ገንዘቡን የሚመጥን ዋስትና እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ አመልካች ስመ-ሀብቱን ተጠሪ የሚያዛውር ስለመሆኑ ዋስትና ያቅርብልኝ ያለውን በተመለከተ አመልካች በእርቁ መሠረት ክፍያውን እስከከፈሉ ድረስ ስመ-ሀብቱ ያልተዛወረ ከሆነ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሲያቀርቡ ተገቢው ትዕዛዝ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡ የሂሳብ ባለሙያውን ክፍያ አመልካች ይክፈሉ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ለመልስ በተቀጠረበት ቀን ተጠሪ ክስ ማቅረቡ፣ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን አለመስጠቱ ሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ያስፈልጋል የተባለው ለአንድ መኪና ሲሆን ከዚህ ውጭ ግን ያልተላለፈ ንብረት አለ፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አመልካች ይክፈል መባሉ የጸደቀውን ሥምምነት የሚያሻሽል ነው፡፡ ተጠሪ ሥመ-ሀብቱን ካላዛወረ ለሁለተኛ ጊዜ አቤቱታ ለማቅረብ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ይከለክለናል፡፡ አመልካች ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1757 መሠረት ግዴታችን እንድንፈጽም ልንገደድ አይገባም፡፡ ተጠሪ ሥመ-ሀብቱን ያላዛወረው በራሱ ፍላጎትና ዝውውሩን በማገዱ ስለሆነና በእርቅ ሥምምነቱ የሚያዛውርበት ጊዜ ገደብ ስላለፈ ወዲያውኑ እንዲያዛውር ትዕዛዝ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ዋስትና ማቅረብ ያለበት አመልካች ሳይሆን ተጠሪ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ በእርቅ ሥምምነቱ መሠረት ተጠሪ ኃላፊነቱን መወጣቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ቀሪ ክፍያ እንዲከፍል መወሰኑ ከፍ/ሕ/ቁ. 1757 አኳያ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ያዘዘ ሲሆን የቀረበው መልስ ይዘትም ጉዳዩ አዲስ ክስ ሳይሆን በጸደቀው እርቅ መሠረት የሚፈጸም የአፈጻጸም ክርክር ነው፡፡ ተጠሪም በዕርቅ ሥምምነት መሠረት የተገኘውን መብት ለማስከበር የአፈጻጸም ክስ ማቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ በሥምምነቱ ያለበትን ግዴታ ፈጽሟል፣ አመልካች ክፍያውን አቋርጠዋል፡፡ የንብረቶችን ሠነድ ከአመልካች ስናገኝ ውክልና ለጉዳይ አስፈጻሚው ሰጥተናል፣ ሥመ-ሀብት ለማዛወር የተጀመረው ሂደት የሽያጭ ውል ከተዘጋጀና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ውስጥ ሠነድ አረጋጋጭ ቢሮ ከደረሰ በኋላ ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የተጠየቀ ሲሆን አመልካች ክፍያውን አልከፍልም በማለታቸው የንብረት ማስተላለፍ ሳይከናወን ቀርቷል፡፡ አነስተኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ከፍለው ማዛወር ሲችሉ ለተጠሪ የሚገባውን ክፍያ ላለመክፈል ያዘገዩታል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገዥ ነው የሚከፍለው፡፡ ንብረቶቹ በሙሉ በአመልካች እጅ ነው የሚገኙት፤ ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአፈጻጸም ክርክሩ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን እና የጸደቀውን የእርቅ ሥምምነት መሠረት በማድረግ የተመራ ስለመሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች እና ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 253220 ክርክር ሲያደርጉ ቆይተው ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ/ም የእርቅ ሥምምነት ያደረጉ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የእርቅ ሥምምነቱን ሐምሌ 23 ቀን 2010 ዓ/ም ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ የእርቅ ሥምምነት በፍርድ ቤት ከጸደቀ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277(2) እንደተመለከተው እንደፍርድ ተቆጥሮ የሚፈጸም ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 05 ቀን 2012 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በእርቅ ሥምምነቱ መሠረት ተጠሪ ማስተላለፍ የሚገባውን ንብረት አላስተላለፈልኝም በማለት ሥመ-ሀብቱን ተጠሪ ተገዶ እንዲፈጽም ሆነ ተጠሪ በዕርቅ ሥምምነቱ መሠረት ገንዘብ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የአፈጻጸም ክስን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ጉዳዩ በመደበኛ ክስ በሚመራበት አግባብ ሳይሆን በአፈጻጸም ክርክር ሥርዓት ሊመራ የሚገባው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ግራቀኙ ላቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ባለዕዳ የሆነውን ወገን ፍርድን ፈጽሞ እንዲቀርብ ወይም የማይፈጸምበትን ሕጋዊ ምክንያት በቃል እንዲያስረዳ ማዘዝ ሲገባው እንደመደበኛ ክስ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጥበት ማድረጉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም፡፡ ለአፈጻጸም የቀረበው ዕርቅ የጸደቀ በመሆኑ እንደፍርድ የሚቆጠር እንጂ እንደውል የሚታይ ባለመሆኑ ጉዳዩን የፍ/ሕ/ቁ. 1678፣ 1731፣ 1757 እና 1771 መሠረት በማድረግ በውል ሕግ መምራቱም ስህተት ያለበት ነው፡፡ በዕርቅ ሥምምነቱ መሠረት አመልካች ገንዘብ የመክፈል እና ተጠሪ ንብረት የማስተላለፍ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ ሁለቱም ወገን የሚያስፈጽሙት መብት ሆነ የሚፈጽሙት

ግዴታ ስላለባቸው ያልተፈጸመላቸውን በመለየት የአፈጻጸም ዳኝነት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ አመልካች ቀድሞ የአፈጻጸም ክስ ማቅረቡ ተጠሪን በሌላ መዝገብ የአፈጻጸም ክስ እንዲያቀርቡ የሚያደርግ አይደለም፤ ለአፈጻጸም መሠረት የሆነው ፍርድ አንድ በመሆኑ ሁለቱም በተመሳሳይ መዝገብ የአፈጻጸም ዳኝነት መጠየቃቸው ወጪና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ውጤታማ በሆነ አግባብ ክርክሩ እንዲመራ የሚያደርግና የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች ለማሳካት የሚረዳ በመሆኑ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የተጠሪን የአፈጻጸም ክስ እንደ ተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በመቁጠር ሥነ-ሥርዓት ሕግን ሳይከተል የቀረበ ነው በሚል የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዋናነት የሥነ-ሥርዓት ሕግ የተቀረጸው ሠዎች ግጭቶችን ሠላማዊ በሆኑ ሁኔታ እንዲፈቱ ለማስቻል (peaceful resolution of disputes)፣ መብታቸውን የሚያስከብሩበት ዘዴ እንዲኖርና ፍርድ ቤቶች ክርክርን ፍትሐዊ እና ወጭ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት እንዲችሉ ነው፡፡ የአፈጻጸም ችሎት ጉዳዩን መምራት ያለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችና ለአፈጻጸም መሠረት የሆነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሲሆን ውጤቱም ሠዎች በፍርድ ያገኙትን መብት ማስፈጸም ነው፡፡ ይሕ ሳይሆን ፍርድ የማይፈጸም ከሆነ የሕግ የበላይነት መገለጫ የሆነውን ዋናውን የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት አለመወጣት ይሆናል፡፡ ዜጎች በፍትሕ ሥርዓቱ የሚጠቀሙት መብታቸውን ለማስከበር ነው፡፡ የመብት ማስከበር መሠረቱ ደግሞ ፍርድን ከማናቸውም መሠናክል ነጻ በማድረግ ማስፈጸም ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ዜጎች በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ያገኙት ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ እና ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ውጤቱ ደግሞ መብት ካለመከበሩም በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት (public trust) እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ሰብዓዊ መብቶችን ከማስከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲኖር ያላቸውን የማይተካ ሚና የመወጣት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና አንዱ መገለጫ የወሰኑትን ውሳኔ ማስፈጸም በመሆኑ በፍርድ የተረጋገጠ መብት ሳይፈጸም ፍርዱ ያለውጤት እንዳይቀር የማድረግ ኃላፊነት መኖሩን ያሳያል፡፡

አመልካች በጸደቀው የዕርቅ ሥምምነት መሠረት በየወሩ መክፈል ያለባቸውን ግዴታ ማቋረጣቸውን በክርክሩ ሂደት ገልጸዋል፤ ለዚህ ምክንያት ያደረጉት ተጠሪ ግዴታውን እየተወጣ አይደለም በሚል የፍ/ሕ/ቁ. 1757ን በመጥቀስ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የእርቅ ሥምምነታቸው በፍርድ ቤት ከጸደቀ በኋላ እንደፍርድ የሚቆጠር ስለሆነ አመልካች ያለባቸውን ግዴታ የመፈጸም እና በተጠሪ የተመለከተው ግዴታ ካልተፈጸመ አሁን እንዳደረጉት የአፈጻጸም ክስ በማቅረብ መብታቸውን ማስከበር እንጂ ገንዘቡን መክፈል ሊያቋርጡ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የበሰለውን ክፍያ እንዲከፍሉና ቀሪውንም በዕርቅ ሥምምነቱ መሠረት አመልካች እንዲፈጽሙ ማዘዙ ፍርዱንና ሕጉን የተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የተጠሪ ግዴታ ንብረቶችን ማስተላለፍ ሲሆን አመልካች ንብረቶችን መረከባቸውን አልካዱም፤ የሚከራከሩት ሥመ-ሀብት አልተዛወረልኝም በሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ተገቢውን ትጋት በማድረግ ያልተዛወረ ንብረቶችን ሥመ-ሀብቱን ወደአመልካች እንዲያዛውር ብይን

መስጠቱ ተገቢ ነው። ንብረት ከመዛወር ጋር በተያያዘ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ በእርቅ ሥምምነቱ ማን ሊከፍል እንደሚገባ ያልተመለከተ በመሆኑና ንብረቱ የሚዛወረው ለአመልካች ስለሆነ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎች መሠረት ከታክሱ መርሕ አኳያ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እንደመሆኑ መጠን የታክስ ክፍያው በገዢ (በመጨረሻ ተጠቃሚው) ሊከፍል የሚገባ ስለሆነ ሥመ-ሀብቱ ሲዛወር አመልካች ሊከፍል ይገባል በሚል የደረሰበት መደምደሚያ ፍርዱን ለማስፈጸምና ሥመ-ሀብቱን ለማዛወር መታለፍ ያለባቸውን ሂደቶች እልባት የሚሰጥ እንጂ ከፍርዱ/ከዕርቅ ሥምምነቱ ውጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያው የሚመለከት ለየትኛው ንብረት ነው፣ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ሊዛወር የሚችል ንብረት መኖር አለመኖሩን በመለየት አፈጻጸሙም አለመቀጠሉ ግን ሊታረም የሚገባው ነው።

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ክፍያውን ከፈጸሙ ሥመ-ሀብት እንዲዛወርላቸው አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ ማለቱ በፍርዱ ላይ ሥመ-ሀብት ዝውውሩ ክፍያው ተጠናቆ ከመከፈል ጋር ያልተያያዘ በመሆኑና አመልካች ያልተፈጸመላቸው እንዲፈጽም የአፈጻጸም ክስ ባቀረቡት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ዳኝነቱን ማስፈጽም ሲገባው አቤቱታ ሲያቀርብ የሚታይ ነው ማለቱ አፈጻጸም ችሎት ያለውን ተግባርና ኃላፊነት ያልተከተለ ነው። በተጨማሪም በዕርቅ ሥምምነቱ አመልካች መክፈል ያለባቸውን ግዴታ በየወሩ የመክፈል ግዴታ ሲኖርባቸው ተጠሪ ደግሞ ሠነዶችን በተቀበለ በ60 ቀናት ውስጥ ንብረቱን የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት በመሆኑ፤ ተጠሪ ያለበትን ግዴታ ለመፈጸም ዋስትና እንዲቀርብ በሥምምነቱ ባልተመለከተበት ሁኔታ ሥመ-ሀብቱን ለማዛወር በቅድሚያ አመልካች ዋስትና እንዲያቀርቡ መታዘዙ ከፍርድ ውጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ተጠሪ በዕርቅ ሥምምነት መሠረት ካልተፈጸመለት አሁን እንዳደረገው የአፈጻጸም ክስ በማቅረብና ገንዘቡ በባለዕዳው ካልተከፈለ ንብረት በማስከበር መብትን ማስፈጸም እንጂ ግዴታውን ለመወጣት ቅድሚያ ዋስ እንዲቀርብለት መጠየቅ የማይችል በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ፍርዱንና የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል። በሌላ በኩል አመልካች ስለሂሳብ ባለሙያ ወጪን በተመለከተ ላቀረቡት የሠበር አቤቱታ በአመልካች የሚከፈለውን ክፍያ ለማስላት የሂሳብ ባለሙያ ተመድቦ የነበረ ሲሆን የባለሙያው ወጪ ክፍያ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ክፍያውን ያቋረጡት አመልካች በመሆናቸው ግዴታው የእርሳቸው መሆኑን በመገንዘብ ወጪውን አመልካች ይሸፍኑ ማለቱ ተገቢ ነው።

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 254342 ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 253220 ጥር 29 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።

2. አመልካች በጸደቀው የእርቅ ሥምምነት መሠረት ያልከፈሉትን ክፍያ ሆነ ወደፊት ሊከፈል የሚገባው ክፍያ እንዲከፍሉ ሆነ ተጠሪ ሥሙ-ሀብት እንዲያዛውር የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተገቢ ስለሆነ ጸንቷል፡፡

3. አመልካች ዋስትና እንዲያቀርቡና ክፍያ ከፈጸሙ በኋላ ስለስሙ-ሀብት ዝውውሩ አቤቱታ እንዲያቀርቡ የተሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

4. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያለባቸውን ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ፣ ተጠሪ ወደአመልካች ስሙ-ሀብታቸው የሚያዛውሯቸውን ንብረቶች በመለየት ንብረቶችን እንዲያስተላልፍ እንደፍርድ ሆኖ በሚፈጸመው በጸደቀው የእርቅ ሥምምነት መሠረት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ጉዳዩን መልሠናል፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሠ/መ/ቁጥር 199836

ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች ፡- አቶ ፀጋዬ አለሙ - ቀረቡ**

**ተጠሪ፡- አቶ ያሲን ኑሩ - ጠበቃ ሲራጅ አብደላ ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸም የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች 6 የፍርድ ባለእዳ በሆኑ ሰዎች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ የፍርድ ባለእዳዎች በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 25 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 529 የሆነ ቤት ስፋቱ 521 ከሆነ ካሬ ሜትር ቦታ ጋር እንዲያስረክቡኝ ተወስኗል፡፡በፍርድ አፈጻጸም በተሰጠ ትእዛዝ በፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በኩል 412 ካሬ ሜትር ቦታ እና ቤቱን ተረክቤያለሁ፡፡ነገር ግን ቀሪዉን 106 ካሬ ሜትር ቦታ የአሁን አመልካች የቤት ቁጥር 529/2 ከሆነዉ ቤታቸዉ ጋር ቀላቅለዉ ስለያዙት ሳልረከብ ቀርቻለሁ፡፡ አመልካች 106 ካሬ ሜትር ቦታ ከራሳቸዉ ቦታ ቀላቅለዉ ካርታ የወሰዱ ቢሆንም ካርታቸዉ መክኗል፡፡ እንዲሁም ሁከት ይወገድልኝ በማለት የመሰረቱት ክስ ዉድቅ ተደርጎ የያዙትን 106 ካሬ ሜትር ቤት እንዲለቁ ተወስኖባቸዋል፡፡ አስቀድሞ ለፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የተሰጠዉ ትእዛዝ የቤት ቁጥር 529 ላይ ብቻ ፍርዱ እንዲፈጸም የሚል ስለነበር ሊፈጸምልኝ ስላልቻለ በፍርዱ መሰረት ቀሪዉን 106 ካሬ ሜትር ጭምር እንዲያስረክቡኝ ትእዛዙ ተስተካክሎ ይታዘዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ ዉሳኔ የተሰጠዉ በቤት ቁጥር 529 ላይ እንጂ በቤት ቁጥር 529/2 ላይ አይደለም፡፡ ስለሆነም መፈጸም ያለበት በዉሳኔዉ መሰረት ስለሆነ አቤቱታዉ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ ዉሳኔዉ የቤት ቁጥር 529/2ን የሚመለከት ቢሆን ኖሮ በወቅቱ ተጠሪ መረከብ ይችሉ ነበር፡፡ እነዚህ ሁለት ቤቶች በአጥር እንኳን የማይገናኙ ኩታ ገጠም ያልሆኑ ቤቶች ናቸዉ፡፡ በሁከት ይወገድልኝ ክርክር ላይ 106 ካሬ ሜትር ቦታ እንዳስረክብ የተወሰነ ቢሆንም ይህ የዉሳኔ ክፍል በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ተሽሯል፡፡ ቦታቸዉን ወስጄ ከሆነ ክስ በመመስረት ሊጠይቁ ከሚችሉ

በስተቀር በአፈጻጸም የሚረከቡበት አግባብ የለም፡፡ ካርታ መክነ የተባለዉም ስህተት ነዉ በማለት የተጠሪ ጥያቄ ዉድቅ እንዲደረግ አስተያየታቸዉን በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 69191 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ዉሳኔዎችን እንዲሁም ከተለያዩ አስተዳደር አካላት የተጻፉ ሰነዶችን መርምሮ በቀን 27/02/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ዉሳኔ የተሰጠበት ቤት የቤት ቁጥር 529 የሚል ቢሆንም ቤቱ ግን በመሬት ላይ 529 እና 529/2 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 392/1 መሰረት ፍርድ መፈጸም ያለበት ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ሲሆን ይገባል፡፡ ለአመልካች አባት አቶ አለሙ አጋ በቀን 27/07/2004ዓ/ም የተሰጠዉ ቁጥሩ አከ/10/08/1/4976 የሆነዉ ካርታ ለተጠሪ በሽያጭ የተላለፈዉን ይዞታ ጭምር በማካተት የተሰጠ መሆኑ ተረጋግጦ መክኗል፡፡ አመልካች በግል ይዞታቸዉ ላይ እንዲፈጸም በማድረግ ሁከት እንደተፈጠረባቸዉ በመግለጽ በመሰረቱት ክስ መነሻ ክርክር አድርገዉ ሁከት አልተፈጠረም ተብሎ ተወስኖባቸዋል፡፡ ስለሆነም እንዲፈጸም በተጠየቀዉ ዉሳኔ ላይ ተጠሪ እንዲረከቡ የተወሰነዉ የቤት ቁጥር 529 የሆነ ቤት ከ521 ካሬ ሜትር ቦታ ጋር በመሆኑና 521 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የቤት ቁጥር 529/2 ጭምር ስለሚገኝ አስቀድሞ በመዝገቡ ላይ በተሰጡ ትእዛዛት መሰረት ለተጠሪ 521 ካሬ ሜትር እስኪሆን ድረስ ርክክብ እንዲፈጸም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 247012 ላይ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 09/04/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፍርድ ያላረፈበትንና ክርክር ያልተደረገበትን የቤት ቁጥር 529/2 የሆነ ቤት እና ይዞታዉን አመልካች ለተጠሪ ያስረክቡ የሚል እንድምታ ያለዉ አይደለም፡፡ ይልቁንም ፍርድ ካረፈበት በቤት ቁጥር 529 ከሚታወቀዉ 521 ካሬ ሜትር ይዞታ ዉስጥ የፍርድ ባለመብት ያልተረከቡት ቀሪ ይዞታ አመልካች ከቤት ቁጥር 529/2 ጋር ቀላቅለዉ የያዙ ስለሆነ ይህንኑ ቀሪ ይዞታ ሊያስረክቡ ይገባል የሚል ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ የተሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 392/1 መሰረት ለፍርድ አፈጻጸም ተስማሚ ትእዛዝ እንደተሰጠ የሚቆጠር ነዉ፡፡ ስለሆነም የተሰጠዉ ትእዛዝ ለተጠሪ የተወሰነላቸዉን ይዞታ አመልካች ከቤት ቁጥር 529/2 ይዞታ ጋር ቀላቅለዉ እንደያዙ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች በቀን 14/04/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- እንዲፈጸም በተጠየቀዉ ዋናዉ ዉሳኔ ላይም ሆነ በየትኛዉም ጊዜ በተሰጠ የአፈጻጸም ትእዛዝ ላይ አመልካች የቤት ቁጥር 529/2 የሆነዉን ቤት እንዳስረክብ የተሰጠ ዉሳኔ የለም፡፡ ሁከት እንዲወገድ በመሰረትኩት ክስ መነሻ 106 ካሬ ሜትር እንዳስረክብ ተሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በይግባኝ አሽሬያለሁ፡፡ የቤት ቁጥር 529/2 የሆነ ቤት በስሜ ተመዝግቦ ካርታ ተሰጥቶኛል፡፡ ካርታዉ መክኖ የነበረዉ ከተጠሪ ይዞታ ጋር በመቀላቀል ካርታ ስላሰራሁበት አይደለም፡፡106 ካሬ ሜትር የተባለዉ ቦታ የእኔ ቤት ቁጥር

529/2 የሆነዉ የሚገኝበት ስለሆነና የቤት ቁጥር 529/2 እንዳስረክብ ዉሳኔ ባልተሰጠበት በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘዉን ቤት እንዳስረክብ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች እንዲለቁ የአፈጻጸም ትእዛዝ የተሰጠበት ይዞታ በፍርዱ የተመለከተ መሆን አለመሆኑ ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 15/06/2013 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች ለተጠሪ ከተወሰነዉ 521 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተወሰነዉን ቦታ ወደራሳቸዉ ጨምረዉ ካርታ ማስወጣታቸዉ ተረጋግጦ ካርታዉ መክኗል፡፡ አመልካች ፍርድ ያረፈበትን ቁጥሩ 529 የሆነዉን ቤት ለለአግባብ አስቀይረዉ 529/1 የራሳቸዉን ቤት ደግሞ 529/2 አስደርገዉ የተገኙ በመሆኑ እንዲረከብ የተባለዉ ቀሪዉ ቦታ የቤት ቁጥር 529/2 ከሆነዉ የአመልካች ይዞታ ተቀንሶ እንዲሰጠኝ በቀን 07/10/2009ዓ/ም በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት የተወሰነ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ የተወሰነልኝ አጠቃላይ ይዞታ ስፋት 521 ካሬ ሜትር ቦታ በመሆኑና ቀሪዉ 106ካሬ ሜትር ቦታ ደግሞ አመልካች ከይዞታቸዉ ጋር ቀላቅለዉ ይዘዉ እንደሚገኙ ተረጋግጦ ስፋቱ 521 ካሬ ሜትር የሆነ ቦታ ከነቤቱ እንዲያስረክቡኝ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት ስለሌለ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 30/06/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካችና የስር የፍርድ ባለእዳዎች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነላቸዉ የቤት ቁጥር 529 የሆነ ቤት ከ521 ካሬ ሜትር ቦታ ጋር እንደሆነ በግራ ቀኙ የታመነና የስር ፍርድ ቤቶችም ያረጋገጡት ይሄዉ ነዉ፡፡ ፍርዱን ለማስፈጸም በተደረገዉ ሂደት ተጠሪ የቤት ቁጥር 529 የሆነ ቤት ከ412 ካሬ ሜትር ቦታ ጋር ተረክበዋል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ቀሪዉ 106 ካሬ ሜትር ቦታ አመልካች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የተወሰነበት አግባብ ነዉ፡፡

በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ስለ ፍርድ አፈጻጸም በሚደነግገዉ ሰባተኛ መጽሐፍ ስር ካሉ ድንጋጌዎች እንደምንረዳዉ የተፈረደለት ሰዉ ማመልከቻ በማቅረብ የፍርድ አፈጻጸም ሲጠይቅ ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት እንዲፈጸም የተጠየቀዉን ፍርድ መሰረት በማድረግ እና በዚህ መጽሐፍ ስር ባሉ ድንጋጌዎች የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ማስፈጸም ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈጸም በሚል የሚሰጠዉ ትእዛዝ ፍርዱን ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑንና የተወሰነላቸዉ ሰዎች የተወሰነላቸዉን ነገር እንዲያገኙ ለማድረግ የሚችል

ተስማሚ ትእዛዝ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 378 እና 392/1 ስር የተደነገገዉ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ፍርዱን ተግባራዊ ማድረግ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ ማስፈጸም ስለመቻላቸዉ ዋነኛ ማረጋገጫ ከመሆኑም በተጨማሪ ነጻነቱ የተጠበቀ እና የሕዝብ አመኔታ ያለዉ ፍርድ ቤት ለመኖሩ ማሳያ ሆኖ የሚያገለግል የዳኝነት ሥራ ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ በፍርዱ መሰረት የመረከብ መብት የሚኖራቸዉ የቤት ቁጥር 529 ተብሎ የሚታወቅ አንድ ቤት ከ521 ካሬ ሜትር ቦታ ጋር ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ ከመነሻዉም የቤት ቁጥር 529/2 የተባለ ቤት የቤት ቁጥር 529 አካል ነዉ በሚል ወይም ራሱን ችሎ ክርክር ተደርጎበት አመልካችና የስር የፍርድ ባለእዳዎች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ አልተወሰነም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤቶች ባቀረቡት ክርክር ላይ እንደገለጹት የቤት ቁጥር 529/2 ተብሎ የሚታወቅ ቤት የመረከብ መብት የላቸዉም፡፡ ስለሆነም የቤት ቁጥር 529/2 የሆነ ቤት የሚገኘዉ ተጠሪ እንዲረከቡ በተወሰነዉ 521 ካሬ ሜትር ቦታ ክልል ዉስጥ የሚገኝ መሆን አለመሆኑ፤ተጠሪ በአመልካችና በስር የፍርድ ባለእዳዎች ላይ ክስ ሲመሰርቱ የቤት ቁጥር 529/2 የሆነዉ ቤት በ521 ካሬ ሜትር ቦታ ክልል ዉስጥ ተሰርቶ የነበረ ነዉ ወይስ ክርክር ከተደረገና ዋናዉ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ለተጠሪ በተወሰነላቸዉ 521 ካሬ ሜትር ክልል ዉስጥ የተሰራ ነዉ የሚለዉን ከቤቶቹ ማህደር፣ ከሚመለከተዉ አካል ማስረጃ በማስቀረብና በባለሙያ በማረጋገጥ ሊፈጸም የሚችል የፍርድ ክፍል ካለ ሊፈጸም የሚችልበትን አግባብ የሚያሳይ ተስማሚ ትእዛዝ መስጠት ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ሲታይ በደፈናዉ አመልካች 106 ካሬ ሜትር ለተጠሪ ያስረክቡ የሚል ብቻ በመሆኑ በዚህ 106 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ፍርድ ያላረፈበት የቤት ቁጥር 529/2 የሚገኝ ከሆነ አፈጻጸሙ ምን ይሆናል ለሚለዉ እልባት ያልሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ ለፍርድ አፈጻጸሙ የማያዳግም ተስማሚ ትእዛዝ ሰጥተዋል የሚያሰኝ ስላልሆነ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69191 ላይ በቀን 27/02/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 247012 ላይ በቀን 09/04/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ የቤት ቁጥር 529/2 የሆነ ቤት የሚገኘዉ ተጠሪ እንዲረከቡ በተወሰነዉ 521 ካሬ ሜትር ቦታ ክልል ዉስጥ የሚገኝ መሆን አለመሆኑ፤ተጠሪ በአመልካችና በስር የፍርድ ባለእዳዎች ላይ ክስ ሲመሰርቱ የቤት ቁጥር 529/2 የሆነዉ ቤት በ521 ካሬ ሜትር ቦታ ክልል ዉስጥ ተሰርቶ የነበረ ነዉ ወይስ ክርክር ከተደረገና ዋናዉ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ለተጠሪ በተወሰነላቸዉ 521 ካሬ ሜትር ክልል ዉስጥ የተሰራ ነዉ የሚለዉን ከቤቶቹ ማህደር፣ ከሚመለከተዉ አካል ማስረጃ በማስቀረብና በባለሙያ በማረጋገጥ የ521 ካሬ ሜትር

አካል የሆነ 106 ካሬ ሜትር ቦታ ባዶ ቦታ ከሆነ በፍርዱ መሰረት እንዲያስፈጽም፤ በዚህ 106 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የቤት ቁጥር 529/2 የሚገኝ ከሆነ ሊፈጸም የሚችል የፍርድ ክፍል መኖር አለመኖሩን አረጋግጦ ለጉዳዩ ተገቢዉን እልባት እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ወስነናል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ                                                            የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ፡-200228

ቀን፡- 03/02/2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ**

**ተሾመ ሽፈራዉ**

**ሀብታሙ እርቅይሁን**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ነጻነት ተገኝ**

**አመልካች ፡- ወ/ሮ አገሪቱ አስናቀ - ወኪል ፎዚያ አህመድ - ቀረቡ**

**ተጠሪ፡- ሼህ ኡመር መሀመድ - አልቀረቡም**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍርድ ቤት የፀደቀ የዕርቅ ስምምነት አፈጻጸም የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች ለደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ግራ ቀኝ በመካከላቸዉ ለነበረዉ የከተማ ቦታ ወሰን ክርክር እልባት ለመስጠት በቀን 23/05/2011ዓ/ም የእርቅ ስምምነት ፈጽመዉ የዕርቅ ስምምነታቸዉም በስር ፍርድ ቤት በቀን 01/06/2011ዓ/ም ፀድቋል፡፡ በዚህ የእርቅ ስምምነት መሰረት አመልካች 5 ሜትር ወርድና 0.80 ሜትር ቁመት (4 ካሬ ሜትር) ስፋት ያለዉን ቦታ በመልቀቅ ተጠሪ በዚህ ቦታ ላይ በሠሩት የሰርቪስ ቤት ግድግዳ ላይ የጣራ ተዛነፍ ጋር በማያያዝ በራሳቸዉ ወጪ ግድግዳዉን በብሎኬት በማድረግ የግንባታ ፈቃድ አዉጥታ መስራት እንድትችል ስምምነት ፈጽመዋል፡፡ በዚህ በፀደቀዉ የዕርቅ ስምምነት መሰረት የአመልካች ይዞታ 196 ካሬ ሜትር እንዲሆን የተጠሪ ደግሞ 139 ካሬ ሜትር ሆኖ ካርታ እንዲሰራልን በዉሳኔ በጸደቀዉ መሰረት የደሴ ከተማ አስተዳደር የመናፈሻ ክፍለ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ስለከለከለኝ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ይታዘዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የደሴ ከተማ መናፈሻ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት ማኔጅመንት የግንባታ ፈቃድ ጽ/ቤትን ጠይቆ የመሬታቸዉ ስፋት 196 ስለሆነና ስታንዳርዱ የሚጠይቀዉን 200 ካሬ ሜትር የሚለዉን ስለማያሟላ የግንባታ ፈቃድ አልተሰጣቸዉም በማለት አስተያየት ሰጥቷል፡፡ይህንን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 23232 ላይ በቀን 18/02/2012 ዓ/ም የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ሥልጣን በተሰጠዉ አስተዳደር አካል የሚታይ እንጂ ፍርድ ቤት የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ሊያዝ የሚችልበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ በፍርድ ቤት ታይቶ ሊወሰን የሚችል የክስ ምክንያት የለዉም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በመ/ቁጥር 44351 ላይ በቀን 25/02/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 ሰርዞባቸዋል፡፡ እንዲሁም አመልካች ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር

አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 0328466 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 13/04/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች እንዲፈጸምላቸዉ የጠየቁትን የእርቅ ስምምነት ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ስለሆነ የእርቅ ስምምነቱን በማጽደቅ የተሰጠዉ ዉሳኔ ይሻርልኝ የሚል ክርክር አቅርበዉ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረዉ ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በፀደቀዉ የእርቅ ስምምነት ላይ አመልካች የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ በዉሳኔዉ ላይ ሰፍሯል ወይስ አልሰፈረም የሚለዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚመለከተዉ የመንግስት አስተዳደር አካል ከ200 ካሬ ሜትር በታች በሆነ ቅይጥ ይዞታ ላይ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት እንደማይቻል ስለገለጸ የሥር ፍርድ ቤቶች የሠጡት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት አፅንቷል፡፡

አመልካች በቀን 21/02/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካችና ተጠሪ የፈጸምነዉ የዕርቅ ስምምነት የሥር የወረዳ ፍርድ ቤት ከመፅደቁም በተጨማሪ በየትኛዉም የበላይ ፍርድ ቤት አልተሻረም፡፡ በፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ እስካልተሻረ ድረስ ሊፈጸም እንደሚገባ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 101345 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ማዘጋጃ ቤቱ ዉሳኔዉ ሊፈጸም የሚችል አይደለም ስላለ ብቻ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የአፈጻጸም ማመልከቻ ዉድቅ ማድረጋቸዉ ስህተት ነዉ፡፡ በጸደቀዉ የእርቅ ስምምነት መሰረት አመልካች ከተጠሪ ግንባታ ጋር በማጋጠም እንድሰራ ስምምነት የተደረገ በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ እንዳገኝ ተደርጎ መፈጸም ይገባል፡፡ እንዲሁም የእርቅ ስምምነቱ ለሕግ ተቃራኒ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ማጽደቅ አልነበረበትም ከተባለም ፀድቆ የነበረዉን የግራ ቀኙ የዕርቅ ስምምነቱ ሊፈጸም የማይችል በመሆኑ በዉሳኔ እንዳልጸደቀ ተቆጥሮ ተሰርዞ ወደነበርንበት እንድንመለስ ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ ለክርክሩ እልባት መስጠት ሲገባቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ እልባት በማያገኝበት መንገድ መዝጋቱ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍርድ ቤት የፀደቀዉንና የግራ ቀኙ ስምምነት ወይም ፍርድ የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ አንጻር ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 20/05/2013 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

የዕርቅ ስምምነቱ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም ተብሎ በፍርድ ቤት ፀድቆ ክርክሩ ተቋርጧል፡፡ፍርድ ቤቱ እንደዉሳኔዉ እንዲፈጸም ለደሴ ከተማ አገ/ግ/ጽ/ቤት እና ለደሴ ከተማ አስተዳደር ለመናፈሻ ክፍለ ከተማ ደርሶ ለአመልካች 196ካ/ሜትር ለተጠሪ ደግሞ 139ካ/ሜትር በሆነ ይዞታችን መጠን ካርታ ተዘጋጅቶ ተሰጥቶን ዉሳኔዉ ተፈጽሟል፡፡በዚህ አግባብ ከተፈጸመ በኋላ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታም ሆነ የዕርቅ ስምምነቱ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ነዉ የሚባል ከሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች ዉድቅ በማድረጋቸዉ የተፈፀመ ስህተት የለም፡፡

የግንባታ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የአስተዳደር አካል እንጂ የፍርድ ቤት ስላልሆነ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 27/07/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ እንዲፈጸምላቸዉ የጠየቁት ከተጠሪ ጋር ለነበራቸዉ የከተማ ቦታ ወሰን ክርክር እልባት ለመስጠት ከተጠሪ ጋር ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት ለሞራልና ለሕግ ተቃራኒ አይደለም በሚል በፀደቀዉ መሰረት የደሴ ከተማ አስተዳደር የመናፈሻ ክፍለ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ስለከለከለኝ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ይታዘዝልኝ በሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ በመካከላቸዉ ለነበረዉ ክርክር እልባት ለመስጠት የዕርቅ ስምምነት አድርገዉ የእርቅ ስምምነታቸዉም በፍርድ ቤት መጽደቁን ሳይክዱ አመልካች የጠየቁት ዳኝነት የክስ ምክንያት ያለዉ ዳኝነት ጥያቄ አይደለም በማለት ተቃዉመዋል፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት የተጠሪን ክርክር ተቀብሎ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ሥልጣን በተሰጠዉ አስተዳደር አካል የሚታይ እንጂ ፍርድ ቤት የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ሊያዝ የሚችልበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ በፍርድ ቤት ታይቶ ሊወሰን የሚችል የክስ ምክንያት የለዉም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ አድርጓል፡፡ በየደረጃዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ታይቶ በመጨረሻ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ የእርቅ ስምምነቱ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ነዉ ተብሎ የፀደቀ ቢሆንም የአመልካች ይዞታ ከ200 ካሬ ሜትር በታች ስለሆነ የመንግስት አስተዳደር አካል ከ200 ካሬ ሜትር በታች በሆነ ቅይጥ ይዞታ ላይ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት እንደማይቻል ስለገለጸ የሥር ፍርድ ቤቶች የሠጡት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት አፅንቷል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት በጸደቀዉ የዕርቅ ስምምነት መሰረት የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠኝ አለመታዘዙ፤ ይህ የማይሆን ከሆነም የዕርቅ ስምምነቱ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ነዉ ተብሎ ፈርሶ ወደነበርንበት እንድንመለስ አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በሚል ነዉ፡፡

በአንድ የፍርድ ዉሳኔ ባለመብት ስለሆንኩ በዉሳኔዉ መሰረት ይፈጸምልኝ በሚል ተከራካሪ ወገን የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ሲያቀርብ ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ስለ ፍርድ አፈጻጸም በተደነገገዉ ሰባተኛ መጽሐፍ ስር ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲፈጸም የተጠየቀዉን ፍርድ መሰረት በማድረግ እና በዚህ መጽሐፍ ስር ባሉ ድንጋጌዎች የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ማስፈጸም ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈጸም በሚል የሚሰጠዉ ትእዛዝ ፍርዱን ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑንና የተወሰነላቸዉ ሰዎች የተወሰነላቸዉን ነገር እንዲያገኙ ለማድረግ የሚችል ተስማሚ ትእዛዝ መሆኑን

ማረጋገጥ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 378 እና 392/1 ስር የተደነገገዉ ያስገነዝባል፡፡ አንድን ፍርድ የመፈጸም ግዴታ የሚኖርበት የፍርድ ባለእዳዉ እንጂ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የለሌለዉ ሦስተኛ ወገን እንዳልሆነ ልብ ማለት ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ፍርዱን ተግባራዊ ማድረግ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ ማስፈጸም ስለመቻላቸዉ ዋነኛ ማረጋገጫ ከመሆኑም በተጨማሪ ነጻነቱ የተጠበቀ እና የሕዝብ አመኔታ ያለዉ ፍርድ ቤት ለመኖሩ ማሳያ ሆኖ የሚያገለግል የዳኝነት ሥራ ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች በፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻቸዉ ፍርድ ቤቱ እንዲያስፈጽምላቸዉ የጠየቁት ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉን ክርክር ለመቋጨት ያደረጉትን የዕርቅ ስምምነትና የዕርቅ ስምምነቱን በማጽደቅ የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ፡፡ የዕርቅ ስምምነቱም ሆነ የእርቅ ስምምነቱን በማጽደቅ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚመለከተዉ ግራ ቀኙን እንጂ አመልካች የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ጠይቂ ስለከለከለኝ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ይታዘዝልኝ ያሉትን የደሴ ከተማ አስተዳደር የመናፈሻ ክፍለ ከተማን የሚመለከት አይደለም፡፡ አመልካች ከደሴ ከተማ አስተዳደር መናፈሻ ክፍለ ከተማ ጋር ያደረጉት ክርክር ካለመኖሩም በተጨማሪ የደሴ ከተማ አስተዳደር የመናፈሻ ክፍለ ከተማ ለአመልካች የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ የተሰጠ ዉሳኔም የለም፡፡ የጸደቀዉ የዕርቅ ስምምነት ለአመልካች የግንባታ ፈቃድ ይሰጣቸዉ የሚል እንኳን ቢሆን የግንባታ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣንና ተግባር የአስተዳደር አካልን የሚመለከት ሥራ እንጂ ተጠሪ የሚፈጽሙት አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ እንደ ፍርድ ባለእዳ ለአመልካች የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጡ ሊታዘዝ ስለማይችል ከዚህ አንጻር አመልካች እንዲፈጸምላቸዉ የጠየቁት የእርቅ ስምምነት በተጠሪ ሊፈጸም የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካችን የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ዉድቅ ማድረግ ነበረባቸዉ፡፡

ሲጠቃለል የወረዳዉ ፍርድ ቤት አመልካች ፍርድ ቤቱ እንዲያስፈጽምላቸዉ የጠየቁት ዳኝነት የፍርድ ባለእዳ በሆኑት ተጠሪ የሚፈጸም አይደለም በማለት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ የፍርድ አፈጻጸም ክርክር እንደ መደበኛ ክስ በመቁጠር አመልካች የጠየቁት ዳኝነት በፍርድ ሊታይ የሚችል (Justiciable matter) አይደለም የሚል ምክንያት ጠቅሶ የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአስተዳደር አካል ተከራካሪ ሆኖ ያቀረበዉ ክርክር በሌለበት የአመልካች ይዞታ ስፋት ከ200 ካሬ ሜትር ያነሰ ስለሆነ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉ የጠየቁትን የሥር ፍርድ ቤት ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ ነዉ ሲል የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ ማጽናቱ አመልካች በቀጣይ በአስተዳደር አካል ላይ ሊያነሱ የሚችሉትን ክርክርና ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጠብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካችም የግንባታ ፈቃድ አለአግባብ ተከልክያለሁ የሚሉ ከሆነ አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት በሚመለከተዉ አካል ላይ ክስ በማቅረብ መጠየቅ ከሚችሉ በስተቀር ከተጠሪ ጋር የፈጸሙትንና በፍርድ ቤት የፀደቀ የዕርቅ ስምምነት መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉ እንዲያዝላቸዉ መጠየቃቸዉ ስለፍርድ አፈጻጸም የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት የተከተለ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23232 ላይ በቀን 18/02/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44351 ላይ በቀን 25/02/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ፣ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 0328466 ላይ በቀን 13/04/2013ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካችም በአስተዳደር አካል የግንባታ ፈቃድ አለአግባብ ተከልክያለሁ የሚሉ ከሆነ አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት በሚመለከተዉ አስተዳደር አካል ላይ ክስ በማቅረብ መጠየቅ ይችላሉ ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 200919

ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ በቀለ ድሪብሳ - ጠበቃ ዘነበ ጥላሁን ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ የምክር በሪሁን - ጠበቃ ግሩም አየለ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን የአፈጻጸም ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የፍርድ ባለእዳ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለመብት በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩን አመጣጥ ስንመለከት ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15170 አመልካችን ጨምሮ በ5 ሰዎች ላይ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 21 የሚገኝ የቤት ቁጥር 552 እንዲያስረክቡኝ እና ስመሀብት እንዲያዛውሩልኝ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርበው መስከረም 26 ቀን 1999 ዓ.ም. አመልካችን ጨምሮ 4 ተከሳሾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡ ተጠሪም ይህንን ውሳኔ መሰረት በማድረግ በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 109064 የአፈጻጸም አቤቱታ አቅርበው ቤቱን ከተረከቡ በኂላ አመልካች እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ ተጠሪ ቤቱን እንዲረከቡ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ውሳኔውን አሽረዋል፡፡ የውሳኔውን መሻር ተከትሎ አመልካች እና ባለቤታቸው ተጠሪ በአፈጻጸም የተረከቡትን ቤት መልሰው እንዲያስረክቧቸው አቤቱታ አቅርበው ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እና ለባለቤታቸው ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ አስረክበው አፈጻጸሙ በመጠናቀቁ የአፈጻጸም መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ከዚህ በኂላ ተጠሪ አጠቃላይ ይዞታዬ 391 ካ.ሜ. የነበረ ሲሆን ከዚህ ላይ ለአመልካች እና ባለቤታቸው ቤቱን ከ200 ካ.ሜ. ይዞታ ጋር ሳስረክብ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ይቀረኛል፡፡ ስለዚህ በቀሪው 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት የይዞታ ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ እንዲሰጠኝ ይታዘዝልኝ በማለት በተዘጋው የአፈጻጸም መዝገብ ላይ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም በተጠሪ አቤቱታ መሰረት የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ለተጠሪ እንዲሰጥ አዟል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዝ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ቅሬታው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካች በ06/05/2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማሳረም ሲሆን የቅሬታው ይዘት በ191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ ለተጠሪ ካርታ እንዲሰጥ ፍርድ አልተሰጠም። የአፈጻጸም ትእዛዙ ሲሰጥም አመልካች አስተያየት እንድሰጥ አልተደረገም። ይዞታው ለ15 ዓመት ግብር የገበርኩበት ስለሆነ ለተጠሪ ካርታ ተሰርቶ ይሰጥ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ የተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ ፍርዱን የተከተለ ነው አይደለም? የሚለውን ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል።

ተጠሪም በ01/07/2013 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ የአፈጻጸም ትእዛዙ የተሰጠው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15170 መስከረም 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በተሰጠ ፍርድ መሰረት ነው። በዚህ ውሳኔ ቤት እንድረከብ የተወሰነ ቢሆንም አመልካች እና ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ በውሳኔው ላይ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25551 ቤት እንድረከብ የተሰጠውን ውሳኔ ክፍል በመሻሩ ከአመልካች እና ከባለቤታቸው በአፈጻጸም የተረከብኩትን ቤት ከ200 ካ.ሜ. ቦታ ጋር መልሼ አስረክቤአለሁ። አመልካች በውሳኔው መሰረት ሳይረከቡ የቀረ ነገር የለም። በተጨማሪም የይዞታ የምስክር ወረቀት ተሰርቶ እንዲሰጠኝ የታዘዘው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02371፣ 04076፣ 04952፣ 34520 እንዲሁም በፌደራል ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 09161 እና 38575 የተሰጡ ውሳኔዎች ታይተው በመሆኑ በተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል።

አመልካችም በ16/07/2013 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል።

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ትእዛዝ እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነው ለቅሬታ መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ትእዛዝ ለተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ሰርቶ ይስጥ የሚል ነው። አመልካች ይህንን ትእዛዝ የሚቃወሙት ተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰራላቸው የተሰጠ ውሳኔ የለም በሚል ነው። ተጠሪ በበኩላቸው በመዝገብ ቁጥር 15170 እና በሌሎች መዝገቦች ላይ በተሰጠ ውሳኔ መሰረት የአፈጻጸም ትእዛዙ የተሰጠ መሆኑን በመግለጽ ትእዛዙ ተገቢ መሆኑን ተከራክረዋል። በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻው ለተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰርቶ እንዲሰጣቸው የተሰጠ ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለው ይሆናል።

በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ ፍርድ ቤቶች ሊያስፈጽሙ የሚገባው በተሰጠው ፍርድ መሰረት መሆን እንዳለበት የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ ከተዘረጋው ስርአት ውጪ የአፈጻጸም ችሎት የፍርዱን ይዘት በሚቀይር መልኩ ወይም ፍርድ ያልተሰጠበትን ነገር ማስፈጸም አይችልም፡፡ የፍርድ አፈጻጸም ስርአት አንድ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በራሱ አማካኝነት በህጉ የተዘረጋውን የአፈጻጸም ስርአት በመከተል ወደውጤት የሚቀይርበት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አፈጻጸሙ ፍርዱን የተከተለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታን በተመለከተ ፍርድ ተሰጥቶበታል የሚሉት አንድም በመዝገብ ቁጥር 15170 በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመስከረም 26 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጠውን ፍርድ በመጥቀስ ሲሆን እኛም የዚህን ፍርድ ይዘት ተመልክተናል፡፡ የፍርዱ ይዘት ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ በአራት ሰዎች እና በአዲስ አበባ መስተዳድር የስራ ከተማ ልማት ቢሮ ላይ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 21 በካርታ ቁጥር 17910 የተመዘገበውን የቤት ቁጥር 552 የሆነውን ቤት ለመረከብ እና ስመ ሀብት እንዲዛወርላቸው ክስ አቅርበው አራቱ ተከሳሾች የተጠቀሰውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካች ባለቤት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25551 የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ተጠሪ ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩን የፍርዱ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን በተጠሪም የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት ተጠሪ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 15170 በግልጽ ቤት ይረከቡ በሚል የተፈረደላቸው ፍርድ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25551 በሰጠው ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 15170 በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ መሰረት ለተጠሪ ሊፈጸምላቸው የሚችል ነገር የለም ማለት ነው፡፡ የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ትእዛዙን ሲሰጥ በምክንያትነት የጠቀሰው  የተጠሪ አጠቃላይ ይዞታ 391 ካ.ሜ. ሲሆን ከዚህ ይዞታ ላይ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 349 መሰረት 200 ካ.ሜ. ቦታ ተቀንሶ አመልካች እና ባለቤታቸው ሲረከቡ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ለተጠሪ ይቀራል በሚል ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት የመዝገብ ቁጥር 15170 ላይ ተጠሪ ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ በተሻረበት ሁኔታ ለተጠሪ ምን ያክል ይዞታ እንደሚቀር እና በሚቀረው ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰራ በአፈጻጸም ችሎት ሊታዘዝ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ይህ ማለት ግን ተጠሪ ከፍርድ ቤት የአፈጻጸም ትእዛዝ ውጪ ለሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው መጠየቅ አይችሉም ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ይዞታው ላይ በሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጣቸው ከሚጠይቁ እና ይህ አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው በተገቢው የህግ አግባብ አለኝ የሚሉትን መብት ክስ በማቅረብ ከሚያስከብሩ በስተቀር ተጠሪ በጠቀሱት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15170 ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ ለተጠሪ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማድረግ የሚፈጸም ፍርድ የለም፡፡

ሌላው ተጠሪ ከአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02371፣ 04076፣ 04952፣ 34520 እንዲሁም በፌደራል ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 09161 እና 38575 የተሰጡ ውሳኔዎች ታይተው ነው የአፈጻጸም ትእዛዝ የተሰጠው በማለት የሚያነሱትን ክርክር ስንመለከት በነዚህ በውሳኔዎች ላይም ቢሆን አመልካች የቤት ቁጥር 552 ን በተመለከተ ሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበው ውድቅ የተደረገበት እንጂ ተጠሪ የሚገባቸው ይዞታ ምንያክል እንደሆነ ተረጋግጦ ፍርድ ያረፈበት አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰርቶ እንዲሰጥ በማለት የአፈጻጸም ትእዛዝ የሰጠው ተጠሪ መብት አግኝቻለሁ የሚሉበት ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ በተሻረበት እና ተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ፍርድ በሌለበት በመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህጉ የተዘረጋውን የአፈጻጸም ስርአት የሚቃረን እና ከአፈጻጸም ችሎት ስልጣን ውጪ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1ኛ. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር109006 በ10/03/2012 ዓ.ም. እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 247114 በ22/04/2013 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

2ኛ. ተጠሪ ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ በተሻረበት እና 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰርቶ እንዲሰጣቸው የተሰጠ ፍርድ በሌለበት የአፈጻጸም ትእዛዝ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡

3ኛ. ይህ ውሳኔ ተጠሪ ለሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ጥያቄ እንዳያቀርቡ የሚያግድ አይደለም፡፡

4ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገ ክርክር ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁጥር 206151

ታሕሳስ 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አቡበከር ዓሊ - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1) አቶ ተስፋዬ እንድሪስ

2) ወ/ሮ ወርቅዓ/ም ደሣለኝ } አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 205344 ሚያዚያ 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር የሚመለከት ሆኖ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጀመረው የአፈፃፀም ክርክር አመልካች ባለቤቴ ናት ከሚላት ሰው ጋር ሆኖ የአፈፃፀም ተከሣሽ ተጠሪዎች ደግሞ የአፈፃፀም ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለሰበር ክርክሩ መነሻ የሆነው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 51165 በሆነው መጋቢት 21 ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡- አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል በተወሰነበት እዳ ምክንያት ተጠሪዎች ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ክርክር በሌለበት ታይቶ በባህር ዳር ከተማ የሚገኘው የአመልካች ቤት በጨረታ ተሸጧል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች የካቲት 23 ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታው በአፈፃፀም ክሱ መጥሪያ አደራረስ፣ የጨረታው አሸናፊ ከፍርድ ባለገንዘቦች ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ከጨረታው ሂደትና የቤቱ ስመ ንብረት የጨረታ አሸኛፊ ነው ለተባለው ሰው እንዲዞር በተሰጠው ትዕዛዝ አፈፃፀም ላይ ተፈፅሟል ያላቸውን የቅን ልቦና ጉድለትና ሕገ ወጥ ድርጊቶችን በመዘርዘር ጨረታው እንዲሰረዝለት የጠየቀ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካች ቀደም ሲል ፍርድ ቤቱ በትዕዛዝ ያለፈውን ጉዳይ በድጋሚ ያቀረበው ነው ሲል ውድቅ

አድርጓል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ስለተሰረዘበት ይህ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 12ቀ ን 2013 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው ቀደም ሲል ያቀረበውና ፍርድ ቤቱ ውድቅ ያደረገበት አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 439 መሰረት እዳውንና ለጨረታው የወጣውን ወጪ ለመክፈል እንደሚፈልግና የጨረታው ሂደት እንዲቋረጥለት ሆኖ ሣለ፣ ተጠሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ፍርድ ቤቱ ሣይፈቅድላቸው በእጅ አዙር በጨረታው ልጃቸውን አሳትፈው ቤቱን ስለመግዛታቸው የደረሰበት መሆኑን በመግለፅ ተጣርቶ ጨረታው እንዲሰረዝለት ጠይቆ ሣለ፣ የቤቱ የጨረታ መነሻ ዋጋና የተሸጠበት ዋጋ ተቀራራቢ መሆኑ በሂደቱ ላይ የተፈፀመ ያልተገባ ድርጊት መኖሩን እያሣዩ፣ በጨረታ የተሸጠው ቤት በአመልካችና በባለቤቱ የጋብቻ ክርክር በሌላ መዝገብ ታግዶ ባለበት፣ ተጠሪዎች የአመልካች አድራሻ አዲስ አበባ መሆኑን እያወቁ መጥሪያ ሣያደርሱ ጉዳዩ በሌለበት መታየቱ እንዲጣራለት ያቀረበውን አቤቱታ በአግባቡ ሳይመረመር በድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎት አመልካች የካቲት 15 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረበው አቤቱታና የካቲት 23 ቀን 2013ዓ/ም ያቀረበው አቤቱታ ተመሣሣይነት ያለው ነው ተብሎና ድጋሚ እንደቀረበ ተወስዶ ውድቅ መደረጉን ተገቢነቱ ላይ ግራ ቀኙ ተከራክረውበት ተመርምሮ ውሣኔ እንዲሰጥበት ታዞ የፅሁፍ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካች የካቲት 15 ቀን 2013ዓ/ም እና የካቲት 23 ቀን 2013ዓ/ም ባቀረበው አቤቱታ የጠየቀው ዳኝነት ተመሳሣይ መሆኑን፣ የሥነ ስርዓት ሕጉ ዋና ዓላማም ክርክሮችን በአጭር ጊዜ መቋጨት መሆኑን፣ በጥቅሉ ተመሣሣይ ጉዳይ እንዲፈፀምለት ሁለት ጊዜ አቤቱታ ማቅረቡን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና በዚህ ችሎት የቀረበውን ክርክር ሲሆን የአመልካች ቤት ለፍርድ ማስፈጸሚያነት እንዲውል ከተሸጠ በኋላ በአፈፃፀም ክርክሩና በጨረታው ሂደት ተፈጽሟል ያላቸውን ተገቢነት የሌላቸው ሕገ ወጥ ድርጊቶችን በመዘርዘር ጨረታው እንዲሰረዝለት አመልካች የካቲት 23 ቀን 2013ዓ/ም ያቀረበው አቤቱታ በድጋሚ የቀረበ ነው እንዲሁም ጨረታውን ሊያሰርዝ የሚችል ምክንያትም አልተገኘም ተብሎ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር በጭብጥነት ይዘን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ተሳታፊ ባልሆነበት የአፈፃፀም ክርክር ባህር ዳር ከተማ የሚገኘው ቤቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት መሸጡን ተከትሎ የካቲት 15 ቀን 2013 ዓ/ምና የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ/ም

የተባፈ አቤቱታ አፈፃፀሙን ለመራው ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረቡን የጉዳዩ አመጣጥ ያስገነዝባል፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው አመልካቹ የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረበውን አቤቱታ የመረመረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበለት አቤቱታ ቀደም ሲል ትዕዛዝ **ሰጥበት** ያለፈውን ጉዳይ መሰረት በማድረግ በድጋሚ የቀረበ ነው እንዲሁም ጨረታው የሚሰረዝበት ምክንያት የለም ሲል ውድቅ በማድረጉና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በማፅናቱ ነው፡፡

ሆኖም አመልካች በሁለቱ ቀናት የቀረበው አቤቱታ የተለያያ ስረ ነግርን መሰረት ያደረጉ ሆነው ሣለ ድጋሚ የቀረበ ነው በሚል ምክንያትና በአቤቱታው ላይ የጠቀሳቸው ጉድለቶች መኖር አለመኖራቸው ሣይጣሩ ለማስረዝ የሚችል ምክንያት የለም በሚል ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ ይከራክራል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በሁለቱም ቀናት የቀረቡት የአመልካች ላይ የተጠየቀው ዳኝነት ተመሣሣይ ሆኖ ሣለ የሥነ ስርዓት ሕጉን ድንጋጌ ቁጥር መቀየሩ ብቻውን የተለያየ አቤቱታ እንዳቀረበ በማስመሰል ክርክር ማቅረቡ ተገቢነት የለውም ሲሉ የስር ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

በቀረበልን ጉዳይ ውሣኔ ለመስጠት ለአጣሪ ችሎቱ የቀረቡትን የአመልካች አቤቱታዎች ይዘት መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች የካቲት 15 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረበው አቤቱታ በዋናው ፍርድ ላይ እንዲከፍል የተወሰነበትን እዳና ቤቱን ለመሸጥ የወጣውን ወጪ መክፈል እንደሚፈልግና ገንዘቡን እንደሚያሲዝ በመግለፅ የጨረታው ሒደት እንዲቆምለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 439 መሰረት መጠየቁን፤ የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ/ም ፅፎ ያቀረበው አቤቱታ ደግሞ በአፈፃፀም ክርክሩ ወቅት ተጠሪዎች የአመልካች አድራሻ አዲስ አበባ መሆኑን እያወቁ ባህር ዳር ከተማ እንደሚኖር በማስመሰል መጥሪያው በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር እንዲለጠፍ አድርገው በጋዜጣ እንዲጠራ አድርገው ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል መደረጉን፣ ተጠሪዎች ፍርድ ቤቱን ሣያሥፈቅዱ በእጅ አዙር በልጃቸው አማካኝነት በጨረታው ተሳትፈው አመልካችን በሚጎዳና አኳኋን የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን፣ በጨረታ የተሸጠው ቤትም በሌላ ክርክር ታግዶ የነበረ መሆኑን በመዘርዘር ጨረታው እንዲሰረዝለት መጠየቁን ያስገነዝባሉ፡፡

እንደሚታወቀው የፍትሐ ብሔር ክርክሮች መቋጫ እንዲኖራቸው በማሰብ በሕግ ከተደነገጉ ስርዓቶች መካከል ፍርድ ወይም ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ ወይም ለቀረበው ነገር መጨረሻ ውጤት የሚያስከትል ትዕዛዝ በተሰጠበት ነገር ላይ በድጋሚ ክስ ወይም አቤቱታ እንዳይቀርብ መከልከል እንደሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ይደነግጋል፡፡ አንድ ክስ ወይም በተጀመረ ክርክር ላይ የቀረበው አቤቱታ በድጋሚ የቀረበ ነው ከሚያስብሉ መመዘኛዎች መካከል አንዱ ደግሞ አስቀድሞ ውሣኔ ወይም የመጨረሻ ውጤት የሚያስከትል ትዕዛዝ የተሰጠበት አቤቱታ ስረ-ነገርና በድጋሚ የቀረበው ነገር ጭብጥ ተመሣሣይ መሆን አለመሆኑን መሰረት የሚያደርግ ነው፡፡

በዚህ መርህ መሰረት የቀረበውን ጉዳይ ስንመረምረው የአሁን አመልካች የካቲት 15 ቀን 2013ዓ/ም ያቀረበው አቤቱታ ዋናውን እዳውንና ቤቱን ለመሸጥ የወጣውን ወጪ ለመክፈል የሚፈልግ መሆኑን በመግለፅ የጨረታውሂደት እንዲቋረጥ እንዲታዘዝለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 439 የቀረበ አቤቱታ ሲሆን ይህን አቤቱታ መሰረት በማድረግ የሚመረመረው ጉዳይ የአመልካቹ ቤት ሳይሸጥ እዳውን ለመክፍል የሚችል መሆኑን አለመሆኑ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የካቲት 23 ቀን 2013ዓ/ም አመልካች ያቀረበው አቤቱታ በአፈፃፀም ክርክሩና በቤቱ ሽያጭ ጨረታ ላይ በተጠሪዎች ተፈፅመዋል የሚላቸውን ቅን ልቦናን መሰረት ያላደረጉ እና ሕገወጥ ድርጊቶች በመዘርዘር ጨረታው እንዲሰረዝለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 430(1)(3) ድንጋጌን መሰረት ያደረጉ ሲሆን በፍርድ ቤቱ ሊጣራ የሚችለውም ጉዳይ  ጉድለቶች መኖር አለመኖራቸውና ነበሩ ከተባለም በጨረታው መሰረዝ ላይ የሚያስከትሉት ውጤትን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ሂደትም ተጠሪዎችና የጨረታው አሸኛፊ ነው የተባለው ሰው ተሣታፊ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለቱ ቀናት የቀረቡት አቤቱታዎች የተለያዩ ፍሬ ነገሮችን መሰረት ያደረጉ የሚያስከትሉት ውጤትም ለየቅል መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች የካቲት 23 ቀን 2013ዓ/ም ያቀረበውን አቤቱታ ተቀብሎ ተጠሪዎችና የጨረታው አሸኛፊ የተባለው ሰው መልስ እንዲያቀርቡ አድርጎ ጨረታው መሰረዝ አለመሰረዝ ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው ጉዳዩን በአግባቡ ሣይመርምር አቤቱታው በድጋሚ የቀረበ ነው፤ ጨረታው የሚሰረዝበት ምክንያት የለም ሲል ውድቅ ማድረጉ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 205344 ሚያዚያ 5 ቀን 2013ዓ/ም እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ ቅላይ  ፍርድ  ቤት  በመዝገብ  ቁጥር 51165 መጋቢት 21 ቀን 2013 ዓ/ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በመዝገብ ቁጥር 51165 መጋቢት 21 ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የተሻረ መሆኑን አውቆ በአመልካች አቤቱታ ላይ ተጠሪዎችና የጨረታው አሸናፊ ነው የተባለው ሰው መልስ እንዲሰጡ አድርጎ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢ ነው ያለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341 መሰረት መልሰንለታል፡፡
3) ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ በሚመለከት ግራ ቀኙ የዬራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

1) ይህ ችሎት ሐምሌ 14ቀን 2013 ዓ/ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
2) መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 215049

ታህሳስ 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ማርታ ዴሬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኢያሱ ፀጋዬ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 9 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.36077 ሀምሌ 15 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በወላይታ ሶዶ ከተማ መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ የአፈፃፀም ተከሳሽ ነበር፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ተጠሪ የአመልካችን ይዞታ ከፊት ለፊት 0.10 ሜ እና ከኋላ 0.70 ሜ እንዲለቅ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን በዚሁ ውሳኔ መሰረት እንዲፈፀምልኝ በማለት ለወላይታ ሶዶ ከተማ መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት አመልክተዋል፡፡ፍርድ ቤቱም አመልካች በውሳኔው መሰረት ይፈፀምልኝ ስትል ያቀረበችው ለማዘጋጃ ቤት እንዲያስፈፅም በተከታታይ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በውሳኔው መሰረት ለመፈፀም የአሁን አመልካች ሳይት ፕላኑን ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነችም በማለት በቁጥር 268/09/2013 በቀን 13/05/2013 ዓ.ም በተፃፈው መግለጫ የገለፁ ሲሆን ዳግም በተሰጠው ትዕዛዝ በቁጥር 400/26/13 በቀን 25/05/13 ዓ.ም በተፃፈው መግለጫ ከፍርድ ቤት ባለሞያ ጋር ለመስራት በጠየቁት መሰረት ከፍርድ ቤቱ ዳኛ ጋር እስከ ቦታው ድረስ በመሄድ ከማዘጋጃ ቤት ባለሞያ ጋር አፈፃፀሙን ለማስፈፀም በሄድንበት የአሁን ተጠሪ ትርፍ ይዞታ ከያዘ ለማስለቀቅ ሲለካ ከዚህ በፊትም ሆነ አሁንም የአሁን ተጠሪ ወደ አመልካች ይዞታ አልፎ ይዟል የተባለው ከፊት

ለፊት 0.10 ሜትር በጎን በኩል ወጣ ገባ አጥር ያለውን ተጠሪ እንዲያነሳ ተብሎ አንስቷል፡፡ወጣ ገባ አጥር የፍልጥ እንጨት ለቅቆ ገብቷል፡፡አሁን በድጋሚ እንዲያስለቅቀው በውሳኔው መሰረት ይፈጸም በሚል የቀረበው ለማስፈፀም በሄድንበት ተጠሪ በጎን በኩል በስተምስራቅ በኩል የተጠሪ ይዞታው ወደ አመልካች ገብቶ ያለ ስለሆነ ማዘጋጃ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ መግለጫ እንዲሰጥ ታዞ በቁጥር 351/9/13 በቀን 22/07/2013 ዓ.ም በሰጡት መግለጫ ክርክሩ ባለበት በስተምስራቅና በስተምዕራብ በኩል የተጠሪ ይዞታ በሳይት ፕላን 13.50 ሲሆን በመሬት ላይ ያለው ግን 13.40 በመሆኑ አጠቃላይ ካሬ ሜትር 499.50 ካ.ሜ ሆኖ በመሬት ላይ ያለው 442.43 ካ.ሜ ነው፡፡ የአመልካች ቁመትና ስፋት የሚያስረዳ ባይሆንም በሳይት ፕላን ላይ 279 ካ.ሜ ሲሆን በመሬት ላይ ሲለካ 244 ካ.ሜ እንደሆነ አረጋግጠው የሰጡት መግለጫ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ እዚህ ላይ ለማስፈፀም ተጠሪ ቤቱን አልፎ ወደ አመልካች ይዞታ ገብቶ የሰራበት የለም፤ሲለካ የተጠሪ ይዞታ ወደ አመልካች ይዞታ ነው የሚገባው ስለዚህ ከዚህ በፊት በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ በመዝገብ ቁጥር.39060 በቀን 04/04/2010 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ከፊት ለፊት 0.10 ሜ ከኋላ በኩል ያሉት ወጣ ገባ አጥሮች ተነስተው ይዞታው ለአመልካች የተሰጠ ስለሆነ አሁን በጎን በኩል 0.70 ሜ ተጠሪ አልፎ የያዘው ባለመኖሩ የግራ ቀኙ ይዞታቸው በሳይት ፕላኑ ላይ ካለው መሬት ላይ ያለው ሲለካ የሚያንስ በመሆኑ ተጠሪ አልፎ የያዘው ይዞታ ስለሌለ የሚፈፀም ውሳኔ የለም፤ በውሳኔው መሰረት ከዚህ በፊት ወርደን የፈፀምን ስለሆነ አሁን የሚፈፀም ውሳኔ የለም በማለት ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች የወላይታ ሶዶ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ፈጽመዋል በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ሰበር ሰሚው ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ውሳኔውን በሙሉ ድምጽ አጽንቷል፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ፡- በአመልካች እና በተጠሪ መካካል በስር ፍርድ ቤት ስንከራከር ቆይተን በዋና ክርክር የተወሰነልኝ በአፈፃፀም እንዲፈፀም በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.378፣ 386፣ 389 በሚያዘው መሰረት በወረዳው ፍርድ ቤት ላይ እንዲፈጽሙልኝ ባቀርብም በውሳኔው መሰረት ያልፈፀሙልኝ ስለሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.28187 በቀን 06/06/2011 ዓ.ም የይግባኝ ቅሬታ አቅርቤላቸው ቀደም ሲል በፍሬ ጉዳይ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ከፊት ለፊት 0.10 ሜ እና ከኋላ 0.70 ሜ አልፎ የያዘውን ለቆ እንዲወጣ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት በአፈፃፀም ይዞታውን ለአመልካች ያስረክብ ብሎ ወስኖልኛል፡፡ በዋና ውሳኔ መሰረት ያልፈፀሙልኝ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በፍርዱ መሰረት እንዲፈፀምልኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች የሚፈፀም ፍርድ የለም በማለት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ዋናውን ፍርድ በተገቢው ያገናዘበ መሆን አለመሆኑ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል

ከተባለ በኋላ ተጠሪ የሰጡት መልስ በአጭሩ፡- በዚህ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.69471 በቅጽ 13 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዋናውን ውሳኔ የወሰነው በዓይን እይታ ሲሆን አፈፃፀም የሚፈጽመው ፍርድ ቤት ወርዶ መሬት ላይ ለክቶ በማየት ሊሆን ይገባል፤ ተጠሪ ከክፍሉ ማዘጋጃ ቤት ሳይት ፕላን ያወጣሁት በ1998 ዓ.ም ሲሆን አመልካች በ2008 ከአስር ዓመት በኋላ አውጥታለች ይህም ቢሆን የአመልካች ሳይት ፕላን ወሰኑን/ድንበሩን/ ከላይም ሆኖ ከታች የማይገልጽ መሆኑን አረጋግጦ የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ በአግባቡ ስለሆነ የአመልካችን አቤቱታው ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡አፈፃፀም ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነውን መሰረታዊ ፍርድ/ውሳኔ የሚከተል በመሆኑ አፈፃፀሙን የሚመራው ፍርድ ቤት ፍርዱን የሚያስፈፅመው በስነ ስርዐት ህጉ በተዘረጋው ስርዐት መሰረት እንደ ፍርዱ ይዘትና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ ሲሆን በዚህ አግባብም ለአፈፃፀም መነሻ የሆነን ፍርድ በይግባኝ ያላሻረ ወይም እንዲሻሻል ያላደረገ ተከራካሪ ወገን በዋናው ጉዳይ ላይ ሊነሱ የሚገባቸውን የክርክር ነጥቦች በአፈፃፀም በተያዘው መዝገብ ላይ የክርክሩ መሰረት ሊያደርጋቸው የማይችል መሆኑን ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.372፣378፣392(1) ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ለመገንዘብ የሚቻል ሲሆን የማይንቀሳቀስ ንብረት ርክክብን አስመልክቶም እንደ ፍርዱ የሚፈፀመው በውሳኔው ላይ የተመለከተውን ንብረት ባለገንዘቡ ራሱ ወይም ወኪሉ እንዲረከብ በማድረግ ለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.402(1) በግልፅ ተመልክቷል፡፡

በግራ ቀኙ መሃል ሲካሄድ የነበረው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ተጠሪ ወደ አመልካች ይዞታ በመግባት የያዙት ይዞታ አለመኖሩን በመግለፅ ቢከራከሩም በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.39060 ታህሳስ 09 ቀን 2010 ዓም በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ተጠሪ ከአመልካች ይዞታ ፊት ለፊት 0.10 ሜትር እና ከኋላ በኩል 0.70 ሜትር ወደ አመልካች ይዞታ አልፈው መገኘታቸው እንዲሁም ይዞታቸው አራት ማዕዘን ቢሆንም አጥሩን ወጣ ገባ አድርገው ማጠራቸው ተረጋግጦ ይኸው ሁከት እንዲወገድ መወሰኑ፤ይህ ውሳኔም በይግባኝ ያልተሻረ የመጨረሻ ውሳኔ መሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ ነው፡፡በዚህ ውሳኔ አግባብም ከፊት ለፊት 0.10 ሜትር በጎን በኩል ወጣ ገባ ያለውን አጥር ተጠሪ እንዲያነሱ በማድረግ በፍርዱ መሰረት መፈፀሙን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው ተጠሪ ከአመልካች ይዞታ ከኋላ በኩል 0.70 ሜትር ወደ አመልካች ይዞታ አልፈው መያዛቸው ተረጋግጦ ይኸው ሁከት እንዲወገድ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ሲሆን ከላይ እንደተመለከተው ይህ የውሳኔ ክፍል በቦታው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስ

ተጠሪ ውሳኔው እንዲሻር ያደረጉ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ካለመኖሩም በላይ የቀረበም ማስረጃ የለም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ በፍርዱ አግባብ ሊፈፀም ሲገባ የሶዶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ የአፈፃፀም ጉዳዩ ሲቀርብለት ግራ ቀኙ በማያገባቸው የመንግስት ይዞታ ልኬት ተደርጎ የቀረበ በመሆኑ በመንግስት ይዞታ ላይ አልፎ ይዟል አልያዘም ብሎን ማስላቱ አስፈላጊ አይደለም በፍርዱ መሰረት ለመፈፀም አለመፍቀዱና የአፈፃፀሙ ጉዳይ በመጨረሻ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ውሳኔው ተሽሮ በፍርዱ አግባብ እንዲያስፈፅም ሲታዘዝም "…ተከሳሽ በአካል የያዙት በሳይት ፕላኑ ላይ ከተመለከተው ያነሰ መሆኑን መነሻ በማድረግ ፤ተከሳሽ ቤቱን አልፎ ወደ ከሳሽ ይዞታ ገብቶ የሰራበት የለም ሲለካ የተከሳሽ ይዞታ ወደ ከሳሽ ይዞታ ነው የሚገባው…" የሚል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ምክንያት በማስቀመጥ በፍርዱ መሰረት አለማስፈፀሙና ይህ የአፈፃፀም ትዕዛዝ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የወላይታ ሶዶ ከተማ መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 18636 ቀን 06/08/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝና ይህንን ትዕዛዝ በማፅናት የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 50777 በቀን 23/09/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 36077 ሐምሌ 15 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የወላይታ ሶዶ ከተማ መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም መዝገቡን በማንቀሳቀስ በመ/ቁ.39060 ታህሳስ 09 ቀን 2010 ዓም በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ አግባብ ተጠሪ ከአመልካች ይዞታ ከኋላ በኩል 0.70 ሜትር ወደ አመልካች ይዞታ አልፈው የያዙትን በማስለቀቅ እንዲያስረክብ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

   ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 174573

ቀን - ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሲቲና ኢብራሂም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መህቡባ አወል -

2. አቶ ከድር ገሜቦ - } አልቀረቡም

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ክርክር አድርገው ከውሳኔ በኂላ አፈጻጸም ላይ እያለ 1ኛ ተጠሪ ቀርበው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ 21 ዓመት ስንኖር በጋራ ያፈራናቸውን በካርታ ቁጥር 189 እና በካርታ ቁጥር 1622/85 የተመዘገቡት ቤቶች ላይ አመልካች ያላፈሯቸው እና መብት የሌላቸው በመሆኑ ንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ መብት ስላለኝ የአፈጻጸም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተቃውሞ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት መልስ የ2ኛ ተጠሪ ሚስት እና የንብረት ባለድርሻ መሆናቸውን ገልጸው 1ኛ ተጠሪም ከንብረቱ ድርሻቸውን መካፈል ይችላሉ ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም በበኩላቸው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ባለቤቶቼ ስለሆኑ ንብረቱን ለሦስት ክፍፍል ሊደረግበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንብረቱን 1ኛ ተጠሪን ጨምሮ ሁሉም ለሦስት እንዲካፈሉት ወስኗል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለጌዲኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው አከራክሮ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን አከራክሮ 1ኛ ተጠሪ የሚከራከሩት፤ ንብረቱ የተፈራው 2ኛ ተጠሪ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት በመሆኑ አመልካች በንብረቱ ላይ መብት የላቸውም በማለት ስለሆነ ጉዳዩን ሳያጣራ መወሰኑ ስህተት ነው በማለት ውሳኔውን በመሻር የግራቀኙ ማስረጃ ተሰምቶ እንዲወሰን ጉዳዩን መልሷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ጉዳዩ ተወስኖ ያለቀ ነው፡፡ የእኔ እና የልጆቼ መብት ላይ

ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ ንብረቱ ተሽጦ ልንከፋፈል ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት 1ኛ ተጠሪ መብታቸውን ማስከበር የሚችሉት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ወይስ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ነው? ጉዳዩ ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ መሆን አለመሆኑ እና የክልሉ ሰበር ችሎት ጉዳዩን መመለሱ ህጋዊነቱን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ባቀረብኩት ክርክር መሠረት ጉዳዩ በማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ ተገቢ ስለሆነ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ መልስ ላይ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የተቃውሞ ማመልከቻ ክርክር የተመራበት ሥርዓት ሕጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ክርክር አድርገው ከውሳኔ በኋላ አፈጻጸም ደረጃ ላይ እያለ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የተቃውሞ ማመልከቻ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ 21 ዓመት ስንኖር በጋራ ያፈራናቸውን በካርታ ቁጥር 189 እና በካርታ ቁጥር 1622/85 የተመዘገቡት ቤቶች ላይ አመልካች ያላፈሯቸው እና መብት የሌላቸው በመሆኑ ንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ መብት ስላለኝ የአፈጻጸም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ ተቃውሞ የቀረበበት ንብረት ፍርድ ያረፈበት መሆኑ እና ቤቶቹ ላይ አመልካች መብት የላቸውም የሚለው የማመልከቻው ይዘት ጉዳዩ የቀረበው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ዋናው ፍርድ መብቴን ይነካል በሚል እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ የአመልካች የአፈጻጸም ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ማለታቸው እና የሥር ዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪን የአፈጻጸም ከሳሽ እና የአፈጻጸም ተከሳሽ በማለት መሠየሙ ተቃውሞ የቀረበው የአፈጻጸም ክርክሩ ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት እንደሆነ ግምት የሚያስወስድ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የመቃወሚያ ማመልከቻ የቀረበበት ምክንያት ዋናው ፍርድ ላይ ነው ወይስ አፈጻጸሙ ላይ የሚለው ጉዳይ አከራካሪ ያደረገው የማመልከቻው አቀራረብ ጉድለት እና የስር ፍርድ ቤት የአፈጻጸሙን ክርክር ዋናው ፍርድ በተሠጠበት መዝገብ በመምራቱ ነው፡፡

የአፈጻጸም ክርክሩ ጉዳዩ በሥረ-ነገሩ በተያዘበት መዝገብ በሚመራበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ የመቃወም ማመልከቻ ማቅረብ የሚፈልጉ ሠዎችን መብት እንዳይነካ ወይም ለተቃውሞው መልስና ክርክር ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ተከራካሪዎች መሠረታዊ የሆነው የመደመጥ መብታቸው እንዳይታለፍ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን

እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡

ተቃውሞ የቀረበው በሥረ-ነገሩ በተሠጠው ፍርድ ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ነው ወይሥ ለፍርድ አፈጻጸሙ በተከበረው ንብረት ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ነው የሚለውን በመለየት ተቃውሞው የቀረበበትን ምክንያት የሚጠይቀውን የክርክር ሂደት መከተል ያስፈልጋል፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት የተቃውሞ ማመልከቻ በቀረበ ጊዜ ተቃውሞ የቀረበበት ንብረት ላይ ተቃዋሚው መብቱን ካሳየ ፍርድ ቤቱ እንደ በቂ ምክንያት በመቁጠር የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ሊሠጥ እንደሚችል ተመለክቷል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት የሚቀርብ ክርክር ጉዳዩ በሥረ-ነገሩ በመጀመሪያ ደረጃ እንደሚታይ የክስ ዳኝነት ሙሉ የክርክር ሥርዓትን የሚከተል ሂደት አይደለም፡፡ ተቃዋሚው በአፈጻጸም የተያዘው ሆነ የተከበረው ንብረት የእርሱ ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበ በቂ ምክንያት አለው ተብሎ ንብረቱ ከክርክሩ ውጭ የማድረግ ዓላማ ያለው እንጂ በተከበረው ንብረት ላይ የባለቤትነት ክርክር ለማድረግ እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ የሚሠጥበት ሥርዓት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የመቃወም ማመልከቻው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በጉዳዩ ሥረ-ነገር ላይ የተሠጠው ውሳኔ መብቴን ነክቷል በማለት ፍርድ ባረፈበት ንብረት ላይ በቀረበ ጊዜ ተቃዋሚው ክርክር ባስነሳው ጉዳይ ላይ የሚያገባው እና ቀድሞም ተከራካሪ መሆን የሚገባው ከነበረ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(1)(2) እንደተመለከተው በማመልከቻው ላይ ሌሎች ተከራካሪዎች መልስ የሚሠጡበት እና ጉዳዩ ላይ እንደገና ሙሉ ክርክር የሚደረግበት ሂደትን የሚከተል ሥርዓት ነው፡፡ ውጤቱም ቀድሞ የተሠጠውን ፍርድ መለወጥ ወይም ማሻሻል ድረስ ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የመቃወም ማመልከቻ ይዘቱ በሥረ-ነገሩ የተሠጠውን ፍርድ የሚመለከት እና ፍርዱ የጋራ ንብረት መብቴን ነክቷል የሚል ነው፡፡ ይህም ማመልከቻው የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት አድርጎ የሚመራ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በመቃወም ማመልከቻው ላይ አመልካች እና ተጠሪ መልስ አቅርበውበት እንደገና ሙሉ ክርክር ሊደረግበት የሚገባ ነው፡፡ በክርክር አመራሩ የግራቀኙ ተከራካሪዎች የመደመጥ መብት መከበሩን ማረጋገጥ እና ሁሉም ክርክር እና ማስረጃ የማቅረብ መብታቸው ተግባራዊ መሆኑን መቆጣጠር የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡

በሥር ፍርድ ቤት ለመቃወም ማመልከቻው መልስ ያቀረቡት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ክርክሩን እንደገና ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ተገንዝበው በዚሁ አግባብ መልስ እና ጉዳዩን ለመከላከል የሚያስችል ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

ከዚህ አኳያ የአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የመከላከል መብታቸው እስከተከበረ ድረስ፣ የ1ኛ ተጠሪ ተቃውሞ የቀረበው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት መሆኑን ተገንዝቦ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔው 1ኛ ተጠሪ የሚከራከሩት፣ ንብረቱ የተፈራው 2ኛ ተጠሪ

አመልካችን ከማግባታቸው በፊት በመሆኑ አመልካች በንብረቱ ላይ መብት የላቸውም በማለት ስለሆነ ክርክሩ በግራቀኙ ማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን መመለሱ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 73880 ጥር 21 ቀን 2011 ዓ/ም፤ የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13802 መስከረም 15 ቀን 2010 ዓ/ም እና የዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05445 ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ/ም የሠጡትን ውሳኔ በመሻር የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

2. ሠኔ 20 ቀን 2011 ዓ/ም በዚህ ችሎት የተሠጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

3. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# የወንጀል ህግ

የሰ.መ.ቁ.203746

መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- ታሪኩ ኬዶ ኬሪ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍርድ</u>**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካችና በዚህ መዝገብ ያልቀረቡ ሌሎች 9 ተከሣሾችን ጨምሮ ያቀረበው የእርስ በእርስ ጦርነት የማነሳሳት ወንጀል የአሁን አመልካች በተከሰሰበት 5 ክሶች እንዲከላከል ብይን ሰጥቶ ክስና ማስረጃውን አልተከላከልክም ተብሎ ጥፋተኛ ተደርጐ በ16 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑ እና በይግባኝም ውሣኔው ያለመታረሙ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ላይው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን 9ኛ ተከሣሽ በማድረግ፣ ሌሎች 9 ተከሣሾችን ጨምሮ በአጠቃላይ 6 ክሶች የቀረቡባቸው ሲሆን፣ አመልካች ግን 6ኛ ክስ ላይ አልተጠቀሰም፡፡

ዐቃቤ ሕግ አቅርቦት የነበረው ክስ በአጭሩ፡-

1ኛ ክስ በሁሉም ተከሣሾች ላይ ሆኖ የወ/ሕ/አ/35/32 (1)(ሀ) 240/3 ስር የተደነገገውን ተላልፈው የእርስ በእርስ ጦርነት ለማነሳሳት ካልታወቁ ቡድኖች ሀሳብ በመቀበል መስከረም 6/2011 ዓ.ም. በግምት ከምሽቱ 12፡45 ሰዓት ሲሆን በወረዳ 01 ሴቂ ማርያም ሞሪንታ ሰፈር ተብሎ የሚጠራው ሰፈር የጋሞ ብሔር ተወላጅ የሆኑ ድንጋይ፣ ዱላ፣ገጀራ፣ አካፋ እና የተለያየ ስለት ያላቸው መሳሪያዎች በመያዝ “ጋሞን ማን ነካ” እና የኦሮሞን ቤት እየለዩ ንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ እየፎከሩ የኦሮሞ ተወላጆች እኛን ገድለው እንዴት ይኖራሉ እያሉ የኦሮሞ ተወላጅ የሆነውን ሰው በያዙት ዱላና ድንጋይ

ቀጥቅጠው በመግደል በፈፀሙት በተሳሳተ እንቅስቃሴ ውስጥ በራሳቸው ፍቃድ ተካፋይ በመሆን የእርስ በእርስ ጦርነት በማስነሳት ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

2ኛ ክስ በሁሉም ተከሣሾች ላይ፣- የወ/ሕ/አ/35፣ 32/1/ሀ/539/1/ሀ ተላልፈው ሰውን ለመግደል አስበው መስከረም 6 ቀን 2011 ዓ.ም. በግምት ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ሲሆን በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 01 ልዩ ቦታው ሱቂ ማርያም ተብሎ በሚጠራው ሰፈር የኦሮሞ ተወላጆች እኛን ገድለው እንዴት ይኖራሉ እያሉ በጤፍ ማሳ ውስጥ ያለውን ዳኜ ፈየራ በያዙት ዱላና ድንጋይ ቀጥቅጠው የገደሉት በመሆኑ በፈፀሙበት ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

3ኛ ክስ በሁሉም ተከሣሾች ላይ፡- የወ/ሕ/አ/35፣32/1/ሀ እና 690/3/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሣሾች በሰው ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም. በግምት 12 ሰዓት በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ ወ/01 የአቶ ብሩ ኢዶ ንብረት የሆነ የተለያዩ ንብረቶች ጠቅላላ ግምታቸው 112,800.00 ብር፣ የአቶ ተሾመ መንገሻ ንብረት የሆነውን ኮድ 2-73289 አ.አ. ቪታራ መኪና ግምቱ ብር 300ሺ፣ የወ/ሮ ብርቂ ገብሬ የሆነውን ንብረት ጠቅላላ ግምቱ ብር 8,000.00 ብር፣ የአቶ ወርቁ ኢዶ ንብረት ጠቅላላ ግምቱ ብር 425,000.00 በሆኑት ንብረቶች ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

4ኛ ክስ በሁሉም ተከሣሾች ላይ፡- የወ/ሕ/አ/ 35፣32/1/ሀ/ 555/ሀ/ ተላልፈው በ1ኛ ክስ በተጠቀሰው ጊዜ እና ቦታ አቶ እስራኤል ተመስገን የተባለውን በያዙት ድንጋይና ዱላ ደብድበውት ሲወድቅ ጥለውት የሄዱ በመሆናቸው ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

5ኛ ክስ በሁሉም ተከሣሾች ላይ፡- የወ/ሕ/አ/35፣32/1/ሀ/ 555/ሀ/ ተላልፈው ወ/ሪት ባንቱ ድናግዴን በያዙት ድንጋይና ዱላ ወርውረው በተለያየ የሰውነት አካሏ ላይ ሲመቷት ስትወድቅ ጥለዋት በመሄዳቸው በፈፀሙት የሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሰዋል በሚል ክስ አቅርቧል፡፡ 6ኛ ክስ አመልካችን የሚመለከት ባለመሆኑ መመዝገብ አላስፈለገም፡፡

አመልካች ክሱን ክዶ በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን የሰማ ሲሆን የዐቃቤ ሕግ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ፣6ኛ፣8ኛ፣9ኛ እና 10ኛ ምስክሮች በአመልካች ላይ ያስረዱት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን 3ኛ፣7ኛ ምስክሮች በአመልካች ላይ የሰጡት ምስክርነት፡- 3ኛ ምስክር አመልካች ገጀራና ድንጋይ ይዘው ከሚያልፉ መሀል እሱም የነበረ መሆኑን፣ ዳኜ ፈይራ የተባለው ሰው ተገድሎ መገኘቱን ማን እንደገደለው ግን እንደማያውቅ፣ አመልካች ንብረት ማውደሙን እና ወደ ተጠለሉ ሰዎች እየመራ የወሰደ መሆኑን መስክሯል፡፡ 7ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር በበኩሉ የአሁን አመልካችን በችሎት ለይቶ ማሳየቱን፣ በጊዜው የኦሮሞ ልጆችን ሲያሯሩጥ የነበረ መሆኑን ማሳ ውስጥም ሰው ሞቶ መገኘቱን እና በተጠለሉ ሰዎች ላይም ጉዳት የደረሰ መሆኑን አውቃለሁ ሲል መስክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የቀረበውን ክስ እና ማስረጃን መርምሮ **በ1ኛ** ክስን አስመልክቶ የቀረበው ማስረጃ የእርስ በእርስ ጦርነት ድርጊትን ሊገልጽ የሚችል አይደለም በሚል የቀረበውን ክስ ወደ **አምባጓሮ ወይም በጠብ**

**ተካፋይ** ሆኖ መገኘትን የሚያሳይ ነው በማለት ድንጋጌውን ወደ 577/3/ በመቀየር አመልካችን ጨምሮ 1፣2፣5፣7፣10ኛ ተከሣሾች እንዲከላከሉ፣ **በ2ኛ** ክስ አመልካችን ጨምሮ 2ኛ፣5ኛ፣7፣8ኛ፣ እና 10ኛ የስር ተከሣሾች **በ539/1/ሀ/ ስር** እንዲከላከሉ፣**3ኛ** ክስን አስመልክቶ በድርጊቱ ሰው ያልሞተ መሆኑ ስለተረጋገጠ በሚል የቀረበውን ድንጋጌ ወደ **690/1/ለ/** በመቀየር አመልካችን ጨምሮ 1ኛ፣2ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 10ኛ የስር ተከሣሾች እንዲከላከሉ፣**4ኛ** ክስን አስመልክቶም ድንጋጌውን በመቀየር በ556/2/ሀ ስር አመልካችን ጨመሮ 1ኛ፣2ኛ፣5ኛ፣8ኛ እና 10ኛ የስር ተከሣሾች እንዲከላከሉ፣ 5ኛ ክስንም እንዲሁ ወደ 556/2/ሀ በመቀየር አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ተከሣሾች እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል። ከዚህ ውጪ ያሉ የስር ተከሣሾችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው ከቀረበባቸው ክስ በነፃ አሰናብቷል።

በዚሁ መሠረት አመልካች የመከላከያ ማስረጃውን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ክስና ማስረጃውን አልተከላከለም በሚል እንዲከላከል ብይን በተሰጠበት የህግ ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ ነው ሲል የጥፋተኝነት ውሣኔ በመስጠት ቅጣቱን አስልቶ በ16/ አስራ ስድስት ዓመት/ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል።

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ነው።

አመልካች መጋቢት 1 ቀን 2013 ዓ.ም. በጠበቃው አማካይነት የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ ይዘቱም በአጭሩ፡- አመልካች በተከሰሰባቸው የወንጀል አይነቶች ላይ የወ/ሕ/አ/35 ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ያለመሆኑን፣ በአመልካች ላይ በተጠቀሰው ከባድ ወንጀል ቅጣቱም እድሜ ልክ ወይም ሞት በሚያስቀጣ ላይ በህብረቱ ውስጥ ተገኝተሀል በሚል ምክንያት ብቻ አመልካች ምን እንዳደረገ ተለይቶ ባልተከሰሰበት እና ባልተመሰከረበት ጥፋተኛ ተደርጉ ቅጣት መጣሉ፣ ዳኜ ፈየራ የተባለው ሰው በተገደለበት በ6/1/2011 ዓ.ም. አመልካች በቦታው የነበረ ስለመሆኑ ባልተመሰከረበት፣ የዐቃቤ ሕግ 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ፣ ምስክሮች አመልካች ከላይ በተጠቀሰው ቀን እንደሌለ መስክረው ባለበት፣ 5ኛ፣7ኛ፣8ኛ፣10ኛ ምስክሮችም በአመልካች ላይ የመሰከሩት ነገር በሌለበት፣ በ3ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክርም ላይ ከአመልካች ጋር ጠበኛ በመሆኑ እንዳይመሰክር አመልክተን እያለ ጥፋተኛ መደረጉ፣ ተመስክሮበታል እንኳን ቢባል በወ/ሕ/አ/540 መሆን ሲገባው በ2ኛ ክስ 539/1/ሀ ጥፋተኛ ተደርጐ መቀጣቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሆኑን ስለሚያሳይ ስህተቱ እንዲታረምልኝ ሲል ጠይቋል።

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች በወ/ሕ/አ/ 35/32/1/ሀ እና 577/3/፣539/2/ሀ፣690/1/ለ/ እና 556/2/ሀ/ን ተላልፎ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በስር ፍ/ቤት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ

የተወሰነበትን አግባብነት ከተጠቀሰው ድንጋጌና ከወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/ አንፃር ለመመርመር መዝገቡ ለችሎቱ እንዲቀርብ በመታዘዙ ሊቀርብ ችሏል፡፡

ለተጠሪ መጥሪያ እንዲደርሰው ተደርጐም በ22/11/2013 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- እንደ አድማና አምባጓሮ የመሳሰሉ ወንጀሎች በአንቀጽ 35 2ኛ ሃሣብ አገላለጽ ከዐ/ሕግ የሚጠበቀው በህብረቱ ውስጥ ተከሣሽ መገኘቱን እንጂ ወንጀል አለመፈፀሙን የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሣሽ የሚዞር መሆኑን፣ ያቀረብነውን ክስ ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ ያስረዳን በመሆኑ፣ ዳኜ ፈየራ የተባለው ሰው ግድያ ላይ አመልካች ከሌሎች ጋር አብሮ ስለመኖሩ በምስክር ያረጋገጥን መሆኑን፣ 3ኛ፣4ኛ እና 7ኛ ምስክሮች የኦሮሞ ወጣቶችን አመልካች ከሌሎች ጋር በመሆን እያባረረ ወደ በቀለ ኢዶ የጤፍ ማሳ የወሰዱ መሆኑ፣ ማሳ ውስጥም ዳኘ ፈየራ ሞቶ መገኘቱ መመስከሩን፣ የወ/ሕ/አ/539/1/ሀ ወደ 540 ይቀየርልኝ ያለውንም አስመልክቶ አመልካች ከሌሎች ጋር በመስማማት ድርጊቱ የፈፀመ በመሆኑ ድንጋጌውን የሚያቋቁም ከሆነው አንዱ የተሟላ በመሆኑ ሊቀየር የሚገባው አለመሆኑን፣ በማንሳት የስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ ተገቢ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ ብሏል፡፡

የአመልካች ጠበቃም የቀደመው የሰበር አቤቱታን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚሁ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭር በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልስ በስር ፍ/ቤቶች ከተሰጠው ውሣኔ እና አጠቃላይ ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የክርክሩ ሂደት የሚያሳየው በአመልካች ላይ ዐቃቤ ህግ 5 ክሶችን ጠቅሶ ከሌሎች ተከሣሾች ጋር ወንጀል ፈጽሟል ሲል ክስ የመሰረተበት መሆኑን፣ የተጠቀሱት ክሶችም 240/3፣ ለጦርነት የማነሳሳት ወንጀል፣539/1/ሀ/ ከባድ የሰው ግድያ፣690 በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣555/ለ/ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽሟል ሲል ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካች ክሱን ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ምስክሮች ተሰምተው ለጦርነት የማነሳሳት ወንጀሉ ድንጋጌን እና በአካል ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ድንጋጌን ወደ አምባጓሮ እና ቀላል አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል በመቀየር ሌሎቹ ክሶች በነበሩበት ሁኔታ አመልካች እንዲከላከል ፍ/ቤቱ ብይን የሰጠ በመሆኑ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ በማድረግ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

በአጣሪ ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ዐቃቤ ሕግ እንዳቀረበው ክስ በማስረጃ ስለማስረዳት አለማስረዳቱና አስረድቷል ከተባለም አመልካች ክሱና ማስረጃውን ተከላክሏል ወይንስ አልተከላከለም የሚለውን እና ተጠቅሰው የቀረቡት

ድንጋጌዎች በተደራራቢ ክስ የመቅረባቸውን አግባብነት ከወ/ሕ/አ/23/2//35 ፣60፣61 እና 141፣577/3/፣ 690 ድንጋጌዎች ጋር ሲመረመር የሚባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የወ/ሕ/አ/23/2/ በግልጽ የሚደነግገው፡- "አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡" በሚል ነው፡፡

ከወንጀል ጉዳዮች የክስ ሂደት ጋር በተገናኘ ዓቃቤ ሕግ ሊያከናውናቸው ከሚገቡ ተግባራትና ኃላፊነቶች ዋናው የተከሰሰን ሰው የወንጀል ድርጊቱን በቀረበው ክስ አይነት ስለመፈፀሙ በበቂና አሳማኝ ማስረጃ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት ያለበት ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 141 እና 142/1/ ድንጋጌ መረዳት እንችላለን፡፡

የወ/ሕ/አ/577/3/ ፡- " በአምባጓሮ ወቅት ከነበረው ሁኔታ የተነሳ በተለይም በጠበኞች መካከል በነበረው ቂም፣የጠብ ማጫር ወይም የስካር ሁኔታ ወይም የጦር መሣሪያዎችን፣ ድንጋዩችን ወይም ማቁሰል ወይም መግደል የሚችሉ ሌሎች ነገሮችን የያዙ ወይም እነዚሁ ነገሮች የተሰጧቸው በመሆኑ በጠቡ መካከል ሰው የቆሰለ ወይም የተገደለ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ከፍተኛው መደበ ቅጣት ሊደርስ ይችላል፡፡" በሚል ይደነግጋል፡፡

በመሰረቱ ተደራራቢ ወንጀሎች በአጠቃላይ በአንድ ጊዜ (ሀሳባዊ መደራረብ) ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ጊዜያት የተፈፀሙ ድርጊቶችን (ቁሳዊ መደራረብ) የሚመለከቱ ሲሆኑ መደጋገም የቁሳዊ መደራረብ መለያ ባህሪ በመሆኑ ተመሳሳይ ድርጊቶች በተለያዩ ጊዜያት ቢፈፀሙ ወይም የተለያዩ ድርጊቶች በተለያዩ ጊዜ ተፈፅመው ቢገኙ ቁሳዊ መደራረብ አለ ለማለት የሚቻል ሲሆን፣ በአንድ ነጠላ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ወንጀሎች መፈፀማቸው የሀሳባዊ መደራረብ መለያ ባህሪ መሆኑን ከወ/ህ/አ.60(ሀ)እና(ለ) ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ላይ ዐቃቤ ሕግ ጠቅሶ ያቀረበውን ክስ ስንመለከት በፍ/ቤቱ ባይለወጥ ኖሮ 1ኛው ክስ የእርስ በእርስ ጦርነት ማነሳሳት የነበረ ሲሆን ይህን ግን የስር ፍ/ቤት የቀረበው ክስ እና ማስረጃ የተጠቀሰውን መስፈርት አያሟላም በሚል ወደ አምባጓሮ ድንጋጌ የቀየረው መሆኑን ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው የወ/ሕ/አ/577/3/ ተጠቅሶ አመልካች ጥፋተኛ የተባለ ሲሆን አመልካች በድንጋጌው ጥፋተኛ ሊደረግ የበቃው የወ/ሕ/አ/35 እና 32/1/ሀ ተጠቅሶ ከሌሎች ጋር በህብረት ወንጀሉን ፈጽሟል በሚል በመሆኑ የወ/ሕ/አ/35 በግልጽ የሚደነግገው ደግሞ አድማና አምባጓሮ በተደረጉ ጊዜ በህብረቱ ውስጥ መገኘቱ የተረጋገጠበት ሰው የማይቀጣው በወንጀሉ ተካፋይ አለመሆኑን ሊያስረዳ ከቻለ ብቻ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አመልካች አምባጓሮው መፈፀሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ቁጥራቸው ትንሽ ይሁኑ እንጂ በቀረቡት ምስክሮች በዚህ ህብረት ውስጥ ስለመገኘቱ የመሰከሩበት በመሆኑ አመልካች አብረውት የተከሰሱት ሰዎች ድንጋይ፣ ዱላ እና ሌሎች

ማቁሰል የሚችሉ መሳሪያዎችን በመያዝ እየፎከሩ የኦሮሞ ልጆች ላይ ጥቃት ሲያደርሱ እሱም የተጠለሉ ሰዎች ያሉበትን ቦታ ይመራ የነበረ መሆኑን፣ የኦሮሞ ልጆችን ያባርር የነበረ መሆኑን፣ እንዲሁም መስከረም 6 ቀን 2011 ዓ.ም. በነበረው ረብሻ ላይ የነበረ ስለመሆኑ እና በዚህ የአመልካቾች ድርጊት የአንድ ሰው ህይወት ያለፈ ንብረትም የወደመ መሆኑ በምስክሮች በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

አመልካች ከላይ በተጠቀሰው ቀን ሰዓትና ቦታ በአምባጓሮው መካከል ስላለመኖሩ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬን በሚፈጥር መልኩ ባቀረባቸው ማስረጃዎች አልተከላከለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የቀረበውን 1ኛ ክስ ወደ 577/3/ ቀይሮ ጥፋተኛ ማድረጉ ተገቢ እንጂ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ነገር ግን የስር ፍ/ቤት የወ/ሕ/አ/577/3/ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ያመነ ከመሆኑ አንፃር ዐቃቤ ሕግ የወ/ሕ/አ/539/1/ሀ/ ጠቅሶ በዛው በተፈጠረ አምባጓሮው ድርጊት ምክንያት ሰው የሞተ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ ድርጊቱ የተደራራቢ ወንጀልን መስፈርት የማያሟላ መሆኑን በመረዳት 2ኛው ክስ በ1ኛው ክስ ውስጥ የሚጠቃለል ነው ብሎ መወሰን ሲገባው በአንድ ወንጀል የመስራት ሃሣብ የተፈፀመን ድርጊት ወንጀሉ እንደተደራረበ አድርጐ በ2ኛ ክስ ጥፋተኛ ማለቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም. አመልካችን ጨምሮ የስር ሌሎች ተከሣሾች የወ/ሕ/አ/35/32/1/ሀ/ እና 690/1/ለ/ ተላልፈው በተለያዩ ሰዎች ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን አስመልክቶ በአመልካች ላይ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ በማስረጃ የተረጋገጠበት በመሆኑ እንዲሁም ወንጀሉ የተፈፀመበት ቀን አምባጓሮ ከተፈፀመበት ቀን የሚለይ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ አመልካችን ጥፋተኛ በማድረግ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ ሊፀና የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ የተፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የበላይ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤትን የህግ ስህተት ሳያርም ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ ውሣኔውን በማሻሻል ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 188605 በ27/5.2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 227015 ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ህዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2) አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው በወ/ሕ/አ/35፣32/1/ሀ እና 577/3 እና 690/1/ለ/ በአምባጓሮ እና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ነው ብለን ወስነናል፡፡ አመልካች በወ/ሕ/አ/539/1/ሀ እና 556/2/ሀ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት አይገባም ብለን ወስነናል፡፡

3) አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አ/577/3/ የአምባጓሮ ወንጀል ድንጋጌ፡- "በአምባጓሮ ወቅት ከነበረው ሁኔታ የተነሳ በተለይም በጠበኞች መካከል በነበረው ቂም፣የጠብ ማጫር ወይም የስካር ሁኔታ ወይም የጦር መሣሪያዎችን፣ ድንጋዮችን ወይም ማቁሰል ወይም መግደል የሚችሉ ሌሎች ነገሮችን የያዙ ወይም እነዚሁ ነገሮች የተሰጧቸው በመሆኑ በጠቡ መካከል ሰው የቆሰለ ወይም የተገደለ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት ሊደርስ ይችላል፡፡" በሚል ይደነግጋል፡፡

በንብረት ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀልን የሚደነግገውና አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አ/690/1/፡- "ወንጀሉ በወንጀል ክስ አቅራቢነትና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና መቀጮ ሊያስቀጣ በሚችል፡- ለ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በዛቻ፣በኃይል ወይም በብዙ ሰዎች ይልቁንም ሁከት፣ የሥራ መዝጋት ወይም የሥራ ማቆም አድማ በተነሳ ጊዜ በሠራተኞች ወይም በአሰሪዎች እንደሆነ----" በሚል ይደነግጋል፡፡

ከላይ በተገለፀው ድንጋጌ መሠረት በተፈፀመው የአምባጓሮ ወንጀል ምክንያት ሰው የተገደለ እንደሆነ አጥፊው በወ/ሕ/አ/577/3/ ስር በተደነገገው መሠረት ቅጣቱ እስከ ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት ሊደርስ ይችላል"፡ ይህም ማለት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539/1/ ስር እንደተደነገገው ሰው በመግደል ወንጀል ከፍተኛ መደበኛ ቅጣት ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም ሞት ነው፡፡ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 577/3/ ስር በሞት ወይም በእድሜ ልክ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል ጥፋተኛ ስለተባሉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 690/1/ ስር ጥፋተኛ የተባሉበት ቅጣት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 184/1/ሀ/ መሠረት ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት ውስጥ የተጠቃለለ ነው፡፡

በመሆኑም የሞት ቅጣት ወይም የእድሜ ልክ እስራት ቅጣት በሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት ሊጣሉ የሚገባቸውን የቅጣት ዓይነቶች ሁሉ አካቶ የሚይዝ ስለመሆኑ በወ/ሕ/አ/ 184/1/ሀ/ ስር የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን ተደራራቢ ወንጀል ማለትም የወ/ሕ/አ/690/1/ለ/ ቅጣቱ ሲሰላ ታሳቢ አይደረግም ብለን ወስነናል፡፡

4) አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የቅጣት መነሻው እድሜ ልክ እስራት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ደረጃ 38 ተይዞ ቅጣቱ መሰላቱ እና ቅጣት መወሰኑ ተገቢ ነው ብለን ወስነናል፡፡

ሆኖም ግን በስር ፍ/ቤት ከተያዘው 3 የቅጣት ማቅለያ በተጨማሪ ከአጠቃላይ ክርክሩ እንደተገነዘብነው አመልካች ይህን ድርጊት እንዲጸትም የገፋፋው አስቀድሞ በጋሞዎች ላይ ተፈጽሞ የነበረው ጉዳት መሆኑን መረዳት የሚቻል በመሆኑ ቅጣቱም ሊጣል የሚገባው ፍትህን ሊያሰፍን በሚችል መልኩ ሆኖ ስላገኘነው ይህን ወንጀል ለመፈፀም ያነሳሳውን

ምክንያት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ በመውሰድ 4 የቅጣት ማቅለያ እንዲያዝና ከተያዘው የቅጣት መነሻ ደረጃ ላይ መቀነስ ተገቢ ነው ብለን የቅጣት ደረጃውን ወደ ደረጃ 34 ዝቅ አድርገን በ15/ አስራ አምስት/ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተደርጐ ቅጣቱ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች እና አመልካች ለታሰረበት ማረሚያ ቤት እንዲደርስ ታዟል፡፡
- አመልካች የታሰረበት ማረሚያ ቤትም አመልካች ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ የታሰረው ታሳቢ ተደርጐ በተሻሻለው ውሣኔ መሠረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡
- የውሣኔው ግልባጭ አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት በፍ/ቤቱ መልእክት ክፍል በኩል እንዲደረስ ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ማ/አ

የሰ/መ/ቁጥር 211167

ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሰፋ

ፀሀይ መንክር

ኑረዲን ከድር

እስቲበል አንዷለም

አመልካች፡- የአ.ብ.ክ.መ. ጠቅላይ ዓ/ህግ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡-አቶ አዲስ አለሙ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 101212 በቀን ሰኔ 23/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት በመሻር ተጠሪን በነጻ ያሰናበተበትን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በቀን ነሐሴ 13/2011 ዓ.ም በጻፈው የወንጀል ክስ በአሁን ተጠሪ እና በሌሎች ሁለት የስር ተከሳሾች ላይ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/2/ እና የጥሬ ገንዘብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 23/1/ እና 24/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በደብረሲና ጤና አጠባበቅ የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት አስተባባሪ በመሆን ስራ ከጀመረበት ታህሳስ 25/2003 ዓ.ም እስከ ግንቦት 17/2011 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ በነበረበት ወቅት የስር 1ኛ ተከሳሽን በስሩ የሚያስተባብር እንደመሆኑ በአግባቡ ባለመቆጣጠር የመንግስትን ስራ በማያመች አኳኋን በመመምራት 252,871.60 ብር (ሁለት መቶ ሃምሳ ሁለት ሽህ ስምንት መቶ ሰባ አንድ ብር ከስልሳ ሳንቲም) እንዲጎድል በማድረግ በፈጸመው ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

በማስረጃነትም የተጠሪን የሥራ ድርሻ የሚገልጽ ሰነድ፣ የኦዲት ሪፖርት፣ የጤና ጣቢያው የገንዘብ እንቅስቃሴን የሚገልጽ ሰነድ፣ ተጠሪ ለፖሊስ የሰጠውን ቃልና የሰው ማስረጃ አያይዘዋል፡፡

ተጠሪ ቀርበው የእምነት ክህደት ቃል የሰጡ ሲሆን ወንጀሉን ያልፈጸሙና የተቋሙ ገንዘብ ወጭና ገቢ ሲደረግ የነበረው በተጠሪ ሳይሆን በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በመሆኑ ስለገንዘቡ ጉዳይ እውቅና የሌላቸው መሆኑን በመጥቀስ ጥፋተኛ አለመሆናቸውን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም እንደ ክሱ ያስረዱልኛል በሚል ምስክሮችን ያቀረበ ሲሆን 1ኛና 2ኛ የአመልካች ምስክሮች የኦዲት ባለሙያ ሲሆኑ ከታህሳስ 2009 እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም ያለው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በክሱ የተገለፀው ብር የጎደለ መሆኑን፣ በክልሉ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 23 መሰረት ከ ሰላሳ ሽህ ብር በላይ በካዝና መቀመጥ የሌለበት መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ተጠሪና ሂሳብ ኦፊሰሩ ገንዘቡን በመቆጣጠር ከጉድለት ሊታደጉት የሚገባ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ 3ኛ የአመልካች ምስክር ደግሞ የመስሪያ ቤቱ ተረኛ ጥበቃ መሆኑን ገልጾ በእለቱ ግንቦት 17/2011 ዓ.ም 11፡30 ሰዓት ንብረት ሲረከቡ የገንዘብ ቤቱ ቁልፍ ሳይቆለፍ ተንጠልጥሎ ስላዩት አልረከብም ብለው ለህግ አካል አሳውቀው ሲታይ ካዝናው ያልተቆለፈና ቁልፉ የሚሰራ መሆኑን አስረድቷል፡፡

ክሱንና የቀረቡትን ማስረጃዎች የመረመረው ፍ/ቤትም ተጠሪ በቀረበባቸው ክስ ስር እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ሲሆን ተጠሪም የመ/ምስክሮች አቅርበው ያሰሙ ሲሆን 1ኛ የተጠሪ መ/ምስክር ተጠሪ ሲሆኑ በሰጡት የምስክርነት ቃልም የግዥ አስተባባሪ ቢሆኑም ምን ያህል ገንዘብ በካዝና እንደሚኖር እውቅና የሌላቸው መሆኑን፣ የፋይናንስ ቢሮ በሩ አልተቆለፈም ብለው እንደደወሉለትና በቦታው ተገኝተው ሲመለከቱትም ተጨራምቶ ተንጠልጥሎ እንዳገኙት፣ ካዝናው ውስጥ ብር የሌለ መሆኑን፣ የሂሳብ ስራውን የሚቆጣጠረው ኃላፊው መሆኑን፣ ገንዘብ ላይ ተጠሪ አዞም ተቆጣጥሮም ፈርመውም የማያውቁ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ 2ኛ የመ/ምስክር ደግሞ ከሂሳብ ኦፊሰሯ ጋር በመሆን ባላንስ ሰርተው ለበላዮቻቸው የሚያሳውቁ መሆኑን፤ ባንክ እንዲገባ ደብዳቤ ሲፃፍላቸው ባንክ የሚያስገቡ መሆኑን፣ ይህ ጠፋ የተባለው ገንዘብ ግን ወደ ባንክ ይግባ ሲባል ተጠሪን ጨምሮ ለእናቶች ገቢ ማሰባሰቢያ ወፍጮ ይገዛበታል በሚል ገንዘቡ በካዝና እንዳለ ተጠሪም የሚያውቅ መሆኑን፣ ተጠሪ አስተባባሪ በመሆናቸው ገንዘቡ እንዲገባ ለኃላፊው መናገር አለባቸው በማለት አስረድተዋል፡፡

3ኛ መ/ምስክር በበኩላቸው የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ መሆናቸውን፣ በቀን የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለሂሳብ ሰራተኛ እንደሚሰጡ፣ ሂሳብ ሰራተኛ ደግሞ ሰርቶ ለዋና ገንዘብ ያዥ አስገብቶ የመስሪያ ቤቱ ዋና ኃላፊ ይፈርምብትና የሚላክ መሆኑን እንጅ ተጠሪ ሲፈርም አይቶ የማያወቅ መሆኑን፣ አስረድተዋል፡፡ 4ኛ መ/ምስክር ደግሞ የመ/ቤቱ የሥራ ባልደረባና ተጠሪ የቅርብ አለቃው መሆኑን፣ የቢአስሲ ውጤቶችን አብረው የሚሰሩ መሆኑን፣ የገንዘብ ስራዎችንና ደብዳቤዎችን

ለኃላፊ የሚጽፍ መሆኑን ገልጸ ተጠሪ ምን ምን ተግባሮችን እንደሚሰራና የስራ ኃላፊነቱን የማያውቅ መሆኑን አስረድቷል፡፡ በሌላ በኩል በሰነድ ማስረጃነት ልዩ ልዩ ደብዳቤዎችን አያይዟል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በቀን የካቲት 11/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ የስራ ሂደት አስተባባሪ ሲሆኑ በመ/ቤቱ የስራ መዘርዝር የሂሳብ አያያዝ ማንዋል ላይ የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት አስተባባሪ የስራ ኃላፊነቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ የመ/ቤቱን የባንክ አካውንትና በካዝና ያለ ገንዘብ አያያዝ የመከታተልና የመቆጣጠር እንዲሁም የመፈረምና የመቆጣጠር ሃላፊነት የተሰጠው በመሆኑና በራሱ ቸልተኝነት በተገቢው መንገድ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ የተገኘ ጉድለት በመሆኑ በቀረበበት ክስ ተከላከል በተባለበት የወንጀል ህግ ጥፋተኛ ነው በሚል በአራት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት እና ብር 2,000.00 (ሁለት ሽህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡና ለአንድ ዓመት ያህል ከህዝባዊ መብታቸው በማገድ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ያጸና ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ የመስሪያ ቤቱ የግዥና ፋይናንስ የስራ ሂደት አስተባባሪ ሲሆኑ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት ደግሞ ገንዘብ ያዥ እንደነበሩ የተረጋገጠ መሆኑን፣ ገንዘብ የሚቀመጠው እና ወደ ባንክ ገቢ የሚደረገው በገንዘብ ያዥ መሆኑን፣ ተጠሪ ገንዘቡ በገንዘብ ያዥ እጅ ከሆነ ገቢ አለመደረጉን የሚያውቅበት አግባብ ስለመኖሩ በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ ይህ ጉድለት ሲከሰት የተጠሪ አስተዋጽዖ በግልጽ ስለመኖሩ የተረጋገጠ ነገር አለመኖሩን በመግለጽ የሥር ፍ/ቤት በገንዘብ ያዥ አማካኝነት የጎደለን ገንዘብ ተጠሪ የወንጀል ኃላፊነት አለበት ተብሎ የመንግስትን አሰራር በማያመች አኳኋን የመምራት ወንጀል ድርጊት በመፈጸማቸው ጥፋተኛ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነጻ አሰናብቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 8/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም ተጠሪ የጤና ጣቢያው የግዥና የፋይናንስ የሥራ ሂደት አስተባባሪ እንደሆነና የሥር 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት ደግሞ በተጠሪ ስር ያለ ተጠሪ ሊቆጣጠረው የሚገባው ገንዘብ ያዥ ሰራተኛ መሆኑ ተረጋግጦ እያለና በኦዲት መመሪያ መሰረት ከብር 30,000.00 (ሰላሳ ሽህ ብር) በላይ በካዝና ሊቀመጥ የማይገባ መሆኑ ተደንግጎ እያለ እንዲሁም የተጠሪ ኃላፊነት በስራ መዘርዝር ውስጥ ገንዘብ ገቢና ወጭ በመፈረም የሚቆጣጠር መሆኑ ተገልጾ እያለ የስር ሰበር ችሎት ገንዘብ ገቢ ማድረግ ያለበት

ገንዘብ ያኘ ነው በሚል ከጭብጥ የወጣ ውሳኔ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፣ ተጠሪ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ሊጠየቅ አይገባም ከተባለ እንኳን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 420 መሰረት ሊጠየቅ ሲገባው የስር ፍ/ቤት በነጻ ማሰናበቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሰው የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ እንዲሻርላቸው በማመልከታቸው ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የጤና ጣቢያው የግዥ ፋይናንስ የስራ ሂደት አስተባባሪ ስለመሆናቸው በስራ መዘርዝሩም ላይ መስሪያ ቤቱ የባንክ ሂሳብና በካዝና ያለውን የገንዘብ አያያዝ የመከታተልና የማጣራት ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ በተገለፀበት በገንዘብ ያዡ በኩል የጎደለውን ገንዘብ በተመለከተ ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉን ተጠሪ በሚያውቅበት አግባብ አመልካች በማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑ የመንግስትን አሰራር በማያመች አኳኋን የመምራት ወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው አልተረጋገጠም በሚል ተጠሪን በነፃ በማሰናት የወሰነበትን አግባብ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/2/ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ነጥቦች አንጻር ለመመርመር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን ጥር 24/2014 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ በአመልካች የተጠቀሰው ገንዘብ በካዝና ስለመኖሩ ተጠሪ የሚያውቁበት አግባብ የሌለና የአመልካች ማስረጃም ተጠሪ ገንዘቡን ስለማወቃቸው ያላስረዱ መሆኑን፣ የኦዲት ስራ ሲደረግ የገንዘቡ ወጭና ገቢ ደረሰኞች በተጠሪ ስም ያልተቆረጡ መሆኑን፣ የቀረበው ሰነድና የሰው ምስክሮች ገንዘቡ በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ትዕዛዝ ገቢና ወጭ ሲደረግ የነበር መሆኑን ያስረዱ መሆናቸውን፣ ተጠሪ በወንጀል ህግ ቁጥር 23 መሰረት ወንጀሉን የመፈጸም የሀሳብ ክፍል የሌላቸው መሆኑን፣ ገንዘብ ያዥው ያለውን ገንዘብ ካላሳወቃቸው በምንም ሁኔታ ሊያውቁ የማይችሉና ገንዘብ ያዡንም አልተቆጣጠርክም ሊያስብል የማይችል መሆኑን፣ በመስሪያ ቤቱ ያለውም ልማድ ገንዘብ ያዡ ለበላይ ኃላፊ በጽሁፍ እያሳወቀ ገንዘቡን ገቢና ወጭ እያደረገ ሲሰራ የቆየ መሆኑን፣ የገንዘብ መባከን ሰራተኛውን ላለመቆጣጠራቸውና ላለመምራቱ ብቸኛ መስፈርት ሊሆን ያማይገባ መሆኑን ገልጸው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች በተጠሪ በቀረበባቸው መልስ ላይ የመልስ መልስ ለማቅረብ ከፈለጉ ለምርመራ ከተቀጠረበት ቀን በፊት እንዲያቀርቡ ቢታዘዙም የመልስ መልሳቸውን ያላቀረቡ በመሆናቸው የአመልካችን የመልስ መልስ የማቅረብ መብት ችሎቱ ቀሪ አድርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ክሱን ያቀረበው የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 13(2)ን በመጥቀስ ተጠሪ የደብረ ሲና ጤና ጣቢያ የግዢ ፋይናንስ ንብረት

አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት አስተባባሪ ሆነው ሲሰሩ የጤና ጣቢያው ዋና ገንዘብ ያዥ ሆነው ሲሰሩ በባንክ በጤና ጣቢያው አካውንትና በካዝና ያለን ገንዘብ አያያዝ ሊከታተሉና ሊቆጣጠሩ ሲገባ በዚህ አግባብም በካዝና ሊቀመጥ የሚገባው እስከ ብር 30,000.00 ብቻ ሊሆን የሚገባ በመሆኑ ከዚህ በላይ የሆነው ገንዘብ ወደ ባንክ ሂሳብ እንዲገባ የማድረግ ኃላፊነት እያለባቸው ይህንን ባለማድረግ ብር 252,871.60 እንዲጎድል ያደረጉ መሆኑን በመጥቀስ በመሆኑ የተጠሪ ወንጀል ኃላፊነት የመነጨው በህግ የታዘዘውን ካለማድረግ (Omission) መሆኑን ከክሱ አቀራረብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የአዋጁ አንቀፅ 13(2) በአንቀፅ 13(1) ከፊደል ሀ እስከ ሐ የተመለከቱን ዝርዝር የህግ ነጥቦች መሰረት በማድረግ የከበደ የወንጀል ኃላፊነትን ለመጣል የተቀመጠ ሲሆን አንቀፅ 13(1) ከፊደል ሀ እስከ ሐ የተመለከቱትን ዝርዝር ሁኔታዎች ስንመለከታቸው ጥቅም መውሰድን ወይም ጥቅም የሚያስገኝን ውል መዋዋልን፣ውል ማቋረጥን፣የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅትን ጥቅም የሚጎዳ ተግባርን መፈፀምን ለመቅጣት የተደነገጉ መሆናቸው አንቀፅ 13 ከመነሻውም ካለማድረግ (Omission) ይልቅ ማድረግን (Comission) ለመቅጣት በህጋችን የተካተተ መሆኑን ያሳያል፡፡ይህም አመልካች በተጠሪ ላይ በስራ ኃላፊነታቸው መሰረት ሊከታተሉና ሊቆጣጠሩ ሲገባ ግዴታቸውን ባለመወጣት የደረሰን ጉዳት በመጥቀስ የአዋጁን አንቀፅ 13(2) መሰረት በማድረግ ማቅረቡ የህጉን ዝርዝር ሁኔታ መሰረት ያላደረገ ክስ ማቅረቡን፣የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መስጠቱና ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ስህተት ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ የአዋጁን አንቀፅ 13(2) መሰረት ያላደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡

ተጠሪ በመ/ቤቱ የስራ መዘርዝር የሂሳብ አያያዝ ማንዋል ላይ የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት አስተባባሪ የስራ ኃላፊነቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ የመ/ቤቱን የባንክ አካውንትና በካዝና ያለ ገንዘብ አያያዝ የመከታተልና የመቆጣጠር እንዲሁም የመፈረምና የመቆጣጠር ኃላፊነት በተጠሪ ላይ የተጣሉ ሀላፊነቶች መሆናቸው ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ እያለ የዐቃቤ ህግ ምስክሮችም ተጠሪ ይህንን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት በክሱ ላይ የተመለከተው ጉዳት መድረሱን በዋነኝነትም ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ምስክሮች እያስረዱ፣የተጠሪ 2ኛ ምስክርም ተጠሪ አስተባባሪ በመሆናቸው ገንዘቡ ባንክ እንዲገባ ለኃላፊው መናገር ያለባቸው መሆኑን ገንዘቡ ካዝና መኖሩን እያወቁ ይህንን ሳያደርጉ መቅረታቸውን እያስረዱ ይህም የተጠሪ ምስክር ጭምር ተጠሪ በስራ መዘርዝሩ አግባብ አለመስራታቸውን እያስረዱ ይህ ሁኔታ ደግሞ በወ/ህ/አ.420(2) መሰረት የስራ ሀላፊነትን ባለመወጣት የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ ሆኖ እያለ ተጠሪን በነፃ ማሰናበቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተጠሪ በወ/ህ/አ.420(2) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ቅጣትን አስመልክቶ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊት በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን ማንዋል ቁ.02/2006 መሰረት የወንጀል ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ አግባብ የሚጣለው ቀላል የእስራት ቅጣት እስከ 5 አመት ሊደርስ እንደሚችል ከወ/ህ/አ.420(2) እና 106(1) የጋራ ንባብ የምንረዳው በመሆኑ ዝቅተኛውን ከ10 ቀን እስከ 1 አመት ከ3 ወር ቀላል እስራትና ከብር 10.00 እስከ ብር 3,333.33 የሚያስቀጣ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተያዘውን ዝቅተኛ የወንጀል ደረጃ በመውሰድ 1 አመት እስራትን ስንወስድ በዝቅተኛው እርከን 5 ላይ የገንዘብ መቀጮው ብር 3,100.00 እርከን 4 ላይ የሚያርፍ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የተያዙትን 3 ማቅለያዎች ከግምት ውስጥ ስናስገባ የእስራት ቅጣቱ እርከን 2 ላይ የገንዘብ መቀጮው እርከን 1 ላይ የሚያርፍ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ካለ ታስቦ በሶስት ወር ቀላል እስራትና በብር 1,000.00 ሊቀጡ ይገባል በማለት በአብላጫ ድምፅ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1.የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.101212 ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.195(2)(ለ)(2) ተሻሽሏል፡፡ ተጠሪ በወ/ህ/አ.420(2) ስር የስራ ሀላፊነትን ባለመወጣት በሚፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

2.ተጠሪ በዚህ ጉዳይ የታሰሩት ካለ ታስቦ በሶስት ወር ቀላል እስራትና በብር 1,000.00 ሊቀጡ ይገባል ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

የክፍሉ ፖሊስ ተጠሪን ለማረሚያ ቤቱ እንዲያስረክብና ማረሚያ ቤቱ ከላይ በተመለከተው የቅጣት ውሳኔ አግባብ እንዲያስፈፅም ታዟል፡፡

**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

<u>**የልዩነት ሃሣብ**</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 ስር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ ከአብላጫው ድምጽ በሚከተለው ምክንያት በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

ተጠሪ ፈጽመውታል በሚል በአመልካች የተጠቀሰባቸው የወንጀል ድርጊት አፈፃፀም የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት አስተባባሪ በመሆን ሲሰሩ የሚያስተባብሩትን ሥራ በአግባቡ ባለመቆጣጠራቸው የመንግስትን ሥራ በማያመች አኳኋን በመምራት ብር 252871.60 እንዲጎድል አድርገዋል በሚል አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/2/ ተጠቅሶ መሆኑን ያሳያል፡፡ በእርግጥ በአብላጫው ድምጽ ድንጋጌ  የተቀየረ ሲሆን በእኔ እምነት ግን ከክሱ የተመለከትነው ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ አጎደሉ ሳይሆን ባለመቆጣጠራቸው ጉድለት ተገኝቷል የሚል ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳውም ሆነ ከአጠቃላይ ከመዝገቡ ይዘት ጎደለ የተባለውን ገንዘብ ያጎደለው ገንዘብ ያዥ መሆኑን ነው፡፡

አንድ ገንዘብ ያዥ የሆነው ሰው እንዲቆጣጠረውና እንዲጠብቀው በኃላፊነት የተረከበዉን ገንዘብ የመጠበቅ ኃላፊነት የራሱ የገንዘብ ያዥ እንጂ የሌላ  3ኛ ወገን ሊሆን አይገባም፡፡ የተጠሪ ሥራ የማስተባበር ሥራ እንጂ በካዝና የሚገኝን ገንዘብ እየቆጠሩ በካዝና መቀመጥ ካለበት በላይ በካዝና ተቀምጧል አልተቀመጠም በሚል መቆጣጠር ሳይሆን አጠቃላይ በስራቸው የሚገኙትን ሥራዎች ማስተባበር ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ከሃሣቡ በላይ እና ህግም ከሚጥልበት ኃላፊነት በላይ በሌላ ሰው ጥፋት ኃላፊ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ሲሆን በየትኛውም የሥራ ኃላፊነት በላይ በሌላ ሰው ጥፋት ኃላፊ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ሲሆን በየትኛውም የሥራ ኃላፊነት ምክንያት ለሚደርስ ግድፈትም ሆነ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው ጥፋቱን የፈፀመውና የሚመለከተው አካል እንጂ በተዋረድ በአንድ ሥራ ስር የሚገኙ የተለያየ ሥራ እና ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች ሁሉ ተጠያቂ የሚሆንበት አግባብ ስለሌለ፣ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሥራ የተለያዩ ሰዎች በኃላፊነት የሚቀመጡትም የየራሳቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ከመሆኑ አኳያ ተጠሪ ስለመቆጣጠራቸው ምክንያት ነው በሚል ከካዝና ለጎደለ ገንዘብ ኃላፊ የሚሆንበት የህግም ሆነ የሞራል ምክንያት የለም በሚል የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል እንጂ አንቀጽ ተቀይሮ ጥፋተኛ ሊሆን አይገባም ነበር ብዬ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 202508

ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ፈለቀ ታደሰ ዘነበ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 09 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 204239 መጋቢት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሐምሌ 17 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 183872 ሕዳር 29 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች እና በሌሎች 4 ተከሳሾች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው ክሶች አራት ሲሆኑ አመልካችን የሚመለከቱት 1ኛ እና 3ኛ ክሶች ናቸው፡፡

1ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) እና 411/1(ሐ)(2) ድንጋጌን በመተላለፍ አመልካች የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ዋና ስራ አስኪያጅ ሌሎቹ ደግሞ የአገዳ ተከላ እና እንክብካቤ ስራ አስኪያጅ፤ የእርሻ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ ቡድን መሪ እና የመሬት ልማትና ዝግጅት ሱፐርቫይዘር ሆነው ከ2005 እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ሲሰሩ የማይገባ ጥቅም ለራሳቸው ለማግኘት ወይም የመሬት መደልደል ውል ከፋብሪካው ጋር ለተዋዋለ ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ ለማስገኘት እና በፋብሪካው ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሠብ ኮንትራክተሩ የካቲት 4 ቀን 2005 ዓ.ም እና መስከረም 2 ቀን 2006 ዓ.ም ከፋብሪካው ጋር በገባው ውል መሠረት የመሬት ድልዳሎ ስራውን ለሸንኮራ አገዳ ተክል በሚሆን ጥራት መሰራቱን በማረጋገጥ መረከብ ሲገባቸው አመልካች የፋብሪካውን ስራ በበላይነት የመምራት እና የመቆጣጠር ሃላፊነት እያለው ባቱ ኮንስትራክሽን ለመስራት በውል የተረከበውን የመሬት መደልደል

ስራ በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት ለአገዳ ተክል ልማት በሚሆን መጠን እና ጥራት ሠርቶ ማስረከብ ሲገባው ተሰርቷል ተብሎ ርክክብ የተደረገው የመሬት መደልደል ስራ በውሉ ላይ የተገለጸው እና ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት በሚፈለገው ጥራትና መጠን እንዳልሆነ እንዲሁም በፋብሪካው ማሽነሪዎች እና ወጪ የተሰራው ባቱ ኮንስትራክሽን እንደሰራው ተደርጎ ክፍያ እንዲሚፈጸምለት በፋብሪካው ሠራተኞች እየተነገረው ካለው ሃላፊነት አንጻር ስራው በአግባቡ ስለመሠራቱ በማረጋገጥ ርክክብ እንዲፈጸም ማድረግ ሲገባው ከ300 እስከ 400 ሔክታር የሚሆን የመሬት መደልደል ስራ ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት በሚሆን ጥራት ሳይሰራ ርክክብ እንዲፈጸም እና በፋብሪካው ማሽነሪዎች እና ሠራተኞች በድጋሚ እንዲሰራ በማድረጉ፤ ከ2-4 ያሉት ተከሳሾችም በተሰጣቸው ሃላፊነት መሠረት ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ እንዲሠራ በውል የተሰጠውን የመሬት መደልደል ስራን ሲጀምር በፋብሪካው ማሽነሪዎችና ሠራተኞች ከሚሠራው ስራ በግልጽ ተለይቶ እንዲሰጠው በማድረግ የሰራውንም ስራ በአግባቡ በመመዝገብ የሚሰራው የመሬት ዝግጅት በፋብሪካው ማሽነሪዎችና ሰራተኞች ስራው ሳይቀላቀል እንዲያከናወን ማድረግ ሲገባቸው ባለማድረጋቸው መጠኑ በግልጸ የማይታወቅና በፋብሪካው የራስ አቅም የተሰራውን ስራ ባቱ ኮንስትራክሽን ከሰራው ስራ ጋር እንዲቀላለቀል አድርገዋል፤ የመሬት ዝግጅት ስራውን ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት በሚሆን ጥራት መሠረት መሠራቱን በማረጋገጥ መረከብ ሲገባቸው ከ300-400 ሔክታር መሬት በውሉ ላይ በተጠቀሰው ጥራት ሳይሰራ ርክክብ አድርገው በፋብሪካው ማሽነሪዎች እና ሠራተኞች ስራው በድጋሚ እንዲሠራ ትዕዛዝ በመስጠታቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት የፋብሪካውን ጥቅም በመጉዳት የመንግስት ሥራ በማያመች አኳሃን መምራት የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

3ኛ ክስ፡- አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 407 /1(ሀ)(2) ድንጋጌን በመተላለፍ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት እና በፋብሪካው ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ሐምሌ 2003 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስኳር ኮርፖሬሽን የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 17/3 ውጪ ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ ከፋብሪካው ጋር ቀደም ብሎ በገባው ውል መሠረት ለመስራት የተረከበውን የመሬት መደልደል ስራ ለአገዳ ተክል ልማት በሚፈለገው ጥራት እና ፍጥነት ሠርቶ ማስረከብ አለመቻሉን በግልጽ እያወቀ መስከረም 2 ቀን 2006 ዓ.ም 1000 ሔክታር የመሬት መደልደል ስራ በብር 29,691,551 እንዲሰራ ተጨማሪ ውል በመዋዋሉ እና ባቱ ኮንስትራክሽንም በውል የተሰጠውን መሬት በጥራት እና በፍጥነት ባለመስራቱ ከ300-400 ሔክታር የሚሆን የመሬት ድልዳሎ ስራ በፋብሪካው ማሽነሪዎች እና በድጋሚ እንዲሠራ ምክንያት በመሆኑ በስልጣን አላግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ ቀሪ ክሶች አመልካችን ስለማይመለከቱ መመዝገብ አላስፈለገም፡፡

ተከሳሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁም ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኂላ አመልካች የፋብሪካው ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ እየሰራ

በነበረበት ጊዜ በባቱ ኮንስትራክሽን እንዲሰራ ውል የተገባለት የሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት ስራ በሚፈለገው ጥራት ባለመሠራቱ ስራው በድጋሚ እንዲሰራ ማድረጉን የባቱ ኮንስትራክሽን ማሽነሪዎቹ ዘመናዊነት የሌላቸው በመሆኑ እና የውሃ ፍሰቱን ጥራት ባለሚሟላቱ በፋብሪካው ዘመናዊ ማሽነሪዎች እንዲሁም ሠራተኞች ከ300-400 ሄክታር የማረም እና ማስተካከል ስራዎች የተሰሩ መሆኑን የዓቃቤሕግ 1ኛ፤ 2ኛ፤ 4ኛ፤ 5ኛ፤ 6ኛ፤ 8ኛ እና 10ኛ ምስክሮች አስረድተውባቸዋል፤ እነዚህ ምስክሮች በተጨማሪ 2ኛ ፤ 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች በፋብሪካው የራስ አቅምና በባቱ ኮንስትራክሽን የተሰራውን የመሬት ድልዳሎ ስራ የሚመለክት ለየብቻ የተያዘ መረጃ ባለመኖሩ መቼና በየትኛው ቦታ ምን ያህል ስራ ተሰርቷል የሚለውን ለማወቅ አለመቻሉንና መጠኑ ያልታወቀ ስራ የተቀላቀለ መሆኑን እንዲሁም በስራው የጥራት ችግር ምክንያት ከላይ የተጠቀሰው የመሬት መጠን በፋብሪካው ወጪ ማሽነሪና የሰው ሃይል እንደገና የማስተካከል ስራ የተሰራ መሆኑን መስክረዋል፤ 12ኛ እና 13ኛ ምስክሮች በፋብሪካው እና በባቱ ኮንስትራክሽን የተሰሩት ስራዎች ያልተለዩ የነበረ በመሆኑ የፋብሪካው የውስጥ ኦዲት ባለሙያዎች ችግሩን እንዲያስተካክሉት መመሪያ ሰጥተው የተመለሱ ቢሆንም በፋብሪካው የራስ አቅም ምን ያህል በባቱ ኮንስትራክሽን ደግሞ ምን ያህል እንደተሰራ ያልተለየ ስለመሆኑ በ1ኛ፤ 2ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ላይ መስክረውባቸውል፡፡ 3ኛ ክስን በተመለከተ አመልካች ከመስከረም 2 ቀን 2006 ዓ.ም በፊት ፋብሪካው በገባው ውል መሠረት ባቱ ኮንስትራክሽን የሚሠራው ስራ የጥራት ችግር የነበረበት በመሆኑ በተደጋጋሚ በፋብሪካው ማሽነሪዎችና ሠራተኞች የማስተካከያ ስራዎች ሲሰሩ የነበሩ መሆኑን እያወቀ መስከረም 2 ቀን 2006 ዓ.ም ከዚሁ ባቱ ኮንስትራክሽን ጋር ተመሳሳይ ውል መፈጸሙን ከመንግስት የልማት ድርጅት የቀጥታ ግዢ የሚፈቀደው ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተሻለ ጥራትና ፍጥነት እንዲሁም የዋጋ ተመጣጣኝነት መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑን ምስክሩ አስረድቷል፤ ሌሎች ተከሳሾችም ድርጊቱን የፈጸሙ ስለመሆኑ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል፤ ስለሆነም ተከሳሾች ክሱን ሊካለከሉ ይገባል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

ተከሳሾችም መከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አስቀርበው አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አቶ ያቆብ ጨረፎ የተባሉት 7ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍርድ ቤቱ በሰጡት ቃል በ2005 ዓ.ም መጨረሻ እስከ 2006 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በባቱ ኮንስትራክሽን ከተሰራ በኋላ 200 ሔክተር የሚሆን መሬት በፋብሪካው ማሽነሪዎች በድጋሚ የተሰራ መሆኑን የድጋሚ ስራው ምክንያቶችም በዝናብና ነፋስ የመሬቱ ተዳፋትነት ሲበላሽ ወይም ወይም የዲዛይን ለውጥ ሲኖር እንጂ በባቱ ኮንስትራክሽን የስራ ጥራት ችግር አለመሆኑን በባቱ ኮንስትራክሽን በጥራት ተሰርቶ ርክክብ ከተደረገ በኋላ በሚመጣ ችግር ምክንያት በፋብሪካው ማሽኖች ስራዎች እየተሰሩ በየቀኑ በሱፐርቫይዘር እስከ ስኳር ኮርፖሬሽን በየደረጃው ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን በመግለጽ ተከሳሾችን በሚጠቅም መልኩ የምስክርነት ቃል የሰጡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የእኚህን ምስክር ቃል ተከሳሾቹ እንዲከላከሉ በማስረጃነት ያልያዘው በመሆኑ እንዲሁም የዓቃቤ ሕግ ምስክር በሰጡት ቃል ላይ ምስክሩ አስጠቂ ምስክር በመሆናቸው መሪ ጥያቄ እንዲጠየቁ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ ፈቅዶ በዋና ጥያቄ እንዲቀርብላቸው የተደረገ

በመሆኑ እና በተከሳሾች በመከላከያነት ምስክርነት ተቆጥረው በችሎት ያልቀረቡ ቢሆንም ተከሳሾች የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ይደግፈናል ብለው በመከራከራቸው ከቀሪ መከላከያ ምስክሮች ጋር ፍርድ ቤቱ አያይዞ የምስክርነት ቃሉን መዝኖታል፤ 12ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር የሆኑት አቶ አድነው ጌጤ ተፈልገው ባለመገኘታቸው ለፓሊስ የሰጡት ቃል ቀርቦ የታየ እና ፍርድ ቤቱም የእኚህን ምስክር ቃል ተከሳሾቹ የተከሰሰቡባቸውን ክሶች ማስረጃውን መዝኖ እንዲከላከሉ በማስረጃነት የተጠቀመበት ቢሆንም እኚህ ምስክር ለአራቱም ተከሳሾች የጋራ መከላከያ ምስክር ሆነው በችሎት ቀርበው የመሰከሩ እና ለመርማሪ ፖሊስ የሰጡት የምስክርነት ቃል በተጽእኖ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ የገለጹ እና በዓቃቤ ሕግ መስቀለኛ ጥያቄ የቀረበላቸው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በተከሳሾች መከላከያነት የምስክርነት ቃላቸውን ተቀብሎ መዝኖታል፤ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ከክሱ ፍሬ ነገሮች ጋር በተገናኘ በቀጥታ አስረድተዋል፤ የተከሳሽ ምስክሮች ርክክብ የመፈጸም ሀላፊነት የለባቸውም ከሚለው ውጪ ሌላውን የክሱን ፍሬነገር ለማስረዳት የሞከሩት ከመሬት ዝግጅት ጋር በተያያዘ ያለውን አሰራር ነው፤ የሒሳብ ሪፖርቱ ኦዲቱ የተሰራበትን መንገድ በዝርዝር የገለጸ እና ደጋፊ ሰነዶችን ከኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን የተከሳሾች ጠበቆች በሒሳብ መርማሪው ውጤት ላይ አስተያየታቸውን የሰጡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የቀረበውን አስተያየት ውድቅ አድርጎታል፤ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የተገለጹት ፍሬነገሮች እንዳለቁ ማስረጃዎች ተደርገው የማይወሰዱ እና የአስረጅነታቸው ሁኔታ የሚመዘን ቢሆንም ተከሳሾች ሙያዊ በሆነ መርህ የኦዲት ስራው በትክክል ስላለመሰራቱ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ ስለመሬት ርክክብ በናሙናነት የቀረበው ማስረጃ በአጠቃለይ ስለፋብሪካው አሰራር ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ከሚችል በቀር ከክሱ ጋር በቀጥታ የአስረጅነት ክብደት የለውም፤ የአቶ ያዕቆብ የምስክርነት ቃል ሲመረመር በዋናነት የድጋሚ ስራው እንዲሰራ ሲያስተባብሩ የነበሩ ስለመሆናቸው በዓቃቤ ሕግ የሰው ምስክሮች የተመሰከረባቸው በመሆኑ እና ምስክሩ ራሳቸውን በሚጎዳ መልኩ ይመሰክራሉ ተብሎ ስለማይገመት ፤ 14ኛው የአመልካች የብቻ ምስክር የግዢ መመሪውን በሚመለከት ያስረዱ ቢሆንም መመሪያው ሲወጣ ሐሳቡ ምን ነበር ሲሉ ዳኞች ትርጓሜ የሚሰጡበት በመሆኑ የምስክርነት ቃሉ ተቀባይነት የለውም፤ እኚህ ምስክር በዓቃቤ ሕግ መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ የኦዲት ሪፖርቱን በዝርዝር ያላዩ እና የተመለከቱት የተሰጠውን አስተያየት ብቻ መሆኑን የመሰከሩ በመሆኑ የምስክሩ ቃል በኦዲት ሪፖርቱ አጠቃላይ ይዘት ላይ ማስተባበያ ሰጥተዋል ማለት አያስችልም፤ አድነው ጌጡ የተባሉት ምስክር ሪፖርት ማድረጉ ቡድን መሪ ላይ ብቻ የሚቀር እና እስከ በኋላ ለማንም ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን የመሰከሩ ቢሆንም የተከሳሾች ሌሎቹ ምስክሮች በሪፖርት መልክ በየደረጃው ላሉ የስራ ሀላፊዎች የሚደረግ ስለመሆኑ ከሰጡት ምስክርነት አንጻር ሲታይ የምስክርነት ቃላቸው ተአማኒ ሆኖ አልተገኘም፤ የመሬት ዝግጅት ስራው የፋብሪካው አንዱ የዕቅዱ አካል በመሆኑ እና ለተከሳሾች የተሰጣቸው የስራ መዘርዝር የለም ስራዎቹ የሚሰሩት በነባር ፋብሪካዎቹ የስራ ልምድ ነው ቢባል እንኳን አመልካች የፋብሪካው ዋና ስራ አስኪያጅ በመሆን ስራውን በበላይነት የመምራት እና የመቆጣጠር ዋነኛው ስራው ሆኖ የሚሰራው ስራ የጥራት ችግር ያለበት መሆኑ ተገልጾለት ሳለ ምንም ዓይነት የማስተካከያ እርምጃ የወሰደ ስለመሆኑ አላስረዳም፤ ዓቃቤ ሕግ ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን በገንዘብ ገምቶ እንዲያቀርብ

ታዞ ክሱን አሻሽሎ ያቀረበ ቢሆንም የድጋሚ ስራው በፋብሪካው ማሽኖች እና በሰው ሀይል ከ300 እስከ 400 ሔክታር መሬት የማድረስ የማስተካከያ ስራ በድጋሚ ስለመሰራቱ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ በጠቀሰው የሕግ አንቀጽ ሳይሆን አመልካች በወንጀል ሕግ 411/1/ሐ በ1ኛ ክስ ጥፋተኛ ናቸው፤ 3ኛ ክስን በተመለከተ አመልካች የስኳር ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ አንቀጽ 17/3 ውጪ ባቱ ኮንስትራክሽን ከዚህ ቀደም የጥራት እና የፍጥነት ችግሮች ያሉበት መሆኑን እያወቀ ድጋሚ የመሬት ዝግጅት ውል ማድረጉ ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠ በመሆኑ በተከሰሰበት ድንጋጌ ሳይሆን በ1ኛ ክስ በተጠቀሰው ምክንያት ዓቃቤ ሕግ ጉዳቱን በገንዘብ ግምት ባለማቅረቡ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1/ሀ ድንጋጌ ነው በማለት ጥፋተኛ ብሎ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እና በብር 7000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን የመጨረሻው ቅጣት ውሳኔ የሚወሰነው ግን በዚያው ፍርድ ቤት ካለው የመ.ቁ 204157 ከሆነው መዝገብ ጋር ተጣምሮ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች የካቲት 09 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ ሆነ ስኳር ፋብሪካ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በመሆናቸው አመልካች አንዱን ጠቅሜ እንዱን ልጎዳ የምችልበት ምክንያት የሌለ እና አቃቤ ህግ ይህንን የሀሳብ ክፍል በህግ ግምት የሚወሰድበትን አሳማኝ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 23(2) ድንጋጌ መስፈርትን አያሟላም፤ ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ ስራው የተሰጠው የግዥ መመሪያውን መሰረት ባደረገ መልኩ ሳይሆን በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን እና በስኳር ኮርፖሬሽን ዋና ዳሬክተር የፖሊሲ ውሳኔ መነሻነት መሆኑን የአመልካች መከላከያ ማስረጃዎች አስረድተዋል፤ የማሳ ርክክብ የሚፈጸመው ማሳው በትክክለኛ ጥራት መሰራቱ በቅድሚያ በሰርቬየሮች በሚወሰድ ሙያዊ ሪፖርት ብቻ ተረጋግጦ እንደሆነ እና አመልካች ጥራትን በማረጋገጥ ሂደት ላይ ምንም አይነት ሙያዊ ተሳትፎ እንደሌለኝ አስረድቻለው፤ በዚህ ረገድ የዐቃቤ ህግ ምስክር የሆኑት አቶ ያእቆብ ጨረፎ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤቱ ሳይመዝን አልፎታል፤ አቃቤ ህግ በምስክርነት ቆጥሮአቸው የነበሩትን አቶ አድነው ጌጡ በአድራሻቸው የሉም በማለት ሀሰተኛ አቤቱታ ለፍርድ ቤት አቅርቦ ለፖሊስ የሰጡትን ቃል በማስረጃነት እንዲያያዝ ማድረጉን አመልካች የተቃወምኩ እና አቶ አድነው ጌጡም በመከላከያ ማስረጃነት ቀርበው እውነታውን ያስረዱ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ውድቅ ማድረጉ ተገቢነት የለውም፤ 1000 ሄክታር የመሬት መደልደል ስራ በብር 29,691,551 እንዲሰራ ተጨማሪ ውል እንዲፈረም የተደረገው በስኳር ኮርፖሬሽን ዋና ዳሬክተር እና በባቱ ኮንስትራክሽን ቦርድ ነው፤ አመልካች የተከሰስኩበት ውል መስከረም 2 ቀን 2006 ዓ.ም ሲፈረም ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ ቀደም ብሎ በዋና ዳሬክተሩ ውሳኔ በፋብሪካው ውስጥ የመሬት ድልዳሎ ስራን ሲሰራ የነበረ መሆኑን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ የተወሰነ ነው፤ ሐምሌ 2003 ዓ.ም በወጣው

የስኳር ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ የአንቀጽ 17/3 ድንጋጌ መሰረት አመልካች መስከረም 2/2006 ዓ.ም በነበረው ሁኔታ የተጨማሪ ስራ ውሉን እንዳይፈጸም ሊያደርግ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፤ ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በሰራቸው የመሬት ድልዳሎ ስራዎች ጥራት ላይ የቀረበ ቅሬታ እንደሌለ በማስረጃ ተረጋግጧል፤ የድጋሚ ስራ የተሰራው በባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ የስራ ጥራት ጉድለት ጋር በተያያዘ አለመሆኑ አመልካች አስረድቷል፤ ከርክክብ በኂላ የሚፈጠሩ የማሳ ጉድለቶች ስራ ተቋራጩ የማስተካከል ኃላፊነት ስለሌለበት በፋብሪካው ማሽንኖች እንዲሰራ መደረጉ ተገቢ አሰራር መሆኑን አመልካች አስረድቷል፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ ወደ ሥራው የገባበት፤ ከቆይታ የተነሳ ስራው በትክክል ስለአለመሰራቱ እና ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ ከሙያው ባሕርይ አንጻር የተጣራበት እንደዚሁም ከአመልካች የስራ ሀላፊነት እና ሌሎች ተመሳሳይ ነጥቦች ጋር ታይቶ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 411/1/ሐ እና 407/ሀ በመተላለፍ የመንግስትን ሥራ በማያመች አኳሃን የመምራት እና በሥልጣን ያላግባብ መገልገል ወንጀል ፈጽመዋል በሚል የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበትን አግባብነት ከመሠረታዊ የክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ጥቅምት 04 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የድርጊቱ አላማ ሌላኛውን ተቋም ጥቅም እንዲያገኝ ባይሆንም እንኳ በሕገ ወጥ ተግባር ውስጥ ለራስ የሚገኝ ጥቅም የሚኖር ሲሆን በሌላ በኩል የአንድን የመንግስት በጀት ለሌላ የመንግስት ተቋም ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሰረት ሳይኖረው ማስተላለፍ በተቋሙ ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረስ ነው፤ ሕገ ወጥ ትዕዛዝን መቀበል በማናቸውም መንገድ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ አመልካች ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ ስራውን እንዲሰራ የመንግስት ፖሊሲ ነው ከማለት ውጪ ያስገደደው አካል ስለመኖሩ ያቀረበው ማስረጃ የለም፤ አመልካች ኃላፊነቱን ወደ ጎን በመተው ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ የሰራው ስራ ጥራት የጎደለው መሆኑን እያወቀ ርክክብ እዲፈጸም ያደረገ እና የድጋሚ ስራው በሙሉ እውቅና ሲያሰራ የነበረ መሆኑ የአቃቤ ህግ ምስክሮች አስረድተዋል፤ በባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ኂላቀር እና ማኑዋል በመሆናቸው ስራው የጥራት ችግር የነበረበት በመሆኑ እና ይህንን ለማስተካከል በፋብሪካው ዘመናዊ መሳሪያዎች የድጋሚ ስራ መታዘዙ የተጠሪ ምስክሮች አስረድተዋል፤ አቶ ያዕቆብ ጨረፎ የተከሳሾች ተባባሪ የነበረ እና በወንጀል ድርጊቱ ላይ ተሳታፊ የነበረ በመሆኑ የሰጠው የምስክርነት ቃል ተዓማኒነት ያለው አይደለም፤ አቶ አድነው ጌጡ ለዐቃቤ ህግ በምስክርነት ተፈልጎ የጠፋ ነገር ግን በመከላከያ ምስክርነት ቀርቦ የተሰጠው ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኒ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ ከመነሻውም ቢሆን ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በሕጉ አግባብ የቀረበ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው 1ኛ ክስ አመልካች ተላልፎታል በማለት የጠቀሰው የወንጀል ሕግ 411/1(ሐ)እና(2) ድንጋጌን ነው፤ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 411/1(ሐ) ማናኛውም የመንግስት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፤ ስልጣኑን ወይም ሀላፊነቱን ተጠቅሞ በጠቅላላው በሥራው ስልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን የሕዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸውም ዘዴ የፈጸመ እንደሆነ በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፤ የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 አክባጅ ሁኔታን የሚመለከት ነው፡፡

በሌላ በኩል ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው 3ኛ ክስ አመልካች ተላልፎታል በማለት የጠቀሰው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1(ሀ)እና(2) ድንጋጌን ነው፤ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1(ሀ) ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፡- የተሰጠውን ሹመት ወይም ሥልጣን በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፤ የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 አክባጅ ሁኔታን የሚመለከት ነው፡፡

ከላይ ከተመለከቱተ ድንጋጌዎች ይዘት በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤ ሕግ ድንጋጌዎቹን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ ድርጊቱ የተፈጸመው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ነው የሚለውን የሕጉን መስፈርት ማሟላት በሚያስችል ሁኔታ በተከሳሹ ተፈጽሟል ያለውን ግዙፋዊ ፍሬ ነገር / material fact / በአግባቡ መመሥረት እና ማስረዳት እንዳለበት ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማሕበር የመንግስት ልማት ድርጅት ነው፡፡ ይህ ድርጅት መንግስታዊ የልማት ተቋም እስከሆነ ድረስ አመልካች ፈጽሞታል በተባለው የሙስና ወንጀል ከዚሁ መንግስታዊ የልማት ተቋም የማይገባ ጥቅም ሊያገኝ ወይም ሊያስገኝ የሚችልበት ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች ያሉ ስለመሆኑ ማሳየት በሚያስችል ሁኔታ ክሱን መመሥረት ይጠበቅበታል፡፡ ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ባቀረበው 1ኛ እና 3ኛ ክስ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም የመሬት መደልደል ውል ከፋብሪካው ጋር ለተዋዋለ ባቱ ኮንስትራክሽን አ.ማ ለማስገኘት እና በፋብሪካው ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሠብ ድርጊቱን ፈጽሟል

በማለት ከመግለጽ በቀር በእርግጥም አመልካች መንግስታዊ የልማት ድርጅት ከሆነው ባቱ ኮንስትራክሽን ላይ የማይገባ ጥቅም ሊያገኝ ወይም ሊያስገኝ የሚችልበት ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች / material facts / ያሉ ስለመሆኑ ማሳየት በሚያስችል ሁኔታ ክሱን አልመሠረተም፤ ባቀረበው ማስረጃም ይህንኑ ማስረዳት አልቻለም፡፡ ስለሆነም ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ አመልካች ክሱን እንዲከላከል ብይን ሊሰጥ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት አመልካችን መከላከል ሳያስፈልገው ከክሱ በነጻ ማሰናበት ሲገባቸው አመልካች ክሱን እንዲከላከል ብይን መስጠታቸው በመቀጠልም አመልካች ባቀረበው ማስረጃ ክሱን አልተከላከለም በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 204239 መጋቢት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሐምሌ 17 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 183872 ሕዳር 29 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች መከላከል ሳይስፈልገው ከክሱ በነጻ ሊሰናበት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

አመልካች በእስር የሚገኝ ከሆነ የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካች በሌላ ጉዳይ የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ ከእሥር እንዲለቀው ታዟል፡ በውሳኔው መሠረት ማስፈጸም ይቻለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

ማ/አ　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁጥር 208890

ታሕሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ዮናታን ጎንቴ ዋልኮ

ተጠሪ፡- የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 206466 ግንቦት 24ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ አመልካች ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈፅሟል በሚል የቀረበበትን ክስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ ሕዳር 4ቀን 2012 ዓ/ም በተፃፈ ክሱ አመልካች ከሌሎች አራት ተከሣሾች ጋር በመሆን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)፣ 671(1)(ለ)ና (ሐ) የሚደነግገውን በመተላለፍ ጥቅምት 20ቀን 2012ዓ/ም ከሌለቱ 10፡30 ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ልዩ ቦታው ገርጂ መብራት ሀይል አካባቢ ንብረትነቱ የግል ተበዳይ የአቶ ተስፋዬ ብርሐኔ የሆነውን ሱቅ ተንጠልጣይ ቁልፍ በብረት መቁረጫ በመቁረጥ የገጠማቸውን ተቃውሞ ለማስቀረት ሲሉ በምስክሮች አይን ላይ የፓውዛ (ከፍተኛ ብርሃን የሚያመነጭ) መብራት በማብራት፣ እፈጭሃለሁ የሚል ማስፈራሪያ ቃል በመናገር እንዲሁም ከቦታው በማባረር ግምታቸው 239,500.00 ብር የሚያወጡ ለሽያጭ የተዘጋጁ ጥቅል የኤሌክትክ ገመድ በመውሰዳቸው ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ክስ አቅርቦባቸው ክደው ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪ ምስክሮች ተደምጠው አመልካች በክሱ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ መከላከል እንዲጀምር ታዞ መከላከያው ከተደመጠ በኂላ ጥፋተኛ ተብሎ በዘጠኝ አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኖበታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ስለፀናው ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሰኔ 7ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው ፈፅሟል የተባለው የወንጀል ድርጊት በክሱ ላይ የተጠቀሰውን አንቀፅ ማቋቋሚያ የሚያሟላ አይደለም ሲል ያቀረበው መቃወሚያ ታልፎ ከባድ ውንብድና ወንጀል ስለመፈፀሙ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ በአግባቡ ሣይረጋገጥ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃም አስተባብሎ ሣለ ጥፋተኛ ተብሎ ከባድ ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በተጠሪ በኩል ቀርበው ከተደመጡት ምስክሮች መካከል 3ኛ ምስክር በተከሳሾች የተፈፀመበት የሀይል ድርጊት ስለመኖሩ ሣያረጋግጥ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 671(1)(ለ) (ሐ) ድንጋጌ ስር የጥፋተኝት ፍርድ የመሰጠቱን አግባብነት ከድንጋጌው ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር አኳያ እንዲመረመር በመታዘዙ ክርክራቸውን በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ማስረጃን የመመዝን የዳኝነት ስልጣን ለሰበር ሰሚ ችሎት ያልተሰጠው መሆኑን ሆኖም በስር ፍርድ ቤቱ የተፈፀመ ማስረጃ ምዘና አለመኖሩን፣ ከባድ ውንብድና ወንጀልን ለመቋቋም የሀይል ድርጊት መኖር ብቸኛ መመዘኛ አለመሆኑን፣ አመልካችም የሐይል ድርጊት መፈፀሙን በማስረጃ መረጋገጡን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች የፈፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ክርክሩን አቅርቧል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 671(1)(ለ)ና (ሐ) የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ ውንብድና ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ በእስራት እንዲቀጣ በተሰጠው ውሣኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት ይዘን የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች ከባድ የውብድና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ክስ እንዲቀርብበት ምክንያት የሆነው በአመልካችና በግብረ አበሮቹ የተፈፀመው የሃይል ድርጊት ስለመሆኑ የክሱ አቀራረብ ያስገነዝባል፡፡

አንድ ሰው ከባድ ውንብድና ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚችለው የውንብድና ወንጀል የተፈፀመው በሰዎች ላይ ወይም በንብረት ላይ የሐይል ተግባር ለመፈፀም በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ሲሆን ወይም ተበዳዩን እገድልሃለሁ ብሎ እርግጠኛ የሞት አደጋ እንደሚያደርስበት በመቃጣት ይልቁንም በጦር መሳሪያ ወይም በተለይም አደገኛ በሆነ ሌላ አይነት መሣሪያ በማስፈራራት ወይም ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ በማንገላታት ወይም ከባድ አካል ጉዳት በማደርስ ሲሆን ወይም በተለይም አደገኝነቱን በሚያሣይ በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ሲሆን እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከባድ ውንብድና ወንጀልን ከውንብድና ወንጀል የሚለየው የሐይል ድርጊቱ የተፈፀመው ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን ከሆነ ወይም የተፈፀመው ድርጊት ከፍ ያለ መንግላታትን ያስከተለ ወይም በጦር መሣሪያ በመጠቀም እርግጠኛ የሞት አደጋ እንደሚያደርስበት በማስፈራራት በተፈፀመ

ጊዜ እንደሆነ ይደነግጋል። በመሆኑም አመልካቹ የፈፀመው የውንብድና ወንጀል ነው ወይስ ከባድ ውንብድና የሚለው አከራካሪ ነጥብ የዚህን ችሎት መልስ የሚሻ ነጥብ ነው።

በዚህም መሰረት በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቀረበው ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን የፈፀመው ከሌሎች ሰዎች ጋራ መሆኑ ቢረጋገጥም አመልካችም ሆነ ሌሎች ግብረ አበሮች የወንበዴ ቡድን አባል ስለመሆናቸው የቀረበ ክርክርና ማስረጃ የለም። በመሆኑም በስምምነት ከሌሎች ሰዎች ጋር የተፈፀመ ወንጀል ሁሉ ከባድ ውንብድና ወንጀል ማቋቋሚያ የሆነውን መመዘኛ የሚያሟላ አይሆንም።

በሌላ በኩል አመልካችና ግብረ አበሮቹ የፈፀሙት የሀይል ድርጊት በወጀል ሕግ አንቀፅ 670 ድንጋጌ የሚጠቃለሉ ናቸው ወይስ አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ሕግ እንቀጽ 671 የሚለው ጉዳይ መልስ ማግኘት ይኖርበታል። በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካችና ጓደኞቹ የፈፀሙት የሐይል ድርጊት ምስክሮች ወንጀሉን እንዳይከላከሉ በአይናቸው ላይ ፓውዛ ማብራትና ማስፈራራት እንደሆነ በምስክሮች ተረጋግጧል። ይህ የማስፈራራቱም ሆነ የሐይል ድርጊቱ በኑሮ ልማድ እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 671 ማቋቋሚያ መርሆዎች መሰረት ሲመዘን ከፍ ያለ መንገላታትን ወይም ፍርሀት አስከትለዋል የሚያስብል ካለመሆኑም ባሻገር ሲፈፀሙም ከፍ ያለ ፍርሀትን ወይም ሞትን በሚያስከትል መሳሪያ የተፈፀሙ ስለመሆናቸውም በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ የአመልካችና ግብረ አበሮቹ የፈፀሙት የሐይል ድርጊት  በወንጀል ሕግ አንቀፅ 670 ስር የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 670 የተከለከለውን የውንብድና ድርጊት ተላልፎ በፈፀመው የውንብድና ወንጀል እንጅ በከባድ ውንብድና ወንጀል አለመሆኑን ስለተገነዘብን ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል።

## ው ሣ ኔ

1) የፌዴራሉ ከተፍኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 244151 የካቲት 29 እና 30 ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ፣ እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 206466 ግንቦት 24ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል።
2) አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 670 የተመለከተውን ተላልፎ የውንብድና ወንጀል የፈፀመ በመሆኑ ይሕ ጥፋቱ በወንጀል ቅጣቶች አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀፅ 17 መሰረት መመሪያ የወጣለት በመሆኑ ደረጃው 5 የእስራት ቅጣቱ እርከን 19 በመነሻነት ተይዞ ወንጀሉ በስምምነት የተፈፀመ መሆኑን በማክበጃነት ተይዞ በስር ፍርድ ቤት የተያዙለትን ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች ተይዘውለት እርከን 28 እንዲያርፍ ተድርጎ በዚህ ጉዳይ የታሰረው ሁሉ ታሣቢ ሆኖለት በሶስት ዓመት ከሰባት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኖበታል።

# ት ዕ ዛ ዝ

1) የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በዚህ ችሎት የተወሰነውን የሶስት ዓመት ከሰባት ወር ፅኑ እስራት ቅጣት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ታዟል፤ ይፃፍ፡፡
2) መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ.መ.ቁ 218957

መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. ዳበረ ሆቴል ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር

2. አቶ አምዴ ከልካይ ሳፎ

3. አቶ ሙባረክ በድር ቡልኑ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጥር 02 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 288398 ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ታሕሳስ 01 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284960 ታሕሳስ 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው ክሶች ሶስት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፦ 1ኛ አመልካች የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 131/1/ለ ድንጋጌን በመተላለፍ በአዲስአበባ ከተማ የካ ክፍለከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 729/13/14 ተመዝግቦ በሚታወቅ የንግድ ድርጅት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግቦ ለሰጠው ጊዜያዊ የአልጋ አገልግሎት በ3ኛ አመልካች አማካኝነት ብር 200 ተቀብሎ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ባለመስጠቱ በፈጸመው ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይነት ወንጀል ተከሷዋል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ፦ 2ኛ አመልካች የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 132/1 እና 131/1/ለ የተመለከተውን በመተላለፍ በክስ 1 ላይ ለተገለጸው ድርጅት ስራ አስኪያጅ ሆኖ ድርጅቱን ሲመራ የወንጀል ድርጊቱ ሲፈጸም ሕጉ የጣለበትን የመከላከል ግዴታ ባለመወጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

3ኛ ክስ፦ 3ኛ አመልካች የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 128 እና 131/1/ለ ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት ሲፈጸም ደረሰኝ ቆርጦ መስጠት ሲገባው ባለመስጠት ተከሷል የሚል ነው፡፡

ክሱ ለአመልካቾች ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ አመልካች ግብይቱ ተከናውኗል ደረሰኝ ተቀርጦአል ነገርግን ደረሰኙን አምጥቼ እሰጣቸዋለሁ ስል በሩ ዝግ ስለነበር መስጠት አልቻልኩም በማለት የእምነት ክሕደት ቃላቸውን የሰጡ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካቾች በክስ አቤቱታው ላይ የተገለጸውን የወንከል ድርጊት ስለመፈጸማቸው በዓቃቤሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በማለት ክሱን እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካቾችም መከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካቾቸ ባቀረቡት መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸውን ፍሬነገር ማስተባበል አልቻሉም በማለት በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ብሎአቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት አስልቶ 1ኛ አመልካች በብር 6600 / ስድስት ሺህ ስድስት መቶ / የገንዘብ መቀጮ፤ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ተሰርዟል፡፡

አመልካች  ጥር 02 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፦ የዓቃቤሕግ ክስ እና ማስረጃ አይጣጣምም፤ ግብይቱ በየትኛው ስርኣት እንደተፈጸመ በግልጸ አይታወቅም፤ በቁጥጥር ሰራተኞቹ ጥድፊያ ምክንያ ከተሰጠው አገልግሎት ባሕርይ አንጻር አገልግለቱ ተሰጠ ለማለት በማያስችልበት ሁኔታ የግብይት ሂደቱ በጅምር እንደቀረ እና በዚህም ምክንያት ደረሰኝ ሳይሰጠ እንደቀረ

ያሳያል፤ ተከፍሏል የተባለው ገንዘብ በሚመለከተው የድርጅቱ ገንዘብ ተቀባይ ወደ ድርጅቱ ካዝና አልገባም፤ አመልካቾች ባቀረብነው መከላከያ ማስረጃ ክሱን ተከላክለናል ፤ 2ኛ እaነ 3ኛ አመልካቾች ያቀረበው የቅጣት ይገደብልኝ ጥያቄ የታለፈው በደፈናው ነው፤ ስለሆነም እነኚህ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ሳይገቡ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ግብይት ክፍያ ካሼ ጋር ባልደረሰበት ሁኔታ በአመልካቾች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 እና ከታክስ አስተዳደር ሕጉ አንቀጽ 132 እና 128 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የአመልካቾች አቤቱታ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘ በመሆኑ አግባብነት የለውም፤ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረባቸው ማስረጃዎች እንደክስ አመሰራራቱ ያስረዳ እና አመልካቾች በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸውን ፍሬነገር ያላስተባበሉ በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካቾች በዓቃቤሕግ ክስ ላይ የተገለጸውን የወንጀል ድርጊት የፈጸሙ ስለመሆኑ እና ባቀረቡትም መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ የተረጋገጠባቸውን ፍሬነገር ማስተባበል ያልቻሉ ስለመሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው እና ባቀረቡት መከላከያ ማስረጃም ክሱን ያላስተባበሉ ስለመሆናቸው ይህንኑ የማረጋገጥ ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ

በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በአመልካቾች ላይ የተላለፋው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡
በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ያቀረቡትን የቅጣት ይገደብልኝ ጥያቄ ቅጣቱን መገደቡ ያስተምራቸዋል ወይም ሌሎችንም ያስጠነቅቃል ተብሎ አልታመነበትም በሚል ውድቅ ማድረጉ አግባብ መሆን አለመሆኑነ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡
በመሠረቱ ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዊች ያሉ መሆኑን፣እነኚህም ሁኔታዎች ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እሥራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ እና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም  ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት አመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነኚህ ሁኔታዎች ውጪ በደፈናው ቅጣቱን መገደብ ጥፋተኛውን ያስተምራል ወይም ሌሎችንም ያስጠነቅቃል ብዬ አላመንኩበትም በሚል ቅጣት እንዳይገደብ ማድረግ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በሕጉ ላይ አልተገለጸም፡፡

ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ በጥፋተኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት ለጊዜው ማገድ ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለውም የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፣ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው በመሆኑ ጥፋተኛው ቅጣቱን ለማስገደብ ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደለም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ የተላለፈው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች መኖራቸውን በውሳኔው ላይ ሳይገልጽ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ይልቁንም 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የዘወትር ባሕርያቸው መልካም እንደሆነ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው፣ የተለያዩ ማሕበራዊ ሀላፊነቶችን ሲወጡ የቆዩ ስለመሆናቸው እና የጤና ችግር ያለባቸው

መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት የቅጣት ገደብ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 288398 ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ታሕሳስ 01 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284960 ታሕሳስ 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ የተላለፈው የእሥራት ቅጣት አፈጻጸሙን በሚመለከት ሳይፈጸም ለሁለት ዓመት እንዲገደብ በማለት ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

- 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እያንዳንዳቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 መሠት የብር 5000/ አምስት ሺህ / መተማመኛ ዋስትና እንዲያስይዙ ታዟል፡፡ይኸው ሲፈጸም የሚመለከተው ማረሚያ ቤት 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችን ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

# አሠሪ እና ሰራተኛ

**የሰ/መ/ቁ.** 201933

ጥቅምት 04 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካቾች**:- 1. ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት

**ተጠሪ**:- አቶ ተስፋዬ ገ/ፃዲቅ

ግራ ቀኙ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በወንጀል ተጠርጥሮ የታሰረ የመንግስት ሰራተኛ ከክሱ ነፃ ሆኖ ወደ ስራዉ ከተመለሰ በኋላ ከደመወዝ ጋር በተያያዘ የሚኖረዉን ህጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ በ1ኛ አመልካች መስሪያ ቤት ውስጥ ክፍያ እና ሂሳብ ደጋፊ የስራ ሂደት መሪ በመሆን ሳገለግል የቆየሁ ሲሆን በማዕከሉ ከስራዬ ጋር በተያያዘ ችግር ተፈጥሯል በሚል ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት በፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክስ መስርቶብኝ ከህዳር 21 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በእስር ላይ ቆይቼ ከክሱ በነፃ ተሰናብቻለሁ፡፡ ነፃ ከተባልኩበት ጊዜ አንስቶ አሰሪዬ የነበረው 1ኛ አመልካች ወደ ስራ እንዲመልሰኝ እና ያልተከፈለኝ ደመወዝ እንዲከፍለኝ ብጠይቅም ቦታ ስለሌለ 2ኛ ተጠሪ ምደባ ይስጥህ በማለት ደብዳቤ ጽፎልኛል፡፡ በዚሁም መሠረት 2ኛ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ ውስጥ ከነሐሴ 01 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ምደባ እንዲሰጠኝ ደብዳቤ የፃፈልኝ ሲሆን ቢሮውም ፍቃደኛ በመሆን ክሊራንስ እንዳመጣ ጠይቆኝ 1ኛ ተጠሪ እንዲሰጠኝ በተደጋጋሚ ብጠይቀው ፍቃደኛ ሳይሆን ቆይቶ ከሁለት ወር በኋላ ያልተሟላ ክሊራንስ ሰጥቶኛል፡፡ የሰጠኝ ክሊራንስ ላይ የተገለፀው የደመወዝ መጠን በቀድሞው መሠረት ሲሆን መንግስት ለመደቡ ያደረገውን ጭማሪ ታሳቢ ያደረገ አይደለም፡፡ ጭማሪ ከመደረጉ በፊት እኔ ይሰራበት የነበረው መደብ ፐሳ 8 ደመወዙም ብር 6,547.00 ሲሆን ከጥር 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ ወር 2010 ዓ.ም ወደ ብር 8236.00 እንዲሁም ከሐምሌ ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ወደ ብር 9,177.00 አድጓል፡፡ 1ኛ አመልካች በዚህ አግባብ

ደብዳቤውን ለአዲሱ መስሪያ ቤት መፃፍ እያለበት ባለመፃፉ አገኝ የነበረው ጥቅም ቀርቶብኛል፡፡ ስለሆነም ደብዳቤውን አስተካክሎ እንዲጽፍልኝ፣ 1ኛ ተጠሪ ከታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 2012 ዓ.ም ድረስ ያለውን ደመወዜን መንግስት በየጊዜው ያደረገውን ማሻሻያ ታሳቢ በማድረግ በጠቅላላው ብር 283,273.00 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ ተጠሪ በስሩ ይሰራ የነበረ ሰራተኛ መሆኑን፣ በመሀልም በወንጀል ተጠርጥሮ ከታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ በእስር ምክንያት የስራ ውሉ ተቋርጧል፡፡ ከእስር ከተፈታ በኋላ ወደ ስራው መመለስ ቢችልም በመታሰሩ ምክንያት የተቋረጠበት ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ግን ሊከፈለው አይገባም፡፡ በሌላ መስሪያ ቤት በመመደቡ ምክንያትም በ1ኛ አመልካች መስሪያ ቤት ውስጥ ሲሰራ የነበረውን የስራ ዓይነትና ሲከፈለው የነበረውን የደመወዝ መጠን በአግባቡ በመግለጽ በቀን 19/01/2012 ዓ.ም የተሰጠው በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪም አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት አስተዳደራዊ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የታሰረው ከስራው ጋር በተያያዘ በወንጀል ተጠርጥሮ በመሆኑ ከክሱ ነፃ ከተባለ በመታሰሩ ምክንያት የተቋረጠበት ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል፤ የሚከፈለው በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ያገኝ በነበረው የደመወዝ መጠን እንጂ እስር ላይ እያለ መንግስት ለመደቡ ባደረገው ማሻሻያ መሠረት አይደለም በማለት ከታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ከክሱ ነፃ እስከ ተባለበት ጊዜ ድረስ በወር ብር 6,547.00 ተባዝቶ እንዲከፈለው፤ ክሊራንሱም ይኸው የደመወዝ መጠን ተጠቅሶ ይሰጠው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት  እና ሰበር ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች በቀን 27/05/2013 ዓ.ም በተፃፈ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሟል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የአመልካች የደመወዝ ጥያቄ ስድስት ወር ካለፈ በኃላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረብነው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ፤ አመልካች ከስራው ሲቀር ለ1ኛ አመልካች ያላሳወቀ ሲሆን በስራው ላይ ላልነበረና የስራ ውሉ ለተቋረጠበት ሰራተኛ ደመወዝ እንድንከፍል መወሰኑ፤ አመልካች በተጠረጠረበት ወንጀል ነፃ ተብሎ ቢሰናበትም ሊመደብ የሚችለው ክፍት መደብ ሲኖር ብቻ ሲሆን 1ኛ አመልካች ጋር ተጠሪ የነበረበት መደብ በመያዙ በ2ኛ ተጠሪ በኩል ምደባ እንዲሰጠው ተደርጎ የስራ ውል ግንኙነቱ ለተቋረጠ ግለሰብ ውዝፍ ደመወዝ ክፈሉ መባሉ ከዚህ ቀደም ይህ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በአመልካች የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ እና የውዝፍ ክፍያ ክርክር ውድቅ ሆኖ የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 56/2010 አንቀፅ 73(5) እና 86(1)(2) አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ በቀን 06/07/2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረት ተገቢውን ክፍያ ለአመልካች ከፈፀሙ እና ጉዳዩ ካበቃ በኋላ የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም፤ የይርጋ መቃወሚያውን በሚመለከት የተጠሪ ጉዳይ በአዋጁ የይርጋ ድንጋጌ ስር የሚጠቃለል አይደለም፤ የይርጋ ድንጋጌው ተፈፃሚነት አለው እንኳን ቢባል ለዚህን ያህል ጊዜ የታሰርኩትና ተዘዋውሮ የመስራት ነፃነቴ የተገደበው በ1ኛ አመልካች ምክንያት በመሆኑ የክፍያ ጥያቄው በይርጋ ሊታገድ አይገባም፤ የይርጋ ጊዜውም ሊቆጠር የሚገባው ከተከሰስኩበት ጉዳይ በነፃ ከተሰናበትኩበት ጊዜ አንስቶ በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከርክሯል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ተጠሪ ላልሰራበት ደመወዝ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲከፈለዉ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ ባቀረበዉ አቤቱታ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ከታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ በእስር ላይ ከቆየ በኋላ በነፃ ተሰናብቶ ከመስከረም 2012 ዓ.ም ጀምሮ ምደባ የተሰጠዉ ቢሆንም ከምደባዉ በፊት ለነበሩት ጊዜያት 1ኛ አመልካች ደመወዙን በተለያዩ ጊዜያት ሲደረጉ ከነበሩት ጭማሪዎች ጋር ለመክፈል ፍቃደኛ ያለመሆኑን ነዉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ከታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም ነፃ እስከወጡበት ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ ያለዉ ሊከፈለዉ ይገባል በሚል የወሰነ ሲሆን የአመልካቾች መሠረታዊ የቅሬታ ነጥብም ተጠሪ ላልሰራበት ስራ ደመወዝ ሊከፈለዉ አይገባም የሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ ደመወዝ የሚከፈለዉ ለተሰራ ስራ በአሠሪዉ አካል የሚከፈል የድካም ዋጋ በመሆኑ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ደመወዝ የሚከፈለዉ በመስሪያ ቤቱ በስራ ላይ ሆኖ በተመደበበት ስራ ለሰጠዉ አገልግሎት መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ ይህ መሠረታዊ መርህ ሲሆን በስራ ላይ ባልነበረበት ጊዜ ለአንድ የመንግስት ሠራተኛ ደመወዝ የሚከፈለዉ በህግ በልዩ ሁኔታ የተመለከተ ግልጽ ድንጋጌ ሲኖር ብቻ መሆኑንም ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም አንድ የመንግስት ሠራተኛ በስራ ላይ ባልነበረበት ጊዜ የሚያቀርበዉ የደመወዝ ይገባኛል ጥያቄ መርምሮ ዉሳኔ በመስጠት ረገድ አመልካች ስራ ሳይሰራ ደመወዝ ሊከፈለዉ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ማየቱ ግድ ይላል፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 በክፍል አራት ስር የስራ ሰዓት እና ፍቃድ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን አንድ ሠራተኛ ስራ ሳይሰራ ደመወዝ ሊከፈለዉ የሚችለዉ ሠራተኛዉ ከስራዉ የቀረዉ በህዝብ በዓላት እና በሳምንት እረፍት ምክንያት፣ በዓመት እረፍት ፍቃድ ምክንያት፣ በወሊድ ፈቃድ ምክንያት፣ በህመም

ፈቃድ ምክንያት፣ ለግል ጉዳይ በሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ምክንያት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ በዚህ ክፍል በአንቀጽ 36 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች ዉጪ በስራ ላይ ላልተገኘ ሠራተኛ ደመወዝ የሚከፈለዉ ስለመሆኑ አዋጁ አይደነግግም፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ከታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም ድረስ ከስራ ላይ የቀረዉ በወንጀል ተጠርጥሮ ጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ የነበረ በመሆኑ ምክንያት ቢሆንም በዚህ እና በመሰል ሁኔታዎች ምክንያት ሠራተኛዉ ከስራ የቀረ እንደሆነ በስራዉ ላይ ባይገኝም መስሪያ ቤቱ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ አዋጁ በተለይ አይደነግግም፡፡ በመርህ ደረጃ ደመወዝ የሚከፈለዉ በስራ ገበታዉ ላይ ተገኝቶ ተገቢዉን አገልግሎት ለሰጠ የመንግስት ሠራተኛ በመሆኑ እና ስራ ሳይሰራ ደመወዝ የሚከፈለዉ በአዋጁ የተመለከተ ድንጋጌ ሲኖር ብቻ መሆኑ እና ይህም ለመርሁ ልዩ ሁኔታ በመሆኑ በጠባቡ መተርጎም የሚገባዉ ሲሆን በእስር ምክንያት በስራ ገበታዉ ላይ ላልተገኘ ሠራተኛ መስሪያ ቤቱ ደመወዝ ለመክፈል የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 193322 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ ተጠሪ በመታሰሩ ምክንያት በስራ ገበታዉ ላይ ተገኝቶ ለመስሪያ ቤቱ ተገቢዉን አገልግሎት ባልሰጠበት ሁኔታ አመልካቾች ከታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 2011 ዓ.ም ድረስ ያለዉን ደመወዙን ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ እና በየደረጃዉ ያሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎቶችም ይህንን አለማረማቸዉ ሠራተኛዉ በስራ ገበታዉ ላይ ሳይገኝ ደመወዝ ሊከፈል የሚችልባቸዉን ልዩ ሁኔታዎችን አስመልክቶ የፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ላይ የተመለከተዉን እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተመለከተዉ መዝገብ ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ባቀረበዉ አቤቱታ 1ኛ አመልካች ደብዳቤ በተገቢዉ ሁኔታ ሳይጽፍለት በመቅረቱ ምክንያት ለሁለት ወራት ያህል ደመወዝ ሳያገኝ መቅረቱን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ተጠሪ ያልሰራበትን ዉዝፍ ደመወዝ አመልካቾች የመክፈል ኃላፊነት አለባቸዉ የሚል አቋም በመያዙ ምክንያት 1ኛ አመልካች ደብዳቤዉን በተገቢዉ ሁኔታ ባለመፃፉ ምክንያት ተጠሪ አጥቻለሁ ያለዉን የሁለት ወር ደመወዝ 1ኛ አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆን ያለመሆኑን በተለይ መርምሮ ዉሳኔ አልሰጠበትም፡፡ ይሁንና በዚህ ረገድ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ከዉዝፍ ደመወዝ ክፍያ በተጨማሪ 1ኛ አመልካች ከደብዳቤ አፃፃፍ ጋር በተያያዘ በፈጸመዉ ጥፋት ለደረሰበት ጉዳት የሁለት ወር ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ይዘት ያለዉ በመሆኑ ተጣርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤት በአ/መ/ቁጥር 1377/12 በቀን 16/06/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32005 በቀን 30/03/2013 ዓ.ም በዋለዉ

ችሎት የሰጡት ዉሳኔ፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 24364 በቀን 27/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ተጠሪ በእስር ላይ በነበረበት ወቅት ሊከፈለዉ የሚገባዉን ደመወዝ አመልካቾች የመክፈል ኃላፊነት የለባቸዉም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተገቢዉን አሟልቶ ደብዳቤ አለመጻፉንና በዚህም ምክንያት 1ኛ አመልካች የሁለት ወር ደመወዝ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆን ያለመሆኑን ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር አጣርቶ ተገቢዉን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 12/06/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**ሄ/መ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሠ/መ/ቁጥር 205420

ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች፡- ጋራንባ ቦትሊንግ ኃላ/የተ/የግል ማኀበር- የጠበቃ ረዳት ቀረቡ**

**ተጠሪ፡- አቶ ንጉሴ ፋሲል**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ በአመልካች ድርጅት በከባድ መኪና አሽከርካሪነት የሥራ መደብ ላይ በወር ብር9900.00 ደመወዝ እየተከፈለኝ ከቀን 26/06/2012ዓ/ም ጀምሮ እየሰራሁ እያለሁ ለሥራ የሚሰጠኝ ነዳጅ በቂ ስላልሆነ በቂ ነዳጅ እንዲሰጠኝ ጥያቄ በማቅረቤ አመልካች የማሽከረክረዉን መኪና ለሌላ ሹፌር በመስጠት የሥራ ዉሌን አቋርጦብኛል፡፡ በመሆኑም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ እንዲባልልኝና የሥንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ቅጣት እና ያልተከፈለኝ የአንድ ወር ደመወዝ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ አመልካች ሌላ በርካታ ተሽከርካሪዎች ስላሉኝ ተጠሪ ያነሱትን የነዳጅ ይጨመርልኝ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ሌላ ተሽከርካሪ በመስጠት ለማሰራት ብፈልግም ተጠሪ ከቀን 18/10/2012ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ገበታቸዉ ላይ አልተገኙም፡፡ በዚሁ ምክንያት ተጠሪ ከሥራ የቀሩበትን ምክንያት ይዘዉ እንዲቀርቡ ማስጠንቀቂያ ቢለጠፍም ተጠሪ ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም የሥራ ዉሉን ተጠሪ በገዛ ፈቃዳቸዉ ያቋረጡ በመሆኑ እና የሰኔ ወር ደመወዝ ቀርበዉ ያልወሰዱ በመሆኑ ክሳቸዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 166841 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች መርምሮ በቀን 27/05/2013 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ነዳጅ ይጨመርልኝ ጥያቄ በማቅረባቸዉ ምክንያት አመልካች በቀን 09/10/2012ዓ/ም ተጠሪ የሚያሽከረክሩትን መኪና እንዲያስረክቡ ማድረጉን፤ተጠሪ በተደጋጋሚ ሥራ ይሰጠኝ እንዲሁም ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ላቀረቡት ጥያቄ አመልካች መልስ ሳይሰጣቸዉ መቆየቱን ምስክሮች ከመሰከሩት መረዳት ተችሏል፡፡የተጠሪ ጥያቄ ነዳጅ ያንሰኛል የሚል በመሆኑ አመልካች ጉዳዩን አጣርቶ መጨመር ወይም ባለዉ እንዲቀጥሉ ማድረግ ሲገባዉ ወይም በመልሱ ላይ እንደገለጸዉ

ሌላ መኪና መቀየር ሲገባዉ መኪናዉን እንዲያስረክቡ አድርጎ ሥራ በመከልከል የሥራ ዉል ማቋረጡን የተጠሪ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡የአመልካች ምስክሮች ቃል ይህንን የሚያስተባብል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ሥራ በመከልከል የሥራ ዉሉን በማቋረጡ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ፡፡ስለሆነም የስንብት ክፍያ ብር 3300.00፣ካሳ ብር 59,400.00፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 9900.00፣ ያልተከፈለ ደመወዝ ብር 9900.00 እንዲሁም ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ብር 9900.00 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 267803 ላይ በቀን 23/07/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሠርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 28/07/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ፡-ተጠሪ ከቀን 18/10/2012 ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ገበታቸዉ ላይ አልተገኙም፡፡በማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎላቸዉም ሊገኙ አልቻሉም፡፡ይህንን የሚያረጋግጥ የሰዉና የሠነድ ማስረጃ ቀርቦለት እያለ የሥር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1/ለ) መሰረት የተቋረጠዉን የሥራ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጧል በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም ተጠሪ እንኳን በክርክራቸዉ ላይ ያላነሱትን ተጠሪ ሥራ ተከልክለዋል በሚል ምክንያት ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ይህ ፍሬ ነገ ሀሰት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሠራተኛ ከሥራ እስካልተሰናበተ ድረስ ሥራ ወይም ደመወዝ ተከልክያለሁ ቢል እንኳን ደመወዝ እንዲከፈለዉ ክስ ይመሰርታል እንጂ እራሱ ጥሎ የሄደዉን ሥራ አለአግባብ እንደተሰናበት ተቆጥሮ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸዉ የሚሰጥ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች አላሰናበትኩም ብሎ እየተከራከረ ይህ ሳይጣራ አመልካች ከተጠሪ ላይ መኪና በመረከቡ ብቻ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 09/09/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ተጠሪ የማሽከረክረዉን ተሽከርካሪ በሥራ ኃላፊዎቹ አማካኝነት በቀን 09/09/2012ዓ/ም ለሌላ ሹፌር እንዳስረክብ ትእዛዝ ሰጥቶኝ አስረክቤ ሌላ ተሽከርካሪ እንዲሰጠኝ በተደጋጋሚ ጠይቄ አመልካች አትመላለስ በሚል ተሽከርካሪ ሊሰጠኝ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን በማስረጃ አስረድቻለሁ፡፡በገዛ ፈቃዶ ከሥራ አለመቅረቴንም በማስረጃ አስረድቻለሁ፡፡ስለሆነም አመልካች በሕገ-ወጥ መንገድ የአመልካችን የሥራ ዉል አቋርጧል ተብሎ መወሰኑና ይህንን ተከትሎ አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 27/09/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅርብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ መሰረት

በማድረግ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ተጠሪ በአመልካች ዘንድ በአሽከርካሪነት ተቀጥረዉ ለሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ በቂ ነዳጅ እንዲሰጣቸዉ አመልካችን በመጠየቃቸዉ አመልካች የሚያሽከረክሩትን ተሽከርካሪ ለሌላ አሽከርካሪ በመስጠት የሥራ ዉላቸዉን እንዳቋረጠባቸዉ በመግለጽ የሥራ ዉላቸዉ ከሕግ ዉጭ እንደተቋረጠባቸዉ በመግለጽ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸዉ ጠይቀዋል፡፡አመልካች ደግሞ አመልካች ሌላ በርካታ ተሽከርካሪዎች ስላሉኝ ተጠሪ ያነሱትን የነዳጅ ይጨመርልኝ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ሌላ ተሽከርካሪ በመስጠት ለማሰራት ብፈልግም ተጠሪ ከቀን 18/10/2012ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ገበታቸዉ ላይ ባለመገኘት በገዛ ፈቃዳቸዉ የሥራ ዉሉን አቋረጡ እንጂ የሥራ ዉላቸዉን አላቋረጥኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን በመመርመር አመልካች ተጠሪ ሲያሽከረክሩ የነበረዉን ተሽከርካሪ በመቀበል ሥራ በመከልከል የሥራ ዉላቸዉን ከሕግ-ዉጭ በሆነ አኳኋን አቋርጦ አሰናብቷቸዋል በማለት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን ለተጠሪ እንዲከፍል የወሰነ ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉም አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ከሕግ ዉጭ አቋርጧል ተብሎ የመወሰኑን የሕግ አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 12(1-3) ስር እንደተደነገገዉ ማንኛዉም አሠሪ፣በሥራ ዉሉ ከተመለከቱት ልዩ ግዴታዎች በተጨማሪ ለሠራተኛዉ በሥራ ዉሉ መሠረት ሥራ የመስጠት፣በሥራ ዉሉ በሌላ አኳኋን የተወሰነዉ ካለ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሥራ የሚያስፈልገዉን መሳሪያና ጥሬ ዕቃ ለሠራተኛዉ የማቅረብ እና ለሠራተኛዉ ደመወዝና ሌሎች ክፍያዎችን በዚህ አዋጅ ወይም በኅብረት ስምምነት መሠረት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ሠራተኛም በአዋጁ አንቀጽ 13 ስር የተመለከቱትን ሌሎች ግዴታዎችን የመፈጸም ግዴታ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሥራዉ ብቁ በሆነ የአእምሮና የአካል ሁኔታ በሥራ ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ተጠሪ ለሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ በቂ ነዳጅ እንዲሰጣቸዉ መጠየቃቸዉና አመልካችም ይህንን ጥያቄ ተከትሎ ተጠሪ ሲያሽከረክሩ የነበረዉን ተሽከርካሪ የተረከቧቸዉ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ከዚህ በኂላ አመልካች ተጠሪ በሥራ ቦታ እንዳይገኙ በማድረግ ያሰናበቷቸዉ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡አመልካች ተጠሪ ሲያሽከረክሩ የነበረዉን ተሽከርካሪ የተረከበዉ ተጠሪ ያቀረቡትን የነዳጅ ጥያቄ መሰረት በማድረግ በሌላ ተሽከርካሪ ለመለወጥ እንደሆነ ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡ከሕግ-ዉጭ የሥራ ዉሌ ተቋርጦብኛል የሚል ተከራካሪ ወገን በአሠሪዉ የሥራ ዉሉ ከሕግ አግባብ ዉጭ በሆነ አኳኋን እንደተቋረጠበት ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ የሚያሽከረክሩትን ተሽከርካሪ አመልካች ስለተቀበላቸዉ የማሽከርካር ሥራቸዉን መስራት እንዳልቻሉ በሌላ አነጋገር አመልካች ሥራ እንደከለከላቸዉ ያስረዱ ቢሆንም በዚህ ደረጃ ያስረዱት አመልካች ተጠሪን ከሕግ አግባብ ዉጭ የሥራ ዉላቸዉን አቋርጧል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደረስ አይደለም፡፡

ተጠሪ አመልካች የማሽከረክረዉን ተሽከርካሪ በመረከብ ሥራ ከልክሎኛል የሚሉ ከሆነ ሥራ እንዲሰጣቸዉ በመጠየቅና ምክንያታዊ ለሆነ ጊዜ አመልካች ሌላ ተሽከርካሪ እስከሚሰጣቸዉ በመጠበቅ በሚሰጣቸዉ ተሽከርካሪ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል እንጂ ያለአመልካች ፈቃድ ከሥራ የመቅረት መብት የላቸዉም፡፡ በመቀጠልም አመልካች ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ሥራ ካልሰጣቸዉ በአዋጁ አንቀጽ 32(1/መ እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 12/1 ስር የተደነገገዉን ሥራ የመስጠትና አሠርቶ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ በመደጋገም አለመፈጸሙን በማረጋገጥ እና ይህንንም በጽሁፍ ለአሠሪዉ በማሳወቅ የሥራ ዉሉን ማቋረጥ ከሚችሉ በስተቀር አመልካች ከሕግ-ዉጭ የሥራ ዉሌ ተቋርጦብኛል በማለት ፍርድ ቤት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ብሎ እንዲወሰን ለመጠየቅ የሚችሉበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ የሥራ ክርክር የሚወሰን አካልም በአዋጁ አንቀጽ 32(1/መ እና 2) ስር የተደነገገዉ መስፈርት ሲሟላ የሥራ ዉሉ በሕግ አግባብ ተቋርጧል ብሎ የሚወስንበት ሁኔታ ቢኖርም አሠሪ ሥራ ከልክሏል በሚል ምክንያት ብቻ የሥራ ዉል ከሕግ ዉጭ ተቋርጧል ብሎ ለመወሰን የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡

በመሆኑም አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ከሕግ-ዉጭ በማቋረጥ እንዳሰናበታቸዉ ተጠሪ ካለማስረዳታቸዉም በተጨማሪ አመልካች ሥራ መከልከሉ ከሕግ-ዉጭ ተጠሪን አሠናብቷል የሚያሰኝ ምክንያት ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የሥራ ዉሉ ከሕግ ዉጭ ተቋርጧል በማለት የሰጡት ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 166841 ላይ በቀን 27/05/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 267803 ላይ በቀን 23/07/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ከሕግ-ዉጭ በሆነ አኳኋን ማቋረጡን ተጠሪ ያላስረዱ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ከሕግ-ዉጭ አቋርጧል ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ እና ለተጠሪ ካልተከፈላቸዉ የ1 ወር ደመወዝ በስተቀር የወሰነዉ የተለያዩ ክፍያዎች ተሽረዋል፡፡

1. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 209939

ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ኢስት ዌስት ኢትዮ ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ነ/ፈ. ይፈሩህል ሙጩ - ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ የበጋ እሸት ወልደጻዲቅ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተለያዩ ክፍያዎች ለማስከፈል የቀረበ የአሰሪ እና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2012 ዓ.ም. የተጠሪን የስራ ውል ካቋረጠ በኋላ የ15 ቀን ደመወዝ በመቅጣት ወደ ስራ እንድመለስ በማድረግ ያለአግባብ ላገኝ የሚገባኝን ክፍያ ስላሳጣኝ የአመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ፤ የካሳ እና የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ህዳር 23 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የይርጋ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ተጠሪ በተደጋጋሚ በስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ በገንዘብ ተቀጥተው ከታለፉ በኋላ በድጋሚ በስራ ላይ ባለመገኘታቸው የስራ ውላቸው እንዲቋረጥ መደረጉ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል የተጠሪን የክፍያ ጥያቄ በከፊል ውድቅ በማድረግ ስንብቱ ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው እና በይርጋ በማይታገዱ ክፍያዎች ላይ ክርክሩ እንዲቀጥል ብይን ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የፍሬ ነገር ክርክሩን መርምሮ ስንብቱ ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ በስራ ገበታቸው ላይ ያልተገኙት በህመም ምክንያት መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ለአመልካች በማሳወቅ ፍቃድ ያላገኙ በመሆኑ ከስራ የቀሩት በበቂ ምክንያት ነው ለማለት ስለማይቻል ስንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ ስንብቱ ህጋዊ ሆኖ እያለ አመልካች ተጠሪን ካሰናበተ በኋላ ስንብቱን በመተው ደመወዝ በመቅጣት ወደ ስራ እንዲመለሱ ማድረጉ የስራ ዋስትናን የሚያስጠብቅ እንጂ ተጠሪ ማግኘት የሚችሉትን ክፍያ ለማሳጣት አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የስንብት እና የካሳ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፡፡ የአመት እረፍት የ57 ቀን ብቻ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ይከፈላቸው፡፡ የፕሮቪደንት ፈንድ በተጠሪ ስም የተቀመጠ ካለም ተጠሪ ክሊራንስ አዙረው ሲጨርሱ ይከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ ለ17 ዓመት ሲያገለግሉ 269 ቀናት የአመት እረፍት ነበራቸው፡፡ ተጠሪ የህክምና ፍቃድ ጨርሰው የአመት እረፍት ሲጠይቁ አመልካች ፍቃድ ከልክሏቸዋል፡፡ አመልካች የአመት እረፍት የጠየቀን ሰራተኛ አመቻችቶ እረፍት ማስወጣት እያለበት የራሱን ጥቅም ብቻ በማየት ተጠሪ ከስራ እንዲሰናበቱ ማድረጉ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች የስንብት፣ የካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት መቀጫ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረበው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ የአመት እረፍት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ከጨረሱ በኋላ ተጨማሪ ፍቃድ ሲጠይቁ የድርጅቱ የስራ ሁኔታ አመቺ ባለመሆኑ ተጨማሪ ፍቃድ በመከልከላቸው ከስራ በገዛ ፍቃዳቸው ለ28 ቀን ቀርተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የስራ ውል መቋረጡ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የካሳ እና የመቀጫ ክፍያ እንዲከፈላቸው መወሰኑ እንዲሁም ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው እያለ የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ክፍያን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ሊጣራ ይገባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች ህመምተኛ መሆኔን እያወቀ የአመት እረፍት ስጠይቅ መከልከሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ህመም ላይ ስለነበርኩኝ በስራ ቦታ መገኘት አልቻልኩም፡፡ አመልካች በዚህ ምክንያት ከስራ ማሰናበቱ ስንብቱን ህገ ወጥ ስለሚያደርገው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎችን መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በበኩሉ መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የተጠሪ ስንብት ህገ ወጥ ነው የተባለበትን አግባብ እና ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ከተባለ ለተጠሪ የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው የመወሰኑን አግባብነት ከግራ ቀኙ ክርክር፣ በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም የተጠሪ የስራ ስንብት ህገ ወጥ ነው የመባሉን ተገቢነት ስንመለከት ተጠሪ ያልተጠቀሙበት የአመት እረፍት 259 ቀን እንዳላቸው፣ ተጠሪ በህመም ምክንያት የአመት እረፍት ሲጠይቁ የድርጅቱ የስራ ሁኔታ አይፈቅድም በሚል አመልካች ፍቃድ መከልከሉን፣ ተጠሪ እረፍት በአመልካች ሳይፈቀድላቸው ለ28 ቀን በስራ ላይ ያልተገኙ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት አመልካች የስራ ውል ማቋረጡ በግራ ቀኙ የታመነ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ተጠሪ በህመም ምክንያት ከአመልካች ፍቃድ ሳያገኙ ከስራ መቅረት ይችላሉ ወይስ አይችሉም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 85 ሰራተኛው በህመም ምክንያት ለአሰሪው ማሳወቅ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር አሰሪውን በማሳወቅ እና በመንግስት እውቅና ካለው የህክምና ተቋም የህክምና ፈቃድ በማቅረብ እረፍት የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የህመም ፍቃድ ማግኘት ለሰራተኛው በህግ የተጠበቀ መብት መሆኑን፣ መብቱን ለመጠቀም ግን በቅድሚያ አሰሪውን የማሳወቅ እና የህክምና ፈቃድ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ በሌላ አባባል ህመም ከስራ ለመቅረት በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችለው አሰሪው ስለሰራተኛው ህመም በተቻለ ፍጥነት እንዲያውቅ በማድረግ እና ሰራተኛው ለአሰሪው የህክምና ፈቃድ ማቅረብ ሲችል ብቻ ነው፡፡ ሰራተኛው የህክምና ፍቃድ ቢኖረውም አሰሪውን በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ ያስፈለገበት ምክንያት ሰራተኛው ከስራ ሲቀር የሚፈጠረውን የሰራተኛ ክፍተት በመሸፈን ምርት እና ምርታማነቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በአሰሪው ላይ እንዳይፈጠርበት ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ሰራተኛው ካቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር የማሳወቅ ግዴታውን በመወጣት እና የሀኪም ፍቃድ በማቅረብ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ሳያሟላ በህመም ምክንያት ቢሆንም እንኳን ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ ቢቀር በበቂ ምክንያት ከስራ እንደቀረ ስለማይቆጠር በአዋጁ አንቀጽ 27/1/ለ መሰረት ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በህመም ላይ የሚገኝ ሰራተኛ የሀኪም ፍቃድ ማቅረብ ባይችል አሰሪው ከተስማማ የአመት ፍቃዱን በመጠቀም ከስራ ለመቅረት እንደሚችል ከአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 76 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በአዋጁ አንቀጽ 78/2 መሰረት ሰራተኛው የአመት ፍቃድ መውሰድ የሚችለው አሰሪው የስራውን ባህሪ ታሳቢ አድርጎ በሚያወጣው የእረፍት ድልድል መሰረት ስለሚሆን አሰሪው ካልተስማማ ሰራተኛው በፈለገ ጊዜ ወይም መታመሙን ለአሰሪው ስለገለጸ ብቻ

የአመት ፍቃድ ሊያገኝ አይችልም። በእርግጥ አንድ ሰራተኛ የታወቀ ህመም ካለበት ህመሙ በተቀሰቀሰ ጊዜ የሀኪም ፍቃድ ባይኖረውም አሰሪው ለሰራተኛው የአመት ፍቃዱን በመስጠት እንዲያርፍ ቢያደርግ በአሰሪ እና ሰራተኛ መካከል መልካም ግንኙነትን በማጠናከር የኢንዱስትሪ ሰላም እና የሰራተኛውን ምርታማነት የሚጨምር እንደሚሆን ይታመናል። ነገር ግን ሰራተኛው ለአሰሪው የሀኪም ፍቃድ ሳያቀርብ በህመም ምክንያት ፍቃድ ሲጠይቀው አሰሪው የስራው ሁኔታ አይፈቅድም በሚል ፍቃደኛ ሳይሆን ከቀረ ሰራተኛው በህግ አግባብ መብቱን ከሚያስከብር በስተቀር አሰሪው ፍቃድ እየከለከለው ሰራተኛው በራሱ ፍቃድ ከስራ የሚቀር ከሆነ ያለበቂ ምክንያት ከስራ እንደመቅረት ያስቆጥራል። ይህም በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 27/1/ለ ላይ በተገለጸው አግባብ አሰሪው የሰራተኛውን የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችለው ምክንያት/ጥፋት ይሆናል ማለት ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በህመም ምክንያት ከስራ መቅረታቸውን የገለጹ ቢሆንም ለቀሩበት 28 ቀናት የሀኪም ፈቃድ እንዳልነበራቸው ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን ተጠሪ የህክምና ፍቃድ አለኝ በሚልም ያቀረቡት ክርክር የለም። እንደዚሁም ተጠሪ ካላቸው የአመት ፍቃድ ላይም እረፍት እንዲሰጣቸው አመልካችን ጠይቀው ተከልክለዋል። ተጠሪ የ17 ዓመት የተጠራቀመ 269 ቀን የአመት እረፍት እንዳላቸው ሲታይ አመልካች በአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጁ አንቀጽ 76/2 መሰረት ተጠሪ የአመት ፍቃዳቸውን ተጠቅመው እንዲያርፉ የማመቻቸት ግዴታውን አለመወጣቱን ያሳያል። ይህ መሆኑ ግን ተጠሪ በህግ አግባብ መብታቸውን እንዲያስከብሩ ከሚያስችላቸው በስተቀር አመልካች ሳይስማማ በገዛ ፍቃዳቸው ለ28 ቀን ከስራ ለመቅረት በቂ እና ህጋዊ ምክንያት ሊሆናቸው አይችልም። በመሆኑም ተጠሪ በአመልካች የአመት ፍቃድ ሳይሰጣቸው ከ5 ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ ለ28 ቀናት ከስራ መቅረታቸው በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 27/1/ለ መሰረት ለአመልካች የስራ ውል የማቋረጥ መብት የሚሰጠው በመሆኑ የተጠሪ ስራ ስንብት ህጋዊ ነው። ስንብቱ ህጋዊ ነው ከተባለ አመልካች ከስንብት ክፍያ አንጻር የሚያቀርበውን ቅሬታ መመርመሩ አስፈላጊ ባለመሆኑ ታልፏል።

ሲጠቃለል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ስንብት ህጋዊ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ ህጉን የተከተለ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ሲቀርብለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማጽናት ሲገባው መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

## ው ሳ ኔ

1ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 267770 በግንቦት 6 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል።

2ኛ. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 94490 በየካቲት 4 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

በዚህ መዝገብ ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

ስ/ጥ                                                  የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ፤-206283

ቀን፤- 01/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ጌታቸው ሀይሉ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት- ነ/ፈጅ ቤተልሄም ግርማ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የዲስፕሊን ዉሳኔ በመቃወም የቀረበ ክስ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ነዉ፡፡የክሱ ይዘት ባጭሩ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከታህሳስ 26 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ በከባድ መኪና ሹፌር የስራ መደብ ተቀጥሬ በማገልገል ላይ ሳለሁ ነሐሴ 6 ቀን 2010 ዓ.ም ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ እያሽከረከርኩ እያለ በጅቡቲ ውስጥ አርታ(ዊያ) በተባለ ቦታ የመልከዓ ምድሩ አቀማመጥ አስቸጋሪ ቁልቁለትና መታጠፊያ በሆነበት ቦታ ሌላ መኪና ደርቦ የእኔን መስመር ይዞ በመምጣቱ አደጋውን ለመከላከል በድንገት ፍሬን ሲያዝ አደጋ ያጋጠመ ሲሆን አደጋው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ስለመሆኑ

ከጅቡቲ ሪፐብሊክ የመንገድ ደህንነት የሰጠው የምርመራ ሪፖርት የሚያረጋግጥ ቢሆንም የተጠሪ ድርጅት የዲስፕሊን ኮሚቴ ከባለሙያ ሪፖርት ውጭ እና አመልካች ሃሳብ ባልሰጠሁበት ሁኔታ በንብረት ላይ የደረሰው አደጋ ግምት ዋጋ ብር 2,820,778.92 መሆኑን የዚህን ግምት ዋጋ 3% ሂሳብ ከአመልካች ደመወዙ በየወሩ 1/3ኛ እየተቀነሰ እንዲከፍል ውሳኔ አስተላልፎ ከሀምሌ ወር 2011 ዓ.ም ጀምሮ እየተቆረጠ ይገኛል፣ በመሆኑም በተጠሪ ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት በመድን ፖሊሲው ሽፋን መሰረት ንብረቱ ተጠግኖ እያለ ያለአግባብ የአደጋ ተጠያቂና ጥፋተኛ በማድረግ የተወሰነብኝ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲነሳልኝ እና የአደጋው ግምት 3% እንዲከፍል የተወሰነብኝ ከህግ ውጭ ነው ተብሎ የተቆረጠውም እንዲመለስልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቆ ተጠሪ በበኩሉ የፖሊስ ማስረጃ አመልካች አደጋውን ማስቀረት ወይም መቀነስ በሚችልበት ሁኔታ አደጋው የተከሰተ በመሆኑ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነዉ በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ፣አመልካች ለዲስፕሊን ክስ የጽሁፍ መልስ፣ ከፖሊስ ሪፖርት ጋር እንዲሁም ከህብረት ስምምነት ድንጋጌ ጋር በማጣራት የፈፀመው ጥፋት ከስራ የሚያሰናብተው ቢሆንም ያለፈ መልካም አገልግሎት ግምት ውስጥ በማስገባት አመልካች ላይ የተወሰደው አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ ተገቢ እና ህጋዊ በመሆኑ ሊነሳ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ስራቸው ሹፌር እንደመሆኑ ከስራቸው ጋር በተያያዘ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ መኪናውን የሚያሽከረክሩበትን አግባብ ከአካባቢው አየር ሁኔታ እና ከመልከዓ ምድሩ ጋር ባገናዘበ መልኩ መሆን ያለበት መሆኑን እና በጠመዝማዛና ቁልቁለታማ በሆነ መንገድ በዝግታና በጥንቃቄ ማሽከርከር የሚጠበቅበት ሙያዊ ግዴታ ነው፣ ስለዚህ በጠመዝማዛና ቁልቁለታማ በሆነ መንገድ ላይ መነዳት ያለበት በ2ኛ እና በ3ኛ ማርሽ እንደሆነ በዚህ ማርሽ ከተነዳ ከፊት ለፊት አደጋ ቢመጣበትም የእጅ ፍሬን በመያዝ መኪናውን አደጋ ሳይደርስ በቀላሉ ማቆም እንደሚችል አመልካችም ተጠሪም ያቀረባቸው ምስክሮች ያስረዱ ሲሆን አመልካች ከጅቡቲ ፖሊስ የመንገድ ደህንነት የተፃፈው ሪፖርትም ከሳሽ ሲያሽከረከሩት የነበረው መኪና ወደ ቀኝ መውደቁን ከመግለጽ ባለፈ አደጋው የተከሰተበትን ምክንያት የሚያመላክት ባለመሆኑ እና አመልካች በቸልተኝነት ጉዳት አለማድረሳቸውን የሚያስተባብል ያቀረቡት ማስረጃ ባለመኖሩ ተጠሪ ድርጅት ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት በአመልካች ቸልተኝነት ነው በማለት፣ ቅጣቱን በተመለከተ በድርጅቱ ህብረት ስምምነት መሰረት በአመልካች ጥፋት በድርጅቱ ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት ከስራ የሚያሰናብት ቢሆንም የቅጣት ማቅለያ በማድረግ 3% እንዲቀጡ መወሰኑ የሰራተኛውን ጥቅም ያስጠበቀ በመሆኑ ቅጣቱ የተወሰነው የህብረት ስምምነት አንቀጽ 31 (3) በሚፈቅደው መንገድ በመሆኑ ህጋዊ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበዉን ይግባኝ ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ግድፈት የለበትም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞበታል፡፡

አመልካች ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤ በድርጅቱ ህብረት ስምምነት መሰረት ጥፋቱ ከ250,000 ብር በላይ መሆኑ ከስራ ማሰናበት እንጂ በገንዘብ እንዲቀጣ ማድረጉ የህግ ስህተት ነው፣ ተጠሪ ይህንን ያደረገው ለአመልካች በማሰብ ሳይሆን አደጋው መድረሱ ካወቀበት ከ06/12/2010 ዓ.ም እርምጃ እስከወሰደበት 28/09/2011 ዓ.ም ድረስ ከ30 ቀናት በላይ በመሆኑ ነው፣በተጨማሪም የጥገና ወጪው ብር 353,162.81 ሆኖ እያለ በተሽከርካሪው ላይ ያልደረሰውን ግምት ጨምሮ ገንዘብ ለማስከፈል የወሰነው ቅጣት ህግና የህብረት ስምምነት ተቃራኒ በመሆኑ የህግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡በህብረት ስምምነቱ የተፈቀደውን በመቃረን በሰዓት 40 ኪ/ሜ ስለማሽከርከር ማስረጃ ሳይቀርብ ማስረጃ እንደቀረበ ተደርጎ በተሽከርካሪው ላይ ለደረሰው ጥገና ግምት እያለ እንዳልቀረበ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና መርህንና ተገቢውን የስራና ሰራተኛ ጥቅም ያገናዘበ መሆን አለመሆኑ ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ባጭሩ የተጠሪ ንብረት የሆነው ከባድ ተሽከርካሪ በአመልካች ቸልተኝነት በመገልበጡ ምክንያት የደረሰው ጉዳት መጠን ለመጀመሪያ ጊዜ የማስጠገኛ ግምት ከቀረበ በኋላ ፕርፎርማ ሲሰበሰብ ግን አስቀድሞ በቀረበው የዋጋ ግምት ተሽከርካሪው ለማስጠገን የማይቻል መሆኑን ተሽከርካሪውን ለማስጠገን በወቅቱ ዋጋ ብር 2,820,778.92 መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ይህም በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ተጣርቶ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በአመልካች በኩል ግምቱ ከዚህ በታች ስለመሆኑ ያቀረበው ምንም ማስረጃ ባለመኖሩ የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡በስር ፍ/ቤት የግራ ቀኞችን ምስክሮች ሲሰሙ በተጠሪ በኩል የቀረቡ ምስክሮች አመልካች አደጋው ባደረሱበት ወቅት በሰዓት 40 ኪ/ሜ ፍጥነት ሲያሽከረክሩ የነበሩ ስለመሆኑ አመልካች ራሳቸው ሞልተው የፈረሙት ወደ ኢትዮጵያ መድን ድርጅት የተላከ ቅጽ በችሎቱ ቀርቦ ተረጋግጧል፡፡የቀረቡ ምስክሮችም አደጋው የደረሰበት ቦታ ላይ ፍጥነት በሰዓት ከ30 ኪ/ሜ በታች በማድረግ በከባድ ማርሽ ተጠቅሞ ቢያሽከረክር ማንኛውም አደጋ ቢፈጠር ያለምንም ችግር ተሽከርካሪ ማቆም እንደሚቻል እና በፍጥነት ላይ ከሆነ በድንገት ፍሬን ሲያዝ የመንሸራተት ወይም የመገልበጥ አደጋ ሊደርስ እንዲሚችል እና አደጋው የደረሰው በአመልካች ጥንቃቄ ጉድለትና ቸልተኝነት መሆኑን አስረድቷል፡፡አመልካች አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ያስረዳ ነገር የለም፣ ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.111839 ላይ የሰጠው ትርጉም የተከተለ በመሆኑ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት የለዉም፡፡የዲስፕሊን የቅጣት እርምጃ በተመለከተ ጥፋቱ ከስራ የሚያሰናብት ቢሆንም ከዚህ በፊት የነበረው ፀባይ፣ የአግልግሎት ጊዜና የቤተሰብ አስተዳዳሪነት ከግምት በማስገባት ቅጣቱን በመቀነስ የአደጋዉ ግምት ዋጋ 3% በየወሩ 1/3ኛ እየተቆረጠ እንዲከፍል ማድረጉ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት

የለም ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብ ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበነዉ አመልካቹ የዲስፒሊን ዉሳኔዉ በመቃወም ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያቀረበዉ የተፈጸመዉ ጥፋት ከባድ ነዉ ከተባለ ከስራ ማሰናበት እንጂ ይህንን ያህል ገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል እና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል ዉሳኔዉ በፍርድ ቤት እንዲታረም ነዉ፡፡ተጠሪም በበኩሉ በአመልካች ቸልተኝነት የደረሰዉ ጉዳት ከባድ በመሆኑና ጥፋቱ ከስራ የሚያሰናብት መሆኑን ነገር ግን አመልካች የሰጠዉ የረጅም ጊዜ አገልግሎት እና የነበረዉ መልካም ባህርይ ከግምት በማስገባት ከስራ ከማሰናበት በመለስ ያለዉ ቅጣት እንደተወሰነበት እና ይህም ለአመልካች ጥቅም ተብሎ የተደረገ ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡

በመሠረቱ አንድ ሠራተኛ ለስራው የተሰጡትን መሣሪያዎችና እቃዎች ሁሉ በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 13/3/ ስር የተመለከተ ሲሆን በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 27/1/ሸ/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ሆኖም ከባድ ቸልተኝነት የሚለውን ቃል መለኪያ በተመለከተ ህጉ በግልጽ አያሣይም፡፡ይሁን እንጂ ቸልተኝነት የጥንቃቄ ጉድለት እንደመሆኑ መጠን የጥንቃቄ ዓይነትና ደረጃ እንደየድርጊቱና አድራጊው የስራ ድርሻ አኳያ በመመልከት ምላሽ ማግኘት እንደሚገባ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 41115 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ጠመዝማዛና ቁልቁለታማ በሆነ መንገድ ላይ በተመጣጣነ ማርሽ አስሮ ባለማሽከርከሩ አደጋው መድረሱ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አመልካች ማስተባበያ ማስረጃ ያላቀረበበት ጉዳይ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶችም ጉዳቱ ሊደረስ የቻለዉ በአመልካች ቸልተኝነት ስለመሆኑ አረጋግጠዋል፡፡በመሆኑም የአመልካች የጥፋት ደረጃ "ከባድ ቸልተኝነትን" ሊያቋቁም የሚችል መሆን አለመሆኑን ከስራው ባህርይ አንፃር መመልከት እና የቀረበዉን ማስረጃ በማመዛዘን በቁልቁለት መንገድ ላይ በከባድ ማረሽ ማሽከርከር እየተገባዉ በቀላል ማርሽ በሰዓት በ40 ኪ.ሜ ፍጥነት በማሽከርከር ጉዳት እንዲደረስ ስለማድረጉ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ጉዳይ በመሆኑ ይህንኑ ከመቀበል አልፎ ይህ ሰበር ችሎት የፍሬ ነገር ጉዳይ የመመርመር ሃላፊነት የለበትም፡፡በዚህም ምክንያት የድርጅቱ ንብረት ላይ የደረሰዉን ጉዳት ለማስጠገን ብር 2,820,778.92 የተገመተ ስለመሆኑ ከመድን ድርጅት የቀረበዉን ማስረጃ መሰረት በማድረግ አመልካች አስተዳደራዊ ዉሳኔ መስጠቱን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡በሌላ በኩል የጉዳቱን ለማስተካካል ወይም ለማስጠገን መጀመሪያ የቀረበዉ ግምት ብር 353,162.81 ስለመሆኑ አመልካች ያቀረበዉ ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያላገኘ ቢሆንም በህብረት ስምምነት ከተመለከተዉ

ጣሪያ በላይ በመሆኑ የመጠን ጉዳይ መመርመር አስፈላጊ አይደለም፡፡ስራ ላይ ባለዉ የድርጅቱ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 33/1/ ተራ ቁጥር 24 ላይ በተደነገገዉ መሰረት የከባድ መኪና አሽከርካሪ በራሱ ጥፋት በድርጅቱ ንብረት ላይ ከብር 250,000/ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ/ በላይ ጉዳት ማድረሱ በዲስፕሊን ኮሚቴ ከተረጋገጠ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከስራ የሚሰናበት ስለመሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱት ከመሆኑም በተጨማሪ በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ የተገለጸ ጉዳይ ነዉ፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች ጥፋት በቀጥታ ከስራ ለማስናበት የሚያበቃ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡አመልካችም አጥብቆ የሚከራከረዉ ጥፋቱ ለስንበት የሚያበቃ ነዉ ከተባለ ተጠሪ ከስራ ሊያሰናብተኝ ሲገባዉ በገንዘብ መቅጣቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት ነዉ፡፡

በዚህ ረገድ የዲስፕሊን ኮሜቲ የቅጣት ዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ የድርጅቱን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 33.3 ተራ ቁጥር 33.3.6 ሲሆን በዚህም መሰረት የከባድ መኪና ሾፌር ከብር 100,000 እስከ 200,000 ድረስ ለሚደርስ አደጋ ለመጀመሪያ ጥፋት ሲሆን ሰራተኛዉ የጉዳቱን ግምት ዋጋ 3% በየወሩ 1/3ኛ ከደመወዙ እንዲከፍል የሚደነግግ መሆኑን መሰረት በማድረግ የአመልካችን የቀደመ መልካም ባህርይና አገልግሎት ታሳቢ በማድረግ እንዲሁም የድርጊቱን ከባቢያዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ቅጣቱ ቀሎ እንዲወሰን የተደረገ ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ምንም እንኳን አመልካች ያደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ቢሆንም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተጠቅመዉ ለአነስተኛ ጉዳት ተብሎ በተገመተዉ ወሰን ዉስጥ ቅጣት መወሰኑ ሲታይ በአንድ በኩል ሰራተኛዉን በስራ ላይ በማቆየት የሥራ ዋስትናዉን ማስከበር በሌላ በኩል ለደረሰዉ ጉዳት ደግሞ በህብረት ስምምነት የተቀመጠዉን ገንዘብ እንዲከፍል በማድረግ የሁለቱንም ወገን ጥቅም ለማስጠበቅ ያለመ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ ቅጣቱ ቀሎ መወሰኑ ከቅጣት ዓላማ አንጻር ሲታይ ስህተት ነዉ የሚያሰኝ ባይሆንም የገንዘብ መጠኑ ከፍተኛ ከመሆኑ አኳያ አመልካች ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ መጠን ያለዉ ገንዘብ ከደመወዙ እንዲቆረጥ የሚያደርግ ዉሳኔ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ ግን በኑሮዉ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጠር መሆኑን መገምት አዳጋች አይሆንም፡፡ከላይ የተጠቀሰዉ የድርጅቱ የህብረት ስምምነት ድንጋጌ የገንዘብ መጠኑን እስከ ብር 200,000 ድረስ ሲገድብ ታሳቢ ያደረገዉም የደረሰዉ ጉዳት መጠን ከዚያ በላይ ሲሆን ጥፋቱ ከባድ ስለሚሆን ሰራተኛዉን ከስራ በማሰናበት ለደረሰዉ ጉዳት ግን በህግ አግባብ መጠየቅ የሚቻልበትን ሁኔታ መኖሩን ከግምት ያስገባ ነዉ፡፡

ይሁንና የዲስፕሊን ኮሚቴ ዉሳኔ የሁለቱንም ወገን ጥቅም በማመዛን የተወሰነ ነዉ የሚባል ከሆነ አመልካች ከደመወዙ እየተቀነሰ ሊከፍል የሚገባዉ በህብረት ስምምነት አንቀጽ 33.3.6 መሰረት እስከ ብር 200,000 ድረስ ያለዉን ጉዳት እንጂ ከተቀመጠዉ ጣሪያ በላይ ሊሆን አይገባም፡፡ከዚህ በላይ ለሆነዉ ገንዘብ ሊጠየቅ የሚገባዉ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት የፍትሓብሄር ክስ ቀርቦ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክርና በማስረጃ ተጣርቶ ሲወስንበት ብቻ ይሆናል፡፡ጉዳዩ ከዚህ አኳያ ሲታይ አስተዳደራዊ ዉሳኔዉ አስቀድሞ በህብረት ስምምነት ያልተደነገገዉን ሁኔታ እና በሰራተኛዉ ላይ ከፍተኛ ጫና በሚፈጥር አግባብ ይልቁንም ተጠሪን ተጠቃሚ የሚያደርግ ዉሳኔ በመሆኑ የህግ መሰረት የሌለዉና ፍትሃዊነትም የጎደለዉ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የዲስፕሊን ኮሚቴ ዉሳኔ ተገቢነትና ፍትሃዊነት ሲመረምሩ ቅጣቱ ቀሎ መወሰኑ በመርህ ደረጃ ለሰራተኛዉ ጥቅም ነዉ የሚለዉን መሰረት በማድረግ ዉሳኔዉን ማጽናታቸዉ ተገቢ ቢሆንም የገንዘብ ቅጣቱ በህብረት ስምምነት ከተመለከተዉ ጣሪያ ወሰን ማለፍ አለማለፉን ሳያረጋገጡና ጉዳቱንም ሳያመዛዝኑ ስራ ላይ ያለዉን የህብረት ስምምነታቸዉን ዓላማ እና ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተላቸው በመ/ቁ/75575 እና 250187 ላይ የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/የተጠሪ መ/ቤት በአመልካች ላይ ያስተላለፈዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ሀ/አመልካች በከባድ ቸልተኝነት በተጠሪ ንብረት ላይ ላደረሰዉ ጉዳት ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነዉ ብለናል፡፡

ለ/በአመልካች ጥፋት ምክንያት በተጠሪ ንብረት ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ማስጠገኛ የወጣዉን ወጪ ብር 2,820,778.92 ዉስጥ 3% በየወሩ 1/3ኛ ከደመወዙ አመልካች እንዲከፍል በዲስፕሊን ኮሚቴ የተሰጠዉ ዉሳኔ በድርጅቱ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 33.3 ተራ ቁጥር 33.3.6 መሰረት ተሻሽሎ ብር 200,000 ድረስ ያለዉን ብቻ 3% በየወሩ 1/3ኛ ከደመወዙ እንዲከፍል በማለት ወስነናል፡፡

ሐ/ለአመልካች የተሰጠዉ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ላይ ስህተት ባለመኖሩ ጸንቷል፡፡

መ/አመልካች ያደረሰዉ ጉዳት መጠን (ግምት) በፊደል ለ ላይ ከተጠቀሰዉ መጠን በላይ ነዉ የሚል ከሆነ ተጠሪ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብቱን ይህ ዉሳኔ የሚገድብ አይደለም ብለናል፡፡

3ኛ/በዚሁ ዉሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ለሚመለከተዉ ክፍል ይተላለፍ፡፡ይጻፍ፡፡

4ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡</u>

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፤

**የሰ/መ/ቁ.** 212603

ሰኔ 02 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** የኢትዮጵያ አየር መንገድ

**ተጠሪ-** አቶ ተከስተ ካሴ

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ እ.አ.አ. ከቀን 22/04/2020 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 42,863.37 እየተከፈለኝ በአውሮፕላን ጥገና አሰልጣኝነት ሳገለግል ቆይቻለሁ፡፡ ከመስከረም 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በድርጅቱ ውስጥ በተቋቋመው የሰራተኛ ማህበር ውስጥ ምክትል ፀኃፊ በመሆን እያገለገልኩ ቆይቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ስለእኔ እውነት ያልሆነ መረጃ በማስተላለፍ ስም እና ዝናዬን አጥፍተሃል፣ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር በስራ ቦታ መተባበር እና ሰላማዊ የስራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት የስራ ውሌን አቋርጦታል፡፡ ከስራ ስሰናበት በህብረት ስምምነቱ መሠረት በተቋቋመው ኮሚቴው ውስጥ የሰራተኛ ማህበር ተወካይ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ያልተከፈለኝ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ፤ ወደ ስራ ልመለስ የማልችልበት አግባብ ካለ ደግሞ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሚያዝያ ወር ሙሉ ደሞዝ፣ እ.አ.አ. የ2020 ዓ.ም የዓመት እረፍት ክፍያ እንዲከፍለኝ እና የስራ ልምድ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪን ከስራ ያሰናበትናቸው የሰራተኛ ማህበር አባል በመሆናቸው ሳይሆን የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም በድርጅታችን መልካም ስም እና ዝና ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄዳቸውና በስራ ቦታ ላይ ሊኖር የሚገባውን መልካም የስራ ግንኙነት እና መግባባት የሚያበላሽ ተግባር በመፈፀማቸው ነው፤ ለአብነት ያህል የኛ ቲዩብ ከተባለ ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ አመልካች ድርጅት ሰራተኛ ሲቀጥርም ሆነ ሲያሰናብት መርህ የለውም፣

የድርጅት ሰራተኞች ለድርጅቱ አመራሮች ብቻ ተገዢ እንዲሆኑ ነው የሚሰራው፤ ድርጅቱም ሆነ አመራሩ የሚያስበው ለውጪ ሃገር ዜጎች እንጂ ኢትዮጵያዊ ለሆነው ሰራተኛ አይደለም፤ የኮቪድ 19 ስርጭትን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ሰራተኞችን በመቅጣት በፍርሃትና በመርበትበት እንዲኖር እያደረገ ነው ሲሉ ስም አጥፍተዋል፤ ይህ የተጠሪ ድርጊት ከስራ የሚያስናብት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፤ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው እንኳን ቢባል በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው መተማመን በእጅጉ የሻከረ በመሆኑ ተጠሪ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የሰጡት ቃለ-ምልልስ የአመልካች ድርጅትን ስም የሚያጠፋ፣ መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፍ ወይም የሚያጥላላ ሳይሆን ያላቸውን የመናገር ነፃነት ተጠቅመው ያደረጉት እንደሆነ ከይዘቱ መረዳት ተችሏል፤ አመልካች በዚህ ምክንያት ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱ ህገ-ወጥ ስለሆነ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደሞዝ ብር 257,174.22 ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው ይመለሱ በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 377 መሠረት ተሠርዞበታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 07/12/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው 08 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ማህበር ጣልቃ መግባትን የሚመለከተውን ክስ ከተጠሪ ስንብት ጥያቄ ጋር አጣምረው ማቅረባቸው ተገቢ ነው ማለቱ፤ ተጠሪ ቃለ-ምልልስ ያደረጉት በግላቸው ሳይሆን ማህበሩን ወክለው ነው መባሉ፤ ቃለ-ምልልሱ የተጋነነ ቢሆንም ካለው ሁኔታ አንፃር እውነት መሆኑን መረዳት ይቻላል ሲል የስር ፍርድ ቤት በደፈናው ድምዳሜ ላይ መድረሱ፤ እንዲሁም ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለሱ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የአመልካች እና የተጠሪን የሻከረ የስራ ግንኙነት ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ተጠሪ ወደ ስራ ይመለሱ በማለት የተወሰነበት አግባብ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት አመልካች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 15/02/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ተጠሪ ንግግሩን ያደረጉት ከማህበሩ በተሰጣቸው ውክልና እንጂ በራሳቸው አይደለም፤ አመልካችም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 26 በመተላለፍ የሰጠው ስንብት አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ሲል ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው፤ ተጠሪ በቃለ-ምልልስ ወቅት ያነሳኟቸው ጉዳዮች እውነት መሆናቸውን በማስረጃ ጭምር በስር ፍርድ ቤት አረጋግጫለሁ፤ ተጠሪ ያደረጉት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ከማህበሩ በተሰጣቸው ውክልና ላይ የተመሠረተ ሲሆን በግላቸው ከአመልካች ጋር ምንም አይነት የሻከረ ግንኙነትም ሆነ መቃቃር በሌለበት አመልካች የተበላሸ

የስራ ግንኙነት ያለን በመሆኑ ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀው ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆን አለመሆኑን? ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢነቱን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ አመልካች ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደሥራ እንዲመልሳቸው፤ ይህ ካልሆነም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የአመልካች ተግባር ያልሆነውን ሀሰተኛ መረጃ በመገናኛ ብዙኂን በመግለጽ መልካም ስምና ዝናውን የሚያጎድፍ ተግባር በመፈጸማቸውና ንብረት ጥቅሙ ላይ ጉዳት በማድረሳቸው ምክንያት የሥራ ውላቸው የተቋረጠ ስለሆነ የሥራ ሥንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል፡፡

ሠራተኛ የአሠሪው ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ ተግባር ከፈጸመ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል ድርጊት ስለመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሽ) ላይ ተመልክቷል፡፡ የአሠሪውን ሥም ማጥፋትም ሥራው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ድርጊት በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ በሠራተኛ ማሕበር አመራርነታቸው ሳይሆን በመገናኛ ብዙኂን በመጠቀም የአመልካች ደርጅት መልካም ስምና ዝና ላይ

ሀሰተኛ የሥም ማጥፋት ዘመቻ የሚያካሂድ ቡድን ላይ ዋና ተዋናይ ሆነው አመልካች የሠራተኛውን ክብር የማይጠበቅ፣ ሕገ-ወጥ ፖሊሲ ተቀርጾ ሠራተኛ ላይ በደል እንደሚፈጸም፣ አመራሩ ከሕግ በላይ ነን የሚሉና በማን አለበኝነት መንፈስ የሚመሩ ግለሰቦች ናቸው፣ ሕግን ያልተከተለ የውጭ ምደባ እንደሚደረግ፣ ምደባ በሥራ አፈጻጸም ሳይሆን ከአመራር ጋር ባለ ቀረቤታና ቁርኝት እንደሚፈጸም፣ የበረራ አስተናጋጆች ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ያልተገባ ድጋሜ ክፍያ እንደሚፈጸም በማለት ሀሰተኛ እና ስም የሚያጠፋ መረጃ ሰጥቷል የሚል ሲሆን ተጠሪ  በበኩላቸው በሠራተኞች ማሕበር ውስጥ በምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ እየሰራሁ እያለ ማሕበሩን በመወከል የተገለጸ ነው፣ የአመልካችን ስም የሚያጎድፍ ሆነ የሠራተኛውን ሰላማዊ ግንኙነት የሚያጠፋ ተግባር ባልተፈጸመበት የተሳሳተ መረጃ ሰጥተሃል፣ ሰላማዊ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት ከግንቦት 04 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ከስራ ማሰናበቱ ሕገ-ወጥ ስንብት ነው የሚል ነው፡፡

የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመለየት፣ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን ኃላፊነት የተሰጠው የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና ተጠሪ የሰጡትን ቃለምልልስ ሲዲዉን አስቀርቦ በመመልከት ተጠሪ ቃለ ምልልሱን ያደረጉት በሠራተኛ ማሕበሩ ተዋካይ በመሆናቸዉ እንጂ በግል ያደረጉት አይደለም፣ በተጨማሪም በሰዓቱ ተጠሪ ሲናገሩ የነበሩት በግላቸዉ ስለደረሰባቸዉ በደል ሳይሆን ሠራተኛዉ በአጠቃላይ ችግሮች አሉበት የሚል ይዘት ያለዉ መሆኑን እና ተጠሪ በቃለ ምልልሱ የገለፃቸዉ ጉዳዮች አለመከሰታቸዉን አመልካች ያስረዳበት ሁኔታ አለመኖሩን፣ ተጠሪ በቃለ ምልልሱ የተናገሩት የግል አስተያየታቸዉ ነዉ ቢባል እንኳን የአመልካችን ድርጅት ስም የሚያጠፋ እና የሚያጥላላ ሳይሆን ተጠሪ ያላቸዉን የመናገር ነፃነት ተጠቅመዉ ያደረጉት እንደሆነ ከይዘቱ መረዳቱን ጠቅሶ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት የፈጸመ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተደረገው የሕብረት ሥምምነት አባሪ ክፍል አንድ ንዑስ ክፍል ሀ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ስምና ዝና የሚያጎድፍ፣ መልካም ግንኙነት የሚያሻክር ከባድ ጥፋት መፈጸሙ ሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ድንጋጌ መጣሱን የሚያስረዳ ሳይሆን ተጠሪ የማሕበሩ ተወካይ በመሆናቸዉ በማሕበሩ አባላት ላይ ደርሰዋል ያሉትን የመብት ጥሰቶችና ግድፈቶች

በመግለጻቸው ከሥራ መሰናበታቸው ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ነው በማለት መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

ወደ ሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ ተጠሪ ወደሥራቸው እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበውን የሠበር አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(1)(2) የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ በአሠሪው የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደሥራው እንዲመለስ ሊወሰን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ሠራተኛው ወደሥራ ሊመለስ የማይችለው ከሥራው ጠባይ ግንኙነት የተነሳ ወይም ከክርክር ሂደት ከወሰደው ግንዛቤ በሥራ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ያስከትላል ተብሎ በፍርድ ቤቱ ሲታመን እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 43(3) ላይ ተደንግጓል፡፡ ከፍተኛ ችግር የሚለው የሕጉ አነጋገር ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት ሠራተኛውን ወደሥራው እንዳይመለስ ማድረግ የማይችል መሆኑን እና የሚያስከትለው ጉዳት ጉልህ የሆነ መሆን እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይህም ሕግ አውጭው በአንድ በኩል የሥራ ዋስትና ማረጋገጥ ለሠራተኛው ሆነ ለሀገር መሠረት የሆነውን የሠራተኛውን ቤተሰብ መጠበቅ እንዳለበት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል የሥራ ሁኔታውን እና የኢንዱስትሪውን ሠላም ማስጠበቅ ለምርታማነት መሠረት መሆኑን በመገንዘብ በሁለቱ እሳቤዎች መካከል ጉዳዩ እንዲገዛ የፖሊሲ ውሳኔ ላይ መድረሱን እና ጉዳዩም የፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ምክንያታዊ በሆነ አግባብ እንዲጠቀም ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ግራቀኙ ተከራካሪዎችም በተለይም አሠሪው ፍርድ ቤቱን ለማሳመን ሠራተኛው ወደሥራ ቢመለስ የሚስከትለውን ጉልህ የሆነ ጉዳት ማሳየት ይኖርበታል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የአውሮፕላን ጥገና ባለሙያ ሲሆኑ ከአመልካች አስተዳደር ጋር አለመግባባት መኖሩ ከሥራ ድርሻቸው አንጻር ወደሥራ መመለሳቸው አመልካች ላይ ጉልሕ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 37454 የሠጠው አስገዳጅ ትርጉም ሠራተኛው የጥበቃ ሠራተኛ መሆኑ እንዲሁም ከአለቆቹ ጋር በተለያየ ጊዜ ግጭት የሚፈጥር መሆኑና በእጁም ትጥቅ ያለ መሆኑ የሥራ ውሉን ለማስቀጠል የማይቻል መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የአሠሪው ሠላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ድርጅትን ጠቅላላ ንብረት ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሠው መሆኑን ግምት ወስጥ በማስገባት ወደሥራ ሊመለስ እንደማይገባ የተወሰነበት ነው፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁ. 64079 የተወሰነውም ገንዘብ ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ መሆኑን በመገንዘብና ጥፋት ፈጽሟል የተባለው ከሥራ ኃለፊነቱ ጋር በተያያዘ በመሆኑ፤ ከአሠሪው ጋር ያለው መተማመን ከቀነስ ባለበት ኃላፊነት ወደሥራ መመለስ መልካም የሥራ ግንኙነት አይፈጥርም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር የተያያዘ ጥፋት ፈጽሟል ያልተባለ በመሆኑና ቀደም ሲል በዚህ ችሎት ከተወሰኑት ጉዳዮች ጋር የፍሬ ነገር ልዩነት ያለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ወደሥራ ቢመለሱ ሥራው ላይ ያለው ከፍተኛ ጉዳትን አመልካች ያላሳየ ስለሆነ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ብለናል፡፡ በሌላ በኩል በአሰሪና ሠራተኛ

አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(5) መሠረት ተጠሪ ወደሥራው እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ታይቶ የጸና በመሆኑ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል ብለናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117180 ላይ ህዳር 13 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 274582 ላይ ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. የሰበር አጣሪ ችሎት ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 213472

ቀን፡- ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ - ነ/ፈጅ ኃ/ማርያም ብርሃኔ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ማርቆስ የሱወርቅ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በግል የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሥራ ውል መቋረጡ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት በአውሮፕላን ጥገና ባለሙያነት በወር ብር 20,805.89 እየተከፈለኝ ስሰራ ነበር፤ በተጨማሪም በሠራተኞች ማሕበር ውስጥም በምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ እየሰራሁ እያለ ማሕበሩን በመወከል የተገለጸውን በግል ደረጃ የተሰጠ መረጃ በማድረግ፣ የአመልካችን ስም የሚያጎድፍ ሆነ የሠራተኛውን ሰላማዊ ግንኙነት የሚያጠፋ ተግባር ባልተፈጸመበት የተሳሳተ መረጃ ሰጥተሃል፣ ሰላማዊ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት ከግንቦት 04 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ከስራ ማሰናበቱ ሆነ በዲሲፕሊን ኮሚቴው በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ከሠራተኛ ማሕበር ሁለት ተወካዮች በሌሉበት መወሰኑ ሕገ-ወጥ ስንብት ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደሥራ እንዲመልሰኝ፤ ይሕ ካልሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች ያቀረበው መልስ ተጠሪ በሠራተኛ ማሕበር አመራርነቱ ሳይሆን በመገናኛ ብዙኃን በመቀጠም የአመልካች ደርጅት መልካም ስምና ዝና ላይ ሀሰተኛ የሥም ማጥፋት ዘመቻ የሚያካሂድ ቡድን ላይ ዋና ተዋናይ ሆኖ ነው፡፡ ድርጊቱ የሥራ ቦታ ላይ መልካም ግንኙነትን የሚያበላሽና በድርጅቱ ንብረት ላይ የሚፈጸም ጉዳት ነው፡፡ ከናሁ ቲቪ ጋር ባደረገው ቃለመጠየቅ አመልካች የሠራተኛውን ክብር የማይጠብቅ፣ ሕገ-ወጥ ፖሊሲ ተቀርጾ ሠራተኛ ላይ በደል እንደሚፈጸም፣ አመራሩ ከሕግ በላይ ነን

የሚሉና በማን አለበኝነት መንፈስ የሚመሩ ግለሰቦች ናቸው በማለት የተሳሳተ መረጃ ሰጥቷል። ፊደል ፖስት ከተባለ ማሕበራዊ ሚዲያና በናሁ ቲቪ ሕግን ያልተከተለ የውጭ ምደባ እንደሚደረግ፣ ምደባ በሥራ አፈጻጸም ሳይሆን ከአመራር ጋር ባለ ቀረቤታና ቁርኝት እንደሚፈጸም፣ የበረራ አስተናጋጆች ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ያልተገባ ድጋሜ ክፍያ እንደሚፈጸም በማለት ሀሰተኛ እና ስም የሚያጠፋ መረጃ ሰጥቷል። ጉዳዩም በዲሲፕሊን ኮሚቴ የታየ ሲሆን የሠራተኛ ማሕበሩ በአግባቡ ያልተደራጀና አድራሻው ስለማይታወቅ የሰራተኛ ማሕበር ተወካይ አልተገኙም። ስንብቱ በተጠሪ ጥፋት ምክንያት የተደረገ ስለሆነ ሕጋዊ ነው፤ ወደሥራ ሊመለስ አይገባም። የ21 ቀን ደመወዝና የ25 ቀናት ዓመት ዕረፍት ያልተከፈለው ክሊራንስ ባለማቅረቡ ነው ብሏል።

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117189 የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት፣ የተቀረጸውን ድምጽ በማዳመጥ ተጠሪ የአመልካች ድርጅት መሠረታዊ የሠራተኞች ማሕበር ምክትል ሊቀመንበር ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳዩ ሚኒስቴር የተጻፈው ደብዳቤ ያስረዳል። የሠራተኛ ማሕበሩ የሥራ አስፈጻሚ አባላት መጋቢት 21 ቀን 2012 ዓ/ም ባደረጉት ስብሳባ ማሕበራቸውና የማሕበሩ አባላት ላይ በአመልካች ድርጅት እየደረሱ ነው የሚሉትን ሕገ-ወጥ የመብት ጥሰቶች በተመለከተ የማሕበሩ ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር(ተጠሪ) እና ምክትል ጸሐፊ ለተለያዩ የመንግስት አካላትና የሰራተኛ ጉዳይ ለሚመለከታቸው መንግስታዊ ላልሆኑ ማሕበራት በሠራተኛ ማሕበሩ ሥም መግለጫና ማብራሪያ እንዲሰጡ በሚዲያ ጭምር ቃለምልልሶችን እንዲያደርጉ አቅጣጫ ማስቀመጡንና በዚህ መሠረት ተጠሪ ከናሁ ቲቪ፣ ፊደል ፖስት ጋር ያደረጉት ቃለምልልስ በሠራተኛ ማሕበሩ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት የተፈጸመ እንጂ በግል ያላደረጉት ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ተረድቷል። አመልካች በሚዲያ የተሰጠው ማብራሪያ በጥቅሉ አመልካችን የማይወክሉና የአመልካች ድርጊት አይደሉም ከማለት ባለፈ በተጨባጭ የተደረገው ቃለምልልስ ስህተት ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም። የቃለምልልሱ ሙሉ ይዘት ሲታይም ተጠሪ የሚወክለውን ማሕበር አስመልክቶ አመልካች ላይ ያላቸውን ቅሬታ የማሳወቅና በአመልካች ድርጅት የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶች የመግለጽ እንጂ የአመልካች ደርጅትን መልካም ሥምና ተግባር የማጥፋት፣ የኢንዱስትሪ ሰላም የሚያደፈርስ ድርጊት ሆኖ አልተገኘም። የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት ኮንፌደሬሽን ለፍርድ ቤቱ በላከው ማስረጃ አመልካች የሠራተኛ ማሕበሩን እውቅና ያለመስጠት፣ የማሕበሩን አባላት ሆነ አመራሮች ያለበቂ ምክንያት ከሥራ ማባረሩን፣ በማሕበሩ አሠራር ጣልቃ መግባት ላይ ቅሬታ ቀርቦ ተግባሩን እንዲያቆም የተጠየቀ ስለመሆኑ ገልጿል።

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 26(2)(ለ) መሠረት ሠራተኛው በሠራተኛ ማሕበሩ አባል መሆኑ ወይም በማሕበሩ ሕጋዊ ተግባራት ተካፋይ መሆኑ ሠራተኛውን ከሥራ ለማሰናበት የሚያበቃ በቂ ምክንያት አለመሆኑ ተመልክቷል። ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ማስረጃ ሲመለከት በሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ/ም የተደረገው የሕብረት ሥምምነት አባሪ ክፍል አንድ ንዑስ ክፍል ሀ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ስምና ዝና የሚያጎድፍ፣ መልካም ግንኙነት የሚያሻክር ከባድ ጥፋት

መፈጸሙ ሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ድንጋጌ መጣሱን የሚያስረዳ ሳይሆን ተጠሪ በምክትል ሊቀመንበርነት በሚመራው ማሕበርና በማሕበሩ አባላት ላይ ደርሰዋል ያሉትን የመብት ጥሰቶችና ግድፈቶች የሚጠቁም ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም ተጠሪ የተሰናበተው የሠራተኛ ማሕበሩን በመወከል ባደረገው ሕጋዊ ተግባር እንጂ ያጠፋው ጥፋት የሌለ በመሆኑ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 26(2)(ለ) በመጻረር ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱ ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት መሆኑን ያስገነዝባል። በተጨማሪም የዲሲፕሊን ኮሚቴው በሕብረት ሥምምነቱ በተመለከተው አግባብ የሠራተኛ ማሕበር ተወካዮች መሳተፍ ሲገባቸው ባልተገኙበት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረቡ አስፈላጊ ሂደቶችን ሳይከተል የተደረገ ሕገ-ወጥ ስንብት መሆኑን ያስረዳል። ስንብቱ ሕገ-ወጥ ቢሆንም ተጠሪ ወደሥራ ቢመለስ በግራቀኙ መካከል የተካረረ እንጂ መልካምና ጤናማ ግንኙነት ላይኖር ይችላል በሚል ተጠሪ ወደሥራው ሊመለስ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፤ ተጠሪ ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ እንዲከፈለውና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጠው በማለት ወስኗል።

ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በማከራከር በሥር ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠው ተጠሪ በግላቸው ያጠፉት ጥፋት የለም፤ ከስራ የተሰናበቱት በሠራተኛ ማሕበር አመራርነታቸው በሰጡት ቃለምልልስ ሲሆን ቃለምልልሱ ስህተት አለመሆኑም የተረጋገጠ በመሆኑ የሥራ ውሉ ቢቀጥል ለኢንዱስትሪ ሰላሙ ችግር የሚፈጥር አይደለም። የተጠሪ የሥራ መደብ የአውሮፕላን ጥገና ባለሞያ በመሆኑና የሥራ ውላቸው የተቋረጠው ከሥራ ተግባራቸው ጋር በተያያዘ ጥፋት ባለመሆኑ በግራቀኝ መካከል ያለው የሥራ መተማመን ላይ ችግር የሚያመጣ አይደለም። ተጠሪ ወደሥራ አለመመለሳቸው ግን የመደራጀትና መብትን የመጠየቅ ባሕል የሚያዳክምና ለወደፊት መልካም የኢንዱስትሪ ግንኙነት እንዳይኖር ስለሚያደርግ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዛቸው ተከፍሏቸው ወደሥራቸው ሊመለሱ ይገባል በማለት ሲወሰን አመልካች ያቀረበውን መስቀለኛ ተቃውሞ ባለመቀበል ሰርዟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። አመልካች በተጠሪ ይግባኝ በተሻሻለው ውሳኔ ላይና የመስቀለኛ ተቃውሞ መሰረዙ ላይ በ25/12/2013 እና በ26/12/2013 ዓ/ም የተጻፉ ሁለት የተለያዩ የሰበር አቤቱታዎች በአንድ መዝገብ ላይ አቅርቦ የሰበር አጣሪ ችሎት ተጠሪ ወደሥራ ይመለሱ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ሰላማዊ የሆነ የሥራ አካባቢ ከመጠበቅ አንጻር ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ መልስ የቀረበ ቢሆንም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በአንድ መዝገብ የቀረበው ሁለት የሰበር አቤቱታ በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤት ክርክሩ መነሻ አንድ መሆኑን፣ በአንድ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የሚገባው አንድ የሰበር አቤቱታ በመሆኑና የአቀራረብ ስህተት ያለበት መሆኑ እንዲሁም ለተጠሪ የደረሰው ነሀሴ 25 ቀን 2013 ዓ/ም የተጻፈው አንደኛው የሰበር አቤቱታ ብቻ መሆኑ የተጠሪን የመደመጥ መብት የሚጥስ መሆኑን በመገንዘብ የሰበር አቤቱታው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91(1) እና 329(2) መሠረት ተጠቃሎና ተሻሽሎ እንዲቀርብ በመታዘዙ አመልካች በ11/06/2014 ዓ/ም የተሻሻለ

የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ የሰጠው ቃለምልልስ ሀሰተኛ መረጃ የሆነ፣ የአመልካች ስምና ዝና የሚጎዳ ተግባር ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የአመልካች ደርጅት ሥራ ከፍተኛ ውድድር ያለበትና እምነት ዋጋ ያለበት ነው፤ የተጠሪ አድራጎት በደንበኞችና በሥራ አጋሮች እምነት ላይና በሥራው ላይ ጉዳት አምጥቷል፡፡ ተጠሪ የሰጠው ቃለምልልስ ሀሰተኛ ነው፤ እውነት ቢሆን እንኳን ድርጅቱን በመጉዳት ሃሳብ የተናገረው በወንጀልም የሚያስጠይቅ ጥፋት ነው፡፡ ድርጊቱ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 13(6)፣ 14(2)(ሀ) እና 27(1)(ሸ) እንዲሁም በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ነው፡፡ ድርጊቱም የተፈጸመው በግል እንጂ በማሕበር ተወካይነቱ አይደለም፤ የሠራተኛ ማሕበሩ የጻፈውን ማስረጃ እንደማያስተባበል ማስረጃ አድርጎ መውሰዱ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመው በማሕበር አመራርነት ቢሆን እንኳን ማሕበሩ ስለአባላቱ መብትና ጥቅም እንጂ ባልተረጋገጠ መረጃ አመልካች ላይ ጉዳት ማድረስ በሕጉ አልተፈቀደለትም፡፡ አመልካችን የሚጎዳ ሃሳብ መግለጽ ሕገ-መንግስታዊ መብት አይደለም፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ቢባል እንኳን የፈጸመው ድርጊት ከአሠሪው ጋር ያለውን መልካም የሥራ ግንኙነትና መተማመን ለማስቀጥል የማይቻል፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን የሚያመጣ ባለመሆኑና በሰ/መ/ቁ. 64079 እና 37454 በተሰጠው ትርጉም መሠረት ተጠሪ ወደሥራው ሊመለስ የማይገባ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት መልስ የሰበር አቤቱታው የአቀራረብ ስህተት ያለበት፣ በተሻሻለው የሠበር አቤቱታ ሰበር አጣሪ ችሎት የሕግ ስህተቱን ሳይለይ መልስ አቅርብ መባሌ ሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም፡፡ በሀሰት የጠፋ ስምና ዝና የለም፡፡ ሀሰተኛ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ በማሕበር ተወካይነቴ የተደረገ ቃለምልልስ ነው፡፡ ማሕበሩን በመወከል ሃሳብ መግለጽ መብት ነው፡፡ ከሥራ መደቤና ሙያዬ ጋር የተያያዘ ጥፋት ፈጽመሃል ያልተባልኩ በመሆኑ ወደሥራ መመለሴ ተገቢ ነው፡፡ በሰ/መ/ቁ. 64079 እና 37454 የተሰጠው ውሳኔ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆን አለመሆኑን? ተጠሪ ወደሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢነቱን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ አመልካች ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደሥራ እንዲመልሳቸው፤ ይህ ካልሆነም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የአመልካች ተግባር ያልሆነውን ሀሰተኛ መረጃ በመገናኛ ብዙኃን በመግለጽ መልካም ስምና ዝናውን የሚያጎድፍ ተግባር በመፈጸማቸውና

የንብረት ጥቅሙ ላይ ጉዳት በማድረሳቸው ምክንያት የሥራ ውላቸው የተቋረጠ ስለሆነ የሥራ ሥንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል፡፡

ሠራተኛ የአሠሪው ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ ተግባር ከፈጸመ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል ድርጊት ስለመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ላይ ተመልክቷል፡፡ የአሠሪውን ሥም ማጥፋትም ሥራው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ድርጊት በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ በሠራተኛ ማሕበር አመራርነታቸው ሳይሆን በመገናኛ ብዙኋን በመጠቀም የአመልካች ድርጅት መልካም ስምና ዝና ላይ ሀሰተኛ የሥም ማጥፋት ዘመቻ የሚያካሂድ ቡድን ላይ ዋና ተዋናይ ሆነው አመልካች የሠራተኛውን ክብር የማይጠብቅ፣ ሕገ-ወጥ ፖሊሲ ተቀርጾ ሠራተኛ ላይ በደል እንደሚፈጸም፣ አመራሩ ከሕግ በላይ ነን የሚሉና በማን አለበኝነት መንፈስ የሚመሩ ግለሰቦች ናቸው፣ ሕግን ያልተከተለ የውጭ ምደባ እንደሚደረግ፣ ምደባ በሥራ አፈጻጸም ሳይሆን ከአመራር ጋር ባለ ቀረቤታና ቁርኝት እንደሚፈጸም፣ የበረራ አስተናጋጆች ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ያልተገባ ድጋሜ ክፍያ እንደሚፈጸም በማለት ሀሰተኛ እና ስም የሚያጠፋ መረጃ ሰጥቷል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው በሠራተኞች ማሕበር ውስጥ በምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ እየሰራሁ እያለ ማሕበሩን በመወከል የተገለጸ ነው፣ የአመልካችን ስም የሚያጎድፍ ሆነ የሠራተኛውን ሰላማዊ ግንኙነት የሚያጠፋ ተግባር ባልተፈጸመበት የተሳሳተ መረጃ ስጥተሃል፣ ሰላማዊ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት ከግንቦት 04 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ከስራ ማሰናበቱ ሕገ-ወጥ ስንብት ነው የሚል ነው፡፡

የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመለየት፣ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን ኃላፊነት የተሰጠው የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማትና ተጠሪ የሰጡትን ቃለምልልስ በመመልከት ተጠሪ ከናሁ ቲቪ፣ ፊደል ፖስት ጋር ያደረጉት ቃለምልልስ በሠራተኛ ማሕበሩ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት የተፈጸመ እንጂ በግል ያደረጉት አይደለም፣ አመልካች በሚዲያ የተሰጠው ማብራሪያ በጥቅሉ አመልካችን የማይወክሉና አመልካች ድርጊት አይደሉም ከማለት ባለፈ በተጨባጭ የተደረገው ቃለምልልስ ስህተት ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፣ የቃለምልልሱ ሙሉ ይዘት ሲታይም ተጠሪ የሚወክለውን ማሕበር አስመልክቶ አመልካች ላይ ያላቸውን ቅሬታ የማሳወቅና በአመልካች ድርጅት የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶች የመግለጽ እንጂ የአመልካች ደርጅትን መልካም ሥምና ተግባር የማጥፋት፣ የኢንዱስትሪ ሰላም የሚያደፈርስ ድርጊት ሆኖ አልተገኘም ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት የፈጸመ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተደረገው የሕብረት ሥምምነት አባሪ ክፍል አንድ ንዑስ ክፍል ሀ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ስምና ዝና የሚያጎድፍ፣ መልካም ግንኙነት የሚሻክር ከባድ ጥፋት መፈጸሙ ሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ድንጋጌ መጣሱን የሚያስረዳ ሳይሆን ተጠሪ በምክትል ሊቀመንበርነት በሚመራው ማሕበርና በማሕበሩ አባላት ላይ ደርሰዋል ያሉትን የመብት ጥሰቶችና ግድፈቶች በመግለጻቸው ከሥራ መሰናበታቸው ሆነ የዲሲፕሊን ኮሚቴው በሕብረት ሥምምነቱ በተመለከተው አግባብ የሠራተኛ ማሕበር ተወካዮች መሳተፍ ሲገባቸው ባልተገኙበት የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ አስፈላጊ ሂደቶችን ሳይከተል የተደረገው ውሳኔ ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ነው በማለት መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

ወደሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ ተጠሪ ወደሥራቸው እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበውን የሠበር አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(1)(2) የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ በአሠሪው የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደሥራው እንዲመለስ ሊወሰን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ሠራተኛው ወደሥራ ሊመለስ የማይችለው ከሥራው ጠባይ ግንኙነት የተነሳ ወይም ከክርክር ሂደት ከወሰደው ግንዛቤ በሥራ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ያስከትላል ተብሎ በፍርድ ቤቱ ሲታመን እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 43(3) ላይ ተደንግጓል፡፡ ከፍተኛ ችግር የሚለው የሕጉ አነጋገር ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት ሠራተኛውን ወደሥራው እንዳይመለስ ማድረግ የማይችል መሆኑን እና

የሚያስከትለው ጉዳት ጉልህ የሆነ መሆን እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይህም ሕግ አውጭው በአንድ በኩል የሥራ ዋስትና ማረጋገጥ ለሠራተኛው ሆነ ለሀገር መሠረት የሆነውን የሠራተኛውን ቤተሰብ መጠበቅ እንዳለበት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል የሥራ ሁኔታውን እና የኢንዱስትሪውን ሠላም ማስጠበቅ ለምርታማነት መሠረት መሆኑን በመገንዘብ በሁለቱ እሳቤዎች መካከል ጉዳዩ እንዲገዛ የፖሊሲ ውሳኔ ላይ መድረሱን እና ጉዳዩም የፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ምክንያታዊ በሆነ አግባብ እንዲጠቀም ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ግራቀኙ ተከራካሪዎችም በተለይም አሠሪው ፍርድ ቤቱን ለማሳመን ሠራተኛው ወደሥራ ቢመለስ የሚያስከትለውን ጉልህ የሆነ ጉዳት ማሳየት ይኖርበታል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የአውሮፕላን ጥገና ባለሙያ ሲሆኑ ከአመልካች አስተዳደር ጋር አለመግባባት መኖሩ ከሥራ ድርሻቸው አንጻር ወደሥራ መመለሳቸው አመልካች ላይ ጉልሕ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 37454 የሠጠው አስገዳጅ ትርጉም ሠራተኛው የጥበቃ ሠራተኛ መሆኑ እንዲሁም ከአለቆቹ ጋር በተለያየ ጊዜ ግጭት የሚፈጥር መሆኑና በእጁም ትጥቅ ያለ መሆኑ የሥራ ውሉን ለማስቀጠል የማይቻል መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የአሠሪው ሠላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ድርጅትን ጠቅላላ ንብረት ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሠው መሆኑን ግምት ወስጥ በማስገባት ወደሥራ ሊመለስ እንደማይገባ የተወሰነበት ነው፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁ. 64079 የተወሰነውም ገንዘብ ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ መሆኑን በመገንዘብና ጥፋት ፈጽሟል የተባለው ከሥራ ኃለፊነቱ ጋር በተያያዘ በመሆኑ፣ ከአሠሪው ጋር ያለው መተማመን ከቀነሰ ባለበት ኃላፊነት ወደሥራ መመለስ መልካም የሥራ ግንኙነት አይፈጥርም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር የተያያዘ ጥፋት ፈጽሟል ያልተባለ በመሆኑና ቀደም ሲል በዚህ ችሎት ከተወሰኑት ጉዳዮች ጋር የፍሬ ነገር ልዩነት ያለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ወደሥራ ቢመለሱ ሥራው ላይ የሚያደርሰዉ ከፍተኛ ጉዳትን አመልካች ያላሳየ ስለሆነ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ብለናል፡፡ በሌላ በኩል በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(5) መሠረት ተጠሪ ወደሥራው እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ታይቶ የጸና በመሆኑ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 268985 ሐምሌ 12 እና 28 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ተጠሪ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# ከውል ውጪ ኃላፊነት

**የሰ/መ/ቁ** - 175660

**ቀን** - ህዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ድንቃለም ግዛዉ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ መሠረት ዘርፉ } የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ያላግባብ በሌላ ሰዉ የባንክ ሂሳብ የተከፈለ ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል የቀረበን ክስ መሠረት በማድረግ የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ ከተከሳሽ ጋር ምንም ግንኙነት ሳይኖረን በባንክ ሂሳባቸዉ በስህተት ያስገባሁትን ብር 42,800.00 ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ከሳሽ ገንዘቡን ያስገቡት በስህተት ሳይሆን የተከሳሽን ስም እና የባንክ ሂሳብ ቁጥራቸዉን ጽፈዉ መሆኑን እና ገንዘቡን ያስገቡትም አቶ ፍቅሩ የሚባል የከሳሽ ቤተሰብ ከተከሳሽ ልጅ አቶ ዳንኤል እልቅነዉ በደቡብ አፍሪካ አገር ብር 42,800.00 ዕዳ ለመመለስ መሆኑን ጠቅሰዉ ክሱ ዉድቅ እንዲሆን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የማይገባዉን ክፍያ የፈጸመ ሰዉ ክፍያዉ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት እንዳለዉ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2164 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ ተከሳሽ ገንዘቡን ለከሳሽ ለመመለስ የማይገደዱበትን ምክንያት በህጉ አንቀጽ 2165፣ 2166 እና 2177 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት የማስረዳት ሸክማቸዉን ያልተወጡ መሆኑና ከሳሽ ገንዘቡን ለተከሳሽ የከፈሉት ከዉል ወይም ከህግ የመነጨ ግዴታ ሳይኖርባቸዉ ስለመሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ ተከሳሽ ብር 42,800.00 ከወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ሚያዝያ 14 ቀን 2011 ዓ.ም ተጽፎ በቀረበ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የአመልካችን ስምና የባንክ ቁጥር ጠቅሰዉ ገንዘቡን በአመልካች ሂሳብ ገቢ ማድረጋቸዉ መረጋገጡን፣ ይህን ያደረጉት በስህተት መሆኑን በክሳቸዉ መሰረት ባላስረዱበትና ገንዘቡ በአመልካች ሂሳብ ገቢ የተደረገዉም የአመልካች ልጅ ደቡብ አፍሪካ ሆኖ የተጠሪ ቤተሰብ ለሆነዉ ላበደረዉ ገንዘብ ዕዳ መክፈያ መሆኑን አመልካች አስረድተዉ እያለ ገንዘቡ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል በሚል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ታርሞ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርቡ ጥሪ የተደረገላቸዉ ቢሆንም ባለመቅረባቸዉ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

ከላይ በአጭሩ የተገለጸዉ የጉዳዩ አመጣጥ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ ተጠቃሹ ገንዘብ እንዲከፈላቸዉ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት፣ ገንዘቡን በአመልካች የባንክ ሂሳብ ላይ ገቢ ያደረጉት ተሳስተዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ያደረጉት ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ.ም እና ጥቅምት 10 2011 ዓ.ም የአመልካችን ስም እና የባንክ ሂሳብ ቁጥር በመጥቀስ መሆኑን ጠቅሰዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር ተጠሪ ክደዉ ያልተከራከሩ ከመሆኑም በላይ በክሳቸዉ አባሪ በማድረግ ያቀረቡት ማስረጃም ይህንኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ ተጠሪ ገንዘቡን በአመልካች ሂሳብ ላይ ገቢ ያደረጉት አስበዉበት እንጂ በስህተት አለመሆኑን ነዉ፡፡

የፍትሐብሔር ህጋችን ያላግባብ ስለመበልጸግ በሚል ርዕስ ክፍል ሁለት ላይ የማይገባዉን ገንዘብ መክፈል (Undue payments) ስለሚያስከትላቸዉ ህጋዊ ዉጤቶችን ይደነግጋል፡፡ የህጉ አንቀጽ 2164 ድንጋጌ ሊከፍል የማይገባዉን ገንዘብ የከፈለ ሰዉ ገንዘቡ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት ያለዉ መሆኑን በመርህ ደረጃ የሚደነግግ ሲሆን፣ በህጉ አንቀጽ 2165-2167 ያሉት ድንጋጌዎች ደግሞ የተከፈለዉ ገንዘብ ለከፋዩ ሊመለስ የማይችልባቸዉን ልዩ ሁኔታዎች የሚደነግጉ ናቸዉ፡፡ ከዚህ ዉስጥ አንዱ ስህተት ሳይኖር የተከፈለ ገንዘብን የሚመለከት ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት ስህተት ሳይኖር ሊከፍለዉ የማይገባዉ ዕዳ መሆኑን እያወቀና የሚያስከፍለዉም ምክንያት ያለመኖሩን እየተረዳዉ በእራሱ ፍቃድ የከፈለ ሰዉ ገንዘቡ እንዲመለስለት መጠየቅ እንደማይችል የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2165 ግልጽ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ኃላፊ ሊያደርጋቸዉ የሚችል የህግ ወይም የዉል ግዴታ የለም ብለዉ የሚያምኑ ከሆነ ገንዘቡን በአመልካች ሂሳብ ገቢ ያለማድረግ መብት እያላቸዉ፣ የአመልካችን ስም እና የባንክ ሂሳብ ቁጥር ጠቅሰዉ ገንዘቡን ገቢ ማድረጋቸዉ ሲታይ በስህተት ሳይሆን በእራሳቸዉ ፍቃድ አስበዉበት እንደከፈሉ የሚቆጠር በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለዉ ድንጋጌ

በህጉ አንቀጽ 2165 ላይ የተመለከተዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በአመልካች የባንክ ሂሳብ ላይ ያስገቡት ገንዘብ እንዲመለስላቸዉ መጠየቅ አይችሉም፡፡

ጉዳዩን ከዚህ አንፃር አይቶ የተጠሪን ክስ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ፣ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌላቸዉን ድንጋጌዎች በመጥቀስ አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ የመመለስ ግዴታ አለባቸዉ በሚል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ ያላግባብ የተከፈለ ገንዘብ ለከፋዩ ሊመለስ የሚችልበትን ሁኔታ በተመለከተ ከላይ የተመለከቱትን የህጉን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 178234 የካቲት 08 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 230421 መጋቢት 23 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ላይ ያስገቡትን ብር 42,800.00 ለተጠሪ ሊመልሱ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**ፅ/ወ**

# የወንጀል ሥነ ስርዓት ህግ

የሰ/መ/ቁ/208644

እና 208645

ጥቅምት 26/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

**አመልካቾች፡- 1. ሽከታ ተፈራ** **የቀረበ የለም**

**2. አንዱዓለም ያሲን**

**ተጠሪ፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም**

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ አንደኛ አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ፤ ሁለተኛ አመልካች ደግሞ በመ/ቁ/208645 ላይ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በተመሳሳይ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ በመሆኑ እና ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብም በሁለቱም መዝገቦች ላይ የተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አንድ ዓይነት በመሆኑ ሁለቱ መዝገቦች ቀድሞ በተከፈተው በዚህ መዝገብ ላይ ተጣምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ጉዳዩ ከባድ የውንብድና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ አመልካቾችን ጨምሮ በአምስት ሰዎች ላይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)፣ ለ)) እና 671(1(ሀ)) ድንጋጌን ጠቅሶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ በቀረበው ክስ ውስጥ የአሁን አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸው አንደኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የክሱም ይዘት ተከሳሾቹ ከሌሎች ለጊዜው ካልተያዙት ቁጥራቸው ከ3-5 ከሚሆኑ ግብረ-አበራቸው ጋር በመሆን የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌን በመተላለፍ የማይገባቸውን ብልፅግና ለራሳቸው አልያም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስበው ህዳር 26/2012 ዓ.ም ከሌሊቱ 10፡30 በአዳማ ከተማ አባገዳ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ “ዳዳ ሞል” ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የአሁን አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች አቶ አሊ መሀመድ የተባሉት የግል ተበዳይ “ፎር ራነር” የተባለ እና የሰሌዳ ቁጥሩ 128D75 ጅቡቲ፤ የዋጋ ግምቱ ብር 1,300,000(አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሽህ ብር) በሆነ መኪና ሁለተኛ የግል ተበዳይ የሆኑትን ወ/ሮ መታሰቢያ ወርቅአገኘሁ የተባሉትን ጋቢና አስቀምጠው

በማሽከርከር ላይ እያሉ አመልካቾች የሰሌዳ ቁጥሩ ለጊዜው ባልታወቀ ብረት መልክ ቪትዝ መኪና ተከትለው “መኪናው የተሰረቀ ስለሆነ አቁም!” በማለት በግል ተበዳይ ላይ መንገድ በመዝጋት ካስቆሙት በኋላ አንደኛ አመልካች በሹፌሩ በኩል ሄዶ አንደኛ የግል ተበዳይን በቀኝ እጁ አንገታቸውን በማነቅ በግራ እጁ ደግሞ የመኪናውን ሞተር ካጠፋ በኋላ ሁለቱም አመልካቾች ተበዳዩን ጎትተው ከመኪናው በማውረድ መሬት ላይ ከደበደቡት በኋላ አንደኛ አመልካች መኪናው ውስጥ ገብቶ ማንቀሳቀስ ሲጀምር 2ኛ አመልካች በተሽከርካሪው የተሳፋሪ በር በኩል በመግባት ጋቢና የነበረችውን ሁለተኛ የግል ተበዳይን ጎትቶ ከመኪናው ውስጥ ወደ መሬት በመጣል መኪናውን፣ የሁለቱን ተበዳዮች ሁለት ዘመናዊ የእጅ ስልክ እና በክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን ልዩ ልዩ ሰነዶችን ይዘው ተሰውረዋል፣ በዚሁ ጉዳይ ላይ በፖሊስ ክትትል በመደረግ ላይ እያለ ታህሳስ 08/2014 ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ የአሁን አመልካቾች እና የስር ፍርድ ቤት 4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በአንድ መኪና ሆነው፣ 3ኛ እና 6ኛ ተጠርጣሪዎች የነበሩ ደግሞ በሌላ መኪና ሆነው በክትትል ላይ የነበሩትን የፖሊስ አባላት ሲከታተሏቸው በጥርጣሬ በቁጥጥር ስር አውለዋቸዋል፣ ታህሳስ 10/2012 ዓ.ም የአሁን ሁለተኛ አመልካች እና የስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ ተዘረፈ የተባለው መኪና ቴዲ በተባለ ግበረአ-በራቸው እጅ እንደሚገኝ ለፖሊስ ጥቆማ ሰጥተዋል፣ ከዚህ አልፎ ቴዲ የተባለው ግበሬ አበራቸው መኪናው የት እንዳለ ለፖሊስ እንዲያሳውቅ በስልክ በነገሩት መሰረት እነርሱ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንዳሉ ቴዲ የተባለው ግለሰብ ታህሳስ 11/2012 ዓ.ም ለፖሊስ ደውሎ መኪናው በቢሾፍቱ ከተማ ዙቃላ ማዞሪያ በተባለ ቦታ መቆሙን በነገራቸው መሰረት ፖሊሶቹ ከግል ተበዳይ ጋር ሆነው መኪናውን በተባለው ቦታ ቆሞ ያገኙት በመሆኑ ተከሳሾች አባሪ ተባባሪ በመሆን በድርጊቱ እና ድርጊቱ በሚያስከትለው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ሁሉም ተከሳሾች ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክደው በመከራከራቸው ዐቃቤ ህግ ሶስት የሰው ምስክሮችን እና ድርጊቱ ሲፈፀም የተቀረፀ ቪዲዮ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቾች እንዲከላከሉ አዟል፡፡ የአመልካቾችን መከላከያ ማስረጃን ከሰማ በኋላም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን መርምሮ አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ አልተከላከሉም በሚል በተከሰሱበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ ብሎ እያዳንዳቸውን በ14 (አሥራ አራት) ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች በየራሳቸው ባስከፈቱት መዝገብ ላይ ሰኔ 01/2013 ዓ.ም በተፃፈ የተናጠል የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

በሁለቱም አመልካቾች በኩል የቀረበው የሰበር ቅሬታ መሰረታዊ ይዘትም በድርጊቱ የግል ተበዳዮች ናቸው የተባሉት እና ቀጥተኛ የዓይንም ምስክር የሆኑት ግለሰቦች ቀርበው መሰማት ሲገባቸው "የሉም" በሚል ድፍን ያለ መልስ ሳይቀርቡ መቅረታቸው መስቀልኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብታችንን አጥፏል፣ ቀርቦ የተሰማው የዐቃቤ ህግ አንድ የዓይን ምስክርም ወንጀሉን ፈፀሙ ያላቸውን ሰዎች "በሰውነት ፈርጠም ያሉ ናቸው" በሚል በምልክት ከመግለፅ ባለፈ አመልካቾችንም ሆነ ሌሎች አባሪዎች ናቸው የተባሉትን ለይቶ አላመለከተም፣ የቪዲዮ ማስረጃ የተባለውም በጨለማ የተቀረፀ ሲሆን የሰውን እንቅስቃሴ ከሚያሳይ በቀር የሰዎቹን ማንነት የማያሳይ በመሆኑ አመልካቾች የወንጀል ድርጊቱ ተካፋዮች መሆናችንን የሚያረጋግጥ አይደለም፣ ተዘረፉ የተባሉት ንብረቶችም በአመልካቾች እጅ ያልተያዙ ከመሆኑም በላይ በተያዝንበት እለት ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ሆነን ስንቀሳቀስ የነበረው መኪና ለመግዛት እንጂ ተሰረቀ ከተባለው መኪና ጋር በሚገናኝ ምክንያት አይደለም፣ ተፈፀመ በተባለው የወንጀል ድርጊት ውስጥ የአመልካቾች የወንጀል ተሳትፎ ተለይቶ ባልተረጋገጠበት ከመነሻው ክሱን እንድንከላከል መታዘዙ አግባብ አይደለም፣ ያም ሆኖ አቅርበን ባሰማናቸው መከላከያ ምስክሮቻችን ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ቀን እና ሰዓት በወንጀሉ ስፍራ ያልነበርን ለመሆኑ አረጋግጠን እያለን በወንጀል ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ በነፃ ልንሰናበት ይገባል የሚል ነው፡፡

የሁለቱም አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ዐቃቤ ህግ በአሁን አመልካቾችና በዚህ ሰበር ክርክር ባልቀረቡ አባሪዎች ጋር ውንብድና ወንጀል ፈፅመዋል ተብሎ በቀረበባቸው ክስ አመልካቾች በወንጀል ድርጊቱ የተሳተፉ ስለመሆኑ ለይተው ባልመሰከሩበት ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት የተወሰነበትን አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/44031 እና 89676 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር ተገናዝቦ በዚህ ችሎት እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪ በሁለቱም መዝገቦች ላይ የፅሑፍ መልስ እንዲሰጥ ታዟል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበውን ክርክር አስመልክቶ ሐምሌ 27/2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ቢሆንም በመ/ቁ/208645 ላይ ለቀረበው ጉዳይ የፍርድ ቤት መጥሪያ ደርሶት መልስ ባለመስጠቱ ይኸው መብቱ ታልፏል፡፡ ተጠሪ በዚህ መዝገብ ላይ ለቀረበው ቅሬታ የሰጠው መልስ ፍሬ ቃልም ቀጥተኛ የዓይን ምስክር ከሌለ ወንጀል ፈጻሚዎች በሌላ ማስረጃ ሊረጋገጥባቸው አይቻልም የሚል ህግ የለም፣ ቀርበው ከተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ውስጥ 1ኛው ሁለት ፈርጣማ ሰዎች ከተሰረቀው መኪና ላይ የግል ተበዳዮችን አውርደው ሲጥሏቸውና መኪናውን ይዘው ሲሰወሩ ማየቱን፣ 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች ደግሞ ተጠርጣሪዎቹን በመጠርጠር ይዘው ሲጠይቋቸው ቴዲ ከተባለ ሌላ ግለሰብ ጋር በስልክ ከተነጋገሩ በኋላ የተሰረቀውን መኪና ማስረከባቸውን እንዲሁም የቪዲዮ ማስረጃ መኪናውን ሰርቀው ሲያመልጡ የሚያሳይ በመሆኑ ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው ተረጋግጧል፣ ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ደግሞ እርስ በራሱ የሚጣረስ በመሆኑ

የዐቃቤ ህግ ማስረጃን የሚያስተባበል ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ ማንም ሰው በወንጀል ህግ ጥፋተኝነቱ ካልተረጋገጠ በቀር በወንጀል ሊቀጣ እንደማይገባ የወንጀል ህግ አንቀጽ 57(1) ይደነግጋል፡፡ ወንጀል ፈፀመ ተብሎ የተከሰሰውን ሰው አስመልክቶ የተከሰሰበት ድርጊት ወንጀል መሆኑን እና ድርጊቱንም የተከሰሰው ሰው የፈፀመው ስለመሆኑ አግባብነት ባለው ማስረጃ የማረጋገጥ ኃላፊነቱ የዐቃቤ ህግ ስለመሆኑ ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 133፣ 134፣ 141 እና 149(1) ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ ደግሞ በማስረጃነት እንዳይቀርብ በህግ በልዩ ሁኔታ ካልተከለከለ በቀር ስለ ድርጊቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊያረጋግጥ የሚችል ማናቸውም ማስረጃ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 19(5) እና የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 137 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩል አንድን የቀረበ የወንጀል ክስ ለማረጋገጥ የሚያስችሉትን ማስረጃዎች የመለየት እና የመወሰን ስልጣኑ የዐቃቤ ህግ ነው፡፡ እናም ክሱን ያረጋግጡልኛል ያላቸውን ማስረጃዎች እስካቀረበ ድረስ የቀረቡት ማስረጃዎች በእርግጥም ክሱን በህግ በተቀመጠው የማስረዳት ደረጃ የሚያረጋግጡ መሆን ያለመሆናቸው ከሚመዘን በቀር አንድን የማስረጃ አይነት ለይቶ "ካላቀረብክ" ተብሎ የሚገደድበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማረጋገጥ አለኝ ያለውን የሰው እና የቪዲዮ ማስረጃን አቅርቧል፡፡ በእርግጥ ቀርበው ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ የግል ተበዳዮች የሉም፡፡ እነዚህ ተበዳዮች በማስረጃነት ስለመቆጠራቸው እና ቀርበው ስላልተሰሙበት ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የሚገልፀው ነገር ባይኖርም አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ውስጥ ምስክሮቹ "የሉም" በሚል ምክንያት መታለፋቸው ተመልክቷል፡፡ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን የግል ተበዳዮቹ ቀርበው ያለመሰማታቸው ሌሎች ማስረጃዎች እንዳይመዘኑ የሚያደርግ አይለም፡፡ አመልካቾችም ቢሆን የቀረበውን ማስረጃ በተገቢው ስርዓት ከሚጠይቁ በቀር ተበዳዮች በማስረጃነት ያለመቅረባቸው መስቀልኛ ጥያቄን ከመጠየቅ አንፃር የሚፈጥርባቸው የሙብት መጣበበ የለም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አኳያ የቀረበውን መከራከሪያ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

ከዚህ በመለስ ያለውን በተመለከተ ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን መርምረውና መዝነው ተገቢ ነው ባሉት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው ውሳኔው በማስረጃ

የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያላደረገ እንደሆነ፣ ወይም በማስረጃ ምዘና ረገድ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ስለመፈፀሙ ሲረጋገጥ፣ ወይም ማስረጃዎቹ መሰረት ተደርጎ በተሰጠ የህግ ትርጉም ውስጥ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ሲኖር ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 78 እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ለችሎቱ ከተሰጡት የዳኝነት ስልጣን መረዳት ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካቾች "ወንጀል ስለመፈፀማችን አልተረጋገጠብንም እንዲሁም "በመከላከያ ማስረጃችን የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃን አስተባብለናል" ከማለት ባለፈ ከላይ በተመለከተው አግባብ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ በሰበር አጣሪ ችሎቱ የተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብም ከማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት አንፃር ቀደም ተብሎ በዚሁ ችሎት የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጠቅስ ቢሆንም ከማስረጃ ምዘና ረገድ የስር ፈርድ ቤቶች የፈፀሙት የምዘና መርህ ጥሰት ተጠቅሶ የቀረበ የስበር ቅሬታ የለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ማስቀረቢያ ነጥቡም ሆነ የአመልካቾች የሰበር ቅሬታ የግራ ቀኙ ማስረጃ በድጋሚ በዚህ ችሎት እንዲመረመርና እንዲመዘን የሚጋብዝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሆኖም ማስረጃን መመርመር እና መመዘን የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ስልጣን ባለመሆኑ ይህ የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ሲጠቃለል በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ተፈፅሟል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ ባለመገኘቱ የአመልካቾች የሰበር ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ/374045 መጋቢት 07 2012 ዓ.ም እና በመ/ቁ/374399 ላይ መጋቢት 22/2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁር 195(2(ለ(2))) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ከመ/ቁ/208645 ጋር ይያያዝ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ ፊርማ አለበት

ማ/አ

## የልዩነት ሀሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 2 እና 3 የተመለከተው ዳኞች የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች (የመዝገብ ቁጥር 208644 እና 208645 አመልካቾች) ላይ በሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ፤ይህ መሰረታዊ የህግ ስህተትም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም ይገባል ብለን ስላላመንን ለልዩነት ምክንያት የሆኑትን ሀሳቦች እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

በስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ተከትሎ የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክሱን ያቀረበው የወ/ህ/አ.671(1)(ሀ) በመጥቀስ ሲሆን አመልካቾች በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብለው የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችለው ለክሱ መነሻ የሆነውን ተሽከርካሪ የግል ተበዳይን ከመኪና አውርደው በመደብደብ ይዘው ተሰወሩ የተባሉት አመልካቾች ድርጊቱን የፈፀሙት "በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የሐይል ተግባር ለመፈፀም በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን" መሆኑን ዐቃቤ ህግ ሲያስረዳ በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ከላይ በተመለከተው ድንጋጌ አግባብ ማስረዳት አለማስረዳቱ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት መሰረታዊ ጭብጥ ነው ብለን እናምናለን፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ዐቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ አመልካቾች የመኪናውን አሽከርካሪ እና አብረዋቸው የነበሩትን ግለሰብ ከመኪና አውርደው በመደብደብ መኪናውን ይዘው መሰወራቸውን አስረዳ እንጂ ይህንን ድርጊት የፈፀሙት "በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የሐይል ተግባር ለመፈፀም በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን" መሆኑን አላስረዳም፡፡ይህም የወ/ህ/አ.671(1)(ሀ) መሰረታዊ መስፈርት በዐቃቤ ህግ ማስረጃ አለመረጋገጡን ያሣያል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የዐቃቤ ህግ ምስክሮች አመልካቾች የመኪናውን አሽከርካሪ እና አብረዋቸው የነበሩትን ግለሰብ ከመኪና አውርደው በመደብደብ መኪናውን ይዘው መሰወራቸውን ማስረዳታቸው ብቻ የግል ተበዳዮችን አንገድልሃለን በማት እርግጠኛ የሞት አደጋ የሚያደርሱባቸው መሆኑን በሚያሳይ መልኩ የወሰዱት እርምጃ መኖሩ ባልተረጋገጠበት፤ድርጊቱን የፈፀሙት በጦር መሳሪያ መሆኑን ምስክሮቹ ባላስረዱበት እንዲሁም የግል ተበዳዮችን ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ ያንገላቱ መሆኑ በዐቃቤ ህግ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ፤በድብደባው ምክንያት የግል ተበዳዮች ላይ ከባድ የአካል ጉዳት መድረሱ በህክምና ማስረጃ ወይም በሌላ መንገድ ባልተረጋገጠበት የወ/ህ/አ.671(1)(ለ) ለተያዘው ጉዳይ አግባብ ነው ሊባል የሚችልበት የህግ አግባብ ሳይኖር ወይም ከላይ በተመለከቱት አግባብ አመልካቾች አደገኝነታቸውን በሚያሳይ ሁኔታ የውንብድና ድርጊቱን በወ/ህ/አ.671(1)(ሐ) አግባብ የፈፀሙ ለመሆኑ ዐቃቤ ህግ ባላስረዳበት ሁኔታ አመልካቾች በወ/ህ/አ.671 ስር የሚወድቅ ከባድ የውንብድና የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ሊባል ስለማይችል አመልካቾች ጥፋተኛ ሊባሉና ሊቀጡ የሚገባው በወ/ህ/አ.670 ስር በውንብድና የወንጀል ድርጊት ሊሆን ይገባል በማለት ከስራ ባልደረቦቻችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ. 211518

ጥር 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ - ዐ/ህግ አበራ ረታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አስቴር አዱሽ ደበሌ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 80076 መጋቢት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 006808 ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 447(ሀ)ን በመተላለፍ በቀን 12/12/2012 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 9፡30 ሰዓት ላይ በየካ ክፍለ ከተማ ምንሊክ ሆስፒታል የሴቶች እና ህጻናት ጾታዊ ጥቃት የወንጀል ምርመራ ክፍል በመቅረብ ተገኔ ረጋሳ የተባሉት አሰሪዬ በመጋቢት ወር 2012 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ ሻይ መኝታ ቤታቸው ድረስ እንዳመጣላቸው ጠይቀውኝ ሳመጣላቸው የመኝታ ቤታቸውን በር በመቆለፍ አንገቴን በመያዝ ራሴን እንዳልከላከል በማድረግ አስገድደው በመድፈር እርግዝና እንዲከሰትብኝ ያደረጉ ስለሆነ በህግ ይጠየቁልኝ ስትል ሌላውን ሰው በባለስልጣን ፊት ክስ በማቅረቧ ምክንያት የግል ተበዳይ በቀን 27/12/2012 ዓ.ም በፖሊስ ተይዘው አንድ ቀን ታስረው እንዲያድሩ ያደረገች በመሆኑ በፈጸመችው ሀሰተኛ ክስ በማቅረብ ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ እንደሌላቸው ገልጸው የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁም ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ ለተጠሪ የዋስትና መብት ጠብቆ መዝገቡ ላይ ብይን ለመስጠት በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርቡ በመቅረታችው ዓቃቤ ሕግ በቀረበው ማስረጃ ብይን ይሰጥልኝ በማለት ጠይቋል፤ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ የተሰወሩት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ይከላከሉ አይከላከሉ የሚለውን ብይን ሳይሰጥ በመሆኑ ተጠሪ በሌሉበት ብይን ለመስጠት የሚያስችል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግም ሆነ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ የለም በማለት የዓቃቤ ሕግን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በተገኙ ጊዜ መዝገቡን እንዲንቀሳቀስ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ትዕዛዝ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አጽንቶታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በሌለችበት ብይን ሊሰጥ አይገባም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 37 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 160 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን የሚቃረን ነው፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ባልቀረበችበት ሁኔታ ብይን ቢሰጥ በተጠሪ መብት ላይ የሚያስከትለው የመብት ጥሰት የለም፤ ስለሆነም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በስር ፍርድ ቤቶች የሰተጠው ትዕዛዝ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ዐቃቤህግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 447(ሀ) ጠቅሶ ባቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ ቀርበው የዐቃቤህግ ማስረጃ ሲሰማ ከተከታተሉ በኋላ ለመከላከል ብይን በተቀጠረበት ዕለት ሳይቀርቡ መቅረታቸውን ምክንያት በማድረግ ተጠሪ በተገኙ ጊዜ ክስ የማንቀሳቀስ መብት ጠብቆ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን የዘጋበትን አግባብ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ድንጋጌዎች አንፃር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ መልስ በጽሁፍ የመስጠት መብታቸውን ፍርድ ቤቱ አልፎታል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት በግልጽ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የዋስትና መብት ተጠብቆላቸው ክሱን ሲከታተሉ የነበረ እና የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በተሰሙበት ዕለትም ቀርበው የነበረ መሆኑን፤ መዝገቡ ለብይን በተቀጠረበት ዕለት ሳይቀርቡ የቀሩ መሆኑን፤ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ የተሰወሩት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ

ከተሰማ በኂላ ይከላከሉ አይከላከሉ የሚለውን ብይን ሳይሰጥ በመሆኑ ተጠሪ በሌሉበት ብይን ለመስጠት የሚያስችል የወንጀል ሥነ-ሥርዓትም ሆነ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ የለም በማለት ተጠሪ በተገኙበት ጊዜ መዝገቡን እንዲንቀሳቀስ በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ በመርህ ደረጃ የወንጀል የክርክር ሂደት ተከሳሾች ባሉበት እንደሚደረግ፣ ይህም ሲደረግ የተከሰሱበትን ምክንያት አውቀው የመከራከር እና የመሰማት መብት ያላቸው መሆኑ፣ በልዩ ሁኔታ ደግሞ የፈጸሙት ወንጀል ቀርበው መከራከር የማይፈልጉና ከፍትሕ ስርዓቱ የሸሹ ግለሰቦች በሕጉ የተቀመጠው መስፈርት ተሟልቶ በተገኘ ጊዜ በፍትሕ ሥርዓቱ መጠየቅ ያለባቸው እና በሌሉበት ነገሩ ሊሰማ የሚችል ስለመሆኑ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 161 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቱም አንድን ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ለማየት እንዲችል ተከሳሹ በቀጠሮ ቀን ያለ በቂ ምክንያት መቅረቱ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑም ይኸው ድንጋጌ ያስገነዝበናል፡፡
በሌላ በኩል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20/4 ላይ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡
በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ክሱ በሚሰማበትና የዓቃቤሕግ ምስክሮች በሚሰሙበት ጊዜ ችሎት ቀርበው የነበረ መሆኑ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፣ ይህም ተጠሪ በሕገ መንግስቱ የተጠበቀላቸውን መብት የተጠቀሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ተከሳሹ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት የዓቃቤ ሕግን ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመና ብይን ለመስጠት በተያዘው ቀነቀጠሮ አለመቅረቡ ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ መርምሮ አስቀድሞ የሰራውን ብይን እንዳያነብ፣ አስቀድሞ የተሰራ ብይን ከሌለም በዕለቱ ወይም በቀጣይ ቀጠሮ ብይን እንዳይሰጥ አያደርገውም፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ፍርድ ቤቱ የዓቃ ቤሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኂላ ተከሳሹ ብይን ለመስጠት በተያዘው ቀነቀጠሮ አለመቅረቡን ምክንያት በማድረግ ተከሳሽ በቀረበ ጊዜ መዝገቡ ይንቀሳቀስ በማለት ብይን የሚሰጥ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በአንድ በኩል የተከሳሽን የመከራከር መብት በሚያረጋግጥ መልኩ ክርክሩን ከመምራት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተበዳዮችን ፍትሕ የማግኘት መብት ከማረጋገጥ አንጻር ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው ክስ የቀረበባቸው ሰዎች ከፍትሕ ሂደቱ እንዳያመልጡ ከማድረግ አንጻር ያለበትን ሚዛኑን ጠብቆ ክርክሩን የመምራት ግዴታ በእጅጉ የሚጻረር ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት ተጠሪ በተገኙበት የተሰሙትን የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ብይን መስጠት ሲገባው ይህን ለማድረግ የሚያስችለኝ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግም ሆነ የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ውሳኔ የለም በማለት ተጠሪ በቀረቡ ጊዜ መዝገቡ ይንቀሳቀስ ሲል የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80076 በቀን 13/07/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 006808 ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተጠሪ በተገኙበት የተሰሙትን የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ብይን እንዲሰጥበት ገዳዩን መልሰንለታል፡፡

- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሠ/መ/ቁጥር 231732

ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች - በፍትሕ ሚኒስቴር - የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ዘነበች ቸሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተከሰሰ ሰው በሌለበት ክርክሩ ሊታይ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 የተደነገገዉን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽማለች በሚል ክስ መስርቶባታል፡፡ ለተጠሪ በአድራሻዋ መጥሪያ እንዲደርሳት ታዞ በአድራሻዋ ባለመገኘቷ መጥሪያ ማድረስ ባለመቻሉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላትም አልቀረበችም፡፡ይህንን ተከትሎ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 266638 ላይ በቀን 07/07/2014ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ላይ በተደነገገው መሰረት ተከሳሹ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በሚቀጣ ድንጋጌ የተከሰሰ እንደሆነ ክርክሩ በሌለበት ሊቀጥል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በተከሰሰችበት ወንጀል ጥፋተኛ ብትሆን ልትቀጣ የምትችለው መነሻውን 5 ዓመት ጣሪያውን 20 ዓመት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች በዚህ ፍቅድ ሥልጣን ዉስጥ ቅጣቱን ስለሚወስን ተጠሪ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ለትቀጣ ትችላለች፡፡ስለሆነም ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ሊያስቀጣ የሚችል ስለሆነ በሌሉበት የሚታይ ባለመሆኑ ተጠሪ ሲገኙ መዝገቡን አመልካች ማንቀሳቀስ እንዲችል መብት ተጠብቆለታል በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡በሀሳብ የተለዩት ዳኛ ተጠሪ የተከሰሰችበት ድንጋጌ ምንም እንኳን መነሻ ቅጣቱ 5 ዓመት የሚል ቢሆንም መድረሻ ቅጣቱ እስከ 20 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ተጠሪ በሌለችበት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል በመሆኑ በሌለችበት ክርክሩ ሊሰማ ይገባል የሚል ምክንያት አስፍረዋል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ቢያቀርብም ችሎቱ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት የለበትም በሚል በመ/ቁጥር 225068 ላይ በቀን 10/09/2014ዓ/ም በሰጠው ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት ይግባኙን ሰርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 25/11/2014ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ - ተጠሪ የተከሰሰችበት ድንጋጌ ላይ የተመለከተው መነሻ ቅጣት ምንም እንኳን 5 ዓመት ቢሆንም እስከ 20 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ተጠሪ በሌለችበት ለመታየት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) የተደነገገው መስፈርት ተሟልቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሌለበት ሊታይ አይችልም በማለት መዝገቡን መዝጋቱም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ ላይ የቀረበዉን ይግባኝ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ታርሞ ክርክሩ ተጠሪ በሌለችበት ሊቀጥል ይገባል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 27/1 እና 540ን ተላልፋለች በሚል የተመሰረተባት የወንጀል ክስ ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ አይችልም በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161 ጋር ተገናዝቦ ተጠሪ ባለችበት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በአድራሻዋ በአካል ባለመገኘቷ ትኖርበታለች በተባለው ቤት ላይ በአስተዳደሩ በኩል መጥሪያዉ ተለጥፎ ባለመቅረቧ መልስ የመስጠት መብቷ ታልፎ በሌለችበት እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረተው የወንጀል ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27/1 እና 540 ስር የተደነገገዉን ተራ የሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ቀርበው እንዲከራከሩ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላት ባለመቅረቧ አመልካች ተጠሪ በሌለችበት እንዲታይ ጠይቋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት እንዲያይ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ን በመጥቀስ ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ሊያስቀጣ የሚችል በመሆኑ ክሱ ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ባለመቀበል ተጠሪ ሲገኙ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ መብት ጠብቆ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትንም የአመልካችን ይግባኝ ሰርዟል፡፡እኛም ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን? በጭብጥነት በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከፍ ሲል በተገለጸዉ መሰረት ለተያዘው ጭብጥ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትን ጨምሮ ሕገ መንግስቱ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በወጡት የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በዋናነት መሰረት በማድረግ በአገራችን ተግባራዊ እየሆነ ያለዉን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ወይም ሞዴሎች (Criminal Justice Administration Process Model/s) ምንነት መመርመር ይጠይቃል፡፡

አገራት በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓታቸው አሜሪካዊው የሕግ ሊቅ ሔርበርት ፓከር (The American legal scholar, Herbert Packer) እ.ኤ.አ.1964 "*The Two Models of the Criminal Proces* (1964)" በሚል ባሳተሙት የምርምር ጽሁፋቸው ላይ ያስተዋወቁትን ሁለት የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎችን በተለያየ ሁኔታና ደረጃ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎች ወንጀል የመቆጣጠር እና ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴሎች (The Crime Control and Due Process Models) በሚል የሚታወቁ ናቸዉ፡፡ የእነዚህ ሞዴሎች መገለጫዎች እና ዓላማዎች በጥቅሉ የተመለከትን እንደሆነ ወንጀል የመቆጣጠር ሞዴል (The Crime Control Model) የሕብረተሰብን ሰላም፣ደህንነትና ጸጥታ ማረጋገጥን ዓላማዉ በማድረግ በቀዳሚነት ዋጋ የሚሰጠዉ ለቅልጥፍና እና የሕዝቡን ደህንነትና ንብረት ከጥቃት መከላከል ላይ ነው፡፡ ይህ ወንጀልን የመቆጣጠር ሞዴል የወንጀል ተጠርጣሪዎች መብት በመጠበቅ ላይ ትኩረት ማድረጉ አጥፊዎችን የማስቀጣቱን ሂደት አስቸጋሪ ስለሚያደርግ በዚህ ምክንያት ወንጀለኞች ከተጠያቂነት ከሚያመልጡ አጥፊዎቹን ለመቅጣት በተዘረጋው ሂደት ንጹሀን የሚቀጡበት ሁኔታ ቢያጋጥም ይሻላል ብሎ ያምናል፡፡ ከዚህ እምነቱ በመነሳት በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ለማስቀጣት ጥቅም ላይ የሚያውለው ሂደት ተጠርጣሪውን እንደወንጀለኛ የሚገምት (Presumption of guilt) መሆኑ፣የወንጀሎች አፈጻጸም መቀነስ ላይ ቅድሚያ መስጠት( Priority is reducing criminal conduct )፣የምርመራና የፍርድ ሂደቱን ፈጣን ማድረግና የመጨረሻ ውሳኔ በመስጠት ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ ከፍርድ ሂደት በፊት በተጠርጣሪው ጥፋተኝነት ላይ ድርድር ማድረግ እና ብዙ ሰዎችን አስሮ መመርመርን (Mass incarceration) ትኩረት የሚያደርግ፣ እውነታን መፈለግ ላይ ውስንነት (Limited fact finding) የሚታይበት እና ጥፋተኛ አድርጎ የማስቀጣት ምጣኔ ከፍተኛ (High Rate of Conviction) እንዲሆን የሚያደርግ ውጤት የሚያስከትል ነው፡፡

በሌላ በኩል ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴል (The Due Process Model) ቀዳሚ ትኩረቱ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ፍትሐዊ እንዲሆንና በተሳሳተ ሂደት በመከተል ንጹሃን እንዲቀጡ ማድረግ አይገባም ብሎ የሚያምን ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ንጹህ ሰው ያለጥፋቱ ቀጥቶ ከመጉዳት በሂደቱ ወንጀለኞች ከተጠያቂነት ቢያመልጡ ይሻላል ብሎ ያምናል፡፡ከዚህ እምነቱ በመነሳት የወንጀል ተጠርጣሪዎች በተጠረጠሩበት ወይም ተከሳሾች በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመገመት (Presumption of innocence)፤ ለተጠረጠሩ/ ለተከሰሱ ግለሰቦች መብት አጠባበቅ ቅድሚያ መስጠት (Priority on protecting individual rights)፣ ሂደቱን ፍትሐዊ ማድረጉ ላይ ትኩረት መስጠት (Emphasizes fairness in the process)፣እውነታን መፈለግ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ማድረግ (Emphasizes the importance of fact-finding) ፣ ማቅለያዎችንና አክባጅ ምክንያቶችን ከግምት በማስገባት እያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ፍትሃዊነት እንዲረጋገጥ ማድረግ (Individualized justice that considers mitigating and aggravating factors)፣ እንዲሁም የሚታሰሩ ሰዎች ምጣኔ አነስተኛ እንዲሆን (Lower incarceration rates) የሚያደርጉ እና እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎች ሂደቶችንና አሰራሮችን መከተልን የሚመርጥ ሞዴል ነው፡፡በዚህ አመለካከቱ የተነሳ የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ መብት እንዲጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት በፖሊስ እና

በሕግ አስፈጻሚ ላይ ይጥላል፤በፖሊሶች ሥልጣን ላይም ገደብ ያደርጋል፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ፖሊስ በወንጀል የጠረጠረውን ሰው እንደፈለገ አስሮ ምርመራ እንዳያደርግ የተጠረጠሩ ሰዎች ስለሚታሰረቡት አግባብ ሥርዓት ይዘረጋል ፣የተጠረጠሩ ሰዎች ስለተጠረጠሩበት ጉዳይ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁ ዝም የማለት መብት እንዳላቸው መርማሪ ፖሊስ እንዲነግራቸው ግዴታ ይጥላል፣ ተጠርጣሪዎችን በማስገደድ ማስረጃ እንዳይሰበስብ ማድረግና ፖሊስ ተጠርጣሪን አስገድዶ የሰበሰበው ማስረጃ ተቀባይነት እንዳያገኝ ማድረግ ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱም ሞዴሎች የየራሳቸዉ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳላቸው በዘርፉ የተጻፉ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡እንዲሁም ሁለቱም ሞዴሎች ነባራዊ ሁኔታን ችላ በማለት የየራሳቸውን ጽንፍ በመያዛቸው እና የወንጀል ተገጂዎችን (crime victims) ዘንግተዋል የሚል ትችት ይቀርብባቸዋል፡፡ ከእዚህ የተነሳ አገራት በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓታቸው ሌሎች ሞዴሎችን በተጨማሪነት ተግባራዊ ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡በዚህ ረገድ የሚጠቀሰዉ አንደኛው በእንግሊዝኛ መጠሪያው The Punitive Model of Victims' Rights በሚል የሚታወቅ ሆኖ በግርድፉ የተጎጂዎችን መብቶች ማዕከል ያደረገ የአስቀጭነት ሞዴል ተብሎ ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡ ይህ ሞዴል የወንጀል ጉዳዮች የማጥራት እና የማስቀጣት ምጣኔ ጥሩ እንዲሆን ከተፈለገ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓቱ ቀጣይነት ባለዉ ሁኔታ ራሱን ማሻሻል ይኖርበታል፤የወንጀል ተጎጂዎች የተፈጸመባቸዉን የወንጀል ድርጊት ሪፖርት የሚያደርጉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደቱ በሚፈጸሙ ተግባራት የዳግም ተጠቂነት ሰለባ እንዳይሆኑ ለመከላከል( to prevent revictimization within the criminal process)የሚያስችል እርምጃ መዉሰድን፣ከወንጀል አፈጻጸም ድርድር (Conduct Plea Bargaining ) እና ከጥፋተኝነት ድርድር (Guilty Plea Bargaining) ጋር በተያያዘ ተጎጂዎችንና የወንጀል ድርጊቱን ፈጻሚ ማዕከል ማድረግ ይገባል የሚሉ አመለካከቶችን የሚያራምድ ነው፡፡

ሌላዉ The Non-Punitive Model of Victims' Rights: A Circle Model በሚል የሚታወቅ ሞዴል ሲሆን ከሚያራምደው አመለካከት ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል አንዴ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ አጥፊውን መቅጣት ተፈጽሞ ያለፈውን ጥፋት(ያለፈ ጊዜ/ተግባር) ማዕከል ማድረጉ ላይ ስለሚያተኩርና እምብዛም የወደፊቱን ጊዜ የማመለከት እና ወደፊት ሊፈጸም የሚችልን ወንጀል የማያስቀር በመሆኑ *ቅጣትን ማዕከል ከማድረግ ይልቅ የወንጀል ተጎጂዎችን መብት በጠበቀ አኳኋን* እና ጉዳዩ የሚያገባቸውን በሂደቱ ማሳተፍ ላይ (የወንጀሉ ድርጊትና ውጤቱ የሚመለከታቸውን ሰዎች ሁሉ በማሳተፍ) ትኩረት በማድረግ በወንጀሉ ምክንያት የተፈጠረውን ማንኛውንም ጉዳት እና አለመግባባት መፍታት/ማከም፣ ተጎጂዉን መካስ እና ከጉዳቱ በፊት ወደነበሩበት የሚመልስ ፍትህ ማስገኘት (healing, compensation, and restorative justice) ይገባል ብሎ የሚያምን ነው፡፡በዚህ መሰረት ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ተሳትፎ ሳያደርግ አጥፊውን ከመቅጣት ይልቅ በተፈጸመው ወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሰዎችን፣ የእነርሱን ቤተሰቦች፣ የወንጀሉን ፈጻሚዎች እና ደጋፊዎቻቸውን ሊያሳትፍ የሚችል አማራጭ የመፍትሄ ዘዴዎችን

በመከተል ለአብነት አጥፊው በሂደቱ በሚያደርገው ተሳትፎ ለፈጸመው በደል በራሱ ኃላፊነቱን ወስዶ ይቅርታ በመጠየቅ በደሉን እንዲያክምና ተጎጂዉን እንዲክስ የሚያደርግ ሂደት መከተል ይገባል ይላል። እንዲሁም አጥፊውን መቅጣት አስፈላጊ ከሆነም ለተጎጂው ጉዳት እውቅና ለመስጠትና ተጎጂውን ከማክበር አኳያ ታይቶ ቅጣት መወሰን ማዕከል ያደረገ ሂደት መከተል ይገባል የሚል አቋም ያለዉ ሞዴል ነው።ይህ ሞዴል በዉጤታማነት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ እና ለወደፊትም የወንጀል አፈጻጸም ምጣኔ እንዲቀንስ የማህበረሰብ እድገት (social development) የሚያመጡ ሥራዎችን በተለይም በሕጻንነት የዕድሜ ጊዜ (Early childhood) ለዚህ የሚያግዙ ሥራዎችን መስራት እንደሚገባ በዚህ ሞዴል ዙሪያ የተጻፉት የሕግ ድርሳናት ያሳያሉ።

ከላይ ስለወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎች ጽንሰ ሀሳባ በአጭሩ የተመለከትነዉን ከግምት በማስገባት የእኛ አገር የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ምን እንደሚመስል መርምረናል። በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት ስለተያዙ እና ስለተከሰሱ ሰዎች መብቶች፣በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት፣የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሠራ ስለመሆኑ፣በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለሚከለክል…ወዘተ መርሆዎች ከአንቀጽ 19-23 ድረስ በዝርዝር ተደንግጓል።በዚህ መልኩ በሕገ መንግስቱ እውቅና ከተሰጣቸው መብቶችና መርሆዎች ውስጥ በአንቀጽ 20 ስር የተደነገገውን የተከሰሱ ሰዎችን መብት ያየን እንደሆነ የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት እንዳላቸው፣በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው፣ የቀረቡባቸውን ማናቸዉንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው፣በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል እና የፍርዱ ሂደት በሚገባቸው ቋንቋ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ተደንግጓል።እነዚህ የተከሰሱ ሰዎች መብቶች ተከሳሽ በሌለበት በሚታይ የፍርድ ሂደት ጭምር ክሱን በሚያቀርበው ዐቃቤ ሕግ እና መብቱን በሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ላይ እንደ ግዴታ የሚቆጠር ቢሆንም እነዚህ መብቶች *በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውሉት* ተከሳሹ በፍርድ ቤት ቀርቦ የፍርድ ሂደቱን ሲከታተል በመሆኑ ሕገ መንግስቱ ተከሳሽ ባለበት የፍርድ ሂደቱ እንደሚከናወን በማሰብ እንደደነገጋቸዉ የሚቆጠሩ ናቸዉ። ይህም ተከሳሽ ባለበትም ሆነ ተከሳሽ በሌለበት በሚታይ የፍርድ ሂደት የተከሰሱ ሰዎች መብቶች እንዲከበሩ ሕገ መንግስቱ እንደሚፈልግ ማሳያ ነው። ከዚህ በመነሳት ሕገ መንግስቱ በአብዛኛዉ ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴል (The Due Process Model) በሚል ለሚታወቀው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ትልቅ ስፍራ እንደሚሰጥ የሚያስገነዝብ ነው።

በተመሳሳይ ኢትዮጵያ በተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 14 ላይም የተከሰሱ ሰዎች ተመሳሳይ መብቶች እንዳላቸው ተደንግጓል።በተለይ በዚህ ቃል ኪዳን አንቀጽ

14(3/መ) ላይ ተከሳሹ በአካል ችሎት ቀርቦ ራሱን የመከላከል (የመዳኘት) መብት እንዳለው በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ በተጠቃሹ ቃል ኪዳን የተደነገገው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/4 እና 13/2 ስር በተደነገገው መሰረት የአገራችን የሕግ አካል ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ በሕገ መንግስቱ እና በተዋረድ ባሉ ሕግጋት ስለተከሰሱ ሰዎች መብቶች የተደነገገው በዚህ ቃል ኪዳን ከተደነገገው ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ሊተረጎም እና/ወይም ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በ2003ዓ/ም ወጥቶ ተግባራዊ እየሆነ የሚገኘዉን የኢፌዲሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የተመለከትን እንደሆነ በፖሊሲው ተራ ቁጥር 3.2 ላይ እንደተመለከተዉ ሕብረተሰቡ የወንጀል ሕጉን ከማስፈጸም አኳያ የወንጀል ድርጊቶችን ሪፖርት በማድረግ እና በተለያየ ደረጃ በወንጀል ምርመራ እና በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎችን በማገዝ እንዲሳተፍ ማድረግ፤ ቁጥር 3.3 ላይ እንደተመለከተው የመርማሪ ፖሊሶችንና የዐቃቤያነ ሕግን የሙያ ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና የሥነ ምግባር ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ እና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን የሚያሳድጉ ሥራዎችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መስራት፤በቁጥር 3.4 ላይ እንደተገለጸው የወንጀል ምርመራ ዓላማ በአጠቃላይ ስለ ወንጀል የማወቅ ፣ወንጀል እንዳይፈጸም የማስቆም፣ወንጀል ከተፈጸመ ጉዳቶችን የመቀነስ፣ የወንጀል ዒላማ የሆኑትን ሰዎች፣ንብረቶች ወይም ጥቅሞችን የመከላከል፣ወንጀል ፈጻሚዎችን ለሕግ የማቅረብ እና የወንጀል ተጎጂዎችን መብቶችና ጥቅሞችን የማስከበር ነው፡፡ ውጤታማና ቀልጣፋ የወንጀል ምርመራ ሥራን በማከናወን የሕዝብ ጥቅም፣በወንጀል ድርጊት የተጎዱ ሰዎች እና የተጠርጣሪዎች መብት እንዲጠበቅ ማድረግ እንዲቻል የወንጀል ምርማሪ የምርመራ ሥራውን ከዐቃቤ ሕግ ጋር ሊያከናውን እንደሚገባ በፖሊሲው ቁጥር 3.6 ላይ መገለጹ፤ በቁጥር 3.9 ላይ እንደተገለጸው በቀላል እስራት ወይም በሕጉ መሰረት በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ እና በግለሰብ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች በተበዳዩ እና በተጠርጣሪው መካከል እርቅ ከተፈጸመ ወንጀል ምርመራው ወይም የተመሰረተው ክስ እንዲቋረጥ ሊደረግ እንደሚችል፤ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ የሆነ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ እና ተጠርጣሪው በሌለበት ክሱ ሊታይ የማይችል እንደሆነ...ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ አይመሰረትም በማለት መወሰን እንደሚችል በቁጥር 3.11 ላይ መገለጹ፤ የክስና የፍርድ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ተከሳሹ ተገቢ ለሆነ አጭር ጊዜ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሊደረግ እንደሚችል እንዲሁም በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ከምርመራ ወይም ከፍርድ ሂደት መጠናቀቅ ጋር በተያየዘ በእስር ላይ የሚቆዩ ተጠርጣሪዎችን ወይም ተከሳሾችን ቁጥር ለመቀነስ እንዲቻል የምርመራ ወይም የፍርድ ሂደት የሚቀላጠፍበትን ሁኔታዎች ከማመቻቸት በተጨማሪ ከእስር ውጭ ያሉ ሌሎች አማራጮችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚቻልባቸውን መንገዶች በጥናት በመለየት ተግባራዊ ማድረግ በቁጥር 3.16.2 ስር መገለጹ፤ የምስክሮች አለመገኘትና የማስረጃ መጥፋት ምክንያት የሚፈጠረውን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማ አለመሆን ለማስቀረት...ተጠርጣሪዎች ቀደም ብለው ጥፋተኝነታቸውን እንዲያምኑ ማበረታታትና የጥፋተኝነት ድርድር የሚካሄድበትን የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣የወንጀል ጉዳዮች ክርክር በመደበኛ የፍርድ

ሂደት ዉስጥ በማለፋቸው ምክንያት በተጎጂዎች፣በምስክሮችና በተከሳሾች ሥነ ልቦና ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለማስቀረት የሚያስችል የጥፋተኝነት ድርድር ማድረግና ተከሳሹ ለፈጸመው ጥፋት በራሱ ነጻ ፍቃድ ኃላፊነት ወስዶ ባደረገው ድርጊት ተጸጽቶ በመታረም ለወደፊቱ ሰላማዊ ሆኖ እንዲኖር ማድረግ እንደሚቻል በቁጥር 4.1.፣4.5.4 ላይ መስፈሩ፤

እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚሰጡ አላስፈላጊ ቀጠሮዎችን ለመቀነስና የፍርድ ሂደቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ...መርማሪዎች እና ዐቃቤያነ ሕግ ከፍርድ ቤት በሚሰጥ መጥሪያ መሰረት ተከሳሽን እና ምስክሮችን በችሎት የማቅረብ ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ በፖሊሲው ቁጥር 4.3.2 ስር መገለጹ፤ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚችል ማስረጃ ቢኖርም ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሄ እርምጃ መታየቱ የሕዝብን ጥቅምና የተጎጂውን መብቶች በተሻለ የሚያስጠብቅ ከሆነ በተጠርጣሪና በግል ተበዳይ መካከል የተፈጠረውን የወንጀል ምክንያት...ከፍርድ ሂደት ውጭ ባሉ አማራጭ ዘዴዎች ተጠርጣሪው/ተከሳሹ በራሱ ፈቃድ ኃላፊነት እንዲወስድ በማድረግ፣ የግል ተበዳዩንና ወንጀል አድራጊውን በማስታረቅ እንዲሁም ተጠርጣሪው ለግል ተበዳዩ ካሳ እንዲከፍል በማድረግ ዘላቂ መፍትሔ እንዲገኝ ማድረግ፣ በተጨማሪም በወንጀሉ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው በጉዳዩ ላይ በሚደረገው የምርመራ ፣የክስ አቀራረብ እና የፍርድ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርግ፣ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ በቅርብ የመከታተል እና ስለሚሰጡት ውሳኔዎች ተገቢውን መረጃ የማግኘት...መብት እንዳለው በቁጥር 4.6.2. እና 6.2.1 ተገልጿል። በምርመራም ሆነ በክስና በክርክር ሂደት ልዩ ትኩረት የሚሰጥባቸው የወንጀል ጉዳዮች በተመለከተም በፖሊሲው ቁጥር 3.15 ላይ በሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ በሕገ መንግስትና በሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈጸሙ እንደሽብርተኝነት፣ የሀገር ክህደት፣ከባድ የሰው ግድያ...የመሳሰሉት ከባድ ወንጀሎች ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ከባድ ወንጀሎች እንደሆኑ ተመልክቷል።

ከዚህ በላይ በዝርዝር የተጠቀሰው የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ይዘት ከፍ ሲል የተጠቀሱትን አራቱንም የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎችን ከግምት ያስገባ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ተግባራዊ ማድረጉንና በሚወጡ ሕጎችም እነዚሁ ሞዴሎችን ታሳቢ ያደረገ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ተግባራዊ እንዲደረግ ፍላጎቱ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

እንዲሁም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገውን የወንጀል ሕጉን ዓላማና ግብ የተመለከትን እንደሆነ የወንጀል ሕጉ ዓላማ የአገሪቱን መንግስት፣ የሕዝቦቹን፣ የነዋሪዎቹን ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት መብትና ጥቅም ማረጋገጥ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩ ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀልን መከላከል፣አጥፊዎች በመቅጣት በማረም ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ በማድረግ እና ሌሎችን የማስተማር ግብ መያዙ ወንጀል የመቆጣጠር ሞዴል(The Crime Control Model) ለሚባለው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ትኩረት እንደሚሰጥ ያሳያል።በሌላ በኩል በሕጉ የመጀመሪያ ታላቅ ክፍል ስለሕጋዊነት መርህ

የተደነገገው፣በሕግ ፊት እኩል ስለመሆን፣የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ፣ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትን የተሻለውን ሕግ ተፈጻሚ ስለማድረግ፣ስለይርጋ ጊዜ አፈጻጸም ደንቦች የደነገገው፣በተሻረው ሕግ መሰረት የተሰጡ ፍርዶች አፈጻጸም …ወዘተ የሚመለከቱ መርሆዎች እና ስለቅጣት ማቅለያዎችና ማክበጃ ምክንያቶችና አፈጻጸማቸው እንዲሁም በሕግ በግልጽ ሲፈቀድ ፍርድ ቤት በመሰለው ቅጣት የሚያቀልበትን አግባብ መደንገጉ የወንጀል ሕጉ ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴል (The Due Process Model) ጭምር የተንጸባረቀበት ሕግ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም በወንጀል ሕጉ በወንጀል ክስ አቅራቢነት ከሚያስከስሱ ወንጀሎች በተጨማሪ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ስለሚያስቀጡ ወንጀሎች (offence is punishable upon complaint) መደንገጉ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት የግል ተበዳይን(የተጎጂን) ተሳትፎ ማረጋገጡንና የተጎጂዎችን መብቶች ማዕከል ያደረገ የአስቀጭነት ሞዴል (The Punitive Model of Victims' Rights) ያካተተ ሕግ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6(3/መ) ስር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የጥፋተኝነት ድርድር እንዲወስን፣ድርድር እንዲደረግ፣አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ መወሰን እንዲችል ከተሰጠው ሥልጣን መገንዘብ የሚቻለው በሕጉ የተንጸባረቀው ወንጀል የመቆጣጠር ሞዴል መከተል ብቻ ሳይሆን ቅጣትን ማዕከል ከማድረግ ይልቅ የወንጀል ተጎጂዎችን መብት በጠበቀ አኳኋንና በወንጀሉ ምክንያት የተፈጠረውን ማንኛውም ጉዳት እና አለመግባባት ፣መፍታት/ማከም፣መካስ እና ከጉዳቱ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ የሚያደርስ አማራጭ ፍትህ የማግኛ መንገዶችን የሚመለከተውን ሞዴል (The Non-Punitive Model of Victims' Rights) ጭምር መከተል እንዲቻል እድል የሚሰጥ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት መከተል እንደሚቻል መደንገጉን የሚያሳይ ሕግ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/8 ስር ስለሰብዓዊ መብት በተመለከተ የተደነገገውም በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት የምንከተለው ሞዴል ወንጀል የመቆጣጠር ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ፣አከበበርና ማሟላት ጋር በተያያዘም ሕጉ ትኩረት መስጠቱን ስለሚያመላክት ፍትሐዊ ሒደት የመከተል ሞዴል በሕጉ መንጸባረቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉን የተመለከትን እንደሆነ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ስለሚያዝበት፣ ስለብርበራ፣የተያዘ ሰው ፍርድ ቤት መቅረብ ስላለበት ጊዜ እና ሁኔታ፣በወንጀል ምርመራ ወቅት ቃሉን ለመስጠት ያለመገደድና ዝም የማለት መብት ያለው ስለመሆኑ፣የተያዘው ሰው ለምርመራ ዓላማ ተጨማሪ ጊዜ በእስር ላይ የሚቆየው በፍርድ ቤት ፈቃድ መሆኑ፣በዋስትና ወረቀት የመለቀቀ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ሲከሰስም ስለወንጀሉ አፈጻጸም በቂ ዝርዝር ከያዘ የክስ ማመልከቻ ጋር መጥሪያ ደርሶት ችሎት ቀርቦ በግልጽ ችሎት የመዳኘት፣ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የመመርመር፣ አለኝ የሚለውን መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ራሱን የመከላከልና የመሰማት መብት እንዳለው በተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ መደንገጉ የተከሰሰ ሰው መብት የተጠበቀበትን ወንጀል የመቆጣጠር ሂደትን ማዕከል ያደረገ ወንጀል የመቆጣጠር እና ፍትሐዊ ሂደት የመከተል የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት

ሞዴሎችን አጣምሮ የያዘ ሕግ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ድንጋጌዎችን የያዘ ሕግ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ሥነ ሥርዓት ሕጉ በዚህ መልኩ ከያዛቸው ድንጋጌዎች መካከል የተከሰሰ ሰው በሌለበት ክሱ ስለሚሰማበት ሥርዓት በተመለከተ በቁጥር 161 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተዘረጋው ሥነ ሥርዓት ይገኝበታል፡፡

ከተያዘው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተፈጻሚነት ያለው የተከሰሰ ሰው በሌለበት ነገሩ ስለሚሰማበት ሥነ ሥርዓት የሚደነግገው የወ/መ/ሥ/ሥሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) እንደሚከተለው ይነበባል፡-

" (2) …ከዚህ በታች በተመለከቱት ወንጀሎች ካልሆነ በቀር ተከሳሹ በሌለበት የወንጀል ክስ አይሰማም፡፡(ሀ) ከአሥራ ሁለት ዓመት በታች በማያንስ ጽኑ እስራት የማያሳስር ወንጀል የሠራ … ሲሆን ነው፡፡" የሚል ሲሆን የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ቅጅ ደግሞ "(2) No accused person may be tried in his absence … unless he is charged with: (a) an offence punishable with rigorous imprisonment for not less than twelve years."የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

ከሕግ አተረጓጎም ጽንሰ ሀሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው የተለያዩ የአተረጓጎም ስልቶችንና መርሆዎችን በመጠቀም አንድ ሕግ ወይም የሕግ ድንጋጌ ሊተረጎም የሚገባው ሕጉ ወይም የሕጉ ድንጋጌ አሻሚ፣ ግልጽነት የጎደለው፣አንዱ ድንጋጌ ከሌላው ጋር የሚጣረስ ሲሆንና የሕግ አውጪውን ሀሳብ በግልጽ የማያሳይ ሆኖ የሕግ አውጪውን ሀሳብ ለማግኘትና በሚተረጎመው ሕግ ወይም ድንጋጌ ለማሳካት የታቀደው ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ለማድረግ ሕጉን/ድንጋጌውን መተርጎም የግድ የሚል ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው ሕጉ/የሕጉ ድንጋጌ ግልጽ በሆነ ጊዜ በቀጥታ ተግባራዊ እንዲሆን ከማድረግ ባለፈ ትርጉም እንደማያስፈልገው ነው፡፡

በመሰረቱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20፣ በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 14(3/መ) ፣በኢፌዲሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ላይ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161 ስር ከተደነገገው መረዳት እንደሚቻለው በመርህ ደረጃ የወንጀል ክስ ተከሳሹ በሌለበት አይሰማም፡፡ የዚህ መርህ ልዩ ሁኔታ ከላይ ይዘቱ የተጠቀሰው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) እና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ለ) ስር በመንግስት ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሆነው በጽኑ እስራት ወይም ከብር 5,000.00 በላይ በሚያስቀጡ ከባድ ወንጀሎች የተከሰሰ እንደሆነ በሚል የተገለጸው ነው፡፡ ይህም ሲባል በሌላ ልዩ ሕግ ላይ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደጠበቀ ሆኖ ማለት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው እና በሌሎች ሕጎቻችን የመንግስትን፣እና የአገሪቱን ሕዝቦች ጥቅም እና የተጎጂዎችን መብት ለመጠበቅ በተለያየ መንገድ ያንጸባረቁት አቋሞች እንደተጠበቁ ሆነው ይህ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) የተከሰሱ ሰዎችን መብት ባስጠበቀ መልኩ ወንጀልን የመቆጣጠር ቅይጥ ሞዴሎች የሚከተል የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት እንዳለን ማሳያ ሊሆን የሚችል ድንጋጌ እንደሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም ምንም እንኳን የሥነ ሥርዓት ሕጉ ሕገ መንግስቱን እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውን ቀድሞ የወጣና ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ እድሜ ያለው ቢሆንም የሥነ ሥርዓት ሕጉ የተከሰሱ ሰዎችን መብት ባስጠበቀ መልኩ ወንጀልን የመቆጣጠር ቅይጥ ሞዴል ነጸብራቅ የሆኑ ድንጋጌዎችን በመያዝ የወጣ ነው

በሚያስብል መልኩ አብዛኛዎቹ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በአካል በተገኙበት ተሰምቶ እንዲወሰን መፈለጉን እና ለተከሳሾች የመሰማትና ራስን የመከላከል መብት እዉቅና ከመስጠቱም ባሻገር ለተከሰሱ ሰዎች መብት ከፍተኛ ጥበቃ ማድረጉን ከዚህ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ይዘት፣መንፈስና ዓለማ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሕግ አውጪው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ን በመደንገግ አቋም ሲወስድ ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ የወንጀል ክሶች ማለትም በወንጀል ሕጉ(በ1949 በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ) መነሻ ቅጣታቸው በአስራ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ውስን መሆናቸውን እና አብዛኞቹ የወንጀል ክሶች ተከሳሽ ባለበት ብቻ የሚታዩ እንደሆኑ እያወቀ ነው፡፡ ሕግ አውጪው እንዲህ አይነት አቋም የያዘው ወንጀል ፈጽመዋል በሚል የሚከሰሱ ሰዎች ከፍርድ ሂደት ተሰዉረዉ የወንጀሉ ተጎጂዎች ፍትህ የማግኘት መብት እንደማይጣስ ብሎም የወንጀል ሕጉ ዓላማ ከግብ ሳይደርስ ቀርቶ ጠቅላላዉ ሕብረተሰብ ተገጂ እንዳይሆን ማድረግ እንደሚቻል በማመን ነው፡፡ ይህም እምነቱ እውን እንዲሆን ፖሊስ እና ሌሎች በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው ሕግ አስፈጻሚዎች የተከሰሰውን ሰው በአድራሻው ፈልገው መጥሪያ እንዲደርሰው ማድረግ እንደሚችሉ እና ተከሳሹ መጥሪያ ደርሶትም ሆነ መጥሪያ ላለመቀበል ብሎ በመሰወሩ ምክንያት መጥሪያ ማድረስ ካልተቻለ ወይም በሌላ በቂ ባልሆነ ምክንያት ተከሳሹ ፍርድ ቤት ካልቀረበ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ተይዞ እንዲቀርብ ተገቢውን ትእዛዝ እንደሚሰጥና ፖሊስ ብርቱ ጥረት አድርጎ ተከሳሹን ካለበት ፈልጎ ችሎት እንዲያቀርበው ከፍተኛ ኃላፊነት በፖሊስና በሌሎች ሕግ አስፈጻሚ አካላት ላይ መጣሉን ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 160 እና 161(1 እና 2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ይዘቱ የተጠቀሰዉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ድንጋጌ ለብቻዉ ሲታይ *በወንጀል የተከሰሰ ሰው በሌለበት ክሱ ሊሰማ የሚችለው የተከሰሰበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ (offence punishable with rigorous imprisonment for not less than twelve years) ሲሆን ብቻ ነው* የሚል ግልጽ ይዘት ያለው ድንጋጌ በመሆኑ ትርጉም ሳያስፈልገው በቀጥታ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ትርጉም የሚሻዉ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል የሚያስቀጣው የጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ሆኖ የጽኑ እስራት ጣሪያ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት በላይ በሆነ የእስራት ቅጣት የሚያስቀጣ ሆኖ በተደነገገ ጊዜ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ተከሳሹ የተከሰሰበት የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ከሚያስቀጣዉ ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በሕጎቻችንና በወንጀል ፍትህ ፖሊስ ስለምንከተለው የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎች የተንጸባረቀውን እና የተከሰሱ ሰዎችን መብት ባገናዘበ መልኩ ሊተረጎም ይገባል፡፡እንዲሁም ተከሳሽ በሌለበት ክስ መስማት(የፍርድ ሂደት ማከናወን) ከላይ እንደገለጽነው ልዩ የሥነ ሥርዓት ሁኔታ(ድንጋጌ) በመሆኑ በሕግ አተረጓጎም ጽንሰ ሀሳብ/መርህ መሰረት በጠባቡ መተርጎም እንዳለበት ከግንዛቤ ማስገባት ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ የመሰረተው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ሙከራ ፈጽማለች በሚል በመሆኑ ይህ ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ነው፡፡የዚህ ድንጋጌ መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያንስ በመሆኑ የተነሳ በተያዘው ጉዳይ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ን መተርጎም ያስፈልጋል፡፡ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት መፈጸሟ በዐቃቤ ማስረጃ ቢረጋገጥና ተጠሪ በማስተባበል መከላከል አለመቻሏ ተረጋግጦ ጥፋተኛ ብትባል ልትቀጣ የምትችለው በሕጉ አንቀጽ 540 ስር በተደነገገው እና በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ አስራ ሁለት ስር በተመለከተው ደረጃና እርከን መሰረት ነው፡፡ በመመሪያው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ለተደነገገው የእስራት ቅጣት 6 ደረጃዎች የወጣለት ሲሆን የደረጃ 1 መነሻ እርከን እርከን 21 ሲሆን ደረጃ 6 ደግሞ መነሻ ቅጣቱ እርከን 33 ላይ እንዲሆን የተደረገ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከወጡት 6 ደረጃዎች መካከል ሁለቱ ደረጃዎች ማለትም በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመደበው የእስራት መነሻ ቅጣት ብቻ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን ቀሪዎች 4 ደረጃዎች ከአስራ ሁለት ዓመት በአነሰ ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ መነሻ እርከኖች የያዙ ናቸው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በተከሰሰችበት ወንጀል ጥፋተኛ ብትባል በአብዛኛው ልትቀጣ የምትችለው ከአስራ ሁለት ዓመት ባነሰ ጽኑ እስራት ሊሆን የሚችልበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተጠሪ ፈጸመች ተብላ የተከሰሰችው ተራ የሆነ የግድያ ሙከራ ወንጀል በመሆኑ ተራ በሆነ ግድያ ሙከራ ጥፋተኛ ብትሆን ፍርድ ቤቱ ከነገሩ ሁኔታዎች በመነሳት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ስር ከተደነገገው አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ዝቅ ብሎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179/ሐ ስር በተደነገገው መሰረት ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ተጨማሪ እድል በመኖሩ ይህም ተጠሪ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት በአነሰ ልትቀጣ እንደምትችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ሲጠቃለል በተከሳሽ ላይ በቀረበው የወንጀል ክስ የተጠቀሰው ድንጋጌ የሚያስቀጣው መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት ባነሰ ጽኑ እስራት ሆኖ የድንጋጌው ጣሪያ ደግሞ ከአስራ ሁለት ዓመት በላይ ከሆነና ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ሊቀጣ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ከሆነ ተከሳሹ በሌለበት ክርክሩ ሊሰማ አይገባም፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተው የወንጀል ክስ ተጠሪ ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ቅጣት ሊወሰንባት የሚችልበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰችበትን ድንጋጌ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ የፍርድ ሂደቱ ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በሰጠው ትእዛዝም ሆነ በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትእዛዝ በመሰረዙ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 266638 ላይ በቀን 07/07/2014ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 225068 ላይ በቀን 10/09/2014ዓ/ም ትዕዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ሲጠይቁ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸው፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሠ/መ/ቁጥር 231732

## የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አራት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽማለች በሚል ክስ መስርቶባታል፡፡ ለተጠሪ በአድራሻዋ መጥሪያ እንዲደርሳት ታዞ በአድራሻዋ ባለመገኘቷ መጥሪያ ማድረስ ባለመቻሉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላትም አልቀረበችም፡፡ይህንን ተከትሎ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 266638 ላይ በቀን 07/07/2014ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ላይ በተደነገገው መሰረት ተከሳሹ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በሚቀጣ ድንጋጌ የተከሰሰ እንደሆነ ክርክሩ በሌለበት ሊቀጥል አይችልም፡፡ ተጠሪ በተከሰሰችበት ወንጀል ጥፋተኛ ብትሆን ልትቀጣ የምትችለው መነሻውን 5 ዓመት ጣሪያውን 20 ዓመት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች በዚህ ፍቅድ ሥልጣን ውስጥ ቅጣቱን ስለሚወስን ተጠሪ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ላትቀጣ ትችላለች፡፡ስለሆነም ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ሊያስቀጣ የሚችል ስለሆነ በሌሉበት የሚታይ ባለመሆኑ ተጠሪ ሲገኙ መዝገቡን አመልካች ማንቀሳቀስ እንዲችል መብት ተጠብቆለታል በማለት መዝገቡን በመዝጋት የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ የወንጀል ዓይነቶች በወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 161 (2) የተጠቀሱት ብቻ ናቸው፡፡ አንደኛው ሁኔታ በፊደል (ሀ) የተገለፀው ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ሁኔታ በፊደል (ለ) የተገለፀው በወ/መ/ሕ/ቁ.354-365 ድረስ ያሉትን ወንጀሎች ፈፅሞ ፅኑ እስራት ወይም ከአምስት ሽህ ብር በላይ መቀጮ በሚያስቀጣ ወንጀል

የተከሰሰ ሰዉ ሲሆን ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በቀላል እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ እንደማይሰማ ያስረዳል፡፡

ተከሳሽ በሌለበት ማየት የሚቻለዉ ለፍትህ ጥቅም ሲባል ቢሆንም ተከሳሹ ስለ ክሱ እና ክርክሩ ሂደት እዉቅና እንዲኖረው ለማድርግ ፍ/ቤቱ ሁሉንም የማሳወቂያ ሂደቶች በመጠቀም የማሳወቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ተከሳሽ በክርክሩ የመገኘት መብቱን በግልፅ የተወ ሆኖ ሲገኝ ግን በራሱ ክርክሩን በመተው (waive) ምክንያት በሌለበት ሊታይ ይችላል፡፡ ይህ የመተው መብት ተገቢ የሚሆነው ፍ/ቤት የራሱን ግዴታ በተለይ ተከሳሹ መከሰሱን እንዲያውቀው ጥሪ አድርጎ እና መጥሪያው የደረሰው መሆኑ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ነው፡፡ ሃገራት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩን ሊመለከቱ የሚችሉ ቢሆንም ይህ የሚቻለው በቅድሚያ ለተከሳሽ በቂ ጊዜ በመስጠት በአግባቡ መጥሪያ ተሰጥቶት ለክርክሩ እንዲቀርብ የችሎቱ ጊዜና ቦታ ተገልፆ የተጠራ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ የቀጠለው ተከሳሹ የመገኘት መብቱን በመተው ምክንያት በሆነ ጊዜ ግን በክርክር የመገኘት መብት ሊታይ የሚገባው ከተከሳሽ የመሰማት መብት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከተጎጂዎችና ከምስክሮች እንዲሁም ከጠቅላላው ማህበረሰብ ጥቅምና ፍላጎት አኳያ ጭምር መሆን አለበት፡፡ የወንጀል ክስ ጉዳይ ዐ/ህግንና ተከሳሽን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የወንጀል ሰለባዎችንም የሚመለከት ሆኖ እዉነትን በመፈለግ ፍትህን የማረጋገጥ ጉዳይ ጭምር በመሆኑ ከዚህ አኳያም ማየት ይገባል፡፡ ይህ ህጋዊ የማህበረሰብ ጥቅም በዋናነት የሚገለፀውና የሚረጋገጠው ደግሞ የተከሰሰ ሰው በወንጀል ክርክር ሂደት በፍ/ቤት እየቀረበ ሲከታተል በመሆኑ የራሱን የተከሳሹን መብት፣ የተጎጂዎችን እና የምስክሮችንም ፍላጎት እንዲሁም ጥቅም የሚያስጠብቅ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

የሥነ-ሥርዓት ሕግ ዓላማውም የሥነ-ሥርዓታዊ ፍትሕን በማረጋገጥ ክርክር ወጭና ጊዜ ቆጣቢ ሆነ ውጤታማ በሆነ አግባብ እንዲመራ ማስቻል ነው፡፡ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትሕ /procedural justice/ በተመሳሳይ በመሠረታዊ ሕግ እንደተመለከተው መብትና ፍትሕ /substantive justice/ መከበርና መተግበር አለበት፡፡ አንዱን ከአንዱ ማበላለጥ ሆነ አንደኛውን የፍትሕ ዘንግ ለማስከበር ሌላኛውን መጣስ ተገቢ አይደለም፡፡ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ሲተረጎም የወንጀል ሕጉ ሊያሳካው የፈለገው ግብ ከተከሳሽ ሰብዓዊ መብት አተገባበር ጋር ተጣጥሞ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ ሂደትም ድንጋጌው ውጤት ሊሰጥ በሚችል መልኩ መተርጎም አለበት፡፡ በወንጀል ጉዳዮች አከራካሪዉ ነጥብ ከ12 ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ የሚለዉ አገላለፅ ምን ማለት ነው የሚለው ነው፡፡ አንዱ የሚነሳው ሃሳብ እና በአብላጫው የውሳኔ ሃሳብም የተገለጸው ተከሳሽ በሌለበት ክሱ ሊሰማ የሚገባው ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል ፍ/ቤቱ በተጨባጭ የሚወስነው ቅጣት 12 ዓመትና በላይ ሆኖ መገኘት ነው የሚል ሲሆን በወንጀል ክርክር ሂደት ማስረጃው ሳይሰማ አስቀድም የሚወሰነውን ቅጣት ምን ያህል እንደሚሆን ማወቅ አይቻልም፡፡ ለምሳሌ በወ/ሕ/ቁ. 27(1) እና 539 ከባድ ሰው ግድያ ሙከራ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የወንጀሉ አፈፃፀም በማስረጃ ተመዝኖ ዝቅተኛውን ቅጣት በ10 ዓመት ፅኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል፡፡ በሌሎች ወንጀሎችም ተመሳሳይ ሁኔታ ይገጥማል፡፡ የቅጣት አስተያየትና

ክርክር በግራቀኙ ወገኖች ሳይደረግ፣ የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች ሳይታወቁ፣ የወንጀሉ ዝርዝር አፈጻጸም ሳይታይ፣ የደረሰው ጉዳት በማስረጃ ሳይጣራ ቅጣት መጠኑን መለየት አይቻልም። ተከሻሽ ጉዳዩ በሌለበት ሊታይ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ማስረጃ ከመስማቱ በፊት በመሆኑና ቅጣቱን ከማስረጃና ከክርክር በፊት በትክክል ለይቶ አስቀድሞ ማወቅ ስለማይቻል ድንጋጌው ይህን ሀሳብ የያዘ ነው ለማለት አይቻልም።

ሁለተኛው ሃሳብ የወንጀሉ ድንጋጌ የቅጣት መነሻ 12 ዓመት ፅኑ እስራት በላይ ከሆነ ነው የሚል ሲሆን የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎችን ስንመለከት መነሻ ቅጣታቸው 12 ዓመት የሚሆን ባይኖሩም ከዚህ በታች መነሻ ኖሯቸው እስከ እድሜ ልክ ወይም ሞት እስከሚደርስ የሚያስቀጡ ድንጋጌዎች የወ/መ/ሕ/ቁ. 522 (ከባድ ሰው ግድያ)፤ 638 (ዘረፋ)፤ 637/2 (ከባድ ውንብድና)፤ 639 (የባህር ላይ ውንብድና) እና 270 (በመንግስት ግዛት ሀገር የሚፈጸሙ ወንጀሎች) ናቸው። በ1996 በተሻሻለዉ የወንጀል ህግ መነሻ ቅጣታቸው በ1949 ከነበረው ከፍ ብሎ ከ12 ዓመት በላይ የተደረጉ ድንጋጌዎችም አሉ (ለምሳሌ የወ/ሕ/ቁ. 620/3 እና 627/1 መመልከት ይቻላል)። የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 161/2 የተቀረጸው የተከሳሽ ሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ልዩ ሁኔታ ሆኖ የሕዝብ ጥቅምን ለማስፈን ነው። ለእነዚህ ውስን ድንጋጌዎች የተቀረጸ ነው በማለት መተርጎም ሕጉ ውጤት እንዳይኖረው ከማድረግ ባለፈ የሕብረተሰቡን ጥቅም የሆነውን የህግ የበላይነት መኖርን የሚያስጠብቅ አይደለም።
ሕጉ የወጣለትን ዓላማ ለማሳካትና ውጤት በሚሰጥ መልኩ መተርጎም ያለበት በወንጀል ህጉ ተከሳሽ የተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ላይ የተመለከተው የቅጣት መጠን በመመልከት ከ12 ዓመት በላይ የመቀጣት እድል ያለው መሆን አለመሆኑን በመመርመር የሚወሰን እንጂ ተከሳሽ ግለሰብ ሊቀጣ የሚችለውን ልዩ ቅጣት በማስላት ነው። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የተከሰሱበት የወ/ሕ/ቁ. 27/1 እና 540 ከ5-20 ዓመት ጽኑ እስራት ያስቀጣል። ከድንጋጌው የቅጣት መጠን አንጻር አማካኙ ከ12 ዓመት በላይ በመሆኑ ተጠሪ ከ12 ዓመት በላይ ሊቀጡበት የሚችልበት እድል ሰፊ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለቡት ሊታይ የሚችል ነው፤ ይህ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በሌለቡት ሊታይ አይችልም በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ማስረጃ ተሰምቶ ጉዳዩ እንዲወሰን ወደሥር ፍርድ ቤት ሊመለስ ይገባል በማለት ከአብላጫው ሃሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ 217557

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አክስዮን ማህበር - ጠበቃ ፐ/ር ጥላሁን ተሾመ እና ነ/ፈጅ አበራ በቀለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ - ነ/ፈጅ ሰለሞን ነጋሽ - ቀረቡ

2ኛ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ - ነ/ፈጅ ታፈሰ ኩሳ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 28/03/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262067 በቀን 05/01/2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀን 01/02/2014 ዓ.ም ለባለጉዳዮች ተነቧል የተባለው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቀ ነው፡፡ ክርክሩ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረው የአሁን አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ጣ/ገብቶ ተከራክሯል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ከሳሽ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ/ም እና በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ነገር ክርክሩን አቅርቧል፡፡ ባቀረበው መቃወሚያ ተከሳሽ ለጣ/ገብ በ04/02/2013 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ቋሚ መመሪያ እስኪወጣ ድረስ በማለት የሰጠውን መመሪያ ለማብራራት የተጻፈ ደብዳቤ እንጂ አስተዳደራዊ ውሳኔ አይደለም፡፡ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ አዋጅ ቁጥር 1183/12 ከመውጣቱ በፊት የወጣ ስለሆነ አዋጁ በመመሪያው ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፡፡ በተጨማሪም ከሳሽ ተከሳሽ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታውን በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 51 መሰረት ለተከሳሽ ተቋም የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ያላቀረበ ስለሆነ ከሳሽ

የተከሳሽን አስተዳደራዊ መፍትሄዎች አሟጦ ያልጨረሰ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጣ/ገብ በበኩሉ ወደ ክርክሩ ገብቶ ባቀረበው መቃወሚያ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ ጣ/ገብ ለተከሳሽ ለጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ለመስጠት ሲሆን በግልባጭ ከሳሽ እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡ ሆኖም ከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 መሰረት ለተከሳሽ ምንም ቅሬታ ያላቀረበ ስለሆነ በአዋጁ መሰረት አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን አሟጦ ያልጨረሰ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ከሳሽ በአዋጁ መሰረት የአስተዳደር ውሳኔው በተወሰነ 30 ቀናት ውስጥ ክስ ማቅረብ ሲኖርበት ግዜው ካለፈ በኋላ በማቅረቡ በይርጋ ይታገዳል፡፡ እንዲሁም በራሱ 22ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው ውሳኔ በ23ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተሻረ ስለሆነ ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ለመቃወሚያ ክርክሩ ከሳሽ በሰጠው መልስ መቃወሚያዎቹ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2) መሰረት የቀረቡ አይደሉም፤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ እንደሚለው ቋሚም ሆነ ግዜያዊ መመሪያ አይደለም፤ የቦርድ ሰብሳቢ መመሪያም ሆነ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የለውም፤ ስልጣን ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤ እነዚህ ደብዳቤዎች የአስተዳደር መመሪያዎች እንዲሁም የአስተዳደር ውሳኔዎች አይደሉም፡፡ መብታችን በመነካቱ ነው ፍ/ቤት የመጣነው፡፡ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ በተጻፈው ደብዳቤ መነሻ ላቀረብነው ቅሬታ ምላሽ የተሰጠን አዋጅ ቁጥር 1183/12 ከወጣ በኋላ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም ስለሆነ ይህንኑ መሰረት አድርገን ነው ክስ ያቀረብነው፡፡ በአስተዳደር ተቋም ውስጥ ያለውን መፍትሄ አሟጦ መጨረስን በተመለከተ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በቦርድ ሰብሳቢ የተጻፈው ደብዳቤ እንደደረሰን በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በውሳኔው ላይ ቅሬታችንን በመግለጽ ለቦርዱ ሰብሳቢ ለራሳቸው አመልክተናል፤ በግልባጭም ለጣ/ገብ አሳውቀናል፡፡ ጣ/ገብም በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጠይቋል፡፡ ቦርዱ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አቤቱታችንን እንዳልተቀበለ በግልባጭ አሳውቆናል፤ ደብዳቤው በአድራሻ የተጻፈው ለጣ/ገብ ነው፡፡ ተከሳሽ ቅሬታ ስናቀርብ ወደ ቅሬታ ሰሚ ሂዱ ብሎ አልመራንም፤ አሁንም ቢሆን ተከሳሽ ቅሬታ ሰሚ አካል ያቋቋመ ስለመሆኑ ይፋ አላደረገም፡፡ በመሆኑም መቃወሚያው ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይርጋ መቃወሚያውን በተመለከተ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ እንደደረሰን በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በውሳኔው ላይ ቅሬታችንን አቅርበን ቦርዱ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አቤቱታችንን እንዳልተቀበለው በመግለጽ ይርጋ ጊዜውን አቋርጦታል፡፡ መብትና ጥቅም የለውም የተባለውን በተመለከተም በክሱ መሰረት ከተወሰነልን በ22ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው ውሳኔ ደግሞ ለመወሰን የሚያስችለን ስለሆነ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም አለን በማለት ተከራክሯል፡፡

የመቃወሚያ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ ደብዳቤዎቹ የአስተዳደር መመሪያዎች አይደሉም እንዲሁም የአስተዳደር ውሳኔዎች አይደሉም፤ መብታችን ስለተነካ

ነው ፍ/ቤት የመጣነው በማለት ለመቃወሚያው ክርክር ቢያቀርብም ከሳሽ ጥቅምት 30/2013 ዓ.ም ባቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም እና 04/02/2013 ዓ.ም የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ የጠየቀ ስለሆነ ክርክሩ ከክሱ አንጻር ተገቢነት የለውም፡፡ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበው ቅሬታ ላይ የሰጠው ምላሽ መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተጻፈ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ በዚህ ደብዳቤ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ ቅሬታ ያቀረበው በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 1183/12 የወጣው ደግሞ መጋቢት 29/2012 ዓ.ም ከመሆኑ አንጻር በአስተዳደር ውሳኔው ላይ ቅሬታው ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ የቀረበው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 የሚሸፈን ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሰረት በአዋጁ አንቀጽ 51 ማንኛውም የክለሳ አቤቱታ ፍ/ቤት የሚቀርበው የመጨረሻ በሆነ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ብቻ መሆኑ የተደነገገ ስለሆነ የአስተዳደር ውሳኔውና በአስተዳደር ውሳኔው ላይ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 በማይሸፈንበት ሁኔታ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ ክለሳ አቤቱታ ማቅረብ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡ በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 56(2) መሰረት ፍ/ቤት የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን የአስተዳደር ውሳኔ ሊያጸና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል ሊሽር እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ የአስተዳደር ውሳኔው እና ቅሬታው በአዋጁ በማይሸፈኑበት ሁኔታ ፍ/ቤት በቅሬታው ላይ የተሰጠውን ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ የአስተዳደር ውሳኔውን ማጽናት ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መሻር አይችልም፡፡ በመሆኑም ሌሎች መቃወሚያዎችን መመርመር ሳያስፈልግ የቀረበውን የክለሳ አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 ስር የማይሸፈን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በቀን 28/03/2013 ዓ/ም ባቀረበው ማመልከቻ በተሰጠው ብይን ተፈፀሙ የሚላቸውን የህግ ስህተቶች ዘርዝሮ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ፍሬ ነገር ክርክር አላግባብ አዛብቶ በመረዳት እና የአስተዳደር ሥነ ሥርአት አዋጁን ተፈጻሚነት በተመለከተ የተሳሳተ ትርጓሜ በመስጠት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ብይኑ እንዲሻርና ስር ፍ/ቤት ወደ ፍሬነገሩ በመግባት ክርክሩን ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ እንዲወሰንልን በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ስር አይሸፈንም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 29/07/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የስር ክርክሩን አጠናክሮ የአስተዳደር ሥነ ሥርአት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከ11 ወራት በኋላ በወጣ ህግ ስለማይዳኝ እና ከአዋጁ መውጣት በፊት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በቀን 29/07/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የስር ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠ በመሆኑ የክለሳ አቤቱታው በአዋጁ የማይሸፈን ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ብይን ትክክለኛና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ሊጸና ይገባል፡፡ ይህ ታልፎ ብይኑ የሚሻር ከሆነ ግን የስር ፍ/ቤት ወደ ፍሬ ነገሩ በመግባት አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ከመታዘዙ በፊት በተጠሪዎች በኩል በተነሱት ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን እንዲሰጥባቸው እንዲታዘዝ በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አይሸፈንም፤ ፍርድ ቤቱም የክለሳ አቤቱታውን ለመመልከት ስልጣን የለውም በማለት ብይን የሰጠው በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለቀረበው ቅሬታ የተሰጠ ምላሽ መሆኑን ተገንዝቦ፤ ነገር ግን በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተጻፈ በመሆኑና በዚህ ደብዳቤ ቅር በመሰኘት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ቦርድ ሰብሳቢ ቅሬታ ያቀረበው በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1183/12 የወጣው ደግሞ መጋቢት 29/2012 ዓ.ም በመሆኑ ለቦርዱ ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 የሚሸፈን አይደለም፤ የአስተዳደር ውሳኔውና በአስተዳደር ውሳኔው ላይ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 በማይሸፈንበት ሁኔታ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ ክለሳ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከወጣበት ምክንያት አንዱ የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎችን እና ሥነ ሥርዓት በመደንገግ እንዲሁም በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ሰው የውሳኔዎቹን ህጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

“የአስተዳደር ውሳኔ” ማለት ደግሞ የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2(3) ከተሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡ በእንዲህ አይነት የአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው ውሳኔው በከፍተኛው

ፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 48(2) እና 49(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በአስተዳደር ተቋሙ በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ በሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው የክለሳ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል መደንገጉን ሲሆን ከዚህ በቀር የአስተዳደር ውሳኔው የተሰጠው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከተሰጠ ውሳኔ ጋር በተያያዘ በመሆኑ የክለሳ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም እንዲሁም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስልጣን አይኖረውም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

በ1952 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለ አስተዳደር ክፍሎች በሚደነግገው አንቀጽ ሶስት ምዕራፍ አንድ ቁጥር 401(1) እና 402(1) ሥር ከተመለከተው ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የአስተዳደር አካላት በህግ የታወቀላቸው የተግባር ስልጣን ከሚዘረጋበት ውጭ ወይም በህጉ የተገደዱትን ሁኔታዎች ወይም ፎርም ባለመከተል የሚፈጽሟቸው ሥራዎች ፈራሾች ሲሆኑ ይህን ፈራሽነት ማንኛውም ባለጉዳይ ሁሉ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ስለሆነም አስተዳደሩ በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ ሲወስን ወይም በህግ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ወይም የተዘረጋውን ስርዓት ባለመከተል ወስኖ ሲገኝ በአስተዳደሩ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ አቤቱታ ቀርቦ ውሳኔው በፍርድ ፈራሽ እንዲሆን ሊወሰን እንደሚችል አስቀድሞም ቢሆን በፍትሐ ብሔር ህጉ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ አመልካች በፅሁፍ ባቀረበው የክለሳ የዳኝነት ጥያቄ ላይ እንዲሁም በተጠሪዎች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተከትሎ ባቀረበው መከራከሪያ ላይ ወጥነት አለመኖሩን በማንሳት የስር ፍርድ ቤት የወሰነ ሲሆን ተጠሪዎችም ይህን በመከራከሪያነት አያይዘው ማንሳታቸውን ተመልክተናል፡፡ ክርክሩ የሚመራበትን ሥነ ስርዓት በተመለከተ የክለሳ ስነ ስርዓት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 58 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ለክለሳ ለክርክሩ በአዋጁ የተመለከቱ ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች የሚፈፀሙበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ የሚመራው በፍትሐ ብሐር ሥነ ሥርዓት ህጉ አግባብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከስነ ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ከሳሽ በህጉ የተፈቀደን መፍትሄ ከፍርድ ቤቱ ለማግኘት በፅሁፍ በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ ይገባዋል፡፡ በዚህ መልኩ በጽሁፍ ግልጽ የዳኝነት ጥያቄውን ካቀረበ በኂላ መቃወሚያን ለመወሰንም ይሁን በፍሬ ነገር ላይ በችሎት የሚያቀርብ ክርክር መሰረታዊ አላማው በጽሁፍ ያቀረበውን ክርክር ለማብራራት እንጂ በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ለማስተናገድ አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 83፣ 222፣ 224፣ 234፣ 235፣ 236፣ 241፣ 244፣ 245 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበው አቤቱታ የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥቅሙን የሚነካና የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ

በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከልስ ለመጠየቅ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ክርክሩ ሊመራና ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባውም ይህንኑ የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ስለሆነም ግራ ቀኙ የየበኩላቸውን ክርክር ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበው ቅሬታ ላይ የሰጠው ምላሽ መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል በሚል ለያይቶ መወሰኑ በግልፅ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ እና ከፍ ሲል የጠቀስናቸውን የህጉን ድንጋጌዎች ይዘት የተከተለ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በግልጽ በጽሁፍ የቀረበውን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽን ብቻ መሰረት በማድረግ የቀረበ አቤቱታ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ፤ ይህን ተከትሎም መሰል የክስሳ አቤቱታ ማቅረብ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፤ አመልካች ያቀረበው የክስሳ አቤቱታ በአዋጁ የሚሸፈን አይደለም፤ እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ብይን የሚነቀፍ ነው፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከእነሙሉ ይዘቱ በአግባቡ ሳይጤን፤ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከክርክሩ ውጪ በመውጣት የተሰጠ ብይን በመሆኑም የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262067 በቀን 05/01/2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ቀሪ ክርክር ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. ከስር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት አግባብ ይመለስ፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁጥር 204288

ጥር 24 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኘ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ ድርጅት፡- ነ/ፈጅ ሚኪያስ ሙሴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ማርቪልደን ካንፓኒ ሊሚትድ፡- ጠበቃ ፍቅሩ ባቲሶ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በባህር እና በየብስ ተጓጉዞ ሞጆ ደረቅ ወደብ የደረሰ እቃ በሐሰተኛ የማስጫኛ ሰነድ ወጪ ተደርጓል በሚል የእቃው ዋጋ እንዲከፈል በአጓጓዡ ላይ ለቀረበ ክስ ተፈጻሚነት የሚኖረው ህግ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ነው ወይስ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከተው የፍትሐ ብሔር ህጉ ድንጋጌ ነው የሚለውን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች 4ኛ ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው ክስ በአመልካች በመርከብ ተጭኖ ወደ ሀገር የገባ እቃ ሞጆ ደረቅ ወደብ ከደረሰ በኋላ አመልካች እቃውን በሐሰተኛ ሰነድ በመልቀቅ ግዴታውን ስላልተወጣ ከስር 1ኛ-3ኛ ካሉት ተከሳሾች ጋር አመልካች በአንድነት እና በነጠላ የእቃውን ዋጋ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የክሱን አጠቃላይ ይዘት እና ዋና ዋና ዝርዝሮችን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ እቃውን ከተረከበበት ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ስላልሰጠኝ ክሱ በስድስት ወር ይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ስራውን የሚያከናውነው በአዋጅ ቁጥር 548/99 መሰረት በመሆኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40/2 መሰረት እቃውን ከተረከበበት ወይም መረከብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በ6 ወር ውስጥ ተጠሪ የክሱን ዝርዝር የያዘ ማስጠንቀቂያ ስላልሰጠ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት በብይን የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በዚህ ብይን ላይ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ ክስ ያቀረበው በተጭበረበረ ሰነድ ወጪ የተደረገን

እቃ በሚመለከት ነው፡፡ ይህም ክሱ ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል ጋር ተያይዞ የቀረበ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይርጋ ድንጋጌ አዋጅ ቁጥር 548/99 አንቀጽ 40/2 ሳይሆን የፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 2143/1 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት ይርጋ ስለሆነ የተጠሪ ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ሽሮ በፍሬ ነገር ክርክሩ ላይ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡

አመልካች በመጋቢት 17 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትን ውሳኔን በመቃወም ለማሳረም ሲሆን የቅሬታው ይዘት ተጠሪ በማጓጓዣ ውል መሰረት ለአመልካች እቃ ማስረከቡን አልካደም፡፡ የአመልካች የውል ግዴታ የሚያበቃው ሞጆ ደረቅ ወደብ ላይ እቃውን ሲያስረክብ በመሆኑ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአዋጁ ተፈጻሚነት እቃው በጉዞ ላይ እያለ ብቻ እንደሆነ በመቁጠር ለጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ጉዳዩ ከውል ውጪ ድንጋጌዎች መሰረት መታየት አለበት ቢባል እንኳን በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ አንቀጽ 24 መሰረት የአዋጁን መከራከሪያ አመልካች ማንሳት ይችላል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ ይርጋን በተመለከተ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 548/99 አንቀጽ 40/2 መሰረት ነው? ወይስ በፍ/ህ/ቁጥር 2143 መሰረት ነው? የሚለውን ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በሚያዝያ 13 ቀን 2013 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ በሐሰተኛ ሰነድ እቃውን ከሞጆ ደረቅ ወደብ የተረከበው ክፍያ ሳይፈጽም የእቃው ገዢ ነው፡፡ ችግሩ የተፈጠረው በሻጭ እና በገዢ መካከል ስለሆነ ለጉዳዩ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ ተፈጻሚነት የለውም፡፡ አዋጁ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ያስቀመጠው ከተጫነ እቃ ጋር በተያያዘ የጎደለ፣ የተበላሸ ወይም የጠፋ ነገር ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ከውል ውጪ ለመጣ ኃላፊነት ህጉ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ አይጥልም፡፡ በሀሰተኛ ሰነድ እቃ ከደረቅ ወደብ ሲወጣ አመልካች የማጣራት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ምክንያት የሚቀርብ ክርክር በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ መሰረት ሊታይ አይገባም በመባሉ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ ቅሬታው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በግንቦት 03 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበው ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ እቃ በአመልካች በመርከብ ተጓጉዞ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ሞጆ ደረቅ ወደብ ከደረሰ በኋላ አመልካች በሀሰተኛ ሰነድ ንብረቱን ማስረከብ ለሌለበት ሰው ስላስረከበ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በአንድነት እና በነጠላ የእቃውን ዋጋ ይክፈለኝ በሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ መሆኑ በዚህ አዋጅ መሰረት ተጠሪ በስድስት ወር ውስጥ የክሱን ዝርዝር የያዘ ማስጠንቀቂያ ስላልሰጠኝ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ለመቃወሚያው በሰጠው ምላሽ አመልካች እቃውን በተጭበረበረ ሰነድ ማስረከብ ለማይገባው ሰው አስረክቧል የሚል በመሆኑ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ ነው የሚል አቋም ይዟል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ ሳይሆን የፍትሐ ብሔር ህጉ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የትኛው ህግ ነው? የሚለውን መለየት ይሆናል፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መኖሩ እና በዚህ ውል መነሻነት ተጠሪ ለአመልካች እቃውን ማስረከቡ በግራ ቀኙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 548/99 አንቀጽ 2/1 ላይ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ማለት ምንማለት እንደሆነ የተተረጎመ ሲሆን ቢያንስ በሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ አይነቶች፤ ወጥ በሆነ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መሰረት መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ከአንድ የተወሰነ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሌላ አገር ውስጥ የሚገኝ የማስረከቢያ ቦታ ለማስረከብ የሚደረግ የማጓጓዝ ስራ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል የትራንስፖርት አከናዋኙ እቃውን ተረክቦ ከአንድ በላይ በሆኑ የማጓጓዣ ዘዴዎች ማለትም በባህር እና በየብስ ወይም በአየር እና በየብስ ወይም በሶስቱም መንገዶች ካጓጓዘ በኋላ በማስረከቢያ ቦታ ላይ ለህጋዊ ተረካቢ ለማስረከብ የሚደረግ ውል መሆኑን ነው፡፡ ይህም ማለት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ወይም አጓጓዡ እቃውን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ እስኪያስረክብ ላለው ጊዜ የተረከበውን እቃ ደህንነት ጠብቆ ለህጋዊ አካል ለማስረከብ ግዴታ የሚገባበት ውል ነው፡፡ እንደዚሁም የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የኃላፊነት የጊዜ ወሰን በአዋጁ በአንቀጽ 15/1 ላይ በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለእቃው ኃላፊ የሚሆነው ከተረከበበት እስከ ሚያስረክብበት ላለው ጊዜ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል በአጓጓዡ ላይ እቃውን ከተረከበበት ጀምሮ እስከ ሚያስረክብ ባለው ጊዜ ውስጥ በእቃው ላይ ለሚደርስ ጉዳት ማለትም በእቃው መበላሸት ወይም መጥፋት በንብረቱ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ከውል የመነጨ ኃላፊነትን የሚያስከትል ይሆናል፡፡

በአጓጓዡ እና በእቃ አስጫኙ መካከል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል አለ ከተባለ በመካከላቸው አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ተፈጻሚነት የሚኖረው ህግ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 548/99 አንቀጽ 3/1 ላይ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ይህ አዋጅ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በማለት የሚያቀርበው አንዱ መከራከሪያ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆነው እቃው በጉዞ ላይ እያለ ጉዳት ቢደርስበት ነው፡፡ ነገር ግን ጉዳቱ የደረሰው በተጭበረበረ ሰነድ ለማይመለከተው ሰው ርክክብ በመደረጉ ስለሆነ አዋጁ ተፈጻሚነት የለውም በሚል ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መሰረት እቃውን ያጓጓዘው አመልካች ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ መሰረት ሳጓጓዘው እቃ ኃላፊነት የሚኖርበት እቃውን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚያስረክብ ሳለው ጊዜ ነው፡፡ አመልካች እቃውን ለተገቢው ሰው አለማስረከቡ ወይም በሀሰተኛ የማጓጓዣ ሰነድ ለማይመለከተው ሰው ማስረከቡ በውሉ ከማስረከብ ጋር ተያይዞ ካለበት ኃላፊነት አንጻር የሚታይ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል የማጓጓዣ ወይም የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል እያለ እና ከዚህ ውል ጋር ተያይዞ ለሚፈጠር አለመግባባት በግልጽ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ ተፈጻሚ እንደሚሆን በአዋጁ ተደንግጎ እያለ ይህን ልዩ ህግ በመተው ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከቱ የፍትሐ ብሔር ህጉ ድንጋጌዎች ሊታይ አይችልም፡፡

ሌላው የተጠሪ ክርክር ችግሩ የተፈጠረው በተጠሪ እና በእቃው ገዢ መካከል ስለሆነ ጉዳዩ በተጠቀሰው አዋጅ ሊታይ አይገባም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ከእቃው ገዢ ጋር ያለው ክርክር ወይም ገዢው የእቃውን ዋጋ ባለመክፈሉ የሚፈጠረው አለመግባባት በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ ሊታይ እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 548/99 መሰረት መታየት አለበት የተባለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር እንጂ የስር ተከሳሽ ከሆነው ከእቃው ገዢ አንጻር ባለመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በግራ ቀኙ መካከል ለተነሳው ክርክር ተፈጻሚነት የሚኖረው ህግ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ ሆኖ እያለ ይህ አዋጅ ተፈጻሚነት የለውም ማለቱ የአዋጁን ተፈጻሚነት ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

በመቀጠል በግራ ቀኙ መካከል ተፈጻሚነት ያለው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ነው ከተባለ የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም? የሚለውን ስንመለከት በአዋጁ አንቀጽ 40 ላይ ይርጋን አስመልክቶ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ በዚህም መሠረት ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች በሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ ካልቀረቡ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆኑ፣ ይሁንና ርክክቡ ከተፈጸመበት ቀን በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ የክሱን አጠቃላይ ይዘት እና ዋና ዋና ዝርዝሮች የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ወይም የዕቃዎች ርክክብ ያልተደረገ ከሆነ የዕቃዎች ርክክብ መደረግ ከነበረበት ቀን ቀጥሎ ካለዉ ቀን ጀምሮ ክስ ካልተመሰረተ የስድስት ወር ጊዜ እንዳበቃ ክሱ በይርጋ እንደሚቋረጥ ከአዋጁ አንቀጽ 40(1) እና (2) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ሁለቱ ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት የሚቻለዉ

አንደኛ የይርጋዉ መቁጠሪያ ጊዜ የሚጀምረዉ የዕቃዎች ርክክብ ከተደረገበት ቀን ወይም ርክክብ ያልተደረገ ከሆነም መደረግ ከነበረበት ጊዜ እንጂ ከሳሽ በዕቃዎቹ ላይ ጉዳት መድረሱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ አለመሆኑን ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ እና የስድስት ወር የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆኑባቸዉ የተለያዩ ምክንያቶች መኖራቸዉን ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነዉ ከሳሽ ርክክቡ ከተደረገበት ወይም ርክክቡ ያልተደረገ ከሆነም መደረግ ከነበረበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ የክሱን ዋና ዋና ይዘት የያዘ ማስታወቂያ ለተከሳሽ ማድረሱ የተረጋገጠ ሲሆን መሆኑንና ከዚህ ዉጭ ባለዉ ሁኔታ ማለትም ርክክቡ ከተደረገበት ወይም መደረግ ከነበረበት ቀን ጀምሮ የክሱን ዋና ዋና ይዘት የሚያሳይ ማስታወቂያ በስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ለተከሳሽ ያላስታወቀ ከሳሽ ርክክቡ ከተፈጸመበት ወይም መፈጸም ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ለፍርድ ቤት ካላቀረበ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የእቃው ርክክብ መደረግ የነበረበት ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ.ም. መሆኑን አመልካች የገለጸ ሲሆን ተጠሪ ርክክብ የተደረገው ወይም ሊደረግ የሚገባው በዚህ ቀን አለመሆኑን ክዶ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ ከህዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ በሚቆጠር 6ወር ውስጥ የክሱን ዋና ዋና ዝርዝር የያዘ ማስጠንቀቂያ ለአመልካች መስጠት ወይም በ6 ወር ውስጥ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ነበረበት፡፡ ተጠሪ ግን በተገለጸው የ6 ወር ጊዜ ውስጥ ለአመልካች ማስጠንቀቂያ ያልሰጠ ወይም ለፍርድ ቤት ክስ ያላቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል ማለቱ ህጉን የተከተለ ሆኖ እያለ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ በመጥቀስ በይርጋ አይታገድም ማለቱ በህግ አተረጓጎም እና አፈጻጸም ረገድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡

**ውሳኔ**

1ኛ. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 193744 በታህሳስ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 236260 በየካቲት 25 ቀን 2012 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

3ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትእዛዝ

በዚህ መዝገብ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

መ/ቁጥር 220042

ህዳር 30 ቀን 2015

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ሌሊሴ ደሳለኝ

ደጀኔ አያንሳ

ሀብታሙ እርቅይሁን

እስቲበል እንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሀና ሰለሞን ዘነበ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- 1.ወ/ሮ አስናቀች ወልዴ ገ/ማሪያም - አልቀረቡም

2.የካ/ክ/ከ/መ/ል/ማ/ጽ/ቤት - ዐቃቤ ህግ ወንድሽ አለሙ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶታል፡፡

## ፍርድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 168017 ላይ በ07/12/2013 ዓም የሰጠዉ ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 279899 ላይ በ22/02/2014 ዓም በትዕዛዝ ያፀናዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለ አቀረቡ ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ የሆነዉ አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራክረዋል፡፡ለክርክሩ መሰረት የሆነዉ በአመልካች በኩል በ20/08/2013 ዓ/ም በተጻፈ ባቀረቡት

የተሻሻለ ክስ ሲሆን ይዘቱም፡-በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 1168 የቦታዉ ስፋት 692 የሆነ ቦታ ከሟች እናታቸዉ በስጦታ ያገኙ መሆኑን 1ኛ ተጠሪ የዉርስ ይጣራ ጥያቄ አቅርበዉ ዉደቅ ሆኖባቸዉ ሳለ 2ኛ ተጠሪ በህገ ወጥ መንገድ 692 ካ/ሜትር ይዞታዉን በእጃቸዉ አድርገዉ ሲገለገሉበት የነበረዉ ይዞታ ከአመልካች ይዞታ ላይ ተቀንሶ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ መስጠቱን ካርታ የወጣላቸዉ በህገ ወጥ መንገድ በመሆኑ በቀን 25/05/2004 በካርታ ቁጥር የካ/172834/04 ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ የአመልካችን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ካርታዉ እንዲመክን ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በ05/06/2013 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት መልስ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 1169 ከ1988 የአየር ካርታ እና ከ1991 ከተሰጠዉ ካድስተር ቢል መነሻነት ከሟች አባታቸዉ ጋር ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ ሲገለገሉበት ቆይተዉ ወንድማቸዉም በ1992 ሲሞት የሟች አባታቸዉና የሟች ወንድማቸዉ ወራሽ በመሆን የያዙት ይዞታ መሆኑን፤ በይርጋ ይታገዳል የተባለዉ የቤት ቁጥር 1168ን በተመለከተ እንጂ የቤት ቁጥር 1169 አለመሆኑን፤ለአመልካች በኑዛዜ የተላለፈላቸዉ ይዞታ ስፋቱ 505 ካ/ሜትር ብቻ ሆኖ ሳለ ተወስዶብኛል በሚል ያቀረቡት ክስ በማስረጃም የተደገፈ አይደለም፤ስለሆነም ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ የሚመክንበት ምክንያት የለም በሚል ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በ26/06/2013 ዓም በተጻፈ ያቀረቡት መልስ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ በመመሪያ ቁጥር 17/2006 መሠረት በስአይኤስ እና በጂአይኤስ መረጃ ላይ መሠረት በማድረግ ከወረዳዉ አስተዳደርም በማረጋገጥ ቅሬታም ካለ ማስታወቅያ በመለጠፍ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ባለመቅረቡ በዚህ አግባብ የተሰጠ ካርታ ነዉ፤በቤት ቁጥር 1169 በሟች አቶ ወልደ ገ/ማርያም መሆኑን አረጋግጠን በህጉ መሠረት የሰጠነዉ ካርታ ነዉ፤የአመልካች ይዞታ የተነፃፃሪ ይዞታ እንደመሆኑ መጠን አጠቃላይ የሚደርሳቸዉ ይዞታ 505 ካ/ሜትር ነዉ፤ በይዞታዉ መሰረት ካርታ ሠርተን ሰጥተናል፤ከአመልካች ይዞታ ላይ ተቀንሶ ለ1ኛ ተከሳሽ የተሠጠ ካርታ የለም፤ይዞታዉ ቀደሞም የቤት ቁጥር 1169 የሟች አቶ ወልዴ ገ/ማሪያም ከሞቱ በኋላ ይዞታዉ በትንሳኤ ወልዴና በአስናቀች ወልዱ ተይዞ የነበረ ስሆን ትንሳኤ ወልዴ በመሞታቸዉ ሟች አቶ ወልዴ ገ/ማሪያም ብቸኛ ወራሽ 1ኛ ተጠሪ በመሆናቸዉ በዚህ አግባብ ካርታ ለ1ኛ ተጠሪ ተሰርቷል፤በተጭበረበረ መንገድ የተሰጠ ካርታ አይደለም፤በመቁ 88002 እና 88446 የተያዘ ጉዳይ በቤት ቁጥር 1168 እንጂ 1169ን አልነበረም፤ በመቁጥር 58002 ተይዞ የነበረዉ ጉዳይም የቤት ቁጥር 1169 ብቻ ሳይሆን የቤት ቁጥር 1168ን በአጠቃላይ በመሆኑ እንዲሁም የቤት ቁጥር 1169 የሟች አቶ ወልዴ ገ/ማርያም መሆኑ ያላከራከረና 1ኛ ተጠሪም ወራሽ መሆናቸዉ እስካልተሻረ ድረስ በወቅቱ 1ኛ ተጠሪና ወንድማቸዉ አቶ ትንሳኤ ወልዴ ንብረቱን በጋራ ማስተዳዳር ይችሉ ነበር፤አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ ሳያረጋግጡ ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ይሁን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የአመልካችን ይዞታ በማካተት ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ ተሰርቶ ተሰጥቷል ወይስ አልተሰጠም? የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ የቤቱን ማህደር በማስቀረብ የሰዉ ምስክሮች በመስማት ጉዳዩን መርምሮ የአመልካችን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ የተሰጠ መሆኑን ያቀረቡት ማስረጃዎች የሚያስረዱ ባለመሆናቸዉ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ ሊመክን አይገባም በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የቀረበዉን የይግባኝ ቅሬታ ሠርዟል፡፡

አሁን የቀረበዉ የሠበር አቤቱታም ከፍ ሰል የተገለፀዉን ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምላቸዉ አመልካች ጥር 20 ቀን 2014 ዓም በተጻፈ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም፡- ተጠሪ የአባታቸዉ ንብረት እንዲጣራላቸዉ የጠየቁት በመዝገብ ቁጥር 88440 ላይ በቀን 30/03/2007 ዓ.ም ሲሆን ካርታ የተሰጣቸዉ በ2004 ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ዉርስ ባልተጣራበት ካርታ መስጠቱ ትክክል አይደለም፤1ኛ ተጠሪ ከአባታቸዉ የሚወርሱት ቀድሞ ወደ ስማቸዉ ያዛወሩት የቤት ቁጥር 1169 የሆነዉ ቤት ብቻ ነዉ፤ ካርታዉ በተገቢ መንገድ የተሰጣቸዉ አይደለም፤ዉርስ ይጣራ ብለዉ ያቀረቡት ክስም በይርጋ ይታገዳል የተባለ መሆኑን፤የስር ፍርድ ቤትም ይህንን በአግባቡ ሳይመረምረዉ እና ሳይመለከተዉ ክሱን ዉድቅ ማድረጉ ትክክል አለመሆኑን፤ ዉርስ ይጣራ ጥያቄያቸዉ ወይም ክስ ያቀረቡት በፍ/ስ/ስ/.ህግ ቁጥር 5(1) መሠረት የአባታቸዉ የዉርስ ንብረት ይጣራ ጥያቄ ዉድቅ የተደረገ መሆኑን፤ሟች አባታቸዉ ትተዉ የሞቱት የዉርስ ንብረት የሌለ መሆኑን ፤1ኛ ተጠሪ ተለይቶ የተላለፈላቸዉ ንብረት በሌለበት ካርታ መሰጠቱ ትክክል አለመሆኑን እያስረዳሁ የስር ፍርድ ቤት ክሴን ዉድቅ ማድረጉ ትክክል አይደለም፤ይዞታዉን በተመለከተ በእጄ ያለዉ ይዞታ ምን ያህል እንደሆነ በትዕዛዝ ሳያጣራ ዉሳኔ መስጠቱ ትክክል አለመሆኑን፤የአመልካች ካርታ የተሰራዉ በአየር ካርታ ልኬት ሲሆን የ1ኛ ተጠሪ ደግሞ በአካል በመሄድ መሆኑን ከአ/አ/መ/ል/ማ/ቢሮ የተሰጠዉ ምላሽ መገለጹ በሁለት ዓይነት ልኬት በአንድ የጋራ መብት የሚጋሩ ባለ ይዞታዎች መካከል ልዩነት የሚፈጥር በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ተጨማሪ ትዕዛዝ በመስጠት ሳያጣራ ማለፉ ትክክል አይደለም፤በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎትም መዝገቡን መርምሮ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የሚከራከሩበት መሬት ልኬት በንፅፅር የተሰራዉ እንዴት እንደሆነ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአ/አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት ቢሮ እንዲያጣራለት ባዘዘዉ መሰረት ቢሮዉ የግራ ቀኙን ማህደር ተመልክቶ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ ይዞታ ተገቢዉን አንጻር ተለክቶ ንፅፅሩ የተሰራዉ በ1988 አየር ካርታ መነሻ ተደርጎ ሲሆን የተጠሪ ንፅፅሩ የተሰራዉ በወቅቱ በልኬት ጊዜ በያዙት ቦታ መጠን መሆኑን ገልጾ በዚህ መልኩ በተለያየ ልኬት ንፅፅሩ መሠራቱ ተገቢ ያለመሆኑን በገለፀበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ላይ

ምንም ሳይሉ በማለፍ የመወሰናቸዉ አግባብነት ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ የፁሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡

በዚሁ መሰረት 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ ያቀረቡት መልስ ይዘቱም፡-የአ/አበባ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመነት ቢሮ የግራ ቀኞችን ተከራካሪ ወገኖች ይዞታዉ የተለየበትን አግባብ ማስረጃ ግልፅ ድጋሚ ማብራሪያ የማያስፈልገዉ የ1ኛ ተጠሪ ሳይሆን አመልካች ካርታ ያገኙበት መንገድ ትክክል አለመሆኑን ያረጋገጠ ነዉ፤የስር ፍርድ ቤት ተገቢዉን ጭብጥ በመያዝ በሰዉ ምስክር በሰነድ ማስረጃ በማጣራት ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን ፤የ1ኛ ተጠሪ መብት በይርጋ ያልታገደ መሆኑን በመግለጽ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ይጽናልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ያቀረቡት መልስ ለአመልካች የተሠራዉ ካርታ ከፍተኛ ካ.ሜትር ተወስዶ መሆኑን ለ1ኛ ተጠሪ ደግሞ በአነስተኛ ካርታ የተሰራላቸዉ መሆኑን ከአ/አበባ ከተማ መሬት ማናጅመንት የተላካዉ ምላሽ የተገለጸ በመሆኑ፤አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ካርታ ይምከን የሚል እንጂ ስለ ዉርስ ሀብት የጠየቁት ነገር የለም በዚህ ችሎት የሚስተናገድ አለመሆኑን፤የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ ያደረገበት ተገቢዉን ጭብጥ በመያዝ ማስረጃ መርምሮ በመሆኑ በተሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በሚል ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከግራ ቀኙ የቀረበዉ ክርክር ከፍ ሲል የተገለጸዉን ሲመስል ይህ ፍርድ ቤትም የቀረበዉ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መሰረት ከሆነዉ ዉሳኔ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካለዉ ህግ አንጻር ጉዳዩን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉም ምላሽ የሚሻዉ ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበዉን ክስ ለመዳኘት የስር ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ስልጣን አላቸዉ ወይስ የላቸዉም የሚለዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክስ የተጠየቀዉ ዳኝነት ከይዞታዬ ላይ ተቀንሶ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ የተሰራላቸዉ በመሆኑ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ ይምከን የሚል ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ለመረዳት ችለናል፡፡ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸዉን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን ያለቸዉ ወይም የሌላቸዉ መሆኑን በመመርመር ተገቢዉን ዉሣኔ መስጠት ያለባቸዉ ስለመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 9(2) ስር ተመላክቷል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 38452 ላይ ገዥ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡የአስተዳደር ዉሳኔዎችን የሚታዩበት ሁኔታ የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 ወጥቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡የአመልካች ክስም የቀረበዉ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ነዉ፡፡የአስተዳዳር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ማዉጣት ያስፈለገዉ የአስተዳደር ተቋማት በሰዎች መብቶችና ጥቅሞች ላይ የሚያስከትሉትን ጣልቃ ገብነት በህግ የሚመሩበትና ለህግ የሚገባ መሆኑን ማረጋገጥ በማስፈለጉና የአስተዳደር ተቋማት የዉሣኔ አሰጣጥና የመመሪያ አወጣጥ መርሆዎችና ሥነ ሥርዓት እንዲሁም የአስተዳደራዊ ዉሣኔዎች ቅር የተሰኘ ሰዉ

የዉሣኔዎችንና የመመሪያዎቹን ሕጋዊነት በፍርድ የሚያስመረምርበት ሥርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ስለመሆኑ የአዋጁ መግቢያ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ከአዋጁ መግቢያ በዝርዝር ስንመለከት የአስተዳደር ህግ የስራ አስፈፃሚዉን ስልጣን ግዴታና ተግባር እንዲሁም የተግባራቱን ህጋዊነት የሚመለከት ህግ ሲሆን እየተለጠጠ እና እየተወሳሰበ ከመጣዉ የመንግስት አስተዳደር ስራ አንፃር የአስተዳደር አካላት ከህግ አስፈፃሚነት ስልጣናቸዉ ባሻገር በተግባር ህግ የማዉጣትና ህግ የመተርጎም ተግባራትን የሚያከናዉኑ በመሆኑ የአስተዳደር ህግ እነዚህን ተግባራት ከመፍቀድ ባሻር የአስተዳደር አካላት ተግባራት በጠባቡ ተግባራዊ እንዲደረጉ በማድረግ ለአስተዳደር አካላት ስልጣን ገደብ የሚያበጅ የህግ ማዕቀፍ ተደርጎ የሚወሰድ ነዉ፡፡የአስተዳደር ህግ የስራ አስፈፃሚዉን የስልጣን ገደብ ከማበጀት ባሻገር ፍርድ ቤቶች ከአስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሚናቸዉ እስከየት ድረስ እንደሚዘልቅ የሚወስን በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በስራ አስፈፃሚዉ ስልጣን ጣልቃ በመግባት ህገ መንግስታዊ የሆነዉን የስልጣን ክፍፍል መርህን እንዳይጥሱ ይረዳል፡፡ከዜጎች ህገ መንግስታዊ መብትና ነፃነት አንፃር ስንመለከተዉም ከላይ እንደተመለከተዉ የአስተዳደር ህግ የአስተዳደር አካላትን ስልጣን ለመቆጣጠር መሰረታዊ የህግ ማዕቀፍ በመሆኑ ዉጤታማ ተግባራዊነቱ የዜጎች ህገ መንግስታዊ መብትና ነፃነት እንዳይጣስ ዋስትናን የሚሰጥ ነዉ፡፡በዚህ አግባብም የአስተዳደር ህግ ተግባራዊ ማድረግ የግለሰቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በተጨባጭ እንዲረጋገጡ ያስችላል፡፡በዚህም አግባብም በህገ መንግስቱ የተቀመጡትን የህገ መንግስታዊነት የመንግስት መርሆዎች በተጨባጭ እንዲረጋገጡ በማድረግ የህግ መንግስቱን መርሆዎች ማስፈፀም የአስተዳደር ህግ መሰረታዊ ህግ ተደርጎ የሚወሰድ ነዉ፡፡የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች አስተዳደራዊ ድንጋጌ የማወጣት(ከፊል የህግ አዉጪነት ስልጣን) እና አስተዳደራዊ ዉሳኔ ሰጪነት (በከፊል የዳኝነት ስልጣን)ያላቸዉ ሲሆን ከፊል የዳኝነት ስልጣናቸዉን በተመለከተ ጥብቅ እና ዝርዝር ለሆነ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ ደንቦች እንዲገዙ የማይገደዱ ቢሆንም እንደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሁሉ ፍሬ ነገሩን በመስማት፤በመመዘን እና በመመርመር አረጋግጠዉ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ የግለሰቦችን መብትና ጥቅም ሊነካ የሚችል ዉጤት ያለዉ ዉሳኔ የመስጠት ስልጣን አላቸዉ፡፡ የአስተዳደር ዉሳኔ ማለት መመሪያ ማዉጣትን ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋማት በዕለት ተዕለት ተግባር ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ መሆኑን በማመልከት የአስተዳደር ሰነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 አንቀጽ 2(3) የአስተዳደር አካሉን የህግ ማስፈፀም እና ከፊል የዳኝነት ስልጣኑን በማደባለቅ የተሰጠ ትርጉም የተከተለ ቢሆንም የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ዳኝነታዊ ወይም የህግ አዉጪነት ስልጣናቸዉ አተገባበርን አስመልክቶ ብቻ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቁጥጥር ሊደረግበት የሚችል በመሆኑ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የአጣሪነት ስልጣን የሚኖራቸዉ የአስተዳደር አካላት የአስተዳዳር ስልጣናቸዉን በመገልገል ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ በሚሰጡት ትዕዛዝ፤ዉሳኔ፤በማድረግ ወይም ባለማድረግ በሚገለፅ አስተዳደራዊ ይዘት ባለዉ ዉሳኔ ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

በእኛችን ወደ አለዉ ጉዳይ ስንመጣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ከይዞታቸዉ ላይ ተቀንሶ አለአግባብ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ያሰጠዉ ካርታ ይምከን የሚል ነዉ፡፡ካርታ የመስጠትም ሆነ የማምከን ስልጣን ያለዉ ካርታዉን የሰጠዉ አካል ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ካርታ የመስጠት ስልጣን የ2ኛ ተጠሪ ስለ መሆኑ አላከራከረም፡፡ይህ ማለት የአስተዳደር ዉሳኔ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡በአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ 1183/2013 አንቀጽ 2(3) መሰረት አስተዳዳር ዉሳኔ አስተዳዳር መስርያ ቤቶች በዕለት ዕለት ስራቸዉ መሰረት የሚሰሩት ስራ ነዉ፡፡ከአስተዳደራዊ ዉሳኔዎች ዉስጥም ካርታ ማምከን አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተደርጎ የሚወሰድ ነዉ፡፡አስተዳደራዊ ዉሳኔዎች ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 44 መሰረት ለተቋቋመ የአስተዳደር ተቋም የቅሬታ ማስተናገጃ አካል በአንቀጽ 43 ቅሬታ የሚቀርብበትና ይህ ቅሬታ ሰሚ አካል በአንቀጽ 46 መሰረት የተቋሙን መጨረሻ ዉሳኔ ሲሰጥ በአንቀጽ 49(1)አግባብ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክለሳ አቤቱታ የሚቀርብበት ነዉ፡፡በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክስም በአዋጁ በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት ያሉትን ሂደቶች ተከትለዉ ያንን ከጨረሱ (exhaustion of available remedies) በኋላ መምጣት ሲገባቸዉ ቀጥታ ለፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አዋጁን ያገናዘበ ሆኖ አላገኘንም፡፡ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መዝገብ ቁጥር 220582(ያልታተመ) ገዥ ዉሳኔ ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ሰጥቷል፡፡ጉዳዩ መጀመሪያ የቀረለበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የቀረበለት ጉዳይ ካርታ ይምከን ዳኝነት ጥያቄ ሆኖ ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን በመጀመሪያ ማየት ሲገባዉ ዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ መስጠቱ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ማረም ሲገባዉ ሳያርም በትዕዛዝ መዝገብ መዝጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ዉሳኔ ነዉ ብለን ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 168017 ላይ በ 07/12/2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ የፊዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 279899 ላይ በ22/02/2014 በትዕዛዝ ያፀናዉ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348(1)መሠረት ተሽሯል፡፡

2.በአመልካች በኩል በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ 1183/2013 አንቀጽ 43 እና 44 የተዘረጋዉን ስነ ስርዓት ሳይጠብቅ የቀረበ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም ብለናል፡፡

3.አመልካች በአዋጁ የተዘረጋዉን ስርዓት ጠብቀዉ ጉዳያቸዉን የማቅረብ መብት ይህ ዉሳኔ አያግዳቸዉም ብለናል፡፡

4.በዚህ ችሎት ለተደረገዉ ክርክር ላስከተለዉ ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

5.የዉሳኔዉ ግልባጭ የስር ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡

መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

ቀን፡- ሐምሌ 28 2015 ዓ.ም

የሰ.መ.ቁ 239711

የሰ.መ.ቁ 233141

ዳኞች፡- ቴዎድሮስ ምሕረት

አበባ እምቢአለ

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

በሰ.መ.ቁ 239711 አመልካች፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር

ተጠሪ፡ አቶ ካሳሁን ግዛቸው — የቀረበ የለም

በሰ.መ.ቁ 233141 አመልካች፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር - አልቀረበም

ተጠሪ፡ አቶ ኢሳያስ መኮንን- ጠ አበበ መንግስቱ - ቀረቡ

በሰ.መ.ቁ 239711 እና በሰ.መ.ቁ 233141 ላይ የሰበር ትርጉም የሚሻው ጭብጥ አንድ በመሆኑ ሁለቱም መዛግብት ተጣምሮ ተመርምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የክርክሩ አመጣጥ በሰ.መ.ቁ 239771 ላይ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 268279 በ29/10/14 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 231725 በ7/2/15 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል እና በሰበር መዝገብ ቁጥር 233141 ላይ ደግሞ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 278868 በ12/7/14 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 225404 በ24/9/14 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የሰበር አቤቱታ በመቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕግጋት እና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይንም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሣሪያ የሚጠቀሙ ሰዎች ለምዝገባ

በተሰጠው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችል መሆን/አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 239711 አቶ ካሳሁን ያዛቸው ላይ የመሰረተው ክስ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ በክሱ በተመለከተው ጊዜ እና ቦታ የውግ ቁጥር የሌለው አውቶማቲክ ሲ.ኤ.ኤል.ኤም 8 የሆነ መሣሪያ ከ05 (አምስት) መሰል ጥይቶች ጋር ይዞ በመገኘቱ እንዲሁም በፍርድ ቤት ብርበራ ትዕዛዝ ቤቱ ሲፈተሽ አምስት ፍሬ የሽጉጥ ጥይቶችን አስቀምጦ ተገኝቷል የሚል ሲሆን፤ በሰ.መ.ቁ 233141 በሆነው መዝገብ ደግሞ በአቶ ኢሳያስ መኮንን ቸኮል ላይ የቀረበው ክስ ከላይ የተገለጹትን የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በክሱ በተጠቀሰው ቀን፤ ጊዜ እና ቦታ መኖሪያ ቤቱ ሲፈተሽ ህጋዊ ፈቃድ ካለው ማካሮቭ ሽጉጥ የውግ ቁጥሩ ዲ 06283 የሆነ ከመሰል 8 ጥይቶች እና አንድ ካርታ ጋር ፈቃድ የሌላቸው ሌላ 31 ፍሬ የሽጉጥ ጥይቶች እና አንድ ካርታ ጋር ይዞ የተገኘ በመሆኑ በፈጸመው ብዛት ያለው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት ወንጀል ተከሷል በሚል ቀርቦባቸዋል፡፡

በሰበር መዝገብ ቁጥር 233141 ተጠሪ የሆኑት አቶ ኢሳያስ መኮንን የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከተው አንድ ዓመት የመመዝገቢያ የእፎይታ ጊዜ ከማለቁ በፊት ልከሰስ አይገባም በማለት ያቀረቡትን የክስ መቃወሚያ የመረመረው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 1177/2012 በሥራ ላይ የዋለው ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን መሳሪያው በተጠሪ እጅ የተገኘው ታህሳስ 10 ቀን 2013 ዓ.ም ነው፡፡ አዋጁ ምዝገባ ያልተደረገላቸው የጦር መሳሪያዎችን በተመለከተ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ የእፎይታ ጊዜ የሰጠ በመሆኑ የተሰጠው የመሸጋገሪያ ጊዜ ሳያልቅ በአዋጁ ስር ክስ መቅረብ የለበትም በማለት በወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 130(2)(ሐ) መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

በሰ.መ.ቁ 239711 አቶ ካሳሁን ግዛቸውም ክሱ ደርሷቸው የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ ዐቃቤ ሕግም ክሴን ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን በሰነድ ማስረጃነትም ተጠሪ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 27(2) እና 35 መሠረት የሰጡትን ቃል አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም ባደረገው ምርመራ፡- በክሱ ላይ በተገለፀው ጊዜ እና ቦታ ተጠሪ የተባለውን ሽጉጥ እና ጥይቶች ይዞ መገኘቱ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ፤ ተጠሪ ሽጉጡንና ጥይቶቹን ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ መያዙን የሰጠው የዕምነት ቃል ያስረዳል፡፡ በተጠሪ እጅ የተገኙት ሽጉጥ እና ጥይቶች ፈቃድ አልወጣባቸውም፡፡ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ ሳይኖራቸው መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚቋቋመው ተቆጣጣሪ ተቋም ፈቃድ መውሰድ ያለባቸው መሆኑና በተጠቀሰው ጊዜ ፈቃድ ያላገኙ ሰዎች የያዙት የጦር መሣሪያ ለተቆጣጣሪው ተቋም ማስረከብ እንዳለባቸው የሽግግር ግዜ በአዋጁ ቁጥር 23 (1), (2) እና (3) ሥር ተደንግጓል፡፡ የጊዜ ስሌዳ የተሰጠው ለመመዝገቢያ እና

ፈቃድ መውሰጃ የሽግግር ወቅት በመሆኑ የእፎይታ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ዕድል አይኖርም፡፡ ተጠሪ ፈቃድ የሌለው የጦር መሣሪያ ይዟል ተብሎ ክስ የቀረበበት ሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም አዋጁ ከወጣ በአምስት ወር ግዜ ውስጥ ሆኖ የአንድ ዓመት ግዜ ሊጠናቀቅ ሰባት ወር ሲቀረው በመሆኑ የወንጀል ተጠያቅነት የለበትም፡፡ ዐቃቤ ሕግ እንደ ክስ አመሰራረቱ የተጠሪ ድርጊት ወንጀል መሆኑን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ኣላስረዳም በማለት በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 141 መሠረት መከላከል አያስፈልገውም በሚል በብይን በነፃ አሰናብቶታል፡፡

አመልካችም በሁለቱም መዛግብት ላይ የተሰጠውን ብይን በመቃወም ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሠረዙ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አስቀድሞ በሰ.መ.ቁ 205727 እና 205827 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጣረስ ፤ የአዋጁ ዓላማ ለብዙሐኑ ደህንነት ሲባል ያለፈቃድ በግለሰቦች እጅ ገብተው የሚገኙ የጦር መሣሪያዎችን መዝግቦ ህጋዊ የቁጥጥር ስርዓትን መዘርጋት ሆኖ እያለ በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማንኛውም ግለሰብ ያለጠያቂ ህገ ወጥ የጦር መሳርያ ይዞ መንቀሳቀስ ይችላል በሚል የተሰጠው ብይንና ውሳኔ የአዋጁን አላማ ስለሚቃረን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) (ለ) ድንጋጌ መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 205727 እና በመ.ቁ 205827 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔዎች አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ክስ መቅረቡ የህጋዊነት መርህን የሚጣረስ ከመሆኑም በላይ አመልካች የጠቀሳቸው አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎች ከተያዘው ጉዳይ ጋር የማይገናኙ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ሆኖ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የሰ.መ.ቁ 233141ን በተመለከተ ተጠሪ በ24/6/15ዓ.ም በተጻፈ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26(1) መሰረት ቀድሞ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205827 በሰ.መ.ቁ 205727 በተሰጠ አስገዳጅ ውሳኔ የተሰጠ የህግ ትርጉም እንዲሻሻል ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲታይ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት በችሎቱ ታምኖበት እንዲሁም በሰ.መ.ቁ 239711 ላይ አከራካሪው ጭብጥ በሰ.መ.ቁ 233141 ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ምክንያት ሁለቱም መዝገቦች ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ታይተው ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ግዜ ውስጥ ሕጉ ከመውጣቱ በፊት የፀና ፈቃድ ሳይኖራቸው በግለሰብ ደረጃ ሊያዝ የሚችል የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት የአዋጁን አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተል አለማስከተሉን በጭብጥነት

በመያዝ የሥር ፍርድ ቤቶች ብይንና ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ለማውጣት ካስፈለገበት ምክንያቶች ውስጥ ከፊሉ ግለሰቦች የታጠቋቸው የጦር መሣሪያዎች ህብረተሰቡን ሰላም እና ፀጥታ ለማስጠበቅ ተግባር የሚውሉበትን ዕድል መፍጠር መሆኑን ፤በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ሕግ በመደንገግ ወጥነት ያለው ሥርዓት መፍጠር መሆኑን፤ ሀገራችን ያፀደቀቻቸው ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ቁጥጥርን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማስፈፀምና ዓለማቀፍ ትብብር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓትን መዘርጋት በማስፈለጉ እንደሆነ ከአዋጁ መቅድም(Preamble) መረዳት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድና በታላላቅ ሀይቆች አካባቢ ሕገ ወጥ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በናይሮቢ ከተማ ሚያዝያ 13 ቀን 1996 የተፈረመውን የናይሮቢ ፕሮቶኮል ለማጽደቅ አዋጅ ቁጥር 429/1997 ወጥቶ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ የጦር መሣሪያዎችን፤ መለዋወጫዎቻቸውንና አካሎቻቸውን እንዲሁም ፈንጂዎችን በሕገ ወጥ ማምረትንና ማዘዋወርን ለመከካከል የወጣው ፕሮቶኮልም አዋጅ ቁጥር 735/2004 ሆኖ ፀድቋል፡፡፡

ማንኛውም ሰው የፀና ፈቃድ ሳይኖረው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4 ሥር የተዘረዘሩትን ተግባራት መፈፀም ክልክል ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 22(2) ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰው በአዋጁ የተመለከተውን ክልከላ እና ግዴታ በመተላለፍ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የጦር መሳሪያ ፤ የጦር ሜዳ መነጽር ፤ በጦር መሳሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛውም አይነት መነጽር ወይም የጦር መሳሪያ ሲተኮስ ድምጽ ለማስወገድ የሚያገለግል መሳሪያ ወደ ሀገር ያስገባ ፤ ከሀገር ያስወጣ ፤ያስቀመጠ ፤ የተገለገለ ፤ ያሳየ ፤ የደለለ ፤ የሸጠ ፤ የገዛ ፤ ያጓጓዘ፤ ያመረተ ፤ ያሰለጠነ ፤ የጠገነ ወይም ያስወገደ ፤ በማናቸውም መንገድ ያስተላለፈ ወይም የያዘ እንደሆነ ከአንድ አመት እስከ ሶስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ እስከ አስር ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተፈጸመው ወንጀል ብዛት ባለው የጦር መሳሪያ ሲሆን ቅጣቱ ከስምንት አመት እስከ ሀያ አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከመቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ህጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ አመት ግዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው የግዜ ሰሌዳ መሰረት በአካል ቀርበው ፈቃድ መጠየቅ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው በተቆጣጣሪ ተቋሙ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው በማለት ደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ፈቃድ ያላገኙ ሰዎች የያዙትን የጦር መሳሪያ ለተቆጣጣሪው ተቋም ማስረከብ አለባቸው በማለት ደንግጓል፡፡ አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ

ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደር፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር መመሪያ ከሀምሌ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ መዋሉን የመመሪያው ቁጥር 58 የሚያመለክት ሲሆን የጦር መሣሪያ ፈቃድ የሚሰጠው በአዋጁ አንቀጽ 7 እና በመመሪያው አንቀጽ 10 ሥር የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልቶ ለተገኘ ሰው ነው፡፡ ፈቃድ ሊሰጠው የሚገባው የጦር መሣሪያ ምንጩ መሣሪያ እንዲያመርት ወይንም እንዲሸጥ ፈቃድ ከተሰጠው ተቋም በግዥ የተገኘ ፤ ከመንግስት ግምጃ ቤት ፤ በዓለም ዓቀፍ ድርጅት ወይንም በውጪ ሀገር ተወካይ ወደ ሐገር ውስጥ የገባ ፤ በውርስ ፤ በሽልማት ወይንም በስጦታ የተገኘ ፤ አዋጁ ከመጽደቁ በፊት ተመዝግቦም ይሁን ሳይመዘገብ በሰው እጅ ተይዞ የነበረ፣ በተለያዩ የፀጥታ አካላት እጅ የሚገኝ እና በሕገ - ወጥ መንገድ ሲዘዋወር ወይም ተደብቆ የተገኘ ሊሆን እንደሚችል አንቀጽ 14 ያመለክታል፡፡ ለግለሰብ የሚፈቀደው የጦር መሣሪያ ዓይነት እና ብዛት በመመሪያው አንቀጽ 19 ሥር ተዘርዝሯል፡፡

የጦር መሣሪያ ለመታጠቅ ብቁ የሚያደርጉ ዝርዝር መስፈርቶችም በመመሪያው አንቀጽ 15 ሥር ተመላክቷል፡፡ በቀደሙት ሕጎች ላይ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 1177/2012 በሕግ አውጪው ወጥቶ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ የአዋጁ ዓላማ በግለሰብ ደረጃ ሊያዝ የሚችልን የጦር መሣሪያ በፈቃድ በመያዝ የሕብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ተግባር እንዲውል ፈቃድ ሳይኖራቸው የጦር መሣሪያ የያዙ ፈቃድ ማግኘት ለሚችሉ ሰዎች ፈቃድ መስጠት ፤ ያለፈቃድ በግለሰቦች እጅ ተይዞ ከቆዩት የጦር መሣሪዎች በፈቃድ ሊያዝ የማይችለውን የጦር መሣሪያ በመሰብሰብ የነበረውን የሕግ ክፍተት በመሙላት ወጥነት ያለው የጦር መሣሪያ አያያዝ ሥርዓትን ለመዘርጋት ነው፡፡ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የጦር መሣሪያ ምንጩ በሕገ - ወጥ መንገድ የሚዘዋወር እና በሕገ - ወጥ መንገድ ተቀምጦ የተገኘ ሊሆን እንደሚችል ከአዋጁ እና መመሪያው ድንጋጌዎች ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 1177/2012 ወጥቶ በሥራ ላይ የዋለው ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ቢሆንም ከላይ የተመለከቱ ተግባራት ፈጽሞ የሕጉን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ግዜ አስፈላጊ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 4 እና 22(2) ሥር የተመለከተው ክልከላ እና የወንጀል ተጠያቂነት አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎች እና አሰራሮች ሳይመዘገብ ወይንም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሣሪያ የያዙ ወይንም የሚጠቀሙ ሰዎች ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአዋጁ እና መመሪያው የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው ፈቃድ እንዲወስዱ የአዋጁ አንቀጽ 23(1) ደንግጓል፡፡ ስለዚህ አዋጁ ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በሥራ ላይ እንደዋለ በማግስቱ የፀና ፈቃድ ሳይኖራቸው የጦር መሣሪያ የያዙትን ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ ከማድረግ በፈቃድ የጦር መሣሪያ ሊይዙ ለሚችሉ ሰዎች ፈቃድ ለመስጠት እና ፈቃድ ከማይሰጣቸው ሰዎች እጅ ደግሞ መሣሪያዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ግዜን ወስኖ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ነው፡፡ አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ አስቀድሞ ያለፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎችን የአዋጁን አንቀጽ 4 እና 22(2) ድንጋጌዎች በመተላለፍ በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአዋጁ

በተቀመጠው አግባብ ፈቃድ እንዳይወስዱ እንቅፋት ስለሚሆን በሕጉ የተመለከተውን የምዝገባ ሥርዓት ያሰናክላል፡፡

ከዚህ ቀደም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዐቃቤ ሕግ የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4(2)ን ጠቅሶ የመሰረተው የወንጀል ክስ በክልሉ በየደረጃው ጉዳዩን ባዩት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመጨረሻ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በተሰጠ ውሳኔ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ የሌለውን የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎች መሳሪያውን አስመዝግበው ፈቃድ ለመውሰድ የሚችሉበትን የጊዜ ሰሌዳ ወስኖ ወደስራ ያልገባ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ጊዜ ውስጥ መሳሪያውን ይዞ መገኘቱ ወንጀል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ተከሳሽን በነጻ በማሰናበቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205727 ላይ ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአዋጁን አንቀጽ 23(2)ን በመተርጎም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ *"...የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ከአዋጁ መሰረታዊ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የዚህ ድንጋጌ ዋናው ዓላማ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ መሳሪያውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የህጋዊነት ጥያቄ ለመጠበቅ እንጂ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ያለማንም ጠያቂ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመፍቀድ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው የጦር መሳሪያን አስመልክቶ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ለመሆኑ አልያም ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ እያለ የተያዘ ስለመሆኑ እንዲሁም በመሳሪያው ላይ ፈቃድ ያላወጣው ተቆጣጣሪ ተቋሙ ወደ ስራ ባለመግባቱ ነው በሚል ያቀረበው ክርክርም ሆነ ከዚህ አንጻር የተረጋገጠ ነገር በሌለበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአዋጁን ድንጋጌ ባልተገባ መንገድ ተርጉሞ ተጠሪን ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡"* በማለት የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመሻር የስር የወረዳ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205827 ላይ ሕዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ላይ *"...የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ከአዋጁ መሰረታዊ አላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የድንጋጌ ዋና አላማ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ መሳሪያውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የህጋዊነት ጥያቄ ለመጠበቅ እንጂ እስከ አንድ አመት ድረስ ያለማንም ጠያቂ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመፍቀድ አይደለም፡፡"* በማለት የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመሻር የስር የወረዳው እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በተጠቀሱት መዛግብት ላይ በሰበር ችሎቱ የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2)ን አተገባበር በተመለከተ የተሰጠው ትርጉም ከአዋጁ ዓላማ እና ከሚከተሉት የወንጀል ሕግ መርሆዎች አንጻር እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የወንጀል ሕግ ዓላማ የሕዝቦችን ፤ የነዋሪዎችን ሠላም ፤ ደህንነት ፤ ሥርዓት ፤ መብት እና ጥቅም ማረጋገጥ ሆኖ ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቅያ በመስጠት ፤ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ግዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ያመለክታል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22(2) ፤ እንዲሁም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(2) ስር ፍርድ ቤት አንድ ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይንም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር ሊያስቀጣ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ይህም የሕጋዊነት መርህ(Principle of Legality)አንደኛው መገለጫ እና የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርህ በመሆኑ በጥብቅ ተግባራዊ መደረግ የሚገባው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ መመስረት የሚችለውም ሆነ ፍርድ ቤት የወንጀል ክሱን ሰምቶ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፍ የሚችለው ሕገ ወጥነቱና እና አስቀጭነቱ (ወንጀልነቱ) በሕግ የተደነገገውን ድርጊት ወይም አል ድርጊት በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሰረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ናቸው ተብሎ በሕጉ የተመለከተው ሕጋዊ ፤ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በውስጡ ያለ ሕግ ወንጀልም ሆነ ቅጣት አይኖርም የሚሉ መርሆች የያዘ ነው፡፡ የወንጀል ድርጊትን በማመሳሰል (by analogy) መፍጠርም አይቻልም፡፡ በሌላ ሕግ በተለየ መልኩ ካልተደነገገ በቀር የወንጀል ሕጉ መርሆች በሌሎች የወንጀል ድርጊት እና ቅጣት በሚደነግጉ ሕጎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 3 ያስረዳል፡፡ የወንጀል ሕግ የሰውን ማህበራዊ ኑሮ ደረጃን ፣ የዘርን ፣ የብሔርን ፣ የብሔረሰብን ፣ የቀለምን፣ የጾታን ፣ የቋንቋን ፣ሃይማኖትን ፣የፖለቲካን ወይም የሌላ አስተሳሳብን ፣ የሃብትን ፣ የትውልድን ወይም ሌላ አቋምን ልዩነት ሳያደርግ በእኩል ተፈፃሚ እንደሚሆን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 4(1) ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ስር አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፍቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ ዓመት ግዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በአካል ቀርበው ፈቃድ መጠየቅ እና መስፈርቱን በማሟላት ፈቃድ መውሰድ እንዳለባቸው ሲደነገግ አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ለሚኖረው ሕጉ ከመጽናቱ በፊት ያለፈቃድ ወይንም በፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች አዋጁ ከፀና አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በወንጀል ተጠያቂ ሳይሆኑ ወደሕጋዊ ሥርዓት ለማስገባት ሕግ አውጪው በግልጽ አቋሙን መግለጹን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ሕጉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አስቀድሞ ያለፈቃድ ለተያዘ የጦር መሣሪያ የወንጀል ተጠያቂነት እንዳይኖር ደንግጎ ሳለ የአንድ አመት ጊዜ ከማለቁ በፊት መሳሪያውን ለማስመዝገብ ሂደት ያልጀመሩ ሰዎች የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል በሚል ከላይ በተጠቀሱት ሁለቱም መዛግብት ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ከሕገ መንግስት አንቀጽ 22(2) ፣ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ፣አንቀጽ 2(2) ፣ (3) ፣ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 23(1) እና (2) አንፃር እንዲሁም ሕግ

አውጪው በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 በተመለከተው አግባብ በሕጋዊ መንገድ መሣሪያ ለመታጠቅ ዝርዝር የአፈፃፀም ደንብ እና መመሪያ በማውጣት ወጥነት ባለው መልኩ በሥራ ላይ ለማዋል የተቀመጠው የአንድ ዓመት ግዜ ሳይጠናቀቅ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፍቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ ዓመቱ ጊዜ ውስጥ መቼ እንደሚያስመዘግቡ ማወቅና መለየት አይቻልም፡፡ ይህንን የሚያውቀው መሳሪያውን ለማስመዝገብ የወሰነ ሰው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሕጉ አስመዝጋቢው ላይ የጣለው ግዴታ የሌለ ከመሆኑም በላይ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ መቼ ማስመዝገብ እንዳለበት የሚወስነው መሳሪያውን ይዞ የሚገኘው ሰው ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተሰጠው አንድ ዓመት ጊዜ ባሉት የመጀመሪያው ቀናት ለማስመዝገብ ሂደቱን የጀመረም ሆነ በዓመቱ መጨረሻ ወር ባሉት ቀናት መዝጋቢው አካል ያወጣውን የጊዜ ሰሌዳ ተከትሎ መሳሪያውን ለማስመዝገብ ሂደት ውስጥ የገባ ሰው ወይም አንድ አመት ጊዜ ሳያልፍ መሳሪያ ይዞ የተገኘ ሰው በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 በሕጋዊ መንገድ በፈቃድ ብቻ የጦር መሣሪያን ለመያዝ የተዘረጋውን ሕጋዊ ሥርዓት ጥሷል በሚል በአዋጁ አንቀጽ 23(2) መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖርበት አይገባም፡፡

የሕጋዊነት መርህ በውስጡ ከያዛቸው ሐሳቦች አንዱ ሰዎችን አስቀድሞ ማስጠንቀቅን ሲሆን በዚህ ሚዛን የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ሲመዘን የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ዜጎች ከአዋጁ በፊት በእጃቸው የያዙትን መሳሪያ እንዲያስመዘግቡ ማሳወቅና በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የማስመዝገብ ግዴታን መጣል ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ባይኖር ያልተመዘገበ የጦር መሳሪያ መያዝ ወይም መጠቀም የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችል የነበረ ሲሆን እንደ ግብ የተያዘው በዚህ መልክ የተያዘ የጦር መሳሪያ በሽግግር ጊዜው ውስጥ ወደ ሕጋዊ ስርዓት በማስገባት በሕጉ የታሰበውን ዓላማ ማሳካት ነው፡፡ ስለዚህ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመዘገበ መሳሪያ መያዝ በራሱ ወንጀልን የሚያቋቁም ሳይሆን በሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ የማስመዝገብ ግዴታን የሚጥል ነው፡፡ በተያዙት ሁለቱም ጉዳዮች የክሱ የሕግ መሰረት በሆኑት የአዋጁ አንቀጽ 4(2) እና 22(2) በግልጽ እንደተመለከተው የወንጀሉ መቋቋም የጸና ፈቃድ አለመኖርን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን በዚሁ አዋጅ ከአዋጁ መጽናት በፊት የተያዙ ነገር ግን ያልተመዘገቡትን መሳሪያዎች ለማስመዝገብ እና ፈቃድ ለማግኘት እንዲቻል የአንድ ዓመት የሽግግር ጊዜ ተሰጥቷል፡፡ ስለዚህ የጸና ፈቃድ አለመኖርን ታሳቢ የሚያደርገው አዋጅ በሽግግር ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችልበትን ሁኔታ ስላስቀመጠ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ወንጀሉ ሊቋቋም የሚችልበትን ሁኔታ አስቀርቷል፡፡ በአንድ አመት ውስጥ በነባሩ ሕግ ያልተመዘገበ መሳሪያ እንዲያስመዘግብ በሕግ ጊዜ የተሰጠው ሰው በዚህ ጊዜ ውስጥ ሕግ ተላልፎ የጦር መሳሪያ ይዘዋል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የሰበር መዛግብት ላይ በተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ መሆን የሚቻለው በምዝገባ ሂደት ውስጥ በመግባት በመሆኑ በአንድ በኩል የአንድ አመት ጊዜ ለመጠናቀቅ ገና የስድስት ወር ጊዜ ቀርቶት እያለ የምዝገባ ሂደት ያልጀመረ መሳሪያ የያዘ ሰው መሳሪያ መያዙ ከታወቀበት በወንጀል እንዲጠየቅ የሚያደርግ በሌላ በኩል መሳሪያ መያዙ

ሳይታወቅበት የአንድ አመት ጊዜ ሊጠናቀቅ ጥቂት ግዜ ቀርቶት እያለ መዝጋቢው አካል ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ወደ ምዝገባ ሂደት የገባ ሰው በወንጀል ተጠያቂ እንዳይሆን የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 በዜጎች መካከል በእኩልነት ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚያደርግ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል ስለሚሆን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 3 እና 4 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው፡፡

ከዚህም በላይ በተጠቀሰው መዝገብ የተሰጠው ትርጉም መሳሪያ ለማስመዝገብ የሚቀርቡ ሰዎች ጭምር በወንጀል ተጠያቂ የማድረግ ውጤት ያለውና አዋጁ በመግቢያው ያሰባቸውን ግቦች የሚያከሽፍ ይሆናል፡፡ አዋጁ የጊዜ ገደብ ያስቀመጠው ከአዋጁ መውጣት በፊት በነበረው የምዝገባ ስርዓት የማይታወቁ የጦር መሳሪያዎችን ወደሕጋዊ ስርዓት ለማስገባት በመሆኑ ለዚህ ዓላማ በሚወጣው መመሪያ መሰረት በአንድ ዓመት ውስጥ በቀድሞ ሕግ ያልተሸፈኑትን መሳሪያዎች ወደ ሕጋዊ ስርዓት ለማስገባት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምዝገባውን ለማካሄድ እንዲቻል ሰዎች ከተጠያቂነት ነጻ ሆነው ማስመዝገብ እንዲችሉ ስርዓት ለመፍጠር የታሰበ ነው፡፡ ወንጀል እንዲከላከልና ተፈጽሞም ሲገኝ እንዲመረምር ስልጣን የተሰጠው አካል ከላይ በተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ከአዋጁ በፊት የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎችን ሕጋዊ አድርጎ ሊመዘግብ የሚችልበት መንገድ አይኖርም፡፡ ይልቅም ለምዝገባ ዓላማ የሚቀርቡ ሰዎችን በሙሉ የወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ደግሞ በሕግ አውጪው ያልታሰበ ከመሆኑም በላይ አዋጁንም ሆነ አፈጻጸሙን ውድቅ የሚያደርግ ነው፡፡ የተጠቀሰው ድንጋጌ አሻሚ ቢሆን እንኳ መተርጎም ያለበት የሕጉን መንፈስ ጠብቆ በሕግ አውጪው የታሰበውን ግብ ለማሳካት መሆን እንዳለበት ወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(4) ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ የሕግ አውጪውን ሐሳብ ማሳካት የሚቻለው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሰዎች ከተጠያቂነት ፍርሀት ውጪ በመሆን ስልጣን የተሰጠው አካል ዘንድ ቀርበው ቀደም ሲል በነበረው ሕግ ያልተመዘገበ የጦር መሳሪያ ማስመዝገብ ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ያለው አተረጓጎም ከላይ የቀረቡት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው አዋጁን እንዳይፈጸም የሚያደርግ በመሆኑና ሕግ መተርጎም ያለበት ሕግ አውጪው ያሰበውን ዓላማ ለማሳካትና የሕጉን መንፈስ ተከትሎ በመሆኑ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ ይህን መስፈርት የሚያሟላ አይደለም፡፡

በተያዙት ጉዳዮች የተከሰሱ ዓይነት ሰዎችን ለመለየት የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ‹‹ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች…›› የሚል አገላለጽ ይጠቀማል፡፡ መልስ ሰጭዎች በዚህ አገላለጽ ስር የሚወድቁ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በነዚህ ሰዎች ላይ የተጣለው ግዴታ ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ቀርበው በእጃቸው የሚገኝን የጦር መሳሪያ ማስመዝገብና መስፈርቱን ካሟሉ ፈቃድ ማውጣት ነው፡፡ ከዚህ አልፎ በሽግግር ጊዜው ውስጥ በሚታዩት መዝገቦች በተለዩት ፍሬ ነገሮች መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ሁኔታ አልተመለከተም፡፡ ግለሰቦች በአዋጁ መሰረት ለመመዝገብ እና ፈቃድ ለማግኘት ጠይቀው ካልተፈቀደላቸው ውጤቱ የሚሆነው የጦር መሳሪያውን ማስረከብ እንደሆነ

በአዋጁ አንቀጽ 23(3) ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ በዚህ አገላለጽ የሚሸፈኑ ሰዎች በሙሉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በእጃቸው የሚገኘውን የጦር መሳሪያ ማስመዝገብ፣ ፈቃድ መውሰድ ወይም ይህ ካልተሳካ የጦር መሳሪያውን የማስረከብ ግደታን ከመወጣት ባለፈ የወንጀል ተጠያቂነት ሊጣልባቸው የሚችልበት ሁኔታ በሕጉ አልተመለከተም፡፡

አንድ ሕግ የሕጉን ይዘት ከመወሰን ባለፈ የጊዜ ተፈጻሚነት ላይ በመበየን የሕጉን ውጤት ወዲያው፣ በሂደት ወይም በሁኔታዎች መሟላት ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ የአንድ ሕግ መውጣት ከሕጉ በፊት የተጀመሩ ወይም በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለውን ተፈጻሚነት የሚገዙ ድንጋጌዎችን በማካተት የሽግግሩ ሂደትን የተሳለጠ ማድረግ የተለመደ ነው፡፡ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ በቀድሞውና በአዲሱ ሕግ መካከል በድልድይነት የሚያገለግል ነው፡፡ ለተከሳሽ የሚጠቅም ካልሆነ በስተቀር የወንጀል ሕግ ተፈጻሚነት የወደፊት (prospective) በመሆኑ ጥያቄው ሊሆን የሚችለው ሽግግሩ በቀድሞ ሕግ የነበረውን ሁኔታ በአዲሱ ሕግ እንዴት እንደሚስተናገድ ማሳወቅ ነው፡፡ ስለዚህ የሽግግር ድንጋጌ ቀደም ሲል ያሉት ሁኔታዎች ወይም ድርጊቶች በአዲሱ ሕግ እንዴት እንደሚስተናገዱ በግልጽ ለማመልከት የሚያገለግል ነው፡፡ አዋጁ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለ ሲሆን ቀደም ሲል የነበረው ሕግን ስለሻረው ከዚህ በኋላ የሚቀርቡ ክሶች ይህን አዋጅ መሰረት አድርገው ነው፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ሕግ መሰረት የተከናወኑ ተግባራትም የሚበየኑት በዚሁ አዋጅ ነው፡፡ ከአዋጁ ግልጽ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የጦር መሳሪያ የያዙና ፈቃድ የሌላቸው ወይም ያላስመዘገቡ ሰዎች ላይ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆነው በሕግ በተመለከተው አግባብ የአንድ ዓመት ጊዜ ገደቡ ሲያበቃ እንደሆነ ነው፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 23 የተካተተው የሽግግር ጊዜ ድንጋጌ ዓላማ ደግሞ የአንድ ሕግ ተፈጻሚነትን ከመጀመሩ በፊት የሚኖረውን ሂደት መግዛት እና ተፈጻሚነትን ማሻሻል ሲሆን የጊዜ ገደቡ ሲያበቃ ወይም ሁኔታው ሲሟላ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ውጤቱም በሽግግር ድንጋጌ በተመለከተው ሁኔታ ጉዳዮች ላይ ሕጉ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ያለው ሂደት የሚጀመርበት ነው፡፡ ይህም ከላይ በዝርዝር ከቀረበው የአዋጁ ዓላማ እንዲሁም ሕግ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ሲደረግ ሊያስከትል የሚችለው ችግር ከመቅረፍ አንጻር ከታየ ሕግ አውጪው የሽግግር ጊዜውን የሕጉን ተፈጻሚነት በማዘግየት ለሕጉ ዓላማ መሳካት በጥንቃቄ የወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ የአዋጁ አፈጻጸም በዚህ የጊዜ ገደብና በተጠቀሱት ሁኔታዎች በእንጥልጥል እንዲቆይ ተደርጓል፡፡ በዚህም የሽግግር ድንጋጌ ምክንያት ወንጀሉን ለማቋቋም ከሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ውስጥ የሕግ መስፈርት ስለማይሟላ የወንጀል ተጠያቂነትን መፍጠር አይቻልም፡፡ ድርጊቱ በሌላ ሁኔታ ጥፋት ቢሆንም በሽግግር ጊዜ ውስጥ የወንጀል ተጠያቂነት የላቀውንና ሕግ አውጪው ያሰበውን አጠቃላይ ዓላማ ማሳካት እንዲቻል በጊዜያዊነት ቀሪ ተደርጓል፡፡

የሕጋዊነትም ሆነ የእኩልነት መርሁ ተፈጻሚነት ከአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ጋር ተገናዝቦ የሚታይ በመሆኑ አዋጁ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በእጁ የጦር መሳሪያ የያዘ ሰውን

የሚመለከት ነው፤ አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ነጻ የጦር መሣሪያ ዝውውር የመፍቀድ ዓላማ የለውም፤ ዓላማው አስቀድሞ በእጃቸው መሣሪያ የያዙ ሰዎች በሕግ አግባብ ማስተዳደር እና ከሕግ ውጭ የጦር መሣሪያ የያዙ ሆነ የሚያዘዋውሩ ሰዎችን በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22/2 እና 22/3 መሠረት የወንጀል ክስ ሲያቀርብ የጦር መሣሪያው ተከሳሽ የሆነው ወገን ይዞ የተገኘው በአዋጁ አንቀጽ 23/2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ከሆነ መሳሪያው አዋጁ ከጸና በኋላ በተከሳሹ የተያዘ ስለመሆኑ ተጨማሪ የማስረዳት ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) በሚተገበርበት ግዜ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 481 ስለጦር መሳሪያ መነገድ ወንጀል ጸንቶ ያለና ተፈፃሚነት ያለው ህግ ከመሆኑ አኳያ የመሸጋገሪያው ግዜ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር የሚፈቅድ ሆኖ መተርጎም ተገቢነት የሌለው በመሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉሙ ሊለወጥ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም በአዋጁ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ መሠረት አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ወጥቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በፊት በፈቃድም ሆነ ያለፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአዋጁ ለፈቃድ ማውጫ በተቀመጠው አንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ፤እንዲሁም በተለምዶ የጦር መሳሪያ የሚያዝባቸዉ አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ እና ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች ሲሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 8(1) መሰረት እንዲያስመዘግቡ በተፈቀደዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ የአዋጁን አንቀጽ 4 ፣ 22(2) ፤ እንዲሁም 22(3) ድንጋጌዎች በመተላለፍ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሁለቱም የሰበር መዛግብት ተጠሪዎች የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ተከሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 233141 ተጠሪ የሆኑት አቶ ኢሳያስ መኮንን የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከተው አንድ ዓመት የመመዝገቢያ የእፎይታ ግዜ ከማለቁ በፊት ልከሰስ አይገባም በማለት ያቀረቡትን የክስ መቃወሚያ ተቀባይነት አግኝቶ አመልካች በተጠሪው ላይ ያቀረበው ክስ ውድቅ መሆኑን ፤ እንዲሁም የሰበር መዝገብ ቁጥር 239711 ተጠሪ የሆኑት አቶ ካሳሁን ግዛቸው ፈቃድ የሌለው የጦር መሣሪያ ይዟል ተብሎ ክስ የቀረበባቸው ሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም አዋጁ ከወጣ በአምስት ወር ግዜ ውስጥ ሆኖ የአንድ ዓመት ግዜው ሊጠናቀቅ ሰባት ወር ስለሚቀር የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ብይንና ውሳኔ ሊነቀፍ የሚችል ባለመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የሰ.መ.ቁ 233141ን በተመለከተ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 278868 በ12/7/14 ዓ.ም እንዲሁም የሰ.መ.ቁ 239711ን በተመለከተ በመ.ቁ 268279 በ29/10/14 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የሰ.መ.ቁ 233141ን በተመለከተ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

በመ.ቁ 225404 በ24/9/14 ዓ.ም እና የሰ.መ.ቁ 239711ን በተመለከተ በመ.ቁ 231725 በ7/2/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ.መ.ህ.ሥ.ሥ.ቁ 195(2) (ሀ) መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 205727 እና 205827 *"…የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ከአዋጁ መሰረታዊ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የዚህ ድንጋጌ ዋናው ዓላማ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ መሳሪያውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የህጋዊነት ጥያቄ ለመጠበቅ እንጂ እስከ አንድ አመት ድረስ ያለማንም ጠያቂ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመፍቀድ አይደለም፡፡"* በማለት ለጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ የሰጠው የህግ ትርጉም ተለውጧል፡፡
3. የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አዋጁ ከጸናበት ከ30/4/12 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አንድ አመት ይኸውም እስከ 30/4/13 ዓ.ም ባለው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ያልተመዘገበ ወይም ፈቃድ ያልተሰጠው በሰው ሊያዝ የሚችል የጦር መሣሪያን የያዘ ወይም የተጠቀመ ሰው የአዋጁን አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም በማለት ለአዋጁ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ የህግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

የሠ/መ/ቁጥር 214219

መጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

**ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ**

**ተሾመ ሽፈራዉ**

**ኑሪዲን ከድር**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ነጻነት ተገኝ**

**አመልካቾች፡- 1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

**2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት**

**ተጠሪ፡- አቶ አበባዉ ታደሰ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ በሰበር መታየቱ አግባብ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ጉዳዩ የተጀመረዉ ተጠሪ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ (ከዚህ በኋላ ጉባኤ በሚል የሚጠቀስ) ባቀረቡት ቅሬታ መነሻ ሲሆን የቅሬታቸዉም ይዘት በአጭሩ፡- ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010 ዓ/ም ባካሄደዉ መደበኛ ስብሰባ በየደረጃዉ ለሚገኙ ሰብሳቢ ዳኞች እና ለሂደት መሪዎች የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ ወስኗል፡፡በዚህ ዉሳኔ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ እና እርከን ከተሰራ በኋላ ደመወዝ የተጨመረ ሲሆን አመልካች የሥራ ሂደት መሪ በመሆኔ የደመወዝ ጭማሪዉ ተግባራዊ ከተደረገበት ከቀን 01/06/2010ዓ/ም ጀምሮ ለሥራ መደቡ የተፈቀደዉን የወር ደመወዝ ብር 13,702.00 እየተከፈለኝ ቆይቷል፡፡ከዚህም ላይ ጡረታ ሲቆረጥ ቆይቷል፡፡ነገር ግን ጉባኤዉ በቀን 28/09/2012 ዓ/ም ባካሄደዉ መደበኛ ስብሰባ የዳኞችን እና የጉባኤ ተሿሚዎችን ደመወዝ እንዲሻሻል ሲወስን አስቀድሞ በሂደት መሪነት ይከፈለኝ የነበረዉን ደመወዝ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት የኃላፊነት አባል ነዉ በሚል በመቀነስ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ይከፈል የነበረዉን ደመወዝ ብር 12,702.00 በመነሻነት በመዉሰድ የደመወዝ ማሻሻያዉ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡በመሆኑም የደመወዝ ማሻሻያ ሲደረግ ለስሌቱ መነሻ መሆን የሚገባዉ ብር 12,702.00 ሳይሆን አስቀድሞ በሂደት መሪነቴ ይከፈለኝ የነበረዉ ደመወዝ ብር 13,702.00 በመሆኑ ስሌቱ በዚህ አግባብ ተሰርቶ እንዲከፈለኝ በማለት ቅሬታቸዉን ለጉባኤዉ አቅርበዋል፡፡

ጉባኤዉ በቀን 26/06/2013 ዓ/ም ባካሄደዉ ስብሰባ በሰጠዉ ዉሳኔ ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010ዓ/ም ባካሄደዉ ስብሳባ የወሰነዉ ክፍያ የኃላፊነት እንጂ ደመወዝ አይደለም፡፡በቀን 28/09/2012ዓ/ም በተደረገዉ ጉባኤም የደመወዝ ማሻሻያ በተመለከተ የቀረበዉን ጥናት በማጽደቅ በእነዚህ የኃላፊነት መደቦች ላይ ተመድበዉ ለሚሰሩ ኃላፊዎች ደመወዛቸዉ በያሉበት ፍርድ ቤት ዳኛ ደረጃ እንዲሆን ሆኖ ለኃላፊነታቸዉ ደረጃ እና መጠን በልዩ ሁኔታ የተሻሻለ የኃላፊነት ክፍያ እንዲከፈላቸዉ በሚል ወስኗል፡፡በቅሬታዉ መሰረት የደመወዝ ማሻሻያ ማድረግ የጉባኤዉን ዉሳኔ መጻረር ይሆናል፡፡እንዲሁም ከአዲሱ ደመወዝ ጭማሪ በፊት በኃላፊነት ላይ በነበሩትና ከደመወዝ ጭማሪ ወዲህ ወደ ተጠቀሱት የኃላፊነት ቦታ በሚመጡት ኃላፊዎች መካከል የደመወዝ ልዩነት የሚፈጥር በመሆኑ ተገቢነት የለዉም በማለት ጥያቄዉን ዉድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑን 1ኛ ተጠሪ በተጠሪነት በመጨመር ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱ ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 03-104522 ላይ አከራክሮ በቀን 30/11/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ጉባኤዉ በአዋጅ ቁጥር 209/2006 መሰረት የዳኞችን እና የጉባኤ ተሿሚዎችን ደመወዝ ጥቅማጥቅም የመወሰን ሥልጣን ያለዉ አካል ነዉ፡፡ጉባኤዉ የሚሰጣቸዉ ዉሳኔዎች አግባብነት ለመከለስ በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉ ሌላ አካል የለም፡፡በመሆኑም ጉባኤዉ በተለያዩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) እና በተሻሻለዉ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17 በግልጽ እንደሚደነግገዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንደሚኖረዉ ያስገነዝባል፡፡በዚህም ጉዳይ ዉሳኔ የሰጠዉ ጉባኤዉ ስለሆነ እና ዉሳኔዉም የመጨረሻ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ስላለዉ አመልካቾች ችሎቱ ስልጣን የለዉም ሲሉ ያቀረቡት ተቃዉሞ ተቀባይነት የለዉም፡፡

በሌላ በኩል ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010ዓ/ም የወሰነዉ ደመወዝ ነዉ ወይስ የኃላፊነት አበል የሚለዉን በመመርመር በጉባኤዉ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 209/2006 ላይ እና በሌሎች የዳኞች መተዳደሪያ ደንቦች ላይ ለደመወዝ ትርጓሜ ስላልተሰጠ በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 2/9 ላይ የተሰጠዉን ትርጓሜ መዋስ ይገባል በማለት ጉዳዩን ከዚህ አንጻር መርምሯል፡፡በዚህ መሰረት ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010ዓ/ም ለሰብሳቢ ዳኞችና ለሂደት መሪዎች ክፍያ ሲወስን መጠኑን የወሰነዉ ሠራተኞች የሚያገኙትን መነሻ ደመወዝ መሠረት በማድረግ ደረጃ እና እርከን መስራቱን የጉባኤዉ ቃለ ጉባኤ ያሳያል፡፡ከፍ ሲል ከተመለከተዉ የደመወዝ ትርጓሜ አንጻር በክፍያዉ ላይ ጡረታ ሲቆረጥ መቆየቱ ሲታይ ጉባኤዉ የወሰነዉ ክፍያ ደመወዝ እንደሆነ ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ስለሆነም ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010ዓ/ም ለሰብሳቢ ዳኞችና ለሂደት መሪዎች የወሰነዉ ክፍያ የኃላፊነት አበል ሳይሆን ደመወዝ በመሆኑና ዉሳኔዉ ፀንቶ ባለበት የዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎች ደመወዝ በተሻሻለ ጊዜ ለስሌቱ በመነሻነት ሊወሰድ የሚገባዉ ተጠሪ አስቀድሞ በሂደት መሪነታቸዉ ሲከፈላቸዉ የነበረዉ

ደመወዝ ብር 13,702 ሆኖ እያለ በብር 12,702 መነሻ ደመወዝ መሰራቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት ጉባኤዉ በቀን 26/06/2013ዓ/ም ያስተላለፈዉን ዉሳኔ በመሻር ጉባኤዉ በቀን 25/05/2013ዓ/ም ባደረገዉ ስብሰባ ለሰብሳቢ ዳኞችና ለሂደት መሪዎች የወሰነዉ ክፍያ ደመወዝ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች በቀን 07/01/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- በፌዴራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3 ፤ በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 67(1/ሐ) እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታዩ የሚገባቸዉ ጉዳዮች በክልሉ ፍርድቤቶች ታይተዉ የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠባቸዉን ጉዳዮች ብቻ እንጅ በማንኛዉም አካል የተሰጠ ማናቸዉንም ዉሳኔ እንዳልሆነ በመግለጽ አመልካቾች ያቀረብነዉን መቃወሚያ ተቀብሎ አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ሳይኖረዉ የጉባኤዉን ዉሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ጉባኤዉ ፍርድ ቤቶችን እና ዳኞችን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉ ሲሆን አከራካሪዉ ጉዳይ የደመወዝ ማሻሻያ እና የኃላፊነት አበል ክፍያ በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ የክርክር አመራር ሂደትን ተከትሎ አከራክሮ የወሰነዉ አይደለም፡፡በመሆኑም ዉሳኔዉ አስተዳደራዊ እንጂ በዳኝነት ነክ አግባብ ታይቶ የተወሰነ አይደለም፡፡በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ሥልጣን ሳይኖረዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔ በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 92546 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ 1ኛ አመልካች በጉዳዩ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ በሌለበት ዉሳኔ የሰጠዉም ጉባኤዉ ሆኖ እያለ ተጠሪ 1ኛ አመልካችን በተጠሪነት በመሰየም አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ማቅረባቸዉ ተገቢ አይደለም በማለት ችሎቱ 1ኛ አመልካችን ከክርክሩ ዉጭ እንዲያደርግ የቀረበለትን ክርክር ምንም ምክንያት ሳይገልጽ 1ኛ አመልካችን የክርክሩ አካል አድርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ የ1ኛ አመልካችን በፌዴራል ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 ስር የተደነገገዉን ፍትህ የማግኘት መብት የሚቃረን ነዉ፡፡

እንዲሁም ጉባኤዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ አባል የሆኑበትን ኮሚቴ በማቋቋም እንዲጠና በማድረግ የደመወዝ ክፍያን በአንድ በኩል በሌላ በኩል የሥራ ኃላፊዎች በኃላፊነታቸዉ ምክንያት ለሚያከናዉኑት ተጨማሪ ተግባር ሊከፈላቸዉ የሚገባዉን ተጨማሪ የኃላፊነት ክፍያ ራሱን አስችሎ በመለየት ያቀረበዉን የጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ በሥራ ሂደት ኃላፊነታቸዉ ለሚሰሩት ተጨማሪ ሥራ ራሱን የቻለ የሥራ ኃላፊነት ክፍያ እንዲከፈላቸዉ የተወሰነ እንጂ ደመወዝ አለመሆኑን ዉሳኔዉ በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህንን ዉሳኔ ያስተላለፈዉ በሕግ የተሰጠዉን ሥልጣን በመጠቀም በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ ጉባኤዉ ከቀን 01/11/2008ዓ/ም ጀምሮ የክልሉ ዳኞች ደመወዝ ወጥነት ያለዉ (flate rate)እንዲሆን ወስኗል፡፡የጉባኤው ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ በጠየቁት መሰረት የኃላፊነት አበል እንደደመወዝ የሚቆጠር ከሆነ በተመሳሳይ ሥራ ላይ ለሚገኙ ሰዎች የተለያየ ደመወዝ የሚከፈልበትን ሁኔታ በመፍጠር ለተመሳሳይ ሥራ እኩል ክፍያ የሚለውንና የእኩልነት መርህ የሚቃረን ይሆናል፡፡ በዚህ

አግባብ በጉባኤው የተሰጠ ውሳኔ በፍርድ ቤቶች ታይተው እንዲከለሱ የሚደረግ ከሆነ የዳኝነት ነጻነትና ተጠያቂነት መርህን የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግልጽ የሆነውን ጉባኤው በቀን 25/05/2010ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ ወደ ጎን በመተው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውንና ለክርክሩ መሰረት ያልሆነውን የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ ስለደመወዝ የሰጠውን ትርጉም በመዋስ በጉባኤው የተሰጠው ውሳኔ የደመወዝ ጭማሪ ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች ለተጨማሪ ኃላፊነታቸዉ ከሚከፈላቸው ክፍያ ላይ የጡረታ መዋጮ ከፍለው ከሆነ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ከሚመለከተው አካል መጠየቅ ከሚችሉ በስተቀር የጡረታ መዋጮ መክፈላቸው ክፍያውን ደመወዝ አያሰኘውም፡፡ ጉባኤው በቀን 25/05/2010ዓ/ም የሰጠውን የክፍያ ውሳኔ እና ከዚህ በፊት የነበረውን ደመወዝ ክፍያ መጠን እንደገና በማየት በቀን 28/09/2012ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የነበረውን የደመወዝ መጠን እና የኃላፊነት ክፍያ ከፍ አድርጎ በማሻሻል ራሱን የቻለ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ጉባኤው ይህንን ማድረጉ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ተግባራዊ አድርጓል ከሚያስብል በስተቀር የክልሉ ሰበር በውሳኔዉ ላይ እንዳሰፈረው አስቀድሞ የሰጠው ውሳኔ ፀንቶ እያለ ያልተገባ ውሳኔ ሰጥቷል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ሳይኖረው በመሆኑ፣1ኛ አመልካች በጉዳዩ ተጠያቂ የሚያደርገው ምክንያት ባለመኖሩ፣በጉባኤው የተወሰነው ደመወዝ ሳይሆን የኃላፊነት አበል በመሆኑ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የጉባኤውን ውሳኔ የከለሰው የጉባኤውን ሥልጣን በሚጋፋ መልኩ በመሆኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሰጠውን ዉሳኔ በመከለስ የጉባኤውን ዉሳኔ የሻረበትን አግባብ ከክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 67/1 እና በክልሉ አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17/2 አንጻር ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ በቀን 05/04/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልሳቸውም ይዘት በአጭሩ፡-አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር የተደነገገውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚያሰኙ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ሊመረመር አይችልም ተብሎ አቤቱታዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 9 መሰረት ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል፡፡ የሰበር አቤቱታው የተጣሰውን ሕግና የተፈጸመውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የማያሳይ ከመሆኑም በተጨማሪ ሥርዓቱን ጠብቆ ያለቀረበና የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ዉድቅ ይደረግልኝ፡፡አቤቱታው አግባብነት የሌላቸውን አገላለጾችን የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ፍርድ የሚኮንን በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 91(3 እና 4) እና 230 መሰረት ሊሻሻል ወይም ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፌዴራሉ ሕገ መንገስት አንቀጽ 80(3/ለ) እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 67(2/ሀ) በክልል ጉዳይ ላይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ያለ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

በተጨማሪም በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17/2 ስር …መሰረታዊ የሕግ ስህተት *ታይቶባቸዋል 'የሚባሉትንና የሚከተሉትን ክልላዊ ጉዳዮች"* በሚል ከደነገገው መረዳት የሚቻለው በአንቀጽ 17(12/ሀ እና ለ) ውጪ ያሉትን አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን የሚመለከት እንጂ ሠበር ሰሚ ችሎት ከፊደል ሀ-ሐ ከተዘረዘሩት ውጪ ሊያይ አይችልም የሚል ትርጉም ሊሰጠዉ አይችልም፡፡በዚህ ሕግ አንቀጽ 17/3 ላይ "በሰበር እንዲታይ የሚቀርብ ማናቸዉም አቤቱታ" የሚለዉ በአንቀጽ 17/2 ስር "የሚባሉትን" ከሚለው ቃል ጋር እንዲሁም በፌዴራልና በክልል ሕገ መንግስቶች ላይ ከተመለከተው ጋር ተጣምረው ሲተረጎሙ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የመመልከት ሥልጣን እንዳለው የሚያሳይ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ይህንን መሰረት በማድረግ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡

አመልካቾች በሰ/መ/ቁጥር 92546 ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ጠቅሰው ቢከራከሩም ይህ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለዉም፡፡ይልቁንም በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም የዐቃቤ ሕግ ጉባኤ በዲስፕሊን ጉዳይ የሰጠው ውሳኔ በሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ የሕግ ስህተት ከመታረሙ አንጻር ሲታይ በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ያለውን የሕግ ስህተት ለማረም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመመርመርና የማረም ሥልጣን እንዳለው ነው፡፡ እንዲሁም የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ የሕግ ስህተት በክልሉም ሆነ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርበው ሊታረሙ እንደሚችሉ በሰ/መ/ቁጥር 61221 እና 43511 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

ጉባኤው የሁሉም ዳኞች እና የጉባኤ ተሿሚዎች ደመወዝ 82% ተሰልቶ ይከፈል የሚል ጥቅል ዉሳኔ ወስኖ እያለ ደመወዙን ሲያሰላ ሲከፈል የነበረዉን ደመወዝ በመቀነስ የኃላፊነት አበል ክፍያ በሚል ቀንሶ ያሰላዉና በጀት የሚያዘው የ1ኛ አመልካች አስተዳደር በመሆኑ በክርክሩ መግባቱ ተገቢ ነዉ ሊፈጸም የሚችል ውሳኔ እንዲሰጥም የሚያደርግ በመሆኑ የክልሉ ሰበር በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ባለመቀበሉ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡

ተጠሪ ጉባኤው ደመወዝና የኃላፊነት አበል የመወሰን ሥልጣን የለውም የሚል ቅሬታ አላቀረብኩም፡፡ችሎቱም በዚህ መልኩ አልወሰነም፡፡ተጠሪ ቅሬታ ያቀረብኩበት ጉባኤው በቀን 26/06/2013ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ጉባኤው በቀን 28/09/2012ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ላይ 82% እየተጨመረ ተሰልቶ ይከፈል ሲል ደመወዝና የኃላፊነት አበልን ለይቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የተጠሪ ቅሬታ በጉባኤው ውሳኔ መሰረት የ1ኛ አመልካች አስተዳደር የተጠሪን ደመወዝ ሲያሰላ በብር 13,702.00 ላይ 82% ጨምሮ ማስላት ሲገባው ከነበረኝ ደመወዝ ቀንሶ ብር 12,702.00 ይዞ 82% ያሰላበት መንገድ ተገቢ ባለመሆኑ ለፍርድ ቤቱ አስተዳደር ቅሬታ አቅርቤ ምላሽ ሳይሰጠኝ ቀርቷል፡፡ለጉባኤው ያቀረቡኩትን ቅሬታም ጉባኤው የተሰላበት መንገድ ትክክል ነው በማለት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡ጉባኤው በቀን 25/05/2010ዓ/ም ደመወዝና የኃላፊነት አበል ለይቶ በወሰነዉ መሰረት ሲከፈለኝ ከነበረዉ ከብር 13,702.00 ደመወዝ ላይ የጡረታ መዋጮ ስከፍል እንደቆየሁ የክልሉ ሰበር

ሰሚ ችሎት አረጋግጦ የሰጠዉ ጉባኤዉ ወስኖ የነበረዉ ደመወዝ እንጂ የኃላፊነት አበል አይደለም በማለት በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም በቀን 04/05/2014 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመለከተው የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የዚህን ውሳኔ የሚሹ ዋና ዋና ጭብጦች የአማራ ክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ(ጉባኤ) የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር አይቶ የመዳኘት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የክልሉ ሰበር የጉባኤውን ውሳኔ በስረ ነገሩ አይቶ ሽሮ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት አለ ወይስ የለም? የሚሉ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእነዚህ ጭብጦች ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ አንድን የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር (cassation) በማየት፣ በይግባኝ (appeal) በማየት እና በዳኝነት አይቶ በመከለስ (judicial review) መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው? እንዲሁም ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ በሰበር ሊታይ የሚገባ ነው ወይስ በዳኝነታዊ ክለሳ ሊታይ የሚገባ ነዉ? የሚሉትን ተጓዳኝ ጭብጦች ጭምር መመርመር እንደሚገባ ተገንዝበናል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ጭብጦች ከመመርመራችን በፊት ተጠሪ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለውም በማለት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ)ን በመጥቀስ ያቀረቡትን መቃወሚያ በቀዳሚነት ተመልክተናል፡፡በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይተው በተሰጡ የመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ ተፈጽመዋል ሊባሉ የሚችሉ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይተዉ ሊታረሙ የሚችሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተቶችን በተመለከተ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች *(1)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሀ) ስር በተመለከተው መሰረት ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ፤ *(2)* በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሸ) ስር እንደተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ፤ *(3)* በአንቀጽ 2(4/ለ) እና 10(1/መ) ላይ እንደተመለከተው የሕዝብን ጥቅም በሚመለከት እና ሀገራዊ ፋይዳ ባለው ጉዳይ ሕግን አላግባብ በመተርጎም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ድንጋጌ ተጠቅሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲሆን ከሚሉ ሦስቱ ምክንያቶች መካከል ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

የተያዘው ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለበት ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ በመከለስ የጉባኤውን ውሳኔ የሻረበት አግባብ የክልሉን ሕገ መንግስት አንቀጽ 67/1 የሚቃረን መሆን አለመሆኑን እንዲመረመር ነው፡፡አመልካቾች በአቤቱታቸውም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በሕገ መንግስት እና በማቋቋሚያ አዋጁ የተሰጠውን ሥልጣን ተግባራዊ እንዳያደርግ የሚያደርግ ውሳኔ ከመሆኑም በተጨማሪ በፌዴራል ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ስር ከተሰጠው ስልጣን ዉጭ በመውጣት የጉባኤውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ የፌዴራሉንም ሆነ የክልሉን ሕገ መንግስት እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በሰ/መ/ቁጥር 92546 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነው በማለት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1ሐ እና መ) ማዕቀፍ ውስጥ ሊታይ የሚገባ ጉዳይ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/2 ስር የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጓል፡፡በተመሳሳይ በአማራ ክልል በተሻሻለው ሕገ መንግስት አንቀጽ 67(1/ሀ) ስር ዝርዝሩ በሕግ በሚወሰነው አግባብ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛና የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/2 ስር ከተደነገገው በተጨማሪ በዚሁ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ስር ዝርዝሩ በሕግ በሚወሰነው መሰረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንዳለው ተደንግጓል፡፡

እኛም ከፍ ሲል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስር ከተጠቀሱት መመዘኛዎች እና በፌዴራሉና በክልሉ ሕግጋተ መንግስታት አንጻር ጉዳዩን እንደተመለከትነው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ በሰበር ተመልክቶ የወሰነው በክልሉ እና በፌዴራል ሕግጋተ መንግስታት የተሰጠውን ሥልጣን በሚቃረን አኳኋን መሆን አለመሆኑ፣ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በክልልም ሆነ በፌዴራል ሕግጋተ መንግስታት የተሰጠውን ሥልጣን ተግባራዊ እንዳያደርግ የሚያደርግ ውጤት ያለው መሆን አለመሆኑን እና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 18342 ፣ 61221 ፣ 43511 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር ተገናዝቦ በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ማዕቀፍ ስር ሊመረመር የሚገባዉ ጉዳይ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር ለማየት ሥልጣን የለውም ሲሉ ያቀረቡትን ተቃዉሞ አልተቀበልንም፡፡

በመጀመሪያም ከላይ ተጓዳኝ ጭብጦች ናቸው ብለን የያዝናቸውን ጭብጦች መርምረናል፡፡አንድን የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር በማየት (cassation) ፣ በይግባኝ (appeal) በማየት እና በዳኝነት አይቶ በመከለስ (judicial review) መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው የሚለዉን በቅድሚያ መመልከቱ ተገቢ

ይሆናል፡፡ ከመዝገበ ቃላት ትርጓሜ የተነሳን እንደሆነ ሰበር ወይም cassation በሚል የሚታወቀው ቃል በታዋቂዉ ብላክስ ሎዉ መዝገበ ቃላት ላይ እንደተመለከተው ካሰር (casser) ከሚል የፈረንሳይኛ ቋንቋ ግስ የመጣ ቃል ሆኖ የቃሉ ጥሬ ትርጉምም የአንድን ፍርድ/ውሳኔ የተፈጻሚነት ኃይል(force) መስበር እና ሕጋዊ ዉጤት እንዳይኖረው ማድረግ(invalidate)፣መሻር ወይም ተግባራዊነቱን ማስቀረት ነው የሚል ትርጓሜ የተሰጠው ነው፡፡ (cassation comes from the French verb casser and its literal meaning is to "quash the force and validity of a judgement.(*black's law dictionary 5ኛ እትም* ገጽ 197 ይመለከቷል፡፡) የሰበር ሥርዓት ምንጭ የሲቪል ሕግ ሥርዓት ሲሆን እዛን ግራዊች(Ezan Grouich) የተባለ ሰዉ (The Soviet Codes of Law)በሚል ባሳተሙት መጸሀፋቸው ላይ እንደገለጹት በራሽያ ፌዴሬሽን የሰበር ስርዓት የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የሕግ ስህተት ያለበትን የመጨረሻ ፍርድ የተፈጻሚነት ኃይል በመስበር በምትኩ ሌላ ፍርድ የሚሰጥበት ሥርዓት ነው ሲል ይገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል Peter Herzos እና Martha Weser እንዲሁም Mauro Cappelletti እና Joseph M. Perillo በፈረንሳይና በጣሊያን የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው መጽሐፍት የፃፉ የሕግ ምሁራን መጽሐፎቻቸው ላይ የሰበር ሥርዓት በእነዚህ አገራት አንድ የይግባኝ የሚታይበትን ሂደት የጨረሰ የሕግ ስህተት ያለበት የመጨረሻ ፍርድ የመጨረሻ የዳኝነት አካል በሆነው ፍርድ ቤቶቻቸው ታይቶ የሚሻርበት ወይም ወደ ሥር ፍርድ ቤት በመመለስ የሚወስኑበት እንጂ የራሳቸውን አዲስ ውሳኔ የሚሰጡበት እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡ከዚህ የምንገነዘበው በሰበር የሚታየው በመጨረሻ ፍርድ ቤት እንደሆነ ፣በሰበር የሚታየውም ፍርድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ፍርድ ሆኖ በይግባኝ የሚታየበትን ሂደት የጨረሰ የሕግ ስህተት ያለበት የመጨረሻ ፍርድ እንደሆነ እና ፈረንሳይና ጣሊያን የሰበር ፍርድ ቤቶች የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ከመሻር ባለፈ እንደ ራሺያ ፌዴሬሽን ፍርድ ቤት አዲስ ውሳኔ እንደማይሰጡ ነው፡፡

በአገራችን "ስለሰበር" ምንነት ትርጓሜ የሰጠ ሕግ ባይኖርም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4 እና 5) ስለመሠረታዊ የሕግ ስህተት እና ስለመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠው ትርጓሜ የምንገነዘበው ሰበር የሚያየው የፌዴራሉ የመጨረሻ ዳኝነት አካል በሆነው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተደራጀ ሰበር ሰሚ ችሎት መሆኑ፣ የሚያያውም ውሳኔ በዚሁ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና በበታች መደበኛ ፍርድ ቤቶች ታይቶ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ብቻ ሳይሆን በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል፣በተቋማት ወይም በአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች የተሰጠ እና ለጉዳዩ እልባት የሚሰጥ ፍርድ፣ብይን፣ትእዛዝ፣ውሳኔ እና/ወይም የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ ፍርድ፣ብይን፣ትእዛዝ ወይም ውሳኔን እንደሚጨምር ተደንግጓል፡፡እንዲሁም በአገራችን እስካሁን በሰበር ችሎቱ ከዳበረው ዳኝነታዊ ፍልስፍና (judicial jurisprudence) እንደሚታወቀው ሰበር ችሎት ያለዉ ሥልጣን መሰረታዊ የሕግ

ስህተት አርሞ ዉሳኔውን ከመሻር እና ጭብጥ ይዞ ከመመለስ ባለፈ በጉዳዩ ላይ አዲስ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ጭምር እንዳለው ነው፡፡ ይህም የእኛ አገር የሰበር ሥርዓት ከሌሎች ከላይ ከተጠቀሱት ውሳኔዎችን በሰበር የማየት ሥርዓት ከዘረጉ አገራት ሥርዓት አንጻር ሲነጻጸር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ከማረም አኳያ ሰፊ ሥልጣን እንዳለው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ይህም የሆነው በሕገ መንግስቱ ይህ ሥርዓት እንዲዘረጋ መነሻ ምክንያት የሆነው የሕግ አተረጓጎም ወጥነት የማምጣትና በዚህም ዜጎች በእኩልነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ዓላማ በተሟላ መልኩ ከግብ እንዲደርስ ለማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል *ዳኝነታዊ ክለሳ* (judicial review) ከላይ በተጠቀሰው መዝገበ ቃላት ላይ፡ A court's power to review the actions of other branches or levels of government; esp.,the courts' power to invalidate legislative and executive actions as being unconstitutional. …And a court's review of a lower court's or an administrative body's factual or legal findings.(*black's law dictionary 9ኛ እትም ገጽ* 924). የሚል ትርጓሜ የተሰጠው ሲሆን ይህም በግርድፉ ሌሎቹ የመንግስት አካላት (ሕግ አውጭው እና ሕግ አስፈጻሚው) እንደ ቅደም ተከተላቸው የሚያወጡት ሕግ ፣ የሚፈጽሟቸው ተግባራት እና የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ሕገ መንግስታዊ መሆን አለመሆናቸውን (constitutionality) እና ሕጋዊነታቸውን (legality) ፍርድ ቤቶች የሚከልሱበትንና ጉድለት ካለባቸዉም ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚወስኑበትን ሥርዓት የሚመለከት ነው የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

እንዲሁም ከተለያዩ የሕግ ድርሳናት መገንዘብ እንደሚቻለው በዳኝነታዊ ክለሳ (judicial review) የሚታዩ ጉዳዮች እንደየአገራት የሕግ ሥርዓት ሊሰፉና ሊጠብ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ አውጪው የወጣ ሕግ እና የተላለፈ ዉሳኔ ፣የሕግ አስፈጻሚው ወይም የአስተዳደር አካላት ተግባራትና ውሳኔዎች በዳኝነት አካል የሚከለስበት ሥርዓት በሰፊው የሚታወቅ ነው፡፡አገራት በሕግ አውጭው የወጣ ሕግ ወይም የተላለፈ ውሳኔ እንደዚሁም በአስፈጻሚው/በአስተዳደር አካል የሚፈጸሙ ተግባራት ወይም የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ሕገ መንግስታዊነት እና/ወይም ሕጋዊነት (Constitutionality and legality) በዳኝነት አይተው እንዲከልሱ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም ለሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት ሥልጣን ይሰጣሉ፡፡ሕገ መንግስትን መተርጎምን የሚጠይቁ የሕገ መንግስታዊነትና ሕጋዊነትን ጥያቄዎችን ተቀብለው ሕገ መንግስትን ተርጉመው የሕግ አውጪውን ሕግና ውሳኔ እንዲሁም የሕግ አስፈጻሚውን ሕግ፣ውሳኔ ወይም ሌላ ተግባር በዳኝነት አይተው እንዲከልሱና የመጨረሻ ውሳኔ ኢንዲሰጡ አሜሪካ እና ሕንድ የመሰሉ አገራት ለመደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤቶቻቸው ሥልጣን የሚሰጡ ሲሆን እንደ ጀርመን ፣ኦስትሪያ እና ደቡብ አፍሪካ ያሉ አገራት ደግሞ ለሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤቶቻቸው ሥልጣን ይሰጣሉ፡፡

እነዚህ ፍርድ ቤቶች አንድ ሕግ ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔ ሕገ መንግስቱን የሚጥስ ወይም የሚቃረን እንዲሁም የሕጋዊነት ጉድለት አለበት የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ሕጉን ከሕግነት ተራ በማስወጣት ተፈጻሚ እንዳይሆን ለማድረግ የአስተዳደር ውሳኔውም ተግባራዊ እንዳይሆን ለመወሰን የሚከተሉበት አካሄድም እንደዚሁ የተለያየ ነዉ፡፡ አሜሪካ የዳኝነታዊ ክለሳ የምታደርግበት ሞዴል ያልተማከለ ዳኝነታዊ ክለሳ ሥርዓትን (The decentralized model of judicial review) ሲሆን በዚህ ሞዴል መሰረት የክለሳ ጥያቄዉ ከበታች ፍርድ ቤት ጀምሮ በየደረጃዉ ይግባኝ ሥርዓት በሚመስል አካሄድ ታይቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ የመጨረሻ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቶበት እንዲቋጭ ታደርጋለች፡፡ እንደጀርመን ያሉት ደግሞ የክለሳ ጥያቄዉ በቀጥታ ለሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚያደርግ ሥርዓት(The centralized model of judicial review) የሚከተሉ ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት ክለሳ ተደርጎ የመጨረሻና አስገዳጅ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋሉ፡፡በደቡብ አፍሪካ ደግሞ የአንድ ሕግ ሕገ መንግስታዊነትና እና የአንድን የአስተዳደር/የአስፈጻሚ አካል ተግባር/ውሳኔ ሕገ መንግስታዊነትና ሕጋዊነት በተመለከተ የአገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሕገ መንግስታዊነት ትርጉም (Preliminary Constutitutional Interpretation) ሕገ መንግስቱን ተርጉሞ እንዲወስን ሥልጣን ትሰጥና የሕገ መንግስታዊነት ጥያቄ የተነሳበት ሕግ እና የሕገ መንግስታዊነትና የሕጋዊነት ጥያቄ የተነሳበት የአስፈጻሚ/የአስተዳደር አካል ተግባር/ውሳኔ ተፈጻሚነት እንዳይኖራቸው የመጨረሻውን ዉሳኔ የመስጠት ሥልጣን የሚኖረዉ ሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት ነዉ የሚል ሥርዓት በሕገ መንግስቷ እንደዘረጋች በዘርፉ የተጻፉ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡

የእኛን አገር ስርዓት የተመለከትን እንደሆነ በሦስቱ የመንግሥት አካላት መካከል ማለትም በሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈጻሚው እና በሕግ ተርጓሚው መካከል በፌዴራልና በክልል ሕግጋተ መንግስታት በተመለከተው አግባብ የሥልጣን ክፍፍል ያለ ቢሆንም በመካከላቸው የእርስ በእርስ ክትትልና ሚዛኑን ተጠብቆ (check and balance) እየተሰራ መሆኑ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ከሌለ ተቋማቱ በሕግ የተጣለባቸውን የዜጎችን ሠብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር አይችሉም፡፡ በአንጻሩ የእርስ በእርስ ክትትልና ሚዛኑን ጠብቆ የመስራት መርህ አተገባበር አለአግባብ ጣልቃ መግባትን ካስከተለ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝንና የተጣለባቸውን ግዴታ እንዳይወጡ ሊያደርጋቸው ስለሚችል ቁጥጥሩ በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት አግባብ መፈጸም አለበት፡፡

አስተዳደራዊ አካላት የሚሠጧቸው ውሳኔዎች በፍ/ሕ/ቁጥር 401/1 እንደተመለከተው ከተሠጣቸው ሥልጣን በማለፍ ከወሰኑ (ultra virus) ወይም በተሠጣቸው ሥልጣን ስር ሆኖ ነገር ግን በሕጉ የተመለከቱትን አስገዳጅ ሁኔታዎችና ፎርም ሳይከተሉ የሚፈጽሙት ተግባር ወይም ውሳኔ ፈራሽ ነው፡፡ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የዳኝነት ክለሳ መኖር ካለበት ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ የመንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍል መርሕ ነው፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 79/1 መሠረት የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህም ከሕገ-መንግሥታዊ ክርክሮች (constitutional disputes) ውጭ ማንኛውም በፍርድ ቤት ታይተው ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮች (justiciable matters) ላይ

ፍርድ ቤቶች ዳኝነታዊ ክለሳ የማድረግ (judicial review) ተፈጥሮአዊ የሆነ ዳኝነታዊ ሥልጣን (inherent judicial power) እንዳላቸው ያሳያል፡፡ በፍርድ ቤት ታይተው ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮች የሚለውም የጉዳዮቹ ባሕሪ በፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር ሊወድቁ የማይችሉ፣ አከራክሮ ሊፈጸም የሚችል ውሳኔ ሊሰጥባቸው የማይችሉ ጉዳዮችን የሚመለከት ሲሆን በሌላ በኩል ጉዳዮቹ በፍርድ ሊታይ የሚችሉ እንኳን ቢሆን ሌሎች የመንግሥት አካላት በሕገ-መንግሥት ባለው የሥልጣን ክፍፍል መርሕ መሠረት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣናቸውን (constitutionally mandated powers) መሠረት አድርገው የሚወስኗቸው ጉዳዮችንም ይጨምራል፡፡ በሌላ በኩል የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78/4 እና 37 ላይ የተደነገገው አንድ ላይ ሲነበብ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓትን የሚከተል የዳኝነት ነክ አካላት በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ሊሰጣቸው እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ የእነዚህ አካላት የዳኝነት ሥልጣን በተፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን በግልጽ ሕግ ለመዳኘት ሥልጣን ሲሰጣቸውና የሚሰሩበት የተደነገገ የዳኝነት ሥርዓት ሲኖራቸውና ይህን ተከትለው ሲሰሩ የሚኖራቸው ሥልጣን ነው፡፡ ይህም በዘመናዊው የመንግሥት ሥርዓት መንግሥት ብዙ ጉዳዮች ላይ ሠፊ ሥልጣን ያለው አስፈጻሚዉ አካል በመሆኑ ለመንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል የዳኝነት ነክ ሥልጣን አስፈላጊ በመሆኑ፣ የተወሰኑ ጉዳዮች ደግሞ ፍሬ ነገሮችን ለመመልከት ልዩ ዕውቀት (specialization) የሚጠይቁ በመሆኑ እና ፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን የሥራ ጫና ለማቃለል ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

ነገር ግን ጠንካራና አስተማማኝ የዜጎች ሰብዓዊ መብት የሚከበርበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሕግ የበላይነትን ማስፈን ወሳኝ ነው፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት መግቢያ ላይ እንደተመለከተው የሕግ የበላይነትን የተረጋገጠበት አሰራር መዘርጋት የሕገ-መንግሥቱ ዋነኛ ዓላማ ሲሆን አንዱ መስፈርት ደግሞ የዜጎችን በፍርድ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በነፃና ገለልተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ መደረጉ ነው፡፡የሕግ የበላይነት መርሕ ሰፊ ሀሳቦችን የያዘ ቢሆንም በሕግ ሥልጣኑ የተገደበ መንግሥት እንዲኖርና የዜጎች መብት የተከበረበት ሥርዓትን ለመፍጠር የሚረዳ ነው፡፡ በፌዴራሉ ሕገ-መንገሥት መግቢያ ላይ የተመለከተው የሕግ የበላይነት ዓላማ ከግብ የሚደርሰው የመንግስት አካላት ለሚወስዱት እርምጃ ተጠያቂ መሆንና ኃላፊነት መውሰድ ሲችሉ ነው፡፡ይህም ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች አንዱ በሰጡት አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ መብቱ የተነካበት ሰው ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ ሲችልና ፍርድ ቤቶችም ተገቢውን መንገድ ተከትለው ጥያቄ የቀረበበት ዉሳኔ ሕጋዊነትን የተከተል መሆን አለመሆኑን በዳኝነት ማየት ሲችሉ ነው፡፡ እንዲሁም የአስተዳደር አካላት የሠጡት ውሳኔ በሕጉ የተዘረጋውን ሥርዓት የተከተለና ዜጎች ተገቢው የመሰማት መብት (due process of law) ያገኙ ስለመሆኑ ቁጥጥር ለማድረግ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የዳኝነት ክለሳ ያስፈልጋል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 79(1) መሠረት የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ላይ ሰዎች ፍትሕ የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፍርድ ሊዳኙ የሚችሉ እስከሆኑ ድረስ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ጉዳዮችን እንዲመለክት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78 መሰረት ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ቀርቦ መታየቱ ነጻ

የዳኝነት አካል ያስፈለገበት ዓላማ ሊሳካ የሚችልበትና ሰዎች ያላቸውን መብት በሕግ ማስከበር የሚችሉበት ዋነኛ መሣሪያ አስተዳደራዊ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ ማየት መቻል ነው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃም አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የዳኝነት ክለሳ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 13(1) ሰብዓዊ መብቶችን የማክበርና ማስከበር ኃላፊነት ከተሰጣቸው አካላት ዋነኛው የዳኝነት አካሉ በመሆኑ የአስተዳደር አካላት ከዜጎች ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳይኖር ለመከላከል ሆነ ጥሰት ሲኖር ዜጎች ጥሰቱን የሚያሳርሙበት ዕድል ስለሚያስፈልግ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የዳኝነት ክለሳ የግድ የሚል ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ከፍርድ ቤት ውጭ በሕግ የዳኝነት ነክ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚሰጡ ዉሳኔዎችንም ሆነ በሕግ በተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሰጧቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በዳኝነታዊ ክለሳ ሂደት በማለፍ በፍርድ ቤት መታየት ይኖርባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል የይግባኝ(Appeal) አቀራረብ ሥርዓት ምንነት የተመለከትን እንደሆነ ይግባኝ የሚባልበት ሥነ ሥርዓት በዋናነት በበታች መደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ በየተዋረዱ ባሉት የበላይ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እንደገና የሚመረመርበትን የሚመለከት ነው፡፡ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 12/2፣ 321 እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 54 ይመለከቷል፡፡) በተጨማሪም አስተዳደራዊ ውሳኔ ወይም የዳኝነት-ነክ ሥልጣን የተሰጠው አካል(Quasi-judicial organ) የሰጠው ውሳኔ በየደረጃው በተቋቋመና በከፍተኛው የዳኝነት-ነክ ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በሕግ በግልጽ ከተደነገገም እነዚሁ አካል የሰጡት ውሳኔ በከፍተኛው መደበኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚታይበትን ሥነ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡(ለአብነት በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 69/2፣98/4፣ 115/2፣ 153/8፤ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(1 እና 4) እና በአዋጅ ቁጥር 714/2003 እና ይህንን አዋጅ በተካው አዲስ አዋጅ ላይ በተመሳሳይ በአንቀጽ 56(1 እና 4) እና በሌሎችም ላይ ተደንገገው ይመለከቷል፡፡የይግባኝ ሥርዓትን ከዳኝነታዊ ክለሳ የሚለዩትም ምክንያቶች በይግባኝ ጊዜ በልዩ ሁኔታ በሕግ እስካልተገደበ ድረስ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበታች ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረውን ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን፣በውስን ሁኔታዎች አዲስ ማስረጃ መቀበልንና የበታች ፍርድ ቤቶች ወይም የዳኝነት-ነክ አካል የሰጡት ውሳኔ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ድምዳሜ ስህተት አለበት ብሎ ሲያምን ዉሳኔዉን ሽሮ አዲስ ውሳኔ መስጠትን ጭምር የሚያካትት ሲሆን በዳኝነታዊ ክለሳ ደግሞ ሕግ አውጪው ያወጣው ሕግ፣ሕግ አስፈጻሚው የፈጸመዉ ተግባር(የወሰነው ውሳኔ) እንዲሁም የዳኝነት-ነክ ሥልጣን የተሰጠዉ አካል የወሰነዉ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ ብቻ ተመስርቶ ሕገ መንግስታዊ ወይም ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን በመከለስ ሕገ መንግስታዊ ወይም ሕጋዊ አይደለም የሚል ከሆነ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰን ወይም ውሳኔውን ሽሮ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን መመለስ አሊያም የክለሳ ጥያቄዉን ውድቅ በማድረግ ውሳኔውን ማጽናት እንጂ የራሱን አዲስ ውሳኔ አይሰጥም፡፡

ከላይ በዝርዝር ከተመለከትነው ከተለያዩ አገራት ልምድ፣ በአገራችን በተለያዩ ሕግጋት እና በዳኝነት ሥራ ከዳበረው ተሞክሮ (judicial jurisprudence) ከተንጸባረቀው የምንገነዘበውም አንድን ዉሳኔ በሰበር የማየት፣ በይግባኝ የማየት እና በዳኝነት አይቶ የመከለስ ሥርዓት በጽንሰ ሀሳብ ደረጃም ሆነ በአተገባበራቸው የተለያየ የክርክር አመራርንና መነሻ ምክንያትን የሚጠይቁ እንደሆኑ ነው፡፡በአገራችን በፌዴራል ደረጃ በልዩ ሁኔታ በሕግ በግልጽ በተቃራኒዉ እስካልተደነገገ ድረስ አንድ በፍርድ ቤት፣ በአስተዳደር አካል ወይም ዳኝነት ነክ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ ውሳኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊመረመር የሚችለው እንደነገሩ ሁኔታ በሕግ በተዘረጋው በይግባኝ እና በዳኝነታዊ ክለሳ ሥነ ሥርዓት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኂላ ብቻ ነው፡፡ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ብቻ መርምሮ ስህተቱን የሚያርም ውሳኔ መስጠት በመሆኑ ከፍርድ ቤት ውጭ ባለ አካል የተሰጠ ውሳኔ በተለይም በዳኝነታዊ ክለሳ ሊታይ የሚችል ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ ሳይታይ በቀጥታ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብ ከሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት በክለሳ ሥርዓት ሊመረመሩ የሚችሉና ፍሬ ነገሮችን ከማስረጃ አንጻር ጭምር መመርመርንና ማረጋገጥን የሚጠይቁ የክርክር ነጥቦች ወይም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልሆኑ ስህተቶች የሚታረሙበትን ሂደት የሚገድብ ይሆናል፡፡

እንዲሁም አንድ አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ ነው ተብሎ እንደነገሩ ሁኔታ በይግባኝ ፣በዳኝነታዊ ክለሳ ቀጥሎም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ከሆነ በሰበር ሥርዓት ታይቶ የማይታረም ከሆነ የሕገ መንግስት የበላይነት መርህ፣የዲሞክራሲያዊ መንግስት መገለጫ የሆነው የተጠያቂነት መርህ እና የዲሞክራሲያዊ መንግስት የሥልጣን ክፍፍል መሠረታዊ መርህ የሆነው የመንግስት አካላት እርስ በእርሳቸው የሚኖራቸዉ የሥልጣን ክትትልና ሚዛን የመጠበቅ (Check and Balance) መርህ እንዲሸራረፍ ያደርጋል፡፡በመሆኑም በሕግ በልዩ ሁኔታ በቀጥታ ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ እስካልተደነገገ ድረስ በሰበር ከመታየቱ በፊት እንደነገሩ ሁኔታ በይግባኝ ወይም በዳኝነታዊ ክለሳ ሥነ ሥርዓት ሊታይ ይገባል፡፡

ከፍ ሲል በዝርዝር የተመለከትነው በአብዛኛዉ የፌዴራል ሕግጋትን ማዕከል ያደረገ ቢሆንም በክልል ደረጃ የሚኖረው የሰበር ሥርዓትም ሆነ ዳኝነታዊ ክለሳ ከላይ ከተመለከትነው የሕግ እና የጽንሰ ሀሳብ ትንተና አንጻር ሲታይ በፌዴራል ደረጃ ከተዘረጋው የሰበር ሥርዓትና ዳኝነታዊ ክለሳ በመሰረታዊነት የተለየ አይደለም፡፡

ከላይ የተመለከትነውን ትንታኔዎች መሰረት አድርገን የያዝናቸዉን ጭብጦች ስንመረምር ከላይ ይዘቱ ከተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ላቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ነው፡፡ ጉባኤው በክልሉ አዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀጽ 4/1 መሰረት

እንደገና የተቋቋመ ሲሆን በክልሉ ሰበር እና በዚህ ችሎት ደረጃ 2ኛ ተጠሪ ሆኖ የተሰየመው የጉባኤው ጽ/ቤት ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አካል ሆኖ እንደተደራጀ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በተለይ ጉባኤው ከሦስቱ የመንግስት አካላት በተለየ ማንነት የሶስቱን የመንግስት አካላት ስብጥር ይዞ ነገር ግን ደግሞ በአስተዳደራዊ ተጠያቂነት ረገድ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ሆኖ እንደተቋቋመ ከክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 66(4/ሐ) እና ከአዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀጽ 7(1/ሐ) መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም ጉባኤዉ ሕገ መንግስታዊ ተቋም እንደሚባሉት ተቋማት ሊቆጠር የሚችል እንጂ ከሦስቱ የመንግስት አካላት የአንዱን መደብ ይዞ የተቋቋመ አይደለም፡፡ይህ ልዩ የሚያደርገው ባህርይ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ሕገ መንግስትና በማቋቋሚያ አዋጁ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባሩ አንጻር የእለት ተእለት ተግባሩን ሲያከናውን አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ጉባኤው የዳኞችን እና የጉባኤውን ተሿሚዎች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ወይም የኃላፊነት አበል በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጠው በክርክር መልክ ሰምቶና አከራካሪውን ጭብጥ በማስረጃ አጣርቶና ማስረጃ መዝኖ ሳይሆን አስፈላጊውን ጥናት አስደርጎ አስተዳደራዊ ሥልጣኑን (ኃላፊነቱን) በመጠቀም አስተዳደራዊ ውሳኔ በማሳለፍ እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡

በሌላ በኩል ጉባኤው አንድ ዳኛ በዲሲፕሊን ምክንያት ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ከሥራ እንዲሰናበት ውሳኔ መስጠት እንዲችል ወይም በሕመም ምክንያት ዳኛዉ ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አልቻለም ብሎ እንዲሰናበት ውሳኔ እንዲሰጥ በክልሉ ሕገ መንግስትና በጉባኤው ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ለጉባኤው ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡በዚህ መልኩ ጉባኤው ውሳኔ የሚሰጠው ክርክርና ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ እንዲሁም ማስረጃዎችን መዝኖ የአከራካሪዉን ጭብጥ መኖር አለመኖር ካረጋገጠ በኋላ በመሆኑ የዳኝነት-ነክ ሥልጣኑን ተጠቅሞ የሚፈጽመዉ ተግባር ነዉ፡፡ የዳኝነት-ነክ ሥልጣኑን ተጠቅሞ በዚህ አግባብ የሚሰጠውም ውሳኔ በክልሉ ምክር ቤት ተመርምሮ የሚጸድቅበት ሥርዓት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 66/4 እና አዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀጽ 7(1/ሐ እና 6) እና 24(1/ሀ፣ሐ እና መ) በግልጽ ተመልክቷል፡፡በመሆኑም በዚህ ሥልጣኑ የሚሰጠው ዉሳኔ በክልሉ ምክር ቤት ሊመረመር ተመርምሮ ተገቢው ውሳኔ ሊሰጥበት ከሚችል በስተቀር በልዩ ሁኔታ በሕግ እስካልተደነገገ ድረስ በመደበኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት የሚታይ አይደለም፡፡

ከላይ በተመለከተው መሰረት ጉባኤው ከዳኝነት-ነክ ሥልጣኑ ዉጭ በሆነ አግባብ ሥልጣንና ተግባሩን መነሻ በማድረግ በሚያስተላልፋቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ በጥቅሉ ሕገ መንግስትንና ሕግን በሚቃረን (Unconstitutionality and Illegality) አኳኋን ወስኗል የሚባል ቢሆን፤በዝርዝር የተመለከትን እንደሆነ ከሥልጣን ገደቡ ዉጭ በመውጣት(ultra virus) ወስኗል፣ ጉባኤዉ ፍቅድ ሥልጣኑን ተጠቅሞ የወሰነው በቂ ምክንያት መሰረት ሳያደርግ (Irrational or unreasonable)ነው፣የሰጠው ውሳኔ በሥልጣን ገደቡ ውስጥ ቢሆንም ውሳኔዉ የሚመለከታቸውን ሰዎች (የዳኞችን ወይም የጉባኤ

ተሻሚዎችን) መብትና ጥቅም ለመጠበቅ የግድ መከተል ያለበትን የሥነ ሥርዓት ሂደት ለአብነት ሰዎቹ ስለጉዳዩ ያላቸዉን ሀሳብ ሳይሰማ (Procedural impropriety) ወስኗል፣ እንዲሁም የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ውሳኔዉ የሚመለከታቸውን ሰዎች መብትና ጥቅም የሚመለከት የሆነ እንደሆነ መብትና ጥቅማቸው ከሚገባው በላይ እንዳይጎዳ ሚዛናዊ ሆኖ (Proportionality) መወሰን ሲገባው ሚዛናዊ ያልሆነ ውሳኔ ሰጥቷል፣ ዳኝነታዊ ክለሳ ሲደረግ ከግምት ሊገቡ የሚገባቸውን ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸውን የመሰማትና ሌሎች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት (due process of law) ሌሎች መሰል መመዘኛዎች ከግምት ሳያስገባ ወስኖ ከሆነ በውሳኔዉ መብቱ በተነካበት ሰው አቤቱታ መነሻ በዳኝነታዊ ክለሳ ታይቶ ጉድለቱ እንዲታረም ሊወሰን ይገባል፡፡

እንዲሁም እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ምክንያቶች መሰረት ባደረገ መልኩ በዳኝነታዊ ክለሳ ታይቶ ከመወሰኑ በፊት የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ የሚታይበት ሥነ ሥርዓት በክልሉ ሕገ መንግስትም ሆነ በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ የተዘረጋ መሆን አለመሆን መርምረናል፡፡ ጉባኤው በሚሰጠው ውሳኔ ላይም ሆነ ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጋር በተያያዘ የሕጋዊነት ቅሬታ ያለው ዳኛ ወይም የጉባኤ ተሿሚ ቅሬታውን በምን አግባብ ለማን ማቅረብ እንዳለበት በፌዴራሉም ሆነ በክልል ሕግጋተ መንግስታት በግልጽ የተዘረጋ ሥርዓት ካለመኖሩም በተጨማሪ በጉባኤው ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 209/2006 ላይ ስለዚህ ጉዳይ በግልጽ የተዘረጋ ሥርዓት የለም፡፡ጉባኤዉ በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 7/6 መሰረት ከሚሰጠው ውሳኔ ውጭ በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ በዚሁ በጉባኤው ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 26/2 ተመልክቷል፡፡በአዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀጽ 7(1/ሀ እና ሰ) ላይ እንደተመለከተው ከዳኝነት ሥራ ጋር የተያያዙ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱን የሥራ ሂደት መሪዎችና ሰብሳቢ ዳኞችን በጉባኤው ሰብሳቢ አቅራቢነት መርጦ የሚሰይመውና ደመወዝ እና አበላቸውን የሚወስነው ጉባኤው ነው፡፡በዚህ መሰረት የአንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥራ ሂደት መሪ እና ሰብሳቢ ዳኛን ደመወዝና የኃላፊነት አበል በተመለከተ ጉባኤው የሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ነው ማለት ነው፡፡ የመጨረሻ ዉሳኔ ነው የሚለው አገላለጽ ይግባኝ ሊባልበት የማይችል ዉሳኔ ነው የሚል ሀሳብ የያዘ ነው፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት የሥራ ሂደት መሪ በነበርኩበት ጊዜ ሲከፈለኝ የነበረው የወር ደመወዝ ብር 13,702.00 ሆኖ እያለ አመልካቾች አለአግባብ ብር 1000.00 ቀንሶብኛል በማለት ተቀነሰብኝ ያሉት ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግላቸውና ለወደፊትም በዚያዉ መሰረት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ለጉባኤው ቅሬታ አቅርበው ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ አስቀድሞም የተወሰነሎት ደመወዝ ሳይሆን የኃላፊነት አበል ስለሆነ የደመወዝ ማሻሻያ ሲደረግ የኃላፊነት አበል ተቀንሶ የደመወዞ መጠን ብቻ መሰረት ተደርጎ የደመወዝ ማሻሻያው መሰላቱ ተገቢ ነው ሲል የተጠሪን

ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ በሰጠዉ አስተዳደራዊ ውሳኔ መብቴ ተነክቷል በሚል ነዉ፡፡በዚህ መልኩ ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀጽ 26/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተጠሪ ይግባኝ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡ይህ ድንጋጌ ከርዕሱ ጀምሮ ስለይግባኝ አቀራረብ የሚደነግግ እንጂ ዳኝነታዊ ክለሳ (judicial review) የሚመለከት ባለመሆኑ ዳኝነታዊ ክለሳን የሚከለክል አይደለም፡፡

እንደሚታወቀዉ የይግባኝ መብት በሕግ የሚገኝ መብት(statutory right)ነው፡፡ተጠሪ ጉባኤው ከላይ በተመለከተው መሰረት በሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት እንደማይኖራቸዉ በጉባኤው ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንደተደነገገ ከላይ ተመልክተናል፡፡በሌላ በኩል ጉባኤው በዚህ መልኩ የሚሰጠው ዉሳኔ ልክ ዳኝነት-ነክ ሥልጣኑን ተጠቅሞ የሰጠው ውሳኔ በክልሉ ምክር ቤት ተመርምሮ ተገቢው በሚወሰንበት አኳኋን ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ የሚመረመር ስለመሆኑ በግልጽ ሥርዓት የተዘረጋለት አይደለም፡፡በመሆኑም በክልልም ሆነ በፌዴራል ሕግጋተ መንግስታት አንቀጽ 9 ላይ ሕግጋተ መንግስታቱ እንደቅደም ተከተላቸው በክልሉና በአገሪቱ የበላይ ሕግጋት በመሆናቸው የጉባኤው ውሳኔ ይህንን መርህ ያከበረ(ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች ያከበረ) መሆን ካለመሆኑ አንጻር፣ የጉባኤው ውሳኔ እና ውሳኔ የተሰጠበት ሂደት በአንቀጽ 12 ስር ስለመንግስት አሠራር ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ከመሆን አለመሆን አኳያ፤ እንዲሁም የጉባኤው ውሳኔ በሕግጋተ መንግስታቱ አንቀጽ 37/1 ላይ የተደነገገውን የተጠሪን ፍትህ የማግኘት መብት ያከበረ ከመሆን አለመሆን ጋር እና በጥቅሉ የሕገ መንግስቱ ዓላማ የሆነውን የሕግ የበላይነት የተረጋገጠበት መሆን ካለመሆኑ አንጻር ተገናዝቦ ጉባኤው የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሕጋዊነት በዳኝነታዊ ክለሳ እና በሰበር አቀራርብ ሥርዓት ሊመረመር ይገባል፡፡ ምክንያቱም በክልሉ ምክር ቤት በማይታይ ጉዳይ ላይ በጉባኤው የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ በዳኝነት አካል የማይታይ ከሆነና በሕገ መንግስት የተረጋገጠ መብት የሚጥስ ውሳኔ ጸንቶ እንዲቀጥል የሚደረግ ከሆነ የሕገ መንግስት የበላይነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል ፤በሕግጋተ መንግስታቱ ስለመንግስት አሰራር ግልጸኝነትና ተጠያቂነት የተደነገገው በጉባኤው አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተፈጻሚ ሳይሆን እንዲቀር እድል ይፈጥራል፤ በጉባኤው የሚተዳደሩ ሰዎች ፍትሕ የማግኘት መብት ሳይረጋገጥ እንዲቀር ያደርጋል፡፡ ይህ እንዲሆን መፍቀድ ደግሞ ሕገ መንግስቱ በሕግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ አሰራር እንዲረጋገጥ የያዘዉ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ ስለሚያደርግ ሊፈቀድ የሚገባ አይደለም፡፡ በዚህ አግባብ የጉባኤው አስተዳደራዊ ውሳኔ በዳኝነት ሊታይ የሚገባው ነው ካልን በዳኝነታዊ ክለሳ ከመታየቱ በፊት በክልሉ ሰበር ታይቶ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17/1 ስር በተደነገገው መሰረት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ማየት የሚችለው በአንድ ጉዳይ ላይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር ነው፡፡ ይህ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን በአንድ አስተዳደራዊ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተነሳ የሕጋዊነት ጥያቄ

በዳኝነት አይቶ ከመከለስ የተለየ ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉባኤው ወይም በሌላ አስተዳደራዊ አካል የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ የማየት ሥልጣን እንዳለው በአዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17 ላይ አልተደነገገም፡፡ በመሆኑም በክልሉ ሰበር ችሎት ከመመርመሩ በፊት በፌዴራል ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 እና 80/2 እንዲሁም በክልሉ በተሻሻለው ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 እና 67(2/ሀ) መሰረት በመጀመሪያ በዳኝነታዊ ክለሳ በክልላዊ ጉዳይ ከፍተኛ እና የመጨረሻ የዳኝነትሥልጣን በተሰጠው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጉባኤው ውሳኔ ሊከለስ ይገባል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በዳኝነታዊ ክለሳ በዚህ አግባብ ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሰጥ በጉባኤው በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቀጥታ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ጉዳዩ በዳኝነታዊ ክለሳ ቢታይ ኖሮ ሊመረመሩ የሚገባቸው ከፍሬ ነገር ጉዳዮች ጋር ጭምር ሊያያዙ የሚችሉ ነጥቦች እንዳይመረመሩ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ከላይ እንደተመለከትነው በዳኝነታዊ ክለሳ አስተዳደራዊ ውሳኔው ተከልሶ ውሳኔው ከላይ ከጠቀስናቸው መመዘኛዎች አንጻር ጉድለት እንዳለበት ከተረጋገጠ ዳኝነታዊ ክለሳ ያደረገው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለጉባኤው ከመመለስ ውጭ ስህተቱን አርሞ በራሱ አዲስ ውሳኔ ስለማይሰጥ ጉዳዩ አስቀድሞ በዳኝነታዊ ክለሳ አለመታየቱ እና በቀጥታ ለክልሉ ሰበር ቀርቦ እንዲታይ መደረጉ *(ሰበር ተገቢ የመሰለዉን አዲስ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ስላለዉ)* የጉባኤው ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ ታይቶ ጉድለት ካለበትም በዳኝነታዊ ክለሳ ሥርዓት ውሳኔ አሰጣጥ መሰረት ጉባኤው እንደገና አይቶ መወሰን እንዲችል ጉዳዩ ሊመለስለት የሚችልበትን አግባብ በማጥበብ አስተዳደራዊ ሥልጣኑን የሚገድብ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የጠቀሱት ከዚህ ቀደም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 92546 ላይ በቀን 18/04/2006ዓ/ም (ቅጽ 15 የታተመ) ፣ ተጠሪ የጠቀሷቸው በሰ/መ/ቁጥር 61221 ላይ በቀን 22/01/2005ዓ/ም እና በሰ/መ/ቁጥር 43511 ላይ በቀን 23/02/2005(ቅጽ 14 ላይ እንደታተመው) የሰጠው የሕግ ትርጉም የዳኝነት-ነክ ሥልጣን ባላቸው አካላት ተወስኖ በውሳኔዎቹ ላይ በተጠቀሱት ሕጎች በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት በይግባኝ ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በመሰጠቱ ለሰበር የቀረበ ጉዳይን መሰረት ተደርጎ የተሰጡ የሕግ ትርጉሞችን የሚመለከቱ በመሆናቸውና በያዝነው ጉዳይ ጉባኤው አስተዳደራዊ ውሳኔ የሰጠው የዳኝነት-ነክ ሥልጣኑን በመጠቀም ባለመሆኑ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያላቸው አይደሉም፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 18342 ላይ በቀን 17/04/1998ዓ/ም (በቅጽ 3 ላይ እንደታተመው የተሰጠው ትርጉም) በዳኝነት-ነክ አካል በይግባኝ ጭምር ታይቶ ውሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት አዲስ ክስ ማቅረብ አይቻልም ተብሎ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ላይ የተሰጠ የሕግ ትርጉም አይደለም፡፡ስለሆነም ግራ ቀኝ እነዚህን የሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጎሞችን በመጥቀስ ያቀረቡትን ክርክር ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ላይ የተሰጡ ትርጉሞች ባለመሆናቸው ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት የላቸውም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኝነታዊ ክለሳ የማድረግ ሥልጣን ጭምር እንዳለዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ በልዩ ሁኔታ ያልተደነገገ በመሆኑ ጉባኤው የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ

በዳኝነታዊ ክለሳ ሥርዓት ከመታየቱ በፊት በስረ ነገሩ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ማየቱ በፌዴራል ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/2 እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 67(2/ሀ) ላይ በተደነገገው መንፈስና ይዘት መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልላዊ ጉዳይ ላይ በጉባኤው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ የማየት ሥልጣን እንዳለው የሚያስገነዝበውን ያላገናዘበ በመሆኑ ሥነ ሥርዓታዊ ስላልሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ) መሰረት ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-104522 ላይ በቀን 30/11/2013 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በጉባኤው የተሰጠ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ እንዲታይ ሥልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት አቤቱታ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግዳቸዉም፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለክልሉ ሰበር ችሎት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸው፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ